የታነቀች ሐገር

Yetanekech hager

ከ፦ዳንኤል ታደሰ በየነ
From:- Daniel tadesse beyene.

የማይሸጥ

ታተመ፦ ጆሀንስበርግ
ደቡብ አፍሪካ 2007 ዓ.ም
Printed:- johannseburg
Republic of south africa 2014

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

★ © አሳታሚ ዳንኤል ታደሰ በየነ
★ የመጀመሪያ ዕትም :- 2007 ዓ.ም.
★ ሽፋን ዝግጅት እና አጠቃላይ ዲዛይን፦ ዳንኤል ታደሰ በየነ
ጆሀንስበርግ ደቡብ አፍሪካ
የባለቤትነት መብቱ ሙሉ በሙሉ የተጠበቀ ሲሆን በአለም አቀፍ ደረጃ የመፅሐፍቶች ቁጥር አይ.ኤስ.ቢ.ኤን 978-0-620-62259-2 ተመዝግቦ ይገኛል።

ከደራሲው በሚሰጥ የፅሁፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር ይህንን መፅሀፍ በድጋሜ ማሳተም ፣ መቅዳት ፣ መተርጉም እንዲሁም ከመፅሐፉ ምንም ዓይነት ክፍል ቀድቶ በማሳተም ማሰራጨት አይፈቀድም።

በፅሁፍ ባልተገኘ ወይም በኢትዮጵያ ፍትህብሔር ህግ አዋጅ ቁጥር 165/1960 ርዕስ 11 አንቀፅ 1647-1674 በተተነተነው መሠረት ካልሆነ በስተቀር ለሚፈፀመው መተላለፎችና ለሚደርሰው ጉዳት በአዋጅ ቁጥር 410/96 መሠረት ተላላፊው በህግ ተጠያቂ ይሆናል።

★ Copy Right© 2014 DANIEL TADESSE BEYENE
★ Cover & page design:- DANIEL TADESSE BEYENE
★ PUBLISHER: - DANIEL TADESSE BEYENE
★ FIRST EDITION PUBLISHED IN: -
REPUBLIC OF SOUTH AFRICA.
Registered by :- ISBn “yetanekech hager” 978-0-620-62259-2
All rights reserved no part of this publication may be reproduced, stored in a retrieval system, or transmitted in any form of by any means, recording or otherwise, without the printer written permissions of the publisher.

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።



የማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ምስጋና

ይህ ነው ብዬ በእርግጠኝነት ልገምተውና ሊጎትትባችሁ የሚችለው ችግር ወይም «ተጠየቅ» ባይኖርም እንኳ ልቦናዬ ውስጥ ባደረችው ስስ ስጋት ምክንያት ስማችሁ ለምስጋና መጠቀስ ኖሮበት ግን ሳልጠቅሳችሁ የማለፌን ምክንያት ሁሉም ልብ ይሏል።

በእርግጥ ለእኔ ብቻ ወይም ይህ መፅሐፍ ለያዘው ጭብጥ ሳይሆን አጠቃላይ ለኪነ-ጥበብ ፍቅር እና ለስነ-ፅሁፍ እድገት ስትሉ ዘወትር ከጎኔ ተገኝታችሁ በተለያየ መንገድ እገዛ ላደረጋችሁልኝ የልብ ጓደኞች ሁሉ በልብ አመሰግናለሁ።

Acknowledgement

I would like to express my gratitude to all those who provided, support and encouraged me South African friends.

I would like to thank Kesosh Kesarnand for printing all my publish books.

Even if that journey was long and difficult, finally I did get all opportunity to publish my books in this country. Above all I want to thank this rainbow nation kind people and South Africa.

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

መግቢያ

የዚህ መፅሐፍ ፅሑፍ ተፅፎ የተጠናቀቀው በ1994ዓ.ም ሲሆን ወደ ህትመት እስኪመጣ ድረስ ያለፉትን 12 ዓመታት ተቀምጧል። በእርግጥ በ1997ዓ.ም ይህንን መፅሐፍ ጨምሮ ሌሎች ስራዎቼ ሊታተሙ የሚችሉበትን መንገድ ማመቻቸት ጀምሬ ወደ ትግበራ ስገባ የወቅቱ የፖለቲካ እንቅስቃሴ በፈጠረው ውጥረትና ያልተረጋጋ ሁኔታ ለጊዜው ጅማሬውን እንዲስተጓጎል ሲያደርግ እኔም ከኢትዮጵያ ወጣሁ።

ከላይ እንደጠቀስኩት መፅሐፉ ለበርካታ ጊዜ የተቀመጠ በመሆኑ በቀጥታ ወደ ህትመት ከመግባቱ በፊት ወቅቱ ከፈጠራቸው አንዳንድ ለውጦች ጋር እንዲጣጣም ጥቂት የመንካት ያህል ማሻሻል የተደረገለት ሲሆን ይህም አጠቃላይ ከሁለት ፐርሰንት አይልቅም።

ሌላው የዚህ መፅሐፍ ጭብጥ ወደ ህሊናዬ መጥቶ ለመፃፍ ስነሳ መጀመሪያ ላይ ሙሉ በሙሉ ልበ-ወለድ fiction መነሻና መድረሻ ያለው እንዲሆን አስቤ ጥቂት ምእራፎችን እንደፃፍኩ ከሙሉ ልቦለዳዊነት ይልቅ ተጨባጭ የሆኑ የታሪክ እና የጥናት ስራዎች ላይ መነሻዬን አድርጌ ብሰራው የተሻለ ስነ-ፅሁፋዊ ፋይዳ ይኖረዋል ብዬ በማመኔ ዋናውን ፅንሰ ሀሳብ ሳልነካ የአገራችንን፤ የአህጉራችንን፤ ብሎም የዓለማችንን በተለይ ቀኝ ገዥ የነበሩ የምእራባውያኑን ብሎም የዘይት ሽያጭ ገንዘብ ያቀወሳቸው የአረብ መንግስታቶችን እንቅስቃሴና ዓላማ፤ እያሳደሩት ካለው አደገኛ ተፅእኖ ጋር ከታሪካቸው በመነሳት ተጠቅሜበታለሁ።

መጨረሻ ላይ ሳልገልፅ የማላልፈው በ1996 ዓ.ም ባሳተምኩት «ርዕስ አልባ ግጥሞች እና...» በሚለው ቅፅ 1 የግጥም መፅሐፍ ላይ የዚህን መፅሐፍ ርዕስ «አፍሮኢዝም» በማለት ያስዋወኩት ሲሆን አሁን ርዕሱ በሽፋኑ ላይ በሚነበበው አዲስ ርዕስ ተለውጧል። መልካም ንባብ.....

ደቡብ አፍሪካ።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

« ወንጀል ማለት የቅጣት ህግ የወጣለት ደንብ መተላለፍ ሲሆን ፖለቲካ ደግሞ የቅጣት ህግ የሌለው ረቂቅ ወንጀል ማለት ነው::»

(ከውስጥ ገፅ የተወሰደ)

ያልታተመ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ምዕራፍ 1

‘ከዚህች ምድር ላይ ወንዶች ሙልጭ ብለው መጥፋት አለባቸው!...’ ስትል አሰበች ሰናይት።

ቀጠለች ‘... ድህነትን የፈጠሩ፤ ህይወትን ያከበዱ፤ መኖርን አፀያፊ ያደረጉ የተፈጥሮ ክፉ ጠንቆች ወንዶች እና ድህነት ናቸው... ውቧን ተፈጥሮ በአልጠግብ ባይነታቸው ጠፍረውና በዝብዘው ያራቆቱ ስስታሞች ወንዶች ናቸው። በዚች ፕላኔት ላይ ወንዶች ባይኖሩ ኖሮ ህይወት እንዴት ውብ እና ሰላም የሰፈነባት ትሆን እንደነበረ..... ግን ምን ዋጋ አለው ይህ የወንዶች ዘመንና የወንዶች ምድር ነው። ስልጣን፤ ሀብት፤ ውሳኔ፤ ጉልበት የነሱ ነው። ግን ብልሆች አይደሉም። ጅል ናቸው። ያቺ ጅልነት ደግሞ ከኤደን ገነት አስጎትታ እንዳስወጣቻቸው ከዚች መሬት ከተባለች ፕላኔትም ጠራርጋ ልታስወጣቸው ይገባል! ’ አለች ቁጣና እልህን በፀነሰው ልቦናዋ።

ብዙ ልታስታውሳቸው የማትፈልጋቸው ነገሮች ቢኖሩም ሁሌም ከህሊናዋ የማይጠፉና በውስጧ ታትመው የቀሩ የህይወት ታዝታዎቿ ዘወትር ከፊቷ ድቅን እያሉ የህዘን የጥላቻና የበቀል ስሜቷ እያባባሱት ሄደዋል። አንዳንዴ ይህን ስሜቷን መቆጣጠር ሲያቅታት ጭንቅላቷ ሊፈነዳ የደረሰ ይመስላትና ፊቷን ትራሷ ውስጥ ቀብራ በምሬት ታለቅሳለች።

ለዛ ሁሉ ተጠያቂዎቹ ደግሞ ወንዶች ናቸው።

ገና ህፃን እያለች እናቷ የሴት አያቷን ፎቶ እያሳየቻት ስለ ቀደምቱ ቤተሰባዊ ታሪካቸው ስትነግራት አያቷ ያለረዳት በሴት አቅማቸው የሰሩትን ዘመናዊ ቤት በዘመኑ በነበሩ የመንግስት አጎብዳጅ ወንዶች በሀሰት ክስና ማስረጃ ተወርሶባቸው ሜዳ ላይ ተጣሉ። በዛ ሀዘንና ብስጭት አያቷ በሞት ሲለዩ ለእናቷ ማውረስ የቻሉት ይህን አሁን

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

እያየችው ያለችውን ከአሮጌ እንጨት በተሰራ ፍሬም ውስጥ የሚገኘውን አሮጌ ፍቶ ግራፍ ብቻ ነበር።

የተወለደችው እና እድሜዋ አስራ ሶስት አመት እስኪሞላት ድረስ ያደገችው የአራዳው ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን መቃብር ጊቢ ጎን በኩል የሚገኝ አካባቢ ላይ ነበር።

ከመቃብር ቤት እምብዛም ስፋት ባልነበራት በኪራይ ቤታቸው ውስጥ እናቷ ቀን ቀን ካቲካላና ጠላ በመሸጥ ምሽት ላይ ደግሞ አካሏን ለወንዶች የወሲብ ስሜት ማራገፊያነት በመሸጥ አሳዛኝ ህይወትን ይገፉ እንደነበረ ሁሉም ነገር ዛሬ ላይ እየተከናወነ ያለ ያህል ሆኖ ይሰማታል።

ቀንና ምሽቱን በካቲካላ ጠጪ ሒሳብ «ክፍል» «አልከፍልም» «ውጣ» «አልወጣም» ንትርክና ጭቅጭቅ ልቧ ሲደክም የዋለችው እናቷ፤ ካለ እረፍት የእድሜዋ ጉስቁልናና የድህነቱ ጫና ያሳረፈባትን ጠባሳ በማይረቡ ቅባትና ልብስ ሸፋፍናው የቤቷን መብራት በቀይ አምፖል ለውጣ ቤቷን በጭሳጭስ አጥናው እንቅልፏ ያልመጣው ትንሽዬ ሴት ልጇን በግድ እንድትተኛ ታዛትና የምሽት ደንበኞቿን ለመጠበቅ በር ላይ ወጥታ ስትቆም ትዝ ይላታል።

በፊት በፊት ልጅ እያለች በግርፋት እስክትረታ ድረስ «እማዬ እንቅፌ አልመጣም አልተኛም.....» እያለች ታስቸግር ነበር። እናቷ አግባብታ በመጋረጃ የተከፈለው ክፍሏ ውስጥ እንድትገባ ስትሞክር እንቢ ካለቻት ያረጀ ጫማዋን አውልቃ በመግረፍ በግድ ታስተኛት ነበር። ከፍ እያለች ስትመጣ አይደለም አልተኛም ማለት ስትተነፍስ እንኳ በተለይ የምሽት የናቷ ደንበኞ ቤት ውስጥ ካሉ እንዳትሰማ አድርጋ በጥንቃቄ ነበር። ታድያ ሁሌም ክረምቶችን ትጠላ ነበር። ክረምት ሲመጣ ብርድን መቋቋም የማይችለው ከሲታ ሰውነቷ በብርድ እየተንዘፈዘፈ ያስላታል። በተለይ ሳሉ ለሊት ለሊት ይብሳል። እናም ባሳላት ቁጥር ሁሌም ስህተተኛ ነሽ ተብላ ትገረፍ ነበር።

ምክንያቱም በሏ ምክንያት ልጅ መኖሩን ካወቁ የናቷ ደንበኞች መካከልም አብዛኞቹ እየተሳደቡና እየተራገሙ ተነስተው «አታለሽኛል አንቺ ሸርሙጣ.....!» እያሉ ተነስተው ሁኔታውን ምክንያት በማድረግ ለቆዩበት እንኳ ሳንቲም ሳይከፍሉ ውልቅ ይላሉ። ይሄኔ እናቷ ምርር ብላ በማልቀስ ትገርፋትና መልሳ እቅፍ አድርጋት «ተይው ይሂድ.....የት

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

አባቱንስና.... ድሮም ወንድ ስሜቱን ከደፋ ምን ጉዳዩ.....» ሰናይት በእድሜዋ ጨቅላነት ምክንያት እናቷ ምን ለማለት እንደፈለገች ያኔ አይገባትም ነበር።

አንዳንዱ ደግሞ ቀድሞውን በመጠጥ ጥንብዝ ብሎ ስለሚመጣ አይደለም የህፃኗን ሳል ይቅርና ፈንጅ ቢፈነዳ አይሰማም። ይህም ሆኖ ግን ሁሌም በሰቀቀን እንደተዋጠች ነበር።

ጠባቧ አንድ ክፍል ቤታቸው ውስጥ የሚታዩት ነገሮች በጠቅላላ ድህነትን የሚያውጁ ይመስላሉ። አሮጌ የጠላ ጣሳዎች፤ የተሸራረፉ ስኒዎች፤ የነተበ መጋረጃ፤ ያደፈ ጋቢ፤ የተቆረጠ ጎንጉ ጫማ፤ የተበሳ ክዳን አልባ ድስት፤ አቧራ የጠጣ የጥንት ፍቶ፤ ሲቀመጡበት የሚንቋቋ አሮጌ አድጋሚ ወንበር፤ የተወላገደ የሸምበቆ ጠረጴዛ..... ሁሉም የቤቱ እቃ ላይ ድህነት በጠንካራ ሰንሰለት ለዘላለም ታስሮ የሚጮህ ይመስላል።

በአረጁ እቃዎች የተሞላች እና በአረጁ መጋረጃዎች የተከፋፈለችው ቤት የመግቢያው በር አካባቢ ለመሸታ ደንበኞች የተዘጋጁ ሁለት አግዳሚ ወንበሮች ከአንድ የሸምበቆ ጠረጴዛ ጋር ተቀምጠው ይታያሉ።

አግዳሚዎቹ ስር ጀበናና ስኒ፤ ማጨሻ፤ አሮጌ ጣሳዎች እና ጥቅማቸው በትክክል የማይታወቁ አሮጌ ቁሳቁሶች ተወታትፈዋል። የክፍሉ በስተኋላ በመጋረጃ ለሁለት ተከፍሏል። ሁሌም ተገልፆ በሚታየው በኩል አንድ አሮጌ የቦንዳ አልጋ ሲኖር በተከለለው በኩል ከጭቃ የተሰራ የሰናይት መደብ አልጋ ሳር ፍራሽ ተነጥፎበት ይገኛል። ከሷ መደብ ጋር ተያይዛ ባለችው ክፍተት ደግሞ የጠላ መጥመቂያና የማብሰያ ቁሳቁሶች አንዱ በሌላው ላይ ተደራድረው ተቀምጠዋል።

ሰናይት ቀን ቀን ሲካሄድ ከምታየው የሰካራሞች ንትርክና ስድብ ይልቅ ሁሌም የለሊቱ ያስጨንቃታል። እንቅልፍ አልወስድ ብሏት ተዳክማ ተኝታ ቢሆን እንኳ ከአራት ነገሮች የአንዱ በግድ ያባንናታል።

ያረጀው ቦንዳ አልጋ ጩኸት፤ ወይም የናቷ የማያቋርጥ የጣር ድምፅ ወይም እንደታረደ በሬ እናቷ ላይ ሆኖ ከወሲብ ስሜቱ ጋር ተናንቆ የሚያጓራው አስፈሪ ሰው ድምፅ ወይም እናቷን ሊተኛት የመጣው ሰው ክፉ የጫማ ግማት.... ክረምቱን ሳል የሚጫወትባትን ያህል በጋው ላይ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

በጫማዎቹ ግማት የተነሳ ጉንፋን ሲቀልድባት ያልፋል። ታድያ ይህም የሷ ጥፋት እንደሆነ ተደርጎ ትቀጣበት ነበር....

አንዳንዴም ለምን እንደሆነ በማይገባት ሁኔታ ሰዎቹ እናቷ ላይ የሚያወርዱባት ንቀት የተቀላቀለበት ዘለፋና ስድብ ከወሲብ ድምፅ ጋር ታጅቦ ለጆሮዋ ይደርሳታል። የፈለገውን ያህል በነተበው የለሊት ልብሷ ጆሮዋን ይዛ ላለመስማት ብትጥርም ሁሌም ለሊቱ አልቆ ያ ጨለማ የናቷን ስቃይ ይዞ የሚያልፍ አይመስላትም።

ሁሌም ለሊት ለሷ ከቀን ሺህ ጊዜ የበለጠ፤ የረዘመና የጨከነ ነገር ነው..... እናም ለሊቶችን ትጠላቸዋለች። አንዳንዴ ለሊቶች፤ ጨለማዎች፤ ወንዶች፤ ድህነት እና የጫማ ግማት የሆነ አይነት ህብረት ያላቸው ይመስላታል።

ኑሮዋቸው ሁሌም ከማትረባ የእለት ጉርስ እና ከቤት ኪራይ አልፋ አታውቅም። የእለት ጉርሳቸውም ቢሆን አብዛኛውን ቀናት ውሃ ውስጥ ተዘፍዝፎ የበቀለ በቆልት ባቄላ በሰናፍጭ ተለውሶ ነበር። እስኪሰለቻት ድረስ ተገዳ እየበላች ያደገችውን የሚሰነፍጥ ባለ ሰናፍጭ ባቄላንም አትወደውም። አባቷንም አታውቀውም..... ብቻ ማታ ማታ እናቷን ይጎበኟት ከነበሩት የወሲብ ደንበኞቿ መካከል ከማይታወቀው ከአንዱ ወንድ እንደተፀነሰች ብቻ ነው እናቷ የነገረቻት። አባትን የሚያህን ትልቅ ነገር ለሷ ከሶስት ፊደላት ያልዘለለ ትርጓሜ ብቻ ነው የነበረው።

በህይወቷ ታላቁን ቦታ የሰጠቻቸው ፈረንሳዊት ሴት የዛሬ ማንነቷን ሲገነቡላት የተናገርዋትን አስታወሰች። ከፊት ለፊታቸው አስቀምጠው አይን አይኗን እያዬዋት « ዛሬ ላይ ቆመን ትላንትን ማሳመር አንችልም.....» ነበር ያልዋት።

«አዎ...» አለች ለራስዋ «... ትላንት ከትላንት ወድያ እንዳደረገው መሆን የሚችለውን ሆኖ አልፎዋል። ዛሬ የትላንት ልጅ ነው..... ዛሬ ነገን ፀንሶታል። ዛሬ ላይ ቆመን ነገን ከትላንትም ሆነ ከዛሬ የበለጠ አሳምረን ልንቀርፀው እንችላለን። የሔደው የኔ አይደለም የሚመጣው እንጂ.....

«... ጊዜ ተጓዥ ነው እኔም የጊዜ ዘልላ ነኝ። ዘለላው ከጊዜ አካል ላይ እየተንጠባጠበ እየወደቀ ይሄዳል ያም ቢሆን ግን እኔን ወደኋላ የማስቀረት ስልጣን የለውም። ወንዶች በዙሪያዬ እስካሉ ብዙ እቅድ፤ ብዙ በቀል እና ቁጣ ውስጤ አለ.....»

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ሞባይል ስልኳ ሲጠራ ከሀሳቧ አባነናት። ከፈረንሳይ ነበር። ከሰላሳ ሰከንድ ያልበለጠ አጭር መልእክት ተቀበለችና እንደዘጋችው ሲም ካርዱን ከስልኳ ውስጥ በማውጣት ሰባበረችው። ብሔራዊ ትያትርን አለፍ ብሎ ከተሰራው ካፌ ወጥታ መራመድ ስትጀምር በአካበቢው ላይ ከነበሩት ተስተናጋጆች እና የሚተላለፉ ሰዎች መካከል አብዛኞቹ ወንዶች በውበቷ ፈዘው በአይናቸው እየተከተሏት እንደነበር አውቃለች። አፍጠው የሚያይዋት ሰዎች የቀሰቀሰባትን የወንድ ጥላቻ እያስታመመች መንገዷን ቀጠለች። ከህንፃው በረንዳ ስር ወደ አስፓልቱ ስትደርስ የሰባበረችውን ሲም ካርድ ማንም እንዳያየው ቀስ ብላ ወረወረችው።

  

ያማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ምዕራፍ 2

ፒየር የቢሮው ጠረጴዛ ላይ የተቀመጠውን ወፍራም ፋይል የመጨረሻ ገፅ አንብቦ አንደጨረሰ ቀና ብሎ ወደኋላው ተለጠጠና በእጆቹ መዳፎች የፊቱን ገፅታ ደባበሰው፡፡

ሀሳቡ በዛች ስለ አንዲት ሴት ግለ ታሪክ ከሚናገረው ፋይል ላይ እንደተዋጠ ነበር፡፡ በዚህ ፋይል ውስጥ የሚገኘውን መረጃ ለማሰባሰብ ከሰባት ወር በላይ በግለሰቧ ላይ ክትትል የተደረገ ሲሆን የበርካታ ሺህ ዶላር ወጪ አስወጥቷል፡፡ ሆኖም ግን የበርካታ ቢልየን ዶላር ትርፍን የሚያዝቅ በመሆኑ ማንም ቅሬታ አልነበረበትም፡፡

“ይማርካል!.....” አለ ለራሱ፡፡

ሲያነበው ከቆየው ፋይል ላይ በማስታወሻ ወረቀት የገለበጠውን ሀሳቦች ደጋግሞ በማየት በህሊናው ሙሉ በሙሉ እንደመዘገባቸው ካረጋገጠ በኋላ ወረቀቱን ቀዳዶ የቆሻሻ ቅርጫት ውስጥ ወረወረው፡፡

ከወንበሩ ተነስቶ ጥቂት ሲያስብ ቆየና መስቀያ ላይ የተንጠለጠለው ኮቱን ለብሶ ወደ አለቃው ቢሮ ለመሄድ በሩን ከፍቶ ወጣ፡፡

ፒየር የሚቀጥለው ክፍል ወደሚገኘው የአለቃው ቢሮ እንደደረሰ በሩን አንኳኳና ከፍቶ እየገባ “እንደምን አረፈድክ ሉዊስ?” “ደህና ነኝ..... ተቀመጥ” በእድሜ እኩያ የሚሆነው አለቃው አስፈሪ እና ጭካኔ የተሞላ እይታውን ከሚያነበው እለታዊ የፈረንሳይ ጋዜጣ ላይ አንስቶ ወደ ፒየር መለሰለት፡፡

የዚህ “የሉዊስ ወኪሎች” በሚል የሚጠራው መስራቤት ዋና ሀላፊ እና ባለቤት ነው፡፡ ለእንቅልፍ ከሚያሳልፋት ጥቂት ሰዓታት በስተቀር

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

ሙሉ ጊዜውን ሳይሰለች በስራ የሚያሳልፍ በመሆኑ “የብረት አጥንት” የሚል ቅጥያን አግኝቷል።

እድሜው 67 አመት ሲሆን ፈርጣማ ሰውነቱ ግን ገና ወደ ጉልምስና እየተጠጋ ያለ ሰው ነው የሚያስመስለው። በወጣትነቱ በፈረንሳይ የባህር ሀይል ውስጥ ተቀጥሮ ለአስር አመታት አገልግሏል። ከዛም የሻለቃነት ማዕረጉን እንዳገኘ ሲያሳየው በኖረው ብስለት የታከለበት አገልግሎቱ የመረጃ አሰባሳቢና አጠናቃሪ እንዲሆን ወደ ማዕከላዊው እዝ ተዘዋወረ። በዛም ለአምስት አመታት እንዳገለገለ አሁንም በእድገት ለዋናው የፈረንሳይ የስለላ ድርጅት ውስጥ ገብቶ ለዘጠኝ አመታት ሲሰራ ቆየና የአገሩ መንግስት ባቀረበለት ጥያቄ፤ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ውስጥ የህገ-ወጥ ጦር መሳሪያ ዝውውር መቆጣጠሪያና የድንበር ይገባኛል ግጭቶችን አስወጋጅ ኮሚቴ ከፍተኛ ልዑክ ሆኖ ሰርቷል።

ይህም የያንዳንዱን የዓለማችን መንግስታቶች ችግሮችን ፤ ድክመትና ጥንካሬያቸውን አብጠርጥሮ እንዲያውቅ ከፍተኛ እድል ሰጥቶታል። በዚህ አጋጣሚ ነበር እንደ ኤሮፓውያኑ አቆጣጠር 1835 በጥብቅ ሚስጥር በአምስት የአውሮፓ መንግስታት መካከል የተከናወነ አስገራሚ የስምምነት ሰነድ ከለንደን የውጭ የፖለቲካ ጉዳዮች መምሪያ መስራቤት ተሰርቆ የወጣ ባለ ሰላሳ ስምት ገፅ መዝገብ እጁ የገባው። ይህም አሁን ለቀረፀው ታላቅ እቅድ የመነሻ ሀሳብን ሰጠው።

ጋዜጣውን አስቀምጦ ፒየርን በሰርሳሪ እይታው እያየው “የሰናይትን ፋይል አየኸው?”

“አይቼዋለሁ”

“እንዴት አገኘኸው ታዲያ?”

“እኛ ከመለመልናቸው ኢትዮጵያዊያን ሰዎች ሁሉ የተሻለውን ሰው እንዳገኘህ ላረጋግጥልህ ነው የመጣሁት”

“ይመስለኛል” አለ ሉዊስ ቆይቶ ቀጠለ “ፋይሉ ስራችን ለመጀመር የሚያስችለንን ያህል መረጃዎች የያዘ ይመስለኛል”

“አዎ..... ሙሉውን አንብቤ ጠቃሚ የሆኑ ማስታወሻዎችን ይዣለሁ። ሴትየዋ የምትንኖርበትን አካባቢ ፤ የህንፃው ስምና የመኖሪያ ክፍሉ ቁጥር ሁሉ ተገልፃ_ል.....”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ሉዊስ ጣልቃ ገባና "አዘውትራ የምትመገብባቸውን ሆቴሎች በቅድሚያ መጠቀሙ ይሻለናል"
"ይቻላል፡፡ የነሱንም ስም ይዣቸዋለሁ፡፡"
"ታዲያ ክትትሉን ለመጀመር ምን ይጐለን ይመስልሀል?"
"ምንም፡፡ ዛሬውኑ ራሴ እጀምረዋለሁ..... ምናልባት ሴትየዋ ግን ፈቃደኝነቷን እንዳትነፍገን እንጂ" አለ ፒየር፡፡

ሉዊስ ሲያስብ ቆየና "አይሆንም ልትለን አይገባም ችሎታህን ተጠቀም ስሜቷ በሚመራህ አቅጣጫ ሂድ ፡፡ እርግጠኛ ነኝ የሆነ ክፍተት ልታገኝባት ትችላለህ ብዬ አምናለሁ በዛ ገብተህ አሳምናት"
ፒየር በዝግታ ጭንቅላቱን እየነቀነቀ ለመሄድ እየተነሳ "ችግር የለም በሷ ባይሳካ ሌሎች ሺህ አማራጮች አሉን ለማንኛውም መልካም እለት" አለና ሊጨብጠው እጁን ሲዘረጋ
"ይህን ስራ ከሷ በስተቀር ማንም እንዲሰራው አልፈልግም! " አለ ሉዊስ፡፡
"መልካም" ብሎት ወጣ፡፡
ፒየር እንደወጣ ሉዊስ ጋዜውን ካቋረጠበት ማንበብ ቀጠለ፡፡ ጐላ ጐላ ያሉት ርዕሶች "የአውሮፓ ኢኮኖሚ እድገት እየጨመረ ሂዷል በአሜሪካ ግዛቶችም እንደዛው" ዝቅ ብሎ "ኢስያ የሚሰጋት ነገር የለም"፡፡

የመጨረሻ ገፆች ዜና ደግሞ "በአፍሪካ በየሰከንዱ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ህፃናትና ወጣቶች ይሞታሉ..... መሀይምነት ተባብሷል..... የህዝብ ቁጥር መጨመር ድህነትን አባብሶታል..... እዚም እዛም የጥይት ድምፆች ይሰማሉ..... አውሬ ገዢዎቻቸው ዛሬም ህዝባቸውን መብላት አላቆሙም....." የሚሉ ርዕሶች ጭፍግግ ዜናዎች ሰፍረውበታል፡፡

ፒየር ከሚሰራበት ባለ አንድ ፎቅ ህንፃ እየወረደ ሰዓቱን አየ፡፡ የምሳ ወቅት መቃረቡን አሰበና የሚፈልጓት ሴትዮ አዘውትራ ወደ ምትመገብበት ሆቴል ቀድሟት ለመገኘት መንገድ ጀመረ፡፡ በእጁ የግለሰቧን ጉርድ ፎቶ ግራፍ ይዞ ነበር፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

የፓሪስ ጐዳናዎች እንስቃሴ መቼም ቢሆን የሚሞቱ አይመስሉም፡፡ ዘወትር በህዝብና በተሽከርካሪ እንደተጨናነቁ ናቸው፡፡ በዓለም ላይ የሚኖር የማንኛውም ሀገር ዜጋ ተወላጅ በከተማዋ ውስጥ አይገኝም ማለት ዘበት ነው፡፡

እንደ ህዝቡ ብዛት ሁሉ ሰማይ ጠቀስ የሆኑት የከተማ ህንፃዎች ከዝብርቅርቅ ውበታቸው በተጨማሪ በየ ጐድጓዳዎቻቸው መሀከል የሚነደፉባቸው እቅዶችና የሚፈፀሙት ውሎች እንደ ግዝፈት ደረጃቸው የተለያዩ ይሁኑ እንጂ የውጤታቸው ተፅእኖዎች አጠቃላይ ዓለምን የሚነኩ ወይም የሚቀሰቅሱ ናቸው፡፡

የሉዊስ ይህኛው እቅድም የዓለምን የጉዞ አቅጣጫ በተለይ ለአፍሪካ እጅግ አደገኛው ሲሆን ትግበራው ዛሬ ተጀመረ::

ፒየር ምክትል ስራ አስኪያጅ ሆኖ የሚሰራበት ድርጅት “ሉዊስ ወኪሎች” በሚል ስያሜ ይጠራል፡፡ ድርጅቱ ስራ የጀመረው የሁለተኛው የአለም ጦርነት ባከተመ ማግስት ነበር፡፡ ያኔ ሲቋቋም ይህን ያህል ጊዜ አቅም ኖሮት ይዘልቃል አልተባለለትም፡፡

ምክንያቱም ያከናውን የነበረው ዋነኛ ስራው በዛ ጦርነት ላይ ተሳታፊ የነበሩትን የጀርመን ከፍተኛ ባለስልጣናት ከተደበቁበት የዓለም ስፍራ እያደነ ለጠየቃቸው መንግስት ሆነ ለሌላ አካል መረጃ በመሸጥና እያጋለጠ በማስያዝ ለፍርድ እንዲቀርቡ በማድረግ ሲሆን በተጨማሪም በጦርነቱ የተጠፋፉ ቤተሰቦችን ማገናኘት ነበር፡፡

ይህም በመሆኑ ከጥቂት አመታት በኋላ ጦርነቱ የፈጠረው ቀውስ እየሻረ ሲሄድ ድርጅቱ ይዘጋል የሚል የብዙዎቹ ግምት ሆኖ ቆየ፡፡

ሆኖም የግምቶች አቅጣጫ የተሳሳተ ሆነና ድርጅቱ መረጃን ፈልፍሎ የመሸጥ ስራውን በናዚዎች ላይብቻ ያነጣጠረ ከመሆን ባሻገር ለማንኛውም ሌላ ተቋም፤ ግለሰብ፤ ለስለላ ቡድኖች፤ ለጋዜጣ አሳታሚዎችና ለመገናኛ ብዙሀኖች ለሚጠየቀው የክትትል ስራ ሁሉ መረጃን መሸጥ ተወዳዳሪ የማይገኝለት ምርጥ ስራ እየሆነለት ሄደ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

በዛው መጠን ስሙ በአውሮፓ፣ ኢስያና አሜሪካ ድረስ ለመሻገር ቻለ፡፡

ይህ 55 ዓመታትን ያስቆጠረው ድርጅት ከአንዱ ግለሰብ ወደ ሌላው በሽያጭ እየተላለፈ በበርካታ ሰዎች የህሊና ሞረድ እየሰላና እየሾለ በመሄዱም አንድ ጠንካራ መንግስት ሊያዋቅረው ከሚችለው የላቀ የስለላ ድርጅት ለመሆን በቃ፡፡

የፈረንሳይ ነገስታት ዝርያ አለብኝ በሚለው በሉዊስ ከ15 ዓመታት በፊት ከተገዛ በኋላ ውስጣዊ መዋቅሩን በማስፋት የተሳለና የሾለ አቅሙን ከመረጃ ሻጭነት በተጨማሪ ሊያሰራው ከሚፈልግ አካል ሁሉ ጋር ስለቱን እየቆረጠበት የሾለ ፍላፃውን እየወጋበት በትረኛ መሆኑንም ማሳየት ከጀመረ ቆይቷል፡፡

በቋሚነት ድርጅቱ የሚያውቃቸው ሰራተኞች አምስት ሰዎች ብቻ ሲሆኑ በዓለም ላይ ግን ሲፈለጉ ብቻ እየተጠሩ መረጃን እጅ በእጅ ሽያጭ የሚያሻግሩለት ከአንድ መቶሺህ የማያንሱ የተለያዩ አገር ከፍተኛ ባለስልጣናት ፣ እፅ አዘዋዋሪዎች ፣ ህገ ወጥ መሳሪያ ሻጮች ፣ ቅጥር ነብስ ገዳዮች እና ቅርስ ዘራፊዎችን በተለያዩ ህጋዊ የስራ ዘርፎች ከለላነት ስር ለ"ሉዊስ ወኪሎች" ድርጅት የሚያገለግሉ ሰራተኞችን አጭቋል፡፡

  

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ምዕራፍ 3

ፀሀይ በአናት ልትውል ጥቂት ቀርቷታል። ሆቴሉ ከማዕከላዊ ፓሪስ አካበቢ ላይ ይገኛል። ስሙ አንርጀንቲዮል የሚሰኝና ጥንታዊ ይዘት ያለው ሆቴል ነው።

ውስጡ ግርግር የለበትም ። ከኮርኒሱ ላይ ትንንሽ አምፖሎች ደብዘዝ ያለ ብርሃን ይረጫሉ።ከመመገቢያው አዳራሹ ትይዩ በሚገኝ ከፍ ያለ ቦታ ላይ አምስት የሙዚቃ መሣሪያ ያነገቡ ሰዎች በማያውክ ዝቅተኛ ድምፅ ለስለስ ባለ ስልት ይጫወታሉ።

ፒየር የሚፈልጋትን ሴት ለማግኘት በሆቴሉ ከአንድ ሰዓት በላይ በመቁነጥነጥ ሲጠብቀው ቆይቶ ትዕግስቱ ሊሟጠጥ ሲቃረብ አንድ አፍሪካዊ ቀለም ያላት ሰው የተዘጋውን በር ገፍታ ገባች። የአዳራሹን ዙሪያ አማትራ ተስማሚ ወደመሰላት ጠረጴዛ በመራመድ ስትቀመጥ ፈዞ ቀረ።

እድሜዋ ወደ ሰላሳዎቹ ጋማሽ ይጠጋል። የለበሰችው የበጋ አለባበስ በመሆኑ የተዋበው ቀጭን ውብ ሰውነቷ ማንንም ይማርካል። አንድ ሜትር ከሰማንያ የሆነው ቁመናዋ በዮጋ እስፖርት የታነፀ ነው። ረጅም ፀጉሯን ሰብስባ አሲዛዋለች። 'እስከዛሬ ድረስ በፓሪስ የቁንጅና መድረክ ላይ ካየኋቸው ሴቶች ሁሉ ውብ ነች' ሲል አሰበ

የለበሰችውን ግራጫ ሸሚዝ ቁልፍ አላላች። አስተናጋጁ አጠገቧ ደርሶ እጅ ነሳላት። የምትፈልገውን በሜኖው እየታገዘች አዘዘች።

ፒየር ፊቷ ላይ በሚታየው ልበ ሙሉነት እየተገረመ ምግቡን እስኪያቀርብላት ጠበቀና መመገብ እንደጀመረች ተነስቶ ወደሷ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ጠረጴዛ በማምራት "እንደምን ዋልሽ ሰናይት..... ፒየር እባላለሁ" አለና "መቀመጥ ይፈቀድልኝ ይሆን?" መልሷን ሳይጠብቅ ከፊት ለፊት ያለውን ወንበር ስቦ ተቀመጠ።።
ሰናይት መመገብ አቁማ በትኩረት እያየችው "አላስታወስኩህም.... "

"አታውቂኝም..... በእርግጥ እኔም በግሌ አላውቅሽም።። መስራቤቴ ግን አንቺን ለሀያ ዓመት ያውቅሻል።። እየተመገብሽ እንጫወት"
"እሺ....." ብላ ሹካዋን ወደ ሰሀኑ እየሰነዘረች
"ከኢሚግሬሽን ነህ?"
ፒየር በአሉታ ጭንቅላቱን ነቀነቀ።።
"ከስደተኞች ጉዳይ?"
"አይደለሁም"
ሰናይት ማላመጡን አቆመችና በሀሊናዋ ‹ማነው ለሃያ ዓመት ሊያውቀኝ የሚችለው?› አለች።። ከጥቂት ፀጥታ በኋላ "እሺ ከውጭ ጉዳይ....." ፒየር እንዳልሆነ ገለፀላት።።
"ይቅርታ እኔ የምትፈለገው ሰው ሳልሆን ከምትፈልገው ሰው ጋር የተመሳሰልኩብህ ሳልሆን አልቀረሁም።።"

ፒየር ግምታዊ አስተያየቶቿ እንዳለቁባት ስለተረዳ ከጥቂት ወራቶች በፊት ከተገዛው ፋይል ላይ ያነበበውን የራስዋን ግለ ታሪክ ሁሉ ልክ ከሃያ ዓመት ጀምሮ ሲከታተሉዋት እንደኖሩ አስመስሎ ለመናገር እየተዘጋጀ "የመስራቤቴን የመረጃ ሰዎች ይሳሳታሉ ማለት ክርስቶስ ዋሽቶን ነበር እንደማለት ነው።።"
"አስቀድመህ ከየት እንደሆንክ ብትገልፅልኝ?"
"እሺ ትደርሽበታለሽ።። መጀመሪያ ግን ትክክለኛ መሆኔን ልግለፅልሽ።። ስምሽ ሰናይት ፍስሀ ነው።። ትውልድ ኢትዮጵያ።።"
ሰናይት ማንኪያውን አስቀመጠችና የወይን ብርጪቆውን አነሳች።።
ቀጠለ ፒየር ".....ከትውልድ አገርሽ የወጣሽው ከሃያ አራት ዓመት በፊት ነው።። በቅርቡ ግን ለጥቂት ዓመታት ተመልሰሽ ሄደሽ ነበር።። ልቀጥል?"
"አዎ"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

“የመጀመሪያ ዲግሪሽን በፖለቲካ ሳይንስ በማርሴል ከተማ በሚገኘው ማርሴል ዩኒቨርስቲ እና ሁለተኛውን እዚሁ ፓሪስ በዲድሮት ዩኒቨርስቲ ወስደሻል.....” ፒየር የሰናይትን የፊት ገፅታ መለዋወጥ እያስተዋለ ንግግሩን ቀጠለ፡፡
“..... በእርግጥ ከከአራት ዓመት በፊት ተመልሰሽ በመሄድ የግልሽን ጋዜጣ አሳታሚ ድርጅት በማቋቋም ለሶስት ዓመታት ያህል ከፍተኛ የሆኑ የመንግስት ሚስጥሮችንና ድክመታቻውን እያሳተምሽ ስታስቸግሪ ሁለት ጊዜ ለእስራት ተዳረግሽ፡፡ ከዛም በኋላ ማስፈራራትና ዛቻዎች በተደጋጋሚ ስለደረሰብሽ የጋዜጣውን ህትመት አቋርጠሽ ወደ ፓሪስ ከተመለሽ አንድ ዓመት ሊሆንሽ ጥቂት ቀርቶሻል፡፡ ታዲያ መረጃው የተሳሳተ ነው ብለሽ ታስቢያለሽ? ”
ሰናይት ምንም ባለመደነቅ ስሜት እያየችው ፊቷን በስስ ሶፍት ነካ ነካ እያደረገች “ልክ ነው.....ግን ይህን ሁሉ ታሪክ ማወቃችሁ ለምን አስፈለገ?”

“መስራቤቴ የሚፈልገው ታሪኩን ሳይሆን የታሪኩን ባለቤት ነው፡፡”
“እሺ ከየት ነው የመጣኸው?” ቁጣ እየተናነቃት ጠየቀች፡፡
ፒየር ከጥቁር የኮቱ ደረት ኪስ በኘላስቲክ የተለበጠች ጉርድ መታወቂያ ከፊት ለፊቷ አስቀመጠ፡፡
መታወቂያዋ ላይ የቆዩት የሰናይት ዓይኖች ፒየር ላይ እያፈጠጡ “ሲ.አይ.ኤ.” በለሆሳስ ተናገረች፡፡‹ለምንድነው የሚፈልጉኝ?› ራሷን ጠየቀች፡፡
ፒየር እንደቦታውና እንደአስፈላጊነቱ የሚገለገልባቸው ከአስር በላይ የሚሆኑ በአለም ላይ ታዋቂ የስለላ ድርጅቶች ወይም የአለም አቀፋዊ ፖሊስ ተቋም ባልደረባ መሆኑን የሚገልፁለት የሀሰት መታወቂያዎች ያሉት ሲሆን በዚህ ቦታ የተጠቀመበትም ከነሱ መሀከል አንዱን ነበር፡፡

ሰናይት ፒየር ላይ እንዳፈጠጠች የሚለውን መጠባበቅ ጀመረች፡፡
ፒየር ፈገግ እያለ “ የሚያሰጋሽ ነገር የለም፡፡ ሲ.አይ.ኤ. ከእንቺ ጋር ሆኖ አንድ ትልቅ እቅዱን ተግባራዊ ሊያደርግ ይፈልጋል”
“ከኔ.....ጋር!?”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“አዎ”
“ምን.....ምን.....ዓይነት!?”
“ከሀምሳ ሚልየን ዶላር ክፍያ በላይ የሚያስገኝልሽ ታላቅ እቅድ”
“ የአምላክ ያለህ” አለች ሰናይት በአድናቆት፡፡
ፒየር ለመሄድ እየተዘጋጀ መታወቂያውን ኪሱ መለሰና “ደህና ዋይ” ብሏት ተነሳ፡፡
“ለመሆኑ የት..... እንዴት..... ከማን ጋር ነው የምንጋገረው?”
“ችግር የለውም፡፡ አንቺ ያለሽበት ቦታ ሁሉ ሲ.አይ.ኤ. አለ፡፡ ስለዚህ እኛው እንመጣለን፡፡”
“መኖሪያዬን ታውቁታላችሁ?”
“በናንትሪ ጐዳና ላይ ጉስታቭ ህንፃ ውስጥ 12ኛ ፎቅ በቁጥር 341 የሚታወቀው ክፍል” መለሰ ፒየር፡፡

  

ያልተሸጠ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ምዕራፍ 4

ከእንቅልፏ ያባነናት የእናቷ የስቃይ ድምፅ ነበር። ለሊት ለሊት ይህን ድምፅ ላለመስማት ጆሮዎቿ የተቀደዱ እስኪመስላት ድረስ ጣቶቿን እና የነተቡ ልብሶቿን ትሰገስግብት ነበር። ግን ይህ አንድም ቀን ረድቷት የማያውቅ የማይረባ ሙከራ ነበር። ከእናቷ ጋር ሊተኙ የሚመጡ ወንዶች የወሲብ ጩኸትና ክብርን የሚያንቋሽሽ የስድብ ቃል እንደሁሌው ቀጥሏል።

አንዳንዴ ራሷን አሳምና በሌላ ሀሳብ በመዋጥ ከሷ የመደብ መኻታ አንድ እርምጃ የማይርቀውን የናቷን የስቃይ ማቃሰትና አብሯት የተኛ ውን ሰው ድምጽ ለሊቱን ሙሉ ስትምግ ታድራለች። የዛሬው ግን እጅግ የተለየ ሆነባት። ሰውዬው ደጋግሞ የሚመጣ ቀን ቀን የካቲካላ ደምበኛ ቸው ሲሆን ማታ ማታ እናቷን ይተኛታል።

በትክክል ስሙን የማታስታውሰው የመንግስት መስራቤት ሰራተኛ መሆኑን ሲወራ ትሰማለች። እንዲሁም ባለ ትዳርና የሶስት ልጆች አባት መሆኑን ጭምር.....

በሷ የልጅነት ህለና ፈፅሞ ሊገባት ያልቻለው ሚስጥር ቢኖር ቤት፤ ሚስት እና ልጆች ካሉት ለምን የሷ እናት ጋር እየመጣ እንደሚያድር ነው..... ያውም እናቷን እንደማይወዳት ታውቃለች ምክንያቱም ሁሌም ሲሰድባት እና ሲያንቋሽሻት ነውና የምትሰማው።

የዛሬው ለሊት ሁኔታው ደግሞ የተለየ ሆኖባታል። “ይህን ያህል የሚሰድባት እና የጠላት ከሆነ ለምን ትቶዋት አይሄድም” እያለች በልጅ ህሊናዋ ታስባለች... በስካር የጎረነነ ድምፁ በወሲብ ስሜት እየተጎተተ እናቷን “ሽርሙጣ... መሆ..ንሽን እንዳትረሺው....” ሲል የቦንዳው አልጋ ሲወዛወዝ ከሚፈጥረው የማያቋርጥ «ሲጥ... ሲጥ...» ከሚለው ድምፅ ጋር እየተቀላቀለ ይሰማታል... እናቷ አልፎ አልፎ ህመም የተሞላበት የስቃይ አተነፋፈስ እየተነፈሰች በታፈነ ሁኔታ «አረ... ቀስ በል ገደልከኝ እኮ.....»

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

«ዝም... ዝ..ም.....በይ!»
«አረ ባክህ ተክሌ»
«ዝም በይ!...» ንግግሩን ተከትሎ «ድም!» የሚል የምት ድምፅ ተከትሎ መጣና እናቷ «እ..ህ» ብላ ስታቃስት ሰማች::
እሱ ግን ወሲቡን እየከወነ መሳደቡን ቀጠለ «...ክብሬን እና ራሴን ዝ...ቅ አድርጌ አንቺ ጋ...ር ብመጣ ባ...ባልሽ ወይስ ውሽማሽ መሰ..ል..ኩ...ሽ... ሻርሙጣ!»
«አሁንስ በዛ ወግድ ተላዬ!»
«ይችን ይወዳል ተክሌ...!» ሌላ የምት ድምፅ... ሌላ ምት...
«እጮሀለው ትዋረዳለህ..... ውረድ ተላዬ... እህህህህ... ውረ....»
ሰናይት አካሏ በፍርሀት እየተንዘፈዘፈ የናቷንና የተክሌን ንትርክ እንቅልፍ እንደወሰደው ሰው ሆና ታዳምጣለች:: በተደጋጋሚ በደረሰባት ግርፋትና ማስፈራራት የፈለገ ቢሆን እናቷ ከሰው ጋር ካለች እንቅልፍ እንደወሰደው ልጅ አይኖቿን ጨፍና የተኛች ማስመሰል እንዳለባት ነበር:: ዛሬም ድምፅ ብታሰማ እቀጣ ይሆናል ብላ ስለፈራች እየጎላ በመሄድ ላይ ያለውን የአልጋ ላይ የፀብ ግብግብ እየሰማች እጇን በቀስታ ወደ ጉንጮቿ ስትሰድ በእምባ ርሰው አገኘቻቸው:: መቼ ማልቀስ እንደጀመረች አታውቀውም::

ተክሌ እየደጋገመ ጥፊና ጉሸማ እናቷ ላይ ሲያሳርፍባት ይሰማል:: እሷም ከስሩ ተፈናጥራ ለመውጣት የምታደርገው ሙከራ ሁሉ በሱ ምትና ጥብቅ አያያዝ እየከሸፈ ብትቸገርም መታገል ግን አላቆመችም:: የመጨረሻዎቹ ምቶች ጭካኔ የተሞላባቸው የከፉና ጠንካሮች ሆኑ:: ርህራሄ አልባዎቹ ተከታታይ ቦክሶች ሁለቱን የላይኛውን የፊት ጥርሶቿን ገንጥሎ ጣላቸው::
«ኡ...ኡ...ኡ.....» የጣር ጩኸት አካባቢውን አናወጠው:: ወድያው ችምችም ካለው መንደር በሮች እየተከፈቱ ሰዎች ብቅ ብቅ ማለት ጀመሩ:: ሰዓቱ ከለሊቱ ዘጠኝ ከሀያ ብሎዋለ:: ተክሌ አውልቆ እየበታተነ የጣላቸውን ልብሶቹን እየለቃቀመ እርቃን የነበረው አካሉን በጥድፊያ ሸፋፈነና ለመውጣት ወደ በሩ ተራምዶ ከፈተው:: የሰናይት እናት ልትይዘው ታገለች ባለው አቅሙ ሁሉ ገፍትሮ ጣላትና ሲወጣ በርካታ ሰዎች ስፍራውን ከበውታል:: ግርግሩን ከርቀት ያዩ የቀበሌ ታጣቂዎች ወድያው ደረሱና ተክሌን ያዙት::
ሰናይት ከናቷ አፍ የሚወርደውን ደም እያየች በፍርሀት የቤቱ ግድግዳ ላይ ተለጥፋና ኩርምት ብላ ተቀምጣ ሳግ ያፈነው ለቅሶ ታለቅሳለች እምባዋም ካለማቋረጥ መንታ መንታ ሆኖ ይወርዳል.....

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

እናቷ አእምሮውን እንደታወከ ሰው ከውጭ ወደ ውስጥ እየዘለለች በመጮህ «ገሎኛል..... በህግ አምላክ..... በህግ አምላክ..... ያዙልኝ በህግ አምላክ.....» ሰናይት በህግ አምላክ የሚለው ቃል የሰው ስም መስሏት አብራት «በህግ አምላክ» እያለች ትጣራ ነበር በፍጥነት ደርሶ የናቷን ደም እንዲበቀል...

ተክሌ ተይዞ በአቅራቢያው ወደሚገኝ የቀበሌው ማረፊያ ቤት ሲወሰድ የሰናይት እናት የሚቀርቧት ጎረቤቶቿ ከአፏ የሚፈሳትን ደም ለማቆም ሁሉም የየራሱን ሀሳብ እያመጣ «ቀና በይ አትዘቅዝቂው..... ጥጥ አምጡ እስኪ..... በእንጆራ ምጣድ ማሰሻ ቅዳጅ ጨርቅ ተኩሱት..... አላስተረፋትም እኮ...»

ለሊቱ አልፎ በቀጣዩ ቀን ከምሳ ሰዓት በውኋላ ተክሌ ተለቆ በመጠጥ ሞቅታ እየተሳደበ የሰናይት እናት ካቲካላ ቤት ገባ። የሰናይት እናት አብጦ የሚጠዘጥዛት ፊቷን በአረጀ ሻሽ አስራ ለአንድ ደንበኛዋ አረቄ እየቀዳች ነበር።
ተክሌ በንቀት ተገላምጦ «ማን መሆኔን የማታውቂ ተራ ሁላ..... አንቺ ነይ ለኔም ቅጂ....!»
የሰናይት እናት እንባ እየተናነቃት «የለም ውጣልኝ»
«አንቺ... ገና አንገትሽን እንደ ዶሮ ጠምዝዤ ነው የምጥልሽ» አለና ለሌላኛው ሰው የተቀዳውን መለኪያ አንስቶ ወደ ፊቷ ወረወረባት። መለኪያዋ የግንባሯን ጠርዝ ገጭቶ ግድግዳው ላይ ተላተመ። እሷም በደመ-ነፍስ ተፈናጥራ እጇ ምን እንዳነሳ እንኳ በቅጡ ሳትለይ አጎንብሳ ስትነሳ እጇ ውስጥ የገባውን የቡና ሙቀጫ አሽቀነጠረችበት። ተክሌ እንደተቀመጠ በዛው ወደ መሬት ተንሸራቶ ወረደ። ወድያውም ፊቱ በደም ተሸፈነ። ይህ ሲሆን ሰናይት ከትምህርት ቤት ገና ገብታ እናቷ የሚበላ እስክትሰጣት እየተጠባበቀች ነበር።

ጩኸቱ ከየት እንደተጀመረ አይታወቅም «ሞተ....ሞተ..... ገደለችው.....» ለሊት ላይ ተክሌን የያዙት የቀበሌው ጥበቃዎች ደረሱ። የሰናይት እናት ወደ እስር ቤት ስትላክ ተክሌ ወደ ሆስፒታል አመራ። በርካታ ደም ከመፍሰሱ በስተቀር የከፋ ጉዳት አልደረሰበትም። የሰናይትን እናት መበደል ማንም ከመጢፍ ሳይቆጥረው የጥፋተኝነት መንስኤና የአካባቢው ሰላም አዋኪ ተብላ የስድስት ወር እስራት ተፈርዶባት ወህኒ ወረደች።
ሰናይትም ከነሱ እምብዛም የተሻለ ኑሮ ያልነበራቸው ጎረቤታቸው ጋር ተጠግታ ትምህርቷን አቋርጣ እነሱን በስራ እያገዘች ማንም እንዳሻው

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

እያዘዛት እና እየላካት፤ ልብሷ በላይዋ አልቆ ረሀብ እንደቀለደባትና እንደ መርገምት ልጅ ተቆጥራ እናቷ ከእስር እስክትፈታ የመከራ ወቅትን አሳለፈች።።
እናቷ ስታገኛት በሚያሳዝን ሁኔታ እየተንሰቀሰቀች «እማዬ እባክሽ ሁለተኛ ትተሽኝ አትሂጂብኝ..... ሁለተኛ..... ለኔ ማንም አያዝንምኮ.....»
እናቷ አቅፋት አብራት ከማልቀስ በስተቀር ልትሰጣት የምትችለው መልስ አልነበራትም።።

  

የማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

ምእራፍ 5

ሰናይት ፓሪስ በናንትሪ ጎዳና ላይ በሚገኘው አፓርትመንት ቤቷ ሆና በዮጋ ስፖርት አካሏን ስታፍታታ ቆየችና ድካም ሲሰማት በቀዝቃዛ ውሀ ገላዋን ታጥባ ጨረሰች በእለቱ ይህ ነው የሚባል የምትሰራው ስራ አልነበራትም። ሰዓቱን ተመለከተች ከቀኑ ዘጠኝ ሰዓት ብሏል።

ወደ ሳሎኑ አመራችና ቀሪውን ሰዓት እንዴት ማሳለፍ እንደምትፈልግ እያሰበች ሳለ የቤቷ ስልክ ጠራ ሳታነሳው ተወችው። የምትኖርበት ቤት አንድ የመኝታ ክፍል፣ አንድ ሳሎን የመታጠቢያና የማብሰያ ክፍሎች አሉት። ወደ መስታውትማ የቤቱ ግድግዳ ጋር በማምራት ብርሃን መከላከያ መጋረጃውን ከፍታ ቁልቁል ተመለከተች። ልዩነት የሌለውን የዕለት-ዕለት እንቅስቃሴ በአግራሞት ማስተዋል ስትጀምር ስልኩ ድጋሜ አንጫረረ።

ፈጥና በመራመድ አነሳችውና "ሀሎ"

"ሰናይት?"

"ነኝ"

"እንደምን ዋልሽ?"

"ማነዎት?"

"ፒየር"

"ፒየር.....?ፒየር.....?" ውድያው ነበር ያስታወሰችው ግን አውቃ የዘነጋችው ለማስመሰል ሞከረችና "ኦው..... አስታወስኩ..... ይቅርታ ደህና ዋልክ?" አለች

"ሰላም ነኝ "

ፒየር ቆየት ብሎም "ከአንቺ ጋር ስለምናካሂደው ስራ ከአለቃዬ ጋር ተወያይተን ጨርሰናል። ላነጋግርሽ ልመጣ መሆኔን ልገልፅልሽ ነው የደወልኩት"

"ይ.....ቻ....ላል" ቃላቱን እየጐተተች መለሰችለት።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“ምናልባት ቅሬታ ካለሽ ሌላ ቦታ መገናኘት እንችላለን”
“አዎ እኔም ወጣ ማለት ፈልጌ ነበር”
“መልካም ብቻችን የምንሆንበት ቦታ ቢሆን ጥሩ ነው፡፡”
“እጋራዋለሁ ስሜትህን”
ከአንድ ሰዓት በኋላ በአንድ ፀጥ ያለ ሆቴል ውስጥ ተገናኙ፡፡

ፒየር ቀጠን ብሎ ረዘም በሚለው ፊቱ ላይ ያጠለቀውን ሰፊ ጥቁር መነፅር እያለወቀ በረዥሙ ተነፈሰና “ሙቀቱ ድካም ይለቃል...” ብሎ የለበሰውን የጥቁር ሙሉ ሱፍ ኮት ቁልፎቹን ማላላት ጀመረ፡፡ እንደተቀመጠ ሁለቱም የሚጠጣ አዘዙ፡፡
ጥቂት ዝም ተባብለው ቆዩና ሰናይት “እሺ ሲ.አይ.ኤ. ምን ይሆን ሊያሰራኝ ያሰበው?”

ፒየር ሰርሳሪ እይታውን በገፅታዋ ላይ ተክሎ “ከዛ በፊት በአፍሪካ ውስጥ ስላለው የሰው ልጅ መብትና እኩልነት ጥቂት ብንነጋገር”
“አስፈላጊነቱ አልታየኝም ሁለታችንም ብዙ እናውቃለን ብዙ ማለትም እንችላለን”
“እስኪ ጥቂት እንበለው ለመነሻነት እንዲሆነን”
“ግልፅ ነው ህዝቦች በገዢ ፖርቲዎች ካለአግባብ ይጨፈለቃሉ፤ ስለ ነፃ መንግስት ማንም ደፍሮ አይናገርም፤ ለሁሉም እኩል መብት የለም አድልኦና ጭፍንነት ተንሰራፍቷል፤ ህዝቦች መስራት እየፈለጉና እየቻሉ እንዳይችሉ ይደረጋሉ፤ መማር እየፈለጉ እንዳይማሩ ይገደዳሉ፤ መዳን እየቻሉ እንዲሞቱ ይተዋሉ ብቻ .....ብዙ..... ልንል እንችላለን መተንፈስ ራሱ ተፈጥሮዋዊ በመሆኑ እንጂ በአፍሪካ የማይፈቀድ ወይም በሽያጭ የሚቀርብ በሆነ ነበር፡፡”
“ጥሩ ተገንዝበሻል፡፡ ይህ ሁሉ ከሚፈፀምባቸው መላው የአፍሪካ አገሮች መሀከል አንዷ ደግሞም በኢትዮጵያ መሆኑን ትቀበይ ይሆን?”
ፒየር ንግግሩን ገታ አድርጎ አያትና “ለዚህ ነው እንግዲህ ሲ.አይ.ኤ. በአፍሪካ ውስጥ ጣልቃ እንዲገባ የተገደደው፡፡ ህዝቦች በነፃነትና በእኩልነት እንደፍላጐታቸው መኖር ስላለባቸው”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ፒየር ሰናይትን ወደሚፈልገው አቅጣጫ እየሳባት እንዳለ በመገንዘቡ "አዎ ውቢት..... በዛ አህጉር ያለ እያንዳንዱ ብሔር ነፃ የሆነ የራሱን መንግስት አቋቁሞ እንዲኖር የሚያስችለው መብቱን ሊረጋገጥለት ይገባል፡፡"

ሰናይት ፊቷን ጨፍገግ አድርጋ "አልገባኝም ብታብራራልኝ?" "ብሔሮች ራሳቸውን ችለው ወደ መንግስትነት መለወጥ አለባቸው፡፡ የራሳቸውን ባራዲራ እያውለበለቡ በነፃነት መኖር መቻል አለባቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ ሲ.አይ.ኤ. ከጐናቸው በመሆንና ከፍተኛ የሆነ በጀትን መድቦላቸው በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡"
ሰናይት በምትሰማው ነገር እንደተመሰጠች "ይህ ታዲያ ከኔ ጋር ምን ሊያገናኘው ቻለ?"

ፒየር ጥሩ ቃላቶችን ለመጠቀም እየጣረ "በኢትዮጵያ ውስጥ ለምናደርገው የብሔረሰቦች ነፃ መውጣትና የራሳቸውን መንግስት መመስረት እንዲችሉ በምናደርገው እንቅስቃሴ ላይ ልታግዥን እንደምትችል በማወቃችን ሲሆን ያለፈ ጊዜ እንደነገርኩሽ በስርሽ የሚመደበውን ቢልየን ዶላር ከሌሎች በተሻለ ሁኔታ ለተፈላጊው እቅድ እንደምታውይው በማመናችን ነው፡፡"

ሰናይት ምን ልትለው እንደሚገባት ጠፍቷ ለደቂቃዎች ስታስብ ቆየችና "ለመሆኑ በግሌ የማገኘው ጥቅም ምንድነው?"
"ሁለት ነገሮችን፡፡ ከመንፈሳዊው ጥቅምሽ ብንጀምር እያንዳንዱ ሲጨቆን የኖረ ብሔር ነፃ ወጥቶ ተነፍጐት የኖረውን የሰላም አየር ሲተነፍስ ማየት በራሱ ላንቺ ምን ያህል እርካታን ሊሰጥሽ እንደሚችል አስቢው፡፡ እንደውም ዋናው ዓላማሽ ይህ ነው ሊሆን የሚገባው አፍሪካ ያጣችውን ሰላም በዚህ የነፃነት መንገድ ለማስመለስ ማስቻልሽን ብቻ አተኩሪበት፡፡ እንዲሁም....."
አቋረጠችው እና "ትክክለኛ አካሄድ መሆን ከቻለ.....አዎ"
"..... ሁለተኛው ይህ የብሔሮችን ነፃ የማውጣት ስራ በጣም በአጭር ግዜ ውስጥ እንዲጠናቀቅ ነው እቅዱ የተነደፈው፡፡ አንችም ከዛ በኋላ ያለፈ ጊዜ እንደነገርኩሽ ለአገልግሎትሽ የሀምሳ ሚልየን ዶላር የመጠሪያ ገንዘብ ይሰጥሽና በዓለም ላይ የምትመርጫቸው ስፍራዎች

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ሁሉ እየዞርሽ ቀሪ እድሜሽን በደስታ እንድታሳልፊው ይፈቀድልሻል፡፡ ይህ ታዲያ ታላቅ እድል አይመስልሽም?"

በህሊናዋ 'ይህኛው ይበልጥ ስሜትን ያነሳሳል' ብላ እያሰበች "ይህ ስራ ምን ያህል አደገኛ እንደሆነ ምንም መነጋገር አያሻውም ለህይወቴ ምን ዋስትና ማግኘት እችላለሁ?"

ፒየር መልስ ሳይሰጣት ተነሳና ወደ መስታወቱ በመራመድ እይታውን የጦዳናው እንቅስቃሴ ላይ ሰድሮ በህሳብ ተዋጠ፡፡ ከዛም "እንደምታውቂው የተቋማችን አሰራር ሚስጥራዊና የተወሳሰበ ነው፡፡ በመላው የዓለም ግዛት ላይ ለኛ የሚሰሩ ከፍተኛ የፖለቲካ ውሳኔ ሰጪዎች፤ ከፍተኛ ባለሀብቶች፤ ወታደሮች፤ አምባሳደሮች አሉን ይህን ስራ አንቺ እንድታስኬጅው ተመረጥሽ እንጂ ከአንቺ በስተጀርባ ሙሉ ዓለም አብሮሽ ነው የሚሰራው፡፡ ሆኖም አንቺም እነሱን አታውቂያቸውም፡፡ እነሱም አንቺን አያውቁሽም፡፡ ሁላችንም ግን ለአንድ መስራበት ነው የምንሰራው፡፡ ስለዋስትናሽ በእርግጠኝነት ልነግርሽ የምችለው ሲ.አይ.ኤ ባለው አቅም ሁሉ ማንኛውንም ዓይነት ጥበቃ፤ ከለላና ዋስትና ሊያደርግልሽ የሚችል መሆኑን ብቻ ነው፡፡"

ፒየር ወደ ወንበሩ ተመልሶ እየተቀመጠ "ያልተረዳሽው ነገር ካለ ብትጠይቂኝ?"
ሰናይት በአሉታ ጭንቅላቷን ነቀነች
"ቅሬታስ?"
"ለጊዜው ትክክለኛ ስሜቴን ለማወቅ ይቸግረኛል፡፡ ስለእንደዚህ አይነት ስራ የጠለቀ እውቀት የለኝም፡፡"

"ቢሆንም ለሶስት ዓመታት በፖለቲካ ጋዜጣ አሳታሚነት ከመቆየትሽም በላይ ከዩኒቨርስቲ ተመርቀሽ የወጣሽው በፖለቲካ ሳይንስ በመሆኑ ለዚህ ስራ ከአንቺ የተሻለ በቂ ግንዛቤ ያለው ሰው ማግኘት ይቻላል ለማለት አልደፍርም፡፡ ሌላው ዋና ነገር ለስራው የሚያስፈልግሽን ሙሉ መረጃ እኛ ራሳችን የምናቀርብልሽ ሲሆን የምትጠይቂው ነገር በሙሉ ይሰጥሻል፡፡ "
"ግን በእቅዳችሁ ባልስማማስ ?" ድንገተኛ ጥያቄ ሰነዘረች፡፡
"በቂ ምክንያት ካለሽ አሳምኚኝ" ፒየር ፊቱን ጨምድዶ ተናገረ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

“በቃ ዝም ብሎ ያለመስማማት ..... ማለት ሌላ አብሮዋችሁ የሚሰራ ሰው ብትፈልጉ.....”

ፒየር ፈገግ አለና የእጅ ሰዓቱን እያየ “እጅግ ቀላል ነው፡፡ አንቺ ግን ማወቅ ከሚገባሽ በላይ ስለአንድ አለማቀፋዊ ሚስጥር ስትሰሚ በመቆየትሽ ለህይወትሽ ጥሩ እንደማይሆን ብነግርሽስ?”
“ልታስገድዱኝ የምትችሉ አይመስለኝም!” በቁጣ ተናገረች፡፡

ፒየር ብልጠት መጠቀም እንዳለበት እያሰበ “እሞ፡፡ፈፅሞ አንችልም፡፡ በፕላኔታችን ላይ ግን ለጋራ ጥቅማችን ስንል ተግባብተን በጋር ለመስራት የምንገደድባቸው በርካታ ነገሮች አሉ፡፡ ይህም ከነሱ መካከል አንዱ ነው፡፡ ለሚስጥራችን ደህንነት ስንል ግን ምናልባት ምን ሊፈጠርብሽ እንደሚችል እርግጠኛ ሆኜ መናገር አልችልም፡፡”
“ልታስፈራራኝ እየሞርክ ነው እንዴ? ”
“በጭራሽ አይደለም..... የተቋማችንን አሰራር ነው የነገርኩሽ”

ሰናይት ለማለት የፈለገው አደገኛ ነገር በትክክል ገብቷት ነበር፡፡ ራስዋን ማምለጫ የሌለው ጉድጓድ ውስጥ የገባች አይጥ ያህል ተሰማት ፡፡ አጣብቂኙ ቀላል እንዳልሆነ ቁልጭ ብሎ ታያት፡፡ ግን ደግሞ ደስ የሚል ስሜት ፈጠረባት፡፡
ቀጠለ ፒየር በእርጋታ “የህዝቦች ነፃነት ፤ የሀምሳ ሚልየን ዶላር ክፍያ..... ጊዜ ልሰጥሽ እችላለሁ አስቢበት” አለና ሰዓቱን ደግሞ አየው፡፡

በሰናይት ላይ ከዛሬ ጀምሮ ክትትል እንዲያደርግ የተቀጠረው ሰው ስራውን የሚጀምርበት ሰዓት በመድረሱ ፒየር መነፅሩን ከጠረጴዛው ላይ አነሳውና “ እደውላለሁ፡፡ መልካም ምሽት.....” ብሎ ወጣ፡፡
ከአንድ ቀን በኋላ ደወለ
“ሀሎ”
“ፒየር ነኝ .....”
“ፈጥነህ ደወልክ”
“እርግጠኛ ነበርኩ በቂ ጊዜ እንደሰጠሁሽ.....” ቀጠለ “ውሳኔሽ ምን ሆነ?”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“ተስማምቻለሁ” በእርጋታ መለሰች።

“ስራውን ከጀመርሽ በኋላ ለመሰወር ብትሞክሪ የገባሽበት የዓለም ጥግ ድረስ መጥተን እንደምናገኝሽ ማስታወስ ይኖርብሻል። ”
ልክ መሆኑን ስላመነች መልስ አልሰጠችውም።

  

ያማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ምዕራፍ 6

ጐዳናዎች በምሽት መብራቶች ወከክ ብለው ይታያሉ። ሰዓቱ በፓሪስ አቆጣጠር 1፡23 ብሎዋል። የአየሩ ቅዝቃዜ ከመጨመሩና በሰማይ ላይ ክዋክብቶች ነቁጥ ሆነው ከመታየታቸው ውጪ አስፓልቶች እንደ ቀኑ ሁሉ በመኪና ትርምስና በጡሩንባ ጩኸታቸው እየታመሱ ናቸው።

እግረኞችም መተላለፊያዎችን አጨናንቀው ይታያሉ። ከየህንፃዎቹ መስኮቶች ውስጥ እና በላያቸው ከተንጠለጠሉት የማስታወቂያና የጌጥ አምፖሎች የተለያዩ ቀለማት መብራቶች ለከተማዋ ልዩ የሆነ ውበትን ሰጥተዋታል።

ቡና ቤቶች፣ የገበያ አዳራሾች፣ ባንኮች፣ ዓለም አቀፍ የሰውና የሸቀጥ ዝውውር ወኪሎች ሁሉም በስራ ወከባ ተጠምደው ይራወጣሉ። ሃያ አራት ሰዓት እረፍት የለም አንዱ ሲተኛ ሌላው ይሰራል። የሰራው ሲያርፍ ያረፈው ሲሮጥ ይታያል። ጊዜ ውድ ነው።

ፒየር ለሰናይት ደውሎ መልሱን እንደሰማ በደስታ እራት ሲመገብበት ከቆየበት ሆቴል ወጣና ያመራው ወደ መስራቤቱ ነበር።እንደደረሰ የራሱን ቢሮ አልፎ ወደ ሉዊስ አመራና አንኳኩቶ ገባ።

ሉዊስ በፈገግታ እንደተዋጠ ቀና ብሎ አየው። ብቻውን ስለ አንድ ጥሩ ነገር ሲያስብ መቆየቱ ያስታውቅበታል። “ጥሩ ዜና አለኝ ፒየር!” ቀድሞ ተናገረ።

ይህ ድራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“እኔም እንዳንተው.....” ጨበጠውና ከጠረጴዛው ፊት የሚገኘውን ወንበር አመቻችቶ ተቀመጠ፡፡
“እስኪ ያንተ ይቅደማ”
ፒየር “ይቻላል” ብሎ ጉሮሮውን አፀዳና “ሴትየዋ ከኛ ጋር ልትሰራ ተስማምታለች፡፡”
“እንቢ ልትል የሚያስችላት ጠንካራ ምክንያት እንደሌላት የጀርባ ታሪኳን ሳነበው አውቄ ነበር ? በአገሯ መሬት ላይ ያደገች ያለመሆኗ በራሱ ተዕእኖ አሳድሮባታል፡፡ ”
ፒየር “ብዙ ምክንያቶች ነበሩ.....” አለና ከሰናይት ጋር ሊስማማ የቻለበትን እውነታ ሁሉ በዝርዝር ገለፀለትና “ለህይወቷ ዋስትና እንድንሰጣት ጠይቃ ነበር”

ሉዊስ ፈገግ እንዳለ “ጣትን እሳት ውስጥ ከቶ እየተጫወቱ እንዳያቃጥለኝ ማለት አይቻልም፡፡ ተራ ነው ጥያቄዋ... ይህ ድርጅት ተቋቁሞ ግማሽ ምዕተ ዓመት ሲንቀሳቀስ እንደዚህኛው ወቅት ያለ ስኬት መቼም ገጥሞት እንደማያውቅ ነው በእርግጠኝነት የምናገረው” “ይመስለኛል..... ባንተስ በኩል ምን ጥሩ ነገር ገጠመህ?”

ጠረጴዛው ላይ የነበረውን ወረቀት ገፋ እያደረገለት “ፈንድ የሚያደርጉን አገሮች ቁጥር እየጨመሩ መጥቷል፡፡ በከፊትነው የባንክ ቁጥር ገብቶ የነበረው የገንዘብ መጠን ከአንድ ቢልየን በላይ የሰላት መቶ ሚልየን ዶላር ጭማሪ ያሳየ መሆኑን ከባንኩ የተላከልኝ ደረሰኝ ይናገራል”
“ከየት አገር ነው ክፍያውን ያገኘነው?”
“አይታወቅም” አለ ሉዊስ፡፡ ቀጠለ “የገንዘቡን መዋጮ የሚልኩልን አገሮች ራሳቸውን ሊያሳውቁን አይፈልጉም፡፡ አብዛኞቹ ሀያላን የአውሮፓ ኢሲያና አሜሪካ መንግስታቶች ግን የአፍሪካን ሰላም ያለመሆን እንደሚመርጡ ነው ክፍያው የሚያሳውቀን፡፡ በተጨማሪም ገቢ የሚደረግልን ገንዘብ ገና በገፍ የሚቀጥል መሆኑን ነው ሁኔታዎች የሚጠቁሙን፡፡” ሉዊስ በስሜት እንደተዋጠ ቀጠለ “.....እኛም አትራፊ እስከሆንን ድረስ ይህን እቅድ ከግቡ ለማድረስ የማንጥርበት ሁኔታ አይታየኝም...” አለ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ቀጠለ "... በሚቀጥሉት ሁለት ሳምንታት ውስጥ በአካል ተገኝቼ ላነጋግራቸው ቀጠሮ ያስያዝኳቸው ቀደምት የስራ ጓደኞቼ አሉ። ስለዚህ አድካሚና ተከታታይ ጉዞዎች ይኖሩኛል። !"
ፒየር "ምንም ችግር የለውም አስፈላጊ ጉዳዮችን እኔ ደርቤ ማከናወን እችላለሁ።"
በዝምታ ጥቂት ቆይተው ፒየር ቀጠለ "አሁን በኢትዮጵያ ስንት መንግስት እንዲፈጠር ነው ለሰናይት መንገር ያለብን?"
ሊዊስ ይህን እቅድ አስቦ ከተነሳበት ወቅት ጀምሮ ስለ አገሪቷ ሲያጠና የቆየውን እያስታውሰ መመለስ ጀመረ "ያለን መረጃ እንደሚጠቁመን ኢትዮጵያ ሰማንያ ብሔረሰቦች አሏት። በዘጠኝ ክልላዊ መንግስትም ተከፋፍላ ትገኛለች"

"ስማቸውን ታውቀዋለህ?" ፒየር ማስታወሻ ለመያዝ እየተመቻቸ ጠየቀው።
"ሰነዱን እንድታነበው እሰጥሀለው። ለማወቅ ያህል የክልሎቹን ስሞች ልንገርህ" አለና ከጠረጴዛው መሳቢያ ኪስ ወፍራም ጥራዝ አውጥቶ በመግለፅ ".....ትግራይ፣ አፋር፣ ሐረር፣ ሱማሌ፣ ኦሮሞ፣ የደቡብ ብሔረሰቦች፣ ጋምቤላ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ እና አማራ ሲሆኑ ሁሉም በማዕከላዊ ፌደራል መንግስት ስር ይተዳደራሉ።
የማዕከላዊውን ጨምሮ አስር ባንዲራ አላቸው።የእቅዳችን መጨረሻ ሊሆን የሚገባው እነዚህ አስር የክልል ባንዲራዎች በኢትዮጵያ ላይ ራሳቸውን የቻሉ አስር መንግስታትን እንዲፈጥሩ ማስደረግ ነው።
".....ለጊዜው ያለን የገንዘብ አቅም ግን ሁሉንም መንግስታት የሚያቋቁም ባለመሆኑን አምስት ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ያላቸውንና ይበልጥ ደግሞ የመገንጠል ፍላጐትን የሚያራግቡ የክልል መሪዎች የሚገኙባቸውን እንመርጣለን። ኢላማችንንም ወደነሱ እናነጣጥራለን። ምናልባት ቀሪዎቹ አምስቶቹ በራሳቸው ጊዜ ራሳቸውን ፈጥረው ሊገኙ ይችላሉ።
"ከዛም ኢትዮጵያ የምትባለዋ አገር እንደ ጥንቱ ባቢሎን ታሪክ በኋላም ተረት ሆና ትቀራለች" አለ ሉዊስ ፊቱን ቅጭም አድርጐ።
ፒየር እይታውን ከሉዊስ ላይ ሳያነሳ "እንደታሰበው ላይሔድልን ቢችልስ?"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“እንኳን ኢትዮጵያ ታላቋ ራሽም ተበታትናለች። ሆዳም የሆኑ የአገር መሪዎች እስካሉ ድረስ ህዝብ መገንጠል ፈለገም አልፈለገም መሪዎቹ እንዳሻቸው ሊያድረጉት ይችላሉ። ዋናው እነዛን የስልጣን ዝናና የገንዘብ ጥማት ያሰከራች መሪዎቻቸውን ይዞ እሳቱን ማራገብ ነው...”

“...መንግስቶችን መፍጠር ቢያቅተን አንዱን ብሔር ከሌላው ጋር ማጋጨት አያቅተንም። አሁን ገዢ ሆኖ ያለው መንግስት ለዚህ ሁኔታ ስፍር ቁጥር የሌላቸውን ቀዳዳዎችን ፈጥሮልናል። ኢትዮጵያ ግለኝነትና ብሔርተኝነት በእጅጉ ነግሶባታል። በኢትዮጵያ ውስጥ እንደ ሩዋንዳና ብሩንዲዎቹ ሁቱና ቱትሲዎችን የመሰለ የሚተላለቅ የጦሳ ብጥብጥን መፍጠር እጅግ ቀላል ነው። እንደ ኦሮሞና አማራን ትሬና ሌላውን የመሰለ በጥላቻ የሚተያይ ብሔር እያለ።
“.....ወይም እንደ ሱማሌዋ አይነት የደደቡ የአንጃ መሪዎችን ፈጥረን እያቀናጀንና በተናጠል ሁሉንም እያስታጠቅን አገሪቷን ፍፁም ልትወጣው ወደማትችልበት አዘቅት ውስጥ ማሽቀንጠር ይቻላል።
“.....ትልቁ ዓላማችን ፈንድ የሚያደርጉን ሀያላን የዓለም አገሮች ፍላጐት እንዲሟላ ማድረግ ነው። በእቅዳችን መሰረት መላው አፍሪካን ለጊዜው ግን ኢትዮጵያን ዘመን ሊፈውሰው የማይችል የህዝብ ለህዝብ የመመራረዝ ነቀርሳ ውስጥ መዝፈቅ ነው። ደግሞም በእርግጠኝነት አያቅተንም እናደርገዋለን!” አለ ሉዊስ።

  

የማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ምዕራፍ 7

“ህይወት ማለት እንደ ሆቴል ቤት ማንም ሰው ዘው ብሎ ገብቶ እንደ መሻቱ የሚስተናገድባት ቆይታ አይደለችም።” ፒየር ነበር ከሶስት ቀናት በፊት በሀምሳ ሁለት ገፅ ላይ የተነደፈ እቅዳቸውን አምጥቶ ለሰናይት ሲሰጣት አላትና አስተውሎ እያያት ቀጠለ “.....በመኖር ውስጥ እንዳሰብነው ከምንኖረው ይልቅ እንዳላሰብነው በመኖር የምናባክናቸው ዘመናችን ስለሚያመዝን አንቺም ይህን ታላቅ ስራ ሰርተሽ ታሪክ ሆነሽ እለፊ።” ብሎ ነበር ወረቀቱን ጥሎላት የሄደው።

ከዛ በኋላ ከማንም ሰው ጋር ተገናኝታ ሚስጥር እንዳታባክን የስልክ መስመሮቿ ተጠለፉ በራሷም ላይ ሙሉ የሃያ አራት ሰዓቶች ጥበቃና ክትክትል ተጀመረባት።

ቤት በዋለችባቸው ቀናት በሙሉ የእቅዱን አጠቃላይ ገፅታ በማንበብ ዋና ዋና ሀሳቡን እየለቀመች ከእምነትና አመለካከቷ ጋር እያስታረቀች ጊዜውን አሳለፈች።

በአራተኛው ቀን ከፒየር ጋር ለመገናኘት አዘውትራ ምሳ ወደ ምትመገብበት ሆቴል ያመራችው ከቀትር በኋላ ነበር። ሰው ስለማይበዛ ያለ ስጋት መወያየት እንዲችሉ ዘጠኝ ሰዓት በተቀጣጠሩበት መሰረት ደረሰች። ፒየር ግን ቀድሟት ተገኝቷል። ስታየው ለምን እንደሆነ ሳይገባት ደንገጥ አለች። ለአለባበሷም አልተጠነቀቀችም ።

ይህ ሁሉ ግን ለፒየር አንድ በጐ ጥቁምታ ሰጠውና በህሊናው ‘ለሚሰራው ስራ ሙሉ ጊዜዋንና መንፈሷን ሰጥታ በሚገባ አጢናዋለች ’ ሲል አሰበ።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ለረዥም ዓመታት እንደሚተዋወቁ ጓደኛሞች ተጨባበጡ።።
“ወረቀቱ ላይ ያሉትን ሀሳቦች በሚገባ እንዳጤንሻቸው ተስፋ አደርጋለሁ” አለ ፒየር።።
“ቀላልም ከባድም በማይባል ሁኔታ።።”
“ምን ያህል ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ይመስልሻል?”
“የተመደበለት የገንዘብ መጠን በአገሪቷ ላይ ሊፈጥር እንደሚችለው ጫና ቢለካ የሚሻል ይመስለኛል።።”
“ሶስት ቢልየን ዶላር እና በሚልዮኖች የሚገመት በነፍስ ወከፍ አግልግሎት ላይ መዋል የሚችሉ የጦር መሳሪያ እርዳታን ነፃ መውጣት ለሚፈልግ የአገሪቷ ብሄረሰቦች ሁሉ ማቅረብ እንችላለን!” አለ በልበ ሙሉነት።።
“ግን.....መሳሪያውን የማስገባቱ ሁኔታ ቢቀርና በገንዘብ ሀይል ብቻ ብንጠቀምስ?”
“እንዴት ሊሆን ይችላል?.....” ቀጠለ ፒየር ከጥያቄያዊ አስተያየቱ ጋር “ለማንም የነፃነት ታጋይ ስኬት እና የመኖር ህልውናውን ሊያስጠብቁለት ከሚችሉት አቅሞቹ መሀከል አንዱ የጦር መሳሪያ መሆኑን አላስተዋልሽም ? የአፍሪካ መንግስታቶች መሳሪያ ካላዩ እውነተኛ ትግል ያለ አይመስላቸውም”
“ጉዳቱ ያመዝናል ብዬ ስላሰብኩ ነው”
“እሱ የአጠቃቀም ጉዳይ ነው።። አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ግዴታ ውስጥ እናሰገባቸዋለን” አለ ፒየር።።ሀሊናዊ እምነቱ ግን በተቃራኒው አቅጣጫ ‘መሳሪያው በእጁ የገባለት ግለሰብ ያሻውን ይፈፅምበት።። ያ ነው የኛ ፍላጐት’ ሲል እያሰበ

ሰናይት ሀሳቡን ለማስለወጥ ጥቂት ሞከረች። በዚህ ዙሪያ መነጋገሩ ምንም ውጤት እንደማያመጣ ስታስብ ቆየችና “እሺ..... እቅዱ በመጀመሪያ ተፈፃሚ የሚሆንባቸው ክልሎችን ብትጠቁመኝ”

ፒየር ከኪሱ በጥንቃቄ የተጣጠፈች ወረቀት አወጣና በላዩ የሰፈረውን አጫጭር ቃላት እያነበበ “የመጀመሪያው ኦሮሚያ በሚባለው ክልል ላይ ነው።። ሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች አሉን።። አንደኛው ክልሉ በርካታ የህዝብ ብዛት አለው።።ሁለተኛው ከኢትዮጵያ ተገንጥሎ ራሱን የቻለ መንግስት ለማቋቋም የጠነከረ ፍላጐት እንዳለው በእጃችን ላይ ያሉት መረጃዎች ይጠቁማሉ።።”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ሰናይት "እኔ ግን ጋዜጣ አሳታሚ ሆኜ በቆየሁባቸው ወቅቶች እንዳጤንኩት ህዝቡ አይደለም የመገንጠል ፍላጎት ያለው። ህዝቡን ወክለናል የሚሉት መሪዎች የግል ፍላጎት ነው እነጂ..."
ፒየር ጥያቄዋን ገሸሽ በማድረግ የራሱን ሀሳብ ቀጠለ «.....ሁለተኛው የሱማሊ ክልል ሲሆን እነሱም የመገንጠል ፍላጐት አላቸው።ሌላው ጠረፍ ላይ የሚገኝ አገር በመሆኑ በሱማሊያ በኩል ወደ ኢትዮጵያ ለሚገባው የጦር መሳሪያ እንደ ማስተላለፊያነት ልንጠቀምባት ስለምንችል በዋናነት ትያዛለች።
".....ሶስተኛው የደቡብ ብሔረሰቦች ክልል የሚባለው ነው።ራሳቸውን የቻለ መንግስት ቢመሰርቱ ለፈጣን እድገት ሊያበቃቸው የሚችል የዳበረ ተፈጥሮዋዊ የሀብት ክምችት ስላላቸው በእቅዱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተመርጠዋል።

"አራተኛው የአማራ ክልል ነው።" አለና ስለዚህ ክልል መመረጥ ከሉዊስ ጋር ሲመካከሩ የተባባሉበትን በጥቅሉ እያስታወሰ "አማራና ኦሮሞ ከዚህ ቀደም በነበራቸው የተዳፈነ ቂም እና የአገሪቱ መዲና በሆነችው በአዲስ አበባ ላይ የሚያቀርቡትን የይገባኛል ጥያቄ የሚያስነሳው ውዝግብ ወደ አስፊሪ የጦሳዎች ጭፍጭፍ ሊያመራ እንደሚችል ካየሁት በመነሳት ላውቅ ችያለሁ" ያላቸውን የአንድ በአዲስ አበባ ያለ መረጃ አቀባያቸውን ዘገባ አስታወሰና 'ይህን ደግሞ እንፈልገዋለን' አለ በውስጡ።
ቀጠለ ፒየር ".....አምስተኛው የትግራይ ክልል ነው በቃ"
"ቀሪዎቹስ?"
"ሌሎቹ..... ክልሎች በጊዜና በገንዘብ አቅማችን ውስንነት በቀጣይ ተፈፃሚ ይሆናሉ።"
"የኔ ስራ የሚያበቃው በአምስቱ ክልሎች ስራ ብቻ ይመስለኛል" አለች ሰናይት።
"ትክክል ነሽ። የነሱን እንዳጠናቀቅን ክፍያሽን ተቀብለሽ መሰናበት ትችያለሽ።"
ቀጠለ ፒየር "ካሁን በኋላ ስራውን እንዴት ማስኬድ እንዳለብሽ የራስሽን መመሪያ ንደፊ። ለዚህ አላማ መሳካት ይጥቃማሉ ብለሽ የምታምኚባቸውን ሰዎች ሁሉ ማግኘት ጀምሪ። በተዋረድ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ለምትመለምያቸው ሰዎችሽ ሀላፊነትን አክፋፍይ፡፡ አንቺ ከበላይ ሆነሽ ሁሉንም ተቆጣጠሪ፡፡ የሚሰጡሽን መረጃዎችና ሀሳቦች ሁሉ ወደኛ አስተላልፊ፡፡ ሌላው ከአሁን በኋላ የምትወስኛቸው ውሳኔዎችና የምትወስጃቸው እርምጃዎች በጠቅላላ ሙሉውን እቅድ የሚነኩ ስለሚሆኑ ሙሉ ሀላፊነት እና ተጠያቂነት አለብሽ፡፡ ከኛም ወደነሱ ማድረስ..... ከነሱም ወደኛ..... የዚህ ሚስጥር አስፈላጊነት ምንም አያነጋግረንም፡፡ የትንሽ ነገር ስህትት የብዙ ሰዎችን የህይወት ዋጋ ያስክፍላልና ጥንቃቄ አድርጊ፡፡ ይህ ነው ተግባርሽ፡፡"
ሰናይት በእሺታ ጭንቅላቷ ነቅንቃ "ስራው መቼ እንዲጀመር ነው የወሰናችሁት?"
"በኛ በኩል ጨርሰናል፡፡ ቀሪው ያንቺ ሀላፊነት ነው፡፡ በአካልም ሆነ በመንፈስ ሙሉ ዝግጁነትሽ ሲጠናቅቅ ልታሳዎቂን ትችያለች፡፡ በማለዳው ሁሉም ነገር ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ ጊዜ ግን የለንም መፍጠን አለብን፡፡" አላት በአዛዥነት መንፈሽ ጫና እያሳደረባት፡፡
"እስከዛው ምን ያህል ግዜ ልትሰጡኝ ፈቃደኛ ናችሁ?"
"ሁለት ሳምንት....."
"ያንሰኛል..... ከኔ ስር ያለውን እቅድ የመንደፍ ስራ አለብኝ እኮ እናም ትንሽ የእረፍት ቀናት"
"እሺ..... ሶስት ሳምንት?"
"በቂ ነው፡፡" ቀጠለች "ክፍያዎችስ እንዴት ይፈፀማሉ?"
"እሱ የኛ ስራ ነው፡፡ ዶላሮች ወደ ኢትዮጵያ ብር ሳይመነዘሩ የአንቺ እጅ የሚገቡበትን ሁኔታ አመቻችተናል፡፡" ቀጠለ ፒየር "....በድጋሜ የማስጠነቅቅሽ እና እጅግ ትኩረት እንድታደርጊበት የምንፈልገው ነገር ከኛ ጋር በሚኖርሽ የመረጃ ቅብብሎሽ ላይ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለብሽ ነው፡፡ የኛን የስልክ ቁጥር የፋክስና መሰል አድራሻዎቻችንን ፈፅሞ ለበታቾችሽ ማሳወቅ የለብሽም፡፡ እንዳስፈላጊነቱ የምትገለገይባቸው የሚስጥር መልዕክት ማስተላለፊያ ኮዶች ያሉበት ማስታወሻ ደብተር ነው ይሄ... " ብሎ አንድ ትንሽ ጥራዝ ከኪሱ አውጥቶ ሰጣትና "ሙሉውን በቃልሽ አጥንተሽ እንደጨረሽ ማንም ሳያገኘው አስወግጂው... ! "
".....ሃያ አራት ሰዓት ሙሉ ለአንቺ ብቻ ክፍት የሚሆን የመረጃ ልውውጥ መስመሮችን በጥቂት ቀናት ውስጥ እንዲከፈቱ አደርጋለሁ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

ምናልባት አድራሻዎቹ በሌላ አካል እጅ የመውደቅ ችግር ቢፈጠር ለጥንቃቄ ስለሚመረጥ በሚስጥር ስሞችና መለያዎች እንድንግባባ በዚህ መመሪያ መሰረት ትጠቀሚያለሽ" አለና ከኮቱ የውስጥ ኪስ ሌላ ባለ አስር ገፆች ያላት የስል ቁጥር መያዣ የምትመስል ትንሽዬ ጥራዝ አውጥቶ እየሰጣት "ቀሪ ነገር ካለህ ብትጠይቂኝ?"
"ለጊዜው ምንም....." ሰናይት በእርጋታ መለሰች፡፡
"እኔ ግን አንድ ነገር ይቀረኛል፡፡"
ቀጥል በሚል አስተያየት አየችው፡፡
"የቃል ኪዳን ስርዓት ነው፡፡ ይህ እቅድ እስኪጠናቀቅ ከህብረታችን ስለመሆንሽ እርግጠኛ ሁኝልኝ፡፡"
ፈገግ አለችና "ካሁን በኋላ ማፈግፈግ በማይቻልበት ሰንሰለት ተጠፍርቄያለሁ"
"ከእምነትህ ጋር በተያያዘ መልኩ?"
"ይመስለኛል....."
"ትክክለኛ ሁኝልኝ?"
"አዎ!"
"ጥሩ ወታደርና ምርጥ ባልደረባችን ሆነሻል፡፡ ራስሽን ከአንዳንድ ተራ ጥቃት ለመከላከል በቂ የቴንኳዶ ስልጠና መውሰድሽን ፋይልሽ ውስጥ ማንበቤን አስታውሳለሁ፡፡"
"አዎ እያቋረጥኩና እየቀጠልኩ ቢሆንም በቂ ስልጠና ወስጃለሁ፡፡"
"ጥሩ..." ብሎ አድራሻ የተፃፈበት ብጣሽ ወረቀት እየሰጣት "... አንድ የኛ ሰው በዚህ አድራሻ እየጠበቀሽ ነው፡፡ አግኝውና የነፍስ ወከፍ መሳሪያዎችን አጠቃቀምና ፈታቶ መግጠም በጥቂት ቀናት ውስጥ ያስተምርሻል፡፡ " አለና ሰዓቱን አይቶ ተነሳ፡፡

«««««« »»»»»»»

ፒየር አመሻሹ ላይ ሉዊስን በስልክ አገኘውና ስለእለቱ ውሎ ሲጨዋወቱ ቆይተው ፒየር "ከሰናይት ጋር በዚህ አገር የሚኖረንን ስራ ጨርሰናል ማለት እችላለሁ" አለ፡፡
ሉዊስ ጥቂት ሲያስብ ቆየና "ስራው ከመጠናቀቁ በፊት አቋርጣ ብትጠፋ ወይም ብትከዳ በስራው ላይ ክፍተት ሳይፈጠር በሷ እግር

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ሊተካ የሚችል ሌላ ኢትዮጵያዊ መዘጋጀት ስላለበት በሁለተኛ አማራጭ ይዘነው የነበረው ሰው ላይ ክትትል መደረግ ይጀመር ።።"
"ልክ ብለሀል" አለና ማስታወሻ መያዝ ጀመረ።።
ቀጠለ ሉዊስ " እንዲሁም በኢትዮጵያ እሷንና ከስራችን ጋር በተያያዘ እየከታተሉ ውጤቱን የሚልኩልን ሰዎች በፍጥነት ይዘጋጁ።።"
"እዛው ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉንን ሰዎች መጠቀም እንችላለን።።"
"አስር ይደርሳሉ?"
"ሰባት ናቸው..... አስር አይበዙም?"
"አይበዙም..... በየክልሉ ላይ ተበታትነው ነው የሚሰሩት።። አንድ ሰው አዲስ አበባ ላይ ይቀመጥና ዘጠኞቹ የሚልኩለትን መረጃ ወደኛ ያሻግራል።።"
"እንዴት ነው አመዳደባቸው?" ፒየር ጠየቀ።።
ሊዊስ ደጋግሞ ያሰበበት ስለነበረ በፍጥነት መመለስ ቀጠለ "በኦሮሞ ክልል ላይ ሶስት ሰዎች ይመደባሉ።። በደቡብ ብሔረሰቦችና በአማራው ክልል ላይ ሶስት ሰዎች፤ በሶማሌና በትግራይ በአማራው ክልል አንድ አንድ ሰዎች" አለና እንደማሰብ ብሎ "አሉ ያልካቸው ሰባት ሰዎች ከዚህ በፊት ለኛ ድርጅት የሰሩ ናቸው?"
"አዎ..... አራቱ በሶማሊያ የቆዩና በዛ አገር ስናካሂድ ለነበረው ተመሳሳይ ስራ የተባበሩን ልምድም ያላቸው ሰዎች ናቸው።። ሶስቱ ግን አሁን ላሉበት ስራ ወደ ኢትዮጵያ ከመሔዳቸው በፊት እዚሁ ፈረንሳይ እያሉ ከኛ ጋር ሰርተዋል።።"
"እዛ በምን ስራ ላይ ነው የሚገኙት?"
"አራቱ ሰዎች በተለያዩ የውጭ አገር የእርዳታ ድርጅት ስር ታቅፈው እያገለገሉ ይገኛሉ።። ሱማሊያ የነበሩትን ማለቴ ነው።።"
"ሌሎቹስ?"
"አንደኛው ሰው በመዲናዋ አዲስ አበባ በሚገኘው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ውስጥ ነው የሚሰራው።።"
"እሱን እዛው አዲስ አበባ ላይ አስረኛ ሰው አድርገህ ትመለምለውና የዘጠኙን መረጃ እንዲያገኝ አድርገው።።"
ቀጠለ ፒየር "ሌላው አንደኛው ሰው ከሁለት ወር በፊት በኢትዮጵያ ቀደምት ታሪክ ላይ ጥናት ለማድረግ ከተጓዘ የአርኪኦሎጂስቶች ቡድን ጋር በመሔድ በትግራይ ክልል ውስጥ እየሰራ ይገኛል።።"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

“እሱም ባለበት እንዲሰራልን አድርገው፡፡”
“ሌላኛው የሃይማኖት ስብከት ለማድረግ መሔዱን ነው ያለኝ መረጃ የሚጠቁመኝ ማለት ትክክለኛ አካሄዱ ለሱ አይመስለኝም” አለ ፒየር፡፡
“ምን ይሆናል ብለህ ትገምታለህ?”
“ለኬ.ጂ.ቢ.. እንደሚሰራም አውቃለሁ አሁን በሃይማኖት ሽፋን በነሱ ተልኮ መሔዱን ነው የማምነው፡፡”
“ምንም ችግር የለውም፡፡ በድራቢነት ለኛም መስራት ስለሚችል አነጋግረው፡፡” ሉዊስ ቀጠለ “ግን ሁሉም ፈረንሳዊ ናቸው?”
“ሶስቱ ብቻ..... ሌሎቹ በትውልድ የሌላ አገር ቢሆኑም ዜግነት ግን አላቸው፡፡”

ሉዊስ በዝምታ ጥቂት ቆየ፡፡ “በሚፈልጉት ክልሎች ላይ ያሉትን እያጣራህ እዛው አሰራቸው፡፡ካልሆኑም ዝውውር በመጠየቅ በእቅዳችን መሰረት በቦታዎቹ ላይ እንዲያገለግሉ አነጋግራቸው፡፡ ቀሪዎቹ ሶስቱን ከዚሁ ፈልገህ መልምልና ከተቻለ በእርዳታ ድርጅቶች ስር ለተወሠኑ ጊዜያት ነፃ የሆነ ግልጋሎት ሊሠጡ ፈቃደኛ የሆኑ የበጐ አሳቢዎች በመምሰል አስመዝግባቸው ካልተቻለ ግን በጐብኚ ስምም ይሁን ስራ ለመስራት በሚሔድ ባለ ሀብት ስም ወደ ኢትዮጵያ እንዲሄዱ አስፈላጊውን ሁኔታ አመቻችላቸውና ለጉዞ ዝግጁ ሆነው እንዲቀመጡ አድርግ፡፡”
“በሚቀጥሉት ሁለት ቀናት ሊጠናቀቅ የሚችል ስራ ነው” ፒየር መለሰ “እሱን እንደጨረስክ የግንኙነታቸውን አቅጣጫ ታመቻችና ለእያንዳንዳቸው ትገልፅላቸዋለህ፡፡ አያይዘህም ጠቀም ያለ ክፍያ የሚያገኙበትን ስራ መሆኑንም ጭምር” አለ ሉዊስ፡፡

ፒየር ማስታወሻ መፃፉን ጨረሰና “ክፍያ ስትል አስታወስኩት ባንክ ገቢ የሆነልንን ገንዘብ ካሁን በኋላ ወጪ በማድረግ እንቅስቃሴ ብንጀምርስ?..... ካለበለዚያ.....”

ሉዊስ አቋረጠው “አይሆንም፡፡ እቅዳችን ለደገፉትና ለተባበሩን ሀያላን አገሮች ደብዳቤውን በትነን ገንዘቡን ስንሰበስብ የገባነው ቃል አለ፡፡ “እቅዱን በኢትዮጵያ ምድር ላይ ተፈፃሚ ማድረግ እስከምንጀምርበት ቅፅበት ድረስ በፈንድ ከተገኘው ገንዘብ ላይ ሽራፊ አንነካም!” ጫን እያለ ተናገረ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“ባሁኑ ሰዓት እንጀምር አንጀምር በምን ያውቃሉ?”
“እነሱም እንደኛው የተጠናከሩ የስለላ ሰዎች በኢትዮጵያ ሊኖራቸው እንደሚችል ማሰብ አለብን፡፡ ሌላው የድርጅታችንን ስም እና ክብር እንደተጠበቀ ለማኖር፤ ሶስተኛውና ዋናው ገና ተሰብስቦ ያላለቀ ገንዘብ ውጪ ተቀምጧል፡፡ በየአገሩ ተሟዙሬ እያገኘሁ እስካሳምናቸውና ሽርፍራፊዋ ሳንቲም ሳትቀር ተሰብስባ ወደ ባንክ ቁጥራችን እስክትገባ ድረስ ምን አጠራጣሪ ስህተ ከመፈፀም መጠንቀቅ አለብን፡፡ ”
“ባለን ገንዘብ መጀመር ነዋ ያለን አማራጭ?”
“እንችላለን በቂ የሆነ ስላለን”
ጥቂት በዝምታ ቆዩ “ሌላ የምንነጋገርበት ጉዳይ አለ?” ፒየር ጠየቀ፡፡
“ጨርሻለሁ” አለ ሊዊስ በህሊናው ከዚህ ስራ የሚያግበሰብሰውን በቢልየን የሚቆጠር ዶላር እያሰበ፡፡ ይህ ገንዘብ በጥሬ የሚገኘውን እንጂ ከጦር መሳሪያዎች ሽያጭ የሚገኘውን የሚጨምር አልነበረም፡፡

  

የማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

ምዕራፍ 8

ሉዊስ ሁለት እጅግ በጣም አስፈላጊ ሰዎችን ለመገናኘት ለንደን እነደደረሰ ምንም ያባከነው ጊዜ አልነበረም። ከቻርልስ ጋር የያየዘው የመጀመሪው የቀጠሮ ሰዓት መድረሱን እንዳረጋገጠ ቀጥታ ወደ ቢሮ አመራ። ከሁለት ዓመት በፊት ከቻርልስ ጋር እንዲተዋወቁ ምክንያት የሆናቸው ሁኔታ የተፈጠረው ሳይታሰብ ነበር።

«««««««« »»»»»»»»»

ወቅቱ ክረምት ሲሆን ጊዜው ከለሊቱ አምስት ሰዓት አካባቢ ላይ በሰሜን አትላንቲክ በኩል ያመራ የነበረ አንድ ግዙፍ መርከብን የዓለም አቀፉ ፖሊስ ተቋም የደህንነ አባሎችን የያዘ ሌላ አነስተኛ የጦር መርከብ መከታል ጀመረ። በዛ የሚያስመርር ቅዝቃዜና ድቅድቅ ጨለማ መሀል በጠንካራ የንፋስ ግፊት የሚናጠውን ውቅያኖስ እየሰነጠቀ ይጓዝ የነበረው ግዙፍ መርከብ የጫነው ግምቱ 150 000 000 የአሜሪካን ዶላር የሚያወጣ ከመለስተኛ የነፍስ ወከፍ ጀምሮ እስከ ከከፍተኛ ሞርታርና የአየር መቃወሚያ ድረስ በጦር መሳሪያ የታጨቀ ነበር። ጭነቱም እየተጓጓዘ የነበረው ወደ ምእራብ አፍሪካዋ ሴራሊዮን ሲሆን ከዚህች በአልማዝ ማእድን ከከበረች አገር ግዢው በአልማዝ ልዋጭ ተከናወነ።

በህገ ወጦቹ የዓለም አቀፍ የጦር መሳሪያ አሻሻጭ ደላሎች አማካኝነት በህጋዊነት ሽፋን ፊላዴልፊያ ከተማ ከሚገኘው የአሜሪካ ግዛት ውስጥ ካለ አንድ የጦር መሳሪያ ማምረቻ ፋብሪካ የተገዛ ነበር። መርከቡ መሳሪያውን እንዲያራግፍ የተፈለገው በሴራሊዮን ወደብ የላይቤሪያ ድንበር አቅራቢ ከሚገኘውና ሱሊማ ከተባለው የወደብ ከተማ በስተሰሜን አቅጣጫ ሀምሳ ኪሎ ሜትር በሚርቅ ስፍራ ሲሆን ቦታው እምብዛም የወደብ አገልግሎት የማይሰጥ ብዙም ነዋሪዎች የሌሉበት ለህገወጥ ድርጊት ማከናወኛነት የተመቻቸ በመሆኑ ተመረጠ።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ሴራሊዮን በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ስር ስትማቅቅ ቆይታ ነፃነቷን ባገኘች ማግስት ነበር ወደ እርስ በእርስ ጦርነት የገባችው። ይህም ችግር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ በመሄዱ አገሪቷን የሚቆጣጠረው ገዢ መንግስት ይሁን ከየአቅጣጫው የሚነሱት ተቃዋሚዎች በጦር መሳሪያ የበላይነትን ለመጨበጥ ከአገሪቷ ማህፀን የሚገኘውን አልማዝ እየቦጠቦጡ ወደ አውሮፓና አሜሪካ በማሻገር በልዋጩ የጦር መሳሪያን ያለማቋረጥ በማስገባ አገሪቷን እና ንፁሀኑን ህዝብ እያመሱ ያለ አንዳች መፍትሄ አመታትን አስቆጥረዋል። እሳቱን ከጆርባ ሆነው የሚያራግቡት የውጭ መንግስታቶችም ለሚያገኙት አልማዝ ሲሉ ዝምታን መርጠዋል።

ይህ የተያዘው ግዙፍ መርከብ ሙሉ የጦር መሳሪያም ለተመሳሳይ ዓላማ በአንድ አማፂ ቡድን በህገ ወጥ መንገድ ተገዝቶ ወደዛው የሚያመራ ነበር። የታዘዘበት ማራገፊያው ሊደርስ የጥቂት ሰዓት ጉዞ ሲቀረው ለቁጥጥር ሲዘዋወሩ በነበሩት የዓለም አቀፍ ፖሊሶች ጥርጣሬ ስር ወድቆ ባለበት ቦታ መህልቁን ጥሎ እንዲቆም ታዘዘ። አባላቱም ጉዳዩን ለበላይ አካላት አሳወቁ።

ወድያውም ጉዳዩ ገለልተኛ በሆነውና በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ስር በረዋቀረው "የዓለም አቀፍ የህገወጥ የጦር መሳሪያ ዝውውር መቆጣጠሪያ ቢሮ" ሪፖርት ደረሰውና ባለው ስልጣንና በተሰጠው ሀላፊነት መሰረት ጉዳዩን ከሁሉም እጅ ተቀብሎ በመያዝ ሁኔታውን የሚያጣሩ የራሱን ከፍተኛ ተወካዮች ከሲውዘርላንድ በኮንኮርድ ጀት ላከ። ወደ ሴራሊዮን ያመራ የነበረው ጀት ከማረፉ በፊት መስመሩን ወደ ላይቤሪያ እንዲያደርግ ሲታዘዝ በስፍራው የነበሩት የአለም አቀፍ ፖሊስ የጦር መርከብም ምክንያቱ ባልገባቸው ሁኔታ የያዙትን መርከብ ትተው ውደ ሌላ አቅጣጫ እንዲጓዙ ታዘዙ።

በጥቂት ሰዓታት ውስጥ ላይቤሪያ ባረፈው ጀት የመጡት ተወካዮች ቀሰስተኛ በሆነ ሄሊኮፕተር ቀሪውን መንገድ እንዲቀጥሉ ተደረገ።

ይህ ሁሉ የሆነው ግን አንድ የስልክ ጥሪ ፊላዴልፊያ ከሚገኘውና መሳሪያውን ከሸጠው የፋብሪካው ባለቤት ለሊዊስ በመድረሱ ነበር። ባለቤቱ የመርከቡን መያዝ እንደሰማ ሶስት ከፍተኛ አደጋዎች ከፊቱ እንደተደቀኑበት አወቀ። አንደኛው ፋብሪካው ወድያው የሚዘጋበት ሲሆን ፤ ሁለኛው ከፍተኛ የገንዘብ ቅጣት ይጠብቀዋል፤ ሶስተኛውና ከሁሉ የከፋው ግን በዓለም አቀፉ የጦር ፍርድ ቤት ቀርቦ ወንጀለኝነቱ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

በተያዘበት ማስረጃ ስለሚረጋገጥበት በእድሜ ልክ ፅኑ እስራት እንደሚያስቀጣው የግል ጠበቃው አስረዳውና ጉዳዩን መፍታት የሚችለው ለዊስ መሆኑን አያይዞ ገለፀለት። የጠበቃው ሀሳብ ሰራ በስልክ የተከናወነው ውይይት ከአስር ደቂቃ በላይ አልፈጀም።
ሉዊስ የመርከቡን መያዝ እንደሰማ እንደሁልጊዜው ሁሉ ከባለቤቶቹ ወይም ከሻጮቹ ወይም ከደላሎቹ በአንዱ ጥሪ እንደሚደርሰው ያውቅ ነበር። እንዳሰበውም ቻርልስ ከፊላዴልፊያ ደውሎ አገኘው።

በንግግራቸው መካከል ሉዊስ "ገንዘብ ምን ይሰራልኛል...? " ነበር ያለው
"ታዲያ ምንድነው ማግኘት የምትሻው...?"
"ሰው"
"ሰው?"
"አዎ ሰው ማግኘት ነው የምሻው።"
ቻርልስ በሀሊናው እብድ እያለው ነበር። ቀጠለ ሊዊስ ከጥቂት ዝምታ በኋላ "ቃልህን ስጠኝ አንድ ቀን የአንተን እርዳታ ፈልጌ ብመጣ ከጎኔ መሆንህን " ሉዊስ ይህን ማድረግ ግን የየእለቱ ተግብር ነበር።

"ቃል ገብቻለሁ።"
"መልካም ሁሉም ነገር መፍትሄ ያገኛል። "
ጎህ ከመቅደዱ በፊት በዛው መስመር አቋርጦ ወደ ጊኒ ያመራ የነበረ ሌላ መርከብ መስመሩን ከጦር መሳሪያ ጋር የተያዘው መርከብ ባለበት በኩል እንዲለውጥና ያኛው ቆሞ የነበረበት ስፍራ እንዲቆም ታዘዘ። በዛው ፍጥነት ባለ መሳሪያው መርከብ ወደ ሚፈለግበት የሴራሊዮን አቅጣጫ እንዲገሰግስ በሉዊስ እና በሱ የውለታ እና የጥቅም ሰንሰለት ውስጥ በተያዙ ሀላፊዎች ሁኔታው ተከናወነ።

በቀስስተኛዋ ሔሊኮፕተር ማለዳ ላይ ዘግይተው ወደ ስፍራው የደረሱት አጣሪ ተወካዮች ያቀረቡት ሪፖርት የሚናገረው የተያዘው መርከብ የጦር መሳሪያ የጫነ ሳይሆን የእርዳታ ስንዴና መድሀኒት መሆኑን የሚገልፅ ነበር።

ከዛ በኋላ ስራውን በተሳካ ሁኔታ ቀጥሎ ኑሮውን ለንደን ላይ ያደረገው ቻርልስ ባለፉት ሁለት አመታት ውስጥ ሶስት ተጨማሪ ግዙፍ የጦር መሳሪያ ማምረቻ ፋብሪካዎችን መክፈት የቻለና በስራው የበላይነቱን ከተቆጣጠሩት ሀያላን መካከል አንዱ ለመሆን ቻለ።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ይህ ከሆነ ጥቂት አመታት ቢያልፉም ሉዊስ ሊያገኘው እንደሚፈልግ ሲነግረው በደስታ ነበር ቀጠሮ የያዘለት::
ሉዊስ ለንደን ገብቶ ጊዜ አላባከነም:: ቀጥታ ወደ ቻርልስ ቢሮ አምርቶ አገኘው:: ከሞቀ የሰላምታ ልውውጥ በውኋላ «ምን ላድርግልህ ይሆነ?" በፈገግታ ጠየቀው::
"ያንን ያስመለጥኩልህን መሳሪያ ራሱን እፈልገዋለሁ....." አለው
"በደስታ ነዋ..... መንግስት ልትገለብጥ አሰብክ እንዴ..." እንደ ቀልድ ጠየቀው::

ለሰላሳ ደቂቃዎች ያህል ሉዊስ ነበር ተናጋሪው:: በኢትዮጵያ ላይ ሊያከናውን ስለነደፈው እቅዱ ተንትኖ ነገረው::
ቻርልስ በአድናቆት እያየው " አፍሪካ ውስጥ ጦርነት ሲኖር ነው የኛም ስራ በጥሩ ሁኔታ የሚከናወነው:: እቅድህን እደግፈዋለሁ:: እንዲሁም የአንተ ውለታ አለብኝ ይህ ትክክለኛ ወቅት ይመስለኛል ብድሩን ለመመለስ:: መሳሪያውን ለመጫን የምትፈልግበትን ቀን ብቻ አሳውቀኝ:: አስፈላጊው የሽፋን የሀሰት ሰነድም ሆነ ዝግጅቱን እኔ ራሴ እጨርስልሀለው:: ይህም አንድ ግዙፍ የእቃ መጫኛ መርከብ መያዝ የሚችለው ያህል ብዛት ያለው መሳሪያ ነው::"
"አመሰግናለሁ..." ብሎ ጨበጠውና ለመሄድ ተነሳ::

««««««« »»»»»»»»»»

በዛው እለት የከሰዓቱ ቀጣይ ቀጠሮው ያገኘው ፊሊፕ ዊልያም ከተባለ ሰው ጋር ነበር:: ይህ ሰው በእንግሊዝ ከፍተኛ የምክር ቤት አባልና ከጠቅላይ ሚሊስትሩ ዋና አማካሪዎች መካከል አንዱና ከፍተኛ ተሰሚነት ያለው "የዓለማችን የፖለቲካ ጠቢብ" የሚል ቅፅልን ያተረፈ ግለሰብ ሲሆን የእንግሊዝ ቅኝ ግዛት በነበረችው ናይጄሪያ ውስጥ በሶስት የተለያዩ ስፍራዎች ላይ ትልልቅ የነዳጅ ማውጫ የግል ጉድጓዶች አሉት::

ሉዊስ ለተባበሩት መንግስታት ይሰራ በነበረበት ወቅት ከዚህ ከፍተኛ ባለስልጣን ጋር ለተለያዩ አለም አቀፍ ጉዳዮች በተደጋጋሚ ተገናኝተው አብረው የሰሩ በመሆናቸው ቅርርባቸው ወደ ጓገኝነት እስከማዘንበል

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ደርሷል። ተደጋጋሚ የተዋቡ የበጋ የእረፍት ወቅቶችን አብረው ከማሳለፍ ጀምሮ በአንድ ጀልባ ላይ አብረው አሳ እስከማጥመድና ሴቶችን አብረው እስከማቅበጥ ደስታን ተጋርተዋል። ይህ አጋጣሚ ስለ ግል ህይወታቸው እና ቀጣይ ፍላጎታቸው ለመወያየትን እድል ሰጥቷቸው ነበር።

በዚህ ወቅት ላይ ፊሊፕ የነዳጅ ማውጫ ተቋማቶቹን ዘይቱ በሚገኝባቸው የዓለማችን ግዛቶች በሙሉ መክፈት እንደሚፈልግ የነገረው። ፊሊፕ በዚህ እቅዱ ውስጥ በተለይ አዳሲስና ድንግል የማውጫ ጉድጓዶችን እያሰሰ እንዳለና በዋናነት ወደፊት ሊሰራባቸው ከሚመርጣቸው ቦታዎች አንዱ በኢትዮጵያ ደቡብ ምስራቅ በኩል የሚገኘው የኦጋዴን ክልል አንዱ ሆኖ ዓይኑ ውስጥ የገባው።

ፊሊፕ ሲቋምጥለት ለኖረው ለዚህ ፍላጎቱ መሳካት የሚማርክ እቅድ በሉዊስ ረቆ የቀረበለት። የእቅዱ የመጀመሪያው ክፍል ግን ኦጋዴንን ከኢትዮጵያ አስገንጥሎ ማስወጣት ነበር። ይህም ሊፈፀም የሚችለው ሉዊስ ባረቀቀው እቅድ መሰረት የክልሉ ሰዎች ወደ ጦርነት እንዲያመሩ የሚያስፈልጋቸው የገንዘብና የጦር መሳሪያ የእርዳታ ድጋፍ መስጠት የሚል ነበር።

ፊሊፕም ሆነ ማንም እርዳታውን ሰጪ አካል ለጥንቃቄ ሲባል ማንነቱ በፍፁም የማይገለፅ ሲሆን እርዳታው ከራሱ ከፊሊፕም ይምጣ ከመንግስት ካዝና "ለሰላማዊ ነፃነት ድጋፍ" በሚል ሽፋን የሚከናወን ነው ብሎ አብራራለት። ሉዊስ አምንታውን ካሰበው ሰዓት ባነሰ ጊዜ ውስጥ አገኘ።
ፊሊፕ ከቢሮው ሊሸኘው ሲነሳ "ይህንን ለመነጋገር ያንን ሁሉ ርቀት መምጣት አያስፈልግህም ነበር እኮ በስልክ መጨረስ ስንችል... "

"ይልቅ እራት ብጋብዝህስ?"
"ተቀድመሀል ዛሬ።"
ተጨባብጠው ተለያዩ።

ከዛ እንደወጣ በቀጣይነት ለንደን ላይ ምን ማከናወን እንደቀረው አሰበና ዋናዎቹ ማለቃቸውን አረጋግጦ በማለዳው በረራ ወደ ሲውዲን ሊጓዝ ቀጠሮውን አስታወሰ። ከዛም ሌላ አገር..... ሌላ ተመሳሳይ ውይይቶች..... በብዛት እንደሚጠብቁት አሰበ። በእርግጠኝነት ሁሉንም

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

አሳምኖ በርካታ ቢልየን ዶላር እና መሳሪያ እንደሚያሰባስብ እርግጠኛ ነበር። በመላው አውሮፓና ሌሎች ሀገራት ሳይቀር ዘመኑን ሙሉ ሲተዋወቃቸውና ውለታን ሲሰራላቸው የኖሩት ሁሉ በዚህ ወቅት ላይ በየሀገራቸው በከፍተኛ ስልጣንና የሀብት ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ያውቃል።

ወድያውም ህሊናው "ምን አለ የዓለም ፕሬዝደንት በኖረ... " ሲል ተመኘና "እኔ ነበርኩ የሁሉንም ድጋፍ አግኝቼና በልጬ ይችን ፕላኔት እመራት የነበር" ሲል ልቡን አሞቀ።

  

የማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ምዕራፍ 9

“ሁልጊዜ ዒላማዎችሽን ድክመት ወዳለባቸው የባላንጣዎችሽ አቅጣጫዎች አነጣጥረሽ ምቺ፡፡ ውጤት ታገኝባቸዋለሽና”

ሰናይት የፒየር ንግግር ደጋግሞ አስተጋባባት፡፡ ሰላሳ ሶስት ቀን የፈጀ ዝግጅቷን አጠናቃ ስትሰናበተው ነበር የተናገረው፡፡ በቅብብሎሽ በረራ ከፓሪስ ሮም ከሮም የአዲስ አበባው አየር መንገድ ለማረፍ የተሳፈረችበት አውሮፕላን እያኮበኮበ ነበር፡፡
በውስጡ የተገጠመለት የድምፅ ማጉያ ተከፈተና እርጋታን የተላበሰ የሴት ድምፅ “እንደምን አደራችሁ መንገደኞቻችን? አውሮፕላኑ ለማረፍ እየተዘጋጀ ስለሆነ በቀቶዋችሁን እሰሩ.....” ንግግሯን ገታ አድርጋ ቀጠለች “አሁን ሰዓቱ በኢትዮጵያ አቆጣጠር ከማለዳው 12፡30 ነው፡፡” አለች፡፡

ሰናይት ንግግሯን ተከትላ ሰዓቷን ሞላችው፡፡ ማስታወሻዋንም አወጣችና “ዕለቱ አርብ የካቲት 2/1994” ብላ መዘገበችበት፡፡ የጋዜጣውን ህትመት ድንገት አቋርጣ ወደ ፈረንሳይ በሄደች በአስራ አንድ ወር ከሁለት ሳምንት በኋላ ተመልሳ መምጣቷ ነበር፡፡

ከአየር መንገዱ ስትወጣ የያዘችው እቃ ሁለት አነስተኛ የልብስ ሻንጣዎችን ብቻ ሲሆኑ ወዴት ማምራት እንዳለባት የወሰነችው ጉዞ ላይ እንዳለች ነበር፡፡ቢጫ ቅብ ካላቸው ታክሲዎች ውስጥ ወደ ቅርቡ አመራችና ሻንጣዎቹን የኋላው ወንበር ላይ በማድረግ ከፊት ገብታ “ሒልተን ሆቴል” አለችው፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

እንደደረሱ አስፈላጊውን ክፍያ ፈፅማ አንድ አልጋ ያለው የመኝታ ክፍል በመከራየት ቀኑን ተኝታ አሳለፈች፡፡አመሻሽ ላይ ገላዋን ታጥባ ቀለል ያለ ልብስ በመልበስ ከተማውን ለመቃኘት ወጣች፡፡

የያዘችው ታክሲ በካዛንቺስ፣ መገናኛ ደርሶ በመመለስ በቤተ መንግስት በኩል አድርጎ አራት ኪሎ ሲደርስ ወደ ራስ መኮንን አቅጣጫ በመመለስ ፒያሳ እንዳደረሳት "እዚህ ጋር አውርደኝ" ብላ ሂሳቡን በመስጠት በእግሯ ወደ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን አቅጣጫ በማምራት ሳታስበው በህፃንነት ወዳደገችበት መንደር ገባች፡፡ አካባቢው እንደዛው እንደድሮው ነበር፡፡ የነዋሪዎቹ ሁኔታ መንደሩ ነዋሪዎቹ ሳይቀሩ ምንም ሳይለወጡ እነደነበሩት ተቀምጠዋል፡፡

አንድ ካሰራም ሰው በአጠገቧ እየተሳደበ ሲያልፍ ሰማችው፡፡ ስድቡ የወቅቱ ገዢ ለሆነው የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ መንግስት ሲሆን "የማንም ዘረኛ ወያኔ መጫወቻ ሆነች ሀገሬ... ብሶት ነው የሚያስጮኸኝ እጮሀለው እሳደባለሁ..... ማን በአፌ ያገባዋል?! እነሱ እኛን ምን እያሉ ነው የሚሰድቡን እ...?! ቆሻሾች፣ ምንደኞች፣ እንክርዳዶች አይደል የሚሉን ማን ምን እንደሆነማ እማውቀዋለን..... እንደውም እጮሀለው ኡኡኡ.... ኡኡኡ....." እሷን አልፎ እየራቃት ሲሄድ ሌላ ሴተኛ አዳሪ አየና ቆም ብሎ "አንቺ የዘመነ ወያኔ አሳሳች ሸርሙጣ ድራሽሽ ይጥፋ! "

ሰናይት "ሸርሙጣ" የሚለውን ቃል ስትሰማ እልህ ተናነቃት፡፡ ወድያው በእናቷ አካል እንደ መሻቱ መጫወቱ ሳያንሰው ደብድቦ ጥርሷን አውልቆ እሱ ምንም ሳይሆን እሷን ለስድስት ወር ያሳሰራትን ሰካራም አስታወሳት፡፡ አንዱ ትውስታ ሌላውን እየጎተተ ይዟት ከዛ በውሃላ የነበረው ሁኔታ ላይ ወስዶ አስቀመጣት...

«««««« »»»»»»»

ትዝ ይላታል እናቷ ከእስር ስትፈታ ምን ያህል ከስታ ይብስ ተጎሳቁላ እንደነበር፡፡ ሁለቱ የፊት ጥርሷ መነቀል ደግሞ የፊቷን ቅርፅ በመጥፎ ሁኔታ አበላሽው፡፡ ድህነቱ ከፋ፡፡ የሚቀመስ የሚላስ ጠፋ፡፡ ከጎረቤቶቿ በመከራ ተበድራ ባገኘችው ገንዘብ የካቲካላውን ስራ ለመቀጠል ብትሞክርም ፈቅ አልል አለ፡፡ በፊት በሚያውቃት በአንድ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

የሰፈሩ ደላላ አማካኝነት ስራ ፈልጋ በተመላላሽ የቤት ሰራተኛነት የኢትዮጵያ ራዲዮ ድርጅት ጀርባ በሚገኘው ሰፈር ውስጥ ለአንድ ግለሰብ ተቀጠረች።

ይህ ሲሆን ሰናይት ቤት በመዋል ካቲካላውን በመሸጥ እናቷን በስራ ማገዝ ጀምራ ነበር። ሁለት ወራቶች እንዳለፉ እናቷ ጥቂት በተሻለ ክፍያ ሊሴ ገ/ማርያም ት/ቤት የምታስተምር አንዲት ፈረንሳዊ ሴት ቤት ስራ ለወጠች። ጥቂት ወራት እንዳለፉ እናቷ መታመም ስለጀመረች ሰናይት አልፎ አልፎ እየሄደች እናቷን በስራ ማገዝ ጀመረች። አሰሪያቸው ስታያቸው እጅግ ታዝንላቸው ነበር። ሰናይት ትምህርቷን ማቋረጧን እንዳወቀች ከሚቀጥለው ዓመት ጀምሮ እየከፈለችላት ልታስተምራት ቃል ገባችላት።

ይህን በተነጋገሩ ከጥቂት ሳምንት በውሃላ ሌላ ያልታሰበ ነገር ተከሰተ..... ሰናይት የምትተኛበት መደብ ላይ እንደተጋደመች ቀና ማለት እንኳ አቅቷት ከዓይኗ መንታ የእንባ ዘለላዎች እየረገፉ እናቷ ስራ ውላ ገባች። ምን እንደሆነች ለማወቅ አፍታም አልፈጀባት።
"ውይ.... ልጄ... ውይ ልጄ..... ጉድ አደረጉሽ..... ጉድ ሆንሽ..... ምናለ ምንአለ እኔስ በሞትኩት..... ምናለ አምላኬ ብትገድለኝስ እኔን..... ምን አለ! "

"እማዬ..... እራሱ ነው..."
"ማነው እሱ...! ማነው...!" እናቷ እንደ ቀውስ አደረጋት
"እኔ እንጃ ጠላ አለ ብሎ ገብቶ ነው እማዬ ሙች..... እራሱ ነው..... በግድ ነው..... አፌን እንዳልጮህ ይዞኝ ነው..... አላውቀውም"
"አውቃለሁ ልጄ..... አውቃለሁ..... እኔን ለኔ ያድገው..... ምነው አምላኬ ምነው መከራዬን አበዛኸው..... ልጄን ምኑን ታውቅና ይህን ፈረድክባት..... ውይ..... ውይ..... " በጭኗ መካከልና በቀሚሳ ላይ ደርቆ የሚታየውን ደም እያየች ምርር ብላ አብራት አለቀሰች።

ወድያውም "ተነሽ... ተነሽ..." ብላ አዝላት ወደ ፈረንሳዊቷ አሰሪዋ ቤት ይዛት ሄደችና እንዳገኘቻት ፍርዱንና በቀሉን እሷ ትመልስላት ይመስል ስቅስቅ ብለው አለቀሱባት። ሴትየዋ ይዛቸው ወደ ፖሊስ ጣቢያ አመራች። ጉዳዩ በማይታወቅ ሰው ተገዶ መደፈርን የሚገልፅ ከአንድ ገፅ ወረቀት ላይ ከመፃፍ የዘለለ ምንም ሌላ ፋይዳ ያላስገኘላቸው ሆኖ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ተጠናቀቀ። እዛ እንደጨረሱ ወደ ሆስፒታል አመሩና ሰናይት የህክምና እርዳታ ወስዳ እንደጨረሰች በሁኔታው በጣም ያዘነችው ፈረንሳዊቷ እሷ ቤት አርፋ እንድታገግም እድል ሰጠቻት።

ሰናይት የወንድ ጥላቻዋ ስር እየሰደደ ሄደ። ወንዶች ለሷና ለናቷ የማይሸር ነቀርሳ መሆናቸውን አመነች። ልቧ ለወንድ ተዘጋ። በነሱ ላይ ለማድረስ የምትፈልገው በቀል ምን ያህል የከፋ እንደሆነ ራሷ ጭምር መረዳት እስኪሳናት ድረስ ከበደ።

ከደረሰባት የህሊና ስብራት ሳታገግም ሁለት ወራት አለፉ። ፈረንሳዊቷ በተለያየ መንገድ ስነ-ልቦናዊ እርዳታ ልታደርግላት ብትሞክርም ሰናይት ግን ጥቂት እንኳ መረጋጋት አልቻለችም። ገለልተኛና ጭምት ድንጉጥ ሆነች። በመካከሉ ፈረንሳዊቷ በግል ቤተሰባዊ ምክንያት ተገዳ ወደ አገሯ መመለስ እንደፈለገች ነገረቻቸውና ይዛት ለመሄድ ሰናይት ፈቃደኛ መሆኗን ጠየቀቻት።
ሰናይት ግን የትም ቢሆን ለሷ ያው አይነት መከራ እንደሚጠብቃት ነበር የሚሰማትና መልስ አልሰጠቻትም።

ፈረንሳዊቷ " እዛ አስተምርሻለሁ። ከኔ ጋር ትኖሪያለሽ። ከዛም ደግሞ ታድጊና ትልቅ ሰው ሆነሽ የራስሽ ህይወት ይኖርሻል። ትምህርት መማር አለብሽ። በዚህ አደገኛ ምድር ላይ ስትኖሪ ራስሽን ከጥቃት ለመከላከልም ሆነ መልሰሽ ለማጥቃት እውቅት ያስፈልግሻል። እውቅት የሁሉ ነገር መሪ መሳሪያ ነው።።» አለቻት። ሰናይት ግን ምንም መልስ አልሰጠቻትም።

ይሄኔ እናቷ ጣልቃ ገብታ "ትሄዳለች እሽ... ትላለች"
አስራ ሶስት ዓመቷን ልታከብር ጥቂት የቀራት ሰናይት አያቷ ለናቷ ያወረሷትን ፎቶና አንድ የናቷን ፎት ብቻ ይዛ ወደ ፈረንሳይ አመራች።

««««««« »»»»»»»

ከምሽቱ 4፡25 ሲል የተኮናተረችው ታክሲ አምጥቶ ሒልተን የሆቴሉ አደረሳት። "አመሰግናለሁ" በማለት ወረደችና ወደ ውስጥ መግባት ስትጀምር በህሊናዋ 'ምንም የሚናፍቅና የሚያዘናጋ ነገር

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

የለም፡፡ በቀጥታ ስራዬን መጀመር አለብኝ፡፡ ' እያለች ነበር ለራሷ፡፡

እንደገባች የለሊት ልብሷን ለውጣ አንደኛውን ሻንጣ እየጐተተች አመቺው ወንበር ጋር ስትደርስ ተቀመጠች፡፡ የሻንጣውን ኪሶች እየከፋፈተች በውስጡ የነበሩትን ወረቀቶች በማውጣት መሬት ላይ ዘረገፈቻቸው፡፡ እያንዳንዱን በማንሳት የአሰፈላጊ ሰዎችን ስምና አድራሻ የያዘውን ወረቀት በመምረጥ 'እነዚህ ሰዎች..... በቀጥታ ወደ ውጤት የሚያንደረድሩኝ ልስልስ ጫማዎቼ.....'

ለሶስት ዓመታት ጋዜጣ አሳታሚ ሆና በቆየችባቸው ወቅቶች ላይ የመንግስት ሚስጥራዊ መረጃዎች እያወጡ የሚቸበችቡላት ከፍተኛ ባለስልጣናት ፣ ህጋዊ እውቅና ያላቸውና ከእውቅናቸው የታደገዱ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች፣ በህቡእ የሚንቀሳቀሱ ድብቅ የመንግስት ተቃዋሚዎች ፣ በየክልሎቻቸው ላይ ጥሩ ተሰሚነት የነበራቸው ግለሰቦችንና የጐሳ ተጠሪዎችን ስም የሚጨምሩ ነበሩ፡፡

  

ያልተሸጠ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ምዕራፍ 10

'ሊሳት በማይችል አደገኛ ሁኔታ ዒላማ ውስጥ የገባ ብሔር ኦሮሞ' ስትል አሰበች ሰናይት ። 'አሁን ገዢ ሆኖ ላለው መንግስት ጥሩ መጠቀሚያ ሆኗል። ብልጥ የሆነ ሁሉ ደግሞ ገና ሲጠቀምበት ይኖራል..... እንደዚህ የሆነው ግን ቀጥተኛና አመኔታን የሚያበዛ ቅን ብሔር በመሆኑ ይሆን?' የማይመለስ ጥያቄን ለራሷ እየሰጠች የቀጣዩን ቀን ስራ ለመፈፀም ዝግጅቷን አጠናቀቀች።

ጠዋት እንደተነሳች ለሰላሳ ደቂቃ በዮጋ እስፖርት አካሏን ስታፍታታ ቆይታ ገላዋን ታጠበችና ቀለል ያለ ልብስ ለብሳ ወጣች። ከምትጠቀምባቸው ዋነኛ ሰዎች መሀከል አንዱን ዛሬ ለማግኘት በወሰነችው መሰረት በህሊናዋ ከሸመደደቻቸው ቁጥሮች መሀከል የአንዱን መደወል ጀመረች።

"አቤት?" በሴት ድምፅ ምላሽ መጣላት።

"የአቶ ሂርዳ ቤት ነው?"

"አዎ"

"ቢያገናኙኝ?"

"እሺ....."

ከጥቂት ጥበቃ በኋላ ጮርነን ያለ ድምፅ በመነጋገሪያው ውስጥ "ሀሎ"

"አቶ ሂርዳ እንደምን ከርመሀል?"

"እግዚያብሔር ይመስገን..... ማን ልበል?"

"ሰናይት ነኝ"

"ሰናይት?...ሰናይት?"

"ሰናይት ማስታወቂያና ህትመት ባለቤት የነ....."

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

አቋረጣትና “እዎ.....! አስታወስኩ የኔ እመቤት ይቅርታ .....እንደምን ነሽ !?”
“ደህና ነኝ”
“ዛሬ በምን አስታውሰሽኝ ደወልሽ?”
“አንተኮ የምትረሳ ሰው አይደለህም”
“የጋዜጣውን ህትመት ስራ ለምን አቆምሽ?”
“የሚያሰራ ነፃ ህግ በኢትዮጵያ ባለመኖሩ”
“ታዲያ ማቆምሽን እንኳን ሳትነግሪን እንዲሁ ብር ብለሽ ትጠፊያለሽ?”
“በጣም ተበሳጭቼ ስለነበረ በስሜታዊነት ነው አቁሜ የጠፋሁት”
“እኔማ አፍነው ገለውሽ ይሆን..... ወይም የማይታወቅ ስፍራ አግዘው አስረውሽ..... እያልኩ ስንቱን ሳስብ ነበር ይሄ መንግስት እንደሆን በሚስጥሮቹ ሲመጡበት ሰውን እንደ ክርስቶስ በአደባባይ ከመስቀል አይመለስ”
“ያው ዛቻውና ማስፈራራቱ ሲበዛብኝ ያልከው ሳይከተል ህትመቱን አቁሜ ሄድኩላቸው”
“በዲሞክራሲ ስም የሚነግድ ሌባ መንግስት ማለት ወያኔ ነው!” አለ ሂርጳ በታመቀ የእልህ ድምፅ ቀጠለ “ታዲያ ተገናኝተን ለምን አንጫወትም?”
ሰናይት ጥያቄው ከራሱ በመምጣቱ ፈገግ እያለች “ደስ ይለኛል መቼ እንገናኝ?”
“እኔ እረፍት ላይ ነኝ፡፡ አንቺ ነፃ መሆን በምትችልበት ጊዜ ሁሉ”
“እንግዲህ ከሰዓት ይሁና..... እንደውም ምሳ ብጋብዝሽስ?”
“ጥሩ” አለች ፡፡

በፊት ይገናኙበት የነበረና በአምባሳደር ፊልም ቤት አካባቢ በሚገኝ አንድ ምግብ ቤት 6፡30 ተቀጣጠሩ፡፡

ሰናይት በዚህ ዕለት ሌላ ተጨማሪ ቀጠሮ መያዝ እንደሌለባት እና በቀጣዩ ከማን ጋር እንደምትገናኝ እያሰበች ይህ ነው የሚባል ነገር ሳታደርግ ቀሪውን ሰዓት አሳለፈችና ቀጠሮው ሲደርስ ወደዛው አመራች፡፡ ሂርጳ አስር ደቂቃ ዘግይቶ ቦታው ደረሰ፡፡ ሰናይት እንዳየችው የልቧ ምት እየጨመረ ‘ስራው ተጀመረ’ አለች ለራሷ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

እንዳገኛት በጥልቅ ስሜት ሰላምታ ሰጣት “ምነው የተስማማሽ አትመስይም አሞሽ ነበር?” ሂርጳ አይኑን ተክሎባት እየተቀመጠ ጠየቃት፡፡
“አይ ስፖርት አብዝቼ ነው፡፡ አላመመኝም...”
“ፀጉርሽንም ተቆርጠሽው ሌላ ሴት መስለሻል ” ሁለቱም ሳቁ፡፡
“ይልቅ አንተ የተስማማህ ትመስላለህ” አለችው ሜትር ከዘጠና በሚሆነው ቁመናው ላይ ድድር ግዙፍ ሰውነቱን እያየችው፡፡
ሂርጳ ፈገግ ሲል ተስተከክለው የተሰደሩት ውብ ጥርሶቹ ታዩ፡፡ መተኛት የሚከጅለው ሉጫ ፀጉሩና ሰልካካ የሆነው ረዥም አፍንጫው ወንዳ ወንድነትን አጉልቶ ካላበሰው ቁመናው ጋር ተደማምሮ የሰዎች እይታን በቀላሉ ይስባል ለሰናይት ልቦና ግን ለበቀል ከምትፈልጋቸው ከሌላው ወንድ ምንም የተለየ ነገር አልነበረውም፡፡
“ምን ይስማማኛል ተፈጥሮዬ ሆኖ እንጂ” በማለት አስተባበለ ሂርጳ፡፡
ሰናይት አጋጣሚዎችን ማለፍ እንደሌለባት ሀሳብ በቅፅበት ውልብ አለላትና “ለነገሩ አንተን የሚስማማህ የምትናፍቀው የኦሮሚያን ነፃ መውጣት ስታየው ብቻ ነው”
“አሁን እውነት ተናገርሽ!”
“አይዞህ በቅርብ ቀን እውን ይሆናል”
“አይ..... ተስፋ ብቻ ሆነን ቀረን” አለ በቁጭት፡፡
“እኔንኮ የሚገርመኝ አንቀፅ 39 ላይ የሰፈረው የመገንጠል መብት ለኤርትራ ሲባል ብቻ ነበር በኢትዮጵያ ህግ ላይ እንዲካተት የተፈለገው?” ሰናይት የሂርጳን ቁስለት ታውቅ ነበርና የባሰ እንዲያመረቅዝበት ግሽለጣውን በጥበብ ጀመረች፡፡
“ታዲያስ!” ጉላ ባለ ድምፅ ተናገረ፡፡ ቀጠለ “.....ለነገሩ ኢትዮጵያ ላይ የሚነሱት ገዢዎች እኛ የነፃነትን ጥያቄ ስናነሳ አይወዱም፡፡ እኛ ደግሞ ከኢትዮጵያ ጋር አንድ መሆን አንፈልግም፡፡ እኛ ኢትዮጵያዊ አይደለንም.....፡” አለ በበቀል ስሜት ተውጠ፡፡
ሰናይትም ቀበል አደረገችና “እዎ፡፡”
“ይልቅ ምሳውን ለምን ቤት አልጋብዝሽም?” ተስማማች፡፡
ወጥተው በፒያሳ ታክሲ ተሳፈሩ፡፡ ከዛም ወደ አስኮ የሚያመራውን መንገድ ይዘው የጳውሎስን ሆስፒታል ጥቂት አለፈ እንዳሉ ወረዱ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

አስፓልቱን ተሻግረው ወደ ግራ ታጠፉና ለአምስት ደቂቃ ያህል እንደተጓዙ የብረት በር ያለው በግምብ የተሰራ ጊቢ ጋር ደርሰው በማንኳኳት አስከፍተው ገቡ፡፡

ብዙም ሰፋት የሌላት ጊቢ ውስጥ መሀከል ቦታ ላይ በሰንቀሌ ደንጊያ የተሰራች አነስተኛ ቪላ ቤት ትገኛለች፡፡
ቀሪው ቦታ ሳር በቅሎበታል፡፡ ሁለት በጐች ጥግ ላይ ታስረው ይታያሉ፡፡ በአንድ አንድ ዓመት የእድሜ ልዩነት የሚበላለጡት አራት ህፃናት የአባታቸውን መምጣት እንዳዩ ተሯሩጠው በመምጣት እግሮቹ ላይ ተጠመጠሙ፡፡ ሂርጳ አራቱንም ግንባራቸው ላይ ሳማቸው፡፡ ወደ ሰናይት ዞሮ “ይሄ የመጀመሪያው ልጄ ነው ስምንት ዓመቱ ሲሆን ስሙ ኡርጌሳ ይሄኛው ደግሞ ዲባባ..... ሶስተኛዋ ሐዊ ትባላለች ይችኛዋም መገርቱ” ብሎ አስተዋወቃትና ወደ ውስጥ ገቡ፡፡ የቤቱ የውስጥ ገፅታ ባህላዊነትን የተላበሰ እንዲሆን ባደረገው የባህል እቃዎች ተውቧል፡፡

ሂርጳ ተወልዶ ያደገው ነቀምት ሲሆን የደርግን ስርዓት ለመጣል “ኦሮሞ ነፃነት ግምባር” የተባለው ፓርቲ ውስጥ በፈቃደኝነት ገብቶ ለአምስት ዓመታት ተዋግቷል፡፡ የወያኔ ጦር በ1983 ዓ.ም አሸንፎ አዲስ አበባን ሲቆጣጠር አብሮ በመግባት ከዛ በኋላ ያለውን ኑሮ እዚሁ መሰረተ፡፡

በጦር ግምባር እያለ በኦነግ ውስጥ ቁልፍ ቦታ ላይ ለመቀመጥ የቻለ በመሆኑም ፓርቲው ከወያኔ ጋር አለመግባባትን ፈጥሮ ቢሮውን በመዝጋት አዲስ አበባን ሲለቅ ሂርጳ ግን ተደብቆ ለሶስት ዓመታት ቆየና አሁን የሚኖርበትን ቤት ገዝቶ ተቀመጠ፡፡
ትውውቃቸው ካለ ምንም ስህተትና የቅሬታ ሀሳብ ለሶስት ተከታታይ ዓመት የጋዚጣው ህትመት ተጀምሮ እስከተቋረጠበት ጊዜ ድረስ አብሮ ለመዝለቅ የቻለ በመሆኑም ሂርጳ በሰናይት ያለው የመተማመን መንፈስ በአንድ ፓርቲ ውስጥ ለአንድ ዓላማ የሚታገሉ ሰዎች የሚኖራቸውን ያህል ለመሆን ችሏል፡፡
“ለመሆኑ አነግ አሁን በምን እንቅስቃሴ ላይ ይገኛል?” ጠየቀችው
“ተይኝ ባክሽ .....መሪዎቹ ሰራዊቱን በየ በረሀና ጫካ በትነው ጠፍተዋል፡፡ የቀረው አባል በየእስር ቤት ታጉሮዋለ፡፡”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“አልገባኝም” አለች በአስተውሎት እያየቸው፡፡
“እና ፓርቲው ተበተነ ነው የምትለኝ?” ያዘነ በሚመስል ቅላፄ ተናገረች፡፡
“አማራጭ የሌለው አባል የተሟጠጠችውን የተስፋ ዲስኩራቸውን እየላሰ አሁንም በመጠባበቅ ላይ ነው፡፡”
“አንተስ?”
“ከነሱ ጋር ያለኝን ግንኙነት በሙሉ አቁሜያለሁ”
ሽምቅቅ አለች፡፡ ሂርጳ ግን አላስተዋላትም፡፡ ‘ትልቁ የእቅዳችን ማስፈፀሚያ ይሆነኛል ያልኩት ሰው ተራ ሆኖ ተገኘ፡፡’ አለች በምናቧ፡፡
“አሁን ታዲያ ምን እየሰራህ ነው?” አፏ ላይ ስለመጣለት እንጂ የሚጠቅም መልስ ይኖረዋል ብላ ተስፋ አላደረገችም፡፡
“ትልቅ ስራ ጀምሬያለሁ.....”በረዥሙ ተነፈሰ፡፡
“የሲቪል ስራ?”
“አይደለም.....” ቀጥሎ ያለውን እውነታ ላለመናገር አመነታ፡፡ መልሶም እሷን በመጠራጠሩ በራሱ እያፈረ ባለፉት ዓመታት ሙሉ ፓርቲውን ሀሳብና መረጃዎች እያተመች ለህዝቡ ስታሰራጭለት መቆየቷን አስታውሶ ከጥርጣሬው መለስ እያለ..... ምናልባት ዛሬም ትልቅ ፋይዳ ያለው ነገርን ልታመጣ ብትችልስ ብሎ እያሰበ ቆየ፡፡

ሰናይት ስሜቱን ስለተረዳችው “ባትነግረኝም ችግር የለውም፡፡ አንዳንዴ እኮ ለሰዎች የማይገለፁ የግል ሚስጥሮች አይጠፉም” ብላ ፈገግ አለች፡፡
“እንደዛ ማሰቤ አይደለም..... ልነግርሽ እችላለሁ”
ሰናይት ብዙም ጉዳይ እንዳልሰጠችው ለመምሰል ዘና አለች፡፡
ቀጠለ ሂርጳ “ተመሳሳይ ፍላጐት ያለን ሰዎች ተሰባስበን ኦሮሚያን ነፃ የሚያወጣ ሌላ ፓርቲ መስርተናል፡፡”
“መንግስት እውቅና ሰጥቶታል?”
“ዓላማችን እውቅናን የማያሰጠን መሆኑን ስለምናውቅ እኛም አልጠየቅንም”
ሰናይት ሳታሳበው ወደፊት ጠጋ ብላ ተቀመጠችና “በጣም ጥሩ!” ጐላ ባለ ድምፅ ተናገረች፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ሂርጳ ድጋፍ በማግኘቱ ደስ እያለው "ስሙ ኦሮሞ አርበኞች ንቅናቄ ይባላል። በምህፃረ ቃል ኦ.አ.ን. ነው።"
"ምን ያህል ጊዜ ሆናችሁ?"
"አንቺ ስራሽን እንዳቆምሽ አካባቢ..... አስር ወር"
"ድጋፍ የሚያደርግላችሁ አግኝታችኋል?"
"እስካሁን አላገኘንም። እዚሁ አባሉ በሚያሰባስበው መዋጮ ነው እንቅስቃሴ የጀመርነው"
"ወደ ህዝቡስ ምን ያህል ለመዝለቅ ችላችኋል?"
"የሚገርምሽ በየ ክልላችን ውስጥ ከጠበቅነው በላይ ብዛት ያላቸው በሺህ የሚቆጠሩ የኦሮሞ ልጆች በፍላጐት ተመዝግበዋል" አለ ሂርጳ አድናቆቱን በሚገልፅ ስሜት እጆቹንም እየተጠቀመባቸው።

"ከየት ከየት ነው የተመለመላችሁት?"
"ሁሉንም የኦሮሚያ ክልሎች ያማከለ ነው። ለምሳሌ እኔ ከወለጋ አንደኛው ከአርሲ፣ ሌላኛው ከጅማ ፣ ከሐረር ከባሌ..... ሲሆን ከነዚህ ሁሉ ቦታዎች ተከታይ ሰራዊት አግኝተናል።
"እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ብዘ ስራ ሰርተህ ነው የጠበቀኝ" አለችው። እሱም አድናቆቱን መደበቅ አቅቶት።
ቀጠለ ሂርጳ "በዛ ላይ ብዙዎቹ አባሎቻችን ቁልፍ በሆኑ የመንግስት መስራቤቶች ውስጥ እንኳ ሳይቀር የሰረጉ ናቸው።"
ሰናይት እዚህ ቦታ ላይ የሂርጳን ህሊና ውስጥ ትንሽ ልብን የሚያንጠለጥል ብልጠት መጠቀም እንዳለባት ውልብ አላትና "ያልከውን ልታረጋግጥልኝ ከቻልክ ከፍተኛ ድጋፍ የሚያደርግላችሁን አካል ላገኝላችሁ ቃል እገባለሁ።"
"እውነትሽን ነው ልትረጂን ትችያለሽ!?" በተደባለቀ ስሜት ጠየቃት።

"በትክክል። ታውቀኛለህ ደግሞ ያለማቋረጥ ምን ያህል አንተንና ፓርቲያችሁን ስረዳላችሁ እደኖርኩ።"
የሰናይት ንግግር ሂላማው ላይ እንዳረፈ የሂርጳ ፊት መሰከረ። ተሸናፊ ሆኗል። እየተቁነጠነጠ በየትኛው አቅጣጫ ቢጓዝ ይበልጥ አሳማኝ የሆነ ማስረጃን ሊያቀርብላት እንደሚችል ሲያስብ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ቆየና "መንግስት እንደ ዓይኑ የሚጠብቀውና ከህዝብ ጋር የሚገናኝበት ትልቁ መሳሪያው ምን ይመስልሻል?"
"መገናኛ ብዙሀን?"
"ትክክል መንግስት አለኝ የሚለው ትልቁ መጠቀሚያውስ?"
"የሬዲዮና ቴሌቪዥን ጣቢያዎቹ ይመስሉኛል"
"ከሬዲዮ ይበልጥ ግን ቴሌቪዥን የሚታይ በመሆኑ አሳማኝነቱ የዛኑ ያህል የሚጨምር ነው።።"
"አዎ" አለ አለች።።
"ጥሩ ..... እኔ ግን በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ላይ ማዘዝ እችላለሁ"
አንድ ግለሰብ ያውም በፀጥታ ሀይሎች ቢደረስበት ሊያዝና ሊገደል የሚችል .....ይህንንም ተቋቋቁሞ ሌላ ፓርቲ የመሰረተ ሰው ይህን በሚያህል የመንግስት መስራቤት ላይ ትዕዛዝ መስጠት የሚችል.....
"እንዴት አርገህ?" በጥርጣሬ ተለሳልሳ ጠየቀችው።።
"ዛሬ ማታ በቴሌቪዥን የኦሮምኛ ስርጭት ክፍለ ጊዜ ላይ የምፈልገውን ዝግጅት እንዲተላለፍ ማስደረግ እችላለሁ.....ይህን ማለቴም አዲስ የተቋቋመ የኦሮሞ አርበኞች ንቅናቄ ፓርቲ ምን ያህል አቅም እንዳለው እንድትረጂልኝ ነው።።"

"ይገባኛል.....ግን ምን ዝግጅት እንዲቀርብ ማስደረግ ትችላለህ?"
"እ.....ነፍጠኞቹ ነገስታቶች በኦሮሞ ህዝብ ላይ የፈፀሙትን ግፍና ጭፍጨፋ የሚያሳይን ታሪክ ላይ ተንተርሶ በኛ ሰዎች እንዲሰራ የተደረገ ነው።። እሱ ይተላለፍ?"
"በእርግጥ የዚህን ያህል አቅም ኖሮህ?"
ሂርጳ መልስ አልሰጣትም።። ተነስቶ ወደ ስልኩ ተራመደና መነጋገሪያውን በማንሳት ቁጥሮችን ተጫነ።። መስመሩ ሲለቀቅለት "ሀሎ...." ብሎ በኦሮምኛ ቋንቋ ትዕዛዝ መሰል ሀሳብ ሲያስተላልፍ አየችው
ጨርሶ ወደ ቦታው ሲመለስም "ከዛሬ ጀምሮ በተከታታይ ለሶስት ቀናት ይህ ዝግጅት ለሰላሳ ደቂቃዎች ስለሚሰራጭ ተመልከችው።። ያኔ አምነሽኝ ትመጣለሽ።።"አለ በሙሉ የመተማመን መንፈስ።። በእርግጥ ቀላል ሰው ያለመሆኑን ታውቃለች።። በርካታ የአነግ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

አባሎች በህገወጥ መንገድ ከኢትዮጵያ እንዲወጡ ሁኔታዎችን አመቻችቶላቸዋል፡፡ በድብቅ የመሳሪያ ዝውውሮች ላይም የሱ ንድፍ ሚናቸው የሚናቅ አልነበረም፡፡ የመንግስት ምስጢሮችንም በራሱ የብልጠት አቅጣጫ እያነፈነፈ ለፓርቲው የሚያቀብል ሰላይም ነበር፡፡ ከፓርቲው ለህዝቡ እንዲደርሱ የሚፈለጉትንም ዜናዎች በየ ጋዜጦች ላይ እንዲታተሙ ያስደርግ ነበር፡፡ ከገጠር ክልል የተላከ መስሎ በኦ.ህ.ዲ.ድ. ስም በርካታ የመንግስት ዝግ ስብሰባዎችን ለመከታተል ችሏል፡፡ ከሁለት የአደገኛ የግድያ ሙከራዎች ራሱን ነፃ አውጥቷል፡፡ 'እስስት ዓይነት ሰው ነው፡፡ ራሱን ከፈለገው ዓይነት ነገሮች ጋር ሁሉ ማመሳሰልን ተክኖበታል' አለች ፡፡ ቀጠለ 'አሁንም ቢሆን ያለውን ለማስፈፀም አቅም አይኖረውም ማለት ሞኝነት ነው፡፡' ስትል አሰበች፡፡

"አንቺስ ለፓርቲያችን ምን ልታግዢን አሰብሽ...?"
ሂርጳ ፈገግ አለና "ጥያቄውን ያቀረብኩልሽ እንድትጨነቂ አይደለም፡፡ ከቻልሽ ደግሞ እኛን ከመርዳት የማታፈገፍጊ ሰው መሆንሽን የቀድሞ ስራዎችሽን ማስታወስ በቂ ነው" አለና ".....ምሳው ተረሳኮ" ብሎ በመጣራት እንዲያቀርቡላቸው አዘዘ፡፡

ገበታ ሲቀርብ ትኩረታቸውን ወደዛ መለሱ፡፡ ሰናይት እስከ ዘጠኝ ሰዓት እሱ ጋር ቆይታ ወደ ሆቴሏ ስትመለስ የተነጋገሩባቸው ነጥቦች በጠቅላላ ወረቀት ላይ አሰፈረች፡፡

አንድ ሰዓት ተኩል ላይ የኦሮምኛ ስርጭት መተላለፉ ሲጀምረ ቴሌቪዥኑን ከፍታ ማየት ቀጠለች፡፡





ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ምዕራፍ 11

በዕለቱ የአንድ ሰዓት ቆይታ የነበረው የኦሮምኛ ስርጭት ግማሹን ክፍል ሙሉ "የነፍጠኛ አገዛዝ በኦሮሚያ ምድር ላይ" የሚል ርዕሳዊ ትርጓሜ ያለውን ዝግጅት ማስተላለፍ ሲጀምር ቀድሞ በቴሌቪዥኑ መስታወት ላይ ብቅ ያሉት የአፄ ምኒልክ ጉርድ ምስል ነበር።።

አዘጋጁ ንግግሩን ሲጀምር የንጉሱን አፄአዊ ማዕረግ ገፎ እንደ አንድ ተራ ግለሰብ በስማቸው እየጠራቸውና በአንተአዊ እሳቦት እያቀለላቸው በሀሰት ሆን ተብሎ የተቀነበባበረውን አተታ አተተ።። ከሳቸውም ቀጥሎ ወደ ራስ ጐበና ዳጩ..... ዘለለ።። እኛን ከኦሮሞ ህዝብ መሀከል የተገኙ ጀግና እንደ ከሀዲ ባንዳ አድርጐ ብዙ አወራባቸው።። እጅግ ቀስቃሽና ስሜታዊ ሊያደርጉ የሚችሉ ቃላቶችን መርጠ እየተጠቀመ በእጅ የተሳሉ መሆናቸው በግልፅ የሚያሳውቁ ስዕሎችን እያሳየ በወቅቱ የተነሱ እውነተኛ ፎቶዎች አስመስሎ ለማሳመን ጥረቱን ቀጠለ።።

በቴሌቪዥኑ መስታወት ላይ ከሚተላለፉት ስዕሎች መካከል አንዲት ሴት እርቃኗን ከዛፍ ጋር በሰንሰለት ታስራ ከላይዋ ሁለቱም ጡቶቿ ተቆርጦ ደሟ ሲንዠቀዠቅ የሚያሳይ ስዕል ታየ።። ገለፃው ቀጠለ ".....ተመልከት የኦሮሞ ህዝብ ሆይ ዘግናኝ አይደለም ታዲያ ..... እናትህን እህትህን ሚስትህን ነፍጠኛው እንዲህ ነበር በጭካኔ የቆራረጣቸው....."

ሌላ ስዕል ተተካ።። ወንድ ነው ራቁቱን እጆቹን ወደ ኋላ ተጠፍሮ መሬት ላይ ተቀምጧል።። እግሮቹ ወደ ግራና ቀኝ ተከፍተው የታሰሩ ሲሆን ብልቱ ከላዩ ተሰልቦ አካባቢው በደም

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

የተጨማለቀ መስሎ ይታያል፡፡ የአዘጋጁ ገለፃ ቀጠለ “..... ተመልከት የኦሮሞ ወንድ ሆይ..... ዘርህን አምክኖ ከተፈጠርክበት ምድርህ ላይ ሊያጠፋህ ይህንን ግፍ ሲፈፅምብህ የነበረው ነፍጠኛ ነው..... ህዝብ ሆይ በዚህ ሰዓት እየተነገረህ ካለው ይልቅ ያልተነገረህና የማይነገርህ እውነታ ይልቃል..... ቀጣዩን ክፍል በነገው ምሽት ይዘን እንቀርባለን” ብሎ የዕለቱን የግማሽ ሰዓት ዝግጅት ፈፀመ፡፡

በዛ ቅፅበት ይህን ዝግጅት ይከታተሉ የነበሩና ከሚያራምዱት ፖለቲካ በስተጀብርባ ለሚያገኙት የግል ጥቅም ሲሉ በተሳሳተ እሳቤ ተሰብኮ ያመናቸው አክራሪው የኦሮሞ ብሔርተኛ ቡድን የደበቀውን ቆንጨራና ሳንጃ በግብታዊነት አንስቶ እየሳለ፤ በየ ክልሉ ያለውም ተፈትቶ የተቀመጠ ጠመንጃውን በእልህና በሲቃ ተውጦ እየገጣጠመ፤ ነፍጠኛ የሚለውን የአማራን ዘር የመበቀያ ግዜውን አሁን እንዲያደርግለት ለ”ዋቃ”ው ፀሎቱን ማቅረብ ቀጠለ፡፡

ሰናይት የኦሮምኛ ቋንቋ የማትሰማ ቢሆንም ሲተላለፈ ከነበረው ምስል በመነሳት በስሜት ተውጣ ነበር የተከታተለችው ሂርጳ የነገራትንም በጠቅላላ ማስተግበር እንደቻለ አወቀች፡፡ የመንግስት አከርካሪ በሆነ መስራ ቤት ይህ ግለሰብ ሙሉ የስልጣን መብት እንዳለው አሳያት፡፡
ከተቀመጠችበት ተነስታ ወደ ስልኩ በማምራት ደወለችለት መስመሩን ያገኘችው ግን ከተደጋጋሚ ሙከራዎች በኋላ ነበር፡፡
“ሂርጳ ቀላል ሰው ያለመሆንህን ተረድቻለሁ”
“እንደምትደውይልኝ እርግጠኛ ነበርኩ... ተከታተልሽው ሁሉንም?”
“በጥንቃቄ ነዋ.....”
“የአቅም ማነስ ነው እንጂ ከዚህ በላይ ስንት ነገር ሰርቼ ባሳየሁሽ ነበር.....” አለ ሂርጳ
“አይዞህ የሆነ መላ መፍጠር እያቅተንም ብዬሀለው እኮ”
“እናያለን እንግዲህ.....”
“ስልክህ ተይዞ ነበር መሰለኝ በድካም ነው ያገኘሁት”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“አዎ..... ዝግጅቱ መተላለፉ እንደጀመረ ብዙ የኦሮሞ ልጆች ከየ ክፍለ ሀገሩ እየደወሉልኝ በአካባቢያቸው ያሉትን የነፍጠኛ ዘሮችን እንጨፍጭፍ እያሉ ሲጠይቁኝ ነበር።”
“እውነትህን ነው!?”
“ለምን እዋሽላለው.....”

“ታዲያ ምን አልካቸው?” በጉጉት ጠየቀችው።
“ቆዩ። ቸኩላችሁ ነገር አታበላሹ.....”
አቋረጠችውና “እና እሺ አሉህ.....?”
“በመከራ ነው እያሳመንኩ ያስተውኳቸው። አየሽ ዛሬ ቸኩለው ጦርነት ቢያነሱ እስከመጨረሻው ገፍተን እንድንሔድ የሚያደርገን የመሳሪያና የገንዘብ አቅም ስለሌለን እንሸነፍና ተመልሰን የነፍጠኛ መጫወቻ ነው የምንሆነው። ስለዚህ መጀመሪያ የሆዳችን በውስጣችን ችለነው እንጠናከር ነው እያልኩ የነገርኳቸው።” አለ።
“ጥሩ አደርገህል..... እኔም እስኪ ሊረዱችሁ ከሚችሉ የውጪ ድርጅቶች ጋር ከአሁን ጀምሮ አንዳንድ ነገሮችን ልነጋገርላችሁ ወሰኛለሁ” አለች።

“በይ በርቺና አግኝን ኦሮሚያ ነፃ የወጣች ዕለት የጀግንነት ሽልማትሽን ትቀበያለሽ።”
“ይሁና..... ውጤቱን በየግዜው አሳውቅህለው። በል ደህና እደር።” አለችው ይህ የገባችበት ነገር ወዴት እንደሚያመራ ለመገመት እየተሳናት ግን ደግሞ የደስታ ስሜት እየፈጠረላት።

ስልኩን ዘግታ ወደ ወንበሩ በመመለስ የተነጋገሩትን የሂርጳን አቅም የሚያሳይ ሰፊ ዘገባ በወረቀት ላይ ስታሰፍር አመሸችና በሚቀጥለው ቀን ማለዳ ላይ ለሉዊስ ተቋም በፋክስ ለማስተላለፍ አዘጋጅታ ወደ መኝታዋ አመራች። እንቅልፏን ግን ተቀምታ አደረች።

በሚቀጥለው ቀን ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ላይ የኦሮሞና አማራን ብሔር እንዲያነካክስ ሆን ተብለው ከተሰሩት ዝግጅት መካከል ሁለተኛውና ከትላንት በይደር የተላለፈው ቀጠለ።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

በዚህ ዕለትም ሰዎች ከቋጥኝና ከገደሎች ላይ ሲወረወሩ፤ የሳር ቤቶች በእሳት ሲቃጠሉ፤ ሰዎች ሰውነታቸውን ከግርፋት ብዛት ተልጦ ደም እንደ ውሃ ሲፈሳቸው የሚያሳይ ቀስቃሽ ስዕሎች በቴሌቪዥኑ መስታወት ተላለፈ።።

የአዘጋጁ ድምፅ የሀዘን ቅላፄን በተላበሰ ሽፋን "ኦሮሚያን ለማጥፋት ነበር ፍላጐታቸው..... የኦሮሞን ህዝብ በባርነት ለመሸጥ ነበር ቀጣዩ ህልማቸው ከክልላችን በገንዘብ የማይተመን ሀብት ነው የተዘረፍነው..... አዎ.....ይህ ሁሉ የደረሰብን በነፍጠኞችና በነገስታቶቻቸው ነው..... ታዲያ ዛሬስ የኦሮሞ ልጅ ለምን ለነፃነት አትነሳም....."

በየስፍራው ዝግጅቱን የተከታተለው የኦሮሞ ተወላጅ መካከል በሀሰቱ ስብከት የተታለለው የዋሁና በአክራሪ ብሄረተኝነት ስሜት የተዋጠው ሁሉ ደርሶ በአውቃለሁ ባይነት እየተነሳ እንደ ነብር ተቆጣ አቅም ያለው ከቻለ ለመግደል ካልቻለም ለመሞት ቆረጠ።። አቅም የሌለው ያለበት ሆኖ አለቀሰ።። አዘነ።።

የዝግጅቱ ሁለተኛው ክፍል ማብቃቱንና ቀጣዩን የመጨረሻ ክፍል በነገው ዕለት እንደሚያስተላልፉት አዘጋጁ ገልፆ ደመደመ።። በዛ ቅፅበት በወለጋ ክፍለ ሀገር ባኮ በሚባለው ከተማ ውስጥ የዕለቱን ዝግጅት በአንድ ቡና ቤት ተቀምጠው ሲከታተሉ የነበሩ አራት የአዲሱ «ኦሮሞ አርበኞች ንቅናቄ» አባል ወጣቶች በቁጣ ስሜት ሂሳባቸውን ከፍለው ወጡ።።

በዝምታ እንደተዋጡ ለአስር ደቂቃ ከተማዋን አቋርጠ በሚያልፈው አስፓልት ላይ ወደ ምዕራብ ተጓዙ።። ሁሉም በውስጣቸው የሚያስቡት አንድ ነገር ብቻ ስለነበረ ተግባብተዋል።።

የከተማው መውጫ ጋር ሲደርሱ ሁለቱ በኦሮምኛ ቋንቋ "ጠብቁን እዚሁ" አሉና ወደ ግራ በመታጠፍ በቤቶች መሀከል የምታልፈውን ጠባብ መንገድ ይዘው በመግባት ከሰባት ደቂቃ በኋላ ተመልሰው ብቅ አሉ።። ሁለቱም ከትከሻቸው ጀምሮ ባጠለቁት ሽርጥ ስር ታጣፊ ክላሽንኮቭ ጠመንጃ አንግተው ነበር።።

አስፓልቱን አቋርጠው ትይዩ ባለው ጠባብ መንገድ በመግባት መጓዝ ቀጠሉ።። አነስተኛ የህዝብ ብዛት ያለባት ይህች አነስተኛ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

ከተማ እንቅስቃሴ አልባ ሆናለች፡፡ በፍልጥና በአጋም እሾህ የተሰሩ የጊቢ አጥሮች መሀከል እየሄዱ ነው፡፡ አልፎ አልፎ የውሻ ጩኸት ከርቀት ይሰማል፡፡ ጨረቃ የሌለች በመሆኑ የፅልመቱ ሀይል ወደ ንጋት የተቃረበ መስሏል፡፡

መንደሩን አቆራርጠው ፈንጠር ፈንጠር ያሉ የገበሬ ቤቶች የሚገኙበት አካባቢ እንደደረሱ ተቀራርበው በሹክሹክታ ተመካከሩና መሳሪያ ያነገቱት ሁለቱ ወጣቶች እርምጃቸውን ቀጠሉ፡፡ ወደ አንድ ደሳሳ ጎጆ ጋር በመጠጋት "እንዳለ..... እንዳለ....." አንደኛው ደጋግሞ ተጣራ፡፡

ከጐጆዋ ውስጥ "አቤት..... ማነው?....." ገርበብ ያለችው የጎጆዋ በር ተከፈተና አንድ ሰው ብቅ አለ፡፡

በበሩ መከፈት ወደ ውስጥ የሚነፍሰው ንፋስ ኩራዟን ለማጥፋት ሲል "በሩን መለስ አድርገው!" የሴት ድምፅ በአሮምኛ ቋንቋ ለሰውዬው ትዕዛዝ ሰጠ፡፡ ሚስቱ ነበረች፡፡ ወጣ ብሎ ዘጋ አደረገው፡፡

የአርባ ሁለት ዓመት እድሜ ያለው እንዳለ ባኮ ከተማ ኦሮሞ ሚስት አግብቶ መኖር ከጀመረ ሀያ አንድ ዓመታት አስቆጥሯል፡፡ "እንደምን አመሸህ?..... አቶ ጉርሙ ፈጥነህ ድረስ ለጥብቅ ጉዳይ እፈልግሀለው ብለዋል፡፡" አለ አንደኛው ወጣት፡፡

ሰውዬው በአካባቢው የገበሬ ማህበር ሊቀመንበር ሲሆኑ የእንዳለን አንድ ልጅ ክርስትናም በማንሳት በአበልጅነት ተዛምደዋል፡፡ወጣቶቹ እሳቸውን እንደምክንያት የተጠቀሙባቸው ለዚህ ነበር፡፡

"ዛዲያ ማለዳ አይደርስም ኖሯል?"

"አሁኑኑ እንዲመጣ ንገሩት ነው ያሉን"

"በጅ እንግዲያው ጐጃም አዘነዬን ደርቤ ልውጣ" አለና ወደ ቤቱ ሲመለስ የወጣቶቹ ልብ አመታት ፍጥነት እየጨመረ ሄደ፡፡

ደቂቃ ሳይቆይ ተመልሶ ወጣና የሽመል ዱላውን እያስቀደመ ከሱ ቤት ጥቂት ራቅ ወደሚለው የሊቀ-መንበሩ ቤት ጉዞ ጀመሩ፡፡

ሰርጥ ያለበት መሀከል ስፍራ ላይ ሲደርሱ ግን ሁለቱ ወጣቶች ካደፈጡበት ተፈናጥረው እየወጡ "ቁም!" ትዕዛዝ ሰጡ፡፡

"እረግ..... እኛ የመንደሩ ገበሮች ነን" እንዳለ ፈጥኖ መልስ ሰጠ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“ዝጋ!” አንተ የነፍጠኛ ዘር .....” አለና አንደኛው በጠመንጃው ሰደፍ ሸንጡ ላይ አሞነው፡፡ ኑሮ ያደቀቀ አካሉ ምቱን ስላልተቋቋመለት መሬት ላይ ወድቆ እያቃሰተ “እንዳለ እኮ ነኝ.....”

“ተነስና ወደምናዝህ ስፍራ አፍህን ዘግተህ ቀጥል” አለ አንደኛው ሊነሳ ግን አልቻለም፡፡ አራቱም በዓይናቸው ተነጋግሩና ሁለቱ ከቤት ያመጡት ወጣቶች ግራና ቀኝ ደግፈው አነሱት፡፡ሲሄዱበት የነበረውን አቅጣጫ ለውጠው ወደ ግራ በመታጠፍ ፈጣን ጉዞ ቀጠሉ፡፡

ገዝፈው በሚታዩ ሁለት ተራራዎች መሀከል ባልተለመደ አቅጣጫ ሲጓዙ ቆዩና ጥቅጥቅ ካለ ደን መሀከል ሲደርሱ ለቀቁት፡፡

ምቱ ላይ ተጨምሮበት እያንዘፈዘፈው ያለው የድንጋጤ ማእበል አሁንም ራሱን ችሎ እንዳይቆም አደረገውና ወደቀ፡፡
መሬት ሆኖ ሊያያቸው እየሞከረ “ምን አጠፋሁ.....?”
“ደሞ ምን አጠፋሁ ትላለህ?” አለና አንዱ በጫማው ጭንቅላቱን ረገጠው ቀጠለ ሌላኛው በበቀል ስሜት እየተቁነጠነጠ “የኦሮሞን ልጆች ስትጨፈጭፉና ስትጫወቱበት ለመቶ አመታት ያህል ኖራችሁ ይህ አልበቃ ብሏችሁ ዛሬም እንደፈለጋችሁት በአገራችን ልትፏልሉበት ትፈልጋላችሁ?” አለው ጥርሱን ነክሶ፡፡

“ስለምትለው ነገር እኔ ምን አውቄ?”
“ዝምበል ነፍጠኛ አይደለህም አንተ?”
ነፍጠኛ ሲሉ አማራ ማለታቸው እንደሆነ ገና አሁን ገባው፡፡
“ዛዲያ አማራነት ወንጀል ነው?”
ተያይተው ተሳሳቁ፡፡
“ዛሬ ተራው የኛ ነው ካለርሕራሔ እንዳጠፋችሁን እናንተንም አንድ በአንድ እናጠፋችኋለን” ብሎ ጠመንጃውን አቀባበለ፡፡
እንዳለ እየተንቀጠቀጠ “እኔኮ የኦሮሞን ህዝብ እወዳለሁ.....ከትውልድ አገሬም ወጥቼ በናንተ መሀከል ገብቼ ኑሮ የመሰረትኩት ለዚህ ነው..... ሚስቴም ብትሆን ኦሮሞ ነች..... ከኦሮሞ ተዋልጃለሁ ተጋምጃለሁ.....” አለ በተቆራርጠ ቅላፄ፡፡
በሹፈት ተሳሳቁ፡፡ ንግግሩን ቀጠለ “.....ልጆቼም በኔ በኩል አማራ ቢባሉ እንኳ አምስቱም ህጣናት ተአማርኛ ይልቅ ኦሮምኛን ነው

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

አቀላጥፈው የሚናገሩት..... ወደፊትም ተዚህ ሌላ የሚያውቁት አገር ስለሌለ ተዚሁ ነው ተዋልደው የሚኖሩት..... እኮ ጥፋቴ እምኑ ላይ ተገኘ?" አለ ለቅሶ ባጀበው ሁኔታ
"ዘራችንን አበላሸህ እንጂ ያጠራኸው መሰለህ?እናንተ አረመኔዎች!" አለ በዝምታ ሲያይ የነበረው ወጣት፡፡
እንዳለ ባልተሟጠጠ ተስፋ "ግን እኮ ሁላችንም ኢትዮጵያዊ ነን ለምን በዘር ለመከፋፈል እንሮጣለን?..... እሱን እንኳ አጢናችሁ ምህረት አድርጉልኝ..... ታሻችሁም ምስትና ልጆቼን ይገፎ ማለዳ ላይ ተዚህ አገር ልሰደድ" ብሎ ተማፀነ፡፡
አንዱ በቁጣ ቅድም በቴሌቪዥን ያየውንና የሰማውን እያስታወሰ "አንተ ውሻ እኛ ኦሮሚያዊ እንጂ ኢትዮጵያዊ አይደለንም፡፡ ምኒልክ ነው ኢትደጵያ ያደረገን!" አለና ወደሱ ያነጣጠረውን ጠመንጃ ቃታ ሳበው፡፡ አንደኛዋ ጎኑን መታችው ሁለተኛዋ የቀኝ እግሩን አጥንት አነከተችና አልፋ መሬት ውስጥ ተቀረቀረች፡፡
እንዳለ በጀርባው መሬት ላይ ተዘረረ፡፡

ተኳሹ ለሶስተኛ ጊዜ ሊመታው ሲመቻች "እንተ ጥይት ሰባት ሰባት ብር ገብቷል አታባክን" አለው ሌላኛው ባለጠመንጃ ፡፡
"አዎ..... ይበቃዋል" ሶስተኛው ደገፈ፡፡ ሲጠጡት የቆዩት መጠጥ ገና መስራት እየጀመረ ነበር::
አራተኛው ወጣት ከኪሱ አነስተኛ ካሜራ አወጣና በቅርበት ፎቶ ካነሳው በኋላ "እንሂድ" አላቸው፡፡
በመጡበት በኩል የሰው እይታ ውስጥ እንዳይገቡ እየተጠነቀቁ ወደየ ቤታቸው ተበታተኑ፡፡
እንዳለ ህይወቱ አላለፈችም፡፡ በርካታ ደም ስለፈሰሰው ግን የማዞር ስሜት ተሰምቶታል፡፡ "ጫልቱ..... ጫልቱ....." የሚስቱን ስም የሚችለውን ያህል ጮክ ብሎ ተጣራ፡፡ ግን ከሱ ሁለት ሜትር ራቅ ብሎ ላለ ሰው እንኳ ድምፁ አይሰማም ነበር፡፡ ለመነሳት ሞከረ አካሉ ላይ ግን ከላዩ ቆመው የሚታዩት አስፈሪ ተራራዎች የተጫኑበት ይመስል ከበደው፡፡ እየተንቋቀቀ ለመሔድ ሞከረ፡፡ በሃያ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ደቂቃ ውስጥ ግን ያለውን ጉልበት አንጠፍጥፎ የተጓዘው ሶስት ሜትር ያህል ብቻ ነበር።።

የልጆቹ ገፅታ ውልብ እያለ የሚያልፍ መሰለው።።እሱ ሳይሆን እነሱ ወደ ሞት እየሄዱ ይመስለዋል።። ሊይዛቸውና ሊመልሳቸው ያስባል።። ደግሞም ህልም መሳይ ነገር።። አስፈሪ ድምፅ በቅርበት ተሰማው።። እሱም ህልም መሳይ ነገር..... የሚያስካካ ድምፅ..... ድጋሜ ጩኸት.....

'የዛሬው ቅዥት ምን አይነት ነው?' ራሱን ጠየቀ።።

የተጨፈኑት አይኖቹን ለመግለፅ ሞከረ።። እንደ ጨረቃ የሚያበሩ መዓት ብርሃኖች ዙሪያውን የከበቡት ይመስለዋል።።'የዛሬው ጨረቃ ብዙ ነው።። ግን ደግሞ ጨለማ.....'

በዙሪያው ተቀምጠው አንዱ እስኪጀምረው ድረስ ሲያፈጡበት ከነበሩት ጅቦች መሀከል ፈርጠም ያለው አንገቱን አስግጐ ተጠጋውና በፍራቻ አፉ የቻለለትን ያህል ሙዳ ስጋ ከተመታው እግሩ ላይ ቦጭቆ ሸሸ።።

እንዳለ በጥቂቱ የሆነነ ነገር ሲያቃጥለው ተሰማው።። በዛው ቅፅበት ነፍሱ ወጣች።። እነሱም ተረባረቡበት።።

በበነጋታው እንጨት ሊለቅሙ ወደ ጫካው የገቡ ሰዎች ያገኙት በደም የተጨማለቀ ልብሱን የእግሮቹንና የእጆቹን መዳፎች እና ጭንቅላቱን ብቻ ነበር።።

በዛን ዕለት ለሊት አሩሲም የሁለት አማራ ገበሬዎች ቤት እንደተኙ በእሳት ተያይዞባቸው ከቤተሰቦቻቸው ጋር አመድ ሆነው ቀሩ።። በባሌም በጅማም እንዲሁ.....

በጥቆማ የእንዳለ የተራረፈ ሬሳ ጋር የደረሱት የክልሉ ፖሊሶች ለማዕከላዊው የመንግስት ሰዎች ያስተላለፉት ዘገባ "በባኮ ከተማ ነዋሪ የነበረ እንዳለ ፍቃዱ የተባለ ገበሬ በትላንትናው ምሽት እዳሪ ለመፀዳዳት ከቤቱ እንደወጣ በጅቦች ተነክሶ ከተገደለ በኋላ ከቤቱ ራቅ ባለ ጫካ ውስጥ ጐትተው በመውሰድ በልተውታል" የሚል ነበር።።

አራቱ የ"ኦ.አ.ን." ምልምሎች እንዳለን ገድለው ያነሱትን ፎቶ ለክልሉ አዛዣቸው እሱም ለበላዩ እያለ መጨረሻ ላይ ሂርጳ እጅ ደረሰ የድርጊቱን በአሁኑ ወቅት መፈፀም ባይደግፈውም አንዳንዴ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

ግን እንደዚህ ዓይነት እርምጃዎች መውሰዳቸው ለመንግስት ማስጠንቀቂያ ይሆነዋል ብሎ ስላመነ በይሁንታ ተቀበለው፡፡

እሱም ፎቶውን ለሰናይት አሳያት፡፡ ሰናይት ለምታሰባስብላቸው እርዳታ እንደሚጠቅማት በማሳመን ተቀበለችውና ከዝርዝር ዘገባው ጋር ወደ ፈረንሳይ ላከችው፡፡

ከፈረንሳይ የመጣላት ምላሽ "የላክሽልንን ፎቶ ለዜና ብቻ ከሚሆን መረጃ ጋር ለጋዜጣ አሳታሚዎችም በመላክ በፍጥነት እንዲያትሙት የጠየቁሽን ክፍያ ከፍለሽ ዜና እንዲሰራበት አስደርጊበት" አሏት፡፡ የአማራው ተወላጅ ደግሞ ሲያነበው የራሱን የብቀላ እርምጃ እንዲወስድና ሁኔታዎች እንዲባባሱ አስበው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ሽብር ለመፍጠርና እቅዳቸው እንዲፈፀም ይህኛው አንዱ የመሸጋገሪያ መንገድ ነበርና፡፡

ሰናይት የተባለችውን ፈፀመች፡፡ ጋዜጦቹ ግን ለጉዳዩ ተጠያቂ አድርገው ያቀረቡት ብሔረሰቦቹን ሳይሆን መንግስትን ነበር፡፡ እንደኛው "ዘረኝነትን የሚያባብሱ የአገዛዝ ስርዓቶች በኢትዮጵያ እየተስፋፉ ሄደዋል" በሚል ርዕስ ሰፊ ዘገባን አሳትሞ አሰራጨ፡፡ ሌላኛው ጋዜጣ ደግሞ "በትክክል ኢትዮጵያዊነት የሚሰማው መሪ ነው ያለን?" በሚል መግቢያ የህዝቡን ስቃይ ለንባብ አበቃ፡፡

ሁለቱም ጋዜጣ አሳታሚ ድርጅቶች ዜናውን ባሰራጩት ዕለት ከሰዓት ከስራ ታግደው ባለቤቶቹ ወህኒ እንዲወርዱ የሚያደርግ የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ደረሳቸው፡፡

ምሽት ላይ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የአማርኛው ክፍለ ጊዜ አንድ ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣን

"በኢትዮጵያ ከመቼውም ግዜ በበለጠ ሁኔታ አሁን የብሔሮች እኩልነትና አንድነት ተጠናክሯል፡፡ ህዝቦች ያለስጋት ወጥተው የመግባት መብታቸው ተረጋግጧል፡፡ ለዚህ ደግሞ እየተሰሩ ያሉትና የሚታዩት የልማት ስራዎች እና እውነታዎች በቂ ማረጋገጫ ሊሆኑ ይችላሉ....." በሚልና በዚሁ ዙሪያ የሚያጠነጥን አሰልቺ የሆነ ያገጠጠ የውሸት ዲስኩር ለአንድ ሰዓት ከሰላሳ ደቂቃ ያህል ተላለፈ፡፡

  

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ምዕራፍ 12

“በሚገርም ፍጥነት መረጃዎች ፈሰስ እየሆኑልን ነው” አለ ሉዊስ ፒየርን አፍጦ እያየው ቀጠለ “.....ይህ ደግሞ ወደ ተከታዩ ስራችን በፍጥነት መራመድ እንዳለብን ነው የሚጠቁመን!”
“የቱን?” ፒየር ቀጠለ፡፡
“ወደ ኢትዮጵያ የሚገባውን በቂ የጦር መሳሪያ እርዳታ ወደ ማሰባሰቡ ስራ!”
“እስካሁን ድረስ በእቅድ ከያዝናቸው አምስት ክልሎች ውስጥ ገና ኦሮሞ የሚባለውን ብሔር ብቻ ነው ሴትየዋ ማነጋገር የቻለችው፡፡”
“ቢሆንም.....” አለ ሉዊስ፡፡ ቀጠለ “.....መሳሪያዎችን የማሰባሰቡ ስራና እንዴት ተጓጉዘው በድብቅ ወደ ኢትዮጵያ መግባት እንደሚችሉ ከአሁኑ ቢጠናቀቅ በኋላ ሊፈጠርብን የሚችለውን ውክቢያ ያቀለዋል፡፡”
“ይቻላል፡፡ የመጠየቂያ ደብዳቤዎች እንደሆን ተዘጋጅተው የተቀመጡ ናቸው፡፡ ቀንና ፊርማ እያሳረፉባቸው ብቻ መበተን ነው” ቀጠለ ፒየር እያሰላሰለ “.....ይልቅ የሚያሰጋኝ ትልቁ ነገር ፈንድ የሚያደርጉን አገሮች ራሳቸውን ላለማሳወቅ ሲሉ ገንዘቡን በተዘዋዋሪ መንገድ ነበር የሰጡን፡፡ አሁንስ የመሳሪያዎቹን እርዳታ እንዴት ባለ ሁኔታ ነው እጃችን እንዲገባ የሚያደርጉት?” አለ፡፡
“እሱን ለኔ ተወው.....”
“ጥሩ..... ምን ያህል ግምት ያለው መሳሪያ እናገኛለን ብለህ ታስባለህ?”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“እርግጠኛ አይደለሁም፡፡ ሆኖም ግን በብዛት ጠቀሜታ ላይ በመዋል አስከፊ ውጤት በማድረስ በኩል በተለይ የነፍስ ወከፍ መሳሪያዎችን እንዲረዱን ነው የምንፈልገው፡፡”
“የባዮሎጂካል መሳሪያዎችን በተጨማሪ ብንጠይቃቸውስ?”
ሉዊስ በሀሳብ ተዋጠ፡፡ ጥቂት ቆየናም “አላስተዋልኩትም ነበር....ጥሩ ይመስለኛል፡፡ በድጋሜ አስብበታለሁ .....የሚዋጉበት እርስ በእርስ እስከሆነ ድረስ ከነሱ ውጪ ማንም ተጠያቂ ሊሆን አይችልም፡፡ የተሻለ ውጤትም ያመጣል ብዬ አምናለሁ፡፡”
ፒየር ሀሳቡን ማስታወሻ ላይ ሲመዘግብ ቆየና “ይልቅ ክፍያዎቹ መጀመር እንዳለባቸው ነግራኛለች፡፡”
“ለፓርቲዎቹ?”
“አዎ..... ለኦሮሞ አርበኞች ንቅናቄ”
“ይቻላል፡፡ ሩብ ሚልዮን ዶላር ይላክላት፡፡ እንደየ ደረጃው እየጨመረ የሚሔድ መሆኑንም ግለፅላት፡፡”
“ገንዘቡ ለማስተላለፍ ማንን እንጠቀም?” ፒየር ጠየቀ፡፡
“ያለፈ ጊዜ አለ ብለኸኝ የነበረው ሰው.....”
“ለጊዜው በሌላ ስራ እንደተጠመደ ነግሮኛል”
ሉዊስ ፈጣን የአመራር ትዕዛዙን መስጠት ቀጠለ “በምስራቅ አፍሪካ አገሮች ውስጥ ህገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውር ቢሮዎች ያሉት ታማኝ ሰው.....” አለና ከአንድ የማስታወሻ ጥራዝ ውስጥ የስልክ ቁጥር አውጥቶ እየሰጠው “.... አግኘው” አለው

ፒየር ወረቀት እየገለፀ “ሌላው .....በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ላይ ከሰናይት ጋር አብሮ የሚሰራ አንድ አውሮፓዊ ሰው ብንቀጥር ይበልጥ ለውጤት የመብቃት እድላችንን ያሰፋዋል ብዬ አምናለሁ”
በሉዊስ አተኩሮ እያየው “ምን እንዲሰራልን?” አለው፡፡
“አየህ ይህ አውሮፓዊ በታሪክ የኘሮፌሰርነት እና የስነ-ተፈጥሮ ደግሞ ሌላ ተጨማሪ ዲግሪ ያለው ምሁር አስመስለን ሰነድ እናዘጋጅለታለን፡፡
«ምን እንዲሰራልን ላልከኝ..... ደቡብ የኢትዮጵያ ክልል ገና ጥናት ያልተካሔደበት የበርካታ ሺህ ዓመታት ታሪክ እንዳለው በአውሮፓ ውስጥ ለህትመት የሚበቁ ስራዎች ላይ መታየት

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ይጀምራል፡፡ 'በዛ ላይ ክልሉ በተፈጥሮ ሀብት የዳበረ መሆኑ ግልፅ ስለሆነ በነዚህ ላይ ምርምር ያደረገ ምሁር በመምሰል ለህዝቡ ተጠሪዎች ነን የሚሉትን ቁልፍ ሰዎች ወደ ግባችን እየጠመዘዘ በማምጣት ሰናይትን ያግዛታል !" አለ፡፡
"ስለ ምርምሩ የሚገልፁትን ጥናቶች አንብቦ በመሔድ?"
"ትክክል!"
"ታዲያ አዲስ አበባ ውስጥ ያለውን መረጃ አቀባያችንን አስረኛውን ሰው ለምን በተደራቢነት አናሰራውም?" አለ ሉዊስ፡፡
"የስራ ጫና አይፈጥርበትም?"
"የምንከፍለው የገንዘብ መጠን እንደዛ እንዳይሰማው ሊያደርገው የሚችል ከሆነስ ?"
"ጥሩ፡፡ አረገግጣለሁ፡፡"
"ፈቃደኛ ከሆነ ቅጠረው፡፡ ጥናቶቹ የተካሔዱበትን ፅሑፎች በጠቅላላ አሰባስበህ በፋክስ ላክለት፡፡"
"ተዘጋጅቶ የተቀመጠ ስለሆነ አንስቶ መላክ ብቻ ነው፡፡"

  

የማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ምዕራፍ 13

ኤም.አይ.፩ በሚባለው የእንግሊዝ የስለላ ድርጅት ውስጥ የሚስጥራዊ ሰነዶች ማከማቻ ዋና ቢሮ ሀላፊ ሆኖ የሚሰራው ስሚዝ ማርክ በሚስጥር ለሉዊስ ተቋም ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ሰነዶችን ከሉዊስ በሚቀርብለት ጥያቄ መሰረት በድብቅ እያወጣ በመሸጥ የግል ጥቅም ማግኘት ከጀመረ ድፍን አምስት ዓመታትን አስቆጥሯል።

በዚህ ወቅት ላይ ነበር ስሚዝ ጠቀሜታቸው ምን ያህል እንደሆነ ያልተረዳቸውና በ1860 ዓ.ም ለንደን ውስጥ በእንግሊዝ መንግስት ሰብሳቢነት ከፈረንሳይ፤ ከጣሊያን፤ ከእስፔንና ከፖርቹጋል የወቀቱ መንግስታት ዋና ዋና ተወካዮች በተገኙበት ሰፊ ውይይት ተካሂዶ ስለተፈረመ አንድ ሰነድ የተጠየቀው።

በወቅቱ እነዛ የአውሮፓ መንግስታት ዓለምን በተለይ የአፍሪካን መሬት በነሱ ቅኝ ግዛት ስር ለመጣል የከፋ ወረራን ከማካሄዳቸው ባለፈ፤ የበለጠ ግዛቶችን ለመቆጣጠር ባላቸው የየግል ፍላጎት ምክንያት እርስ በእርስ በጥላቻ ከመተያየት አልፈው ግልፅ የወጣ ፖለቲካዊ መቃቃር ውስጥ እስከመግባት ደርሰው የነበር ቢሆንም በዛ ስብሰባ ላይ የሚወሰነው ውሳኔ ለሁሉም ከፍተኛ ጥቅም ያስገኝ ስለነበር ልዩነታቸውን ወደ ጎን ትተው በጥሪው መሰረት ተሰባሰቡ።

ቀዳሚው እቅዳቸውም በቀኝ ግዛት ስር በወደቁ አገሮች በሚበዘብዙት ሀብት መጀመሪያ አገራቸውን ማበልፀግ ቀጥሎም እንደ አህጉር አውሮፓን ለይቶ በፕላኔቷ ላይ በኢኮኖሚ፤ በስልጣኔ፤ በእውቀት እና አጠቃላይ የፖለቲካ ጉዳዮችን በበላይነት ጠቅልሎ መቆጣጠርን የሚጨምር ነበር።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

በመካከላቸው ያለው ቅራኔ እንደተጠበቀ ቢሆንም በዋናው መስመር ላይ ለተቀመጠው እቅድ መሳካት ከ142 አመት በፊት አምስቱ የወቅቱ ታላለቅ ቅኝ ገዥ መንግስታቶች ለንደን ላይ ተቀመጡና የአንድ ወር ጊዜን የጨረሰ ስብሰባ በማካሄድ ቀኝ በተያዙ የአፍሪካና የሌሎች አህጉር ግዛቶች ውስጥ ተተግባሪ የሚያደርጓቸውን ሰባት ዋና ዋና ሀሳቦችን የያዘ የስምነት ውሳኔ ተፈራረሙ:: ፊርማው ያረፈበት ሰነድም በአምስት ቅጂ ተባዝቶ የየሀገራቱ መንግስታት አንድ አንድ ቅጂ እንዲሰጣቸው ተደረገ::

ሉዊስ የዚህን ሰነድ ቅጂ በእስሚዝ በኩል ተሰርቆ እንደደረሰው ደጋግሞ ነበር ያነበበው:: ሰባቱን ዋና ዋና ነጥቦችንም ለይቶ በራሱ ማስታወሻ ላይ ማስፈር ጀመረ
« 1. ከአውሮፓ ውጭ ያሉ አገሮች ሁሉ በተለይ ከፍተኛ የተፈጥሮና የሰው ሀይል ሀብት ክምችት ያላት አፍሪካን ሙሉ በሙሉ በቀኝ ግዛት ቁጥጥር ስር ማዋል » የስምምነቱን ሀሳብ ገልብጦ እንደጨረሰ ከጎኑ "... ይህ እቅድ ከኢትዮጵያና ከላይቤሪያ በስቀር በመላው የአህጉሪቱ ግዛት መተግበር ችሏል:: " ብሎ ፃፈና ወደ ቀጣዩ ነጥብ አለፈ

«2. በቀኝ ግዛት ስር የወደቁ አገሮች ሀይል እንዳይኖራቸው እና እንዲዳከሙ በብሔር ፤ በሐይማኖት፤ በቋንቋ፤ በባህልና በቆዳ መልክ ለያይቶ መግዛት:: በዚህም አንዱ ከሌላው የተለየና የተሻለ ወይም የበለጠ ስሜት እንዲሰማው በማድረግ ስነ-ልቦናዊ ልዩነቶችን በመካከላቸው መፍጠር» የሚለውን እንዳነበበ ወድያው ወደ ህሊናው የመጣው የሩዋንዳ ቡሩንዲ የጎሳ ጦርነት መንስኤው ይህ እንደነበረ ፍንትው ብሎ ታየው:: የራሱን ማስታወሻ ያዘና ወደ ሚቀጥለው ነጥብ አለፈ

«3. ቀኝ ተገዥ አገራት በተለያዩ የራሳቸው ምክንያቶች እርስ በራስ የሚያነሷቸው ግጭቶች እና ጦርነቶች እንዳይከስሙና ቀጣይ ሆነው እንዲኖሩ ማድረግ፤ በዚህም የማይሽር የበቀል እና የቁጣ ስሜትን ለቀጣዩ ትውልዶቻቸው ጭምር እያወረሱ እንዲያልፉ ማድረግ» የሚል ነበር::
ከስሩ "በቀኝ ግዛት ያልተያዘችውን ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ የአፍሪካ ሀገራት ውስጥ ያሉት ህዝቦች የዚህ ዓላማ ውጤት ሰላባ የሆኑ ሲሆን ብሔርን ፤ ጎሳን ፤ ቋንቋን ፤ ሀይማኖትን መሰረት አድርገው በነፃ አውጭ ስም ወደ ጦርነት የገቡ ተራ የፖለቲካ አራማጆችም በየስርቻው ተፈጥረዋል:: " ብሎ የራሱን ሀሳብ አሰፈረ::

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

«4. አምስቱም የወቅቱ ሀያላን የቅኝ ገዥ መንግስታቶች በተለይ የአፍሪካን አገራቶች አቀማመጥ ንድፍ (ካርታን) እንደፈለጉና እንደመሰላቸው አድርገው በከፍተኛ ምሁራኖቻቸው በጥንቃቄና በትክክለኛ መንገድ በጥናት የተሰሩ አስመስሎ የተለያዩ አይነት አጨቃጫቂ ካርታዎችን በመሳል በዓለም ላይ ማሰራጨት እንዲሁም ወደ ግጭት እንዲያመሩ መንገድ የሚፈጥሩ የሀሰት ታሪኮችን የጥንት ታሪክ አስመስሎ በማሳተም ማሰራጨትን ይጨምራል።

የዚህ ነጥብ ጠቀሜታው በአፍሪካ ውስጥ መቼም የማያባራ የድንበር ይገባኛል ጭቅጭቅና ጦርነቶች መንስኤ ስለሚሆን ለቀኝ ተገዥነት ይዳርጋቸዋል።» ይላል።

ሉዊስ ይህንን ነጥብ እንዳነበበ ቆም ብሎ ማሰብ ጀመረ። በዚህ ምክንያት ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ የአፍሪካ ሀገራት መጠኑ የማይታወቅ የሰው ህይወትና የአጉሪቷን ሀብት መስዋእት ያስከፈለ ብጥብጥ ውስጥ እንደገቡና እስካሁንም ድረስ ብዙዎቹን አገራት መሳሪያ በማማዘዝ ላይ ያለ አደገኛ ነጥብ መሆኑን እያሰበ ማስታወሻ ፃፈና ወደሚቀጥለው ነጥብ አለፈ።

«5. ቀኝ ገዥ መንግስታት በራሳቸው ፍላጎትም ሆነ በአስገዳጅ ምክንያቶች ከያዙዋቸው አገሮች ለቀው በሚወጡበት ወቅት፤ በዛ አገር ውስጥ በርካታ ተቃራኒ ዓላማ ያነገቡ የማይግባቡ አንጃዎችን መፍጥር እና ሁሉንም የጦር መሳሪያ ማስታጠቅ እንዲሁም የተለያዩ ባንዲራዎችን መስጠት። ለሁሉም አንጃ እንደ ልዩነቱ ተቀባይነት መስጠት እና ሉአላዊነት ያለው ነፃ መንግስት መመስርት የሚያስችለው ብቃት ያለው በማስመሰል ለጥያቄያቸው እውቅና መሰል ተስፋ መስጠት።

ይህም ለቅኝ ገዥ ሀገራቶች ሁለት ጠቀሜታ ሲኖረው፤ አንደኛ ይህ ሀገር በፖለቲካም ሆነ በኢኮኖሚ ጉዳዮች በኩል ከአውሮፓ እርዳታና ጥገኝነት እንዳይላለቅ ሲያደርገው፤ ሁለተኛ መቼም የማያቆም የእርስ በእርስ ጦርነት እንዲኖር ያስችላል። በዚህም አውሮፓ የቀኝ አዙር አገዛዝ ሁሌም ይቀጥላል።»

ሉዊስ አንብቦ እንደጨረሰና በራሱ ማስታወሻ ላይ ገልብጦ እነደጨረሰ አያይዞ "ይህም ኢትዮጵያና ኤርትራን ጨምሮ የበርካታ አፍሪካ አገራት ግልፅ ችግር እንደሆነ ቀጥሏል። "

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

«6. ቅኝ ተገዥ አገራቶች በሚፈጠርባቸው የእርስ በእርስ እና የጎረቤት አገራት ጦርነቶች ውስጥ ከቀላል ግጭቶች አንስቶ እስከ ትልልቆቹ ድረስ የዳኝነትም ይሁን የወታደራዊ ሎጅስቲክ እርዳታዎችን በጠቅላላ ቅኝ ይገዙዋቸው ከነበሩት የአውሮፓ መንግስታት ብቻ እንዲጠይቁ በእጅ አዙር መቆጣጠር።»

«7. በአፍሪካ ውስጥ ሁሌም ወደ ስልጣንና ከፍተኛ የአመራር ደረጃ የሚመጡ ፓርቲዎችም ሆኑ ግለሰቦች አመለካከት እና ድርጊት በጠቅላላ የአውሮፓ መንግስታትን የማይቃወሙ፤ ቢቻል ለአውሮፓ አገራቶች ፖሊሲና ህግጋት ተገዢ የሆኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ። ይህ ካልሆነ ግን እነሱን በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ አስገድዶ ከስልጣን በማውረድ ከላይ ለተቀመጠው የኛ ሀሳብ የሚሰራ ፓርቲን እና ግለሰብን ማስመረጥ።»

የሚለውን የመጨረሻውን የስምምነት ውሳኔ ፅፎ እንደጨረሰ “ይህም በተለይ በአፍሪካ ውስጥ በተገደጋጋሚ ለተፈጠረው መፈንቅለ መንግስት እና ጦርነቶች መንስኤ ሊሆን ችሏል። ” በማለት የራሱን ሀሳብ ጨመረበት።

«««««« »»»»»»

ከ142 አመት በፊት በአምስቱ ሀያላን መንግስታት ስምምነት መሰረት የተፈረመው ይህ ሰነድ የዓለማችን ፖለቲካ እና ኢኮኖሚ ላይ በቃላት መግለፅ ከሚቻለው በላይ ለውጥን ያስከተለ ነበር።

19ኛው ክፍለ ዘመን እንደጀመረ ዓለማችን ላይ ያልተጠበቁ ታላላቅ ለውጦች ተከሰቱ። በተለይ የአንደኛውና የሁለተኛው የዓለም ጦርነቶችን ተከትሎ በአፍሪካና መካከለኛው መስራቅ ውስጥ በርካታ ቅኝ ተገዥ አገራት ነፃ ስለወጡ አውሮፓውያኑ የኖረና የጥቱን የአገዛዝ ስልታቸውን መቀየር ግድ ስላለ ስምምነት ያደረጉባቸውን መዛግብት እያገላበጡ ተለዋጭ ግን ቀጣይ የእጅ አዙር አገዛዝ ስልታቸውን ቀጠሉ።

በቅኝ ግዛት ተስፋፊነቷ ዓለምን ጉድ ከማሰኘት አልፋ «ፀሀይ የማይጠልቅባት አገር» እስከመባል የበቃችው «ታላቋ ብሪታንያ» በሷ ቅኝ የተገዙ አገሮችን አጠቃላይ ጉዳይ የሚቆጣጠር ተቋም ከገነባች አንድ ምዕተ ዓመት ደፍናለች። የተቋሙ እጅ በጣም የረዘመ፤ የረቀቀና ሀይል የተሞላ ከመሆኑ የተነሳ እስካሁን ድረስ በብሪታንያ ቅኝ የተገዙ አገሮችን

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

የፖለቲካና ማንኛውንም የውስጥ ጉዳዮች በይፋም ይሁን በስውር እየተከታተለና እየመራ ይገኛል።

እዲሁም የተቋሙ ባለስልጣናት ብሪታንያ ከዚህ ቀደም በማንኛውም መልኩ ባከናወነቻቸው ድርጊቶች በሀላፊነት እና በወንጀል እንዳትጠየቅ አገራቸውን መከላከል ሌላው ዋና ተግባራቸው ነበር። በዚህም ምክንያት ከዛሬ 142 ዓመት በፊት በብሪታንያ ሀሳብ አፍላቂነት እና ጥሪ አቅራቢነት ስለተፈረመ አንድ ሰነድ እንዲያስታውሱ የዘመኑ መለወጥ ግድ አላቸው።

ሰነዱ በዚህ ወቅት ላይ ማንም ከጉዳይ የማይፅፈው እንደውም የተረሳ መስሎ ቢታይም የዓለማችን በፈጣን ሁኔታ መለወጥ በድንገት ይህን የተረሳ የመሰለ ሰነድ በሆነ መልኩ አውጥቶ ለዓለም ህብረተሰብ ይፋ ቢያደርገው እንግሊዝን በከፍተኛ ሁኔታ የሚያስወነጅላትና ከቅኝ ግዛት ጋር በተያያዘ ምክንያት እስካሁን ለተከሰተው እና አሁንም እየተከሰተ ላለው ችግር፤ ለጠፋው የሰው ልጅ ህይወትና ለወደመው የአገራቶች ንብረት እና ሀብት ሁሉ እሷን የመጀመሪያ ተጠያቂ አድርጎ እንደሚያቀርባት ቀድመው ገመቱ።

ገምተውም አልተቀመጡም ያንን እንደ ማስረጃ ሆኖ ሊቀርብ የሚችለውን ሰነድ በወቅቱ ተፈራርመው ከወሰዱት አገራቶች ውስጥ በእንግሊዝ ሰላዮች አካማኝነት እየተሰረቁ እንዲሰበሰቡ ተወሰነና ስራው ተጀመረ። በጊዜ ሲሰላ ከሁለት ዓመት በላይ የፈጀና በርካታ ሚልዮን ፓውንድ ለስራው የፈሰሰበት ይህ ሰነድ ሃያ አንድ በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠኑ የእንግሊዝ ሰላዮችን ህይወት ያሳጣና ሰነዱ በየተሰረቀበት አገራት ለበርካታ ሰዎችን ሞት መንስኤ የነበረው ስራ በውጤት ተከናውኖ የእንግሊዝ እጅ ገባ።

የዚህን ሰነድ ጉዳይ ሉዊስ ከሰማበት ጊዜ ጀምሮ ቅጂውን ለማግኘ ት የነሱን ያህል አልደከመም። የኤም.አይ 6 ሚስጥራዊ መዛግብት ማከማቻ ክፍል ሀላፊ ለሆነው ሰው አንድ የስልክ ጥሪና የገንዘብ ክፍያ ብቻ ፈፀመና ሰነዱ ደረሰው። አንብቦት እንደጨረሰ ወደ አንድ ትልቅ ደረጃ እንደሚሸጋገርበት አመነ። ሰነዱ ውስጥ በምንም የማይተመን ከፍተኛ የስልጣንና የሀይል ምንጭ አለ። ሰነዱ ውስጥ ተዝቆ የማያልቅ የገንዘብ ምንጭ አለ። ሁለቱ ደግሞ ፕላኔቷን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ብቸኛ መንገዶች ነበሩ። እናም ሊጠቀምበት ቆርጦ ተነሳ።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

የትና እንዴት ቢተገብረው ውጤቱ እንደሚፈጥንለትም አውቋል። ኢትዮጵያ ዋናና ብቸኛ ምርጫው ነበረች። ለሱም ምክንያት የሆነው ደግሞ በተባበሩት መንግስታት ተቋም ውስጥ በሰራባቸው ወቅቶች ያካበተው እውቀት ጠቅሞታል። በተባበሩት መንግስታት ባሞያዎች እና ፖለቲካ ተንታኞች በተደጋጋሚ የተከናወኑ ጥናቶችን አንብቦ እንደተረዳው ከሆነ በመልከዓ ምድር አቀማመጣቸው እና ተፈጥሮ በለገሰቻቸው ሀይል አማካኝነት በፕላኔቷ ላይ ተፅእኖ ማሳደር ከሚቻላቸው በጣም ጥቂት አገሮች መካከል ኢትዮጵያ አንዷና ዋናዋ ነበረች።

የኢትዮጵያ ሰላም ለዓለም ሰላም፤ የኢትዮጵያ ብጥብጥ እና ቀውስ ለቀሪው የዓለም ክልል ሁሉ አደገኛና አስቸጋሪ ተፅእኖ ማሳደር እንደሚችል አረጋግጧል። ይህ ሊሆን የቻለበት ምክንያት ቀይ ባህርና የጥቁር ዓባይ ወንዝ ምንጭ መሆኗ ነው።

ዓለምን በበላይነት ለመምራት በተለያዩ ወቅቶች ላይ ሙከራ ያደረጉ ሀያላን መንግስታት ሁሉ አዘውትረው አይናቸውን የሚጥሉበት የምድሪቷ ማእከላዊ ክልል የሆነውና መላው አውሮፓን፤ ኢስያን፤ አፍሪካን እና ቀሪዎቹን የዓለም ግዛቶች ዋና አገናኝ የሆነው መተላለፊያ መንገድ ቀይ ባህር መሆኑ አንዱ ሲሆን ቀይ ባህርን መቆጣጠር የቻለ ሁሉ ዓለምን መቆጣጠር መቻሉ የተረጋገጠ መሆኑ ነው።

ቀይ ባህር ሲነሳ ደግሞ ኢትዮጵያ ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ሆና ቆይታለች። በዚህ ክልል ቀጣይ ተጠቃሽ አገር ግብፅና ሱዳን ይሁኑ እንጂ የሁለቱም አገሮች ህልውና የተገነባው በዓባይ ወንዝ ላይ መሆኑና የዓባይ ምንጭ ባለቤት ኢትዮጵያ መሆኗ ዞሮ ዞሮ አሁንም የኢትዮጵያ ተፅእኖ የማሳደር ሀይል አይሎ እንዲገኝ ምንያት ሆኗል።

የግብፅ መልክ ምድር አቀማመጥ መካከለኛውን ምስራቅን ለመቆጣጠር የተሻለ ምቹ ቢሆንም እንኳ በዓባይ ወንዝ ምክንያት በግድም ይሁን በውድ ለኢትዮጵያ ተገዥ በመሆኗ የሀይል ሚዛኑን አጥታለች። እናም የቀሪው ዓለም ትኩረት እና ዓይኖች ሁሉ ለዘመናት ኢትዮጵያ ላይ እንዲሆን ግድ ብሏል። ጥያቄው ዓለምን መግዛት የሆነ ሀያል አገር ቀድሞ ቀይ ባህርን መግዛት መቻል ሲኖርበት ከዛ ቀድሞ ግን ኢትዮጵያን መግዛት መቻል ይኖርበታል። ኢትዮጵያ ሲይዝ ደግሞ የታላቁን ወንዝ የጥቁብ ዓባይ ምንጭ ተቆጣጠረ ማለት ነው።

በዓባይ ግብፅን አያይዞም መካከለኛውን ምስራቅ እና የበካርታ አረብ አገራት ግዛቶችን፤ በመቀጠልም የቀይ ባህርን መግቢያና መውጫ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ሲይዝ ቀሪውን ዓለም ያለ ድካም በስሩ ማስገበር እንደሚቻለው ታውቋል።

የአንደኛው የዓለም ጦርነት ከተከሰተበት ወቅት ጀምሮ እንግሊዝ፤ ፈረንሳይ፤ ሩሲያና አሜሪካ እንዲሁም ሌሎቹም በወቅቱ ሀይል የነበራቸው አገሮች ይህንን ክልል በበላይነት ለመቆጣጠር ያላሰለሰ ትግልና ፖለቲካዊ ሽኩቻዎችን አካሂደዋል። አሁንም በዛው እንደቀጠሉ ይገኛሉ።

በዚህ ተጨባጭ ምክያት ነበር ሊዊስ ኢትዮጵያን ቀዳሚ የኢላማው ተመራጭ አገር እንድትሆን ያደረጋት።

  

የማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ምዕራፍ 14

ሰናይት ለሊቱን እንቅልፍ በዓይኗ ሳይዞር አሳለፈች። ካመጣቻቸው ለውጦች መሀከል አንደኛው ነበር። ሌላኛው ደግሞ ማንም ሰው ካለምንም ምክንያት በአትኩሮት እንዲያያት አትሻም። ኮሽታዎችም ያስበረግጓት ጀምረዋል። በእያንዳንዷ ቅፅበት ህሊናዋ ከስህተት የፀዳ ጠንቃቃ ሰው መሆን እንዳለባት ይጠቁማታል።

ይህ ሁሉ ግን ገና የለውጡ የመጀመሪያው ምዕራፍ መሆኑን አላወቀችም ነበር። ረፋዱ ላይ ከሆቴሉ እንደወጣች ያመራችው በመገናኛ መስመር የሚከራይ ቤት ፍለጋ ነበር። ባነጋገረችው ደላላ መሪነት የትራፊክ ፅ/ቤት አካባቢ ሲደርሱ ወደ ቀኝ ታጠፈች። ጥቂት መቶ ሜትሮችን ገባ እንዳሉ ብረት በር የሆነ አንድ ሰፊ ጊቢ ጋር ደርሰው ቆሙና የደውሉን መጥሪያ በመጫን አስከፍተው ገቡ።

እጅግ በተዋበ ሁኔታ የተጠበቀ ይዞታ ነው። ባለቤቷ የሰባ ሁለት ዓመት አሮጊት ሲሆኑ ባላቸው ከሞቱ ዘጠኝ ዓመት ሞልቷቸዋል። የወለዷቸው ስድስት ልጆች በጠቅላላ በአውሮፓና በአሜሪካ ናቸው ያሉት። ወይዘሮዋ የሚኖሩት ከአንዲት የአስራ ስድስት ዓመት የዘመዳቸው ልጅ ጋር ሲሆን ዘበኛና የማዕድ ቤት ሰራተኛም አሏቸው።

በደንጊያ ከተሰራው ቪላ አጠገብ ራሱን ችሎ የተገነባ ሁለት ክፍል ቤት ይታያል። ስልክን ጨምሮ ለስራዋ የሚያሰፈልጉትን ነገሮችን ያሟላ ነበር። ሰናይት እንዳየችው ነው የወደደችው ሳታቅማማ በየወሩ 1350 ብር እየከፈለች ልትገለገልበት ተዋውላ ጨረሰ።

ቀጥሎ ያመራችው ሩዋንዳ ወደሚባለው አካባቢ ነበር። ዋናው ቦሌ ለመድረስ ጥቂት ኪሎ ሜትሮች ሲቀረው ወደ ቀኝ ተገንጥሎ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

900 ሜትር ያህል እንደገባች ጥያቄውን ባካባቢው ላሉ ወጣቶች አቀረበች፡፡
“2000 ብር ይባላል ትከፍያለሽ?” በእድሜ ከሁሉም የሚበልጠው ወጣት መልሶ ጠየቃት፡፡
“እንየዋ.....” ከጥቂት እርምጃዎች የወደፊት ጉዞ በኋላ ዋናው መንገድ አጠገብ የሚገኝ ጊቢን አስከፍተው ገቡ፡፡ ይህም ቢሆን ይዞታው ከቅድሙ ቤት አይተናነስም ነበር፡፡ የቤቱ ባለቤቶች በሌላ ስፍራ ከዚህ ሌላ የመኖሪያ ቤት ስላላቸው ይህንን ሙሉውን በማከራየት ገቢ ያገኙበታል፡፡

ቤቱ ባለ አንድ ፎቅ ሲሆን ከላይም ከታችም ራሳቸውን የቻሉ ሳሎኖችና ሁለት የመኝታ ክፍሎችን እንዲሁም ማብሰያና ባኞን ያካተቱ ናቸው፡፡
“የላይኛው ተይዟል” አለ ወጣቱ፡፡ ቀጠለ “የግልሽ ስልክም አለው”
“ክፍያው የመጨረሻ ነው?”
“እንደውም ቀንሰዋል፡፡ ከዚህ በላይ ነበር የሚከራየው፡፡”

ሰናይት ጥቂት አሰበችና ከፍላ ቁልፉን ተረከበች፡፡

ሶስተኛው ቤት ግን የከተማዋ ማዕከላዊ ስፍራ ላይ እንዲሆንላት ስለፈለገች እውቅና ያላቸው ደላሎች ቢሮ ድረስ በመሔድ ጠይቃቸው በቀላሉ ከብሔራዊ ቲያትር ጀርባ የሚገኘው በድሉ ህንፃ በሚባለው አፓርታማ ውስጥ ልታከራይ ፍላጐት ከነበራት ሰው ጋር አገናኟት፡፡

ክፍሉ የህንፃው አምስተኛ ፎቅ ላይ ሲሆን የመኝታ ክፍሎች ሳሎን ማብሰያና ባኞ አለው፡፡
ደላላው “አከራይሽ አብዛኛን ጊዜ ኢትዮጲያ ውስጥ አትኖርም፡፡ ብትመጣም ከአንድ ክፍል በላይ አትጠቀምም ሙሉ በሙሉ ልትይዥው ትችያለሽ” ሲያወራ ይነፋነፋል፡፡ አጠር ብሎ ኮሳሳ ሰውነት ሲኖረው ገባ ብሎ መሸበት የጀመረው ፀጉሩና አልፎ አልፎ እንደ መጥቆር ካለው ጨምዳዳ ፊቱና ከበለዘው ጥርሱ ጋር ተዳምረው ሀይለኛ ጠጪና አጫሽ መሆኑን ይናገሩበታል፡፡
ሰናይት የሰውዬውን ዝርዝር ሀሳብ አዳመጠችና ተስማማች፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ለሶስቱም ቤት አልጋ፣ ፍራሽ፣ ወንበርና ጠረጴዛን ጨምሮ ለጊዜው የሚያስፈልጉትን ቁሳቁሶች ገዝታ ስታስገባ ዕለቱን አሳለፈች። ያደረችው ግን በሆቴሉ ነበር።

በቀጣይ ዕለት ልታነጋግረው የመረጠችውን ሰው ስም እያሰላሰለች ወደ ስልክ አመራች። የደወለችው መስመር ሲከፈት "እባክዎ አቶ ጳውሎስ ኩንቴን ነበር" አለች።
"ማን ልበል?" ጠየቀ በስልኩ ውስጥ የሚመጣው ድምፅ።
"ሰናይት ነኝ አስታወስከኝ"
ከጥቂት ዝግታ በኋላ "አዎ....."
" እንዴት ሰንብተሻል? "
"ደህና ነኝ"
"ምንድነው ስራውን አቁመሽ ድንገት የጠፋሽበት ምክንያት"
"ያው በዛን ሰሞን መንግስታቹ አላሰራ እንዳለኝ ነግሬህ አልነበረም?"
"አዎ አስታውሳለሁ"
ጥቂት አወሩና ከአንድ ቀን በኋላ በሚመጣው እሁድ ተገናኝተው በሰፊው ለመጫወት ቀጠሮ በመያዝ ተለያዩ።
ጳውሎስ ተወልዶ ያደገው በኢትዮጵያ ደቡባዊ ክልል ሆሳዕና በሚባለው ከተማ ነው። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን እንዳጠናቀቀ ወደ አዲስ አበባ መጥቶ በመምህርነት ሙያ በዲኘሎማ ተመርቋል። ከዛም ወደ ተወለደበት ክልል በመመለስ በማስተማር ሙያ ላይ ተሰማርቶ ለአንድ ዓመት ቆየ።
የ "ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ." እህት ፓርቲ ለሆነው ለ "ደ.ህ.ዴ.ድ." እጩ ተወዳዳሪ ሆኖ ቀረበና በተለያዩ ወቅቶች ለቀበሌ፣ ለወረዳ፣ ለዞን፣ ለክልል እየተመረጠ የእድገት እርከኖችን በማለፍ ለምክር ቤት ተወዳደረ። ተሳክቶለት ለማለፍ በመብቃቱም የክልሉን ህዝብ ወክሎ አዲስ አበባ መጣ።
ሆኖም ግን በውጫዊ አቋሙ የ "ደ.ህ.ዴ.ግ." ፓርቲ አባል ሆኖ ይታይ እንጂ በደቡብ ክልሎች ላይ ለሚንቀሳቀስና መንግስትን ለሚቃወም ሌላ ድርጅት ነበር በድብቅ የሚያገለግለው "ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ." ስልጣን ከጨበጠበት ወቅት አንስቶ በክልሉ ላይ በተለያዩ ወቅቶች

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

በተደረጉት የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የጐላ ተሳትፎ ነበረው፡፡ በኋላ ላይ በሚስጥር በሚያገለግለው ድርጅት አንድ ዕቅድ ተነደፈ፡፡

ዕቅዱ ውስን አባሎችን መንግስትን በሚደግፉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ እንዲሰርፁ በማድረግ ለነሱ እንዲሰልሉ የሚያስችል ነበር፡፡ ለዚህ ስራ ከታጩት መሀከል አንዱ ጳውሎስ ሆኖ ተመረጠ፡፡ ከዛም በድርጅቱ አባሎች የድምፅ ድጋፍ ለመንግስት የቆመ ታማኝ አገልጋይ አስመስለውት ምርጫዎቹን በማጭበርበር እያሸነፈ እንዲያልፍ አስቻሉትና መጨረሻም ላይ የምክር ቤት አባል እስከመሆን ደረሰ፡፡ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. ራሱ ጳውሎስን ትክክለኛ የደ.ህ.ዴ.ግ አባል ነው የሚል የተሳሳተ ግምት ስለነበረው ምርጫዎችን ያለ ችግር በማጭበርበር እያለፈ እንዲጓዝ የመንገዱን ጥርጊያ መንግስት ራሱ አመቻችቶለታል፡፡

እየተመረጠ በቆየባቸው የስልጣን እርከኖች ላይ የሚያውቀው ድረስ ያሉትን የመንግስት ሚስጥሮችን በድብቅ ለሚያገለግለው የተቃዋሚ ድርጅት እያቀበለ የቆየና እስካሁን ለማን እየሰራ እንዳለ ያልተደረሰበት ግለሰብ ነው፡፡

ከሰናይት ጋር የተዋወቁትም በጋዜጣው ላይ በምታትምላቸው ዜናዎች ነበር፡፡ ሰናይት በቀጠሮው መሰረት ከአንድ ቀን በኋላ ወደ ጳውሎስ ቤት አመራች፡፡ የሚኖርበት አካባቢ ወደ ቦሌ በሚወስደው ጐዳና ላይ ወሎ ሰፈር ለመድረስ ጥቂት ሲቀረው በስተግራ በኩል በሚታዩት የኪራይ ቤቶች ድርጅት ንብረት ከሆኑትና አጠገብ ላጠገብ ከተሰሩት ሶስት ረጃጅም ህንፃዎች መሀከል በአንደኛው ላይ ነበር፡፡

የከሰዓቱ ፀሀይ ከዕለቱ የመስራቤቶች ዝግ መሆን ጋር ተዳምሮ እንቅስቃሴዎችን አቀዝቅዞታል፡፡ ሰናይት በዛ ቅፅበት የፓሪስ መንገዶች በህሊናዋ መጡባት፡፡ ያላቸው ትርምስና ወከባ ናፈቃት፡፡ “መቼ ይሆን ተመልሼ የምረግጣቸው?” ስትል ራሷን ጠየቀች፡፡

የህንፃው መግቢያ ጋር ስትደርስ ሰዓቷን አየች 8፡30 ብሏል፡፡ የቀጠሮው ትክክለኛ ወቅት ነበር፡፡ ወደ አሳንሰሩ ገባችና ሰባተኛ ፎቅ እንዲያደርሳት ቁልፉን ተጫነችው፡፡

እንደደረሰችም የጳውሎስን የመኖሪያ ቤት አንኳኩታ በማስከፈት ገባች፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

በፅዳት የተያዘው ቤት እይታን ይማረካል፡፡ ሶፋዎች፣ የመመገቢያ ጠረጴዛ፣ አነስተኛ የሳሎን ቡፌ ከነ ሙሉ ዕቃው በስርዓት ተቀምጠዋል፡፡ ወለሉ ደብዘዝ ያለ አረንጓዴ ቀለም ያለው ቀላል ምንጣፍ ለብሷል፡፡

ጳውሎስ ጋደም ብሎ ጋዜጣ ሲያነብ ከነበረበት ሶፋ ላይ ተነስቶ የሞቀ የወዳጅነት ሰላምታ አቀረበላትና "ተቀመጭ እዚህች ጋር" አጠገቡ ያለውን ቦታ እየጠቆመ ተናገረ፡፡
"ባለቤትህስ?"
"የለችም፡፡ልጆቹን ይዛ ዘመድ ጥየቃ ሄዳለች፡፡"
"ልጆችህ ሁለቱም ደህና ናቸው?"
"አዎ..... ተመስገን ነው፡፡ ሁላችንም ደህና ነን፡፡" አለ ማደግ የጀመረ ፂሙን እየደባበሰ፡፡ ዕድሜው አርባ ሶስት ዓመት ሲሆን አጠር ብሎ ሞላ ያለ ሰውነት አለው፡፡ ጠቆር ብሎ ክብ የሆነ የፊት ገፅታው ላይ ወፋፍራም ከንፈሮቹና ጐረድ ያለ አፍንጫ አለው፡፡ አይኖቹ ጐላ ጐላ ያሉ ሲሆን ከቅንድቦቹና ጆሮ ግንዶቹ መሀከል ቦታ ላይ በሁለቱም በኩል ክብ ጠባሳዎች አርፈውበታል፡፡
"ስራ እንዴት ይዞህል?" ጠየቀች ሰናይት፡፡
"ምኑን ስራ ትይዋለሽ የፖለቲካ ፍልስፍና ትምህርት የሚሰጥበት ኮሌጅ በይው እንጂ!" አለ በምፀት፡፡
"እዛው ምክር ቤት ነው አይደለም ያለኸው?"
"ለስሙማ አዎ....."
"ታዲያ ምኑ ነው ኮሌጅ የመሰለህ?"
"አንዴ አብዮታዊ ዲሞክራሲን ፣ አንዴ ሊበራሊዝም ሲላቸው ቦናፖርቲዝም እያሉ የማይመሳሰሉና አብረው የማይራመዱ የፖለቲካ ፍልፍልናዎችን እየጋቱን ውለን እንመጣለን" አለ እያንገሸገሸው፡፡
"ምንድነው የማያስመስላቸው?"
"የአብዮታዊ ዲሞክራሲን ፅንሰ ሀሳብ የማሌ መዝገበ ቃላት ላይ ፈልገሽ ብታየው ፀረ-ፊውዳል እና ፀረ ካፒታል የሆነውን ትግል የሚደግፉትን የሚያካትት ሲሆን ሂደቱ ወደ ሶሻሊዝምና ብሎም ኮምኒስት እያደገ የሚሔድ መሆኑን ነው የሚያሳየው፡፡
እዚህ ግን አብዮታዊ ዲሞክራሲን እየሰበኩ ካፒታሊዝምን እንገነባለን እያሉ ነው የሚደሰኩሩት፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“ሊበራሊዝምስ?” አለች ሰናይት በጳውሎስ ስሜት ፈገግ እየተሰኘች፡፡
“ሊበራሊዝም “የፖለቲካ ንድፈ ሀሳብ ታሪክ” በሚለው መፅሀፍ ጆርጅ ኤች .ሳቢን ትርጉም ሲሰጥ ሊበራሊዝም ለለውጥ የተመቸ ነገር ግን ስር ነቀል ለውጥን የሚቃወም በወግ አጥባቂነትና በሶሻሊዝም መካከል ላይ የሚገኝ የፖለቲካ አቋምን ለመግለፅ የሚጠቅም ነው፡፡ እያለ ይቀጥልና “ስርዓቱ ስልጣንን የእድሜ ልክ ንብረታቸው እዲያደርጉ ልዩ መብት የተሰጣቸው ፓርቲዎች ያለመኖራቸውን ሀቅ ከልብ መቀበልን፤ የተደራጀ ተቃዋሚ መኖር የሊበራል መንግስት አስፈላጊ አካልና ስልጣንንም ለመጠበቅ የሚጠቅም ብቸኛውና ህጋዊ መንገድ መሆኑን መረዳት ይጠይቃል..... ከሁሉም በላይ ለህዝብ ጥቅም መከበር የራሱን ህብረት ፈጥሮ ኃላፊነቱን ለመወጣት ጠንካራ መንፈስ ያለው ማህበረሰብን ይጠይቃል ይላል መፅሀፉ፡፡

ቀጠለ “ይህን ደግሞ የሚጠቀሙበት ምዕራባውያኖቹና በካፒታሊዝም ርዕዮተ-ዓለም የሚተዳደሩት ሀያላን አገሮች ናቸው፡፡ በኛ አገር የምታየው የተቃረኑ ርዕዮተ-ዓለም ፍልስፍናዎችን ይዘው በአንድ አቅጣጫ ለማስኬድ እንደ አመቺነታቸውም ከአንዱ ወደ ሌላው እንደፈለጉ እየተገለባበጡ ህዝብንና ያልገባውን ሁሉ እያደነጋገሩ ስልጣናቸውን ለማራዘም የሚያደርጉት አስቂኝ የብልጣብልጥ ስራ ነው፡፡” አለ ጳውሎስ፡፡ “ገጠመኞችን አሁን ደግሞ ቦናፓርቲዝም የሚባለውን ይዘውልን መጥተዋል”
“የሱ ፅንሰ ሀሳብ ደግሞ ምንድነው?” ጠየቀች ሰናይት፡፡
“ይህንንም የማሌ መዝገበ ቃላት ላይ ፈልገሽ ብታይው ለካፒታሊዝም ርዕዮተ-ዓለም ዕድገት የሚሰራ ቢሆንም ፀረ-አብዮትና ፀረ-ዲሞክራሲ መሆኑን ይገልፃል፡፡ በዛ ላይ ሰፊው ህዝብ ከካፒታሊዝም በላይ ተሻግሮ እንዳይሂድ፤ ካፒታሊዝም ሊደርስ ወደሚችልበት ከፍተኛ ጫፍ እንዳይጓዝ ለመግታት የቆመ ሀሳብ ነው ይላል፡፡ በውስጡ እጅግ የተበላሹ አሰራሮችን አጠቃሏል..... ለምሳሌ ጉበኝነት፣ የወገንተኝነትን አሰራር፣ ስልጣንን ለሌላው ያለማካፈልን ሁሉ ጨምሮ የያዘ ነው፡፡
“ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. እና ጀሌዎቹ ፓርቲዎች በእርግጥ ቦናፓርቲዝም አይደለንም ቢሉም ስላለመሆናቸው ግን ከራሳቸው አፍ የሚወጣውን የምስክርነት ቃላቸው በስተቀር ምንም ማስረጃ ማቅረብ አይችሉም፡፡”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“ለምን?” ጠየቀች ሰናይት፡፡
“ምክንያቱም በፓርቲዎቹ ውስጥ በተለይ በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. ገደብ የለሽ ጉበኝነት፣ የብሔር ትምክህተኝነት፣ በስልጣን መባለግ፣ እንዲሁም ስልጣንና ሀገርን የህዝብ ሳይሆን የራስ ብቻ አርጐ የማሰብና የመጠቀም ብልሹ አሰራሮች በእጅጉ ተንሰራፍቶባቸዋልና ነዋ”
“በሚገርም ሁኔታ አንተ ራስህ የፖለቲካዊ አስተሳሰቦችህ በእጅጉ እየዳበሩ ሄደዋል፡፡”
“ሌላ የሚሰራ ስራ የለማ!..... ነጋ ጠባ ስለ ርዕዮተ-ዓለም ፍስልፍናዎች ንትርክ ብቻ ነው ያለው” አለ ጳውሎስ፡፡
“ይልቅ ያኖው የምትታገልለት የድብቅ ድርጅታችሁ እንቅስቃሴ ምን ላይ ደርሷል?”
ጳውሎስ አቀረቀረ፡፡ ለደቂቃዎች በዝምታ ተውጠ ቆየናም “ወደ መፈራረሱ እየተቃረበ ነው” አለ በዝቅተኛ ድምፅ፡፡
“ለምን?”
“ድርጅቱ ከተወሰኑ ዓመታት በኋላ እድገት ሊያመጣ አልቻለም፡፡ ባለበት ቆሞ ቀረ፡፡”
“እና በቃ?”
“አስቀያሚ ገጠመኞቹማ አላበቁም፡፡” ቀጠለ “አባሎች መክዳት ጀመሩ፡፡ ከድተውም አርፈው አልተቀመጡም ቀሪዎቹንም እየጠቆሙ በማስያዝ በደቡብ ኢትዮጵያ የተለያዩ ቦታዎች የነበሩ በርካታ አጋሮቻችንን አሳፍነው አስገደሉብን” በአይኖቹ እምባ እየተሞላ ቀጠለ “.....አሁንም ውስኖች የሞራል ውድቀት እየደረሰባቸው ስለሆነ መበታተናቸውን እያባባሱት ሄደዋል፡፡” አለ፡፡
“እንቅስቃሴያችሁን ማሳደግ ያልቻላችሁበት ምክንያት ምንድነው ብለህ ታምናለህ?”
“የአቅም ማነስ.....”
ሰናይት አቋረጠችውና “ገንዘብ ማለትህ ነው?”
“አዎ..... እና መሳሪያ”
“የድርጅታችሁ መሪ ዓላማ ምን ነበር?”
“ይህን የወያኔን መንግስት ማውረድና ለክልላችንም ሆነ ለኢትዮጵያ እድገት የተሻለ አቋም ያለውን ስርዓት መፍጠር ነበር ጨነገፈ እንጂ.....”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“አልተጨናገፈም፡፡ ሆኖም ግን በዓላማችሁ ላይ ትንሽ ማሻሻያ ማከል ከቻላችሁ እቅዳችሁን ዳር የማድረስ እውነታ እውን ይሆናል ብዬ አምናለሁ፡፡” ሰናይት ቀስ እያለች የጳውሎስን ስሜት እያጠናች ተናገረች፡፡
ጳውሎስ እይታውን ከወለሉ አንስቶ ወደ እሷ እየመለሰ “ምን ዓይነት ማሻሻያ?”
“ማለት..... በራሳችሁ ክልል መንግስት የመመስረት ሁኔታ..... ተገንጥላችሁ ወጥታችሁ.....” ቃላቱን እየጎተተች ተናገረች፡፡
“እሱማ እንዴት ሊሆን ይችላል?..... በጣም አስቸጋሪ ነው”
“እስኪ ከአንድ ሰው ጋር ላገናኛችሁና ተነጋገሩ፡፡ በሀሳብም በሌላም በሌላም እርዳታ እጅግ ሊጠቅማችሁ የሚችል ነው ብዬ አስባለሁ፡፡” አለች፡፡
“ምን ዓይነት ሰው?”
“ፈረንሳዊ ፕሮፌሰር ነው፡፡ እዛ እንተዋወቅ ነበር፡፡ ስለ ደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ሁልጊዜ በቅናት ሲናገር እሰማዋለሁ፡፡”
“በትክክል ጠቃሚ ነው ብለሽ ታምኛለሽ?”
“አዎ.....”
“በኋላ ደግሞ ለዚህ መንግስት የሚሰልል እንዳይሆንና እንዳያጋልጠኝ” አለ ጳውሎስ በጥርጣሬ፡፡
“የኔን ያህል..... ከዛም በላይ ልታምነው የሚገባ ሰው ነው፡፡”
“ጥሩ.....” ሙሉ አመኔታ በሌለው ስሜት መለሰላት፡፡
“መቼ ላገናኛችሁ?”
“እ..... ሰሞኑን ከአስራ አንድ ሰዓት በኋላ በማንኛውም ቀን ሊሆን ይችላል”
“ነገ?.....”
“እ..... ነጌ አይመቸኝም”
“ከነገ ወድያ? ”
“እሺ ..... ግን ቤት ባይሆን ይመረጣል፡፡”
“ምንም ችግር የለውም፡፡ በአንድ ሆቴል ቀጠሮ አሲዘውና አንተን ደውዬ አሳውቅሀለሁ”
ተስማሙና ጭውውታቸውን ተራ ወደሆኑ ዕለታዊ ጉዳዮች ለወጡት፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

«««««« »»»»»»

በቀጣዩ ቀን ከሰዓት በኋላ ነው። ጳውሎስ ከስራ እንደተመለሰ በዕለቱ ስለያዘው ቀጠሮ በህሊናው ማሰላሰል ጀመረ። ወደ መኝታው አመራና አረፍ ማለት ፈለገ። ግን ሊያሸልበው የሚችል ሰላም አላገኘም 'ሊያሲዙኝ ቢሆንስ? በዚህ ዘመን የትኛው ሰው ሊታመን ይችላል ?' በማለት ለራሱ በርካታ ጥያቄዎችን አቀረበ።

ሆኖም ግን ከቀጠሮው የሚያስቀረው የውስጣዊ ግፊቱ ሊያሸንፍ አልቻለም። ተነስቶ ልብሱን አጠላለቀና ከቤት ወጣ። ከመስቀል አደባባይ ፊት ለፊት በሚገኘው አነስተኛ ቁርስ ቤት ነበር የቀጠሮው መገናኛ ስፍራ። ቦታው ሲደርስ ጥቂት ደቂቃዎች ቀደም ብሏል። ልክ 12፡45 ሲል ሁለት ሰዎች የመጡበትን መኪና ከኢትዮጵያ ቱሪዝም ኮሚሽን ዋና መስሪያ ቤት ህንፃ በስተ-ቀኝ በኩል አቁመው ወደ ቁርስ ቤቱ ሲመጡ አየ።

ገብተው እሱ ወዳለበት ጠረጴዛ ሲደርሱ ሰናይት "እንደምን ዋልክ አቶ ጳውሎስ?" እጇን ለመጨበጥ እየዘረጋች ሰላምታ ሰጠችው።

እንደመነሳት እያለ "እግዚያብሔር ይመስገን ደህና ዋላችሁ?" ጥርጣሬና ፍርኃት በተላበሰ ቅላፄ መልስ ሰጠ።

"ይህ ሰው ከትላንትና በስትያ ላስተዋውቅህ ያልኩህ ፈረንሳዊ ፕሮፌሰር ጆፍሪ ይባላል።"

"እሺ ጳውሎስ እባላለሁ" በእንግሊዝኛ ራሱን አስተዋወቀ።

ፈረንሳዊው እድሜው ሀምሳ ሶስት ዓመት ሲሆን ከንፃቱ የተነሳ በፊቱ ቆዳ ውስጥ ያሉት የደም ስሮች አዥጉርጉረውት ይታያሉ። አመድማ ቀለም ያለው ፀጉሩን በጥቂቱ አስረዝሞታል። ዘለግ ባለ ቁመናው ላይ የሚመጣጠነው ሰውነት አለው። ደብዘዝ ያለ ወይን ጠጅ ቀለም ያለው ሙሉ ሱፍ ለብሷል።

ሁለቱም ወንበር ስበው ተቀመጡ። ስለ ዕለቱ አዲስ ገጠመኞቸው በእንግሊዝኛ ጥቂት አወሩና ምሽቱ አንድ ሰዓት ሲሞላ "እራት የት እንብላ..... እግረ መንገድ እዛው እንነጋገራለን" አለች ሰናይት።

"ያልተለመደ ሆቴል ቢሆን ይመረጣል።" አለ ጳውሎስ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ሁለቱም ጥያቄያዊ አስተያየት ሲሰነዝሩበት ቀጠለ "እይታ ውስጥ እንዳንገባ ለመጠንቀቅ ያህል ነው። ታዋቂ ወደሆኑ ሆቴሎች ብናመራ አንዱ የዚህ መንግስት ሰላይ ሊያየኝ ይችላል። ይህ ደግሞ ከናንተ ይበልጥ ለኔ አደገኛ ነው የሚሆነው።"

ተስማሙ። ፈረንሳዊው ምርጫውን ለሱ እንዲሰጡት ጠየቀና አሮጌው አውሮኘላን ማረፊያ አካባቢ በሚገኝ አንድ የውጭ አገር ምግብ ቤት ይዞዋቸው ሄደ።

ቤቱ ባለ አንድ ፎቅ ጥንታዊ ስራ ሲሆን የአካባቢው ጠቅላላ ድባብ ፀጥታንና እርጋታን የተላበሰ ነበር። ፎቁ ላይ በሚገኙና ለነጠላ እንግዶች ከተዘጋጁት ክፍሎች መሀከል ወደ አንደኛው ገቡ። ደብዘዝ ያሉ አምፖሎች ቁልቁል ይፈነጥቃሉ።

መሀከል ቦታ ላይ የሰፈረውን ጠረጴዛ ዙሪያ ከከበቡት አራት ወንበሮች ሶስቱም የየራሳቸውን ስበው ተቀመጡ።

እየመራ ያደረሳቸው አሳላፊ እጁን ወደ ኋላ እንዳደረገ በአክብሮት ዝቅ ብሎ ምግብ መምረጫ ዝርዝሩን የጠረጴዛው መሀከል ላይ አስቀመጠው።

ሰናይት ሁለቱንም በየተራ እያየች "ጥቂት ብንቆይ ምን ይመስላችኋል?" ተስማሙ። "እስከዛው ወይን እንዘዝ....." ብሎ ወደ አስተናጋጁ እያየ "አንድ ጠርሙስ ጥሩ የሚባለውን የአገር ውስጥ ወይን ብታመጣልን?" በእሺታ አጎንብሶ ወጣ።

"እስከዛው ድረስ እንደውም ሁለታችሁ መነጋገር ትችላላችሁ" አለች።

ጳውሎስ ጥርጣሬው አለቀቀውም። አየር በረዥሙ ሳበና ወደ ፈረንሳዊው ዞሮ "እየተሰለልኩ ስላለመሆኔ ማሰረጃ ብታቀርብልኝ?" አለው የቀልድ በሚመስል ግን ባልተረጋጋ ቅላፄ ።

"ጊዜ ያለፈበት ጥያቄ አይመስልህም?" ፈገግ እያለ መለሰለት።

"ማለት?"

"ለዚህ መንግስት የምሰራ ቅጥረኛ ብሆን ኖሮ ከሰናይት ጋር የነበረህን ግንኙነት ማወቄ ብቻ በቂ ስለሆነ ነዋ!"

ፈረንሳዊው ቀጠለ "በጣም ተጠራጣሪ ሰው ነህ"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. የስለላ መረብ ቀላል እንዳይመስላችሁ፡፡ በየት በኩል እንደሰረጉባችሁ ሳታውቁት ነው አናታችሁ ላይ እንደ ፀጉር ተባይ ተሰግስገው የምታገኟቸው.... በዛ ላይ ዛሬ የአገሪቷን የአመራር ቦታ ለመጨበጥ የበቁት ትላንት እንደኛ ካሉ አንድና ሁለት ሰዎች ተነስተው ነው..... ስለዚህም በነገሮች ላይ ሊኖረን የሚገባው ጥያቄ እነሱ ካለፉበት ሚስጥራዊ አካሄድ የላቀ መሆን አለበትና ነው” አለ ሊያሳምናቸው እየጣረ፡፡

“ተጠራጣሪ መሆንህ አይጠላም፡፡ ብዙ ጊዜ ጥርጣሬ ጥንቃቄን ይወልዳል” አለ ፈረንሳዊው፡፡

“ጥሩ ከተማመንን ወደ ዋናው ጉዳይ መግባት እንችላለን” ጳውሎስ እየተመቻቸ ተናገረ፡፡

ጆፍሪ ከሉዊስ ተቋም ተልኮለት ሲያጠናው የሰነበተውን ምርጥ ሴራ እኔነትን አላብሶት መተረክ አልፈለገም፡፡ ምክንያቱም የክልል ቦታዎችን የሚመለከት መስቀለኛ ጥያቄ ከጳውሎስ ቢቀርብበት መመለስ እንደማይችል ቀድሞ ስለተረዳው ነበር፡፡ ለሱ ደግሞ የተላከለት ሴራ ላይ የራሱን ፈጠራ አክሎበት በመዘጋጀት ከየት መጀመር እንዳለበት ሲያስብ ቆየና ቀጠለ፡፡

“በኢትዮጵያ ደቡብ ክልል ላይ አራት አመታት ቆይቶ ትልቅ ነገር የሰራ አንድ የታሪክ ኘሮፌሰር ጓደኛ ነበረኝ.....” አለና በሀዘን ድምፁን እያሰለለ “ከስድስት ወር በፊት ግን በሀይለኛ የአጥንተ ካንሰር ህመም ሲሰቃይ ቆይቶ በኋላም አረፈ፡፡” አለ፡፡

ከደቂቃ ዝምታ በኋላ ቀጠለ “ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ሲኖር በአካባቢው ስላሉት ህዝቦች የስነ-ባህል ክምችት ለሽልማት ያደረሱትን በርካታ ጥናታዊ ፅሁፎች አዘጋጅቶዋል፡፡ ከነዛ ስራዎቹ በተጨማሪም በክልሉ ላይ ከአፄዎቹ ገዢዎቻቸው ጀምሮ እስካሁን ድረስ በሚመሯቸው መንግስት ህዝቡ እየደረሰበት ያለውን ግፍና መከራ ሰፊ ጥናት ያካሄደበትን በማስረጃ የተደገፈ የፅሁፍ ስራውን አጠናቆ ለህትመት ሊያበቃው ሲል ነው ያረፈው፡፡ ያንን ረቂቅ ደጋግሜ አንብቤዋለሁ፡፡” ጳውሎስ እይታውን የፈረንሳዊው አፍ ላይ እንደተከለ ያዳምጣል፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ቀጠለ"..... በሰሜኑ ካሉት የኢትዮጵያ ክልሎች ሁሉ ደቡቡ ከሌሎቹ የአፍሪካ አገሮች የተቀራረበ የአኗኗር፣ የአለባበስ፣ የአመጋገብ፣ የአጨፋፈር፣ የቋንቋ በአጠቃላይ የማህበራዊና ጂኦ.ፖለቲካዊ ትስስር ያለው ህዝብ መሆኑን ገሀድ አውጥቶታል። ይህም የበርካታ አውሮፓዊ ምሁሮችን እምነት ወዴት የወሰደው መሰለህ....." ንግግሩንም ቆም አድርጐ ቀጠለ..... "ደቡቡ የኢትዮጵያ ክልል በአፄዎቹ ስርዓት ወቅት በጉልበት ወይም በቅኝ ግዛት ኢትዮጵያ ወደተባለችው አገር እንዲጠቃለል ተደረገ እንጂ ራሱን የቻለ አንድ ታላቅ አገርና ህዝብ ነበር ወደሚለው ነው" አለ።

ጳውሎስ እንደተመሰጠ ለቅፅበት የሆነ ሀሳብ ውልብ አለበትና "ላልከው ነገር በተጨባጭ የምታቀርብልኝ ማስረጃ ይኖርብህል?" አለው።

"አዎ....." ፈረንሳዊው በልበ ሙሉነት መናገሩን ቀጠለ ".....ሰሜኑ ኢትዮጵያ የነበረው የስልጣኔ ታሪክ የሶስት ሺህ ዓመታት ይመስለኛል"

ጳውሎስ በአዎንታ ጭንቅላቱን ነቀነቀ።

"ደቡብ ክልል ግን የአስራ አምስት ሺህ ዓመታት ታሪክና ስልጣኔ ያለው አገር እንደነበር በአውሮፓ ውስጥ በታላላቅ የታሪክ ተመራማሪዎች ህብረት እየታተሙ ባሉት በርካታ መፅሀፎች ላይ መገለፅ ከጀመረ ቆይቷል። አንዱና ተጨባጩ ማስረጃ ይህ ነው"

"የአስራ አምስት ሺህ አመታት ታሪክ!?" በአድናቆት ተናገረ

"አዎ....."

"ታዲያ ያንን ስልጣኔ ምን ሰወረው?"

"ካሁን በኋላ ከክልሉን ምሁሮች የሚጠበቀው ትልቁ ስራ እሱ ነው። ያ ስልጣኔና ታሪክ ለምን ሊጠፋ እንደቻለ የረቀቀ ምርምርና ጥናት ያስፈልገዋል። ያንን እውነታ ሊያረጋግጡ የሚችሉ የአርኪኦሎጂስቶች ማስረጃዎች እየተቆፈሩ መውጣት አለባቸው ለሱ ደግሞ ክልሉ ከኢትዮጵያ ተገንጥሎ ራሱን የቻለ መንግስት መመስረት በዋናነት እንዲሁም የተማረ ሀይልና ገንዘብ ያስፈልገዋል" አለ ጥንቃቄ በታከለበት ተቆርቋሪ መሰል ስሜት ተውጦ።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“በእርግጥ ገንዘብ ቢኖር ይህ ታሪክ ሊወጣ ይችላል?” ጳውሎስ በጉጉት ጠየቀ፡፡
“በሚገባ ነዋ.....” የማጥመጃ ዕቅዱን መተንተን ቀጠለ፡፡
“ሀብትም ቢሆን እኮ ክልሉ ከየትኛውም የኢትዮጵያ ግዛቶች የበለጠ ክምችት አለው፡፡ ግን ወደ ገንዘብ ያልተለወጠ፡፡”
“እንዴት?”
“የስነ-ተፈጥሮ ሀብቱ ድንቅ ነው፡፡ አካባቢውን አምላክ አስቦበት የፈጠረው ይመስላል፡፡በከፍተኛና በበርካታ ማዕድናት የታመቀ ነው፡፡ ለምሳሌ ኘላቲኒየም፣ ወርቅ፣ ታንታለም፣ ጠገራ፣ ብረት እና ሌሎችም ዝርዝራቸውን የማላስታውሳቸው ክምችቶች ይገኝበታል፡፡”

“የሚገርምህ ይህ ሁሉ ሀብት ሊወጣ ቢችል ልክ እንደ አረብ አገር ግዛቶች ሁሉ የራሱን የደቡብን ህብረተሰብ እስከ ልጅ ልጆቻቸው ድረስ ሳይሰሩ ግን በቅንጦት ሊያኖራቸው በቻለ ነበር፡፡” በቁጭት ተናገረ፡፡ በቅፅበት ስሜቱ ጳውሎስ ላይም ተላለፈና እየተንገበገበ ጥርሱን ነከሰ፡፡
ቀጠለ ፈረንሳዊው “.....መሬቱ ለም ነው፡፡ ከምግብ ሰብሎች በተጨማሪ ከፍተኛ መጠን ያለው የቡናና በዓለም ላይ ተቀባይነት በማግኘት በርካታ ገንዘብ እንዲዘዋወርበት እያስቻለ ያለው የጫት ምርት ይበቅልበታል፡፡ በአጠቃላይ ከኢትዮጵያ አስር በመቶ ብቻ ስፋት ያለው ይህ ክልል ዛሬ ለኢትዮጵያ አከርካሪ በመሆን ወደ ሰባ ሚልዮን ሊጠጋ የተቃረበውን የአገሪቷን ህዝብ ኑሮ ቀጥ አድርጐ የያዘላት ደቡብ ምድር ነው እስከማለት ተደርሷል፡፡”

“የዛ ክልል ህዝብ ግን ዛሬም ጐስቋላ ነው፡፡ ትምህርት ቤት የለው፤ ሆስፒታል የለው፤ መንገድ የለው፤ መብራት የለው፤ ..... የተፈጥሮ ሀብቱን ግን ከአፄዎቹ ጀምሮ ዛሬ ድረስ በግልፅ ይበዘበዛል፡፡ በዛ ላይ በኢትዮጵያ ውስጥ ሌላው ብሔር በሚታይበት ዓይን ሳይሆን በበታችነት ነው የሚገኘው፡፡ ቋንቋው፣ ባህሉ፣ አመጋገቡ፣ አለባበሱ፣ ማህበራዊ ኑሮው በጠቅላላ የተናቀ ነው፡፡..... ስለነዚህ ጉዳዮች ጥናት አደረገበት ያልኩህ ኘሮፌሰር ጓደኛዬ ሲናገር በሀዘንና የእንባ ሲቃ እየተናነቀው ነበር፡፡” አለ ጆፍሪ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ጳውሎስም ሳያስበው አይኖቹ ውስጥ ያቀረዘዙት እንባ በጉንጮቹ ላይ እየተሸኳለሉ ወረዱ፡፡
"የምትለው ሁሉ ትክክል መሆኑን ሁላችንም እናውቃለን አቅም አጥተን ነው እንጂ!" ጳውሎስ በእልህ ተናገረ፡፡
"እና ያ ያልኩህ ጓደኛዬ ህመሙ ከተገመተው ፈጥኖ በአካሉ ተሰራጨና ሊሞት ሲቃረብ አንድ ትልቅ ቃል አስገባኝ....." አለ ፈረንሳዊው
"ምን?" አለ ጳውሎስ በጉጉት፡፡

"ይህች ደቡባዊ ክልል ኢትዮጵያን በጫንቃዋ ላይ ባትሸከም ኖሮ ዛሬ ትልቅ ደረጃ ላይ በተገኘች ነበር አለኝ፡፡ ትክክል ነው፡፡ ከጥቂት ግዜ በኋላም ራሷን የቻለች ነፃ መንግስት ብትሆን በአጭር ግዜ ሀያል ልትሆን እንደምትችል ነግሮኛል፡፡ ለዛም ሲል የክልሉን ነፃነት የሚደግፉ መንግስታቶቻችን በአውሮፓና በአሜሪካ ግዛቶች እየተዘዋወረ ለማሰባሰብ በትልቅ እቅድ ላይ እንዳለ ነበር በሽታው ፀንቶበት ያስተኛው.....
"እና ወደ ሞቱ አፋፍ መቃረቡን ሲረዳ ማስረጃዎቹን በጠቅላላ ለኔ ሰጠኝና እሱ የጀመረውን በጐ ግብ ለፍፃሜው እንዳደርስለት ቃል አስገብቶኝ አለፈ" አለ ረገብ ባለ ንግግር፡፡

ለደቂቃዎች በዝምታ ቆዩ፡፡ በኋላም "ታዲያ ምን አሰብክ?" ጳውሎስ ጠየቀ፡፡
"እኔማ በክልሉ ላይ አብሮኝ የሚሰራ ሰው እስካለ ድረስ የገባሁት ቃል ለማሳካት ያለኝን ፍላጐት ለሰናይት ስነግራት ነበር አንድ የማውቀው ሰው አለ ላገናኛችሁና ሀሳቦችን ተለዋወጡ ብላ ካንተ ጋር እንድንተዋወቅ ያደረገችው....."
ጳውሎስ ወደ ሁለቱም በየተራ እያየ "በእውነት አምኛችኋለው፡፡ አንቺ ደግሞ ከማንም በላይ የኛ ታማኝ ሰው መሆንሽ ይበልጥ ዛሬ አረጋግጫለሁ አለ፡፡"
ሰናይት ቀጠለች ".....የደቡብ ብሔረሰቦች ከኢትዮጵያ ተገንጥለው ራሳቸውን የቻሉ ነፃ መንግስት መሆናቸው ከላይ ካነሳናቸው በርካታ ሁኔታዎች አንፃር የሚጠቅም እንጂ የሚጐዳቸው ያለመሆኑን ነው እኔም በግሌ ያመንኩትና ሁለታችሁን ለማገናኘት የወሰንኩት" አለች

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ጳውሎስ በተረጋጋ ሁኔታ "እስኪ ..... ሁኔታውን አብረውኝ ለሚሰሩት የድርጅታችን አባሎች አሳውቅና አዲስ እቅድ እንዲነድፉ አስደርጋለሁ፡፡"
"ጥሩ..... በቅርቡ ወደ ፈረንሳይ ስለምመለስ መልሱን ቶሎ አሳውቁኝ"
"እሺ አዲስ አበባ የሚገኙትን ዛሬ ለሊት አነጋግራቸዋለሁ፡፡ በየክልሉ ላይ ያሉትንም.....እ..... ያም ሆነ ይህ በሁለት ሶስት ቀን ውስጥ የምንደርስበትን ነጥብ ለሰናይት እነግራታለሁ" አለ ጳውሎስ፡፡

ቀስ በቀስ የጭውውታቸውን ርዕስ አሁን በአገሪቷ ውስጥ ስላለው የተበላሸ ፖለቲካዊ ስርዓት ለወጡና በአመራር ስፍራዎች ላይ ስላሉት የ "ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ" ከፍተኛ ባለስልጣናቶች ግለ-ታሪካቸው ላይ መነጋገር ጀመሩ፡፡
በዚህ መሀከል ጳውሎስ "እረ..... ይልቅ" ብሎ የሁለቱንም ትኩረት ወደ ራሱ መለሰና ".....በ1994 ታህሳስ ወር ገብቶ ጥቂት ቀናት እንዳለፉ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ከፍተኛና ልዩ አማካሪ የግል ቢሮ ውስጥ ሶስት ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ሚስጥራዊ የሆነ ስብሰባ ሲያካሂዱ የተነጋገሩትን ንግግር በቴኘ ካሴት የተቀዳ አግኝቼ ነበር፡፡" አለ፡፡
"ምን የሚል!?" ሰናይት ቀድማ ጠየቀች፡፡
"በረሃ በትግል ላይ እያሉ ትግራይንም እንደ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ለማስገንጠል እቅድ እንደነበራቸውና አሁን ግን ምክንያቱን በደንብ ባላብራሩት ሁኔታ እንዲቆይ እንዳደረጉት የሚገልፅ ነው፡፡ ለኔ ብዙም ግልፅ አልሆነልኝም፡፡ ከነሱ መሀከል ግን ይህን ሚስጥር የሚያውቅ ሰው ከድቶ እንደተሰወረባቸውና አሁን በዋሺንግተን ሆኖ ትግራይን በማስገንጠሉ አላማው እንደሚገፋበት የሚገልፅ መረጃ የደረሳቸው መሆኑን ነው የሚወያዩበት፡፡"

ቀጠለ "ምናልባት ወደ ተግባር ከገባ ለነሱ ችግር የሚፈጥርባቸው ጉዳይም እንደሚከሰት ስላመኑ ያ ከመሆኑ በፊት ሊያስቆሙት ይመስለኛል ውይይቱን ያደረጉት" አለ፡፡
"ካሴቱን እንዴት ልታገኘው ቻልክ?"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

“በዕለቱ የጠዋት ስራችንን ጨርሰን ለምሳ ወደ ቤት ልናመራ ስንወጣ መንግስት ለኔ ከሾፌር ጋር መድቦልኝ የነበረው መኪና ለድንገተኛ ስራ መሔዱ ተነገረኝ፡፡ ከዛም ሾፌር የሌለው መኪና ተግኝቶ ስጠየቅ ራሴ እየነዳሁት መሄድ እንደምችል አስረድቼ ጉዞ ጀመርኩ፡፡ በማምራት ላይ ሳለሁ ዘፈን መሰማት ፈለኩና ቴፑን ስከፍት አሁን ያልኩህ ውይይት የተቀዳበትን ካሴት ውስጡ ስለነበረ አደመጥኩት፡፡ በቀጥታ ወደ ሙዚቃ ቤት አመራሁና ቅጂ አሰርቼ በመውሰድ ዋናውን እንዳገኘሁት ተውኩት፡፡

ምሳ ደርሼ ስመለስ መኪናውን ለፈቀደልኝ የትራንስፖርት ክፍል ሀላፊው በሰላም አስረከብኩት፡፡ በኋላም መኪናውን አዘውትሮ ማን እንደሚጠቀምባት በሚስጥር ሳጣራ ከ “ህ.ወ.ሀ.ት” ከፍተኛ ባለስልጣናቶች መካከል አንዱ ሰው መሆኑን አወቅሁኝ” አለ፡፡
“እባክህ ሰምቼው ልመልስልህ?” ሰናይት ጠየቀች፡፡
“በፈለግሽው ሰዓት መውሰድ ትችያለሽ፡፡ እንደውም እንደወጣን በዚሁ ወደ ቤት እናምራና ውሰጅው፡፡”
“አመሰግናለሁ” አለችና ለጉዳዩ ብዙም ትኩረት ያልሰጠችበት በማስመሰል “በጣም እርቦኛል” አለች፡፡

ሰዓቱ ሶስት ለመሙላት ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ ነበር የቀረው፡፡ አሳላፊውን ጠርተው እራት አዘዙ፡፡

  

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

ምዕራፍ 15

ከፍተኛ ጥበቃና ቁጥጥር በሚካሄድበትና ዋናው የጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ የሚገኝበት ህንፃ ላይ ቢሮ ካላቸው ከፍተኛ የህ.ወ.ሐ.ት. ባለስልጣናት መካከል አንዱ የሆነው ተክለአይ እየተጣደፈ ቢሮውን ከፍቶ ገባ።

እንዲሁም ሁለት የፓርቲው ማዕከላዊ ፖሊት ቢሮ አባልና በአገሪቷ በከፍተኛ የስልጣን ቦታ ላይ የሚገኙ ግለሰቦች በተክለአይ በተላከላቸው ትዕዛዝ መሰረት ፈጥነው ወደ እርሱ ቢሮ እያመሩ ነበር።

የተክለአይ ቢሮ ውስጣዊ ውበት የማንንም ሰው ትኩረት የመማረክ ሀይል አለው። የወለሉ ምንጣፍ፤ በግራና በቀኝ የሚገኙት ውድ የቢሮ እቃዎች እንዲሁም የእንግዶች መስተናገጃ ወንበርና ጠረጴዛዎች በጥበበኛ ባለሞያ የተሰሩ ከፍተኛ ዋጋ የፈሰሰባቸው መሆናቸውን ይናገራሉ።

ተክለአይ ያንን በመሰለ ሰፊ ቢሮ መካከል ውሃ ውስጥ የገባች አይጥ ይመስል ወንበሩ ላይ ኩርምት ብሎ ተቀመጠ። ያልተጠበቀ ድንገተኛ ነገር ሲከሰት ሁሌም ይሸበራል። ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጋር እጅግ የጠበቀ ግንኙነት ያለው ሲሆን በአመለካከትም ሆነ በድርጊቱ እንዲሁም በአካላዊ አቋሙ በጣም የሚመሳሰል በመሆኑ የቅርብ ጓደኞቹ «መንትያው ሚኒስትር» እያሉ ይጠሩታል። ለገዢው ፓርቲ እጅግ ታማኝ ከሚባሉት መካከል አንዱ ሲሆን የዛኑ ያህል ለህግ የማይገዛ ስልጣኑን ባሻው መንገድ የሚጠቀም ሰው ነው። የጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ ሳይቀር ከታጠቀው ሽጉጥ ጋር ሳይፈተሽ መግባት የተፈቀደለት ሰው ነው።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ዋና ስራው በአገር ውስጥም ይሁን ከአገር ውጭ ስልጣን ላይ ያለውን የህ.ወ.ሐ.ትን ፓርቲ ከማንኛውም አስጊ ሁኔታ መጠበቅ ሲሆን በተሰጠው ገደብ የለሽ ስልጣኑ የአገሪቷን የደህንነት መስራቤትንና የፖሊስ ተቋምን ያዛል። እንዲሁም በራሱ ቢሮ ስር የተደራጁ የራሱ የደህንነት አባላቶችን በዋናነት ይመራል።

የተክለአይን ስራ በተባባሪነት የሚመሩና በፍጥነት የሱ ቢሮ እንዲገኙ ጥሪ የተደረገላቸው ሁለቱ ሌላ ባለስልጣናት እኩል ደረሱ። እንደዚህ አይነት ድንገተኛ ጥሪ የሚደርሳቸው በጣም አሳሳቢ ሁኔታ ሲፈጠር ብቻ እንደሆነ ያውቃሉ። እነሱም እንደ ተክለአይ ለረጅም አመታት ከበረሀው ትግል ጀምሮ አብረው የተጓዙ ባልደረቦቹ ነበሩ።

" ዛሬ ደግሞ ምን አዲስ ነገር መጣ?" ሀጎስ በተሰላቸ ቅላፄ ነበር ጥያቄውን ያቀረበው።
" እስኪ መጀመሪያ ተቀመጥ" ሁለተኛው ሰው ግን ምንም ሳይናገር ጨበጠውና ወንበር ስቦ በዝምታ ተቀመጠ። ሀጎስ ግን የእጆቹን ጣቶች የጓልዮሽ አቆላልፎ ሁለቱንም በየተራ እያየ ወዲህ እና ወድያ ማለት ጀመረ።
"ትላንትና ለሊት በአሜሪካ የሚኖሩት የመረጃ ሰዎቻችን እጅግ ሊጐዳን የሚችል ነገር ሊካሄድብን እንደሆነ ገልፀውልኛል"
"ምን?" ወዲ ሀለፎም እያሉ የሚጠሩት እና እንደገባ የተቀመጠው ሰው ጠየቀ።

ቀጠለ ተክለአይ "በትግል ላይ እያለን ከኛ መሀከል አፈንግጦ የጠፋ አንድ ግለሰብ እኛ የፈጠርነውን ትግራይን የማስገንጠል ፖሊሲ የራሱ አስመስሎ እዛው አሜሪካ ውስጥ እና በሌሎችም አገሮች ድጋፍ የሚያደርጉለትን ሰዎች እየመለመለ የትግል እንቅስቃሴ ሊጀምር መሆኑን ተጠቁመናል"
"የትኛውን ፖሊሲ!?" ወዲ ሀለፎም ሚስጥሩ ጠፍቶት ሳይሆን በተፈጠረበት የመረበሽ ስሜት ነበር ጥያቄውን ያቀረበው።
"በረሃ እያለን 1968 እኛ ሶስታችን ወደ ሱዳን በመሔድ አንድ ሀሳብ ይዘን መጥተን እንደነበረ ታስታውሱታላችሁ..... በዛ ማኒፌስቶ ላይ ከሰፈሩት እቅዶቻችን መሀከል አንደኛው "የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ሪፕብሊክ መንግስት ምስረታ" በሚል የነደፍነውን እቅዳችንን ነዋ"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“ለመሆኑ ግለሰቡ ማነው?” አለ ሀጎስ
“በግሌ ላስታውሰው አልቻልኩም..... ሆኖም ግን በረሃ እያለን እንደኛው ቁልፍ ቦታ ላይ ተቀምጠ የቆየና ብዙ ሚስጥሮችን ያውቅ የነበረ በኋላም በማናውቀው ምክንያት የከዳ ሰው ይመስለኛል፡፡ ስሙ በርሔ አብርሃ ይባላል”
“በርሄ አብርሃ!?” ሀጎስ በጩኸት ጠየቀ፡፡
“አዎ.....”
“ፍፁም ሀሰት ነው፡፡የምተለው ሰው ሞቷል!”
“ታውቀው ነበር?” ተክለአይ ጠየቀ፡፡
“ጠንቀቅ አድርጌ ነዋ፡፡ የአያቱ ስም እቁባይ አይደል?”
ተክለአይ ጠረጴዛው ላይ የነበረ ወረቀት አየት አድርጎ “አዎ”
“በቃ ሀሰት ነው..... እሱ ሳህል በረሃ ላይ ሞቷል”
“ትግል ላይ ነው የሞተው?” ወዲ ሀለፎም ነበር
“ዋይ አንተም ዘንግተኸዋል?”
“እኔንጃ አላስታወስኩትም”
“.....በ1966 ዓ.ም. መሰለኝ ግዜው” ሀጎስ ለማስታወስ እየጣረ ንግግሩን ቀጠለ “..... “ማህበረ ገስገስቲ ብሔረ ትግራይ” ን አቋቁመን በመንቀሳቀስ ላይ ሳለን በመኻከሉ ቅድም እንዳልከው በ1968 ካርቱም የነበሩ ሰዎቻችን የሚስጥር ስብሰባ አዘጋጅተው ጠሩን፡፡ ማንም ታጋይ ሳይሰማ ሶስታችን ብቻ ተደብቀን ሔድንና “የትግራይ ዲሞክራሲያዊ ሪፕብሊክን መንግስት ምስረታ” የሚለውን ፖሊሲ ቀርፀን በመመለስ ትግል ስንቀጥል በተጨማሪነት የአመራር ቦታዎች ላይ አዲሱን ፖሊሲ በሙሉ እምነታቸው የሚደገፉ ሌሎች አባሎችን አልመለመልንም?”
ሁለቱም ባለስልጣናት በአዎንታ መለሱ፡፡
“.....በቃ በርሔ በዛን ግዜ ለስልጣን የበቃ ሰው ነው” አለ፡፡
“ታዲያ እንዴት ሊሞት ቻለ ውጊያ ላይ ነው?” ወዲ ሀለፎም ጠየቀ ለማስታውስ እየጣረ፡፡
“በወቅቱ ታስታውሱ ከነበረ የትግራይ ነፃ ሪፕብሊክ ምስረታ ፖሊሲያችን ይፋ ስናወጣው የትግራይ ህዝብ እኛ ኢትዮጵያዊነታችንን ነው የምናምነው ብሎ አልቀበልም በማለት ተቃወመን፡፡ ግንባር የነበሩትም ታጋዮች እኛ ወታደራዊውን የደርግ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

መንግስት ለመጣል እንጂ ትግራይን ለማስገንጠል አልተነሳንም በማለት ከትግል ሜዳ እየጠፉብን ሲሔዱ የሰው ኃይላችን በእጅጉ ተጐዳ፡፡ እንደገና ለማጠናከር በዛው ዓመት ላይ አንድ ነባር ታጋይ ባቀረበው ፅሁፍ መሰረት ሌላ የከለላ ፓርቲ ማዘጋጀት እንዳለብን በዝግ ስብሰባ ውሳኔ ላይ ደረስን...»
ተክለአይ እና ሀለፎም ሀጎስን በዝምታ ያዳምጡ ነበር፡፡
ቀጠለ ሀጎስ ሁኔታውን ለማስታወስ በየመካከሉ እያቋረጠ “.....በውሳኔው መሰረት ለህዝቦች አንድነትና ነፃነት የሚታገል የሚመስል ሌላ ፓርቲ መመስረትንና ከትግራይ ውጪ ያሉትም ብሔሮች ቢሆኑ በዚህ ፓርቲ ስር ማሳተፍና መጠቀሚያ በማድረግ ከግዜ ወደ ጊዜ ጥሩ ውጤት በማሳየት ሚስጥራዊ የሆነውን ትግራይንና ኤርትራን የማስገንጠል እቅዳችንን በውስጠ ታዋቂነት በማካሔድ ጦርነቱን ቀጠልን፡፡ በዚህ ግዜ አመራር ላይ በነበርነው ሰዎች መሀከል አስቸጋሪ ክፍፍል ተፈጠረ፡፡

“የኛ ወገን ከላይ በገለፅኩት ዘዴ የብልጠት እቅድ በአላማችን እንግፋበት ሲል ጥቂት የሆነው ሌላኛው ወገን ግን “የትግራይ ህዝብ ቀርቶ የኢትዮጵያ መላው ህዝብ ፖሊሲያችንን አልደግፍም ቢል እንኳ “ትግራይ ዲሞክራሲያዊ ሪፕብሊክ መንግስት ምስረታ” የሚለው አቋማችንን በግልፅ አስቀምጠን መታገል አለብን ብለው ደመደሙ፡፡
“.....ልናሳምናቸው ብዙ ሞከርን አልሆን ሲል ግን የደርግን መንግስት ለመጣል ከፍተኛ የሰው ሀይል እንፈልግ ስለነበረ መፍትሔ ለመሻት እኛ በድብቅ ስብሰባ ተቀመጥንና የመጨረሻ ውሳኔ ላይ ደረስን፡፡ ውሳኔው የተቃወሙትን በሙሉ እንዲረሸኑ የሚል ነበር፡፡ በዚህ ግዜ አስራ አንድ ከሆኑት ተቃዋሚዎች መሀከል አንዱ በርሔ አብርሃ ነበር፡፡ ለሊት ከተኙበት ታፍነው ወደ ሳህል በረሃ ተወሰዱና ማንም ታጋይ ሳይሰማ ሁሉም ተረሸኑ፡፡” አለ ሀጎስ የወቅቱን ግዳጅ የመራው እሱ ስለነበር እያስታወሰ፡፡

ተክለአይ እና ወዲ ሀለፎም የወቅቱን አስቸጋሪ ሁኔታ ቢያስታውሱም የሰውዬው ምስል ግን ሊከሰትላቸው አልቻለም፡፡

በዝምታ ጥቂት ቆዩና ተክለአይ “እና በርሄ ያኔ ተረሸኖ ከነበረ ታዲያ አሁን አሜሪካ ሆኖ ይህን ትግራይን የማስገንጠል ሚስጥራዊ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ስራችንን በጥበብ ከፍፃሜው ሳናደርሰው አድበስብሶ ሊያሰናክልብን የተነሳው ግለሰብ ማነው?" ሁለቱንም በየተራ እያየ ጠየቀ፡፡
"ምናልባት ሚቹን በርሔን ያውቅ የነበረና ራሱን በበርሔ ስም ፈጥሮ የሚንቀሳቀስ ሌላ ሰው ይሆናል" አለ ሀሳስ፡፡
"በትክክል ስለመሞቱ ግን ምን ማረጋገጫ አለ?" ተክለአይ ጠየቀ፡፡

"ቧ!..... ለምን አንተማመንም፡፡ ሁሉም ተረሽነዋል" ሀሳስ ትእግስቱ በተሟጠጠ ሁኔታ መለሰ ምክንያቱም ግዳጁን የመራው ራሱ ስለነበረ በሌላ በኩል በሀላፊነት እንዳይጠየቅ እየተጠነቀቀ፡፡
"ጥሩ አሁን ወደ መፍትሔው ነው መሔድ ያለብን" አለ ተክለአይ፡፡ ቀጠለ ".....ይህ ግለሰብ በእርግጥ ትግራይ ከኢትዮጵያ እንድትገለል ይፈልጋል፡፡ ይህ ደግሞ እኛም ትግል ላይ እያለንም ሆነ አሁን በውስጣችን ያለ ፍላጐትና ገና የሚተገበር የወደፊት እቅዳችን ነው፡፡ በእርግጥ በአሁኑ ወቅት ላይ በቀጥታ ስራውን ከማስተግበር ሊያስተጓጉለን የሚችል አንድም ሀይል በኢትዮጵያ ምድር ላይ የለም...

«ሆኖም ግን የአገሪቷ ስልጣን በመዳፋችን መሀከል እስከሆነ ድረስ ትግራይንም ሆነ ራሳችንን፤ በሀብትም ሆነ በሰው ሀይል እያፈረጠምን የሚያሰጋን ነገር እስኪመጣ ድረስመቆየት እንደምንችል ከዚህ በፊትም በተደጋጋሚ የፓርቲያችን የፖሊት አባላቶች ባደረጉት ተደጋጋሚ ስብሰባ ተማምነንበታል፡፡"
ቀጠለ ሁለቱንም በየተራ እያየ ".....እና ያ ግለሰብ ግን አሁን በመሀከል ገብቶ እኛ በከፍተኛ ሚስጥርና ጥንቃቄ እናስፈፅመዋለን ያልነውን እቅድ ሊበጠብጥብን ስለሆነ ባለበት እንዲቆም ማስቻል አለብን፡፡ እና ምን የመፍትሔ ሀሳብ አላችሁ?" ጠየቀ፡፡
"እ..... አሜሪካ በየትኛው ግዛት ነው ያለው?" ወዲ ሀለፎም ጠየቀ፡፡

"ከዋሺንግተን ነው መረጃው የደረሰኝ፡፡ ትክክለኛው አድራሻው ግን የሚታወቅ አይመስለኝም"
"ለፓርቲው የአሜሪካ መንግስት እውቅና ሰጥቶታል?" ሀሳስ ጠየቀ
"እውቅና እንዲሰጠው አልጠየቀም ፡፡ግና በሀቡእ ተደራጅተው ነው እየተንቀሳቀሱ ያሉት "

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“ፈልገን እናነጋግረውና እናሳምነዋ” ወዲ ሀለፎም ነበር፡፡
“ማሳመን ስትል እንዴት?..... ትግሉን አቁም?” ተክለአይ ጠየቀ፡፡
“ሳይሆን የትግራይ መገንጠል የኛም ፍላጐት መሆኑን ነግረነው የቆየንበትን ምክንያት በማብራራት..... ፈቃደኛ ከሆነም ጠቀም ያለ ገንዘብ በመስጠት ከኛ ጋር እንዲሰራ ማድረግ ወይም እንቅስቃሴውን በግድም ይሁን በውድ እንዲያቆም ማስደረግ”
“ሊሆን የሚችል አይመስለኝም” ተክለአይ፡፡
ከብዙ ክርክሮች በኋላ ሶስቱንም ባለስልጣናት የሚያስማማ ውሳኔ ላይ ተደረሰ፡፡
ውሳኔው ግን በርሔ አብርሃ የተባለውን ግለሰብ ከነ ዋና ዋና ተከታዮቹ ባሉበት ማስገደልና ጉዳዩ ተዳፍኖ እንዲቀር ማስደረግ በሚለው ነበር፡፡
ሀጎስ “ግን በጣም በጥንቃቄ እና በሚስጥር መከናወን ስላለብት ደረጃውን የጠበቀ የነፍሰ ገዳይ ቡድን ነው መቅጠር ያበጠን፡፡ ለስራው የሚጠይቁት ክፍያም ወደድ ሊል ይችላል»
ተክለአይ «የገንዘቡ ጉዳይ የሚያስጨንቅ አይደለም፡፡ ከኪሳችን የምናወጣው ነገር የለም፡፡ እንደዚህ ባሉ ወቅቶች በሀገሪቷ ሀብት ላይ ማዘዝ ካልቻልን ምኑን መንግስት እንሰኛለን? ግፋ ቢል የሚወጣው ወጪ ከአስር እስከ ሃያ ሚሊዮን ብር..... ቢደርስ ነው፡፡”
“ባይበቃስ” አለ ሀጎስ
“እሺ አስርና ሃያ ሚልዮን ዶላር ገንዘቡ አይደለም ችግሩ ሰውዬውን ማስቆም ነው ዋናው ጉዳይ.... ያስቀመጥካቸውን ሴቶች ብትቀንስ ይበቃህ ነበር!” ሀጎስ ማንነቱን ያውቃልና ፈገግ ብሎ ዝም አለ፡፡
“አዎ..... የሚኖሩበትን ስፍራ ለማወቅ ራሱ በጣም ሊያስቸግር ይችላል፡፡” አለ ወዲ ሀለፎም፡፡
“የተጠየቀው ክፍያ ሁሉ ወጪ ሆኖ በኛም ሰዎች ይሁን በፈረንጆቹ ክትትል ይደረግባቸውና የማያዳግም እርምጃ ይወሰድባቸው” አለ ተክለአይ፡፡
ቀጠለ በየተራ እያያቸው “ይህን ስራ ማን በሃላፊነት ያስፈፅመው?”
“ሀጎስ ይሻላል” አለ ወዲ ሀለፎም እንደዚህ አይነት ግዳጆችን በተደጋጋሚ ሀጎስ ሲያስፈፅም በመኖሩ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

እሱም ስራውን በእምንታ ተቀበለ፡፡ ከተክለአይ ቢሮ ሊወጡ ሲነሱ የመሳቢያውን ኪስ ከፈተና ስለተባለው ግለሰብ ያገኘውን ግምታዊ መረጃ የያዘ ሰነድ እና እዚህ ቢሮ ከገቡ በውኋላ የተወያዩትን ሀሳብ የተቀረፀበት ካሴት ለሀጎስ እየሰጠው "በደንብ እንድትገመግመውና የሚረዳን ሀሳብ እንድትፈጥር ይሁን፡፡ ይህን የቴኘ ካሴት ቤትህ ወስደህ ስማው ግን በፍፁም ከእጅህ እንዳይወጣ፡፡ የማትፈልገው መሆኑን ስታምን አቃጥለው" አለው፡፡

ሀጎስ ተቀብሎት ወጣ፡፡ ሰነዱን በአግባቡ አንዴም ሳያየው መኪናው ውስጥ አብሮት ላይ ታች እያለ ሰነበተ፡፡ በመካከሉ መኪናው መጠነኛ ብልሽት ገጥሞት ወደ ቤተ-መንግስቱ የተሸከርካሪዎች መጠገኛ ጋራዥ ሲላክ ሰነዱን ሁሉ አወረደው፡፡ ካሴቱን ግን ረስቶት ነበር፡፡

  

የማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

ምዕራፍ 16

ጳውሎስ የነዚህን ሶስት ባለስልጣናት ንግግር የተቀረፀበትን ካሴት ነበር ለሰናይት የሰጣት፡፡ ሰናይት ቤት ደርሳ አዳምጣው እንደጨረሰች ምን ማድረግ እንዳለባትና በምን መልኩ ልትጠቀምበት እንደምትችል እያሰበች ቆየች፡፡

ውይይቱ መቼ እንደተከናወነ ባታውቅም ካሴቱን ከመኪና ውስጥ አገኘሁት ካለው ግምታዊ ዕለት አንስቶ እስካሁን ድረስ በመሀከሉ ያለፉትን ጊዜያቶች አሰላችና "ሁለት ሳምንት ሆኖታል" አለች፡፡ ቀጠለች በሀሳቧ 'በዚህ መሀከል ውስጥ እንደተናገሩት ሰውዬውን አግኝተው ገድለውት ይሆን?' መልስ የማታገኝለትን ጥያቄ ለራሷ አቀረበች፡፡ የሚያሰሯት ሰዎች ይህን መረጃ ቢያገኙት ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ ገመተች፡፡

ረጅም ሰዓት በዚህ ዙሪያ ስታስብ ቆየችና ሰውዬውን ፈልጎ የማግኘቱ ሁኔታ ቢሳካም ባይሳካም እንዲሞከር መረጃውን ወደ ፒየር ቢላክ እንደሚሻል ስላመነች የሶስቱንም ባለስልጣናት ንግግር አሰዳደሩን ሳታዛንፍ ቃለ-ተውኔት በመሰለ ሁኔታ በፈረንሳይኛ ቋንቋ ተረጐመችው፡፡ በሚቀጥለው ቀን ፋክስ ልታደርግላቸው አዘጋጅታ ስትጨርስ ሰዓቱ ከለሊቱ 10፡20 ብሎ ነበር፡፡

በዕለቱ ለአዳር የመረጠችው የበድሉ ህንፃ ላይ በተከራየችው ቤት ነበረ፡፡ ወደ መኝታዋ ከማምራቷ በፊት ወደ መስኮቱ ተራመደችና መጋረጃውን ገልጣ እይታዋን ከመስታወቱ ውጪ ሰደደች፡፡ወደ ሜክሲኮ የሚያደርሰው አስፓልት በረዶ የቀጠቀጠው

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ዛፍ ይመስል እርቃኑን ቀርቷል፡፡ ትንሽ የፍርሀትና የባዶነት ስሜትን አሳደረባት፡፡ መጋረጃውና ዘግታ በትካዜ ወደ አልጋዋ ተራመደች፡፡

ማለዳ ላይ ከእንቅልፏ ያባነናት የስልክ ጥሪ ነበር፡፡ ሰዓቷን ስታይ አንድ ሰዓት ይላል፡፡ ማን ሊሆን እንደሚችል ለመገመት እየተቸገረች መነጋገሪያውን በማንሳት "ሀሎ..... "

"ሀሎ.... ሰናይት እንደምን አደርሽ? " ንግግሩ ፈረንሳይኛ ነበር፡፡

"ማን ልበል?" ነቃ ለማለት እየጣረ ጠየቀች፡፡

"አኔልካ እባላለሁ ለፒየር ነው የምሰራው ስልክሽንም ከሱ ነው ያገኘሁት በኔ በኩል የሚደርስሽ እቃ አለ እንዴት ላገኝሽ እችላለሁ?"

" ምንድነው የተላከው? "

ሰውዬው ጥቂት እንደማቅማማት አለና " ሁለታችንም ለአንድ ድርጅት ነው የምንሰራው፡፡ ከአሁን በኋላ ግንዘብ የሚደርስሽ በኔ በኩል ነው፡፡"

ፈረንሳዊው ቀጠለ "እንቀጣጠርና ዛሬ መውሰድ ትችያለሽ"

"ስንት ሰዓት ላይ ይመችሀል?"

"እ.....2፡30?"

"ይቻላል፡፡"

"የት እንገናኝ?" ፈረንሳዊው ጠየቀ

"ራስ ሆቴል አካባቢ ቢሆን....."

"ጥሩ..... ራስ ሆቴል በራፍ ላይ ጥቁር መርሴዲስ መኪና ቆሞ ይጠቅብቅሻል"

"እሺ....."

ሰናይት ለቀጠሮው አስር ደቂቃ ሲቀረው ከህንፃው ወርዳ በመውጣት ወደ ግራ ተጠፈችና ቀጭኗን አስፓልት ይዛ ወደ እስታዲዮም አቅጣጫ ለአምስት ደቂቃ እንደተጓዘች ወደ ላጋርና ቸርቸል ጐዳና የሚወሰደው ዋና መንገድ ጋር ስትደርስ ድጋሜ ወደ ግራ ታጠፈች፡፡

በመንገዱ ዳር በተሰራው አሮጌ ህንፃ በረንዳ ስር አልፋ ራስ ሆቴል በር ትይዩ ለመድረስ ጥቂት ሲቀራት ቆመችና አካባቢውን አማተረች፡፡ የሚፈለገው ጥቁር መርሴዲስ መኪና ግን አልነበረም፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ሰዓቷን አየች፡፡ 2፡30 ለማለት ሁለት ደቂቃ ቀርቶታል፡፡ ከቆመችበት ሳትንቀሳቀስ 'ወጥመድ ይሆን ይህ ቀጠሮ?' ራሷን ጠየቀች፡፡

ከዛም ወደፊት እርምጃዋን በመቀጠል የሆቴሉን በር በማለፍ የቀጣዩ ህንፃ በረንዳ ስር ከመግባቷ በፊት የሆነ እጅ ትከሻዋን መታ አደረገው፡፡ በድንጋጤ ዞረች፡፡

ረዘም ብሎ ቀጠን ያለ ቁመና ያለውና ተራ ልብስ የለበሰ ጐስቋላ መሳይ ጐልማሳ ነጭ ፈረንሳዊ እጁን ለሰላምታ እየዘረጋላት "ቅድም አኔልካ እንደምባልና ለፒየር እንደምሰራ የነበርኩሽ ሰው ነኝ፡፡" አላት በፈረንሳይኛ፡፡

"መኪና ውስጥ ነበር የቀጠርከኝ?" በጥርጣሬ እያተኮረችበት ጠየቀች፡፡

"ስልኩ ተጠልፎ ቢሆንስ?..... የምንገናኘው እኮ ገንዘብ ለመቀባበል ነው፡፡"

"የምትፈልጋተ ሰው እኔ መሆኔንስ እንዴት አወቅክ"

" ስለ አንቺ ማወቅ የሚገባኝ ሁሉ በፒየር በኩል በበቂ ሁኔታ አውቄያለሁ"

ነጩ ፈገግ እያለ "እየተራመድን እንነጋገር" አለውና የቀጣዩ ህንፃ በረንዳ ስር ገብተው ጥቂት እንተጓዙ አንዲት ኬክ ቤት ጋር ደረሱ፡፡

"እዚህ እንግባ" ፈረንሳዊው ተናገረና እየመራት በመግባት ፎቁ ላይ ወደሚገኘው የመስተናገጃ ክፍል ደረሱ፡፡

ብዙ ሰው አልነበረም፡፡ በአንደኛው ጥግ ላይ በሚንተገተግ አፍላ ፍቅር የተዋጡ የሚመስሉ ወጣት ፍቅረኞሞች ሌላውን ሰውና እንቅስቃሴ ረስተው በራሳቸው ዓለም ተውጠዋል፡፡ ፈንጠር ብሎ ከጉልምስና አለፍ ያሉ ትልቅ ሰው ሻይ ይጠጣሉ፡፡ ሁለት ሴት አስተናጋጆች በመግቢያው አካባቢ ቆመዋል፡፡

አንደኛዋ ወደነሱ መጣችና "ምን ልታዘዝ ?" እይታዋ በስርቆት ፈረንሳዊውን እየቃኘ ሰናይትን ጠየቀች፡፡

አስተናጋጇ የታዘዘችውን ለማምጣት ስትመለስ ፈረንሳዊው የክፍሉን ዙሪያ ቃኝቶ ወደነሱ ያተኮረ ሰው ያለመኖሩን ካጣራ በኋላ ወገቡ ላይ ሰፊ ቀበቶ በሚመስል ሀር ጨርቅ የተጠቀለለውን ገንዘብ ፈቶ በጠረጴዛው ስር አቀበላትና "ለመያዝም ሆነ ለማጓጓዝ እንዲመቸን ገንዘቡ በጥቅላላ በፓውንድ የተመነዘረ ነው"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ሰናይት ተቀብላ እንደ ተራ እቃ ጠቅልላ እግሯ ላይ አስቀመጠችውና "ፒየር ነግሮኛል" አለች

ተመግበው እንደጨረሱ ሁለቱም የየራሳቸውን ክፍያ ጠረጴዛ ላይ አኖሩ፡፡

የመውጫውን በር እንዳለፉ ፈረንሳዊው "በዚህ .....ነኝ....." አለ ወደ ብሔራዊ ቲአትር የሚወስደውን አቅጣጫ እያመለከተው "ወደፊት ጥሩ ባልደረቦች እንደምንሆን ተስፋ አደርጋለሁ፡፡" ጨበጣትና መራመድ ቀጠለ፡፡ ሰናይትም ወደ ቤቷ መመለስ ጀመረች፡፡

የዛኑ ዕለት ለሂርጳ ደውላ በአካል እንዲገናኙ ቀጠሮ አስያዘችው፡፡ ከሰዓት ላይ ሲገናኙ "በገንዘብ በኩል ጥሩ ድጋፍ የሚያደርጉላችሁን ድርጅቶች አግኝቻለሁ"

" ከሁሉ በፊት ግን ያቋቋማችሁት "የኦሮሞ ንቅናቄ ድርጅት" የተባለው ፓርቲያችሁ እንዴት ባለ ሁኔታ ፖሊሲውን እንደቀረፀ ዝርዝር ሰነድ እና ማኒፌስቶዋችሁን ማወቅ ይፈልጋሉ"

"ይቻላል፡፡ የተወሰነውን ለአንቺም ማብራራት እችላለሁ....." አለ ሂርጳ ማስታወሻ መያዣ ደብተሩን ከኪሱ እያወጣ፡፡

"አጠቃላይ ፖሊሲዎቹ የተነደፉበትን ጥራዝ ሰሞኑን እሰጥሽና ትልኪላቸዋለሽ፡፡ ለጊዜው ግን ወደ ነፃነት የሚያራምዱን ጥቂት ነገሮችን ልጠቁምሽ እችላለሁ" ብሎ ከማስታወሻው እያነበበ "ብላንከዝም የሚባለውን የትግልና የፖለቲካ እንቅስቃሴ ልንጠቀምበት ወስነናል፡፡"

"የት አገር ነው የተፈጠረው ፅንሰ-ሀሳቡ?"

"ፈረንሳይ ነው፡፡ ግዜው ከ1805-1881 ሲሆን ተምኔታዊ ኮሙኒስት ነው"

"ፅንሰ ሀሳቡ ከሌላው የተለየ ምን ጥሩ ነገር ስላለው ነው የመረጣችሁት?"

"ከሁሉም የበለጠ ለውጤት እንደሚያበቃን በማመናችን ነው" አለ ሂርጳ፡፡

"ስለ ይዘቱ ጥቂት ነገሮች ብትሰጠኝ?"

"እ....." ከማስታወሻ ላይ ያነብላት ጀመር፡፡ "ከላይ ተጭኖን ያለውን ገዢ መንግስት በድንገተኛ የትጥቅ አመፅና ትግል ለመገርሰስ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

የሚያስችል ንድፍ አለው፡፡የንድፉ አደረጃጀት ህቡእና ተዋረድ ያለውን ድርጅት በመመስረት እንደሆነ በግልፅ ያስቀምጣል"
ሰናይት ሀሳቡን ስትመዘግብ ቆየችና "ከሰፊው ህዝብ ጋር ያለው ትስስር ምን ያህል ነው?"
"እ..... እንቅስቃሴው በድርጅቱ ታማኝ መሪና ወታደሮች ብቻ ነው የሚካሂደው፡፡" አለ፡፡
"ህዝቡን ያላማከለ አካሔድ ታዲያ ምን ያህል ለውጤት ያበቃል ብላችሁ ታምናላችሁ?" አለች ሰናይት፡፡
"በዚህ ነገር ላይ ብዙ ተነጋግረናል፡፡ በመጨረሻው ለውሳኔ የደረስንበት ሀሳብ ግን የፅንሰ-ሀሳቡን ንድፍ በመከተል ለመንቀሳቀስ እንሞክርና ሊያስኬደን የማይችል ከሆነ ህዝቡን በቅስቀሳ የምናነሳሳበት መንገድ እንፈጥራለን በሚለው ተስማምተናል፡፡"
"አዎ..... ህዝብ ቅስቀሳ ያስፈልገዋል፡፡ ስታነቃቂት ብቻ ነው ጠቃሚ የሰው ሀይል ማግኘት የምትችሉት..... እንደውም ለሱ ስራ ቅድሚያ ብትሰጡት ጥሩ መሆኑን ልጠቁማችሁ እፈልጋለሁ፡፡"
ሂርጳ በቀዘቀዘ ስሜት "ለቅስቀሳ ስራ ደግሞ ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ ሀይል ያስፈልጋል"
"ስለ ገንዘብ አታስቡ፡፡ ቅድም እንዳልኩህ እገዛ የሚያደርጉላችሁ ድርጅቶችን አግኝቼላችኋለሁ፡፡ እንደውም የመጀመሪያ ድጐማ ሁለት መቶ ሺህ ፓውንድ ተልኮላችኋል፡፡" አለችና በሀር ጨርቅ የተጠቀለለ ገንዘብ ፈታችና በታዘዘችው መሰረት የተወሰነውን ቀንሳ ሌላውን ሰጠችው፡፡
ሂርጳ የሚያየውን ማመን አልቻለም፡፡
"ይህን ገንዘብ በትክክል የፓርቲያችሁ እንቅስቃሴ ላይ ብቻ ካዋላችሁት ገና በሚልዮን የሚቆጠር የገንዘብ ድጋፍ እንደሚያደርጉላችሁ ቃል ገብተውላችኋል፡፡"
"እናደርገዋለን!..... እናደርገዋለን!" አለ ብሩን ጨብጦ፡፡

"እሱ በሂደት የሚታይ ይሆናል....." "ይህን ገንዘብ ለመሳሪያ ግዢ እንዳታውሉትም ታዛችኋል፡፡"
ሂርጳ ለምን የሚል እይታውን ሰደረባት፡፡ "የሚያስፈልጋችሁን ያህል ዘመናዊ የመሣሪያ እርዳታ እንደሚደርግላችሁ ከገንዘቡ ጋር የተላከው

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ደብዳቤ ላይ ተገልፆልኛል፡፡ ከናንተ የሚጠበቀው በቅስቀሳ የሰው ሀይላችሁን ማዳበር ብቻ ነው፡፡"
"እንደታዘዝነው እናደርጋለን....."
"እናም ለቅስቀሳው ስራችሁ አንድ ኘሮጀክት ቀርፃችሁ እንድትልኩ ተጠይቃችኋል፡፡"
"እንዴት አይነት?" ጠየቀ ሂርጳ
"ማለት ህዝቡን የምታነሳሱበት የቅስቀሳ መረብ በምን በምን ዘዴ ሊካሄድ እንደሚችል የሚገልፅ፡፡"
"በጥቂት ቀናት አልቆ ይላክላቸዋል!"
በዝምታ ጥቂት ደቂቃዎች አለፉ፡፡
"እውነት ኢልሻለሁ አንቺ ማለት ባለውለታ ነሽ" አለና ቀጥሎ ምን ማለት እንዳለበት ስሜቱን መግለፅ ስላቃተው አጥብቆ ጨበጣት::

  

ያልተሸጠ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ምዕራፍ 17

ተክለአይ የደህንነት ጉዳዮችን በተመለከተ በቀጥታ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ትእዛዛትን ከሚቀበሉት ከፍተኛ ባለስልጣናት መካከል አንዱና ዋናው እንደመሆኑ ዘወትር ከጠቅላይ ሚስትሩ ቢሮ አካባቢ አይታጣም ነበር። በዚህ ሰሞን ግን እጅግ በተለየመልኩ ረጃጅም ሰዓቶችን የሚወስዱ ስብሰባዎችን እያደረገ ነበር የሰነበተው። ዛሬም እንደተለመደው ስብሰባ ላይ ቆይቶ ሲወጣ ፊቱ በንዴት እንደበገነ ያስታውቅበት ነበር። በእጁ አንድ የተጠቀለለ ወረቀት ይዟል።

የነበረበትን ስብሰባ ጨርሶ ከመውጣቱ በፊት እዛው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ እያለ ነበር ሀጎስ እና ወዲ ሀለፎም ቢሮው እንዲመጡ የነገራቸው። ሲደርስ ሁለቱም ቀድመው ጠበቁት። የያዘውን ወረቀት ጠረጴዛው ላይ ወርውሮ የለበሰውን ጃኬት እያወለቀ በንዴት "ምን እየተሰራ ነው ያለው?" ሀጎስ ላይ እያፈጠጠ ጠየቀ።

በገፅታው ላይ ጮልተው የሚታዩት አይኖቹ አንድ ቦታ መርጋት አልቻሉም። በቢሮው ዙሪያ እየተቅለበለቡ ተመልሰው ሀጎስ ላይ ይተከላሉ።
ቀጠለ ".....ያንን ከሀዲ ሰውዬ ፈልገህ እንድታስቆመው ሀላፊነትን ከወሰድክ ስንት ጊዜ አለፈህ። ግን አንተ ምንም ላይ ሳትደርስ እሱ የትግል እንቅስቃሴውን ሊጀምር ጥቂት ቀርቶታል።" አለ።

ሀጎስ እድሜው ወደ አርባዎቹ መጨረሻ ደርሷል ፀጉሩን የወረረው ሽበት ግን ከዛ በላይ እድሜው የገፋ ሰው አስመስሎታል።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

በትግል ወቅት ሃምሳ አምስት አልፎ የማያውቀው ክብደቱ አሁን በእጥፍ ጨምሮ ረጅም ሰውነቱን ስለሞላው ግዙፍ ቁመናን አላብሶታል። የፊቱ ገፅታ የሀውልት አይነት በድንነትን የተላበሰ በመሆኑ በካሜኔ ስለመሞላቱ ያሳብቅበታል። በባህሪውም ቢሆን ግትር አቋም ያለው ሲሆን በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ ሽጉጥ እየመዘዘ ካልገደልኩ እያለ በገላጋይ ነበር የሚለያየው። ልዩ የሚያደርገው ግን የተሰጠውን የቤት ስራ አለቆቹ ከሚፈልጉት በላይ አሳምሮ ሰርቶ በመጨረሱ ነበር። በዛ ምክንያትም ሌላው የባህሪ ችግሮቹን ማንም አንስቶ የሚወቅሰው አልነበረም። ሀጎስን እንደ ዛር ፈረስ እንዳሻቸው ከሚጋልቡት በጣም ጥቂት ባለስልጣናት መካከል አንዱ ተክለአይ ነበር።

ወዲ ሀለፎም በሀጎስ ላይ እየወረደ ያለውን የተክለአይን ቁጣ በዝምታ ያዳምጣል።

ወቅቱ ለየካቲት ወር እኩሌታ ጥቂት ቀናት ቀርቶታል።

ተክለአይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እሱን በተናገሩት መሰረት አንድም ቃል ሳያዛንፍ ሀጎስን በጥያቄና በዝርዝር ሀሳቦች ማጣደፍ ቀጠለ።

"በትግራይ ምን እየተፈፀመ እንዳለ ሰምተሀል?"

"አልሰማሁም" ጮርነን ባለ ቅላፄ መለሰ።

"በሰሜኑና በምስራቁ አካባቢ ባሉት ከተሞች የቅስቀሳ ወረቀቶች መበተን ተጀምሯል!"

"በማን?" ሀጎስ ፊቱን አጨፍግጎ ጠየቀ።

"የደረሰኝ መረጃ እንደሚጠቁመው በዛ በርሔ አብርሃ በሚባል ግለሰብ ነው....."

ወዲ ሀለፎም አቋረጠውና "የትግራይ ነፃ ሪፕብሊክ መንግስት ምስረታ የሚለው ፖሊሲያችንን አወለጋግዶ ሊያሰናክልብን የተነሳው ሰው አይደል?"

"አዎ....." አለ ተክለአይ ቀጠለ "የቅስቀሳ ወረቀቶችን ማስበተን ጀምሯል..... ሁኔታውን በጣም አስከፊ የሚያደርገው ደግሞ ....." ንዴት ስለተናነቀው ሀሳቡን መጨረስ አልቻለም።

"ምንድነው ሂደቱ.....ምን ላይ ደርሷል?" ሀጎስ ባሳየው ቸልተኝነት ምንም ሳይደናገጥ ጠየቀ።

ተክለአይ በመዳፉ ተረተር ጠረጴዛውን ነርቶ በረጅሙ ተነፈሰና ".....በክልሉ ካሉት ሰዎቻችን በኩል የተላከልኝ መረጃ እንደሚገልፀው ህዝቡ የመገንጠሉን ሀሳብ በከፍተኛ ሁኔታ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

እየተቃወመው መሆኑን ነው..... ይህ ደግሞ ወደፊት እኛም ትግራይን እንዳናስገነጥል ጥንቃቄ ያልታከለበት ምረዛውን በህዝቡ ህሊና ውስጥ እየከተተብን ነው፡፡....."

ቀጠለ ".....ይባስ ብሎ ትላንትና አሜሪካን በሚገኘው የኛ ኤምባሲ የፖለቲካ ክፍል መምሪያ ይሄ ደብዳቤ በፋክስ ተላከለት፡፡ እነሱም የጉዳዩን አሳሳቢነት ገልፅው በቀጥታ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ላኩት፡፡ እንኩ አምብቡት!" ብሎ ይዞት የመጣውን ወረቀት ከጠረጴዛው ላይ በማንሳት ሰጣቸው፡፡

በወረቀቱ ላይ ከላኪው ሙሉ ስም በስተቀር ሌላ አድራሻ አልሰፈረበትም ነበር፡፡ ሀጎስ ድምፁን ከፍ አድርጎ ማንበብ ጀመረ፡፡

"የዚህ ደብዳቤ ቅጂ ለሁሉም የፖ.ሊ.ት. ቢሮ አባላትና ባለስልጣናት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ እንደሚደርሳቸው አምናለሁ፡፡ በተለይ በወቅቱ በትግል ላይ የነበርን ሁሉ የዛሬው ምኞት እና ስልጣን በ1969 ዓ.ም ምን ተከናውኖ እንዳለፈ ለማስረሳት በቂ ሀይል ያለው አይመስለኝም፡፡

ሳልህ በረሃ ላይ ከለሊቱ 7፡00 ሰዓት በርሔ አብርሃ በናንተ ተገድሏል፡፡ ተቀብሮም ተረስቷል፡፡ እውነቱ ግን ሌላ ነው፡፡ እናንተ ከቀበራችሁበት እሱ ግን ተነስቷል፡፡ የተተኮሰበት ሁሉ የቆሰለ ሁሉ ሟች አይደለም፡፡

ዝርዝሩን ስለምታውቁት አልዘበዝበውም፡፡

ዛሬ እናንተ ኢትዮጵያን በሚያክል ሰፊ የስልጣን ውቅያኖስ ውስጥ እንዳሻችሁ እየዋኛችሁ ስላላችሁ ጥንት ወደ ትግሉ ስትገቡና እኛንም ስታስገቡን የነበራችሁን ትግራይን ነፃ የማውጣት እቅድ ሰርዛችሁት ሊሆን ይችላል፡፡

እኛ ደግሞ የዛ የመከራ ትግል ሰለባና ተራፊዎች ልንሆን የቻልን ጥቂት ሰዎች ያንን የነፃነት አላማ ከጫፍ ለማድረስ ወስነን ተነስተናል፡፡ እስኪ ማን እንደሚያቆመን እናያለን፡፡ በእርግጥ የትግራይ ህዝብ ይህን የመገንጠል ዓላማ ጥንትም ስንጀምረው እንዳልተቀበለው ታውቁታላችሁ፡፡ ዛሬም ከዛ የተለየ ስሜት የለውም፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ሆኖም ግን የኤርትራ አብዛኛው ህዝብ ወይም በማስገንጠሉ ሂደት ውስጥ ቅጥም ያገኙ ከነበሩ ውስን ግለሰቦች በስተቀር ሰፊው ህዝብ ከኢትዮጵያ መገንጠልን እንደማይፈልግ ግልፅ ነበር።።

ግና በድምፅ አሰጣጡ የሸር ሂደትና በጥቂት ግለሰቦች ፍላጐት አገሯ ተገንጥላ ነፃ ወጥታለች።። ትግራይም እንደዛው ትሆናለች።። ህዝቡ ወደደም ጠላም እንደ ኤርትራ ትገነጠላለች።። ይህን ደግሞ እኛ እውን እናደርገዋለን።።

ምናልባትም በተጨማሪም እናንተ ደርግን የሚያህል አስፈሪ መንግስት ገልብጣችሁ ለስልጣን እንደበቃችሁ ሁሉ እኛ ደግሞ የእናንተን በትረ- ስልጣን እንቀበል ይሆናል።።

ነፃነት ለትግራይ ህዝብና ለትግራይ መሬት!

እናሸንፋለን!" ይላል።።

ተክለአይ ሀጎስ እስኪጨርስ ጠበቀና "ሰውዬውን አድነህ ለማስቆም ሀላፊነቱን ወስደህ አልነበረም እንዴ?"

"ዋሺንግተን ያሉት ሰዎችን ፈልገው እንዲያገኙት ተደጋጋሚ ትእዛዝ ሰጥቼ ነበር። ሰውዬው ግን ፈፅሞ ሊገኝ አልቻለም።። በድብቅ ነው እየተንቀሳቀሰ ያለው።።"

"በፍለጋው ምን ያህል ልትሔድ ችለህ ነበር?"

"በርካታ ሰዎችን አሰማርቼ ነበር። ገንዘብ ከማባከን ውጪ ውጤት ሊታይ አልቻለም።።"

"ስለ ገንዘብ አታንሳ!" ተክለአይ አንቧረቀ።። "ሃምሳ ሚልዮን ዶላር ይድረስ ቢፈልግ!..... ከአንተ ኪስ ወይም ከኔ አይወጣ..... ያ የአገሪቷ ወጪ ነው! ምን የሚያስጨነቅህ ነገር አለ!?"

ሀጎስ በእልህ ጥርሱን ነክሶ ተነሳና በቢሮ መንጐራደድ ጀመረ።። ተክለአይ ቀጠለ "የምትቀጥራቸውን የክትትል ሰዎች በእጥፍ ጨምር እንደውም ፕሮፌሽናል የሆኑ ልምድና አቅም ያላቸውን ሰዎች ብቻ ተጠቀም።። የፈለገውን ያህል ክፍያ ቢጠይቁ ይፈቀድላቸው።።" አለ።።

ወዲ ሀለፎም "ለመሆኑ ይህ ግለሰብ ዋሺንግተን ነኝ ያለሁት ይበል እንጂ በሌላኛው የአሜሪካ ግዛት ውስጥ ቢሆንስ ያለው?"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

“እሱም ላለመገኘቱ አንድ ምክንያት ሊሆን ይችላል” ሀጎስ ፈጥኖ ሀሳቡን ደገፈ፡፡

“በምትጠራጠርባቸው ግዛቶች ሁሉ ሰዎችን ቅጠር! ሲኦልም ቢሆን” ቀጠለ ተክለአይ “ይህን ሰውዬ መቅደም አለብን፡፡የትግራይ ህዝብ ከነቃ በኋላ ለኛም ቢሆን ወደፊት የማስገንጠሉን እቅዳችንን ተቃውሞ ገጥሞት ሊከሽፍብን ይችላል፡፡”

ረዥም ዝምታ በመሀከላቸው ሰፈነ፡፡

“ ራሴ መሄድ አለብኝ ” አለ ሀጎስ፡

ተክለአይ በግልግል ስሜት እየተነፈሰ “ወዲ ሀለፎም የትግራይን ሁኔታ በጥብቅ ተከታተል”

“ስልጣን ላይ እስካለን ድረስ ትግራይን የማስገንጠሉን ሀሳብ በማንም እንዲነሳ አንፈልግም፡፡ ስልጣን ከለቀቅን ግን ያኔ ራሳችን የምንወስንበት ይሆናል፡፡” እኛና እኛ ብቻ ነን አለ ተክለአይ፡፡

  

የማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ምዕራፍ 18

ፒየር ሰናይት በፈረንሳይኛ ተርጉማ የላከችለትን የሶስቱን ኢትዮጵያዊ ባለስልጣናት ውይይት አንብቦ እንደጨረሰ በፍጥነት ወደ ሉዊስ ቢሮ ነበር ያመራው።

ሉዊስ በዛን ወቅት ኮትና ሸሚዙን አውልቆ እስፖርት እንደሚሰራ ሰው በከነቴራ ብቻ በመሆን የሀይማኖት ግጭት በቀላሉ ሊነሱባቸው የሚችሉ የአፍሪካ አገሮች ላይ ብጥብጥና እልቂትን እንዴት ማስነሳት እንደሚቻል የሚዘረዝር ንድፍ እየፃፈ ነበር።

“ይህን ወረቀት አንብበው እስኪ?” ፒየር እየሰጠው ተናገረ።

ሉዊስ ሁለቴ ደግሞ አነበበውና እንዳቀረቀረ “ሰውዬውን ልናገኘው ብንችል ጠቃሚ ይሆን ነበር.....” አለ።

“እኮ ለምን አናስፈልገውም?”

እይታውን በወረቀቱ ላይ ወደተፃፈው ስም እየመለሰ “በርሔ አብርሃ እስካሁን ተገድሏል።”

“እንዴት ልናውቅ እንችላለን?”

“ባለስልጣናቶቹ ይህን ውይይት ያደረጉት ከረዥም ጊዜ በፊት ነው። ውሳኔ ላይ የደረሱትም ሰውዬው ይገደልና ፓርቲው ይፍረስ በማለት ነበር። ታዲያ እስካሁን ይህን ማስተግበር የሚያቅታቸው ይመስልሀል?”

“ምናልባት አይታወቅም ብንሞክርስ?”

“ጊዜያችንን ከማባከን ውጪ ጥቅም የለውም”

“ሉዊስ.....” ፒየር እንዴት ሊያሳምነው እንደሚችል ግራ እየተጋባ ቀጠለ “.....አየህ ራሱ ሰውዬው በመገደሉ ልናገኘው ባንችል እንኳ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

የሱ ፓርቲ አባል የነበረ የቅርብ አጋሩን ልንደርስበት ስለምንችል እሱን እናሰራዋለን..... ትንሽ ሀሳብ ብቻ ስጠኝ?"
ሉዊስ የፒየር ምላሽ ፈገግ አሰኘውና "ምን ዓይነት ሀሳብ?"
"ሰውዬውን ከዋሺንግተን ህዝብ መሀከል እንዴት አግኝተን ልናጠምደው እንደምንችል?"
ሉዊስ እስኪሪኘቶውን አስቀምጦ ተነሳና የህሊናውን የልምድ ማከማቻና መፍጠሪያ ካዝና መበርበር ጀመረ፡፡
ከሶስት ደቂቃ በኋላ "እንድ ቀላል መንገድ አለ፡፡ ሌላ የተሻለ ልንፈጥር እስከምንችል ድረስ..... እኛ ወደ ምናሳድደው ሰው ከምንሄድ ይልቅ እሱ ራሱ ወደ እኛ እንዲመጣ ማድረግ ነው..... "
ፒየርም የሉዊስን የወጥመድ ሀሳብ በህሊናው መገልበጥ ጀመረ፡፡ እናም እንደ ሁልጊዜው ሁሉ ምርጥ ቀላል እና ውጤታማ ሊያደርጋቸው የሚያስችል ነበር፡፡

«««««« »»»»»»

ሰዓቱ በዋሺንግተን ዲሲ አቆጣጠር ከለሊቱ 5፡20 ብሎዋል፡፡ በዚህ ከተማ ለ"ሉዊስ ወኪሎች" ድርጅት በኮንትራት ከሚሰሩ ታማኝና በርካታ ሰዎች መሀከል አንድ እድሜው አርባ ሶስት ዓመት የሆነ አሜሪካዊ ጐልማሳ በፍጥነት "ኒው ላይን" የሚል የግል ጋዜጣ አሳታሚ ድርጅት ቢሮ ለመድረስ በራሱ መኪና እየከነፈ ነበር፡፡ ጋዜጣው እለታዊ ሲሆን በመላው ዲሲና በአቅራቢያው ያሉ በካርታ ከተሞች ላይ ሰፊ ተነባቢነት ያለው ጋዜጣ ነው፡፡ በዋናነት በአፍሪካ ፖለቲቲካዊ ጉዳዮች ላይ የሚፅፍ ሲሆን በተለይ በስደኛው ህብረተሰብ ሰፊ ተነባቢነት አለው፡፡ የሚባክን ጊዜ አልነበረም፡፡ ጎልማሳው ሰው በመጣበት ፍጥነት የዋና አዘጋጁ ቢሮ ገባ፡፡ ይተዋወቃሉ፡፡
"ጆን ዛሬ ምን ጉዳይ ቢገጥምህ በዚህ ሰዓት መጣህ?" አዘጋጁ በሚያሞቅ ፈገግታ እጁን ለሰላምታ እየዘረጋለት ጠየቀው፡፡
"ስራ..... ጥሩ ክፍያ የምታገኝበትን ስራ ላሰራህ....."
"ለኔ..... ላንተ.....ወይስ ለሁለታችንም የሚጠቅም?"
"ጥቅሙ ከኛም ሊያልፍ ይችላል፡፡ ጊዜ ስለሌለ ወደ ተግባሩ ብንገባስ?"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“ይህን ያህል አጣዳፊ.....?”
“አዎ..... ለመሆኑ ነገ ጠዋት የሚወጣው ጋዜጣ ህትመት ተጀምሯል?”
“ከሰላሳ ደቂቃ በኋላ ይጀመራል” አለ አዘጋጁ ፂሙን እያከከ
“ጥሩ..... ፖለቲካ በሚለው ገፅህ ላይ ግማሹን ቦታ ለአንድ አጭር ማስታወቂያ መሰል ፅሁፍ እንድትሸጥልኝ እፈልጋለሁ?”
“የዛሬው ሞልቷል..... የነገው ማታ ህትመት ላይ ቢወጣስ?”
“የሃያ አምስት ሺህ ዶላር ክፍያ ታገኝበታለህ!”
“ሃያ አምስት ሺህ!.....” አይኖቹን ጆን ላይ አፈጠጡ።።

የአሳታሚው ድርጅት ባለቤት ሴት ስትሆን የህትመቱን አጠቃላይ ስራ ሀላፊነትን ወስዶ የሚሰራው ዋና አዘጋጁ እና የኤዲተሮችን ቦርድ የሚመራው እሱ ነበር።።

ገንዘብ አጥፊ ስለሆነ በየወሩ የሚያገኘው ደሞዙ አይበቃውም።። አልፎ አልፎ እንደዚህ አይነት ጥቅም የሚያስገኙለትን ስራዎች ለድርጅቶችና ለግለሰቦች በድብቅ እየሰራና የሚያገኘውን ክፍያ ወደ ኪሱ በመክተት ኑሮውን ይደጉማል።።
“ለመሆኑ ጉዳዩ ምንድነው?”

ጆን እያሳጠረ ገለፀለትና ከኪሱ አነስ ያለች ወረቀት አውጥቶ በርቀት አሳየው።። ወረቀቷን ከመስጠቱ በፊት ግን ሃያ አምስት ሺህ ዶላሩ የተፈረመበትን ቼክ ጠረጴዛው ላይ አደረገለት።።

አዘጋጁ አላመነታም ቼኩን አንስቶ ኪሱ ከተተና ወረቀቷን ተቀበለው።።
ወረቀቱ ላይ ለሰፈረው ፅሁፍ የተሰጠው ርዕስ “ነፃ መሆን ለሚፈልጉ አፍሪካውያን ሁሉ ነፃነት!” ይላል።።

የያዘው ሀሳብ ስለ ነፃነት ጥቅም የሚያትት ሲሆን የመጨረሻ መስመሮቹ ላይ

«.....*በአፍሪካ ውስጥ ነፃ መንግስት ሊያቋቁም የሚፈልግ እና በተለይ ተቀማጭታቸው ዲሲ አካባቢ ያሉ ፓርቲዎች ሁሉ ከሰር በሰፈረው አድራሻ መሰረት በስልክ፣ በፋክስ፣ ወይም በኢሜል እየተጠቀሙ ያሉበትን ቢያስመዘግቡ ይህ ፋውንዴሽን የገንዘብ የምክርና የተለያዩ የአቅም ድጋፎችን በነፃ ሊሰጣቸው የተቋቋመ መሆኑን ያሳውቃል።*» የሚል ነበር።።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ህትመቱ ከሶስት ሰዓት በኋላ ተጠናቆ የቀጣዩ ቀን ጎህ ከመቀወዱ በፊት ጋዜጣው በየ ጐዳናዎቹና መደብሮች መስኮት መሸጥ ጀመረ።።

በጋዜጣው ላይ የታተመው የፅሁፉ አድራሻ የሚገኝበት የጆን የግል ቢሮ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ በስልክ፣ በፋክስና በኢሜል በሚላኩ አድራሻዎች ተጨናነቀ።።

ከአፍሪካ ውስጥ በኮንጐ፣ በአንጐላ፣ በሱማሊያ፣ በኢትዮጵያ፣ በአልጄሪያ፣ በኡጋንዳ፣ በላይቤሪያ፣ በታንዛኒያ፣ በዙምባቤ፣ ሱዳን ናይጄሪያ ላይቤሪያ ሴኔጋል..... ውስጥ የሚንቀሳቀሱና ገና እንቅስቃሴ ለመጀመር የተዘጋጁ ከሁለት መቶ በላይ የሚሆኑ ፓርቲዎች አድራሻቸውን ለጆን ቢሮ ሰጡ።።

ጆን ዝርዝሩን በአግራሞት እያየው "እነዚህ ሁሉ የየራሳቸውን መንግስት ለመመስረት የሚፈልጉ ደደቦች..... እንዴት አንድነትና ህብረት የሚያመጣውን ሀይልንና ጥቅም አያውቁም?ራስ ወዳድ ሁሉ..... የስልጣን ጥማት እንጂ እውን ለአገራቸው እድገት አስበው አይመስልም!" እያለ በስላቅ እያሰላሰለ ሳለ የሚፈልገው የስልክ ጥሪ ከገመተው ወቅት ቀድሞ ደረሰው "ሀሎ"

"ሀሎ..... ነፃ መንግስት ለማቋቋም ለሚፈልጉ ፓርቲዎች በሰጣችሁት እድል መሰረት ድጋፍ እንዲደረግልን ለመመዝገብ ነበር....."

"ይችላሉ..... አስፈላጊው እገዛ ሁሉ ይደረግላችኋል"

"አመሰግናለሁ በቅድሚያ..... ከየት ልጀምር?" ጠየቀ ሰውዬው።።

"መንግስታችሁን ማቋቋም የምትፈልጉበት አገር ስም?"

"ኢትዮጵያ"

"እሺ..... የፓርቲያችሁ ስም?"

"ትግራይ ነፃ ሪፐብሊክ መንግስት ምስረታ ይባላል"

"መቼ ነው ያቋቋማችሁት?"

"እ.....ትክክለኛ ጊዜውን ባላስታውስም ከ1976-1977 እ.ኤ.አ. ባሉት ወቅቶች መሀከል"

"አሁን በዚህ አገር ቢሮ ከፍታችኋል?"

"እስካሁን አልከፈትንም በቅርቡ ግን ለመክፈት ዝግጅቱን ጨርሰናል"

ጆን የእያንዳንዱን ጥያቄ መልስ ሲፅፍ ቆየና "የምናደርግላችሁን እርዳታ ምዝገባውን እንደጨረስን በቅርቡ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

መስጠት እንጀምራለን፡፡ እናም ልንጠራችሁ የምንችልበትን አድራሻ ቢሰጡኝ" ወሳኟ ጥያቄ ይህች ነበረች፡፡
"በስልክ ልታገኙኝ ትችላላችሁ"
ጆን አቋረጠውና "በማንኛውም ወቅት ይኖራሉ?"
"ጠዋት እስከ አምስት እና ከሰዓት ከዘጠኝ እስከ ምሽት አልገኝም፡፡ ከዛ ውጪ ግን አዎ....."
"እሺ .....ቁጥሩን ይስጡኝ"
ሰውዬው ተከራይቶ በሚኖርበት ህንፃ ውስጥ ያለውን የክፍሉን ስልክ አስመዘገበ፡፡
"ጨርሰናል፡፡ መልካም ነፃ መንግስት ምስረታ እንመኝላችኋለን"
"አመሰግናለሁ" ስልኩ ተዘጋ፡፡
ቀሪው ስራ የሱ አልነበረም፡፡ ፒየር በሰጠው ሌላ አድራሻ ደወለና ግለሰቡ የሰጠውን ስልክ አስተላለፈላቸው፡፡ ለዚህ ስራውም በአንድ ቀን የአስር ሺህ ዶላር ክፍያውን ወደ ኪሱ ከተተ፡፡

«««««« »»»»»»

ሁለት ግዙፍ ሰውነትና ቁመና ያላቸው ሰዎች በዲሲ ከተማ ምስራቃዊ ዳርቻ አካባቢ ከተገነቡት የመኖሪያ ህንፃዎች አንደኛው ጋር ሲደርሱ የመጡበትን ጥቁር ካዲላክ መኪና አቁመው ወረዱ፡፡ አካባቢው በስደተኛ ነዋሪዎች መኖሪያነት የታወቀ ቦታ ነው::
ሁለቱም ሙሉ ኮትና ሱሪ ከጥቁር ካፖርት ጋር ለብሰዋል፡፡ እድሜያቸው ከአርባ ጥቂት የዘለለ መሆኑ ያስታውቅባቸዋል፡፡ አንደኛው ፈንጣጣ የበላው የሚመስለውን የፊቱን ጠባሳ ለመከለል ሰፊ ቡኒ መስታወት ያለው መነፅር አጥልቋል፡፡ ሁለተኛው ያደገው ሪዙ የገፅታውን እኩሌታ ሸፍኖታል፡፡ አረማመዳቸው የችኮላ ነበር፡፡
ከጆን የተነገራቸውን ስልክ ቁጥር የማውጫ መፅሀፍ ላይ ፈልገው የት ቦታ እንደሆነ ለማወቅ የፈጀባቸው ጊዜ ሁለት ደቂቃ ብቻ ነበር፡፡ በእንዝላልነት የባከነ ጊዜ የለም፡፡ ከአስራ አምስት ደቂቃ ጉዞ በኋላ ስልኩ የተመዘገበበት ክፍል በራፍ ላይ ደርሰው ቆሙ፡፡
መነፅር ያጠለቀው ሰው መግቢያውን ለጓደኛው ለቀቀለትና ጐኑን በመያዝ የመጥሪያ ደውሉን ተጫነው፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

በሩ ሲከፈት የተጐሳቆለ የፊት ገፅታና ረዥም የሰውነት አቋም ያለው የሃምሳ ዓመት ሰው ጭንቅላት ብቅ አለ፡፡
“በርሔ አብርሃ ማለት እርስዎ ነዎት?” በትህትና ጠየቀው፡፡
የሰውዬው ፊት በቅፅበት ሲለዋወጥ አስታወቀበት፡፡ “ተሳስታችኋል!” ብሎ በሩን መዝጋት ሲጀምር መነፅር ያጠለቀው ሰው በቅፅበት የድምፅ ማፈኛ የተገጠመለት ሽጉጡን መዞ ግንባሩ ላይ ደገነበትና ወደ ውስጥ ገፍትሮት ተከታትለው ገቡ፡፡
ከሰውዬው ሌላ ውስጥ ማንም አልነበረም፡፡
“ፈትሸው!” የደገነበት ሰው ለጓደኛው ትዕዛዝ ሰጠ፡፡
ፈትሾት ምንም እንዳልያዘ ካረጋገጠ በኋላ ከኪስ ቦርሳው ውስጥ መታወቂያውን አውጥቶ ሲያነበው ስሙ “ጎይቶም ገብረ እግዚያብሔር” እንደሚል ለጓደኛው ገለፀለት ባለመነፅሩም ይህ ሰው በርሔ ባለመሆኑ በሚያመቻቸው አኳኋን መረጃ መውሰድ እንደሚችሉ መታዘዛቸውን አስታወሰ፡፡
ኢትዮጵያዊው በድንጋጤ እየተርበተበተ የሚሰሩትን ያያቸዋል፡፡
“በርሔ አብርሃ የት ነው ያለው?” ሽጉጥ የደገነበት ጠየቀው፡፡
“እኔንጃ.....”
“ አንተ ምኑ ነህ?”
“እኔ አላውቀውም ጭራሽ.....”
ሁለቱም ሳቁ፡፡ “ጥሩ.....ረስተኸውም ከሆነ ታስታውሰዋለህ.....” ግንባሩ ላይ ደግኖት የነበረውን ሽጉጥ ወደታች መለሰና የቀኝ እግሩ መጫሚያ ላይ ተኮሰበት፡፡
“አ.....” የጣር ድምፅ አሰምቶ ወደቀ፡፡
“ታውቀዋለህ?”
“አ..... አላውቀውም!”
ሁለተኛውን ጥይት የሁለተኛው እግሩ ላይ ተኮሰበት፡፡
“አ.....ስለ እግዚያብሔር ብላችሁ አትግደሉኝ.....” በሲቃ ተማፀነ ሶስተኛዋ ጥይት የግራ እግሩን ጐልበት ሎሚ አደቀቀችው፡፡
“ወይኔ.....አ.....ኡ.....”
ተኳሹ ተጠጋውና የደቀቀው አጥንቱን በጫማው ቆሞበትና ከወለሉ ጋር አሸው፡፡ ጎይቶም ስቃዩን መቋቋም ስላልቻለ ተንፈራግጦ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

በመንሸራተት እግሩን ከሰውዬው ስር አወጣና ".....እባካችሁን..... ተውኝ.....አ....."
"ታውቀዋለህ?"
መልስ አልሰጠም፡፡ ተኳሹ ሽጉጡን ያልተመታው ጉልበቱ ላይ ደገነበት
"አዎ..... አውቀዋለሁ....."
"ምንህ ነው?"
"ጓ..... ጓደኛዬ....."
"በምን ላይ ነው ጓደኝነትህ?"
"በስራ..... ስራ ላይ ነው የተዋወቅነው....."
"ዋሽህ" አለና ሽጉጡን መልሶ ደገነበት
"እሺ.....እሺ.....እውነቱን ልናገር....."
"ቀጥል" ሁለተኛው ሰው ማስታወሻ ለመፃፍ እየተዘጋጀ አዘዘው፡፡
"ከሰባት ዓመት በፊት ሱዳን ነው የተዋወቅነው፡፡ ኤርትራ ነበርን፡፡ ከኤርትራም ወደ አሜሪካ መጣን፡፡"
"ለምንድነው የመጣችሁት?" የሚፅፈው ጠየቀ፡፡
"የፖለቲካ ድርጅት ለማቋቋም ነበር፡፡ እንቅስቃሴ ከጀመርን አራት ዓመት ሆኖአል"
"ምን የሚባል ድርጅት?"
"ትግራይ ነፃ ራፐብሊክ መንግስት ምስረታ የሚባል"
"ስንት ናችሁ?"
"ስለ አላማው ሙሉ እውቀት ያለን ሰዎች አምስት ብቻ ነን፡፡ በአባልነት ግን ወደ ሰባ የሚደርሱ..... ሰዎችን መልምለን መዝግበናል.....እ....." በስቃይ የጣር ስሜት ተውጦ
"እነሱ የት ነው የሚኖሩት?"
"እዚሁ በአሜሪካና በተለያዩ አገሮች ውስጥ....."
"አንተ ኢትዮጵያዊ ነህ?"
"አዎ ነኝ"
"የፓርቲው ዋና አዛዥ ማነው?"
"በርሔ..... አብርሃ"
"አሁን የት ነው ያለው?"
"እ..... አዲስ አበባ....."

ይህ መፅሐፍ ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“ዋሽህ!” ባለሽጉጡ በቁጣ ደገነበት፡፡
“በእግዚያብሔር ስም እምላለሁኝ አልዋሸሁም.....አ.....አዲስ አበባ ገብቶ በድብቅ መኖር ከጀመረ ሁለት ዓመት ሆኖታል፡፡”
“እዛ ሆኖ ነው ፓርቲውን የሚመራው?”
“አዎ..... በዛውም ሰዎችን ከዛ ለመመልመል ነው የሔደው”
“እዛ ስለመሆኑ ምን ማረጋገጫ አለህ?”
“በየግዜው የሚልክልኝን ፖስታዎች እና የፋክስ መልዕክቶችን ከዛ መሳቢያ ውስጥ..... አውጥተህ ተመልከት፡፡” ብሎ በደም የበሰበሱ ጣቶቹን ወደ አንድ ጠረጴዛ አመለከተ፡፡ ሁለተኛው ሰው ተራምዶ ከፈተው፡፡ በውስጡ ሃምሳ የሚሆኑ ደብዳቤዎችን የያዙ ፖስታዎች ነበሩበት፡፡ ሁሉም ከበርሔ የተፃፉ፡፡
“አዲስ አበባ የት ነው የሚኖረው?” ደጋኙ ጠየቀ፡፡
“በኪራይ ቤት ሰለሆነ ቋሚ አድራሻ የለውም፡፡.....ለጊዜው አሁን ያለበትን ቤት ስልክ ቁጥር ብቻ ነው የማውቀው.....”
“ልተኩስብህ ነው ባትዋሽ ሳይሻልህ አይቀርም.....”
“ካካ.....ካላመንከኝ.....ት.....ች...ላለህ”
“የታለ የስልክ ቁጥሩ?” ሁለተኛው ሰው ጠየቀ፡፡
“ማስታወሻ መፃፊያውን ከቦርሳው ውስጥ አውጣና እየውሞ”
ከበርካታ የስምና የስልክ ቁጥር ዝርዝሮች መሀከል አገኘውና በአይኑ ሽጉጡን ለያዘው ጓደኛው ምልክት አሳየው፡፡
“መልካም አድርገህል!” አለና አከታትሎ ጭንቅላቱን በሁለት ጥይት በረቀሰው፡፡
በመጡበት ፍጥነት አካባቢውን ለቀው ሲወጡ ጎይቶም ቤት ያባከኑት ጊዜ ሰባት ደቂቃ ብቻ ነበር፡፡
ወድያውኑ ያገኙትን መረጃ በጠቅላላ ለሉዊስ አሻገሩና የሰላሳ ሺህ ዶላር ክፍያቸውን ለመውሰድ በአካባቢያቸው ወዳለው ባንክ ጉዞ ቀጠሉ፡፡

«««««« »»»»»»

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ፒየርም ከሉዊስ ጋር ተነጋግሮ ጨረሰና በርሄ አብርሃን ፈልጎ የማግኘቱ ቀሪው ስራ የሰናይት መሆኑን ስላመኑበት የተገኘውን የበርሔን የስልክና የፖስታ ሳጥን ቁጥር ወደ ኢትዮጵያ ላኩት፡፡

  

ያማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ምዕራፍ 19

ሰናይት በአንድ ሳምንት ውስጥ ለአምስተኛ ቀንና ብዛቱን ለማታስታውሰው በርካታ ጊዜ ነበር ሙከራ ማድረጓን የቀጠለችው። ሆኖም ግን ሊሳካላት አልቻለም። የሰውዬው መገኘት ደግሞ እስካሁን ከተሰሩት ስራዎች ሁሉ እጅግ አስፈላጊና እጅግም ጠቃሚ የሆነ ጉዳይ መሆኑን ፒየር አስቀድሞ ገልፆላታል።

"ምናልባት ወደ ውጪ አገር ሄዶ ሊሆን ይችላል" ብላ ነበር ለራሷ። ሆኖም ግን በሚቀጥለው ቀን ማለዳ ላይ ስትነሳ ሰውዬውን ፈልጎ የማግኘት ተስፋዋ ገና አልተሟጠጠባትም።

ቀኑ የካቲት ሃያ አራት ሲሆን ዕለቱ እሁድ ነበር።

ያደረችው መገናኛ አካባቢ በተከራየችው ቤቷ ነበር። የቤቱ የፊት ለፊት ገፅ ወደ ምስራቅ ዞሮ የተሰራ በመሆኑ በመስኮቱና በበሩ መስታውቶች በኩል አልፋ በመግባት ወከክ ብላ የምትታየው የማለዳዋ ጀንበር በህይወት የተሞላች ትመስላለች።

ከአልጋዋ ተነስታ መጋረጃዎቹን ገለፀችና ወደ ጊቢው አፀድ እይታዋን ላከች። ፊት ለፊት በሚታየው የተስተካከለ የሳር፣ የፅድና የአበባዎች ዙሪያ የተንጠላጠሉት የጤዛ ዶቃዎች፤ ያረፈባቸውን ብርሃን መልሰው ይፈነጥቁታል። የብርሀኑ ነፀብራቅ የሚፈጥረውን ወበት ለረሺም ደቂቃ በተመስጦ ስታይ ቆየችና ክላሲል ሙዚቃ በዝቅተኛ ድምፅ በመክፈት በዮጋ እስፖርት ሰውነቷን ማፍታታት ጀመረች።

ስልኩ አንጫረረና ከተመስጦዋ አባነናት። ተራምዳ አነሳችው "ሀሎ"
"ሰናይት ኖው?"
የአነጋገሩን ቅላፄ ገና ስትሰማ ማን መሆኑን ለየች።
"አቡበከር መሀመድ!?....." ባለማመን ስሜት ጠየቀች።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“አዎ..... ደህና ኖው?” አማርኛ ሲናገር የፊደል አሰዳደሩ ያስቸግረዋል።።
“አንተን ፍለጋ መደወል ከጀመርኩ ሳምንት ሞላኝ”
“አልነበርኩም..... ሞቃዲሾ ሄጄ.....”
“መቼ ገባህ ታዲያ?”
“ቲላንት ሌሊት ገቢቼ..... ሚስት ነገረችኚና ሲላንተ ስልክ ቁጥር እንዴተውክ ደወልኩኝ አሁን.....”
“ትረሳኝ ይሆናል በማለት አስቤ ነበር”
“በችራሽ..... ቶሎ ነው ያስታወስኩኝ አንተን”
“ሰላም ነህ ግን?”
“አልሀም ደሊላ..... ሲራ እንዴት ነው?..... ጋዜጣ ማሳተም ትተሀል”
“አዎ..... አቁሜ ፈረንሳይ ሂጄ ነበር።። እዛ አንድ ዓመት አካባቢ ቆይቼ ገና መመለሴ ነው።።”
“አሁን ሲራ የለማ?”
“አዎ.....”
“ችርግ የሌም ኬኛ ጋር ትሰራለህ..... አንተ እኔን በታም እንደምትፈልግ ሰማሁ ” አለ አቡበከር።። ቀጠለ “ዛሬ እኔ ቤት ቻት እየቃምን አንቻወትም?”
“ደስ ይለኛል ጫት ባልቅምም መገናኘታችንን ግን እፈልገዋለሁ።።” አለች ሰናይት።። “ለመሆኑ ቤትህ የት አካባቢ ነው?”
“ቦሌ መስመር.....ሩዋንዳ ኤምባሴ አክባቢ.....”
“ኦው ሩዋንዳ.....” አለች ራሷም ወደዛው አቅራቢያ የተከራየችውን ቤት አስታውሳ።። “ስንት ሰዓት ላይ እንገናኝ?”
“ሴባት ይሻላል.....ኬቦሌ ወደ ሩዋንዳ የሚገነጠለው ሜዞሪያ ላይ.....”
“እሺ.....” ስልኩ ተዘጋ።።

«««««« »»»»»»

አቡበከር እና ሰናይት የተዋወቁት እዚሁ አዲስ አበባ ከጥቂት ዓመት በፊት ሰናይት የጋዜጣ አሳታሚ እያለችና እሱ ደግሞ በሱማሊያ ጠረፍ በኩል ገና ህገ-ወጥ ንግድ ለመጀመር በሚፍጨረጨርበት ወቅት ላይ ነበር።።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

እናቱ በኡጋዴን አካባቢ የሚኖሩ የኢትዮጵያ ሱማሌ ሲሆኑ አባቱ ደግሞ በሱማሊያ ማእከላዊ ክፍለ ግዛት አካባቢ ኤልዶብ በሚባል ቦታ ከታዋቂና ስመጥር ጐሳ የሚወለዱ ሰው ነበሩ።።

አባቱ መሐመድ ኢስማኤል በጐሳቸው ውስጥ ከትውልድ ትውልድ ሲወራረስ የመጣ የጠረኝነት ስምና ዝና ነበራቸው።። እሳቸውም በዘመናቸው የሶማሊያን ግዛት እንደ ብረት በደደረ ጡንቻቸው አርበትብተው ከሃያ ዓመት በላይ የገዟትን የዚያድ ባሬን በትረ መንግስት በመቃወም ወደ ኡጋዴን በተደጋጋሚ እየመጡ በመሸሸግ ሲታገሉ ቆዩ ከከማል እናት ጋር የተዋወቁትና ያለጋብቻ እሱን ጨምሮ ሶስት ወንድ ልጆች የወለዱትም ወደ ትግል ከመግባታቸው በፊት እዚሁ የኢትዮጵያ ክልል ላይ በሚመላለሱበት ወቅት ነበር።።

በ1983 ዓ.ም. የዚያድ ባሬ ስልጣን ሲገረሰስ ሶማሊያም ማንም ሊያበርደው ወደማይችለው የጐሳና የአንጃዎች ጦርነት ውስጥ በመዘፈቅ ለውድቀት ተዳረገች።። በዚሁ ወቅት ሞቃዲሾን በበላይነት ለማስተዳደር በተደረገው ሽኩቻ መሀመድ ኢስማኤል ህይወታቸውን አጡ ሚስታቸውም በጥቂት ወራት ልዩነት በድንገተኛ ህመም አረፉ።።

ይህ ሲሆን አቡበከር እና ሁለቱ ወንድሞቹ አግብተው የየራሳቸው ቤተሰብ መስርተው ነበር። በወቅቱ የተፈጠረው የሐገሪቷ ያለመረጋጋት ሂደት አቡበከርን ስላሰጋው የኡርጌሳ ተወላጅ የሆነችው ሚስቱንና ሁለት ልጆቹን አስከትሎ ወደ አዲስ አበባ በመምጣት መኖር ከጀመረ አራት አመታት ሊደፍን የወራት ጊዜ ቀርቶታል።።

ሁለቱ ወንድሞቹ ግን ዛሬም ድረስ የአባታቸውን ፈለግ በመከተል ሞቃዲሾን የሚያማክለው ደቡባዊ ሶማሊያ ክልል ላይ የበላይነትን ተቀዳጅተው አገሪቷን ለመምራት በየወቅቱ ከተቃዋሚ አንጃዎች ጋር በጦርነት እየተሻኮቱ ይገኛሉ።።

አቡበከርን ከሰናይት ጋር እንዲተዋወቁ ያደረጋቸው ሰው ደግሞ በወቅቱ ለሰናይት የጋዜጣውን ህትመት የሚያስፈፅምላት አንድ የግል ማተሚያ ቤት የነበረው ግለሰብ ነበር።።

አቡበከር ለዛ ግለሰብ ለማተሚያ ስራው የሚያስፈልጉትን ቀለሞች፣ ማጣበቂያ፣ ወረቀትና ሌሎች ቁሳቁሶችን በሶማሊያ ድንበር

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ወደ ኢትዮጵያ በህገ-ወጥ መንገድ እያስገባ ይሸጥለት ነበር፡፡ ሰናይትም ከሰውዬው ጋር በነበራት ቀረቤታ ምክንያት ሁሉንም ሳይደብቅ ይነግራት ነበር፡፡ ከዛም አልፎ በአንድ ቀን ቢሮ ተቀምጠው እየተጫወቱ ሳሉ አቡበከር መጣና ከሰናይት ጋር ተዋወቁ፡፡

በወቅቱ ለማተሚያ ቤቱ ባለቤት የተወሳሰበ ችግር ገጥሞት ነበር፡፡ ሁለት ትልልቅ ማሽኖቹ በብልሽት ምክንያት ቆመው መለዋወጫ ጥበቃ ረጅም ጊዜ የወሰደበት ሲሆን ይባስ ብሎ የቀረው ሶስተኛውና አሮጌው ማሽን ጭራሽ ተሰብሮ ቆመ፡፡ ሶስቱ ሰዎች ቢሮ ቁጭ ብለው ኋላ ቀር የሆኑትን እነዚህን የህትመት ማሽኖች በዘመናዊ መተካት እንደሚያስፈልግ ሀሳብ መጣ፡፡

ይህ አጋጣሚ አለቡበከር ምን ያህል አቅም እንዳለው ማሳያ መሆን ቻለ፡፡ ለማሽኑ ግዢ የሚያስፈልገውን የቅድሚያ ክፍያ የማተሚያ ቤቱ ባለቤት ካለ ምንም ማስያዣ ለአቡበከር ለመስጠት አላመነም፡፡

ከብዙ ክርክር በኋላ ሰናይት "በኔ ዋስትና የክፍያውን አንድ ሶስተኛ ገንዘብ ይሰጠው" አለች፡፡

በግማሽ ሞኝና በግማሽ ስሜታዊ ሆኖ እንደነበረ የገመተችው ግን አቡበከር ገንዘቡን ተቀብሎ ለሁለት ወራት ድምፁን አጥፍቶ ሲሰወር ነበር፡፡

ከሁለት ወር በኋላ ባላሰቡት አንድ ዕለት አቡበከር እቃውን በከባድ መኪና አስጭኖ የማተሚያ ቤቱን በር አስከፍቶ ገባ፡፡

የቆየበትን ምክንያት ሲገልፅ የእቃዎቹ ግዢ ከህንድ ተከናውኖ በርካታ ጦርነቶች የሚካሄድባቸውን የሶማሊያ ግዛትን በማለፍ ከዛም በብዙ ቦታዎች የህገ-ወጥ ንግድ ቁጥጥር የሚደረጉባቸውን የኢትዮጵያ ክልሎችን ኬላ በጉቦና በተጭበረበረ የሀሰት ሰነድ ለማሳለፍ ሲል ያባከነው ጊዜ መሆኑን ገለፀ፡፡

ስራውን አከናውኖ ሲጨርስ ሰናይትን "እንቴን ኬማንም ቤላይ አሜሰግናለሁ..... ካሁን ጀምሮ ሂዎቴን የምሌውጥበት ዬራሴ የሆነ ገንዘብ ኢንዳገኝ ረድተሀልና..... በምትፈልግ ጊዜ ሁሌ..... ትራኝ..... የምችላቸውን ሁሉ አዴርጋለሁ..... ላንቴ....." ብሏት ነበር፡፡ የማተሚያ ቤቱ ባለቤትም እጅግ ዝቅተኛ በሆነ ዋጋ የአዲስ ማሽን ባለቤት መሆን ቻለ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

ለሰናይት በወቅቱ የገረማት ጉዳይ ይህንን የሚያህል ግዙፍ ማሽን መንግስት "አለሁ" ብሎ በሚያወራበት ሀገር ውስጥ ከሱማሌ ጠረፍ አንስቶ መሀል አዲስ አባባ ድረስ በህገወጥ መንገድ እንዴት መግባት እንደቻለ ነበር። ከዛ በውሃላ ታሳትመው ነበረው ጋዜጣ ላይ በተለያየ ርዕስ ስር የፃፈች ቢሆንም ድርጊቱ ግን ስለመቀጠሉና ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ሳይቀሩ የተመሳሳይ ድርጊት ተሳታፊዎች እንደነበሩ ደርሳበታለች።

ይህም ቢሆን ግን አቡበከር እንዳንዴ በፖለቲካ ጉዳዮች ዙሪያ ገባ ወጣ እያለ በኢትዮጵያው የሶማሌ ክልል ውስጥ ከመንግስት ጋር ይጋጭ እንደነበረ ለሰናይት ገልፆላታል። እሷም ቦታው ድረስ ሄዳ እውነታውን በማየት ዘገባ ሰርታበታለች።

ብዙ ጊዜ ለግጭቱ መንስኤ የሚሆኑት ጥያቄዎቹ ግን ስልጣንን የሚመለከቱ ሳይሆኑ የኢትዮጵያን ሶማሌ ክልል አጠቃሎ በሌሎች አጐራባች ክልሎች ውስጥ የሚካሄደውን የህገ-ወጥ ንግድ ስራው በመንግስት ወታደሮች ሲስተጓጐሉበት በጠመንጃ እስከመታኮስና የክልሉን ሌሎች ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችን እንዲሁም ተመሳሳይ ነጋዴዎችን በማነሳሳት ወደ መግንጠል ጥያቄ እንዲያመሩ እያደረጋቸው ይገኛል።

««««« »»»»»

ሰናይት ለምታስፈፅመው ዓላማ እንዴት አግባብታ መጠቀሚያ ልታደርገው እንደምትችል እያሰላሰለች አረፈደች።

ረሃብ ሲሰማት ተነሳችና ወደ ኮመዲናው በመሄድ ዳቦና የለውዝ ቅቤ እሽግ የአናናስ ጭማቂ ይዛ ወደ አልጋዋ በመመለስ ከምግቡ ግማሹን ጭማቂውን ግን ሁሉንም ጨረሰች።

ወደ ባኖው በማምራት ሻወር መውሰድ ስትጀምር ህሊናዋ አላረፈም። በቀጣዩ ዕለት ከመቼውም ግዜ የከፋ ስራ እንደሚጠብቃት እያሰበች ነበር። የዛሬው ስራ ከዛኛው ጋር ሲነፃፀር ይህኛው ምንም ያህል አስቸጋሪና አስጊ ሊሆንባት እንደማይችል አሰበች። ግን ደግሞ ተራ ያልሆነ.....

የቀጠሮው ሰዓት መቃረብ ሲጀምር ልብሷን ለባብሳ ከቤት ወጣች። የአየሩ ሙቀት ያስመርራል።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ቦታው ቀድማ የተገኘችው እሷ ነበረች። ከመዞሪያው በስተቀኝ በኩል ያለው የአጥር ግምብ ስር ቆማ ጥበቃ ጀመረች። ከቀጠሮው የአስራ ሁለት ደቂቃ እንዳለፈ ወደ ቦሌ የሚወሰደውን መንገድ ይዛ ትጓዝ የነበረች ላዳ ታክሲ ፍጥነቷን ቀንሳ ወደ ቀኝ ተጠመዘዘችና ጥቂት ሜትሮችን አለፍ ብላ ቆመች።

የፊተኛው በር ተከፈተና ሲጃራ የሚያጤስ ሰው ወረደ።እንደ ኮት የደረትና የታች ኪስ ያለው እጅ ጉርድ ነጭ ሸሚዝ ግራጫ ቀለም ካለው ስስ የጨርቅ ሱሪ ጋር በሸበጥ ጫማ አድርጓል። ወደሷ ሲመጣ አየችው።

አቡበከር ነበር። ቁመናው ረዥም ሲሆን ወደፊት የገፋ ቦርጭና የገዘፈ መቀመጫ አለው። ሲራመድ ቀልጣፋ አይደለም። ያለእድሜው ግዙፍ ሰውነት በመሸከሙ የስልሳ አምስት ዓመት ሰው ይመስላል።

“ሰናይት..... ደህና ኖው?”

“ምንድነው ይሄ ሁሉ ውፋሬ?.....” እየተጨባበጡ ጠየቀችው።

“ተመችቶ ኔዋ.....”

ፈገግ እያለ “እንዴት.....ነው አንቴ ደግሞ ከስቷል...” በሲጃራ የጠቆሩት ከንፈሮቹን ሲያላቅቅ ከቡኒነት አልፈው መሸራረፍ የጀመሩ ጥርሶቹ ታዩ። ስልክክ ብሎ ፀየም ያለ ፊቱ ላይ የበቀለ ፂሙና ፀጉሩ በሽበት ስለነፃነት ቡኒ ቀለም ተቀብቶዋቸዋል። የእጆቹ መዳፎችና የጥፍሮቹ ጫፎች ወደ መጥቆር እየሄዱ ነው።

ተያይዘው ወደ ታክሲዋ በማምራት አቡበከር ከፊት ሰናይት ከኋላ ገቡ።

“ተ.....ዋወቀው ዘመድ.....ኖው....”

ከኋላ ተቀምጠ የነበረው ሶማሊያዊ ከንዶቹ ላይ አጋድሞት የነበረውን ወፍራምና ረዥም የጫት ዙርባ ገፋ አድርጐ እያያት “ከድር እባላለሁ....”

“ሰናይት.....”

ታክሲው ይዞዋቸው በመሄድ የመጨረሻ ማዞሪያው ጋር ከመድረሱ በፊት “ቤዚህ ታጠፍ.....” አለ አቡበከር ወደ ግራ አቅጣጫ በኮረኮንችማ መንገድ እያመለከተ። ለሶስት ደቂቃ እንደተጓዙ አስቁመው ወረዱና የአንድ ቪላ ቤት ብረት በር አስከፍተው ገቡ።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ጊቢው ውስጥ መለስተኛ ድግስ ያለ ይመስላል። ሁሉም የሶማሊያ ዜጋ ናቸው። ወደ ሰላሳ የሚጠጉና በተለያዩ የእድሜ ክልሎች ውስጥ የሚገኙ ወንዶች ሴቶችና ህፃናት በቡድን በቡድን ሆነው ይሳሳቃሉ፣ ያውካካሉ፣ ይጨቃጨቃሉ..... ከወንዶቹ አብዛኞቹ ይቅማሉ።

አንዱ አጠገቡ ላለው ሲያወራ ከጊቢው ውጪ ያለ ሰው እስኪሰማ ድረስ ጮኾ ካልተናገረ የልቡ አይደርስለትም። በዛ ላይ ብዙ ጊዜ ተናጋሪና አድማጭም አይለይም። ሁሉም እኩል ይጪጪሀል።

አቡበከር ቢሰሙትም ባይሰሙትም ግድ ሳይሰጠው በሶማሊኛ ትርጉሙ ያልገባትን ነገር እየተናገረ ወደ ቤት ገቡ።

ቤቱ ትልቅና ከደንጊያ የተሰራ ሲሆን ሰፊ ሳሎን፣ ሶስት የመኝታ ክፍሎች፣ ባኞ፣ ማብሰያና ሌሎች የጓሮ ክፍሎች አሉት።

ወደ ሳሎን ሲገቡ የሳሎኑ ሙሉ ወለል በውድ ምንጣፍ ተሸፍኗል። አነስተኛ እንደ ኩርሲ ያሉ ወንበሮች ሲኖሩ ቀሪው የቤቱ ዙሪያ ግን የውጭ አገር ስሪት የሆነ "አረቢያን መጅሊስ" ተነጥፎበታል። ከላዩም የሚዳ አህያ የመሰለ ኹንጉርጉር ቀለም ባለው ፀጉራማ አልባስ ተሸፍኗል።

"አንተ ደስ ያለህ ቦታ ኩች በል.... እኛ ኢዛ ጋር ኢንሁን....." ብሎ በስተቀኝ የፊት ለፊቱ ጊቢ በመስታውቱ ወደሚታይበት ጠርዝ አመለከተና ሸበጡን አውልቆ መጅሊሱ ላይ ተቀመጠ።

"ሱራር!.....ሱራር.....!" ተጣራ።

ፀየም ብላ ረዘም ያለ ቀጭን ቁመና ያላት ሴት ቀይ ድሪያዋን እየጐተተች ከውስጠኛው ክፍል ብቅ አለች። በሱማሊያ ቋንቋ የሆነ ነገር አላትና ወደ ሰናይት ዞሮ "ሚስት ነች ቴዋወቃት"

ወደሷም እያየ "ቲላንት ማታ.....ደውሎ ዬነበረው ሴትዮ.....ኖው" በቆመችበት ፈገግ አለች። ረዘም ብለው የተስተካከሉት ችምችም ጥርሶቿ ከቀጭኑ ፍንጭታ ጋር ልዩ ውበት ፈንጥቀውባታል።

"ሱራር እባላለሁ....." አማርኛ ከቧላ የተሻለ ትችላለች።

"ምግብ.....አምቺልን....."

በእሺታ ተመልሳ ወጣች። የዶሮ ሾርባ፣ የተቀቀለ ሩዝ በዳቦ፣ ከአትክልት የተሰሩ ምግቦች ቀረቡ።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

እንደየ አቅማቸው በሉለት፡፡
አቡበከር እና ከድር በዛው ጫት መቃም ቀጠሉ፡፡ሰናይት ግን ቅማ የማታውቅ መሆኑን ገልፃላቸው በቅመም የተፈላ ሻይ ቀርቦላት ጨዋታ ጀመሩ፡፡
ሰናይት ተለሳልሳ "ለመሆኑ ምን እየሰራህ ነው አሁን?"
"ስራ ሞልቷል... ሁሉንም ስራ እንሰራለን" በደፈናው መለሰላት
"ያው እንደ በፊቱ ኮንትሮባንድ ነው ወይስ ፈቃድ አውጥተህ?"
"ኮንትሮባንድ ኔው.....እንጂ..... እ...ሌነገሩ የዛሬ አሜት አከባቢ ፍካድ ሌማውጣት እኔ ጠይቆ ነበር፡፡ ግን በፍካድ.....የሚሰራ ከሆነ እንዲምከስር ጓደኞች ስሌነገሩኝ ቴውኩና ቤዛው ኬተልኩኝ.... "
"የመንግስት ተቆጣጣሪዎች አያስቸግሩህም?"
"አንዳንዴ አዎ.....አሁን ግን ኬሁሉም ጋር ቴዋውኬናል.....ጉቦ ትከፍላሌህ ያለፋል....."
"የት የት ባሉት ቦታዎች ውስጥ ኮንትሮባንድን ማንቀሳቀስ ትችላለህ?"
"ያው..... ሲገባ ከሶማሊያ በርበራ በኩል አድርጐ ኖው.....ኬዛም በሞቃዲሾ ኢና በየ መንገዱ ላይ ወንድሞቼ የሚመሩ ወታደር ስላሌ ታጅቦ አርትሼክ የሚባለው ድንበር ድረስ ይሜጣል፡፡ ኬዛም ሁለት አማራች አሌ..... አንዱ በፌርፌር፣ ሙስታሂል፣ ከላፎ፣ ጐዴ..... ከብሪደሀር ደገሀቡር ጂግጂጋ ሲሆን.....እ..... ሌላው ፌርፌር፣ ሺቦላ፣..... ከብሪደሀር..... ደገሀቡር አዲርጐ ጂግጂጋ ድሬዳዋ..... እያለ ኖው..... ወይም ደግሞ ሌላ በር አሌ....."
የቀነጠባቸውን የጫቱን ዘለላ ወደ አፉ እየከተተ መናገሩን ቀጠለ
".....በዶሎ ኦዶ..... ሀርገሌ.....ያደርጊና ከፈለገ ሲዳሞ ወይም ወደ ባሌ መሄድ ይችላል፡፡"
"ሌላስ በየት በኩል እንደፈለከው ማስገባትና ማዘዋወር ትችላለህ?" ሰናይት ጠየቀች፡፡
"እ.....ያው..... የኢትዮጵያ ጠረፍ ወደ አምስት ሜቶ ኪሎ ሜትር ይጠጋል፡፡ይህ ጠረፍ ኬጂቡቲ ከሶማሊያና ከኬንያ ጋር የተያያዘ ኖው፡፡ ቡዙ.....ጊዜ በአርቲሺክና በጂግጂጋ በኩል ኢንስራ እንጂ .....ካስፈለገ በሁሉም አቅታጫ መንከሳቀስ ይቻላል" ሲጃራ እየለኮሰ መለሰላት፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“እ.....ያኔ እንገናኝ በነበረበት ወቅት ላይ አንድ ነገር አጫውተኸኝ ነበር፡፡” አለች ሰናይት አሁን ለማወቅ ያህል ብቻ የምትጠይቅ ለማስመሰል እየጣረች ቀጠለች “.....በኢትዮጵያ ስር የተጠቃለሉትን የሶማሊያ ክልሎች መገንጠል አለባቸው የሚል እቅዳችሁን ከምን ላይ አደረሳችሁት?”

“እ.....ኢኔ እንኳ አሁን ትቼዋለሁ.....ምክንያቱም ባሁኑ ሴዓት ያ ክልል በኢትዮጵያ ስር ኖው ያለ ይባል እንጂ በሶማሊ ሂዝብ ኖው እንደተፈለገ የሚታዘዘው፡፡..... ሁሉም ሶው ኮንትሮባንድ ይነግዳል.....ቱሩ ኑሮ ይኖራል.....በቃ፡፡ አሁንም ቢሆን ግን ስራ ኢንዳንሴራ ኬተከለከልን.....በኡጋዴን አክባቢ ባሉት ወታደሮች ጋር ቤመቀላቀል ቴዋግተን ኢንገነጠላሌን.....”
“አዎ!.....እሱ ነው የሚሻላችሁ፡፡ አየሀ በጣም ሊረዳችሁ ከሚችል የውጪ አገር ድርጅት ጋር ላገናኛችሁ እችላለሁ”
አቡበከር ሲያስብ ቆየና “ሌጊዜው አሁን..... ይቆይ.....አሁን..... ገንዘብ ሜያዝ ነው ዬሚሻለን”
ምላሹ ለሰናይት የመርዶ ያህል ቅስም ሰባሪ ነበር፡፡
ጥቂት ቆይታ “ለመሆኑ በኮንትሮባንድ ምን ምን ማስገባት ትችላለህ?”
“ጌንዘብ ማስገኘት እስከቻሌ ድረስ.....የፈለገው ይሁን.....ማስጌባት ይቻላል፡፡....”
“የጦር ማሳሪያ.....ምናምን ትችላለህ?”
“ቤየጊዜው ከሶማሊያ እያስገባን ኢንሸጣለን ኢሱንም.....”
“ለግለሰብ አንድ ሁለት እያስገባችሁ.....ወይስ በደንብ?”
“በብዛት ኖው.....በትልልክ መኪናዎች እያስቻንን”
“ለመሆኑ ማነው የሚገዛችሁ?”
አቡበከር ፈገግ አለና “ሚስትር ኖው.....ሌሌላ ሶው አይኔገርም.....”
“ጋዜጣ ላይ ዜና አድርጋ ታሳትመዋለች ብለህ ነው” እየሳቀች አዋዝታ ተናገረች፡፡
“አይ ሌሱ ሳይሆን..... እንዳትናገር ሲላሉኝ ኖው....ግን.....ኬፈለክ መንገር ኢችላለሁ..... አንቴን አሚናለሁ.....የመንግስት ተካዋሚ የሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች ናቸው፡፡ ቡዙ ጊዜ አስገብቼ ሸቼላችዋለሁ፡፡”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“አሁንም ብትጠየቅ ማስገባት ትችላለህ?”
“ዋናው ጌንዘቡ ኖው.....የሚፈልጉትን ያህል..... ይቻላል፡፡”
“ብትያዝስ ግን?”
“ማነው.....የሚይዘኝ?.....ሶማሊ ክልል ኢኮ በኢትዮጵያ ካርታ ስር ተጠቃላ ቲገኝ እንጂ የኢትዮጵያ ሚንግስት አያዝባትም..... አዚዛለሁ..... ካሌ ደግሞ ኦጋዴን በረሃ ገብተን ወታዴር እያሰለጠንን ኢንዋጋለን፡፡”
“ እዛ ክልል ላይ ያሉት የኢትዮጵያ ወታደሮችስ?”
“ለታኢታ ኖው ዬተቀመጡት.....”
ሰናይት አቡበከርን አሁን በሚጓዝበት አካሄድ ፈፅሞ ልታጠምደው እንደማትችል ተረዳች፡፡ ቢሆንም ግን ወደ ኢትዮጵያ እንዲገቡ የሚደረጉትን የጦር መሳሪያዎች በክፍያ ሊያሻግርላት እንደሚችል ገብቷታል፡፡ ውጤታማ የማድረግ አቅሙ ግንምን ያህል አስተማማኝ እንደሆነ ለማወቅ አልቻለችም፡፡
“አንቴስ አሁን.....ምን ሌመስራት እያሰብክ ኖው?” አላት::
“ገና አላሰብኩበትም፡፡”
“ኬፈለክ ኬኛ ጋር ሜስራት ትችላሌህ.....ጌንዘብ ችግር የለም፡፡ ኬሌላ አበድራለሁ.....”
ሰናይት በትክክል አላዳመጠችውም:: ህሊናዋ እንዴት ወደ ግቧ ልታመጣው እንደምትችል ነበር የሚያስበው::
ቀጠለች መናገር “እ.....እዛ ፈረንሳይ እያለሁ አንድ ድርጅት የሆነ ጥያቄ አቅርቦልኝ ነበር፡፡”
“ሚን?”
“ድርጅቱ ለስራው የሚከፍለው ገንዘብ እስከ አምስት ሚልዮን ብር እንደሚደርስም ገልፀውልኛል.....” የአቡበከር አይኖች ጮልተው ተከፈቱ፡፡
ጉንጩን ያሳበጠውን ጫት ማኘክ አቁሞ ሲጃራውን በማከተታተል እየማገ “ሲራው አስቸጋሪ ኖው?”
“ከኔ ይልቅ አንተ ታዋቀዋለህ ስለስራው.....ቅድም እንዳልኩህ የጦር መሳሪያዎችን ወደ ኢትዮጵያ በድብቅ ማስገባት ይፈልጋሉ፡፡እና ይህን ማድረግ ለሚችል ሰው የአምስት ሚልዮን ብር ክፍያ እንደሚፈፅሙለት ነግረውኝ ነበር፡፡”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“በሶማሊያ ካሉት ወንድሞቼ ጋር እመካከራለሁ..... ሚንም ችግር ዬለም..... በርበራ ዬኛ ኖው..... ቤሱ ገብቶ ወዴ ኢትዮጵያ ቤጣም .....ኬላል ኖው.....”

“እኔም ይቻላል ልበላቸዋ.....”

“ትንሽ ቀን ተብክ ኢኔ ደውላለሁ:: ቡዙ ዬሰው ኃይል አሌ....ስራውን አቢረን ኢንሰራዋልን...”

ምሽቱ ወደ አንድ ሰዓት ሲቃረብ ሰናይት ለመሔድ ተነሳች፡፡ አቡበከርም ከአሁን በኋላ አዲስ አበባ እንኳን ባይኖር እንዴት በቀላሉ ልታገኘው እንደምትችል ገልያላት በጅጅጋ የሚገኝ የስልክ ቁጥር ሰጣት፡፡ እዛም ከሌለ ጅጅጋ ባሉት ሰዎች በኩል ሞቃዲሾ ድረስ መልእክቱ ሊደርሰው እንደሚችል ነገራትና መጨረሻ ላይ “ሌነገሩ እዚሁ..... ቡዙ ሳልኮይ አልኬርም.....” አላት፡፡

ዘወትር ተደውሎለት እየተጠራ አገልግሎት የሚሰጣቸው ታክሲ መጣና ከቤት ይዟት መንገድ ጀመሩ:: ኮረኮንቹን መንገድ ጨርሰው አስፓልት ደረሱ፡፡

ዙሪያ ገባው በጠቅላላ ሶማሊያኖች ብቻ..... አካባቢውን መንግስት ለዛ አገር ስደተኞች ከልሎ የሰጣቸው እስኪመስል ድረስ ብዛታቸው ማንንም ያስገርም ነበር፡፡

ሱቅ አላቸው..... ምግብ ቤቶች ከፍተዋል..... የአገራቸውን አልባሳቶችና ቁሳቁሶች የሚገበያዩበት መደብሮች..... ጫት ቤቶች..... ትንሿ ሶማሊያ በአዲስ አበባው ቦሌ ሩዋንዳ ሰፈር ተመስርታ ነበር፡፡

  

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ምዕራፍ 20

ሉዊስ በቀኝ እጁ ሁለት የተለያየ መጠን ያላቸው ነጭ ፖስታዎችን እንደያዘ የፒየርን ቢሮ በር ከፍቶ ገባ። ሰዓቱ በፓሪስ አቆጣጠር ከቀኑ 9፡ 20 ብሎዋል።

ፒየር በሰናይት ከተላከለት አንድ ወፈር ያለ ጥራዝ ላይ እቅድ የተነደፈበት ፅሁፍ እያነበበ አጫጭር ማስታወሻዎችን እየያዘ ነበር። ሊዊስ ሲገባ ንባቡን አቋርጦ ቀና እያለ አየውና "ልመጣ ነበር?"

ሊዊስ ከጠረጴዛው ፊት ያለውን ወንበር ጐትቶ እየተቀመጠ "ምን አዲስ ነገር አለህ?"

ፒየር ጥራዙን አጥፎ ማስታወሻውን እያየ "ያለፈ ጊዜ ጠይቀን የነበረው የቅስቀሳ ኘሮጀክት የተቀረፀበት ፅሁፍ ተልኮልናል"

"የትኛው?"

"አሮሞ በሚባለው ክልል ላይ የሚንቀሳቀሰው ፓርቲ ህዝቡን ለማነሳሳት ምን እንደሚያስፈልገው የጠየቅነው....."

"አዎ.....አስታወስኩት....." ቀጠለ "እሺ.....ተላከልን?"

"ይኸው....." በእንግሊዝኛ የተፃፈውን ጥራዝ ገፋ አደረገለት አልፎ አልፎ እየገላለፀ አየውና "እንዴት ነው ሙሉውን አነበብከው? ጥሩ እቅድ ይመስላል?"

"አዎ ጥሩ እየሰሩ ይመስላል። " አለና ከመሀል ገፅ ላይ የግርጌ ማስታወሻ መሰል ሀሳብ የሰፈረበትን ያነብለት ጀመር።

"..... ይህ እቅድ ውጤታማ ሊሆን እንደሚችል ማረጋገጥ ከፈለጋችሁ በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያን እየመራ ያለው መንግስት በትግል ላይ እያለ ይጠቀምበት የነበረውን የቅስቀሳ ዘመቻ ተመልከቱት ይላል።"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ዝቅ ብሎም “ሰባ በመቶ የሚሆነውን የቅስቀሳ ንድፍ ከነሱ ነው የወሰድነው፡፡ሰላሳ በመቶውን ግን ለኦሮሞ ህዝብ በሚያመች መልኩ የቀየርነውና ያሻሻልነው ነገር አለው” የሚል ነው
ሉዊስ በጥሞና ሲሰማ ቆየና “እንዴት ባለ መልኩ እንደሚሰሩ አሳጥረህ ብትገልፅልኝ?”
“በአራት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈለ ነው፡፡
አንደኛው፦ በየአስራ ሁለት ሰዓት ውስጥ ለሁለት ሰዓት የሚተላለፍ የሬዲዮን የስርጭት መስመር መክፈት ሲሆን አፈፃፀሙ ከኢትዮጵያ ውጭ በሚገኝ አገር የአየር ጊዜ በመግዛት ህዝቡን በሬዲዮ መቀስቀስ፡፡ በቅንፍ ውስጥ የሰፈረና ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያለው ሌላ ሀሳብ አለ፡፡”

“ምን የሚል?”
“ትግሉን ቀጥለው የኦሮሞን መሬት ከመንግስት ወታደሮች ነፃ ማውጣት ሲጀምሩ በተቆጣጠሩት ቦታ ላይ የራሳቸውን የራዲዮ ጣቢያ መገንባት የሚል ነው፡፡”
“በጣም ጥሩ ሙሉ ድጋፍ ይደረግላቸዋል”
“ሁለተኛው፡- የቅስቀሳ ስራ የሚካሄደው ፅሁፎችን አሳትሞ በማሰራጨት ነው፡፡ ይህም በውስጡ ንዑስ አሰራሮች አሉት፡፡” አለና ዋናውን ጥራዝ የሚፈልገው ገፅ ድረስ ገልፆት “ሁለት አንድ፦አነስተኛና እጅግ አነሳሽ የሆኑ በራሪ ፅሁፎችን በየጊዜው እያሳተሙ በመላው የኦሮሞ ግዛቶች ላይ መበተን፡፡
ሁለት ሁለት፦ስለ ኦሮሞ ህዝብ ታሪክ ፣ሀያልነት፣ ባህልና አገራዊ ሀብቶች የሚገልፁ፤ እንዲሁም ተያያዥ በሆነ መልኩ ነፍጠኛው የአማራ ብሔር ያደረገባቸውን በደልና ስብራት አነስ ባሉ መፅሔትና ጋዜጠኞች ላይ እያገነኑ ፅፎ በማሳተምና በነፃ በማደል ህዝቡን በስሜታዊነት ሆ ብሎ ለውጊያው እንዲነሳ ማድረግ፡፡
ሁለት ሶስት፦ኦሮሞ ከኢትዮጵያ ተገንጥሎ በመውጣት የራሱን መንግስት ማቋቋም እንዳለበት የሚሰብክ፤ ይህ የነፃነት ጥያቄ ግን በነፍጠኛው የአማራ ገዢ ተቀብሮ እንዲቀር የተሞከረ ግን አሁንም ቢሆን የሚቻል መሆኑን መንገር... ” አለና ቀና ብሎ እያየው “... በተለይ እዚህ ጋር ያቀረቡትን ሀሳብ በጣም ወድጀዋለሁ::

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ቀጠለ ንባቡን "... በተለይ ይህ የአሁኑ መንግስት ገዢ ከሆነ በኋላ በአማርኛ ቋንቋ ተፅፈው የታተሙና የኦሮሞን ህዝብ ስሜት የሚያነሳሱና የሚያስቆጡ መፅሀፍቶችን በድጋሜ እንዲታተሙ ከተቻለም በላቲን ቋንቋ እንዲተረጎሙ በማድረግ ታትመው ለኦሮሞ ህዝብ በነፃ እንዲታደል ማድረግ። ሌሎች መሰል አዳዲስ መፅሀፍቶችንም እያሳታሙ ማሰራጨት" የሚል ነው።

"እሺ ቀጣዩ የመቀስቀሻ መሳሪያቸው ምንድነው?"
"በሶስተኛነት ያስቀመጡት ደግሞ ዘፈኖችን ነው። ይህም ንዑስ ክፍሎች አሉት። ሶስት አንድ ስር፦በኦሮሞ የተለያዩ ግዛቶች ላይ ህጋዊ ሽፋን ያላቸውንና ለዚህኛው ዓላማ የተቋቋሙ የሙዚቃ ተጫዋቾችን በማደራጀትና ሙሉ መሳሪያዎችን በመስጠት በገጠሩና በከተማው እንዲሁም በየ ትምህርት ቤቱ አመቺ አጋጣሚዎችን እየፈጠሩ ህዝቡን በዘፈን ማነሳሳት።
"ሶስት ሁለት፦ደግሞ..... በተለይ የአሁኑ መንግስት ስልጣን ከያዘ ወዲህ በኦሮሞ ድምፃውያኖች የተዜሙ ቀስቃሽ የትግል ዘፈኖችን ከአሳታሚዎቹና ከድምፃውያኖቹ ጋር በመነጋገር ድጋሜ በበርካታ ኮፒዎች ተባዝተው በዝቅተኛ ዋጋ ወይም በነፃ ለህዝቡ እንዲታደሉ ማስደረግ።
".....ሶስት ሶስት፦ለዚህ የነፃነትና የትግል ወቅት የሚሆኑ ሌሎች አዳዲስ ዘፈኖችን ወጪውን በመሸፈን እንዲቀረፁ ማስደረግ የሚሉ ናቸው። በአራተኛነት የቀረበው ደግሞ በየ ክልሉ ያሉ የጦሳ አለቃዎችን በገንዘብ እየቀጠሩ ህዝቡን በተለያዩ ቦታዎች ሰብስቦ ለዚህ ጦርነት የቻለውን ድጋፍ እንዲሰጥ ማሰበክ የሚል ነው።"
"ጥሩ ይመስላል" አለ ሉዊስ።
"አዎ..... የእነዛ ሁሉ አፈፃፀም እንዴት እንደሚከናወን ዝርዝር ሀሳቡ በዚህ ፅሁፍ ላይ ሰፍሯል።"
ሉዊስ ሲያስብ ቆየና "የጠየቁትን ያህል ገንዘብ ይለቀቅላችው።" ቀጠለ "ሁሉም ነገር በታቀደው መሰረት እየተጓዘ ነው።" ብሎ ይዞዋቸው የገባውን ሁለት ፖስታዎች በመክፈት በውስጣቸው ያሉትን ደብዳቤዎች አወጣና ዘረጋለት። "በአንድ ሰዓት ልዩነት ውስጥ ነው የደረሱኝ።"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“ኮምፊደንሻል!” የሚል መሀተም አርፎባቸዋል፡፡
“የምንድናቸው?” ተቀብሎት አድራሻዎቹን እያነበበ ጠየቀው፡፡
ቻይናና ሩሲያ አገር ከሚገኙ የጦር መሳሪያ ማምረቻ ድርጅቶች የተላኩ ነበሩ፡፡

ሉዊስ ቀጠለ “የጦር የመሳሪያ እርዳታ እንዲያደርጉልን ከጠየቅናቸው አገሮች መካከል ማን እንደሁነ ራሱን ማሳወቅ ባልፈለገ አገር አማካኝነት ክፍያ ስለተከናወነልን መሳሪያዎቹን መቼ እና እንዴት እንደምንረከባቸው ነው የጠየቁን::”
“ይህ ደብዳቤ የተላከልን ክፍያውን ከፈፀሙልን አገሮች ነው?”
“አይደለም..... ገዢዎቹማ አሁንም ራሳቸውን ማሳወቅ አልፈለጉም፡፡ እንዳየኸው አንዱ ከቻይና ሌላው በሩሲያ ለሚገኙ የግል መሳሪያ አምራች ፋብሪካዎች ክፍያውን ፈፀሙልንና የመረከቢያውን ደረሰኝና ደብዳቤውን ነው ፋብሪካዎቹ የላኩልን፡፡”
“ለፋብሪካዎቹ ደውለህ ክፍያውን የፈፀመልን ማን እንደሆነ አልጠየክም?”
“እንዲህ ዓይነት ውሎች ላይ መረጃ ለሶስተኛ ወገን እንደማይሰጥ ነገሩኝ፡፡”
“ለነገሩ ማንም ይሁን ማን ምን አገባን፡፡ አላማችን የጦር ማሳሪያዎችን ማግኘት ነበር፡፡ ተሳክቷል፡፡” ቀጠለ ፒየር “እስከመቼ ነው እንድንረከብ ያዘዙን?”
“ሶስት ወር ድረስ..... ከዛ ካለፈ የማስቀመጫ ቦታ ኪራይ እንደምንጠየቅ ነው በደብዳቤው ላይ የገለፁት፡፡”
“በቂ ጊዜ አለን፡፡”
“ይመሰለኛል፡፡”
የደቂቃ ዝምታ በመሀከላቸው ሰፈነ፡፡ ከዛም ሉዊስ “ሰናይት ከአሜሪካ መጥቶ በተላከላት የስልክ ቁጥር መሰረት የሚፈልገውን ግለሰብ ጉዳይ ምን ላይ አደረሰችው?..... ከኦሮሞ ክልል ውጪ በሌሎቹ የኢትዮጵያ ክልሎች ላይ የምንፈልገውን ያህል አልተጓዘችም እኮ..... ጦርነቱ ሁሉም ጋር እኩል እንዲፈነዳ ነው የምንፈልገው” አለ፡፡
“ለነገሩ ያልከውን ያህል ዘገምተኛ አይደለችም..... አንተ ገንዘብ እና የጦር መሳሪያውን ለማሰባሰብ ጊዜ ስለሌለህ እሳ የምትልክልኝን የየቀኑን

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ሪፖርት ሁሉንም ለአንተ ስለማላስተላልፍልህ ነው። ለምሳሌ በደቡብ የኢትዮጵያ ክልል ላይ የደረሰችበት ደረጃ በጣም ጥሩ ነው። በሶማሊያም ቢሆን ቢያንስ መሳሪያውን አስርጐ ማስገባት የሚቻልበትን ክፍተት መፍጠር እንደቻለች ገልፃልኛለች....." ብሎ በዝምታ ቆየና "....ይልቅ ቢያንስ በሃያ አራት ሰዓት አንዴ መላክ የነበረባትን ሪፖርት ሳትልክ ይኸው ዛሬ ሌላ አስራ ስምንት ሰዓት አለፈ....." አለ በመጠነኛ ስጋት ተውጦ።

"ከዚህ በፊት እንደዚህ ዓይነት ነገር ተከስቶ ነበር?"

"የመጀሪያው ነው።።"

"ምን ሊሆን ይችላል ብለህ ትገምታለህ?"

"እርግጠኛ አይደለሁም..... ግን ቅድም እንዳልከው ከአሜሪካ የመጣው የስልክ ቁጥር የፈጠረባት ችግር ሊኖር ይችላል።።"

"እጅግ አደገኛ.... ልክ ነህ ተፈላጊው ግለሰብ ከቀደማትና ማንነቷን ካወቀ ያለ አንዳች ጥያቄ ሊገድላት ይችላል።።" ከተቀመጠበት እየተነሳ ቀጠለ "....ይህን ሀሳብ ከዚህ በፊት አንስተነው ነበር። ምናልባት ሰናይት ብትገደልም ሆነ ብትሰወርብን ሌላ በሷ እግር የሚተካ ሰው ተዘጋጅቶ ይቀመጥ የተባባልነው....."

አቋረጠውና "አዎ..... ብለን ነበር።።"

"አለ..... አዘጋጅተሀል?"

"ጥናት አድርገን ከያዝናቸው የሰዎቹ ስም በስተቀር ግንኙነት የጀመርነው ማንም የለም።።" ፒየር በቀዘቀዘ ስሜት መለሰ።

ሉዊስ ከመናገሩ በፊትም ቀጠለ "እንደምታየን ሁለታችንም ሙሉ ጊዜያችንን ለዚህ ስራ ብቻ ትኩረት ሰጥተን አይደለም እየተንቀሳቀስን ያለነው።።"

"ጥሩ..... ከአሁን በኋላ ሌሎቹን ሁሉ እናቆማቸዋለን..... ትኩረታችን ለዚህኛው ብቻ!" አለ የቢሮው በር ከፍቶ ለመውጣት እየተራመደ።



ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ምዕራፍ 21

ሰናይት ከፒየር የተላከላት የስልክ ቁጥር እና የተፈላጊው ግለሰብ ስም ብቻ ቢሆንም በተነገራት የስልክ ቁጥር መሰረት አንድን ግለሰብ ፈልጐ ማግኘት..... ይህን ያህል አስቸጋሪ ይሆናል ብላ አልገመተችም፡፡ 'ከቴሌኮሙኒኬሽን መስራቤቶች ወደ አንደኛው ቅርንጫፍ በመሔድ ማውጫ መፅሀፍት ላይ መመልከት ከዛም ወደ ተመዘገበበት ስፍራ ማምራት' ስትል ነበር ያሰበችው፡፡

ይልቅ አስቸጋሪ መስሎ የታያት 'ከግለሰቡ ጋር እንዴት መተዋወቅና አብሮ መስራት ይቻላል?' የሚለው ጥያቄ ነው፡፡

አረፋፍዳ ከቤት እንደወጣች ታክሲ ይዛ ላጋር አካባቢ ወደሚገኘውና "ፍልውሃ ቅርንጫፍ" በመባል የሚታወቀው የቴሌ መስራቤት አመራች፡፡

መስራቤቱ በር ጋር እንደደረሰች ታክሲውን አስቁማ ወረደችና መተላለፊያውን አቋርጣ መግቢያው ጋር ደረሰች፡፡
በር ላይ ከነበሩት ጠባቂዎች ሴቷ እንደመፈተሽ ደባበሰቻትና "ይግቡ"
"የስልክ ቁጥር ማውጫ መፅሀፍ የቱ ጋር ነው የማገኘው?"
"ወደ ቀኝ ይታጠፉና የመጀመሪያዋን አዳራሽ እንደጨረሱ በስተ ቀኝ በኩል ያለችው ክፍል ውስጥ ገብተው ይጠይቁ"
"አመሰግናለሁ"

አልፋት ወደ ተጠቆመችበት ክፍል አመራች፡፡ እንደደረሰች በጠረጴዛዎቹ ላይ ወፍራም መፅሀፎች ተቀምጠው አየች፡፡ አንደኛውን አንስታ በስተግራው በኩል ያለው ወንበር ላይ ተቀመጠችና እየገላለፀች መፈለግ ጀመረች፡፡

አስር ደቂቃ ሲሞላት የሚፈልገው ቁጥር እንዳልተመዘገበ አወቀች፡፡ የማውጫውን የህትመት ወቅት አየችና 'ምናልባት አዲስ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

መስመር ስለሆነ ይሆናል ያልተፃፈው' ብላ ሌላውን አነሳች፡፡ ሁሉም ግን ተመሳሳይ ነበሩ፡፡
ተነሳችና ከፊት ለፊት ተቀምጦ ኮምፒውተር ላይ ሰነድ ይመዘግብ ወደ ነበረ የድርጅቱ ሠራተኛ ተራምዳ "ጤና ይስጥልኝ?"
ቀና ብሎ አያትና በውበቷ ተስቦ ስራውን ሙሉ በሙሉ በመቋረጥ ትኩረቱን ሲሰጣት አየችውና "ጤና ይስጥልኝ....."
"እ..... እባክህን አድራሻ እንዴት ማግኘት እንደምችል እንድትጠቁመኝ ነበር?"
"የማንን አድራሻ?"
የስልክ ቁጥር የተመዘገበበትን ወረቀት አውጥታ ሰጠችውና "የዚህን ቁጥር ባለቤትና አድራሻውን ማወቅ ፈልጌ ነበር?"
ያልተለመደ አይነት ጥያቄ ስለሆነበት እይታውን ከወረቀቱ ወደ ሰናይት እየመለሰ "አልገባኝም?" ቀጠለ ".....በኛ አሰራር ውስጥ የአንድን ድርጅት ወይም የግለሰቡን ስም ይነግሩንና ስልክ ቁጥሩን ሲጠይቁን ነው የምንናገረው እንጂ እንደዚህ ዓይነቱን ጥያቄ ለማስተናገድ አስቸጋሪ ይመስለኛል"
"አዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ነው የመጣሁት.....ቁጥሩ ለክትትል ስለተፈለገ ነው፡፡" በቅፅበት የመጣላትን ሀሳብ ተናገረች፡፡
ግራ በመጋባት ሲያያት ቆየና " በቀጥታ የኔ ቢሮ ውስጥ ሊያልቅ ቢችልና ብረዳሽ ደስ ባለኝ ግን ይቅርታ..... መረጃ ክፍሎችን ጠይቂ እነሱ ይረዱሻል፡፡ ወይም ወደሚመለከተው ቢሮ ይመሩሻል" አላት፡፡
ሙከራዋ አልተሳካም፡፡ "አመሰግናለሁ" አለችና አደራሹን ለቃ ወጣች፡፡ የአካሔዱን መጥፎነት የተረዳችው የመስራቤቱን ህንፃ በር ስታልፍ ነበር፡፡ ' ህጋዊነትሽን የሚያሳውቀኝን መረጃ አሳይኝ ቢለኝስ?' ራሷን ጠየቀች፡፡
ከህንፃው ፊት ለፊት አቅጣጫ እንደ ጐጆ የተሰሩት የህዝብ ስልኮች የተንጠለጠሉበት የመንገዱ ጠርዝ ጋር ስደርስ ሌላ ብልሃት ታሰባት፡፡
የያዘቻት አነስተኛ የእጅ ቦርሳ ውስጥ ዝርዝር ሳንቲም ፈልጋ ስታጣ ድፍን ብርን በዘጠና ሳንቲም በመመንዘር ከሚተዳደሩ ታዳጊዎች ላይ መነዘረችና ወደ አንዱ ስልክ ተጠጋች፡፡ ቁጥሩን እያየች መነጋገሪያውን አነሳችና ሳንቲሞቹን በመክተት በቀጥታ ፒየር የላከት ስልክ የተመዘገበበት ቤት ደወለች፡፡ ይጠራ ነበር፡፡ የልቧ አመታት

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ሲጨምር ታወቃት፡፡ መነጋገሪያው ተነሳና "ሀሎ?" የሴት ድምፅ ነበር፡፡

"ሀሎ....." ብላ የስልኩን ቁጥር ነገረቻት

"አዎ.....ራሱ ነው....."

"ከቴሌኮሙኒኬሽን ነበር የምደውለው፡፡ በአካባቢያችሁ የስልክ እንጨት ወድቆ መስመሮች እየተበጣጠሱ ስለሆነ የጥገና ሰራተኞች እንዲላኩ የአካባቢያችሁን አድራሻ ለመውሰድ ነው?"

"የኛ ስልክ እኮ ይሰራል»

"ጥቂት ቆይቶ ሊቋረጥ ይችላል፡፡ አድራሻውን ብነግሪኝ?»

"የኛን ነው የሰፈሩን?"

"ሁለቱንም"

"እ..... ሰፈሩ ጐላ ሚካኤል ቤተክርስቲያን በስተጀርባ በር በኩል ነው....." አለችና የወረዳ የቀበሌና የቤት ቁጥሩን ነገረቻት፡፡

"እ.....የናንተ ቤት የቱ ጋር ነው የሚገኘው?"

"ከአባድር ትምህርት ቤት ፊት ለፊት በምታስገባው ቀጭን መንገድ መቶ ሃምሳ ሜትር ገባ ሲሉ ቀይ ቀለም የተቀባ አጥር ያላት ጊቢ"

"አመሰግናለሁ..... ሰራተኞች አሁኑኑ ይላካሉ" አለቻትና መነጋገሪያውን ቦታው መለሰች፡፡ ጊዜ ሳታባክን ታክሲ ተኮናትራ ወደ ስፍራው ጉዞ ጀመረች፡፡

ታክሲዋ በቸርችል ጐዳና በመውጣት ሜጋ አምፊ ቴአትር ጋር ስትደርስ አፄ ቴዎድሮስ በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ላሰሩት መድፍ መታሰቢያ በቆመው ሴቫስታፖል ሀውልት ጎን ዞራ ወደ ግራ በመታጠፍ ጉዞ ቀጠለች፡፡ ቁልቁለቱን ጨርሳ ዳገቱን ጥቂት እንደወጣች ሾፌሩ በታዘዘው መሰረት አባድር ትምህርት ቤት ጋር ደረሰና አቆመ፡፡

ሰናይት ወደ መንገዱ እያየች የተዋዋሉበትን ሂሳብ ከፍላ በመውረድ ዋናውን አስፓልት ተሻግራ መጓዝ ጀመረች፡፡

አስፓልቷ ፈራርሶ ወደ ኮረኮንቻማነት እየተለወጠች ባለችው ጠባብ መንገድ ላይ በግምት መቶ ሃምሳ ሜትር ሊደርስ እስከሚችልበት ድረስ እያሰበች ወደ ውስጥ ገባችና የተባለውን ቀለም የተቀባችው ትንሽ የቆርቆሮ ጊቢ በርቀት ታየቻት፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

አካባቢው መንደር ነው፡፡ ህፃናትና ወጣቶች ይበዛሉ፡፡ አብዛኛዎቹም በተጐሳቆለ ኑሮ ውስጥ ታጭቀው ህይወትን የሚኖሩ መሆናቸውን አለባበሳቸውና አካላዊ አቋማቸው ይናገራል፡፡

ሰናይት ሀሳቧን ወደ ራሷ መለሰችና 'ሁለተኛው ስራ ተጠናቀቀ' አለች ለራሷ፡፡ በቀጣዩም ግለሰቡን እንዴት ማግኘት እንደምትችል ማሰብ ቀጠለች፡፡

ከጊቢዋ ትይዩ አቅጣጫ ወደ ግራ ሃያ ሜትር ራቅ ብሎ አነስተኛ የሸቀጥ ሱቅ ይታያል፡፡እርምጃዋን ሳትገታ ወደ ሱቁ አለፈች፡፡

አንዲት ወጣት ሴት ልጅ በጠባቧ መስኮቱ አቅጣጫ ተቀምጣ የስኳር ማሽጊያ ወረቀቶች እየቀደደች ትጠቀልላለች፡፡
"እሙዬ..... ባለ አንድ ብሩ ሶፍት ይኖርሻል?" ተለሳልሳ ጠየቀቻት፡፡
"አለ"
"ስጭኝና..... አንድ ፓኪት ሮዝማንም ጨምሪልኝ....."
ሰጠቻት፡፡ "ሂሳቡ ስንት ይመጣል?"
"እ.....አስራ አንድ ብር"
ድፍን መቶ ብር አውጥታ ሰጠቻት፡፡ ወጣቷ ከገንዘብ ማጠራቀሚያዋ ሳጥን ውስጥ ያሏትን ብሮች እያስተካከች ቆጠረች፡፡ ሰባ ሁለት ብር ከካርቶኖች ስር ተጠቅልለው የተቀመጡትን እያወጣች ጨማመረችበት፡፡ ሰማንያ ሶስት ብር ብቻ ሆነ፡፡ መልሱ ምን ያህል እንደሚመጣ ደግማ አሰላችና 'ሰማንያ ዘጠኝ' አለች ለራሷ፡፡ ስድስት ብር እንደሚጐድላት አሰበችና እየተጨነቀች "ይቅርታ መንዝሬ..... ልምጣ?" በመለማመጥ ቅላፄ ጠየቀችው፡፡
"ምን ያህል ጐደለሽ?"
"ስድስት ብር....."
"ተይው....."
"ወይም በቀሪው ብር ሌላ እቃ ቢወስዱበት....."
"አይ.....ደህና" አለቻትና የያዘችውን ብር ተቀብላ ቦርሳዋ እየከተተች "እዚህ ሰፈር ሰው ፍለጋ መጥቼ ላገኘው አልቻልኩም ባክሽ....."
"ማን የሚባል?....." ከንግግሯ ሙሉ ስሜቷን እንደገዛች አወቀች፡፡
"በርሔ አብርሃ የሚባል ነው..... የትግራይ ሰው....."

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“እ.....ጋሽ በርሔ.....አንከስ የሚሉ አንድ እጃቸው አርቴፊሻል አይደል?”
በሰማችው ነገር ደንገጥ አለችና “ማለት ከኔ ጋር አንተዋወቅም.....መልዕክት ላደርስላቸው ነበር አመጣጤ.....”
“ያው.....እዛ ጊቢ ውስጥ ነው የሚኖሩት” አለቻት በጠባቧ መስኮት ተንጠራርታ እጇን አውጥታ ሰውዬው ወደ ሚኖርበት ጊቢ እያመለከተች፡፡
“የራሱ ቤት ነው ወይስ ተከራይቶ ነው የሚኖረው?”
“የእህታቸው ቤት ነው፡፡”
“እሺ አመሰግናለሁ” ብላት ሄደች፡፡ እሷም ድፍኑን መቶ ብር እየደባበሰች ተቀመጠችና በልቧ የደንበኛዋን ቸርነት እያሰበች ወረቀቷን መጠቅለል ቀጠለች፡፡

ሰናይት መረጃ ለማግኘት ስትል ብቻ የገዛችውን ሶፍትና ሲጃራ እየደባበሰች በቀስታ በመራመድ በጊቢው ፊት አለፈች፡፡

ሁለት ጊዜ ደጋግማ ተመላለሰች፡፡ ከዚህ በላይ መቆየቷ ግን በአካባቢው ጐልታ እንድትታይ ስለሚያደርጋት መታወቂ እንደማይቀር አሰበችና የግድ ሌላ ሰው በጊቢው አካባቢ ማቆም እንዳለበት አምና በመውጣት ወደ ዋናው አስፓልት ጋር ለመድረስ ጥቂት ሲቀራት እድሜው ከአስራ ሁለት ዓመት የማይልቅ ጫማ ጠራጊ ሳጥኑን ይዞ ሲመጣ አየቸው፡፡
“ማሙሽ” ጠራችው፡፡
“አቤት ይጠረግ?”
“አዎ.....”
በስተቀኝ በኩል የሚገኝ የቆርቆሮ አጥር ስር ተጠጋና ጫማዋን ሳጥኑ ላይ እንድታደርግ ማመቻቸት ጀመረ፡፡ “በቀን ስንት ብር ትሰራለህ?”
“አራትም.....አምስትም ብር.....” ተበጣጥሶ የተንጀላጀለበት የሹራቡን እጅጌ ሰብስቦ ለመጥረግ እየተቻኮለ መለሰ፡፡
“ጐበዝ:: እኔ ዛሬ ሃምሳ ብር እሰጥሃለሁ.....”
ልጁ መጥረጉን አቁሞ ወደ ሰናይት ቀና በማለት አፈጠጠ፡፡
ቀጠለች “..... ግን አንድ ስራ ልትሰራልኝ ነው፡፡”
“ምን ዓይነት?”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“እዛ ጋር አንድ ቤት አሳይሃለው፡፡ ከቤቱ ትንሽ ራቅ ብለህ ትቀመጥና የሆነ ሰው ሲወጣ ጠብቀህ መጥተህ ትነግረኛለህ፡፡ ያኔ ሃምሳ ብር ታገኛለህ፡፡”
“እሺ!.....የትኛው ቤት ነው?” በጉጉት ጠየቀ፡፡
“እዛ ጋር ቀይ ቀለም የተቀባ ጊቢ አለ፡፡”
“አዎ.....አውቀዋለሁ፡፡”
“እዛ ጊቢ ውስጥ አንከስ የሚል አንድ እጅ አርቴፊሻል የሆነ ሰውዬ አለ፡፡”
“እሳቸውንም አውቃቸዋለሁ ደምበኛዬ ናቸው፡፡”
“የዚሁ ሰፈር ልጅ ነህ እንዴ?”
“አዎ.....”
“ጥሩ.....እሱ ሰውዬ ሲመጣ ጠብቀህ ትነግረኛለህ፡፡”
“እሺ”
ሰናይት ድፍን አስር ብር አውጥታ እየዘረጋችለት
“ሌላው በኋላ ይጨመርልሀል፡፡”
“እሺ” ባለማመን ስሜት ተቀበላት፡፡
“ግን..... ለሰውዬውም ሆነ ለሌላ ሰው አንድ ነገር ትንፍሽ እንዳትል”
“ኧረ..... እኔ አቃጣሪ አይደለሁም ሚካኤልን!” አለ ልጁ፡፡ ቀጠለ
“እዚሁ ነው የሚጠብቁኝ?”
“አይ..... እዛ የአስፓልቱ መድረሻ ጋር ያለው ኬክ ቤት በረንዳ ላይ ነኝ፡፡” ቦርሾ እንደጨረሰ ሳጥኑን አንስቶ ወደተባለው ጊቢ ተፈተለከ፡፡ አሰልቺ ጥበቃን ነበር ያደረገችው፡፡ ከበረንዳው ላይ ሳትንቀሳቀስ ለሶስት ሰዓታት ያህል ተቀምጣለች፡፡
በመጨረሻ ላይ ልጁ እየሮጠ ደረሰና “እኛው መጥተዋል፡፡”
“ወዴት ነው እየመጣ ያለው?”
“ወደዚሁ መንገድ”
ድፍን ሃምሳ ብር አውጥታ የጠጣችውን የቡና ሂሳብ ከፍላ “የቱ ጋር ደርሷል?”
“እዚህ ጋር ይደርሳሉ.....” ብሎ ዞር አለና “እኛውና!” ጣቱን ወደ ሰውዬው ሲቀስር

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“እጅህን አውርድ!” ጮሀ አዘዘችው፡፡ ጥቂት ቢዘገይ ግን በርሄ ዋናው አስፓልት ጋር ደርሶ አካባቢውን ለመቃኘት ዞር ዞር ሲል ያየው ነበር፡፡

“በቃ ሂድ ” አለችው፡፡

ብሩን እንደጨበጠ ሩጫውን ወደ ዳገቱ ቀጠለ፡፡

ሰዓቱ ከምሽቱ 2፡10 አለ፡፡ ሰናይት ቀኑን በሙሉ ያሳለፈችው የሰውዬውን ዱካ በመከተል ነበር፡፡ ሲበዛ አስጨናቂና አድካሚ ስራ ሆኖባት ዋለ፡፡

በእለቱ ከሰውዬው ጀርባ ሆና በርካታ ድርጊት ሲያከናውን ለማየት ቻለች፡፡ ፒያሳ ከመብራት ኃይል ህንፃ ትይዩ ከሰዎች ጋር ደብዳቤ መሰል ነገር ሲለዋወጥ፤ መርካቶ ከአውቶቡስ ተራ ፊት ለፊት ባሉ የመኝታ ቤቶችን አከራዮች ጋር በሻንጣና በመያዣ ላስቲክ የተሞሉ ወረቀቶችን ከአንዱ ተቀብሎ ለሌላው ሲሰጥ፤ ካዛንቺስ ትግሪኛ ተናጋሪ ከሆኑ አምስት ሰዎች ጋር ረጅም ሰዓት የፈጀ ውይይትን በአንድ ኬክ ቤት በረንዳ ላይ ሲያደርጉ እየተከታተለች ስታይ ዋለች፡፡ ምሽት ላይ ወደ ተክለሃይማኖት ቤተክርስቲያን አካባቢ ነበር የተመለሰው፡፡

አንድ ሆቴል ገባና ሁለት ሰዎች ብቻ ወደነበሩበት ጠረጴዛ በመሄድ ጨብጠዋቸው ተቀመጠ፡፡

ጐላ ካለ እስፒከር የሚወጣና የሚያስጨፍር የትግሪኛ ዜማ ይሰማል፡፡

ከቤቱ ጠባብነት አንፃር ከገባች ለእይታ ስለምትጋለጥ ውጭ ሆና ተመልሶ ይወጣ እንደው በማለት ለግማሽ ሰዓት ያህል በበራፉ አካባቢ እየተንቀሳቀሰች ጠበቀችውና መቅረቱን ስታውቅና ሰዓቱም ወደ መምሸቱ ሲጓዝ ወደ ቤቷ አመራች፡፡

በቀጣዩ ቀን ክትትሏን በተመሳሳይ መልኩ ቀጠለች፡፡ በዚህ እለት ግን በደንብ አምሽታ እስኪወጣ ድረስ ጠበቀችው፡፡ ራሱን ባይስትም ብዙ መጠጣቱን ወድያው ለየች፡፡ ከመጠጥ ቤቱ ብዙም ሳይርቅ መንገድ ላይ ቆማ ደንበኛ ስትጠብቅ ወደ ነበረች ሴተኛ አዳሪ ተጠግቶ ሲያወራ አየችውና ጥቂት ቆይተው እንደ መሳሻሸምና መላፋት ብለው አብረው ሲሄዱ አየቻቸው፡፡

ቀጣዩም ቀን ተመሳሳይ ነበር፡፡ ቀኑን በተለያዩ ጉዳዮች አሳልፎ ምሽቱን ወደ መጠጥ ቤት ያመራና ሌላ ሴት ይዞ ወደ ቤቱ ያመራል፡፡ አምስት ቀን ያህል ክትትል ስታደርግበት ቆየች፡፡ ምንም የተለየ ነገር

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

ሲያከናውን አላየችውም:: እሱን ለማጥመድ ኩሁሉም የተሻለው አማራጭ ጠጥቶ ሲወጣ ሴተኛ አዳሪ መስሎ መቅረብ የተሻለ ሆኖ አገኘችው::

በቀጣዩ ቀን ምሽት የማንንም ወንድ ስሜት የሚያነሆልል አለባበስ ለብሳ በቀጥታ ወደ መጠጥ ቤቱ ነበር ያመራችው:: መጠጥ ቤቷ ከውጭ እንደምትታየው ሰፊ አይደለችም:: ደብዛዛና የተለያዩ ቀለማት ያሏቸው መብራቶች ከተለያዩ አቅጣጫዎች ይፈነጥቃሉ:: ሶስት ሴት አሳላፊዎች ሲኖሩ በአበሻ ቀሚስና በትግሬ ሹሩባ ተውበው ደንበኞችን ለማስተናገድ በፈገግታ ይራወጣሉ::

ወደ ባንኮኒው አምርታ ቆመችና ከውስጥ ላለችው አስተናጋጅ "ዊስኪ ቅጂልኝ" አለቻት

"ምን ዓይነት?"

"ጓይት ሆርስ"

ቀዳችና "አምቦውሃ ላርግበት?"

"በረዶ ቢሆን ይመረጣል::" አድርጋለት ሰጠቻት::

እይታዋ ከቤቱ ብርሃን ጋር እስኪላመድ ድረስ ጠበቀችና በቀስታ ዞራ የውስጡን አጠቃላይ እንቅስቃሴና ገፅታ ቃኘች:: አብዛኛዎቹ ጠረጴዛዎች በተስተናጋጆች ተይዘዋል::ሁሉም ትግሪኛ ተናጋሪ ናቸው ማለት ይቀላል:: ከፍ ባለ ድምፅ ያለ ስርአት ያወራሉ፣ ይቃለዳሉ፣ ከዛም ይሳሳቃሉ.....

በርሄ በስተግራው አቅጣጫ በኩል ነበር:: አብረውት ካሉት ሁለት ሰዎች ጋር የሚያደርጉት የቅብብሎሽ ወሬ እና አካላዊ እንቅስቃሴያቸውና በፊታቸው ላይ ከሚነበበው ስሜት ጋር ተዳምሮ ሚስጥራዊ ጉዳይ እንዳልያዙ ገመተች:: ብርጭቆዋን አንስታ ወደነሱ ተራመደችና ስትደርስ "ወንድሞች ይህችን ትርፍ ወንበር ልቀመጥባት?"

ሁለቱ ሰዎች ደስ እንዳላላቸው በዓይናቸው ተናገሩ::በርሄ ጥቂት ቆይቶ "ተቀመጭ....." አላት::

"አመሰግናለሁ::" ቁጭ አለች:: የሰዎቹ ስሜት መለወጥ ጥርጣሬ ላይ እንደጣላቸውና ከነሱ ጋር በራሷ ለመቀላቀል የወሰደችው እርምጃ ስህተት መሆኑ ዘግይቶ ነበር የገባት::

ሶስቱም የሚጠጡት ጂን ነበር::

ሁካታው እየደራ ቢመጣም የነሱ ጠረጴዛ ላይ የሰፈነው ዝምታ ግን አስፈሪ ነበር:: አብዛኛዎቹ ጠጪዎች ሞቅ እያላቸው ሄዷል:: ሰናይት

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ብርጭቆው ውስጥ የቀረችውን ጨለጠችና ለአሳላፊዋ እንድቅጨምርላት በምልክት ነገረቻት። የሷን ብርጭቆ አቅርባ ልትመለስ ስትል "ቆይ....." አስቁማትና ወደ ሶስቱ ሰዎተ በየተራ እያየች "ወንድሞች ብጋብዛችሁ ደስ ይለኛል....." መልስ ከነሱ ሳትጠብቅ "ቅጂላቸው" አለቻት። ለመከላከል ሞከሩ።

ከልባቸው ስላልነበረ አሳላፊዋ ገበያዋን ሳያከላክሉባት ለማምጣት ሄደች።

በዚህ ጊዜ የባለ አርቴፊሻሉ ሰው አስተያየት እየተለወጠ ነበር።በጣም ያደገው አፍሮ ፀጉሩ ሽበት ጣል ጣል አድርጐበታል ፊቱ ረዥምና መጣጣ ሲሆን አስተያየቱ የሰርሳሪ ዓይነት ነው። በቅንድቦቹ ላይ አንድ ቁጥር መሳይ እና በግምባሩ መሀከል የመስቀል ቅርፅ ያለው ጠባሳዎች አሉበት። ግራ እጁ ከክንዱ አጋማሽ ጀምሮ አርቴፊሻል ነው።

"የአገር ልጆች ትመስላላችሁ እኔ ሰናይት እባላለሁ። የተወለድኩት ዓዲ-ግራት ነው ያደኩት እና የኖርኩት ግን ፈረንሳይ ነው።"

"ሲያዩሽ ግን የትግራይ ሰው አትመስልም።" ከሁለቱ መሀከል ፊቱን ፈንጣጣ የበላው ሰው ተናገረ።

"እድሜዬን ከግማሽ በላይ ያሳለፍኩት ፈረንሳይ ነው። ከመጣሁ ገና አንድ ሁለት ወር ቢሆነኝ ነው።"

"እኔ አፈወርቅ እባላለሁ" ባለ ፈንጣጣው ስሙን ተናገረ።

ሁለተኛው "አርአያ"። ባለ አርቴፊሻል እጅ ነፃ ባልሆነ ስሜት "በርሔ....."

"ለስራ ነው የመጣሽው ለእረፍት?" አፈወርቅ ጠየቀ።

"አመጣጤስ ለስራ ነበር ግን..... የሚቻል ስላልመሰለኝ ትቼዋለሁ....."

"ለምን?"

"ስራው ቀላል አይደለም። በተወለድኩበት አገሬ ላይ አንድ ትልቅ ፋብሪካ ለማቋቋም አቅጄ ነበር....."

"ዓዲ-ግራት ላይ" አርአያ ጠየቀ።

"አዎ....."

"ታዲያ ለምን ተውሽው?"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“በመንግስት በኩል አዎንታዊ ስሜት ስለሌለ በሚልዮን የሚቆጠር ገንዘቤን ካፈሰስኩኝ በኋላ ዞር በይ እንዳልባል ስለፈራሁ” አለች ሀሰት በሆነው የመግባቢያ ታሪክ። በርሔ ግን አሁንም በዝምታ ያያታል።

“እና አሁን ተመልሰሽ ልትሔጅ ነው?” አርአያ ጠየቀ።

“ምን ማድረግ እችላለሁ ታዲያ..... አመጣጤ በትግራይ ልማት ውስጥ ያቅሜን ያህል ልሳተፍ ነበረ.....” ቀጠለች “.....ይልቅ እናንተ የትግራይ ልጆች ናችሁ?”

“አዎ.....” ባለ ፈንጣጣው መለሰ።

“ከምንም ነገር በላይ እሱ ያስደስተኛል። እናትና አባቶቼ በልጅነቴ ነበር የሞቱት። ወንድምና እህት ወይም ዘመድ የለኝም። ለኔ ቤተሰቦቼ ወይም ዘመዶቼ ማለት የአገሬ የትግራይ ልጆች ናቸው።.....በቃ እንደሰት.....እንዝናና.....” አለች ድጋሜ እንዲቀዳላቸው በምክልት እያሳየች።

ለአንድ ሰዓት ተኩል ያህል በጀመሩት ርዕስ ብቻ በሁለቱም ወገኖች በኩል ጥንቃቄ የታከለበት ንግግር ሲያደርጉ ቆዩ። ከዛ በኋላ የሰአቱ መሄድ ሰናይት እያስጋት ስለመጣ ወደ ቤቷ የመሔድ አዝማሚያ ማሳየት ጀመረች። ጥቂት ቆይቶም “መቼም ታክሲ እንደማላጣ እገምታለሁ”

“ መኪና የለሽም? ”

“አልያዝኩም” መልሷ ስህተት መሆኑን ድጋሜ ተረዳች። እንደ አንድ ባለ ሀብት ቀርባቸው መኪና አልያዝኩም ማለቷ ጥርጣሬያቸውን ሲያጎላው ታወቃት።

“ታክሲ አዎ..... ይኖራል።” አርአያ መለሰ።

በርሔ ተነሳና ከመደርደሪያው በስተቀኝ ባለው የግድግዳው ጥግ በኩል ወደ ሽንት ቤት የሚያደርሰውን በር ገፍቶ ወጣ። ሽንት ቤቱ ጋር ከመድረሱ በፊትም ወደ ቀኝ ታጠፈና በቤቱ ውስጥ ለውስጥ አድርጐ በጀርባ ወዳለው የጊቢ መውጫ ጋር ደረሰ።

የመቀሌ ሰው የሆኑት የመጠጥ ቤቱ ባለቤት ወፍራምና አጭር ወይዘሮ ጥይት ባሳጠረው ቀኝ እግሩ አንከስ እያለ በፍጥነት ሲራመድ አዩትና “በርሔ ምንድነው?..... ደህና አይደለህም?”

“ደህና ደህና.....” እየመለሰላቸው በቀጭኗ በር ከጊቢ ወጣ።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ከአምስት ደቂቃ በኋላም በወጣበት በኩል ተመልሶ ወደ መጠጥ ቤቱ ገባ።።
ሰናይት ጥቂት ቆየችና ሂሳቡን ከፍላ "በዚሁ ባንለያይ ደስ ይለኛል።። እስከምሔድ ድረስ አንዳንዴ እየተገናኘን ብንጫወት ምን ይመስላችኋል?"
"ጥሩ..... ደስ ይለናል" በርሔ በሰለለች ድምፅ መለሰ።። የቤቱ ሙዚቃ ለመለወጥ ዝም በማለቱ ሲናገር በደንብ የሰማችው ለመጀመሪያ ጊዜ ነበር።።
"ታዲያ የት አገኛችኋለው?"
"ማታ ማታ እዚሁ ብትመጪ አታጪንም" አሁንም በርሔ ነበር ተናጋሪው።። ይነፋነፋል።። ጉሮሮው አካባቢ በጥይት ሳይመታ እንዳልቀረ ገመተችና ከደረሰበት አደጋ በተአምር የተረፈ መሆኑን አሰበች።።
ተሰናብታቸው ልትወጣ ስትል "እኛም ጨርሰናል እግረ መንገድ እናሳፍርሻለን" በርሔ ተናገረና ለጓደኞቹ የተነሱ ምልክት ሰጣቸው።። አብረው ወጡ።። ሰናይት የባለ ፈንጣጣው ሰው ቁመት ሁለት ሜትር እንደሚልቅ ያየችው ይሄኔ ነበር።። በዛ ላይ ቀጭን።።
ቁልቁል ወደ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የሚወስደው አስፓልት ጭር ብሏል።። አልፎ አልፎ ብቻ አንዳንድ ሰዎች ይታያሉ።። አካባቢው ላይ ካሉ መጠጥ ቤቶች የሚወጡ የተደበላለቁ የሙዚቃ ድምፆች በርቀት ይሰማሉ።።
ከቡና ቤቱ ፈንጠር ብላ የቆመች አንዲት ትንሽ ታክሲ ትታያለች።።
"ያ አይሔድም እንዴ?..... አፈወርቂ ሂድና አነጋግረው እስኪ....." በርሔ ባለፈንጣጣውን ሰው አዘዘው።።
አፈወርቂ ተራምዶ ተጠጋና አንገቱን ዝቅ አድርጎ ከሹፌሩ ጋር ጥቂት ተንሾካሾኩ።። ከዛም ማንም እንዳያይ ተጠንቅቆ ለሹፌሩ ድምፅ ማፈኛ የተገጠመለት ሽጉጥ አቀበለው።።
ከዛም ወደነ ሰናይት ዞሮ "ይሄዳል....." አለ።።
ሰናይት ፈገግ ብላ "በሉ ነገ እመጣለሁ..... እንዳላጣችሁ..... አደራ" እያለች ወደ ታክሲው በመሄድ የኋላኛውን በር ከፈተች "ሽራተን ሆቴል ነው የምታደርሰኝ።።" ሾፌሩ በእሺታ ጭንቅላቱን ነቀነቀ።። ወደ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

መኪናው ለመግባት ዝቅ ስትል ማጅራቷ ላይ አቅል የሚያስት ምት አረፈባት:: ማን እንደመታት ሳትለይ ተዝለፍልፋ ልተወድቅ ስትል ፈንጣጣ የበላው ሰው ደገፍ አደረጋትና ወደ ታክሲው ውስጥ አስገባት:: ከጎኗ ገብቶ በሩን ሲዘጋው ታክሲው አስነስቶ ጎዞ ጀመረ:: ወዴት መሔድ እንዳለበትም ጠንቅቆ ያውቅ ነበር::

«««««« »»»»»»

ሰናይት ስትነቃ ራሷን ያገኘችው በአንዲት ጠባብ ክፍል ውስጥ እጅና እግሯ ከእንጨት ወንበር ጋር ታስሮ ነበር::

የክፍሉ አየር እምክ እምክ ይላል:: መሬቱ አፈር ሲሆን ግድግዳውም መፈራረስ የጀመረ የጭቃ ቤት ነው:: ኮርኒስ የለውም:: የዛገው የቤቱ ጣሪያ ላቦት አርግዟል:: ከደብዛዛ አምፖል የሚጨንቅ አይነት ብርሀን ይፈነጥቃል::

ልብሷ በአቧራ ተለውሷል::

ከፊት ለፊቷ በርሔ፣ ሁለቱ ሰዎችና የታክሲው ሾፌር ተቀምጠው ከጣርሙሱ ሊያልቅ ጥቂት የቀረው ጂን ይጠጣሉ::

ቀና እንደማለት ስትሞክር ምቱ ያረፈባት የአንገቷ ዙሪያ ህመም ተሰማትና የጣር ድምፅ አሰማች:: በርሔ አያትና ከጠረጴዛው ላይ ሽጉጡን አንስቶ እየተጠጋት "ገና ስልጠና የሚቀርሽ ጀማሪ ነሽ....." በንቀት እያፈጠጠባት ተናገረ:: ቀጠለ ".....ከሀዲ ለሆኑት የወያኔ ጥርቅም ሰላዮች መሰልጠኛ እንዳልሆንን እናሳያቸዋለን!"

"የምን ሰላይ.....እኔ ሰላይ አይደለሁም"

"ይልቅ እሱን ተይውና እኔ አዲስ አበባ መሆኔን እንዴት አወቃችሁ?" በርሔ በሽጉጡ አፈሙዝ ጉሮሮዋን እየገፋ ጠየቃት::

"ማነህ.....አ.....ንተ እኔ.....አላ.....ውቅህም....."

"ቢያንስ ሳትሰቃይ እንድትሞች መተማመኑ አይሻልሽም.....?" ጥርሱን ነክሶ በጭካኔ እያፈጠጠባት ተናገረ::

"እውነቴን ነው አላ.....ውቅህም.....ከዚህ በፊት....."

አቋረጣትና "ነገርኩሽ እኮ ገና ገና ጀማሪ ነሽ:: ብዙ ትምህርት ያስፈልግሽ ነበረ::..... አንድ ወቅት ላይ ከወያኔ ጋር በትግል ላይ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ሳለን አንቺ እንዳደረግሺው በየ መጠጥ ቤቱ እየገባን ስንቱን የደርግ ባለስልጣን ጉድ ስንሰራው ኖረናል.....” እየሳቀ ቀጠለ “ዱሮ እኛ እናጠምድበት የነበረው ወጥመድ ዛሬ ለኛ ተጠመደ። የሞኝ ስብስቦች ናችሁ” አርአያ አፈወርቅና ሹፌሩ አብረውት ሳቁ።
“እውነተኛነቴን ለማወቅ በኪሴና በቦርሳዬ ውስጥ ያሉትን መረጃዎች አውጥታችሁ..... ተመልከቱ.....”
“አይተነዋል።”

ከቦርሳዋ ውስጥ የተገኙት የፈረንሳይ ፓስፖርት ፣ የዛ አገር ዜጋ መሆኗን የሚገልፅ መታወቂያ፣ በፈረንሳይኛ የተፃፉ አንዳንድ ወረቀቶች የማስታወሻ ደብተር ተገኝተው ነበር። እንዲሁም ሁለት ሺህ የአሜሪካን ዶላርና ድፍንና ዝርዝር የኢትዮጵያ ብሮች....
በርሔ ፓስፖርቱን አንስቶ እየገላለፀው “በዚህ በኩል ጥሩ ከለላን አዘጋጅተው ነበር የላኩሽ..... ግን ገና እንጭጭ ነሽ..... ይልቅ አዲስ አባ መሆኔን እንዴት አወቃችሁ!?”
“አንተ ማነህ!?” ሰናይት ድፍረቷን አሰባሰባ በቁጣ ጠየቀችው። ቀጠለች “.....ደግሞም ማንም ብትሆን ለኔ ጉዳዬ አይደለም..... ጥፋቱ የራሴ ነው አገር አለኝ ብዬ ወደዚህ መምጣቴ.....” አለች በምሬት።

  

ያማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ምዕራፍ 22

ጐህ ሊቀድ አካባቢ ስካራቸው በረድ እያለላቸው መጣ፡፡ የታክሲው ሾፌር ለሊት ላይ ወጥቶ ሄደ፡፡ ሶስቱ ግን ሰናይት ራሷን ካወቀችበት ሰዓት ጀምሮ በጥያቄ እየተቀባበሉ ሲያስለፈልፏት ነበር፡፡ ምቾት የሌለው ወንበሩና እንቅልፍ እጦቱ በእጅጉ አዝለፍልፏታል፡፡

በየተወሰነ ሰዓት ሶስቱ ይሰባሰቡና ለሷ በማይሰማ ድምፅ በትግሪኛ ተንሾካሾከው ሲጨርሱ በጥላቻ ያፈጡቡታል፡፡ ይሄኔ ብርክ ይይዛታል፡፡ ሆዷ ይገላበጣል፡፡

የፈለገውን ዓይነት ጥያቄ ቢጠይቋት ግን ቅብጥርጥሩ ውስጥ እንደማትገባ በራሷ ቃል በገባችው መሰረት በአቋሟ ፀንታ ነበር፡፡ ቀጣይ ሁኔታዎች ግን ወዴት እንደሚያመሩ ለመገመት አልቻለችም፡፡

ስለሷ የተደበቀ ማንነት የሚጠቁም ምንም ነገር ባያገኙባም በጭራሽ እንደማይለቋት ግን ተነጋግረዋል፡፡

ሰናይትም ከነሱ ጋር ሊያግባባት የሚችል አንዳንድ ሙከራዎችን ከማድረግ አልተቆጠበችም፡፡

ቀጠለች መናገር “ምናልባት እኔን ያገኛችሁኝ እውነት በመግንስት ሰላይነት ጠርጥራችሁኝ እንዳልሆነ አውቀዋለሁ.....”

“እና ምንድነው?”

“አላማችሁን በግልፅ ነግራችሁኝ በማንኛውም ዓይነት መንገድ ድጋፍ እንዳደርግላችሁ ብትጠይቁኝ ፈቃደኛ ለመሆን እችል ነበር፡፡ .....ይህን የምለው ከመሬት ተነስቼ አይደለም..... ካለኝ ሀብት ላይ ውስኑን ለበጐ አድራጐት ተቋማት ለማውረስ እቅድ ይዣለሁ.....

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

የናንተ ዓላማም ከነዛ ተቋማት የላቀ ተግባር ካለው ንገሩኝ..... ያሰብኩትን ገንዘብ ላስተላልፍላችሁ.....”

“ለመሆኑ ምን ያህል ገንዘብ ቢኖርሽ ነው በልበ ሙሉነት የምትናገሪው?” አፈወቅር ጠየቀ፡፡

በሞትና በህይወት መካከል የነበሩ ሁለት ቀናትን እንደታገተች አሳለፈች፡፡ በእርግትጥ የገንዘብ መስጠት ጥያቄን ካቀረበችላቸው ሰአት አንስቶ በጭፍንነት ሲጠይቋትና ሲያመነጫጭቋት የነበረው ድርጊታቸውን ገታ አድርገውላት ነበር፡፡ መጨረሻ ላይ እሷ በነሱ ስር እንዳለች የጠየቋትን ገንዘብ መስጠት ከቻለች ብቻ ወደ መግባባት እንደሚመጡ ነገሯት፡፡ ከዛ በኋላ ለሷ አንድ የስልክ ጥሪ ማድረግ ብቻ ነበር ያስፈለገው፡፡ በወቅቱ ለሉዊስ የበርሄ መገኘት ነበረና ዋናው አስፈላጊ ዜና፡፡

ገንዘብ የሚያስተላልፍላቸው የኢትዮጵያው ወኪላቸው የተቀጠረበት ቦታ ተገኝቶ በርሄ ለላከው ሰው የታዘዘውን ገንዘብ ለማቀበል ከጥቂት ሰአት በላይ አልወሰደም፡፡ ይህም ለሰናይት ህይወት መትረፍ ዋስትና መሆን ቻለ፡፡ በዛው ቅፅበት ነበር ሰናይትም ሌላ ተጨማሪ የሀሰት ታሪክ ያዘጋጀችው፡፡ በርሄን በስም እንደምታውቀው ይህም ሊሆን የቻለው ከአራት አመት በፊት በኢትዮጵያ መንግስት የተገደለው ባሏ ስለ በርሄ እንዳጫወታት ነገረችው፡፡ የባሏን እቅድ የነበሩና ተከታታይ የሆኑ በትግራይ ላይ እንዲከናውኑ የምትፈልጋቸው በርካታ ጉዳዮች እንዳሉ ነግራቸው ከጎኗ ሆነው ሊያግዟት ከፈቀዱ አብረዋት እንዲሰሩ ጠየቀቻቸው፡፡

ገንዘብን በተመለከተ በፈረንሳይ እና ከፈረንሳይ ውጭ ጭምር በርካታ የንግድ እና የአክሲዮን ተቋማት ከፍተኛ ገቢ እንዳላት ነገረቻቸው፡፡ ይህን መስማት ለነሱ ትልቅ ዜና ነበር፡፡ እያደረጉ ላሉት ትግል ያለባቸውን የገንዘብ ችግር የተወሰነም ደረጃ ቢሆን ልትቀርፍላቸው እንደምትችል ጉጉትን በህሊናቸው ማሳደር ቻለች፡፡

አፈወርቅ በርሔን “ናአ..... እስኪ” ብሎት ወደ መቀመጫቸው ተመለሱ፡፡ ለሃያ አምስት ደቂቃ በሹክሹክታ ተነጋገሩ፡፡

ይህም ቢሆን ግን ሙሉ አመኔታን ከነሱ ለማግኘት ገና ብዙ እንደሚቀራት ተረድታዋለች፡፡ በእለቱ አመሻሽ ላይ መለቀቋን አሳወቋት፡፡ በቀጣዮቹ ቀናት በፒየር በታዘዘችው መሰረት ከበርሄ ጋር በተከታታይ መገናኘት ጀመረች፡፡ በተቀራረቡ ቁጥር እሱም ለጓደኝነት ብዙም አስቸጋሪ ያልሆነ ሰው እንደሆነ አወቀች፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

«««««« »»»»»»

ከበርሔ ጋር በተከታታይ ለሁለት ሳምንታት እየተገናኙ በነሱ እንቅስቃሴ ዙሪያ አንዳንድ ነገር በግልፅ እንዲነግራት አደረገች። እንዲሁም ተጨማሪ የገንዘብ እርዳታን ሰጠቻቸው። ይህም ሙሉ አመኔታን በአጭር ጊዜ ውስጥ አስገኘላት። ግንኙነታቸው ጤነኛ አቅጣጫን መያዝ ቻለላት።

በአንድ እለት ማለዳ ላይ ሁለቱ ብቻ ቁርስ አብረው እየበሉ ሳሉ "እስኪ ዛሬ እንዴት ወደ ትግል እንደገባህ ንገረኝ?" አለችው ።
በርሔ በሀሳብ ተውጦ ቆየና ጣቶቹንና ከንፈሩን በሶፍት ጠራርጐ "እኔን ከኤርትራ ውስጥ የመለመለኝና ያሰለጠነኝ ጀብሐ ነው"
"ታዲያ እንዴት ለትግራይ ነፃነት ትታገላለህ?" አለችውና መልሳ "ወደ ኋላ ልመልስህና ስለ ራሱ ስለ ጀብሐ አመሰራረት ንገረኝ?"
"እ.....የጀብሐ አመሰራረትና የትግል አካሔድ ውስብስብና የሌሎች አገሮች መንግስታትን ሁሉ የነካካው ነው። ጀብሐ ሊመሰረት ጥቂት ሲቀረው በወቅቱ የተከሰቱት ሁኔታዎችም በእጅጉ ረድተውታል....." አለ በርሔ ስለ ሁኔታው እያሰበ።
ቀጠለ " .....ጊዜው ከ1950ዎቹ አጋማሽ አንስቶ የ1960ቹን ዓ.ም. ያጠቃልላል። በዛን ወቅት የግብፁ መሪ የነበሩት ኮሎኔል ጋማል አብዱል ናስር በ1965 ዓ.ም. በአስደናቂ ሁኔታ እንግሊዝን አሸንፈው የስዊዝ ቦይን ተቆጣጠሩ። ይህ ክስተት በሌሎች አረብ አገሮች ዘንድ ጀግና አሰኛቸው።እሳቸውም ቀጠሉና አረባዊነትን አራምዳለሁ ብለው ተነሱ። በዚህ ጊዜ የመካከለኛውን ምስራቅ ንቅናቄና የአፍሪካን ፖለቲካ ከሚቆጣጠሩት መሪዎች እንደ ዋነኛ ለመታየት በቁ።.....
".....በተመሳሳይ ሁኔታ በዛው ወቅት ሶሪያዊ የነበሩ ወጣቶች በአገራቸው "የባዝ ንቅናቄ" የተባለውን ፓርቲ ማቋቋማቸውን አሳወቁ። ፓርቲው ከሶሪያ አልፎም በኢራቅና በሌሎች ውስጥም ጥሩ ተቀባይነትና ድጋፍ አገኘ። ፓርቲው የተቋቋመበት መሪ ዓላማ "የአረቡን ዓለም ከነሀይማኖቱ ማስፋፋትና የአረብን ታላቅነት መገንባት" የሚል ነበር።ሂደቱ እየሰፋ ሲመጣ ግብፅም ደገፈችውና

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“ሶሪያና ግብፅ አንድ ፌዴሬሽን ሆነናል” በማለት “የግብፅ አረብ ሪፐብሊክ” ተባሉ፡፡.....

“.....እነሱ በዚህ የተፋፋመ ስሜት እያሉ የኤርትራ ተለይታ ለስልሳ ዓመት በቀኝ ግዛት የቆየችበት ወቅት አበቃና ከኢትዮጵያ ጋር የተዋሀደችበት ሁኔታ ተከሰተ፡፡ በእርግጥ ጣሊያን ከወጣች በኋላ እንግሊዝ በእግሯ ተተክታ ክልሉን በተራዋ ቅኝ ለመያዝ ያላሰለሰ ሙከራ አድርጋ ነበር፡፡ ሆኖም የገመተችውን ያህል ቀላል ስላልሆነላት ጥላ ለመውጣት ተገደደች፡፡ ስትወጣ ግን የኤርትራን ወደ ኢትዮጵያ መቀላቀል በግልፅ ባላሳወቀችው የራሷ የግል ጥቅምና ምክንያት አልደገፈችውም ወይም እንዲቀላቀሉ አትፈልግም ነበር፡፡ ለዚህም ክልሉ ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያ ስር እንዳይፀና በወቅቱ ግልፅ እርምጃዎችን ወስዳለች፡፡ ክልሉን ቆርጣ በማውጣትና ካርታ በማሳተም እስከማሰራጨት ድረስ ሄዳለች፡፡”

“ምንድነው ዋና ምክንያቷ?” ጠየቀችው በትኩረት እያዳመጠች
“እንግሊዞች ምን እንደሚያስቡ ሴጣን ራሱ የሚያውቅ አይመስለኝም..... ” አለና በራሱ ንግግር ብቻውን ሲስቅ ቆይቶ ቀጠለ “እንዲሁም የክልሉን እንዳንድ ታዋቂ የወቅቱን ግለሰቦች በማነሳሳት መሳሪያ በመርዳት እና በጥቅም እስከመደገፍ በመጓዟ ማንም ስልጣን ፈላጊ ግለሰብ ሁሉ እየተነሳ እንዲያምፅ ዋናውን መንገድ ከፈተ፡፡ እንዲሁም ከሌሎች ጥቃቅን ችግሮች ጋር እየተያያዘና እርስ በራሱ እየተጠላለፈ የመጣው ሁኔታ በውህደቱ ማግስት ቅርፁን በመቀየር ውህደቱን አንቀበልም የሚል ምክንያት ያላቸው ጥቂት ግለሰቦች እንዲፈጠሩ ምክንያት አገኙ፡፡.....

“ከዛም ከኤርትራ “ሐረካ” በሚል የፓርቲ ስም ወደ ተባበሩት መንግስታት እየሔዱ አቤቱታ ማቅረብ ጀመሩ፡፡ ከነሱ ጋር “የምሁራን ፓርቲ” አቋቁመናል የሚሉትና በነ ወልደ አብ ወልደማሪያም የሚመሩት ደግሞ በቀጥታ ወደ ካይሮ በማምራት ከወቅቱ የግብፅ ፕሬዝዳን ኮሎኔል ጋማል አብዱል ናስርን ማማከር ያዙ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

“.....ናስርም ሲመጡት የኖሩትን ድንቅ ገጠመኝ በደስታ ተቀበሉት፡፡ አንደኛው ምክንያት ግብፅ ውስጣዊ ለሆነው አገራዊ ጥያቄዋ መፍትሔን የሚሰጣት ነበር፡፡”
ሰናይት አቋረጠችውና “ምንድን ነበር ጥያቄዋ?”
“የአባይ ወንዝ፡፡.....ግብፅ የአባይን ወንዝ ከምንጩ ጀምሮ በቁጥጥሯ ስር ለማዋል ከጥንት አንስቶ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከሰላሳ የማያንሱ ጦርነቶችን ከኢትዮጵያ ጋር ገጥማ ነበር፡፡ ግና ሁሉም በሽንፈት ከሽፈውባታል፡፡ በመጀመሪያ ኢትዮጵያን ከፋፍሎ በማዳከም ለአባይ ጥያቄዬ መልስ አገኝበታለሁ ብላ ያመነች በመሆኑ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አጠቃላዩ የአረቡን ዓለም ሲያነጋግር ለቆየው ጥያቄ ስትል ነው፡፡.....”

ሰናይት እይታዋን የበርሔ አፍ ላይ ተክላ ታዳምጣለች፡፡
ቀጠለ በርሔ “.....ግብፅን ጨምሮ በበርካታ የአረብ አገሮች ፍላጐት መሰረት ኢትዮጵያን ከቀይ ባህር የጋራ ባለቤትነት ለመቁረጥ፤ የአረቡን ዓለም ከስዊዝ ካናል አንስቶ እስከ አፍሪካ ቀንድ ድረስ በግራም በቀኝም በኩል በማስፋፋት ቀይ ባህርን “የአረብ ባህር” በማለት ሰይመው በቁጥጥራቸው ስር ለማድረግ፤ እንዲሁም ከእስራኤል ጋር ሁለት ቤት ናቸው የሚሏቸውን የአፄውን አገዛዝ ለማዳከምና ለመጣል ከፍተኛ ፍላጐት ነበራቸው፡፡ ለዚህ የአረቡ ዓለም ቀይ ባህርን የመቆጣጠር ፍላጐት እንቅፋት በመሆን ያስቸገረቻቸው አገር ኢትዮጵያ ነበረች፡፡....

“.....በመሆኑም ናስር ኤርትራን ለማስገንጠል ጥያቄ ይዘው የመጡትን ግለሰቦች በደስታ ተቀበሉ፡፡ ወድያውም በሶሪያ ውስጥ ከተቋቋመው “የባዝ ፓርቲ” ጋር አገናኙዋቸው፡፡ “የባዝ ፓርቲም” የአረቡን ዓለም ለማስፋፋት በጀመረው ትግል የመጀመሪያው እርምጃ ኤርትራን እስከ ጅቡቲ ጫፍ ድረስ ከኢትዮጵያ ቆርጦ በዓረቡ ዓለም ካርታ ላይ መቀላቀል ሆነ፡፡ ካርታውም ወድያው ተስሎ በመላው የአረብ አገራት እንዲሰራጭ ተደረገ.....
“ ነገሩ እንዲህ እየተፋፋመ ሲመጣ “ሃረካ አልታህሪር ኤርትሪያ” በሚባለው ፓርቲ ውስጥ አባል የነበሩ ጥቂት ሰዎች ተገንጥለው

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

በመውጣት “ጀብሐ አልታህሪር ኤርትሪያ” የሚለውን ሌላ ፓርቲ በ1961 ዓ.ም. አካባቢ አቋቋሙት።”
“በምክክር ነው ያቋቋሙት?”
“አይደለም በውስጥ ጉዳያቸው ተጣልተው ነው።፡የፓርቲ መሰንጠቅ ነው የተፈጠረው ማለት ይቻላል። ከዛ በኋላም በርካታ ጦርነቶችን እርስ በእርስ አካሂደው ነበር።፡” አለ በርሔ ፊቱን ፈታና ጨምደድ እያደረገ።፡
ቀጠለ “.....እና በሶሪያ የተቋቋመው እስልምናን አስፋፊው የባዝ ፓርቲ መጀመሪያ ለሁለቱም ፓርቲዎች በኋላም ሀይሉን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያጠናከረ ለሄደውና “ጀብሐ” ለተሰኘው ኤርትራን አስገንጣይ ፓርቲ ከፍተኛ እርዳታዎችን ከአረቡ አገራት እያሰባሰበ መስጠት ያዘ።፡....

“.....በሱዳን ውስጥ የነበሩት የግብፅ ወታደርና ፖሊሶችም የጀብሀን አባላት በማሰልጠንና አብሮም በመሰለፍ አቅሙን አጐለበቱለትና ወደ ትጥቅ ትግል እንዲገባ የመንገዱን ጥርጊያ አመቻቹለት። ግንኙነታቸው እየጠነከረና “ጀብሐም” በአረቡ መንግስታት አመኔታን እያገኘ ሲመጣ የፍልስጤም ነፃ አውጪ ግምባር መሪዎች ወደ ኤርትራ ጀብሐ የተቆጣጠራቸው ምሽጐች በመምጣትና ጀብሐዎችም ወደነሱ እየሔዱ ስልጠናቸውን አጠናከሩት። ቅድም እንደገለፅኩልሽ የ”ሻዕቢያ” ምስረታ እንደታሰበ እነ ኢሳያስ አፈወርቂ፣ መሐመድ ኑር፣.....የተባሉ በርካታ ሰዎች ንቅናቄውን ተቀላቀሉት።፡”

ሰናይት ስትሰማ ቆይታ “ወደፊት ይህ የቀይ ባህር ክልል ሙሉ በሙሉ የአረቦች ጥብቅ ይዞታ መሆኑ ነዋ!?” ጠየቀች በአግራሞት።፡
“ለዚህ አይደል የኢትዮጵያ አቅም እንዲዳከምና ይህን የባህር ክልል እንዳትጋራ ለማድረግ ሲሉ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች በመደገፍና በማስታጠቅ ሁሌም ከጦርነት እንዳትወጣ የሚያደርጓት!” አለ በርሔ።፡
“በዚህ ላይ ያለው የአንተ እምነት ምንድነው?”
“ለጊዜው ትግራይን ከማስገንጠል በስተቀር ምንም ያሰብኩት ነገር የለም ወደፊት የሚታይ ይሆናል።፡” አለ።፡
“እነ ኢሳያስ አፈወርቂ ግን ስለዚህ ሚስጥር ያውቃሉ?”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“ኧ..... በደንብ ነዋ፡፡ መለስ ዜናዊ ራሱ ያውቃል፡፡ ለዚህ ስራቸው ከአረብ መንግስታቶች የተከፈላቸውና እየተከፈላቸው ያለው ገንዘብ ቀላል እንዳይመስልሽ.....”
“አሁን እንዴት ነው ቀይ ባህር ሙሉ በሙሉ የአረብ ባህር የምትሆነው?”

“የኢሳያስ አፈወርቂ አገዛዝ ከስልጣን ሲወርድ ቦታውን እንዲይዙ ከፍተኛ ድጋፍ እየተደረገላቸው ያሉት ቆለኞቹ ራቢጣዎችና አክራሪ የሆኑት የአረብ ጥገኞች ናቸው፡፡ ራሳቸውን “የአዋተ ቡድን” ብለው ይጠሩታል፡፡ እነሱን ስልጣን በማስጨበጡ በኩል ግብፅና የአረቡ ዓለም ገና ቀጣይ የቤት ስራ አለባቸው፡፡ የኤርትራ ፊደል አረብኛ የተደረገበት ዋና ምክንያት ራሱ አገሪቷን በአረብ ግዛት ስር ለማጠቃለል ባላቸው እቅድ ምክንያት ሲሆን በቅርቡ ሊፈፀም ባይችል እንኳ ወደፊት ጊዜውን ጠብቆ መጠናቀቁ አይቀርም፡፡”
“ሻዕቢያዎች ይህን የሚያውቁ ከሆነ መጀመሪያውኑ ጀብሐን ለምን መቷት?” ጠየቀች ሰናይት፡፡

“መጀመሪያ ስለ አጠቃላዩ ሁኔታ ምንም እውቀት ስላልነበራቸው ነው፡፡ በኋላ ላይ ግን ካለ አረብ አገሮቹ ድጋፍ በስተቀር መታገል ስላልቻሉ ለእርዳታ ሲሉ የአረቦቹን እቅድ ተቀበሉት፡፡ ከዛ በኋላ ጀብሀን ያላቀፉበት ጉዳይ የሚያገኙትን ጥቅም እንዳይጋሩዋቸው ስለፈለጉ ብቻ ነው” አለ በርሔ፡፡
ሰናይት ስታስብ ቆየችና “በጀብሐ ተመልምለህ እንዴት ለትግራይ ነፃነት ለመታገል ተነሳሳህ?”
“በናቴ በኩል የትግራይ ልጅ ነኝ፡፡”
በርሔ ንግግሩን ቀጠለ “ያደኩትም እዛው ነው፡፡ ኤርትራ የሔድኩት ግን ከዛ በኋላ ነበር፡፡ በዛ አጋጣሚ ነው ጀብሐ ያገኘኝ፡፡”
“ጊዜው መቼ ነበር?”
“በ1965 ዓ.ም. “ግምባር ገድሊ ትግራይ” በተባለ የፓርቲ ስም ስር፡፡” ቀጠለ ሁኔታውን እያስታወሰ “.....ከጀብሀ ቀጥሎ ሻዕቢያም በሌላ ጐን “ተጋድሎ ሓርነት ትግራይ” የተባለ ቡድን የካቲት 11/1967 አቋቁሞ መጣ፡፡”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“ለምንድነው ለየብቻ የተመለመላችሁት?”
“በኋላ ላይ ነገሩን ስንደርስበት በ1964 ዓ.ም. አካባቢ ሻዕቢያና ጀብሐ ተገናኝተው በመመካከር ከስራቸው የሚንቀሳቀስ ሌላ አንድ ፓርቲ ለመፍጠር ምክክር አድርገው እንደነበረ ነው።”
“ይህን ያደረጉት ከትግራይ ህዝብ ድጋፍ ለማግኘት ነበር?” ጠየቀችው
“አዎና.....” ቀጠለ “በዛን ጊዜ በአዲስ አበባ ሆነው የተማሪዎችን ረብሻ ያፋፍሙ የነበሩት የኤርትራ ተወላጆች እና ሻዕቢያ ካደራጀው “ተጋድሎ ሓርነት ሕዝቢ ትግራይ” አባል ከነበሩት መሀከል ጴጥሮስ ሰለሞን በአድዋ ሚሽን ተማሪ ከነበረው ከመለስ ተክሌ ጋር ይገናኛል።
“.....ከዛም እሱን ይይዝና መለስ ዜናዊን በበፊት ስሙ ለገሰ ዜናዊን፣ አባይ ፀሀዬን እና ሌሎች ሙሉ ኤርትራዊ ወይም ትግራይ ድብልቅ ዝርያ ያላቸውን ሰዎች መለመለና “ማገብት”ን ወይም “ማህበረ ገስገስቲ ብሔረ ትግራይን” ከ1965-67 ባለው ጊዜ መሀከል መሰረቱት።”
“ምንድን ነበር በናንተ ፓርቲና በነሱ መሀከል የነበረው ልዩነት?”
“በአመዛኙ ይመሳሰላል.....የኔ ፓርቲ ማለትም ግምባር ገድሌ ትግራይ ሲመሰረት መሪ አቋሙ “ትግራይ የኢትዮጵያ አካል አይደለችም። ቅኝ ግዛት ናት።” የሚል አቋምን ይዞ ነው የወጣው።”
“በሻዕቢያ የተፈጠረው ማህበረ ገስገስቲ ብሔረ ትግራይስ?”
“አቋሙ ከኛ ጋር ተመሳስሎ ቢኖረውም የትግራይን ህዝብ ለማደናገር ሌላ የከለላ መፈክር ይዞ ነው የተቋቋመው።”
“ምን የሚል?"
“እ.....እኛ ለትግራይ ብሔር ቆመን በክልላችን ውስጥ ያሉትን ችግሮችን ኢትዮጵያዊ በሆነ መልኩ ለመፍታት እንሞክራለን። የሚል ነበር። በመሀከሉ ግን ሻዕቢያና ጀብሐ በነበረባቸው የውስጥ ችግር ድጋሜ ተጣሉ።” ብሎ ዝም አለ።
“ምን ተፈጠረ ቀጥሎ?”
“ጀብሐ የሻዕቢያ ውላጅ የሆነውን “ማ.ገ.ብ.ት.”ን ለማጥፋት ፈለገ። ሻዕቢያም በአፀፋው “ግምባር ገድሌ ትግራይን” ወይም እኛን ማፋጥት ፈለገ። እዚህ ውሳኔ ላይ ሲደርሱ ሻዕቢያ ጀብሐን በብልጠት

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ቀደመውና" ብሎ በሀሳብ ሲመለስ ፊቱ በቅፅበት አመድ የተነፋበት መሰለ።።
ቀጠለ ".....በ1968 ዓ.ም. በሻዕቢያ የተነደፈና በ"ማገብት" የሚተገበር እቅድን ነበር ይዘው የመጡት።።"
"ምን የሚል?" በጉጉት ጠየቀው።።
"የ"ማ.ገ.ብ.ት." የበላይ ተጠሪዎች በቀጥታ ወደኛ ሰዎች ጋር መጡና "እኛ ሁለታችን የትግራይን ህዝብ ወክለን የቆምን ቢሆንም በመሀከላችን ልዩነቶች አሉ።። ነገር ግን ልዩነቱን በማስወገድ በጋራ ብንታገል ይሻለናል" ሲሉ ሀሳብ አቀረቡ።።"
"እነማን ነበሩ የመጡት ግን?"
"እ..... በአሁኑ ሰአት ኢትዮጵያን በመምራት ላይ ከአሉት መካከል ዋና ዋናዎቹ"
"ምን መልስ አገኙ?"
"ጉዳዩን ጀብሐ እንዲያየው አደረግን።። ጀብሐም ተቀበለውና ሁለታችን የበታች ፓርቲዎች በ1968 ዓ.ም. መስከረም ወር ይመስለኛል.....በ..... አጋሜ አውራጃ አይጋ ከሚባል ቦታ ኘሮግራማችንን ይዘን እንድንገናኝ ተደረገ።። በኛ በኩል ያው "ትግራይ ቅኝ ግዛት ናት" የሚለው ፖሊሲያችን ቀረበ።። በነሱ በኩልም የትግራይ ህዝብ እንዳይመታን ፈርተን ነው እንጂ ልዩነት የለንም በዚህ እንስማማ በቀጣዩ ደግሞ ምን ዓይነት ኘሮግራም እንደምንፅፍ ወደፊት እንደራደር ተባባልን።።"
"ከተስማማችሁ ታዲያ ምን ተፈጠረ?"

"ሊያጠምዱን ነበር የተሰማሙት።። በጥቅምት መጨረሻ አካባቢ ሁለታችንም እንደገና ተገናኘን ሙሉ እርቅ ወረደ ተባለ።።ለሊት አብረን እንድተኛ ሲደረግ ግን ያላሰብነው ነገር ተከሰተ.....
".....ሻዕቢያ ረሽኑዋቸው ብላ የ"ማገብትን" ሰዎች አዛቸው ነበር።። ለሊት አስር ሰዓት አካባቢ የእንቅስቃሴው መሪ በነበረው ሰው ምልክት ሰጪነት የግምባር ገድሌ ትግራይ ሰዎች በብዛት ተገደሉ።። እኔም በሁለት ጥይት ትከሻዬ ላይ እና ክንዴን ተመትቼ ለመትረፍ ከቻሉት ጋር አመለጥኩኝና ተመልሼ ከጀብሐ ጋር ተቀላቀልኩኝ።።"
"ማነበረ ትግራይ ትግሪኝ የተባለው ፓርቲስ ማን ነበር?"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

“ግምባር ገድሌ ትግራይ የተባለውና በጀብሐ የተቋቋመው የኛ ፓርቲ ነው፡፡ የስም መቀያየር ተከስቶ ነው እንጂ.....”
“ማኅበረ ተጋሩና የተባለውስ?”
“እሱ ደግሞ ሁለቱንም አገናኝ ሆኖ የተፈጠረ ነው፡፡”
“ማንና ማንን?”
“ትግራይንና ኤርትራን”
“ለምን ዓላማ?”
“የትግራይ ህዝብ ኢትዮጵያዊነቱን የሚያምንና የሚፈልግም ሲሆን በኤርትራ የትግል መሪዎች በኩል ግን የቅኝ ግዛት ጥያቄ እየተፋፋመ ነበር፡፡ የትግራይ ህዝብ ደግሞ ይህን የኤርትራ ጥያቄ አይደግፈውም አይቀበለውምም ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ የትግራይ ህዝብ በአንድነት ተነስቶ እንዳይደመሰሳቸው “ማኅበረ ተጋሩና” ከትግራይ ሰዎች መሀከል በጥቅም ተደልለው የኤርትራን ሀሳብ የሚደግፉትን መልምለው አቋቋሙት፡፡ ይህም ያው በትግይ ተወላጆች አማካኝነት የትግራይን አንድነት ከፋፍሎ ለማዳከም የታቀደ ነበር፡፡”
“ይህን ኤርትራን የማስገንጠሉን ሀሳብ ግን የኤርትራ ህዝብ ሙሉ በሙሉ ደግፎት ነበር?”
“በአመዛኙ አልደገፈውም ነበር ማለት ይቻላል፡፡”
“እንዴት?” አለች ሰናይት መልሱ አስገርሟት፡፡
“እ.....የተለያዩ ስሞችን በመያዝ ፓርቲዎች በኤርትራ ምድር ላይ መፈጠር የጀመሩት በ”ጀብሐና” በ”ሃረካ” ብቻ አልነበረም፡፡ ከነሱ በፊትም የጣሊያንና የእንግሊዝ አገዛዞችን በመቃወም የተንቀሳቀሱ በርካታዎች ነበሩ፡፡ ከነሱ መሀከል አንዱ ጠንካራ የነበረውና የኤርትራ ህዝብ ሰማንያ በመቶው ይደግፈው የነበረው “የአንድነት ማኅበር” የሚባለው ነው፡፡ መሪ ዓላማው “ኢትዮጵያ ወይም ሞት” የሚል ሲሆን የእንቅስቃሴው ዋናው ፍፃሜም ኤርትራን ከኢትዮጵያ መቀላቀል ነበር፡፡ እናም የሱን ማኅበር ፓርቲ ደጋፊዎችን ስትመለከት ህዝቡ በፍፁም ከኢትዮጵያ መገንጠልን አይፈልግም ነበር፡፡.....” ንግግሩን ገታ አድርጐ ቀጠለ “.....በኋላ የህዝቡን ስሜት የሚያሸፍት ችግር መጣ እንጂ”
“ምን?” አለች፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“የአረብ አገሮች ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ በፈጠሩት ዘዴ የኤርትራን ህዝብ አረባዊነት መስበክ ጀመሩ.....”
“እንዴት አድርገው?”
“ሶሪያና ግብፅ በቀጥታ በራዲዮ የሚተላለፍ ስርጭት ሲጀምሩ ሱዳን፣ ሳውዲት አረብ፣ ኢራቅና ሌሎችም በየጋዜጦቻቸው በየስብሰባውና በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ በመጠቀም ነው፡፡ በቆላው የኤርትራ ክልል የሚኖሩት የእስልምና ተከታዮች በቀላሉ ሀሳቡን ተቀብለው በማስተጋባት ኮበለሉ በሌላም በኩል በንጉሰ ነገስቱም ሆነ በዘመነ ደርግ የህዝቡን የስሜት ፍልሰት ለመግታት በቂ እንቅስቃሴ ባለመደረጉ “ሃረካና ጀብሐ” ጨምሮ ሌሎቹም ይበልጥ ተጠናከሩ፡፡” አለ፡፡
“ ሌላው በደንብ ግልፅ ያልሆነልኝ ነገር እነዚህ የኤርትራ ሰዎች ምንድነው ከፍልስጤም ጋር በጥብቅ እንዲግባቡ ያስቻላቸው?”
“ ኢትዮጵያ በእስራኤል ውስጥ ያላትን ግዛት እና የሀይማኖት ስፍራዎች ከድሮም ጀምሮ ለቃ እንድትወጣ ፍልስጤማውያኑ ይፈልጋሉ፡፡ በወቅቱ ኢትዮጵያ ይህንን ብታደርግ ኖሮ እስራኤልን አዳክሞ መሬቱን ለመንጠቅ ይቻላል ብለው ያምኑ የነበረ ሲሆን ኢትዮጵያ የማትነቀል ጋሬጣ ስለሆነችባቸው ነው፡፡ እንዲሁም ኢትዮጵያ ከእስራኤል ጋር ያላት ታሪክና ሀይማኖታዊ ትስርር ለዘመናት ሲያበሳጫቸው የኖረ ሲሆን በተገኘው አጋጣሚ ኢትዮጵያን በተዘዋዋሪ ለማጥቃት ሲናፍቁ ቆይተዋል፡፡ የወቅቱ የኤርትራውያኑ ጥያቄ ፍልስጤም በኢትዮጵያ ጉዳይ ጣልቃ እንድትገባ አጋጣሚ ፈጠረላት፡፡ ሌላው እንግዲህ የቀይ ባህር ጉዳይ፣ አረባዊነትን እና ሀይማኖትን ከማስፋፋት አንፃር የሚያያዝ ሚስጥርም አለው” አለ፡፡

“እሺ..... ወደ ራስህ ታሪክ እንመለስ እስኪ.....” አለችና ያቆሙበትን አስታውሳ “ቆስለህ ካመለጥክ በኋላ የገጠመህ ምንድነው?”
“ብዙ ስላልተጐዳሁ ነው ለማምለጥም ለመትረፍም የበቃሁት፡፡ እንዳልኩሽ ወደ ጀብሐ ተመልሼ በቀላል ህክምና ለመዳን ቻልኩኝ፡፡ ከዛ በኋላም የጀብሐ ውስጣዊ ፖሊሲ አመቺ ስላልነበረ መጥፋት እንዳለብኝ አመንኩ፡፡”
“ምንድነው የፖሊሲው ችግር?”
“ብዙ ቢሆንም..... ዋናው ግን በአመዛኙ የጦር ማሳሪያና የገንዘብ እርዳታ የሚያደርጉለት የአረብ አገሮች ስለነበሩ ከሚሰጡት

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

መሳሪያ ጐን ለጐን አክራሪ የሆነ የሀይማኖት ስርዓትን አብሮ በኤርትራ ምድር ላይ እንዲያሰፍን ይገፋፉት ነበር። ከሻዕቢያ ጋር እያጋጨው የሄደው ችግርም ይኸው ነው።"
"ሻዕቢያስ የተፈጠረው እንዴት ነው?"
"በራሱ በጀብሐ ነዋ..... መልሶ ሻዕቢያ ጀብሐን ደመሰሰው እንጂ..... ጀብሐ በአመዛኙ አረባዊ የሆነ ሀይማኖታዊ እሳቤን ይዞ ነበር የሚታገለው። ምክንያቱም በርካታ የሆነ የጦር መሣሪያና ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞች ከነሱ ያገኝ ስለነበር። ይህ አካሔዱ ደግሞ በኤርትራ ውስጥ የነበሩትን ክርስቲያን ህዝቦችን ሊስብና ወደ ትግል ሊያስገባለት አልቻለም። በዚህ መኻከል ክርስቲያኑን ሊያጠምድበት የሚችልበት መንገዱ ጠባብ ነበር። በጦር መሳሪያ እያስገደደ ወደ ትግሉ ከማስገባት ውጪ። እንደዛም ሆኖ ክርስቲያን የሆኑት ታጋዮች ላይ ከፍተኛ ግፍና በደል ይፈፀምባቸው ነበር።.....

".....ለሻዕቢያ መፈጠር እንስቃሴን ያስጀመረው ስሜት ይህ ሲሆን ወቅቱ የ"ሀረካና የጀብሐ" ፀብ እየተካረረ ሄዶ ወደ መጥፎ ደረጃ ላይ ደርሶ የነበረበት ጊዜ ነው። ይህንን ያጤኑት የእስልምና አገሮች በሱዳኗ ካርቱም ከተማ ሊያስታርቋቸውና ትግሉን በጋራ ተቀናጅተው የኤርትራን ማስገንጠል እንዲያፋጥኑ ለመምከር ስብሰባ ጠሩ። በወቅቱም የ"ጀብሐ" ዋና ተጠሪዎች ስለቀሩ በዛው ዕለት በ"ጀብሐ" ስር የነበረው "ሻዕቢያ" በግልፅ ተገንጥሎ መውጣቱን አወጀ.....
"....."ጀብሐ"ም የ"ሻዕቢያን" ለብቻ መንቀሳቀስ ተቀበለው ምክንያቱም ክርስቲያን የሆነውን ህዝብ ያንቀሳቅሳል ብሎ ስላሰበ ነበር።" ብሎ ብርጭቆውን አነሳና ከውሃው ተጐነጨ።
ከዛም ወደ ራሱ ታሪክ በመመለስ..... ቀጠለ ".....እና እንዳልኩሽ ጠፍቼ ወደ ሱዳን ገባሁና ጥቂት ወራት እንደቆየሁ ተመልሼ ወደ ሻዕቢያ በመምጣት አዲስ ታጋይ መስዬ ተቀላቀልኳቸው።"

"ከልብህ ደግመህ ወደ ትግል ለመግባት ፈልገህ ነው ግን?"
"አዎ..... የትግራይን መገንጠል ዛሬም እፈልገዋለሁ..... እሰዋለታለሁም" አለ በስሜት።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“በዛው ዓመት የ”ማገብት” አባላት ወደ “ሻዕቢያ” በመምጣት የአመራር ሰዎች እንዲሰጣቸው ጥያቄ አቀረቡ፡፡ ቁጥርና ስማቸውን የማላስታውሳቸው ሰዎችን ሲሰጧቸው ከነሱ መሀከል አንዱ እኔ ነበርኩ፡፡ ትግራይ ተመልሰን እንደገባን “ሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ” ወይም “ሕ.ወ.ሓ.ት” በማለት የቀድሞ ስሙን ለወጡትና ትግል ቀጠልን፡፡

“ከዛ ተመልሰን ጥቂት እንደቆየን የወያኔ አባል ሳይሰበሰብና ለበታች ታጋይ ሳይነገር ሶስት ከፍተኛ የህወሀት የወቅቱ መሪዎች ሱዳን በድብቅ ሄደው “1968 ማኒፌስቶ” የሚል ንድፍ ይዘው መጡ፡፡”

“ምንድነው የማኒፌስቶው ፅሁፍ?” አለች ሰናይት፡፡

“ባጭሩ የሚለው እንደዚህ ነበረ፡፡....” እያስታወሰ መናገሩን ቀጠለ፡፡

“.....ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል አይደለችም፡፡ቅኝ ግዛት ናት እንጂ፡፡ ስለዚህ እሷን ማስገንጠል፡፡ ሁለተኛ ትግራይንም ቆርጠ ነፃ የሆነ ሪፐብሊክ መንግስት መመስረት፡፡ በሶስተኛ ደረጃ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ብሔር ብሔረሰቦችን ራሳቸው ተገንጥለው የራሳቸውን መንግስት እንዲመሰርቱ ማስቻል፡፡ የሚለውን ማኒፌስቶ ይዘው መጡና ለኤርትራ መገንጠል ሙሉ ኃይላችንን እናውላለን፡፡ እስከመጨረሻውም ደማችንን እናፈሳለን አሉ፡፡ በሀሳቡ ተስማምተን ትግል ቀጠልን፡፡ በኋላ ላይ ግን ይህ የ”1969 ማኒፌስቶ” ድርጅቱን እየከፋፈለው መጣ፡፡”

“ምንድነው የክፍፍሉ መንስኤ?”

“አንደኛዎቹ ወገኖች” ይህ የጠባብ ብሔርተኝነት ስሜት ነው፡፡ ማኒፌስቶውን አንቀበለውም የሚል ነበር፡፡ ሁለተኛዎቹ ማለትም በአመራር ላይ የነበሩት ዋኖቹ.... የተባሉት ክፍሎች ደግሞ አብዛኛው ታጋይና የትግራይ ህዝብ እንዳልተቀበለው ስላዩ ማኒፌስቶውን በግልፅ አናስቀምጠው፡፡ ይልቅ ሌላ ከለላ የሚሆን የአንድነት ፖሊሲ እንያዝና በውስጥ ለውስጥ ግን የማኒፌስቶውን እቅድ እንተግብር አሉ፡፡.....

“.....ሶስተኛዎቹ ወገኖች ደግሞ አይሆንም “የትግራይ ነፃ ሪፐብሊክ መንግስት ምስረታ” የሚለው አቋማችንን በግልፅ አስቀምጠን እንታገል ሲል እንቢ አለ፡፡”

“ያስከተለው ውጤት ምን ነበር?”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“የድርጅቱ ታጋዮች በብዛት እየከዱ ወደ ደርግ መቀላቀል ወይም ወደ ሱዳን በመሰደድ የፓርቲውን ህልውና አደጋ ላይ እየጣሉት መጡ። በዚህ ጊዜ መሪዎቹ ከሻዕቢያ ጋር መከሩበትና ማኒፌስቶውን የተቃወሙትን በሙሉ እና እኔ የነበርኩበት ክፍልም አቋም ለአደጋ ያጋልጠናል ብለው ስላመኑ እኔን ጨምሮ አስራ አንድ የምንሆነውን የበላይ ሰዎች ለሊት ሳናስበው አፍነው ወሰዱን።”
“ወዴት?”
“ሳልህ በረሃ ወደሚባል ቦታ”
“ሊያስሯችሁ ነበር?”
“እሱማ ቢሆን ባልከፋ..... ሊረሽኑን እንጂ..... ስንቱ ታጋይ በነሱ በራሳቸው በየበረሀው ተረሽኖ ቀርቷል”
“እናስ?”
“እናማ..... ሳህል ላይ እንደደረስን እኛን ይዞ ይጓዝ የነበረው የሕ.ወ.ሓ.ት ጓድ የ”ጀብሐ” ታጋዮች ጋር በአጋጣሚ ተገናኘና ተኩስ ተከፈተ። ጦርነቱ ድንገተኛና መጥፎ ስለነበረ ከ”ሕ.ወ.ሓ.ት” አዋጊዎች እኛን ረሽነው እንዲያፈገፍጉ ትዕዛዝ ተሰጠ።” ቀጠለ በርሔ “.....እንደምታይው አንድ እጄን ለመቆረጥ የሚያበቃው ምት ደረሰብኝ.....” አለ አርቴፊሻሉን እየነካካ። “የቀኝ እግሬ ላይም በደረሰው ምት አንካሳ ሆንኩ..... የከፋው ግን ጉሮሮዬን ሸርፋ ያለፈች ጥይት ነበረች።..... እግዚያብሔር ጊዜህ ገና ነው ስላለኝ ብቻ እሷም ድምፄን አሰለለችው እንጂ ለሞት አላደረሰችኝም።” አለ እልህና እምባ እየተናነቀው።

ቀጠለ “..... ከአስራ አንዳችን ሶስታችን ቆስለን የ”ጀብሐ” እጅ ወደቅን። ይዛን ወደ መሸገችበት ስፍራ ሸሸች። አንዱ እዛ ስንደርስ ሞተ። ሁለታችን ጊዜያዊ ህክምና ተደርጐልን ወደ ሱዳን ተላክን። ከረዥም ጊዜ ህክምና በኋላ ዳንን.....”
“አሁንም እሱ አብሮህ አለ?”
“የለም..... እሱ ከዛ በኋላ ሁሉንም እርግፍ አድርጐ በመተው በቀይ መስቀል አማካኝነት እንግሊዝ ገባ።”
“አንተስ?”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“ህልሜን ማስፈፀም አለብኝ ብዬ ከራሴ ጋር እልህ ተያያዝኩና እዛው ሱዳን ውስጥ ለአስራ ስድስት ዓመት ተቀመጥኩኝ፡፡”
“ምን እያደረክ?”

“በአመዛኙ ከፖለቲካው እንቅስቃሴ አልራቅኩም፡፡ እዛም ሆኜ የትግራይን ነፃ መንግስት የሚደግፉ ሰዎችን ሰብስቤ ፓርቲ ለማቋቋም ብዙ ጥረት አድርጌአለሁ፡፡ የገንዘብ አቅም ስላልነበረኝና የጠበቀ ቅንጅትም መፍጠር ባለመቻሌ ውጤት ማየት አልቻልኩም እንጂ፡፡.....

“ከዛም በሱዳን የሰበሰብኳቸውን ጥቂት ሰዎች ይዤ ወደ ኤርትራ ተመለስኩኝ፡፡ ኤርትራም እንዳሰብኩት አመቺ ስላልነበረች ከአንድ ዓመት በኋላ ጥቂቶቹን ይዤ አሜሪካ ገባሁ፡፡ በዛም ለሶስት ዓመት ተኩል ተቀመጥኩና የፓርቲው አቅም መስመር ለማስያዝ ከቻልኩኝ በኋላ ተደብቄ አዲስ አበባ ከመጣሁ ሁለት ዓመት ሆኖኛል፡፡ አሁን እዚህ ሆኜ በተለይ በሰው ሀይል ትግሉን እያጠናከርኩ እገኛለሁ፡፡”

“አሁን ምን ያህል አቅም ማካበት ችለሀል?”
“ያው..... ትግራይ ውስጥ ባሉት ሰዎቼ አማካኝነት ቀላል የማይባሉ ለትግል የተዘጋጁ ደጋፊዎችን ማግኘት ችያለሁ”
“የት ነው የምታሰለጥናቸው?”
“አሁንማ ከአንድም ሁለት ትልልቅ አማራጮች አሉኝ፡፡ ያለፈ ወር ላይ እዚሁ አዲስ አበባ ካሉ የ”ሻዕቢያ” ባለስልጣናት ጋር በድብቅ ተነጋግሬ ነበር፡፡ በቻሉት አቅም ሁሉ ከጐኔ እንደሚሆኑ ገልፀውልኛል፡፡

“እንዴት አዲስ አበባ ሊመጡም ሆነ ልታገኛቸው ቻልክ?”
“አሁንም እኮ በድብቅ የ”ሻዕቢያ” ባለስልጣናት ከኢትዮጵያ መንግስት የሚስጥር አባላት ጋር ይገናኛሉ፡፡ በዚህ ምክንያት የመጡና ከኔ ጋር ትውውቅ የነበራቸው ናቸው” አለ በርሔ፡፡
ቀጠለ “.....ሱዳንም ልትተባበረኝ ፈቃደኛ መሆኗን ገለፀች፡፡”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“እኔ የሚገርመኝ ነገር ሱዳን ሁልጊዜ ከኢትዮጵያ ለሚነሱት ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በቀላሉ የትብብር እጆቹን እንደ እናት የምትዘረጋው ለምንድነው?” ሰናይት ጠየቀች።።

“ግልፅ ነው..... ከአባይ ለምታገኘው ጥቅም ስትል ነው።። ኢትዮጵያ ላይ ሰላም ከሰፈነ በአባይ ወንዝ የመቀጠም የባለቤትነት መብትን ታነሳለች።። ይህ ደግሞ የመኖር ህልውናቸውን በአመዛኙ በአባይ ወንዝ ላይ የመሰረቱት ሱዳንና ግብፅን በእጅጉ የሚጐዳና የሚያስቆጣ ይሆናል።።.....

“ለዚህ ሲሉ ሁለቱም አገሮች በኢትዮጵያ ውስጥ ተቃዋሚ ፓርቲ ባይኖር እንኳ ራሳቸው ባጀት መድበው በማቋቋም የኢትዮጵያን ህዝብና መንግስት ትኩረት ወደ ጦርነት ያዞሩታል።። ጀብሐንም፣ ሻዕቢያንም፣ ሕወሓትንም፣ ኦነግንም፣ እኛንም ሌሎች ካሉ ሌሎችንም..... በፈቃዷ የምትቀበለው ለዛ ነው።።..... የሚገርምሽ በደርግ ጊዜ እሱን በመቃወም ለትግል የወጡ ከሰላሳ ሶስት በላይ የሚሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሱዳን ውስጥ ቢሮ ከፍተው ይንቀሳቀሱ ነበር።።”

“ትብብራቸው ግን ምን ምንን ይጨምራል?”
“በሱዳን የወታደር ማሰልጠኛ መሬትን ከመስጠት ጀምሮ ለትግሉ ድጋፍ የሚደጉሙ የንግድ ተቋማትን ከፍተሽ እስከመንቀሳቀስ ድረስ የምትችይ ሲሆን.....”
“እውነት ይህን ታደርጋለች?”
“ቧ..... ለምሳሌ “ሕወሓት” በሱዳን ውስጥ በከባድ የጭነት መኪናዎች በትራንስፖርት ግልጋሎት ላይ ተሰማርቶ ይሰራ ነበር።። ሰፋፊ የእርሻ መሬቶች ነበሩት።። በዛ ላይ የታወቀ ትልቅ ጋራዥ እና ሌሎችም የንግድ ተቋማት ነበሩት።።”
“ግብፅስ ምንድነው የምታደርገው ድጋፍ?”

“የጠር መሳሪያ እርዳታ..... በባለሙያዎች የወታደራዊ ትምህርትና የግንዘብ ድጋፍ ማድረጓ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው።።”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ቀጠለ በርሔ ".....ከዚህ ውጪ "ጀብሐ" ከሃይማኖት ጋር በተያያዘ ሁኔታ ባህር ማዶ ከሚገኙ የእስልምና አገሮች ሳይቀር ከፍተኛ እርዳታ ያገኝ ነበር።።....

".....ሌላው አጠቃላይ የኢትዮጵያ ተፈጥሮዋዊ አቀማመጥ የተነሳ በርካታ የእስትራቴጂ ጠላቶች እንዲነሱባት ዋና ምክንያት ሆኗል። ቀይ ባህር በራሱ ለመካከለኛው ምስራቅ የዓለም ፀጥታና እንቅስቃሴ ቁጥጥር እጅግ ወሳኝ የሆነ ክልል በመሆኑ የአለማችን ሃያላን አገሮች በበላይነት ሊያስተዳድሩት ይፈልጋሉ። እነሱም ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ በርካታ ብጥብጦችንና ጦርነቶችን በኢትዮጵያ ላይ እንዲነሱ ዋነኛ ምክንያቶች ሆነዋል።"

"አንድ እጅግ የምናደንቅትን ታሪክ ላጫውትሽ..... መሪዎቹ በህዝብ ስም ምን ይሰሩ እንደነበሩ ለምሳሌ ሱዳን እያለሁ በ1977 ዓ.ም. ላይ ኢትዮጵያ በከፍተኛ ድርቅ ተመታ ነበር። በዚህ ጊዜ ከትግራይ ወደ ግማሽ ሚልዮን የሚደርስ ህዝብ በ"ሕ.ወ.ሓ.ት" ታጋዮች ተገደው ወደ ሱዳን እንዲሰደዱ ተደረገ። በሱዳን ህዝቡን የተቀበሉት የ"ሕወሓት" የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ አራማጆች ስደተኞቹን ለሁለት ጥቅም አዋሉዋቸው።።.....

".....አንደኛ ለዓለም አቀፉ ህብረሰተብ "ህዝቡ መንግስትን ከመጥላቱ የተነሳ ስለተሰደደ ሁሉም አገሮች ግፊት አድርገውበት የደርግ መንበረ ስልጣን እንዲገረሰስ ይደረግ ሲል፤ በሌላ በኩል በስደተኞች ስም ከዓለም ዙሪያ የሚሰባሰቡትን የእርዳታ ምግብ መድኃኒት ልብሶችና የመጠለያ ቁሳቁሶች በቀጥታ ለሱዳን ህዝብ ይቸበችቡት ነበር። እዛ ያሉት የትግራይ ተወላጆች ግን..... እናትና ልጅ አንድ ላይ ሆነው ኑሮን ለማሸነፍ ለሽርሙጥና ስራ እስከመዳረግ በቅተዋል።"

በርሔ በእልህ እየተወራጨ ቀጠለ ".....እነሱ ግን በዛ ህዝብ ስም በሚልዮን ዶላር የሚቆጠር ገንዘብ አፈሱበት። ስደተኛው ግን በረሃብ ተረፈረፈ። እንደዛ አድርገው ባገኙት ገንዘብ ሌላ ፓርቲ መሰረቱ።"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“ምን የሚል?”
“ “ማርክሳዊ ሌኒናዊ ሊግ ትግራይ” በምህፃር “ማሌሊት” የሚባል፡፡”
“መቼ ነው የተመሰረተው?”
“በዛው ዓመት..... ሰኔ ሶስት 1977 ዓ.ም. ወረኢ የተባለ ቦታ ላይ”
“ሌላ ፖሊሲ ይዘው ነው “ማሌሊት”ን የመሰረቱት?”
“ታጋዩንና የኢትዮጵያን ህዝብ ለማደናገር ነው፡፡ ሽፋኑ “የአልባኒያ ሶሻሊስት በሆነ ርዕዮት ለኢትዮጵያ አንድነት እና እኩልነት የሚታገል አቋም ነው ያለው” ቢሉም የ”1968 ማኒፌስቶ”ን የሚያስተገብር ነበር፡፡”
“ለምንድነው በየወቅቱ የፓርቲያቸውን ስም የሚለዋውጡት”

“አንደኛ ቅድም እንዳልኩሽ ለውጪ መንግስታት በአገሪቷ ወስጥ ብዙ ተቃዋሚ ያለ ለማስመሰል ሲሆን፤ ሁለተኛ ህዝቡን ለማደናገር ነው፡፡ አንዳንዴ “ሕወሓት ማሌሊት” እየተባለ ይጠራል፡፡ “ሕ.ወ.ሓ.ት” እንደ አንድ መንግስት ሲሆን “ማሌሊት” ደግሞ እንደ አንድ ኮሚኒስት ፓርቲ ሆኖ ግንባሩን ይመራል፡፡ በኘሮግራም ደረጃ ሁለቱም አንድ ናቸው፡፡ በውጪ ግን ሁለት የተለያዩ ፓርቲዎች መስለው ይታያሉ፡፡.....

“.....በቃ “ጀብሐ” “ሻዕቢያን” ወለደ፡፡ “ሻዕቢያም” “ሕ.ወ.ሓ.ትን” “ማሌሊትን” ወለደ፡፡ “ሕ.ወ.ሓ.ት” ደግሞ በመሀከሉ የአሁኑን “ብአዴን”ን በበፊት ስሙ “ኢሕዲን” ብሎ ወለደው፡፡ የ”ኢሕዲን” የአመራር ሰዎች አማርኛ ተናጋሪዎች ናቸው፡፡ ይህ የተደረገው ለዘዴ ነው፡፡ ትግሉ በአማራውም የሚደገፍ ነው ለማስባል ነበር፡፡ “ኢሕዲን” ለኢትዮጵያ አንድነት ታጋይ ነኝ ይበል እንጂ የኤርትራን ብቻ ሳይሆን የትግራይንም መገንጠል ዛሬም ድረስ ይደግፋል፡፡ በአጭሩ “ኢሕዲን” የ”ሕወሓት” አማርኛ ክፍሉ ነበር ብሎ ማስቀመጡ ይቀላል፡፡.....
“.....በአጠቃላይ “1968 ማኒፌስቶ” እስኪተገበር ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን ብሔረሰቦች መለያየት የሚል እንቀፅ አለው፡፡ ለምሳሌ አሁን የትምህርትና የስራ እንቅስቃሴ እያንዳንዱ ክልል ላይ በየራሱ ቋንቋ ይሰጥ መባሉ አንዱ አላማውን መምቻ መሳሪያ ነው፡፡ ሌላው

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ኢትዮጵያ የሶስት ሺህ ሳይሆን የመቶ ዓመት ታሪክ እንዳላት መስበክ የመሳሰሉትን ያጠቃለለ ነበር።"

" "ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ." የተባለውስ ለምንድነው?"
"ይህን ስያሜ ያመጡት ደርግን ሊገረስሱ ጥቂት ዓመት ሲቀራቸው ነው። አጠቃላይ የኢትዮጵያን ህዝብ ያማከለ ፓርቲ ነው ለማለት ነው። በስሩ አሁን "እህት የፖለቲካ ድርጅቶች" የሚላቸውን አቅፎ የያዘ ነው ግን አመራሩና ፖሊሲው "ሻዕቢያ" የነደፈውና "ሕ.ወ.ሓ.ት" ይበልጥ አጠናክሮ ያረቀቀው ነው።"
"እሺ..... እስኪ ደግሞ ወደ ሌላ ጥያቄ ልመለስ?"

"ምንድነው?"
"አሁን ኤርትራ ከኢትዮጵያ ተገንጥላለች። ያኔ ስትገነጠል የኔ ናቸው ያላለቻቸውንና አልተካለሉልኝም ያለቻቸውን የትግራይ መሬቶች ወርራ በመያዝ በጦርነት ነው የለቀቀችው። የዚህ ታሪክ መነሻ መቼ እንደሆነ ታውቀዋለህ?"
"በደንብ አድርጌ ነዋ..... በ1969 ዓ.ም. "ሻዕቢያ" የመሬት ይገባኛል ጥያቄን አንስቶ ነበር። ለነገሩ "ጀብሐ"ም አንስቷል። ሆኖም ግን ስለተመታ በጣም ተዳክሞ ስለነበረ አጥብቆ ሳይገፋበት አቆመ.....
"ጥያቄው ሲነሳ ከትግራይ ውስጥ ከባድመ አንስቶ ደደቢትን፣ ጓል ደደቢትን፣ ወሀደን፣ እስከ መንጠብጠብ ያለውን ይይዛል። ወደ ላይ ሲመጣ ደግሞ አዲ አገራይ፣ አዲ ነበረኢ፣ አዲ ቋላ፣ አዲ ዳውሮን ሲሆን ቀጥሎ የጭላ ነው። አልፎ ደግሞ አሳዬ የሚባል ወረዳ አለ። እገላ የሚባል ሌላ በአንጪቾ ወረዳ የሚገኝ ነው። እነዚህ ደግሞ በዓድዋ አውራጃ ውስጥ ያሉ ናቸው። እሱን አልፎ ወደ ዛላ አምበሳ ይሄዳል። በአጋሜ አውራጃ የሚገኝ ነው።ሁሉም የተያያዙ ናቸው። እነዚህ በ"ሻዕቢያ" በኩል የኤርትራ ስለሆኑ የይገቡናል ጥያቄ ቀረበባቸው።....."

ቀጠለ በቁጭት "....በዛን ጊዜ ለድርድር የተጠሩት ከ"ሕ.ወ.ሓ.ት" መለስ ዜናዊና አባይ ፀሐዬ ነበሩ። ከ"ሻዕቢያ" ደግሞ ወዲ ኤፍሬምና

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ጴጥሮስ ሰለሞን ተገኙ፡፡ እነመለስ በድረድሩ ላይ "ይህ ቦታ በታሪክ የኤርትራ አካል መሆኑን ደርሰንበታል" ብለው አመኑ፡፡"

ሰናይት አቋረጠችውና "ታሪክ ግን የኤርትራ መሆኑን ይናገራል?"
"ሃሰት ነው..... ሃሰት ነው፡፡ ሊሰጧቸው ስለፈለጉ እንጂ፡፡ ስምምነቱ አበቃ፡፡ "ሻዕቢያ"ም ቦታውን እንዴት እንደምትቀበላቸው ጠየቀች፡፡ እነሱም "አሁን ይህን መሬት ቆርሰን ለኤርትራ ብንሰጥ ጠቅላላ የትግራይ ህዝብ ተነስቶ ይደመስሰናል፡፡ ስለዚህ ተፈራርመን እንቆይ በተባባሉት መሰረት ውሉ በፊርማቸው ፀና "ሻዕቢያ"ም ከድል በኋላ እንድትሰጣቸው ስትጠይቅ የ"ሕ.ወ.ሓ.ት" ቆይ የሚል ምላሿ አላበቃ ስላለ በወረራ ለመውሰድ ሞከረች፡፡"
"ለምን ነበር የ"ሕወሓት" ሰዎች እንዲቆይ የሚፈልጉበት ምክንያት?"

"የደርግ መንግስት በወደቀ ማግስት ኤርትራ ከአማራው መንግስት ቅኝ ግዛት ነፃ ትወጣለች፡፡ ትግራይም በሒደት የራሷን መንግስት ስትመሰርት ጥያቄው በተግባር ይጠናቀቃል" የሚል ውል ስለነበረበት ነው፡፡"
"ትግራይ ከኢትዮጵያ ብትገነጠል ግን በራሷ ነው የምትቆመው?"
"የኛ የግል ኘሮግራም እሱ ነው፡፡ የነመለስ ዜናዊ ፍላጐት ግን "ትግራይስ ከኢትዮጵያ ከተገነጠለች በኋላ በፌዴሬሽን ከኤርትራ ጋር ተዋህዳ አንድ ትሆናለች፡፡" የሚል ነው፡፡"
"ትግራይስ ከኢትዮጵያ ስትገነጠል የራሷን ክልል ይዛ ነው?"

"አይደለም..... "ሕወሓት" የነደፈው አንድ ካርታ አለ፡፡ እሱን ካርታ የኛም የትግል ሰዎች ግዛትን የሚያስፋፋ ስለሆነ ይደግፉታል፡፡"
"ልታብራራልኝ ትችላለህ?"
"አዎ..... ከጐንደር ከወሎና ከአፋር ክልል የሚወሰዱ መሬቶች አሉ፡፡ ለነገሩ ከአፋር የሚወሰደው አሰብ ከኤርትራ ጋር አብሮ ስለተገነጠለ ወደፊት ትግራይ ነፃ ስትወጣ በድርድር ወደኛ እንዲመለስ እናስደርጋለን፡፡"
"ከጐንደርና ከወሎስ?"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“ከጐንደር ሰቲት ሁመራን፣ ጠለምትን፣ ወልቃይትን፣ ጠገዴን፡፡ ከወሎ ራያና ቆቦ እስከ አሸንጌ ድረስ ያለውን በትግራይ ካርታ ስር አስገብተውታል፡፡ ይህን መሬት በ”ሕ.ወ.ሓ.ት” ሆነ በኛ “ትግራይ ትግሪኝ” በማለት እንጠራዋለን፡፡”
“ተፈፃሚ ይሆናል ብለህ ትገምታለህ?”
“የመስዋዕትነት ጉዳይ ነው፡፡ “ሕወሓት”ም እኛም እንደ ፖሊስ የሚተገበር ብለን ይዘነዋል፡፡” አለ በርሔ፡፡
“እኔም አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ ለመስጠት ፈቃደኛ ነኝ” አለችው እርግጠኛ በሆነ ስሜት፡፡
“በደስታ እንቀበላለን፡፡”
“ ለመሆኑ የውስጥ ሰዎች አሉህ? ” በጥያቄዋ ግራ መጋባቱን አየችና “ማለት የህ.ወ.ሓ.ት አባል ሆኖ በሚስጥር ለአንተ የሚሰራ?”
“ አዎና..... በርካታ ሚስጥም የምናገኘው በነሱ በኩል ነው....” አለና እየሳቀ “ ለነገሩ ከህ.ወ.ሓ.ት ሚስጥር ለማግኘት ምንም የረቀቀ ጥበብ ወይም ስለላ አያስፈልግም፡፡ ”
“እንዴት? ”
“ቦቃ..... የሆነ ነገር ሲጠየቁ የተጠየቁትን በትክክል ከመመለስ ይልቅ የልባቸውን ሀሳብና የፓርቲውን ሚስጥር በአደባባይና በሚዲያው ዞርግፈውት ቁጭ ይላሉ፡፡ ምን አለፋሽ እንደተበሳ ቅል ማለነት ናቸው፡፡ ለሰላምታ አፋቸውን ከከፈቱ ድብቅ ዓላማቸውን የሚያጋልጥ አንድ ሁለት ሚስጥር ሳያንጠባጥቡ ከንፈራቸውን መልሰው መዝጋት አይችሉም»» አለ እየተሳለቀ፡፡
ሰናይት ጋዜጣ አሳታሚ ሆና በሰራችባቸው ወቅቶች ውስጥ በተለይ የፓርቲው ከፍተኛ አመራሮች ይህንን ስህተት በተደጋጋሚ ሲፈፅሙት እንደኖሩ በልቧ አስታወሰች፡፡ ለሱ ግን ምንም እንደማታውቅ መስላ ጥቂት ሚስጥሮችን እንዲነግራት በማሰብ “ እነማንን? ” አለችው

“ቧ..... ሁሉም ያው ናቸው፡፡ ለምሳሌ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አንዴ ለተጠየቀው ጥያቄ በቀጥታ መልስ መመለስ እየቻለ ህ.ወ.ሓ.ት ስለዚህ አገር ጉዳይ በድብቅ ያስቀመጠውን ውሳኔ በአደባባይ « ኢትዮጵያም ራሷ በሂደት የምትፈረካከስበት » በማለት ከጥያቄው ጋር ምንም ተያያዥነት የሌለው መልኩ ተናግሯል፡፡ በዚህ መልኩ አምልጦ የወጣው ሚስጥር በአስቀመጡት ስሌት መሰረት ኢትዮጵያን በሂደት የመፈረካከስ ግብ እንዳላቸው ያጋለጠ ነበር፡፡ ይህንን እቅዳቸውን በተጠናከረ መልኩ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

እንደሚቀጥሉ አንዴም እንዲህ በማለት ገልፆት ነበር...” ብሎ እያስታወሰ መናገር ቀጠለ “...የትግራይ አክሱም ለደቡብ ህዝብ ምኑ ነው!? የአገው ላሊበላ ለኦሮሞ ወይም የፋሲል ቤተ-መንግስት ለወላይታ ምኑ ነው?! በማለት አንዱ ከሌላው ምንም ትስስር እንደሌለው ተናግሯል። የዚህ ንግግር ፅንሰ ሀሳቡ አንዱ ከሌላው ህብረትና አንድነት የለውም ለማለት ሳይሆን ሁሉም መበታተን አለበት የሚለውን መልዕክት ለማስተላለፍ ሆን ተብሎ የታለመ ነበር። አንዴም ገና ስልጣን በያዙ ሰሞን ለንደን በተደረገ ስብሰባ ላይ ከዚህ በኋላ ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ. የሚባል መንግስት የለም ሕ.ወ.ሓ.ት እንጂ ብሎ ሌሎች ፓርቲዎች ባሉበት በግልፅ ተናግሯል። እንዳለውም ይኸው የአገሪቷን ስልጣን ለብቻ ጠቅልለው በመያዝ እንደሚመሯትም እያየን ነው። ”

ሰናይት የዚህን ቅያቄ ቃለ መጠይቅ ምን ላይ እንዳነበበችው ወይም እንደሰማችው ትዝ አይበላት እንጂ ተከታትላው እንደነበር አስታወሰች። በወቅቱ በርካታ ህዝብንና የአገሪቷን አንድ መሆን በሚደግፉ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ቁጣ ያስነሳ ቢሆንም ሁኔታው በተለያዩ የአፈናና ህገ ወጥ መንግታዊ እርምጃዎች ተዳፍኖ እንዲቀር እንደተደረገ አስታወሰች።

ቀጠለ በርሔ “..... በተለይ የአቦይ ስብሐትን ኢንተቪዎች ብትከታተይ የህ.ወ.ሓ.ትን ዓላማና ግብ ለማወቅ ምንም ተጨማሪ ጥረት አያስፈልግም” አላት።

ሁለቱም በየራሳቸው ሲያስቡ ቆዩና “ይህን ጊዜ የ”ሕ.ወ.ሓ.ት” ባለስልጣናት ይህ ሁሉ ሚስጥራቸው የማይታወቅ ይመስላቸው ይሆን?” ጠየቀች ሰናይት።

“ታዲያስ!” በርሔ በጠንካራ ቃላት ቀጠለ “በዚህ ምድር ላይ የተደረገ ነገር ሁሉ ጊዜና ሁኔታን ይጠብቃል እንጂ ገሀድ መውጣቱ አይቀርም..... አዎ..... እውነታዎች ያንቀላፉ እንደሆን እንጂ አይሞቱም!” አለ።

  

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ምዕራፍ 23

የኢትዮጵያ ትኩሳት ከዕለት ወደ ዕለት እየተባባሰ ሄዷል። በተለይ የ94 ዓ.ም. ሁለተኛ ግማሽ ዓመት አስጊ ሁኔታዎች እያገጠጡ መውጣት ጀምረዋል። በአገሪቷ የሚታተሙት የግል ጋዜጦች በጠቅላላ ይህንኑ እውነታ ነው በመጀመሪያ ገፆቻቸው ላይ በጉልህ ፊደላት የሚያትሙት።

መንግስት ግን እየተፈጠሩ ያሉትን ችግሮች እያድበሰበሰ በማለፍ ነጋ ጠባ ሁኔታዎች ሰላም መሆናቸውን፤ በልማት ስራ ተጠምዶ የማረፊያ ፋታ ያጣ መሆኑን ፤ አገሪቷ ፈጣን ወደ ሆነ የእድገት እርከን እየተሸጋገረች መሆኑን..... አሳትሞ በሚያሰራጫቸው ጋዜጦች፤ መፅሔቶች፤ እንዲሁም በሬዲዮና ቴሌቪዥን ይወተውታል። በሌላ በኩል ደግሞ የራሱን ቡድን የሆኑ የቅስቀሳ ስራዎቹን የሚቃረኑ ነገሮችን ሲያትት ይታያል።

ከነሱም መሀከል "ወቅታዊ ሪፖርት" መሰል ዝግጅቶችን በቴሌቪዥንና በሬዲዮ እያዘጋጀ ከሃያና ሃምሳ መቶ ዓመታት በፊት የተከወኑ ነገሮችን እያነሳና አንዱን ከሌላው እያማታ ሲያቀርብ ችሎት መሀከል ገብቶ የሚዘላብድ ወፈፌ ወንጀለኛ ይመስላል።

በሌላም በኩል ነጋ ጠባ በየመስራቤቱ የሚታየውና ወደ ውጤት የማያመራ የስብሰባ፣ የግምገማ፣ የተሀድሶ ሲገፋም በየወሩ የሚካሔደውም ሹም ሽር ገዢው ፓርቲ በጭንቀት የተዋጠ መሆኑ ለማንም ታዛቢ ፍንትው ብሎ ይታያል።

የወቅቱ የሽብር ችግር ደግሞ ከመሀከል ከተሞች ይልቅ በክልሎች ላይ እጅግ አስደንጋጭ በሆነ ሁኔታ ተባብሶዋል። ህዝቡ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

በያለበት እርስ በራሱ ይናጣል። ወደ ምን ውጤት እየተጠጋ እንዳለ ግን አያውቀውም።

በአራቱም ማዕዘናት ያሉት ዘጠኙ የሉዊስ የስለላ ሰዎች በቀን ሶስትና አራት ጊዜ አዲስ አበባ ለሚገኘው አለረኛ ሰው መረጃዎችን እያሻገሩለት ይገኛሉ።

በተለይ በምዕራቡ ኢትዮጵያ ከአምቦ ከተማ አንስቶ አጠቃላይ ወለጋን በመያዝ አሶሳ ድረስ ከፍተኛ የፖለቲካ ውጥረት እንደነገሰ ነው የሚጠቁሙት። የተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች እንዲሁም ህዝቡ አንድ ላይ በመወገን ከመንግስት አካላቶች ጋር መጋጨት ቋሚ ተግባራቸው እየሆነ ሄዷል። ትምህርት ቤቶችና መስሪያ ቤቶችን አገልግሎት መስጠት እስከማቆም ድረስ ተገደዋል።

በሚካሄዱበት የተኩስ ልውውጦች ከህዝቡም ሆነ ከመንግስት ወገን ዕለት ዕለት ሰዎች እየተሰዉ ይገኛሉ።

ግጭቱ ገኖ የታየው በዛ ይሁን እንጂ በባሌ፣ አርሲ፣ ሀረርና ጅማም እየተስፋፋ ነው ያለው።

በደቡብ ክልሎች ላይም ሁከት መበራከት ጀምረዋል። የመንግስት ሀይሎች ግን ችግሩን አፍነው ለማስቀረት ሲሉ ኢ-ሰብአዊ በሆነ መልኩ ህዝቡን እየጨፈጨፉ እያሰሩና እየገደሉ መሆናቸው መረጃው ለ"ሉዊስ ወኪሎች" ድርጅት በየዕለቱ ይደርሱታል።

በሶማሌ ጠረፍ አካባቢም የተቃዋሚ ድርጅቶች በእንገንጠል አቋማቸው እየፀኑ ሄደዋል።

ትግራይም አድራሻው ባልታወቀ ፓርቲ በየ ማለዳው ላይ የቅስቀሳ ወረቀቶች የከተማውና የገጠሩ መንደሮች ውስጥ ተበትነው ይገኛሉ።

ባጠቃላይ ዙሪያ ገባ ያለው የኢትዮጵያ ህዝብ ማስተንፈሻ በሌለው ድስት ውስጥ እንደሚንተከተክ ውሃ ሆኗል። አንድ ዕለት ሲፈነዳ ግን ምን ሊፈጥር እንደሚችል ማንም አያውቀውም።

የፒየር ሰዎችም ይህኑ መረጃ ነበር የሚያስተላልፉት። በተለይ የአዲስ አበባው ሰው ስራው ከአቅሙ በላይ እየሆነበት ሄዷል።

ይህ ሁሉ ሲሆን ግን በመዲናዋ አዲስ አበባ ያለው ህዝብ የመከፋፈል ስሜትን አላሳየም። "ህበሻ" የሚለው ስያሜና "ድብልቅ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ህዝብ" የሚል ትርጓሜ ያለው የ"አረንጓዴ ቢጫ ቀይ" የአንድነትና የትብብር ኢትዮጵያዊነት እሴት አሁንም እንዳለ ነው ማለት ይችላል፡፡

ይህም ቢሆን ግን አልፎ አልፎ አንዳንድ ከክፍለ ሀገር የመጡና ከገዢው መንግስት ለሚያገኙት ጥቅም ተሸጠው "ጠባብ ብሔርተኝነት" የተዋህዳቸው ወይም ያልዳበረ ንቃት ያላቸው ግለሰቦች ካልሆኑ በስተቀር ይህ "ትግሬ ነው፣ ይህ አማራ ነው፣ ይህ ኦሮሞ ነው፣ ይህ ሲዳሞ፣ ይህ ስልጤ ....." የሚለው ከፋፋይ ሀሳብ ፈፅሞ ሲነሳ አይታይም፡፡ ሁሉም በአንድነት የዕለት ኑሮውን ለማሸነፍ ሲታትር ይውላል፡፡ ያገኛትንም አንዱን ከሌላው ሳይለይ እኩል ተካፍሎ በመጠቀም ተመስገን ብሎ ያድራል፡፡

ይህን ለዘመናት የኖረና የስንት ትውልድ የህይወት ዋጋ የተከፈለበት የአንድነት ስሜት ነው በተለይ ከ1983 ዓ.ም. አጋማሽ ጀምሮ የ"ሕ.ወ.ሓ.ት." ፓርቲ በትረ ስልጣኑን ሲጨብጥ ከመላው ኢትዮጵያ ምድር ላይ እንዲፋቅ መጣር የጀመረው፡፡ ምክንያቱም የ"1968 ማኒፌስቶ" በሚለው ስምምነታቸው ውስጥ የ"ሕ.ወ.ሓ.ት." እና የ"ሻእቢያ" የወቅቱ ከፍተኛ ባለስልጣናት በሱዳን ካርቱም ከተማ በጥብቅ ሚስጥር ተሰብስበው ካፀደቁዋቸው አስር ዋና ዋና ተተግባሪ ዓላማዎች መካከል፦

«-ኤርትራን ከኢትዮጵያ ማስገንጠል»
«-ትግራይንም ከኢትዮጵያ በሂደት ማስገንጠል እና በፌደሬሽን ከኤርትራ ጋር መቀላቀል»
«-የኢትዮጵያ ብሔር-ብሔረሰቦች ከኢትዮጵያ ተገንጥለው የራሳቸውን መንግስት እንዲመሰርቱ ማድረግ»

የሚሉትና ከላይ ያሉት ስምምነቶች ተፈፃሚ ሆነው ኢትዮጵያ ብትንትኗ እንዲወጣ ህጋዊ የሚያስመስል ሽፋን ለመስጠት ደግሞ በኢትዮጵያ ህገ-መንግስት ውስጥ፦

«-የራስን መብት በራስ መወሰን እስከመገንጠል» የሚል በዋናነት የሰፈሩ አደገኛ ግብ እንዳላቸው ሉዊስ ማወቁ ነበር፡፡

የ"ሉዊስ ወኪሎች" ድርጅትም ከእንግሊዝ የስለላ ተቋም አሰርቆ ያስመጣውን ዋናውን እቅድ በየትኛው የአፍሪካ አገር ላይ ማስተግበር እንደሚችል ጥናት ሲያደርግ የኢትዮጵያን ያህል የተመቻቸ ፖሊሲና ማኒፌስቶ እንዲሁም ህገ መንግስት ያለው አገር ሊያገኝ አልቻለም፡፡ ይህ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

እንደ ገሞራ እየታመሰ ያለው ዕቶን ደግሞ ከዳር ክልሎች ጀምሮ በመዲናዋ ላይ ጭምር እንዲፈነዳ ይፈልጋል። ያን ጊዜ ግቡ ካለ ጥርጥር የሚሰምር ይሆናልና።

«««««« »»»»»»

ሰናይት "የኦሮሞ አርበኞች ንቅናቄ" የበላይ አራማጅ ከሆነው ከሂርጳ ጋር በያዘችው ቀጠሮ መሰረት ቤቱ ሔዳ ተገናኘችው።

ሚያዝያ ከገባ ሁለት ቀን ሞላው። ዕለቱ ረቡዕ ነው። ማለዳ ላይ ፍንትው ብላ የነበችው ፀሀይ ሊረፋድ ሲል በደመና ተጋረደች። ወዲያም እንደ ማካፋት ጀማመረ።

"አቦ ሂርጳ እንደምን ሰነበትክ?" ፊቷ ብሩህ በሆነ ፈገግታ እንደተዋጠ ሰላምታ ሰጠችው።

"እግዚያብሔር ይመስገን....." ወደ ሳሎን ይዟት ገባ። "ትግል እንዴት ነው?"

"እንደምታይው ነዋ..... መንግስት ገና ካሁኑ መሸናት ጀምሯል" አለ ቀጠለ ".....አሁን በትኩሱ ሁሉንም ነገር ማፋፋም ነው..... ህዝቡም እያገዘን ነው ያለው።"

"ታዲያ ለምን አትገፋበትም?"

"መሳሪያ እየጠበቅን ነዋ..... አሁን በእጃችን ላይ በቂ መሳሪያ የለም እንጂ የግምባር ውጊያ መጀመር እንችል ነበር....."

"በቂ የሰው ኃይል ማግኘት ችላችኋል?"

"አዎ....."

"ጥሩ ጥያቄያችሁን በፍጥነት አስተላልፋለሁኝ..... እስከዛ ግን የሰዎቻችሁ ሞራል እንዳይወድቅ የፖለቲካ ቅስቀሳና እንቅስቃሴያችሁ መዳከም የለበትም።"

"እሱንማ ከወያኔ የወረስነው ልምድ ነው።" አለ ሂርጳ ጥቂት ሲያስበ ቆየናም "በሚመጣው ሳምንት እዚህ አዲስ አበባ ውስጥ በአማራ ከፍተኛ ባለስልጣናቶች ላይ ትልቅ ጥቃት ለመሰንዘር አቅደናል።"

"ምን ዓይነት ጥቃት ነው!?" ጐላ ባለ ድምፅ ጠየቀችው።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“እንደደረስን መረጃ ህወሐት እህት ድርጅት እያለ የሚያላግጥበትና እንደ ጭቃ አቡክቶ ረግጦና ለጣጥፎ የሰራው የ “ብ.አ.ዴ.ን.” አስረኛ ዓመት በዓሉን አስታኮ የፓርቲውን ውስጣዊ መዋቅር ይበልጥ ለማደራጀት ገቢ ማሰባሰቢያ ቴሌቶን ሊያዘጋጅ አቅዷል፡፡”
“የት?”
“እዚሁ አዲስ አበባ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት አዳራሽ ውስጥ”
“ለምንድነው በሆቴል ወይም መሰል አዳራሾች ያላዘጋጀው?”
“ሚስጥራዊ እቅድ ስለሆነ ነው፡፡ በቴሌቶኑ ላይ እርዳታውን የሚሰጡት በአብዛኛው “ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ.” ጃንጥላ ስር የተቋቋሙት እህት ፓርቲዎች ሲሆኑ ጥሩ ድጋፍ ሊያደርጉ ይችላሉ የተባሉ ጥቂት የአገሪቷ ባለሀብቶችና በውጭ አገር የሚገኙ “ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ.”ን የሚደግፉ ግለሰቦች ብቻ ናቸው እንዲገኙ የተጋበዙት፡፡ ምንም ዓይነት የመገናኛ ብዙሀንም እንዳይገኙ ታዟል፡፡”
“እንዴት ልትደርሱበት ቻላችሁ?” ሰናይት ጠየቀች፡፡
“አዳራሹ የሚገኝበት መስራቤት የሚሰራ ሰዋችን ነው መረጃውን የሰጠን፡፡”
“ከ “ብ.አ.ዴ.ን.” እነማን ይገኛሉ ተብሎ ይጠበቃል?”
“የበላይ ባለስልጣናቶች በጠቅላላ..... የሌሎችም ፓርቲ መሪዎች እና አገሪቷን በሚኒስትር ደረጃ እያስተዳደሩባት የሚገኙ ጠላቶቻችን” አለ ሂርጳ ጥርሱን ነክሶ፡፡
“ጥቃት የመሰንዘር እቅዳችሁ እንደሚሳካ ሙሉ እምነት አለህ?”
“አዎ..... በጥንቃቄ ተዘጋጅተንበታል፡፡”
ሰናይት በሀሳብ ተዋጠችና እቅዱ ቢተገበር ሊያስከትል የሚችለው ለውጥ ምን እንደሚሆን ለመገመት ሞከረች፡፡ ከፍተኛ ሽብር በአገሪቷ ላይ እንደሚነግስ ገብቷታል፡፡ የሚፈጠረው ሽብር ግን ህዝብና መንግስትን ከማስደንገጥ የዘለለ ሌላ ጥቅም ማስተከል መቻሉን ልታምንበት አልቻለችም፡፡
በኋላ ላይ አንድ የሙከራ ሀሳብ ፍንትው አለላት፡፡ በአማራው ክልል ላይ የነሱን እቅድ የሚያስፈፅምላት አቅም ያለው ሰው እስካሁን እንዳላገኘች አሰበች፡፡ ‘በዚህ ቴሌቶን ላይ እኔ መጠቀም ይገባኛል’

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

አለች ለራሷ፡፡ ስለዚህ የነሂርጳ እቅድ መሰረዝ አለበት፡፡ ግን እንዴት አድርጋ ነው የምታሳምነው?

ሌሎች ደቂቃዎች አለፉ፡፡ ከዛም "ፈፅሞ ትክክል አይደለም እቅዳችሁ!" ከቁጣ ባልተናነሰ ድምፀት ሂርጳን አተኩራ እያየችው ተናገረ፡፡

"ለምን?" ጥቂት እንደመደንገጥ ብሎ ጠየቀው፡፡

ከፍተኛ የሆነ ድጐማ እያደረገችላቸው በመሆኑ አንዳንዴም በትዕዛዟ እቅዶችን ማስረዘም ሆነ ማስነደፍ የምትችል መሆኑን አሰበችና "እቅዱ ለነፃነት የሚታገል አንድን ፓርቲ የሚወክል ሳይሆን በአሸባሪነት ላይ የተሰማራ ተራ የውንብድና ስራ ነው !" አለች

ቀጠለች "..... ይህን ጥቃት ብትሰነዝሩ ብዙ በጐ ነገሮችን ታጣላችሁ፡፡"

"ለምሳሌ ምንን?" ሂርጳ አሁንም ግራ እንደተጋባ ጠየቀ፡፡

"አየህ..... እርዳታ ሊያደርጉላችሁ የተነሱት የውጭ መንግስታቶች ሁሉ እቅዱን አይደግፉትም፡፡ ፊታቸውን ሊያዞሩባችሁ ይችላሉ፡፡ በአለም አቀፉ ህብረተሰብ ልትወገዙና እንደ ወንጀለኛም ልትቆጠሩ ትችላላችሁ፡፡..... የአሜሪካ ምክር ቤት አባሎች በስብሰባ ላይ እንዳሉ ማንም ተራ ወምበዴ ድምጥማጣቸውን ሊያጠፋቸው ይችላል፡፡ ከሚያገኘው ውጤት ይልቅ ግን የሚደርስበት የፖለቲካ ክስረት ይበልጣል፡፡ የናንተም የአሁኑ እቅድ ከዚህ ጋር የሚመሳሰል ነው፡፡ እናንተ የነፃነት ታጋይ ናችሁ እንጂ አሸባሪዎች አይደላችሁም፡፡ በስንት መከራና መስዋዕትነት እዚህ ያደረሳችሁት ፓርቲያችሁን ባንዲት ስህተት ፍርስርሱ እንዳይወጣ ይህንን ሀሳብ እንድትሰርዙት ነው የማስጠነቅቀው" አለችው፡፡

ረዥም ሰዓት ተነጋገሩበት፡፡ መጨረሻ ላይ ሂርጳ ተነስቶ ወደ ስልኩ አመራና በከሰዓቱ ክፍለ ጊዜ ጥቃቱን እንዲያስፈፅም ከተዋቀሩት አባላቶቹ ጋር ተገናኝቶ በድጋሜ ለመወያየት ቀጠሮ ያዘ፡፡

««««««« »»»»»»»

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ሰናይትም የዛኑ ዕለት ምሽት ላይ "ደ.ሀ.ዴ.ግ."ን ወክሎ የምክር ቤት አባል ከሆነውና በድብቅ ግን "ህዝበ ደቡብ ነፃነት ሀይል" በምህፃር "ህ.ደ.ነ.ሀ." ታማኝ አገልጋይ ከሆነው ጳውሎስ ኩንቴ ጋር ለመገናኘት በተነጋገሩት መሰረት ወሎ ሰፈር አካባቢ ወደሚገኘው ቤቱ አመራች፡፡

ስትደርስ ጳውሎስ ሁለት ልጆቹን እያስጠናቸው ነበረ፡፡ ሞቅ ያለ ሰላምታ ተለዋወጡና ልጆቹን "ለዛሬ በቃችሁ..... ወደዛ ጋር ሂዳችሁ ደብተሮቻችሁን ሰብስቡ" አላቸው፡፡ ከሶፋው ፈንጠር ብሎ በሚታየው ክፍት ቦታ እያመላከተ፡፡

ከዛም በተጣደፈ ስሜት "ቅድም በስልክ በጣም እንደምትፈልጊኝ ነግረሽኝ ነበር..... በሰላም ነው?"

"አዎ....." ተረጋግታ መለች፡፡

"ችግር የተፈጠረ መስሎኝ ተደናግጬ ነበር"

"አይ..... አንድ ነገር ሰማሁና እውነት መሆኑን ለማጣራት ፈልጌ ነው፡፡"

"ምንድነው?"

"በሚመጣው ሳምንት ውስጥ የሚካሔድ አንድ የድጋፍ ማሰባሰቢያ ቴሌቶን እየተዘጋጀ መሆኑን መረጃ ደርሶኝ ነበር....."

"የ "ብ.አ.ዴ.ን" ን ነው?"

"አዎ..... እውነት ነው ሰምተህል?"

"ሰምቻለሁ..... ታዲያ ምን ይጠቅምሻል?"

"አይ..... እንደው ቢቻል ገብቼ ሁኔታውን ማየት ፈልጌ ነው፡፡"

"ምንም ችግር የለም፡፡ የመግቢያ ወረቀት የምታገኝበትን መንገድ እኔ አመቻችልሻለሁ"

"እንተስ በዝግጅቱ ላይ ትሳተፋለህ?"

"እንደሱ ያሉ ዝግጅቶች ናቸው የሰለቹኝ፡፡"

"እና ልትቀር?"

"አዎ..... የምገኝ አይስለኝም፡፡"

"ግን ሚስጥራዊ ስለሆነ ማንንም ተጋባዥ ሰው ያስገባሉ?"

"ለእርዳታ ማሰባሰቡ ይጠቅማሉ ተብለው የሚገመቱ ማንም ቢሆኑ እንዲሳተፉ ጥሪ ይድረሳቸው ተብሏል፡፡ እንደውም አንዳንድ ባለ ሀብቶችን

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

በግድ እንዲሳተፉ ግፊት እያደረጉባቸው ነው። ስለዚህ አንቺም መሳተፍ ከፈለግሽ በዝግጅቱ ላይ መገኘት ትችያለሽ።"

ቀጠለ ጳውሎስ በተሰላቸ ስሜት "ሚስጥር የተባለው ቴሌቶኑ በመገናኛ ብዙሀን ለህዝብ እንዳይተላለፍ ስለተፈለገ ብቻ ነው።" ቀጠለ ".....ዝም ብለው ነው ከህዝብ ምንም መደበቅ አይቻልም።"

"ጥሩ ሀሳብ ነው"

ከሁለት ቀን በኋላ ሲገናኙ ጳውሎስ የስራ ወረቀቶችን ከሚይዝበት የቆዳ ቦርሳ ውስጥ አንድ የታሸገ ፖስታ አውጥቶ እየሰጣት " በክብር እንግድነት እንድትገኚ መጋበዝሽን የሚገልፅ ካርድ ነው "።

"ብከፍተውስ?"

"ትችያለሽ"

አውጥታ አየችው። ከተፃፉበት ነገሮች መካከል "በዕለቱ በአዳራሹ ተገኝተው ለ "ብ.አ.ዴ.ን" መሞልበት የአቅምዎን ያህል ድጋፍ እንዲያደርጉ በአክብሮት ተጠርተዋል። ከአዘጋጅ ኮሚቴው" የሚል ነበር።

"እሺ..... ሌላ ምን አዲስ ነገር አለ?" ካርዱን ወደ ፖስታው እየመለሰች ጠየቀች

"በጣም ብዙ አለ....." ብሎ ሌላ ወረቀት ከቦርሳው አወጣና "ቅድም ነው የደረሰኝ..... የጦር መሳሪያ በብዛት እንደሚያስፈልገን እዛ ባሉት ሰዎች ተጠይቀናል..... እንዲሁም ተጨማሪ ገንዘብ። ሁሉም በተፈለገው ፍጥነት ከተሟሉ በቀጥታ ወደ መገንጠሉ ጥያቄ ማምራት የምንችል መሆኑን ገልፀዋል።"

"በጣም ጥሩ..... መልሱን ቶሎ አሳውቅሀለው።" አለችውና ተሰነባብተው ተለያዩ።

  

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ምእራፍ 24

በሳምንቱ ረቡዕ ዕለት ልክ አስራ አንድ ሰዓት ሲሆን በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት በሚገኘው አዳራሽ ውስጥ "ብ.አ.ዴ.ን." ያዘጋጀው የእርዳታ ማሰባሰቢያ ቴሌቶን ተጀመረ።።

በኦሎምፒያና በፍላሚንጐ መሀከል ቦታ ላይ የሰፈረው የመስራቤቱ ልዩ ሀንፃ ከመቼውም በላቀ ሁኔታ እየተጠበቀ ነበር።። ታጣቂ ወታደሮችና ፖሊሶች በመኪናና በእግር ሆነው ዙሪያ ገባውን ያስሳሉ።።
"ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ." የመሰረታቸው በርካታ የፖለቲካ ድርጅት አባሎች፣ የአገሪቷ ባለሀበቶችና ከውጪ ጥሪው ደርሷቸው የመጡ ደጋፊ ግለሰቦች አዳራሹን ሞልተውታል።።

ዝግጅቱ ሲጀመር የፓርቲው ዋና ኘሬዝዳንት አጭር የመግቢያ ንግግር አደረጉ።። ከዛም መድረኩ ዝግጅቱን ለሚመራው ግለሰብ ተለቀቀና የቅስቀሳ ስራውን ጀመረ።።

ይህ ፓርቲዎችን በእርዳታ የማጠናከር ስራ በሁሉም የተለመደ ስለ ነበረ ብዙ ጉትጐታ አላስፈለገም።። "ሕ.ወ.ሓ.ት. አምስት ሚልዮን ብር ሰጥቷል" "ኦ.ህ.ድ.ድ. ሰባት ሚልዮን!....." በድምፅ ማጉያው የሚተላለፈው ንግግር ቀጠለ።። "ደ.ህ.ዴ.ግ. አስራ አንድ ሚልዮን!..... ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉና በመሀከላችን የሚገኙ አንድ ግለሰብ ሶስት ሚልዮን!....." በሰላሳ ደቂቃ ውስጥ ሰላሳ ሁለት ሚልዮን ብር ተገኘ።። ስሜቱ ግን ገና እንደተጋጋለ ነበር ያለው።።

አንድ ሰዓት ሲሞላው እየረገበ መሄድ ጀመረ።። ሰጪዎቹም ከሚልዮን ብር ወደ አስር ሺዎች መውረድ ጀመሩ።።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

ሰናይት ስትጠብቀው የቆየቸው ወቅት ይህች መሆኗን አስተዋለችና ከቦርሳዋ ቼክ አውጥታ በመፃፍ ለሰብሳቢው ሰጠው፡፡ ከደቂቃ በኋላ አዳራሹን በሚያናጋ ድምፅ "አንድ ደረሰኝ አሁን ደርሶኛል ..... ወይዘሪት ሰናይት ከተባሉ ግለሰብ ሁለት ሚልዮን የአሜሪካ ዶላር!"

አደራሹ በጭብጨባና በአድናቆት ቀለጠ፡፡ በግል ከተሰጡት እርዳታዎች ሁሉ የሚልቅ ክፍያ የሷ ነበር፡፡ የተሳታፊዎች እይታ በጠቅላላ ወደሷ ሲዞሩ አስተዋለች፡፡ ሁሉም በግል ከሷ ጋር ወዳጅነት ለመመስረት በአይናቸው ሲማፀኗት አስተዋለችባቸው፡፡ እሷም ይህንን ነበረና የምትፈልገው ለሁሉም ልብን በተስፋ የሚሞላ ውብ ፈገግታ ሰጠቻቸው፡፡

ከአስር ደቂቃ በኋላ አጭር ማስታወሻ የተፃፈባት ወረቀት ደረሰቻት፡፡ "የብ.አ.ዴ.ን ፓርቲ ዋና ኘሬዝዳንት መጨረሻ ላይ ሊያናግሩሽ ይፈልጋሉ፡፡

ከአክብሮት ጋር" ትላለች፡፡

ሁኔታዎች ባቀደችው አኳሀን ሄደዋል፡፡ አስራ ሁለት ሰዓት ተኩል ላይ ሁሉም ነገር ተጠናቀቀ፡፡ ሰው መበተን ሲጀምር ሰናይት ግን በሁለት ሰዎች ታጅባ ከአዳራሹ ወጣችና አጠገብ ወዳለችው ቢሮ በአጃቢዎቿ እየተመራች ደረሰች፡፡ በሩ አቅራቢያ ከነበሩት ጠባቂዎች መካከል አንዱ ተሸቀዳድሞ ከፈተላት፡፡

በሩን አልፈው ሲገቡ የ "ብ.አ.ዴ.ን." ባለስልጣናት ፊታቸው እንደ አደይ ፈክቶ ተቀበሏት፡፡ በዕለቱ ዘጠና ሶስት ሚልዮን ብር ማሰባሰብ የቻሉ ሲሆን ከግማሽ በላይ በጥሬ ገንዘብ ገብቶላቸው ነበር፡፡ ሁሉም ከወንበራቸው ተነስተው የአክብሮት ሰላምታ ሰጧት፡፡

ከምስጋና ውጪ ግን ስለ ማንነቷ ጥያቄ ሊያነሳላት የደፈረ አልነበረም፡፡ እሷም ሁኔታው ስለገባት ከፈረንሳይ በደረሳትው ጥሪ መሰረት በዚህ ቴሌቶን ላይ ተገኝታ ለፓርቲው ድጋፍ ማድረግ በመፈለጓ የመጣች መሆኗን ገለፀች፡፡ እንዲሁም ወደፊት በአማራው ክልል ላይ በከፍተኛ የልማት ስራ መሳተፍ እንደምትሻ አሳወቀች፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

የፓርቲው ኘሬዝዳንት በደስታ እንደሚያስተናግዷት ገልፀው "እግረ መንገድ ለግንዛቤ እንዲረዳሽ ለምን ክልላችንን አትጐበኝም?"
"ግብኖውን ተቀብያለሁ፡፡"
"የሚያኮራ ክልል አለን፡፡ ባህርዳርን በዚህ ዓመት ዩኒስኮ በዓለማችን ላይ ለመኖር አመቺና ተስማሚ ከሆኑ አገሮች መካከል አስረኛ አድርጐ መርጧታል" አሏት፡፡
"ሰምቻለሁ፡፡ በጣም ነው ደስ ያለኝ፡፡ ላያት ጓጉቻለሁ፡፡"
"ዝግጅትሽን ስታጠናቅቂ በዚህ ስልክ ደውይልኝ፡፡ ሁሉንም ነገር አመቻችተን እንጠብቅሻለን፡፡"

"አመሰግናለሁ" ብላ ቁጥሩን በመቀበል ተሰናብታቸው ወጣች፡፡ በእርግጥ በስብሰባው ላይ ተሳታፊ ከነበሩት የሕወሓት አመራሮች መካከል አንዳንዶቹ ሊቀርቧት ቢሞክሩም በነበረው ግርግር ምክንያት አልተሳካላቸውም፡፡ የተከራየችውን ዘመናዊ መርሰዲስ መኪና እያሽከረከረች ስትወጣም በርካቶች በአይናቸው ከመሸኘት ውጪ ምንም ማድረግ አልቻሉም፡፡ ከዕለቱ የምሽት ወሬ መካከል እሷ ዋናዋ ሆና ነበር፡፡

መኪናውን ለአከራዩ ድርጅት በመመለስ ሩዋንዳ አካባቢ ወደ ተከራየችው ቤት ነበር ያመራችው፡፡ ባህር ዳር መሄዷ የማይቀር ስለነበር የግድ አንድ እዚህ ሆኖ የሚረዳት ሰው ማዘጋጀት እንዳለበት እያሰበች አመሸች፡፡

አዲስ አበባ ውስጥ ግን አብሯት በመስራት የሚያግዛት ሰው ከአንድ በላይ ማንም ትዝ ሊላት አልቻለም፡፡ እሱም ጋዜጣ አሳታሚ በነበረችበት ወቅት በዋና አዘጋጅነት ተቀጥሮ ይሰራላት የነበረ አንድ ወጣት ብቻ ነበር፡፡ አማራጭ ስለሌላት ስልኩን አንስታ ወደ ወጣቱ ቤት ደወለች፡፡
መስመሩ ሲከፈት "መስፍን ይኖር ይሆን?"
"ይጠብቁ....." ወፍራም ድምፅ መለሰለት፡፡
"ሀሎ?....."
"መስፍን ነህ?"
"አዎ"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“ሰናይት ነኝ.....”
“ሰናይት!?”
“አዎ”
ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ “ዛሬ በምን ትዝ ብዬሽ ነው ከፈረንሳይ የደወልሽልኝ?”
“መጥቻለሁ። ያለሁት አዲስ አበባ ነው”
“እውነት?”
“አዎ.....ይልቅ እንዴት መገናኘት እንችላለን?”
“እ.....”
“ለመገባበዝ እንዳይመስልህ”
“ካልተጋበዝኩማ አልመጣም.....” እየሳቀ መለሰላት።
“እየቀለድኩ አይደለም..... ስራ ይዤልህ መጥቻለሁ።”
“ጋዜጣ አሳታሚዎች ስትባሉ ነገር ማግነን ትወዳላችሁ።”
“ግድ የለም የሚገባውን ያህል ያላጋነንኩት መሆኔን በኋላ ትረዳዋለህ”
“እሺ የት እንገናኝ?”
“ዋቢ ሸበሌ ሆቴል ጠዋት በሶስት ሰዓት።”

««««««« »»»»»»»

መስፍን ተወልዶ ያደገው በአዲስ አበባ ሲሆን ትምህርቱንም ከአዲስ አበባ የመገናኛ ብዙሀን በጋዜጠኝነት ሙያ በዲፕሎም አጠናቋል። ሲያዩት ግን አካላዊ ክሳቱና ራሱን የማይጠብቅ በመሆኑ የተማረ ቀርቶ መዋያ ስራ ያለው ሰው አይመስልም። ግን ንቁና ቀልጣፋ ሲሆን የተመረቀበት ሙያ ደግሞ በራሱ ተፈጥሮዋዊ ተሰጥኦውን ይበልጥ አዳብሮታል።

እድሜው ሃያ ዘጠኝ ዓመት ነው።ቁመቱ አጭር ነው። ህይወትን አሰልቺ ከሚያደርጉት ነገሮች መሀከል አንዱ ፀጉር ማበጠር ነው የሚል እምነት ስላለው አቆጥቁጦ ገና ማደግ ሲጀምር ዘወትር ይላጨዋል። ያለማቋረጥ ጫት የሚቅም እና ሲጃራ የሚያጤስ በመሆኑ ከንፈሩ ዘወትር አመድ የተነፋበት ይመስላል።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

በህሊናዊ ችሎታና ጥንካሬው መጠቀም የጀመረው ገና ተማሪ እያለ ነበር፡፡ ከሰናይት ጋር መስራት የጀመረውም ከመመረቁ አንድ ዓመት አስቀድሞ ሲሆን ከዘጋቢነት ተነስቶ በአጭር ጊዜ ውስጥ ዋና አዘጋጅ ሆኖ እስከመስራት ደርሷል፡፡
በሰናይት እይታ ውስጥ መስፍን ለዕለት ህይወቱ ከመኖር የዘለለ ሌላ ዓላማ የሌለው ሰው ብቻ ይመስላት ነበር፡፡

«««««««« »»»»»»»

በቀጠሮዋቸው መሰረት በሆቴሉ ተገናኙ፡፡
“ተለውጠህል ልበል?” ጠየቀች ሰናይት
“በምን?”
“ከኔ ጋር ትሰራ በነበረበት ወቅት ላይ ራስህን የመጠበቁ ችግርህ ሁሌ እንዳጨቃጨቀን ነበር፡፡”
“ያንቺ መስራቤት የኘሮቶኮል ህግና መቀጫ ስለሌለው ነበር፡፡ አሁን.....ግን.....” ብሎ መሳቅ ሲጀምር ብልዝ ጥርሶቹ ታዩ፡፡
“ለመሆኑ ምን እየሰራህ ነው?”
“በአንድ የግል ኢንሹራንስ ድርጅት ውስጥ የአደጋ ሪፖርቶችን ለሀላፊዎች በፅሁፍ እዘግባለሁ፡፡”
“እዛ መስራቱን መረጥክ?”
“ምን ይደረግ ታዲያ..... የመንግስት ጋዜጠኛ ብንሆን የምናየውንና የምንገነዘበውን እውነታ መዘገብ አንችልም፡፡.....በቃ የመንግስት አፍ! ውሸታም..... ለህሊና የማንሰራ..... ለፊልድ ስራ ወጥተን ህዝቡ በረሀብ ሲረፈረፍ እያየን..... “የግብርና መርህ እስትራቴጂ የኢትዮጵያን ገበሬ ጥጋብ በጥጋብ አድርጐት በቁንጣን እያለቀ ነው ብለን ዜና እንድንሰራ እንገደዳለን፡፡ የግል አሳታሚዎች ጋር ተቀጥረን እንዳንሰራ ግማሹ በኪሳራ እየተዘጋ፣ ሌላው በሀሰት ውንጀላ ቢሮ እየታሸጉባቸው እነሱም ወህኒ እየማቀቁ ነው፡፡ በራስ እንዳናቋቁም በአንድ በኩል አቅም የለም በሌላ አቅጣጫ የኛም እጣ እንደነሱ መታሰር ነው”.....”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

ሰናይት ሁሌም ቀልደኛ በሚያስመስለው የፊቱ ገፅታ ስትስቅ ቆየችና "አሁን ሁሉንም ልትገላገል ነው፡፡ ምርጥ ስራ ከምርጥ ክፍያ ጋር ይገፍልህ መጥቻለሁ፡፡"
"ስራው ምንድነው?"
"ባሁኑ ሰዓት እኔ ከሲ.አይ.ኤ. ላይ ትልቅ የኮንትራት ስራ ወስጄ በመስራት ላይ ነኝ፡፡"
"ከሲ.አይ.ኤ.!"
"አዎ.....፡፡"
"መጨረሻ ላይ ግን ሀብትን ሳይሆን ሞትን እንዳይቸሩሽ"
ሰናይት መሳቅ ጀመረች፡፡ መስፍን ግን አላቆመም "....እነሱ አንድ መመሪያ አላቸው ማንንም ሰው ለፈለጉት ዓላማ ተጠቅመውበት ሲያበቁ ማስወገድ የሚል"
"ግዴለም..... የምትለውን ያህል የሚያሰጋን አይደለም፡፡ ይልቅ ስራውን አብረሽኝ ልትሰራ ከፈቀድክ ሲጠናቀቅ ዳጎስ ያለ ክፍያህን ተቀብለህ ወደ አንዱ የአውሮፓ ወይም አሜሪካ ገብተህ መኖር ትችላለህ፡፡ ህይወትህን ኑሮህን ለዘላለሙ የሚቀይር ክፍያ ነው፡፡ ከአንተ ጋር አብሬ መስራት ስለፈለኩ ነው ለይቼ የመረጥኩህ ፡፡"
"ጥሩ ቀላጅ ሆነሻል"
"መስፍን!..... ቀልድና ስራ ቦታና ልዩነት አላቸው" በጠንካራ ቃላት ተናገረችው፡፡
"ሲ.አይ.ኤ..... እንዴት ብዬ ልመን? እስከሚገባኝ ድረስ ለዘመናት ተጉዞ እዚህ በደረሰው የህይወት ሂደት ውስጥ ሰንካይ አስተሳሰብ ባላቸው ሰዎች ምክንያት ብዙ ነገር እየተመረዘ እዚህ በደረሰባት አደገኛ ምድር ላይ መኖራችን እንዳትዘነጊው"
"ፍልስፍናው ይቆይህና ካልገባህ ጠይቅ፡፡ የስራው አብዛኛው ክፍል ተጠናቋል፡፡ የቀረው ጥቂቱ ብቻ ነው፡፡ ምን መሰለህ....."
ሰናይት ከፒየር ጋር መገናኘት ከጀመረችበት ዕለት አንስቶ ያከናወነችውን ጉዳዮች ሁሉ በጠቅላላ ለሃምሳ ደቂቃ ያህል ስትገልፅለት ቆየች፡፡
መስፍን አሁንም አሁንም በግምባሩ ላይ የሚያቸፈችፈውን ላብ በሶፍት ይጠርጋል፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

መጨረሻ ላይ “.....አሁን እኔ በአማራው ክልል ላይ የሚሰራልኝ አቅም ያለው ሰው ፍለጋ ሰሞኑን ወደ ባህርዳር ሳልሔድ አልቀርም። አንተን እዚህ ካሉት ከሁሉም ጋር አስተዋውቅህና የኔን ቦታ ተክተህ ትቆያለህ። እኔ ያለሁበትን የምታውቀው አንተ ብቻ እንጂ እነሱ መሆን የለባቸውም። ጥብቅ ችግር ካለ ስለምደውልልህ ትነግረኛለህ።”

“እስኪ መጀመሪያ ላስብበት እፈልጋለሁ።”

“እስከ መቼ?”

“እ.....ነገ.....ልነግርሽ እችላለሁ።”

“ጥሩ.....”

ቁርስ የተመገቡበትን አዳራሽ ለቀው ሲወጡ የመስፍን ህሊና ይህ አገርን አሲድ እንደፈሰሰበት ጨርቅ የሚበጣጥስ አላማ ወዴት ሊያመራ እንደሚችል ማሰቡን ቀጠሉ ነበር። ተሰነባብተው ተለያዩ።

  

የማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ምዕራፍ 25

ክልል ሶስት የተባለው የአማራ አገር ለበርካታ ተፈጥሮዋዊና ሰው ሰራሽ ቅርሶች የታደለ ነው። 168.966 ካሬ ኪ.ሜ. ስፋት ሲኖረው ከሱዳን፣ ከኦሮሞ፣ ከአፋር፣ ከቤኒሻንጉልና ከትግራይ ጋር ይዋሰናል። አብዛኛው ህዝብ ኑሮውን የሚገፋው በባህላዊ ግብርናና በከብት ማርባት ስራ ነው።

አገሩ በረሃ፣ ውርጭ፣ ቆላ፣ ደጋ፣ ወይናደጋ የተባሉት አምስቱም ዓይነት የአየር ንብረቶች ይገኙበታል። መሬቱም በማዕድን ውሃ፣ በድንጋይ ከሰል፣ በፍል ውሃ፣ በኖራ ድንጋይ፣ በቤንቶናይት፣ በሳህን አፈር ጨው፣ በድኝ፣ በብረት አፈር፣ ሲልካና፣ ጂምስቶን የተባሉትን ማዕድናት በፅንሱ ይዟል።

እንደ ማዕከላዊ ከተማው አድርጐ የሚጠቀምባት ባህርዳር የተባለችውን ከተማ ነው። መልከዓ ምድራዊ አቀማመጧ ለመኖሪያነት እጅግ ውብ ነው።ከባህር ጠለል በላይ 1820 ከፍታ በ11^0 ሰሜንና በ37^0 ምስራቅ መካከል ከጣና ሀይቅ ጋር በስተ-ደቡብ አቅጣጫ ተዋስና ትገኛለች። የከተማዋ ስያሜም የተገኘው ከተፈጥሮዋዊ አቀማመጧ እንደሆነ ይታመናል።

ለኢትዮጵያ ተከታታይ ጦርነቶችን በማምጣት ነቀርሳና የታይታ ውበት ከመሆን ውጪ ሌላ ጥቅም ሊያስገኙላት ያልቻለው የጢስ አባይ መውረጃም ከባህር ዳር 30 ኪ.ሜ. ርቆ ይገኛል። የስድስት ሺህ ኪ.ሜ. የበረሃ ለበርሃ ጉዞውን የሚያያዘው ከዚህ ስፍራ ተነስቶ ነው። ጥልቀት ካለው ገደል ላይ እየተውዘገዘገ የሚወርደውን ፏፏቴው ታች

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ደርሶ ሲጋጭ የሚፈጥረው ጢስ ከውሃ ሳይሆን ከሚቃጠለ ነገር ላይ የሚወጣ ይመስላል።

በዚሁ ጊዜ ከጢሱ ጋር አብረው የሚነሱት ብናኝ መሳይ የውሃው ፍንጣቂዎች ዙሪያ ገባውን እስከ አንድ ኪ.ሜ. ድረስ በመጓዝ አካባቢውን እፅዋቱንና ምድሩን ያርሱታል።

ይህንን ጢስ አባይ ሀያሉ እግዚያብሔር በመፅሀፍ ቅዱሱ ላይ "ወንዝም ነገትን ያጠጣ ዘንድ ከዔደን ይወጣ ነበር። ከዚያም ለአራት..... ክፍል ይከፈል ነበር።....."

የሁለተኛው ወንዝ ስም ግዮን ነው እርሱም የኢትዮጵያን ምድር ሁሉ ይከባል።....." ብሎ ገልያታል። ይህም 'ኤደን ገነት ተሰውራ እንጂ በዚሁ አካባቢ ትሆን ያለችው?' የሚለውን ጥያቄ በሰው ህሊና ላይ ያጭራል።

ሌላው ድንቅ ነገሩ ደግሞ ረፋዱ ላይ ከቷቷቴው ጋር ጐልቶ የሚታየው ቀስተ ደመና ወደላይ ቁመቱ 45 ሜትር ወርዱ 400 ሜትር በሆነ ስፋት ላይ ዕለት ዕለት በተለይ ከመስከረም እስከ ታህሳስ በህብረ ቀለማቱ አሸብርቆ ይታያል።

ይህም አምላክ ከኖህ የውሃ ዘመን ጥፋት ማግስት ጀምሮ ምድርን ዳግመኛ በውሃ እንደማያጠፋት ሲገልፅ ለቃሉ ማሰሪያ ይሆን ዘንድ ያደረገውን ቀስተ ደመናን ለሰው ልጆች ሊያስታውሰው ይኖራል።

«««««« »»»»»»

ሰናይት በአራተኛው ቀን ነበር ወደ ባህር ዳር ያመራችው። ከመነሳቷ በፊት በክልሉ ኘሬዝዳንት የተወከለላትን ሰው ደውላ ተገናኝ ችውና እንደምትመጣ አሳወቀችው።

ባህር ዳር አየር ማረፊያ እንደደረሰች የመንግስት ታርጋ የለጠፈ ቶዮታ ላንድ ክሩዘር መኪና የያዙ ሁለት ሰዎች መጥተው ተቀበሏት። አንደኛው ሾፌር ሲሆን ሌላኛው ግን በቴሌቶኑ ዝግጅት ዕለት ከተዋወቀቻቸው የፓርቲው ካድሬዎች መካከል ክንዴ አጥናፉ ብሎ ራሱን ያስተዋወቃት ሰው ነበር።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ከአየር ማረፊያው ወደ ከተማው ማዕከል ሲጓዙ የአካባቢውን ተፈጥሮ እያደነቀች ቆየች፡፡
“ወይዘሮ ሰናይት የማረፊያ ሆቴል ተይዞልሻል፡፡ ጥቂት እረፍት ማድረግ የምትፈልጊ ከሆነ..... ወይስ አሁኑኑ የክልሉን ኘሬዝዳንት ማግኘት ትፈልጊያለሽ?” ጠየቃት ደርቤ፡፡
ሰናይት አሰበችና መጣደፉን አልመረጠችውም፡፡ ሰዓቷን አየች፡፡ 5፡05 ብሏል፡፡
“ከሰዓት ስምንት ሰዓት አካባቢ ብትመጡና ብትወስዱኝ?”
“ይቻላል.....ይቻላል.....” እየተሽቆጠቆጠ መለሰላት፡፡
ከከተማው በስተ-ሰሜን አቅጣጫ ወደተሰራ ባለ ሶስት ፎቅ አዲስ ሆቴል አደረሷትና ሻንጣዎቿን የተያዘላት ክፍል ድረስ አስገብተውላት ተመለሱ፡፡
ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ የክፍሉ ስልክ አንጫረረ፡፡ ከማን ሊደወለ እንደቻለ ግራ ተጋብታ አነሳችውና “ሀሎ.....”
“ወይዘሮ ሰናይት ግጥችንን ተቀብለሽ በመምጣትሽ ደስታዬን ለመግለፅ ነው የደወልኩት” የክልሉ ኘሬዝዳንት ድምፅ መሆኑን ወድያው ለየችና “አመሰግናለሁ”
“ጉዞው አድካሚ ነበር?”
“በፍፁም.....”
“ከሰዓት እንደምትመጪ ነግረውኛል”
“አዎ”
“እጠብቅሻለው.....ምናልባት በመሀከሉ ከፈለግሽኝ ደውይልኝ”
“እሺ.....” አለች፡፡ ጋዜጣ አሳታሚ ሆና በሰራችባቸው ወቅቶች ውስጥ በተደጋጋሚ ለቃለ-መጠይቅ ፈልጋቸው በክልከላ ምን ያህል ጊዜ ሳይሳካላት እንደቀረ እያስታወሰች፡፡
ድጋሜ አመስግነዋት መነጋገሪያውን ቦታው መለሱ፡፡
ምንም የምትሰራው ስራ ስላልነበረ የባኞ ቤቱን ገንዳ ለብ ባለ ውሃ ሞላችውና ገብታ ተኛችበት፡፡ ከዛም ስለቀጣይ እቅዶቿ እያሰበች ለአንድ ሰዓት ያህል ቆየች፡፡ ከጨረሰች በኋላ ልብሷን ለባብሳ ወደ መመገቢያ አዳራሹ በመውረድ ምሳ እንደነገሩ ቀማመሰች፡፡ ቀጥላም በህንፃው አናት ላይ ለእንግዶች በተዘጋጀው በረንዳ ላይ ወጥታ በመቀመጥ ቡና አዘዘች፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

የጣና ሀይቅ በርቀት ይታያል፡፡ የዙሪያ ገባውን የመልከዓ ምድር ገፅታ በፎቶ ቀርፆ ለማስቀረት እየተዟዟረ ሲያነሳ የቆየ ፈረንጅ እሷ ወዳለችበት ስፍራ ቀረበ፡፡ ጥቂት ቆየናም ወደ ተቀመጠችበት ጠረጴዛ መጥቶ
“እባክሽ..... እዚህ ቦታ ፎቶ አንሽኝ?”
ሰናይት ካሜራውን ተቀብላው እንደ ምርጫው አምስት ፎቶ አነሳችው፡፡
“ብሩስ ፓውል እባላለሁ..... አመሰግናለሁ” ካሜራውን እየተቀበለ ስሙን ነገራት፡፡ አያይዞም አሜሪካዊ መሆኑን ገለፀላት፡፡
ውይይታቸው ያዘነበለው በአገራዊ ቅርሶች አጠባበቅ ላይ ነበር፡፡
ቀጠለ ነጩ “ከአስር አመት በፊት አባቴ ወደዚህች አገር ለጉብኝት መጥቶ ነበር፡፡ በዛን ጊዜ የነበሩና እሱ ፎቶ ያነሳቸውን በርካታ ቅርሶችን ፈፅሞ ማየት አልቻልኩም፡፡”
“ለምን?” አለችው
“በብዛት ተዘርፈዋል ውስኖቹ ወድመዋል የሚል መልስ ነው ያገኘሁት”
“በማን ነው የተዘረፈው?”
“በአመዛኙ የሀይማኖት ሰባኪና የበላይ ጠባቂ እየተባሉ የሚሾሙት ቄሶች ጋር የተያያዘ ነው አሉኝ በእንደዚህ ዓይነት ጉዳይ ውስጥ የጳጳሳቱ እጅ ሁሉ እንዳለበት ነው የየገዳማቱ ቄሶች የገለፁልኝ..... ቅርስ ማለት ስላለፈው የማንነት አሻራ የታተመበት እና ስለቀጣዩ አንቺነትሽ የምትናገሪበት በገንዘብ የማይገዛ የዳበረ የሞራልና የስነ-ልቦና ሀብትህ ነው፡፡ በአፍሪካ ላይ ብዙ አገሮች ዞሬያለሁ፡፡ ሰውን የሚገድል ገዢና አገዛዝ ሞልቷል፡፡ ማንነትና አገርን የሚገድል ግን እንደ ኢትዮጵያ ማንም አላጋጠመኝም፡፡ በኢትዮጵያ ሰው ብቻ ሳይሆን አገርና ታሪክ እየሞተ ሲሔድ ነው ያየሁት” አለ አሜሪካዊው ነፃ በሆነና ግልፅ ስሜት፡፡
ከግማሽ ሰዓት በላይ አወሩና ነጩ ተሰናብቷ ከህንፃው አናት ላይ ወረደ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

የቀጠሮው ሰዓት ሲደርስ ብርማ የተቀባች ጥቁር መስታውት ያላት ዘመናዊ መርሰዲስ መኪና መጣችና የክልሉ ምክር ቤት ወደ ሚገኝበት ህንፃ ይዛት ተፈተለከች፡፡

ወደ ኘሬዝዳንቱ ቢሮ ደርሳ ስትገባ ከወንበራቸው ተነስተው ተቀበሏት፡፡

የወለሉ ምንጣፍ ጠረጴዛዎች ወንበሮቹ እንዲሁም ሌሎቹ ቁሳቁሶች በጠቅላላ ውብና አዲስ ነበሩ፡፡

የሞቀ ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ከጠረጴዛቸው ፊት የሚገኘውና ጥቁር ቆዳ ወደ ተለበጠው ምቾት ያለው ሶፋ ላይ እንድትቀመጥ አመላከቷት፡፡

“እሺ ከፈረንሳይ መምጣትሽን ያለፈ ጊዜ ነግረሽኝ ነበር፡፡ ከዛ ሁሉ ቆይታሽ በኋላ ኢትዮጵያን እንዴት አገኘሻት?”

“አሁን እጅግ ተለውጣለች፡፡ በተለይ ያን ደርግ የተባለ አውሬ መንግስት ወድቆ አገሪቷን እናንተ መምራት ከጀመራችሁ በኋላ.....”

“አዎ..... የኛ ራዕይ እንደተለጐመ በቅሎ ወደ አንድ አቅጣጫ ብቻ ነው የሚገሰግሰው፡፡ እሱም ወደ ልማት፡፡” አሉ፡፡

ሰናይት ይህን አባባል ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ኮርጀው ቃላቱን በመለዋወጥ የተናገሩት መሆኑን አስታወሰችና ፈገግ ብላ “.....እያየን እኮ ነው፡፡ በአስር ዓመት ውስጥ የመጣው እድገት ራሱ ብዙ ይመሰክርላችኋል” አለች፡፡

ቀጠለች “.....እኔም አሁን በተለይ በዚህ በናንተ ክልል ላይ ትልልቅ ልማቶችን ለማካሔድ እቅዱ አለኝ..... በምን ላይ ብሰማራ አገሪቷን መጥቀም እንደምችል ግን መረጃ የለኝም፡፡”

“ምን ችግር አለው ታዲያ.....ብዙ ያልተዳሰሱ የስራ ዘርፎች አሉ፡፡ ግና ምንም ያልተሰራባቸው ናቸው፡፡”

ሰናይት በህሊናዋ ‘ ወሬ ማሳመር ታውቁበታላችሁ ወደ ተግባር ሲገባ ግን የተተበተበው ቢሮክራሲ ካለፈው ስርዓት ጋር በምንም አይለያችሁም እንጂ’ እያለች ነበር፡፡

ቀጠሉ ኘሬዝዳንቱ “ይህን ሁሉ ለማረጋገጥ ከፈለክሽ ደግሞ አሁን በጉብኝቱ ወቅት ታይዋለሽ” ብለው ከጠረጴዛቸው መሳቢያ ኪስ ሁለት በአንድ ላይ የተያያዙ ወረቀቶች አወጡና “ኘሮግራም አውጥተንልሻል በመጀመሪያ የጣና ሀይቅ ላይ ጉብኝት ሲሆን በመቀጠል በጐንደር

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

በጐጃምና በወሎ እየተዘዋወርሽ እንድትጐበኝ አቅደናል፡፡.....እ..... ለምናሳይሽ ነገር ሁሉ በቂ ጊዜ ባይሆንም መሰረታዊ ግንዛቤን እንድታገኝ ያህል ለአስራ ሁለት ቀን ትቆያለሽ፡፡ ይህም ማለት እንግዲህ አንቺ ፈቃደኛ ከሆንሽ ማለት ነው፡፡ "

"እሺ....."ብላ ወረቀቱን ተቀበለቻቸው፡፡

"ዛሬ ማታ የእራት ግብዣ ስላዘጋጀንልሽ እንድትገኝ እጠይቃለሁ?"

"እመጣለሁ....."

በአክብሮት ተነስተው ጨበጧትና "አንድ ሰዓት ላይ ሆቴል ድረስ መጥተው ይወስዱሻል፡፡"

በእሺታ ተሰናብታቸው ወጣች፡፡

ማታ ላይ ቀን የወሰደቻት መርሰዲስ መኪና መጣችና ይዛት ግብዣው ወደ ሚካሄደበት ስፍራ አደረሰቻት፡፡ በረዥም ግምብ የታጠረ ሰፊ ጊቢ፤ በአራቱም ማዕዘናት የተሰሩ ማማዎች ላይ በወታደሮች ይጠበቃል፡፡

ልቧ በፍርሀት መራዱ አልቀረም፡፡ ወደ ሾፌሩ ዞረችና "የት ነው ቦታው?"

"የፕሬዝዳንቱ መኖሪያ ቤት ነው፡፡"

በመጠኑ ተረጋጋች፡፡ ወደ ቤቱ እየተቃረቡ ሲመጡ በርካታ መኪናዎች መቆማቸውን አየች፡፡ ቀዝቀዝ ያለ ነፋስ ይነፍሳል፡፡ የዛፍ ቅርንጫፎች በለሆሳስ ወዲህና ወዲያ ይንቀሳቀሳሉ፡፡

የቤቱ መግቢያ ጋር ስትደርስ ራሳቸው ወጡና "ወይዘሮ ሰናይት....." ሰላምታ ተለዋወጡ፡፡ እየመሯት ወደ ውስጥ ገቡ፡፡ ሳሎኑ ሰፊ አዳራሽ ሲሆን በውድ እቃዎች የተዋበ ነበር' 'በህዝብ እና በአገር ልማት ስም የሚሰበሰበው ገንዘብ ለነሱ የግል ኑሮ መንደላቀቂያ ነው የሚያድረጉት' ስትል አሰበች፡፡ ከሃያ የማይበልጡ ሰዎች በቡድን በቡድን እየተሳሳቁ ያወራሉ፡፡ ፕሬዝደንቱ "የምሽቱ የክብር እንግዳችን እሷ ነች....." ጮሳ ባለ ድምፅ ተናገሩና "ይሄ ምክትል ኘሬዝዳንቱ ነው..... ይሄ የከተማችን ከንቲባ ነው..... ይሄ ጀነራል ምትኩ ይባላል..... ይሄ ደግሞ የምክር ቤታችን አፈ ገባኤ....." ሁሉንም ከነማዕረጋቸው አስተዋወቋት፡፡

ተጨማሪ ስድስት የሚሆኑ የፓርቲው ባለስልጣናት መጡ፡፡ ራት ከተበላ በኋላ ወደ መጠጡ ነበር የተዞረው፡፡ አሳላፊዎች ዊስኪ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ዋንጫ በመሰለች ብርጭቆ እየሞሉ በተጋባጦች መሀከል በመዞር ያድላሉ፡፡

አብዛኛዎቹ የሰናይትን ማንነት ከኘሬዝዳንቱ በተነጋገራቸው መሰረትና የቴሌቶኑ ዝግጅት ላይ ያደረገችውን የገንዘብ እርዳታ እያነሱ በመነጋገር በአክብሮት ሲያሞጋግሷት አመሹ፡፡ የተወሰኑት ሰዎችም በነሆለለ ስሜት በስርቆሽ ሲያዩዋት አስተውላለች፡፡ ከነሱ መካከል አንዱ ጀነራል ምትኩ ነበር፡፡ እሷም ለመጣችበት የግል ዓላማዋ መጠቀሚያ ማድረግ የምትችለው ሰው ማን ሊሆን እንደሚችል ከማጥናት አልተዘናጋችም፡፡ በጉልህ የተረዳችው እውነታ ቢኖር ሁሉም የገንዢው ጫማ መሆናቸው ነበር ከወሬያቸውና ሽቁጥቁጥ ድርጊታቸው የሚነበበው፡፡

ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ላይ እንግዶች እየወጡ መሔድ ጀመሩ፡፡ ቀሪዎቹ ግን ከመጠጣት አልተቆጠቡም፡፡ ኘሬዝዳንቱ ሂያጆቹን ለማሰናበት ገባ ወጣ ማለት ሲጀምሩ ሰናይት ብቻዋን መሆን ያስዋለው ጀነራል ምትኩ ክፍተቱን ተጠቅሞ ተጠጋት፡፡ ሲጠጣ በቆየው ውስኪ ሞቅታ ውስጥ መግባቱ ከሁኔታው ያስታውቅበት ነበር፡፡

ኘሬዝዳንቱ ሲያስተዋውቋት የተናገሩት ስሟን በመከራ ለማስታወስ እየጣረ “አዲሷ እንግዳችን ”

“እሺ..... ጀነራል ምትኩ....” ከፊት ለፊቷ ሌላ ወንበር ስቦ ተቀመጠ፡፡ “ይቅርታ ስምሽን ማን ነበር ?” ስካር በተጫጫነው ጐርናና ድምፅ ጠየቃት፡፡ አይኖቹም ቦዘው ነበር፡፡

“ሰናይት”

“ስላንቺ አብረውኝ የነበሩት ሰዎች ሲያወሩ ሰምቻለሁ፡፡”

“ምን እያሉ?” በተለሳለሰ አኳኋን ልብ በሚሰርቅ ሁኔታ ፈገግ ብላ ጠየቀችው፡፡

“ሀብትሽን እዚህ ክልል ላይ ልትሰሪበት እንደምትፈልጊ”

“አዎ..... ክልሉን ለማልማት እፈልጋለሁ፡፡ እንዳንተ አይነት ማዓረግ ያለውና መከታ መሆነ ከሚችል ሰው ጋር መተዋወቅ ደግሞ የበለጠ ተደሳች አድርጎኛል፡፡”

ሳቀና የመጠጡን ብርጭቆ አንስቶ ጨለጠው፡፡

“ምነው ሀሳቤ ጥሩ አይደለም እንዴ?”

“አይመስለኝም.....፡፡”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

“የኔ ስራ ስለ ጦርነት ማቀድ፤ መዋጋት፤ ታንክ፤ ጥይት..... ምናምን ነው ”
“ጄነራል አንድ ነገር ልትነግረኝ የምትፈልግ መሰለኝ”
“አልፈለኩም፡፡ ሁሉም ነገር ልክ ነው፡፡” አሳላፊው በሌሎች ብርጭቆ የተቀዱ ዊስኪ ይዞ ሲመጣ ጀነራሉ በራሱ ብርጭቆ ውስጥ የቀረችውን ጨለጠና ሌላ እያነሳ “ አንድ በኔ ግብጣ ለአዲሷ እንግዳችን” ብሎ ለሷም አቀበላት፡፡
“የአንተ ግብጣ በሰው ግብጣ ላይ ተደርቦ መከናወን አይችልም፡፡ ከፈለክ የራስህን ግብጣ አዘጋጅተህ ጥራኝ፡፡” አለችው በተዋበ ፈገግታ እያዋዛች፡፡
“ፈቅደሽልኝ ነው..... ለምን ዛሬ አይሆንም አንቺ ከፈቀድሽ?..... በጣም ተግባቢ ሰው ነሽ፡፡ ”
ሳቀችለት፡፡ እሱም ደስ አለው፡፡ በሀሳቡ አልጋ ላይ ምን አይነት ሰው ልትሆን እንደምትችል እያሰበ ነጎደ፡፡ ወድያውም ሲያስብ የቆየውን ያወቀችበት ይመስል ደንገጥ እያለ “ አሁን በአንድ የዋህ ጀነራል ልብ እንደዚህ ባትጫወችበት ምን ይጎዳሻል? ”
ሰናይት የበለጠ እንዲቀርባት ልቡን ለማንጠልጠል እያሰበች “ይልቅ ጄነራል የዚሁ ክልል ሰው ከሆንክ አብረኸኝ እንድትሰራ ሁኔታዎችን ባመቻችልህስ?”
“ወታደር እኮ ነኝ.....i” በስላቅ መለሰለት፡፡
“ይገባኛል”
“እንዴት አብሬሽ እሰራለሁ ታዲያ?”
“የግድ በቢሮ የመገኘት ጫና ላይኖርብህ ይችላል..... ለምሳሌ አክሲዮን መሰል በሆነ ዘዴ.....አብረን.....”
አቋረጣትና “ይልቅ..... ” ብሎ ሀሳቡን ገታው፡፡
“ምን ንገረኝ እንጂ?”
“ከባድ ነው”
“እስኪ ዛሬ ሚስጥረኛህ ልሁን..... ደስ ያለህን ጠይቀኝ” አለችው በሚያስተማምን ሁኔታ እያየችው፡፡
“ከዚህ አገር እንዴት ማምለጥ እንዳለብኝ ነው እያሰብኩ ያለሁት.....”
“ችግር አለ እንዴ?”
“አዝናለሁ..... አገሪቷ ያለችበትን ሁኔታ እንዳልነግርሽ የሚሊተሪ ህግ ይከለክለኛል..... ግን ሀብትሽን ከማፍሰስሽ በፊት ዓይንሽን ገልፀሽ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

በደንብ ተመልከች፡፡ ይህን ስልሽ አንችን በማመኔ ነው እንጂ አንገትን ለሰይፍ የመስጠት ያህል በራሴ ላይ ፈርጄ ነው፡፡ »

ቀጠለ«... ይህን ነገር ደግሞ ለአንድ ሰው ብትናገሪ ለኔ ብቻ ሳይሆን ላንቺም ጥሩ እንደማይሆንህ አስተውይ ፡፡ በዚህ ምድር ላይ ግልፅና ቀጥተኛ ሰው ሆኖ መገኘት የመኖር እድልን በእጅጉ ያቀጭጨዋል" አለ፡፡

"አንተ ለኔ በአሁኑ ሰዓት ግልፅም ቀጥተኛም ሆነህልኛል፡፡ በጣም አመሰግናለሁ የዚህን ያህል ስላመንከኝ፡፡"

"ካሁን በኋላ ቢገድሉኝም ምንም ስለማይመስለኝ ነው፡፡ ስንቱ ጥቅም ያለው ጀግና በነሱ ሴራ እንዲያልቅ ተደርጓል፡፡ ነገ የኛም እድል ይኸው ነው፡፡ ለዛ ነው ማለት የማይገባኝን ሁሉ ያወራሁት ይቅርታ " አላት፡፡

በዚህ ጊዜ ፕሬዝዳንቱ ወደነሱ ሲመጡ አየ፡፡ "እያጫወትካት ነው ጄነራል?" ጠየቁ በፈገግታ፡፡

ፊቱ ሲለዋወጥ አየች፡፡ ፕሬዝደንቱ ግን አላስዋሉም፡፡ ምትኩም በህሊናው አንድ ጀነራል የአንዲት አዲስ እንግዳ አጫዋች መሆን በይፋ ሲነገር ከመስማት በላይ ምን ክብርን የሚነካ ነገር አለ እያለ በማሰብ "ስለ ክልላችን የተፈጥሮ ሀብት እያወጋሁላት ነበር፡፡"

ሰናይትም ቀጠል አድርጋ "አዎ..... አዎ.... ጉብኝቱን እስክጀምረው ጓጉቻለሁ" አለች፡፡

"ነገ ጠዋት ይሆናል..... ባለሞያዎች መድቤልሻለሁ፡፡"

"አመሰግናለሁ"

እድሜው ወደ አርባ አምስት ዓመት የሚጠጋው ረዘም ብሎ ሞላ ያለ ሰውነት ያለው ጄነራሉ ብርጭቆው ውስጥ የቀረውን መጠጥ ጨልጦ "በሉ እንግዳዋን አስረክቤዋለሁ ልሂድ" አለና ሁለቱንም ጨብጦ ወጣ፡፡

ሰናይት ምትኩን በዓይኗ በመከተል ውጪ ምንም ልታደርግ አልቻለችም፡፡ 'ፈጣን ሰው ባለመሆኔ ነው ያመለጠኝ' ስትል ራሷን ወቀሰች፡፡ ለዕቅዷ የሚሆን ሰው ለማግኘት ደግሞ ከዚህ የተሻለ አጋጣሚን ፈፅሞ ማግኘት እንደማይችል ነበር ያሰበችው፡፡ የምሽቱ ግብዣ ተጠናቀቀ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ወደ ሆቴሉ ሲሄዱ ንዴቷ አልበረደላትም፡፡ መጨረሻ ላይ አንድ ሀሳብ ውል አላት፡፡ እንዲያደርሳት ወደታዘዘው ሾፌር ዞረችና
“እኔ የምልህ.....”
“አቤት”
“ጄነራል ምትኩን ታውቀዋለህ?”
“አዎ.....የተወሰነ ወቅት ሾፌራቸው ነበርኩኝ”
“ስልኩ አንተ ጋር ይኖራል?”
“ከወታደሩ ጋር ካምኘ ውስጥ ነው የሚኖሩት፡፡ ስልካቸውን አላውቀውም፡፡”
“እንዴት ላገኘው እችላለሁ?”
“መስራቤታቸው ድረስ በመሔድ ነዋ”
“የት ነው ለመሆኑ ካምፑ”
“አየር ሀይሉ ጊቢ”
“እስኪ ሌላ የማግኛ መንገድ ፈልግ”
“ምንም የለም”
ሰናይት ከምትኩ ጋር ለመገናኘት ሌላ ዘዴ ሊኖር እንደሚችል ብታምንም ፈርቶ ወይም በአንድ ሌላ ምክንያት ሊነግራት እንዳልፈለገ አውቃበታለች፡፡
“ሆቴል ከመድረሳችን በፊት አንድ ቦታ ጐራ እንበልና ትንሽ እንጠጣ፡፡”
“እዛው መጠቀም ይችላሉ እኮ”
“አብረን እንድንቆይ ፈልጌ ነው”
ይሄት ከዋናው አስፓልት ተገንጥሎ ገባ ባለ ሰዋራ ቦታ ወደ ተሰራ ሌላ የከተማው ታዋቂ ሆቴል ወሰዳት፡፡
ራት አዘዙ፡፡ እሷ አልበላችም ፡፡ ሾፌሩ ደህና አድርጐ ተመገበ፡፡ ሙሉ ውስኪ አስወረዱ፡፡ እየጠጡ ጨዋታ ቀጠሉ፡፡ ስለ ከተማዋ ሁኔታ ጥቂት አወጉ፡፡ በዚህ ዕለት ከተገናኘቻቸው ሰዎች መካከል ሶስት አራተኛ የሚሆኑት ያወሩላት ስለ ባህር ዳር ከተማ ውበት ብቻ ነበር፡፡ ይህም ፈረንሳውያኑ ስለ ፓሪስ ውበት ገና ምንም ማውራት አልጀመሩም ብላ እንድትሳለቅ አስገደዳት::
ክፍተት ጠብቃ “ይልቅ የጄነራሉን ነገር ረሳነው፡፡ በሚስጥር ላገኘው እፈልግ ነበረ፡፡ እንዴት ላድርግ?”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“አስቸጋሪ ነው አልኮትኮ”
“እንደው.....አንዳንዴ.....ሲዝናና የሚያመሽበት ቦታ.....”
“እሱማ.....ከክብራቸው ጋር አይሔድ እንደሆን ብዬ እንጂ መቼስ ወንድ እስከሆኑ ድረስ እንደሱ አይነት ነገርማ መች ይጠፋል፡፡”
“ልክ ነህ ቦታውን ታውቀዋለህ?”
“አዎ.....” በዝቅተኛ ድምፅ መለሰላት፡፡
“ልታሳየኝ ፈቃደኛ ከሆንክ አስር ሺህ ብር እከፍልሀለው”
“ይቻላል!.....” በልቡ ግን ‘ያልታሰበ ሲሳይ!’ ፡፡
ቀጠለ”.....ግን ዛሬ አይገኙም፡፡ የሚመጡት ማክሰኞና ቅዳሜ ብቻ ነው፡፡”
“ነገ ማለት ነዋ”
“አዎ”
ጉብኝቱን ከጀመረች እንደማይመቻት አሰበችና “በቃ ጉብኝቱን ጨርሼ እንደተመለስኩ ደውዬ ልንገርህና ይሁና”
“ይቻላል” ብሎ የሚገኝበትን ስልክ ቁጥር ሰጣት፡፡
እሷም አንድ ሺህ ብር ጠቅልላ አስጨበጠውች፡፡ ተነስተው ወጡ፡፡

«««««« »»»»»»»

በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ላይ ሶስት ሰዎች ሆቴሉ ድረስ መጥተው አስጠሯት፡፡አንደኛው ሰው የአማራ ክልል ቱሪዝም ቢሮ የስነ-ቅርስና ታሪክ ምሁር ሲሆን በጉብኝቱ ወቅት እያንዳንዱ መረጃ እንዲነግራት ከበላይ ታዞ ነው የመጣው፡፡ ሁለቱ ግን እጀባውን ለማድመቅ የተላኩ ግለሰቦች ነበሩ፡፡
ጉብኝቱ 367 ካሬ ኪ.ሜ. ስፋት ካለው የጣና ሀይቅ ላይ ተጀመረ፡፡ ጣና በስፋቱ ከኢትዮጵያ አንደኛ ሲሆን በአፍሪካ የሶስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ በሀይቁ ላይ ሰላሳ ሰባት ደሴቶች ሲኖሩ በሃያዎቹ ላይ መነኩሳት የመነኑባቸው ገዳማት ይገኛሉ፡፡ አንዳንዶቹ ሰንሰለታማ ሂደታቸው ሳይበጠስ ከሰባት መቶ ዓመት በላይ እድሜ ያላቸውና ዛሬም ቢሆን ሰዎች የሚኖሩባቸው ናቸው፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ኢትዮጵያ ከሶስት ሺህ ዓመት በሚልቀው ታሪኳ ውስጥ በተካሄዱባት አውዳሚ ጦርነቶች ወቅት የነበሯት ቅርሶች ከውድመት እንዲተርፉ ተሰውረው ይቀመጡ የነበረው በደሴቶቹ ላይ በተሰሩት ገዳማቶች ነበር።

ዛሬም ቢሆን ከሺህ ዓመት የሚልቅ እድሜ ያላቸው ታሪካዊ ቅርሶች ተቀምጠውባቸው ይገኛሉ።

1543 በኢትዮጵያ አቆጣጠር አፄ ገላውዲዎስ አስከፊ ወረራና ውድመትን በኢትዮጵያ ቅርሶች እና ስልጣኔ ላይ አድርሶ የነበረው ግራኝ መሀመድን ድል አድርገው የገደሉት በዚሁ ሀይቅ ዙሪያ ነበር።

እነ ሰናይት በሀይቁ ላይ ባሉት እያንዳንዱ ደሴቶች ያካሄዱት ማራኪና ልብ አንጠልጣይ ጉብኝት የጨረሱት ከሁለት ቀናት በኋላ ረቡዕ ማታ ላይ ነበር።

ከዛም የክልሉ መንግስት በተከራየላቸው ጀልባ በጣና ምስራቃዊ ጐን ዙሪያ ጥምጥም አድርገው ቀሪውን በመኪና በመጓዝ ከባህር ዳር በስተሰሜን አንድ መቶ ሰባ ኪ.ሜ. ርቀት ላይ የምትገኘው ጐንደር ደረሱ።

ጐንደር በአፄ ፋሲል ዘመነ ንግስና የአገሪቷ ማዕከል ሆና ትታወቅ እንጂ የአፄው አባት የነበሩት ሱስኒዮስም ብቅ እያሉ ቆይታ ያደርጉባት ነበር።

ኢትዮጵያውያን ለሶስት መቶ ዓመታት ከፋፍለው እንደ መሻታቸው ይገዟት የነበሩት ነገስታቶችን ድል አድርገው ወደ አንድነት ምዕራፍ እንድትጠቃለል ያደረጓት ባለ ውለታዋ አፄ ቴዎድሮስም የተገኙት ከዚሁ ምድር ላይ ነበር። ጐንደር ዛሬም ድረስ በርካታ ጦርነቶችንና ጐስቁልናን ተቋቁመው ለመታየት የቻሉ ታሪካዊ ቅርሶች የሚገኙባት ስትሆን ከነሱም መሀከል ነግሰውባት የነበሩ የአፄዎችን አሻራ አትመው ያስቀሩ የማይንቀሳቀሱ ግዙፍ የቤተ-መንግስት ግምቦችና ስነ-ህንፃዎች አሏት።

ሶስተኛው የጉብኝት ምዕራፍ ወደ ሰሜን ብሔራዊ ፓርክ ነበር። ይህ ፓርክ በኢትዮጵያ የመጀመሪያውና በአፍሪካ አራተኛ የሆነውን የራስ ዳሽንን ተራራ የያዘ ሲሆን ከፍታው ከባህር ወለል በላይ 4620 ሜትር ነው።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ፓርኩ በውስጡ በሌላው ዓለም የማይገኙ ዋሊያ፣ ቀይ ቀበሮና ጭላዳ ዝንጀሮ ይገኙበታል። ይህን ፓርክ ዩኒስኮ በ1962 ዓ.ም. በመዝገቡ ላይ ዓለም አቀፍ እንዲሆን በአዋጅ አፅድቆታል።

ከብሔራዊ ፓርክ ተነስተው ወደ ውቅሮ ላሊበላ ገቡ።

ይህን ከአንድ ዓለት የተፈለፈለና በምድር ውስጥ የተሰራውን ቤተ-መቅደስ ያስጀመረው ላሊበላ ሲሆን ያስጨረሱት ደግሞ አቡነ መልከፄዴቅ ናቸው።

ወደ መቅደሱ ለመግባት በርካታ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ማለፍ ግድ ይላል። በቦታው ሲደርስ በስልሳ ስድስት ዓምዶች ላይ የቆመውን ቤተ መቅደስ ወደ ላይ ቀና ብሎ ማየቱ እውን ከአንድ ዐለት መፈልፈል መቻሉ ጉድ ያሰኛል።

ሌላው የተለያዩ ቅርፅ ያላቸው አስራ ሁለት ዓይነት የመስቀል ስራዎች ከዛጉዌ ነገስታት መሀከል አንዱ በነበረው በላሊበላ ነው የተፈጠሩት።

እሱ ያሳነፃቸው እነዛ አስራ አንዱም አብያተ ክርስቲያናት በቅርፅም በመጠንም አንዱ ከሌላው የተለያዩ ናቸው። መሬት ውስጥ ካለ አንድ ወጥ ደንጊያ 33.5 ሜትር ወርድ 23.5 ሜትር ጐንና 11 ሜትር ቁመት ያለውን ውቅር ህንፃ ከነ ጌጣጌጡ ፈልፍሎ ለመፈፀም ሃያ ሶስት ዓመት ፈጅቶዋል። ያውም በአፈ-ታሪክ እንደሚነገረው የመላዕክት እገዛ ተደርጐበት።

እነ ሰናይት ባህር ዳርን ከለቀቁ አስራ አንድ ቀን ሞላቸው። በየደረሱበት ቦታ ሁሉ እየተቀበሉ የሚንከባከቧቸው የየክልሎች የመንግስት አካላት ነበሩ። ለጉብኝቱ መሳካት መኪና መሔድ በሚችልባቸው መኪና ካለበለዚያም ፈረስ ተጭኖ ይጠብቃቸዋል።

ጉብኝቱ ለማጠናቀቅ ቢያንስ የአንድ ሳምንት ተጨማሪ ጊዜ እንደሚጠይቃቸው በአስጐብኚው እየተነገራት ደብረ ታቦር ከተማ ደረሱ።

ከተማዋ ቀዝቀዝ ያለች ነው። ሰዓቱ እየመሸ ነበር። ከተከራዩበት ሆቴል ብቻዋን ወጣችና ለመናፈስ እያሰበች በለሆሳስ መንገዱን ይዛ መራመድ ጀመረች።

ደሳሳ ጐጆዎች ይታያሉ። ህዝቡ በአመዛኙ የጉስቁልና ህይወትን እንደሚገፉ አለባበሱና አካላዊ አቋሙ ይናገሩበታል።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ከከብት ኋላ ኋላ የሚሮጡ ወይም ሌላ ስራ የሚሰሩ ካልሆኑ በስተቀር የሚጫወቱ ህፃናት አይታዩም፡፡ አጠቃላይ ድባቡ ህይወት መከራ ናት የሚል ይመስላል፡፡

አንድ ጋዜጣ ሻጭ ወጣት ተጠጋትና "እትዬ ጋዜጣ"

"ለመሆኑ እዚህ አገር ጋዜጣ በወጣ በስንት ቀን ይደርሳል?" ጠየቀችው

"በሁለትም በሶስትም..... አንዳንዴም ቆይቶ" መለሰ ወጣቱ፡፡

ሰናይት ልትገዛ አላሰበችም፡፡ ሌላ ጥያቄ ልትቀጥል ስትል ከላይ በያዘው ጋዜጣ ላይ በጉልህ ፊደላት ወደ ተፃፈ ፅሁፍ ፈጣ ቀረች፡፡

"ኢትዮጵያ ሊያቅላት ነው!" ይላል፡፡

ዝቅ ብሎም፦ "ማንነቱ በውል ያልታወቀ የውጭ ድርጅት ኢትዮጵያን ሊበጣጥሳት በርካታ በህቡዕ የሚመሩ አንጃዎችን እያደራጀ እንደሚገኝ ራሳቸውን መግለፅ ያልፈለጉ ግለሰቦች አስታወቁ....."

በቅፅበት ጋዜጣውን ነጠቀችውና ወደ ተከታዩ ገፅ የሚዞረውን ቀሪ ዜና ፈልጋ አገኘችው፡፡

".....እንዳሉትም ከሆነ እስካሁን ከሶስት የሚበልጡ የተደራጁ አንጃዎችን ከየጐሳው መሀከል ለመፍጠር ችለዋል፡፡ ይህን ጉዳይ ምላሽ እንዲሰጡበት የተጠየቁት የመንግስት ባለስልጣንም ውሸምብር ህዝቡ ላይ ለመፍጠር የታቀደ ሴራ ነው እንጂ ምንም የሚያሰጋ ነገር የለም ሲሉ አስተባብለዋል፡፡" ይላል፡፡

ለሁለት ደቂቃ ባለችበት ደርቃ ቆመች፡፡ በሷ ላይ የተሰራ ዜና ስለመሆኑ ቅንጣት ታህል አልተጠራጠረችም፡፡

"እትዬ ልሔድ ነው ሂሳብ ስጡኝ?"

ጋዜጣውንና አንድ ብር አውጥታ እየሰጠችው "ስልክ የት አገኛለሁ?"

"እዛ ጋር....."

መስፍንን በስልክ ለማግኘት ደጋግማ ያደረገችው ሙከራ በኔትዎርክ ችግር ምክንያት ሳይሳካላት ቀረ::

ልቧ በሁለት ተከፈለ፡፡ ጉብኝቱን አቋርጣ አንድም በቀጥታ ወደ አዲስ አበባ አልያም ወደ ባህር ዳር መመለስን፡፡

ለሊት እንቅልፍ በአይኗ ሳይዞር እንደተቁነጠነጠች አደረች፡፡ የወሰነችው ግን ወደ ባህርዳር መሔድን ነበር፡፡ እዛ ያልተጠናቀቀውን ስራ መስመር አሲዞ በፍጥነት ወደ አዲስ....

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

አስጐብኚውንና ሁለት አጃቢዎቹን ማለዳ ላይ ክፍላቸው ድረስ ሄዳ በመቀስቀስ "ዛሬ ወደ ባህርዳር መመለስ አለብን" አለቻቸው። የጉዞ ሻንጣቸውን ሸክፈው ተነሱ።

«««««« »»»»»»

ሰናይት ባህርዳር በደረሱ የዕለቱ ዕለት የኘሬዝዳንቱ ቢሮ ነበር ያመራችው። እንዳዩዋት ከወንበራቸው ተነሱና "በጉብኝቱ እንደረካሽ ሙሉ እምነት አለኝ" አሏት
"ከሚገባው በላይ" ፈገግ ብላ መለሰች።

"አዎ.....እንዳየሽው ክልላችን የቅርስና የተፈጥሮ ሀብት ባህር ነው ማለት ይቻላል"
"ልክ ነዎት"
"የዛኑ ያህል ደግሞ በስልጣኔና በእድገት ወደ ኋላ የቀረች በመሆኑ ለልማት የሚመርጣት ሁሉ በግምባታ፣ በትምህርት፣ በጤና፣ በቱሪዝም፣ በፋብሪካ..... ዘርፎች ቢሰማራባት አትራፊ ሊሆን ይችላል።"
"አዎ..... ብዙ ኘሮጀክቶችን ለመቅረፅ የሚያስችለኝን ግንዛቤ ስላገኘሁ በቅርቡ አብረን መስራት እንደምንጀምር ተስፋ አለኝ" አለች።
"ደስ ይለናል....." ቀጠሉ ቆየት በለው "አዲስ አበባ መቼ ለመመለስ አስበሻል?"
"ነገ ወይም ከነገ ወዲያ"
"ጥሩ..... የበቀደምለቱ ሆቴል ውስጥ ማረፊያ ተይዞልሻል"
"አመሰግናለሁ" አለቻቸውና ለመሄድ ስትነሳ ጨብጠው አስናበቷት።

የምክር ቤቱ ህንፃ ስር ቆሞ ይጠብቃት የነበረው ሾፌር ባለፉት ጊዜ እንዲያመላልሰው የተመደበው ራሱ ነበር።
አጭር ሰላምታ ተሰጣጡ። መኪናዋ ተንቀሳቅሳ አስፓልት መንገዱ ላይ ጉዞ ስትጀምር "ዛሬ አርብ ነው..... ቅዳሜ ዕለት ከጄነራል

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ምትኩ ጋር አገናኝሻለሁ ብለኸኝ ነበር.... ቀሪው ብርህ እንዲሰጥህ.....”
ሾፌሩ አቋረጣትና “አልሰሙም እንዴ?”
“ምኑን?”
ፊቱ ላይ ሀዘን እያጠላ “አዝናለሁ ”
“ለምን!?”
“ጄነራል ምትኩ ረቡዕ ዕለት አዲስ አበባ እንዲዘዋወሩ ተደረገ፡፡”
“አዲስ አበባ!”
“አዎ”
በቡጢ ጭኗን መታች፡፡ በንዴት ጨሳ የምትለው ጠፋት፡፡ ሆቴሉ ጋር ሲደርሱ መኪናው ቆመ፡፡ “እሺ የአዲስ አበባ አድራሻውን ታውቀዋለህ?”
“ምን አድራሻ ይኖረዋል..... ያለው ምናልባት ቤተ-መንግስት ወይም ክፍለ ጦር ጊቢ ወይም መኮንኖች ክበብ ወይም በሌላ ካምኘ ነው” በሀዘኔታም ቢሆን ትንሽ ገንዘብ እንድትጨምርለት አፉ ላይ የመጣውን ሁሉ ቀበጣጠረ፡፡

“የመስራቤት ስልክ እንኳ አይኖረውም?”
“እኔንጃ..... ካገኘሁ ግን ነገ ጠዋት ላመጣሎት እችላለሁ”
“አዎ..... እኔም ቀሪውን ዘጠኝ ሺህ ብር እሰጥሀለው”
“ከተቻለኝ እሺ”

«««««« »»»»»»

ከምሽቱ አራት ሰዓት ገደማ የክፍሏ በር ተንኳኳ፡፡ በድንጋጤ ከተቀመጠችበት ተወርውራ ተነሳችና “ማነው?” ጠየቀች፡፡ በህሊናዋ ስታስብ የቆየችው ስላነበበችው የጋዜጣ ዜና ነበር፡፡
“መኩሪያ ነኝ ”
“የቱ መኩሪያ?”
“ሾፌሩ ነኝ..... የቅድሙን እቃ አምጥቻለሁ.....”
ለመረጋጋት በረዥሙ ተነፈሰች፡፡ ከዛም ተራምዳ ከፈተችለትና እሱ መሆኑን አይታ “ግባ”
እየገባ የስልኩ ቁጥር የተፃፈበትን ወረቀት ሰጣት፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“የቤት ነው የቢሮ?”
“አዎ” አለ።

እሷ ግን አልሰማችውም ብሩን አውጥታ በመቁጠር እየሰጠችው “ለአንድ ሰው ስላደረክልኝ ነገር ትንፍሽ ብትል በገዛ እጅህ አንገትህን ሸምቀቆ ውስጥ ከተህል ማለት ነው።።”

“እረግ ምን ቆርጠኝ.....!” አለውና ብሩን ተቀብሎ ወጣ።

ሰናይትም በቀጣዩ እለት ወደ አዲስ አበባ የሚበረውን አውሮፕላን ለመሳፈር እያሰበች ወደ አልጋዋ ሄደች። እንቅልፍ ግን የማይታሰብ ነገር ነበር።

  

የማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ምዕራፍ 26

በጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ ለሊቱን ሙሉ ስብሰባ ላይ ያደሩት የአገሪቷ ከፍተኛ ባለስልጣናት እና የማእከላዊ ፖሊት ቢሮ አባላቶች ማለዳ ላይ ሲወጡ አይናቸው በእንቅፍ እጦት አብጦ ሊፈነዳ መድረሱ ያስታውቅ ነበር።

እንደሌሎቹ ሁሉ ተክለአይም ከስብሰባው በኋላ በቀጥታ ወደ ቢሮው ነበር ያመራው። ከቀን ወደ ቀን ወደ እሱ የሚተላለፉት የስራ ሀላፊነቶች እየተደራረቡ በመሄዳቸው እረፍት የለሽ ሆኗል። ቢሮው እንደደረሰ ለሀነስ እና ወዲ ሀለፎም ቢሮው እንዲመጡ አዞ በሰፊውና ውብ ቢሮው ውስጥ ግራ በተጋባ ሁኔታ ከወዲህ ወዲያ ይመላለስ ጀመረ።

የለበሰው እጀ ጉርድ ነጭ ሸሚዝ ላይ ድረስ ስላልተቆለፈ ደረቱን በመጠኑ ለዕይታ አጋልጦታል። እያጨሰ የነበረውን ሲጃራ ጨረሰና ድጋሜ ሌላ ለኮሰ። 1994 ዓ.ም. በተለይ ከግማሽ ዓመት በኋላ ውጥረቶች እየተባባሱ ሄደዋል።

ከመላው ኢትዮጵያ አራቱም ማዓዘናት ወደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ የሚላከው ተከታታይ መረጃ እጅግ አስደንጋጭና አስጨናቂ እየሆኑባቸው መጥተዋል።

በአንድ በኩል ስለ አገሪቷ ኢኮኖሚ ከጊዜ ወደ ጊዜ መውደቅ፤ በሌላ በኩል ኢትዮጵያ በጦረቤት አገሮች ጋር ሊኖራት የሚገባው ትስስርና ሰላም እየላላና እየሻከረ መሄዱ፤ የአገሪቷ የጦር ሀይል በየወቅቱ የሚያነሳው ጥያቄና ክፍፍል መስፋቱ፣ የአገሪቷ ጥንታዊና ታዋቂ የድንበር ቦታዎችን በማስጠበቁ በኩል የሚታየው እንዝላልነት፤ የስራ አጥ ቁጥር ማሻቀብ፣ የፋብሪካና ድርጅቶች ከስሮ መዘጋት፣ ስልጣናቸው የፈጠረላቸውን ሀይል በመጠቀም በጉቦ ቅሌት እየተያዙ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

በግል ጋዜጦች ላይ ስማቸው እየጠፋ ያሉ የፓርቲው ዋና ዋና አባላት ቁጥር መበራከት፣ አጠቃላይ ህገ-ወጥነት መባባስ..... ስፍር ቁጥር የሌላቸውና "ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ." ወይም "ሕ.ወ.ሓ.ት." ቀርፆ በሚንቀሳቀስበት ጠባብ የፖለቲካ ንድፈ ሀሳብ ሊመለሱ የማይችሉ ሀገር በአቀፋዊ ጥያቄዎች በጠቅላላ በትልልቅ ጥራዞች ተጠቅልለው ወደእሳቸው ቢሮ ነው የሚላኩት፡፡

ለነዚህ ሁሉ ችግሮች መፍትሄ እንዲያመጡ ኀላፊነት ከወደቀባቸው ሰዎች መካከል አንዱ ተክለአይ በመሆኑ እሱም በጭንቅት ተውጧል::

ከሁሉም በላይ እሱን ሰላም የነሳው ግን ከላይ የተዘረዘሩት ኢትዮጵያዊ ችግሮች አልነበሩም፡፡ የፓርቲውን ደህንነት የመጠበቅ ጉዳይ የሱ ኀላፊነት ስለነበር በሱ ላይ ነው ይበልጥ ያተኮረው::

በተለይ ሚያዝያ ወር ከገባ አንስቶ ማንነታቸውን በውል ባልተለዩ አካላቶች በአገሪቷ እየተካሄዱ ያሉ የአመፅ አንቅስቃሴዎች የሚመሩት በማነው የሚለው ነበር፡፡ ምክንያቱም የገዢውን ፓርቲ የስልጣን ዘመን ያሳጥረዋልና.....

ሁኔታውን ይበልጥ ያባባሰው ደግሞ ኤርትራ በኢትዮጵያ ላይ ባካሔደችው ወረራና በኋላ ላይም ጉዳዩ ዘሔግ ለሚገኘው ዓለም አቀፍ ፍርድ ቤት ተመርቶ ወራቸው በነበሩት ክልሎች ላይ ያነሳችው የይገቡኛል ጥያቄ ውሳኔው የሚሰጥበት ይኸው ወር በመሆኑ ነበር፡፡

በአገሪቷ ውስጥም ይሁን ከአገሪቷ ውጪ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ከውሳኔው በፊት እጅግ ሲሯሯጡ ነበር የሰነበቱት፡፡ ምክንያቱም አገሪቷን እየመራ ያለውና መላውን ህዝብ እወክላለሁ ብሎ ክርክሩን የጀመረው "ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ." ለፍርድ ቤቱ ያቀረበው የመከራከሪያ ነጥብና ማስረጃ የኢትዮጵያን ሙሉ አካል የማይገልፅና እስከ መጨረሻው ድረስ የባህር በር እንዳይኖራት የሚያደርግ በመሆኑ ነው፡፡

ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችም ልዩነታቸውን ወደ ጐን አድርገው ህብረት በመፍጠርና መንግስት ያላቀረባቸውንና እውነተኛውን የአገሪቷን ገፅታ የሚያሳዩ ማስረጃዎች ተደብቀው እንደሚገኙ ለህዝቡና ለዓለም አቀፉ ህብረተሰብ እንዲሁም ጉዳዩን ለያዘው የዓለም አቀፉ ፍርድ ቤት ለማሳወቅ በመሞከራቸው፤

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

መንግስትም የተቃዋሚ ፓርቲዎችን እንቅስቃሴ ለማፈን በመሞከሩ በአገሪቷ ውስጥ የመረጋጋት መንፈስ አልነበረም።

አንዳንድ የክልል ከተሞች ከዛም አልፈው ግልፅ ተቃውሞን በመንግስት ላይ እስከማቅረብ ደርሰው ነበር። ግና በረቀቀ ጥበብ እንዲታፈኑ ተደረገ።

የዘሔጉ ፍርድ ቤትም ሚያዝያ አምስት ቀን ውሳኔውን ሰጠ። የአሰብ ወደብ የኢትዮጵያ ሳትሆን የኤርትራ አካል መሆኗን አፀናው። ቀድሞውኑ የወያኔ መንግስት አግባብ ባለው መልኩ በወደቡ ላይ የይገባናል ጥያቄን አላቀረበም። ይህን ወደብ ለአንድ አገር ያለውን ጠቀሜታ የሚረዳ ቀናዒ ዜጋ ሁሉ ውሳኔውን የናቱ ሞት መርዶ የሚነገረው ያህል በሀዘን አደመጠው።

በሌላ በኩል ግን ውሳኔውን እንደ አምላካዊ ፍርድ አሜን ብሎ ለመቀበል ያላስቻለው ተቆጣ። ምክንያቱም ሰማዕት ከሆኑት አያትና ቅድም አያቱ የተረከበው የታሪክና የአገር፤ አደራና ውርስ እየፈነቀለው በመውጣቱ ተቃውሞውን በሚችለው አቅም እየገለፀ ሄዷል። ይህ ደግሞ ለመንግስት ሌላ ቁርጠት ሆኖበታል።

ተክለአይ ስለነዚህ ጉዳዮች ሲያሰላስል ከቆየ በኋላ እንዲመጡ በስልክ የጠራቸው ሀጎስ እና ወዲ ሀለፎም የቢሮውን በር ከፍተው ገቡ።

"ሀጎስ..... በርሔ አብርሃ ስለተባለው ግለሰብ ጉዳይ ምን ላይ ደረስክ?"

ከጠረጴዛው ፊት ያለው ወንበር ላይ እየተቀመጠ "ፈፅሞ በአሜሪካ ውስጥ ልናገኘው አልቻልንም።"

"እንዴት!?" ተክለአይ ጥያቄውን በንዴትና ቁጣ ድብልቅ አቀረበ።

"መልስ ልሰጥበት አልችልም..... በያንዳንዱ ግዛት ከሃምሳ የማያንሱ አፈላላጊዎችን ነበር የቀጠርኩት..... ግን ፍንጭ እንኳ ሊገኝ አልቻለም።"

"ለመሆኑ ያዋቀርከው ቡድን ብቃት እንዴት ነበር?"

"ከዓለም አቀፍ ከሆኑ ህጋዊ አፈላላጊዎች አንስቶ የማፊያ ቡድን አባል የሆኑ ግለሰቦች ጭምር በስራው ላይ ተሳትፈዋል..... ከአንድ ሚልዮን ዶላር የማያንስ ገንዘብ ያለውጤት ወጪ ሆኗል" ተክለአይ በጨበጠው ቡጢ ጠረጴዛቸውን ቁልቁል መታ። ስልኩን አነሳና

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

በከተማዋ ውስጥ ያሉትን አራት ከፍተኛ ባለስልጣናት ቢሮው ድረስ በፍጥነት እንዲመጡ አዘዙ፡፡

በአስር ደቂቃ ውስጥ ቀድመው የደረሱት በመከላከያ ሚኒስትሩ ስር የፖለቲውን ክንፍ በዋናነት በመምራት ውሳኔን የሚሰጡት ባለስልጣን ነበሩ፡፡ ማዕረጋቸው ሻለቃ ቢሆንም ጀነራሎችን ጭምር ያዛሉ፡፡ ከዛም የፖሊስ ሰራዊት ኮሚሽን ኮሚሽነር፤ የፌደራል ፖሊስ ዋና አዛዥ እና የህዝብ ደህንነት ክፍል ዋና ሀላፊ የሆኑት ባለስልጣኖች ተሰባሰቡ፡፡ ሁሉም ከትግራይ ክልል የተመለመሉና የገዢው ፓርቲ ታማኝ አገልጋይ ነበሩ፡፡

ተክለአይ የሁሉንም ትኩረት ወደሱ ከመለሰ በኋላ “ትላንት በአንድ የግል ጋዜጣ ላይ የወጣ ዜና አምብቤ ነበር” የፖሊስ ኮሚሽነሩ በአዎንታ ጭንቅላታቸውን ነቀነቁና “አዎ.....የማስተባበያ ምላሹን የሰጠሁት እኔ ነኝ” አሉ፡፡ እድሜያቸው ከሃምሳ ጥቂት ቢዘል ወይም ቢያንስ ነው፡፡ ረዥም ቁመትና ግዙፍ ሰውነት አላቸው፡፡

“ለመሆኑ ጋዜጣው መረጃውን ከማን እንዳገኘ ነግሮህ ነበር?”

“ስጠይቀው ለመመለስ አልገደድበትም ነው ያለኝ፡፡”

ወደ ህዝቡ ደህንነት ሹሙ ዞረና “በናንተ ቢሮ በኩልስ የደረሳችሁ መረጃ አለ?” ጠየቀ፡፡

ከአርባ ዓመት የወጣ እድሜ ያለው ደመ ግቡ ጐልማሳ “በወሬ ደረጃ የሚናፈሱ ናቸው እንጂ ተጨባጭ ነገር አላገኘንም” አለ፡፡

ሻለቃው ጣልቃ ገቡና “እኔ ግን ትክክል ሳይሆን አይቀርም ወደሚለው መደምደሚያ አመራለሁ.....”

“እንዴት?”

“በአገሪቷ ውስጥ ከአራቱም አቅጣጫ የሚዘገቡት ወታደራዊ መረጃዎች እንደሚያሳዩት የተኩስ ምልልሶች እየተጠናከሩ መሔዳቸውን ነው፡፡”

“የት የት ከተሞች ላይ?” አለ ተክለአይ፡፡

“በዋናነት በኦሮሚያ ክልል ውስጥ በወለጋ መስመር ትምህርት ቤቶችና መስራ ቤቶች ስራ እስከማቆም እየተገደዱ ሂደዋል፡፡”

“ኦ.ነ.ግ. ነው?”

“አይመስለኝም ሌላ ፓርቲ ሳይፈጠር አልቀረም”

“ማን የሚባል?”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“ሙሉ መረጃ የለንም፡፡ ግን ኦሮሚያን እናስገነጥላለን የሚሉ ናቸው፡፡”
“ቢሮዋቸው የት ነው?”
“ቢ..... አይታወቅም እያልኩህ! ” ቀጠሉ “በደቡብ ክልሎች ላይም አመፆች ተባብሰዋል፡፡ ወረቀቶች ይበተናሉ..... የመንግስት ወታደሮች ተገድለው ይገኛሉ..... የአስተዳደር ሰዎች ይደበደባሉ..... በሰሜን ትግራይም የዚሁ ተመሳሳይ ድርጊት ተባብሷል፡፡ በሶማሌ አካባቢም የግምባር ውጊያዎች ተጀምረዋል.....” አሉ፡፡
“መነሾው ምንድናቸው ትላለህ?”
“አላውቅም.....ግን ቅድም እንደተባለው የጋዜጣውን ዜና ትክክለኛነት ለመቀበል ተገድጃለሁ” አሉ፡፡
ተክለአይ ወደ ፌደራል ፖሊሱ ዋና አዛዥ ዞሩናም “በናንተ በኩልስ በዚህ ዙሪያ የምትሉት አለ?”
“እኛ ምን እናውቃለን የታዘዝነውን ከመፈፀም ውጪ.....” በየዋህነት መለሱ ከትግራይ ተመልምለው የመጡት ሀላፊ፡፡
“ጥሩ..... አሁን የጋዜጣውን ዜና እንደመነሻ እንውሰደውና ይህን የተባለው እርዳታ ሰጭ የውጭ አገር ድርጅት እንዴት በቁጥጥር ስር ልናውለው እንችላለን?” ሁሉንም በየተራ እያዩ ጠየቁ፡፡
“አስቸጋሪ ይመስላል.....”አለ ሀጎስ፡፡
“ሁልጊዜ ነገሮችን በዚህ ሀረግ አትክፈት!” ተክለአይ በቁጣ በግኖ ተናገረ፡፡
“ትኩረታችን በጠቅላላ ወደ እርዳታ ድርጅቶት ላይ ይዙራ” የፖሊስ ኮሚሽነሩ ተናገሩ፡፡
“እንዴት ባለ ሁኔታ?” ጠየቀ ተክለአይ ሁሉንም በየተራ እያየ፡፡
“ነጭ ለባሽ የህዝብ ደህንነት አባሎች በብዛት ይበተኑና የእያንዳንዱን ድርጅት እንቅስቃሴ ያነፍንፉ፡፡”
“ውጤት የሚያመጣ ከሆነ ይቻላል.....” የደህንነት ሹሙ በቅሬታ መለሰ፡፡ ተክለአይ ሀሳቡን ስለተረዳ “ቅሬታህን ብታስቀምጠውና ብንነጋገርበት?”
“ቅሬታ ሳይሆን እካሔዳችን ለፈጣን ጥሩ ውጤት እንደማያደርሰን ስለተሰማኝ ነው፡፡”
“ባንተ በኩል ክትትሉ ከየት ይጀመር ትላለህ?”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“ዜናው ካሳተመው ጋዜጣ ድርጅት”
“እንዴት አድርገን ማውጣጣት እንችላለን?”
“ፈቃደኛ ከሆነ በሰላም ካለበለዚያም አስፈላጊውን ሁሉ በማድረግ.....”
“ያሰብነውን ሁሉ አድርገን ምንም መረጃ ላናገኝበት ባንችልስ?”
የፖሊስ ኮሚሽነሩ ጠየቁ፡፡
“ቢያንስ አንድ አቅጣጫ ይጠቁሙናል..... ያኔ እይታችን መላ ምት ሳይሆን ያገኘውን ይዘን መፍጠን ይሆናል”
ተክለአይ ሲያስብ ቆየና “ጥሩ..... ስራውን ሁለታችሁ በትብብር ስሩታ”
የደህንነት ሹሙ “አይሆንም..... የህዝባዊ ፖሊስ አባሎች በጠቅላላ የሚታመኑ አይደሉም፡፡ እነሱ ኪስ አውላቂን ካሳደዱ በቂ ነው ፖለቲካ ነክ በሆነ ስራ ግን..... እነሱ ባይገቡበት ” አለና ሀሳቡን ሳይጨርስ አቋረጠው፡፡
ተክለአይ ሳቅ አለና “ልክ ነህ፡፡ ከፌደራል ፖሊስ አባሎች ጋር ትሰራላችሁ..... የአፈፃፀሙን መዋቅር አሁኑኑ ቅረፅና ወደ ተግባር ግባ..... የምትደርስበትን ሁሉ አሳውቀኝ እኔም ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ሪፖርት አደርጋለሁ” አለ ፡፡
ወደ ፌደራል ፖሊስ ሀላፊው ዞረናም “የሚያዝህን በሙሉ ተፈፃሚ አድርግ፡፡”
የፌደራል ፖሊስ ቢሮ ጎላፊው በእሺታ ጭንቅላቱን ሲነቀንቅ ቆየና “የሰራዊቱ አባሎች ግን ያቀረብነው ጥያቄ ስላለ እሱ ካልተመለሰ ካሁን በኋላ የወታደራዊ ደንቡን በመተላለፍ ለምንም ዓይነት ግዳጅ አንወጣም ብለዋል፡፡”
“ምንድነው ጥያቄው?”
“ፊልድ ጃኬት ይሰጠን ብለዋል፡፡”
ሁሉም በአንድነት ሲስቁ ቆዩና ተክለአይ “እንደውም በትጋት እንዲሰሩ ሙሉ ልብስና ጫማ በተጨማሪነት እንዲታደላቸው አሁኑኑ አዛለሁ” አለ የሰራዊቱ ንቃት ደካማነት እያስገረመው፡፡ በሌላ በኩልም በተራ ጥቅማ ጥቅም እየደለሉ እንዳሻቸው የሚጠቀሙበት ብቸኛ ሀብታቸው በመሆኑ ተደሰተ፡፡
ወደ ፖሊስ ኮሚሽነሩ ዞረናም “በናንተ በኩል ምንም ዓይነት እንቅፋት እንዳይገጥማቸው ተባበሩዋቸው፡፡ እንደአስፈላጊነቱ ሊያዛችሁም ሙሉ ስልጣን ተሰጥቶዋቸዋል፡፡”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ወደ ሻለቃው ዞረናም "..... በናንተ በኩልም በተቻላችሁ አቅም ችግሮች ወደ መሀከል ከተሞች እንዳይሰራጩ አግዱ። አመፁ ወዳሉባቸው አካባቢዎች ሁሉ የጦር ሀይሉ ተዘዋውሮ ይስፈርና እንዳስፈላጊነቱ ወታደራዊ እርምጃዎች ይወሰዱ።" ሲሉ አዘዘ።
ቀጠሉ "..... ማናችሁም ብትሆኑ አዲስ ችግር ወይም መረጃዎች ካገኛችሁ ወዲያውኑ አሳውቁኝ።"

ከሀጎስ እና ወዲ ሀለፎም በስተቀር አራቱ ባለስልጣን እየተጣደፉ ከቢሮው ወጡ።
ከጥቂት ደቂቃዎች ፀጥታ በኋላ ወዲ ሀለፎም "እኔ የምለው..... 1968 ማኒፌስቶ ሶስተኛው አንቀፅ....." ብሎ ፀጥ ሲል ሀጎስ ጣልቃ ገባና "አዎ..... እያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብ ከኢትዮጵያ ተገንጥሎ ወጥቶ የየራሱን መንግስት እንዲመሰርት ማስቻል የሚለው አይደል?"
ወዲ ሀለፎም ቀጠለ "አዎ..... እሱ እቅድ ባላሰብነው ወቅትና ሰዓት በራሱ ጊዜ ፈንድቶ በኢትዮጵያ ሊተገበር ይሆን እንዴ?"
"ገና ነው። ለመተግበር የሚያስችለውን የህዝብ ለህዝብ የመለያየት ስራችን በስሎ ወደማይሽር በሽታነት አልተቀየረም " አለ ተክለአይ።
"አሁኑኑ ቢጀመር ግን ውጤቱ ምን ይሆናል ብለህ ትገምታለህ?" ሀለፎም ጠየቀ
"ለተወሰኑ ዓመታቶች ህዝቡ ብሔር ለይቶ እንደ ሶማሊያ ሊጨፋጨፍ ይችላል። ግን እቅዱ ግቡን ለመምታት የሚያስችለውና የብሔረሰቦች የእርስ በእርስ ማቃቃር ስራ ገና ስር ስላልሰደደ ኢትዮጵያ ሳትይቆራረስ በአንድነት መቀጠሏ አይቀሬ ነው።"
ቀጠለ "....ነገሩን አፍነነው እየነፈረ ይቀጥላ....."
"እኔም የሚመስለኝ እንደዛ ነው።" አለ ሀጎስ ቀጠለ "አሁን የተባሉት ድርጅቶችና ግለሰቦች ከተያዙ ምን እርምጃ ይወሰድባቸው?"
"የማያዳግም ቢሆን ይመረጣል!..... በእቅዳችን ላይም ሆነ በስልጣናችን ላይ እንዲወስኑበት እድል መስጠት የለብንም። የኛ እቅድ የግላችን ብቻ ነው። በፈለግነው ሰዓት የምንጠቀምበት!" መለሰ ተክለአይ።
" በርሔ ስለተባለው ሰውዬ ጉዳይ ምን እናድርግ?" ሀጎስ ድጋሜ ጠየቀ።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“ይህ የአሁኑ የአገር ውስጥ የሰላም ችግር ረገብ ይበልና እሱን የሚከታተል ሌላ ኮሚቴ እናዋቅራለን:: አሁን በአገር ውስጥ ደህንነት ላይ እናተኩር::”
ሀሳስ ተገላገልኩ በሚያሰኝ ስሜት ተነፈስ::

«««««« »»»»»»

የዛኑ ዕለት ከሰዓት በኋላ በህዝብ ደህንነት መስራቤት ስር ጥቂትና የተመረጡ አባሎች ብቻ የሚያውቁት “ግዳይ 200” የሚባል አሳሽና አፋኝ ሀይል ተቋቋመ::

የፌደራል ፖሊስ ወታደሮችም አዲስ የሚሊቴሪ ልብስ እና ጫማ ታደላቸው:: እንዲሁም የህዝቡን ስነ-ልቦና ጥንካሬ ለመግደል በተጨማሪነት ብረት የሆነ ሔልሜት ኮፊያ እንዲያጠልቁ ተደረገና በወታደራዊ፤ የፖሊስና የመከላከያ መስራቤት ታርጋ በለጠፉ መኪናዎች ሆነው በከተማዋ ጐዳናዎች ላይ እንዲዟዟሩ ታዘዙ::

ሁሉም ሙሉ ትጥቅና ክላሺንኮቭ ጠመንጃ የያዙ ሲሆን በሚዘዋወሩባቸው ክፍት መኪናዎች ላይ ግን የተገጠሙ መትረየስ ጠመንጃዎችም ነበሩበት:: በዕለቱ አብዛኞቹ የሰራዊቱ አባላት አዲስ የታደላቸውን ልብስ እና ጫማ ወስደው ሸጡት:: ባገኙት ገንዘብም ሴተኛ አዳሪ ቤቶችን ሲያዳርሱ አመሹ:: በከተማዋ በርካታ መጠት ቤቶች ውስጥም ከሰላማዊው ህዝብ ጋር ሲጣሉ፤ ሲደባደቡ፤ ሲሯሯጡ፤ ያሻቸውን ሲፈነክቱ ሲያስሩና ሲያንገላቱ አነጉ::

አድራጐታቸውና አስተያየቻው በጠቅላላ የእናት አገራቸውን ሰላም ለማስከበር ሳይሆን አንድን አገር በቅኝ ግዛት ለመያዝ በወረራ የገባ የባዕ አገር አውሬ ወታደሮች ይመስላሉ::

እነሱ ህዝቡን በሚያዩበት የጥላቻ አተያይ መልሶ የሚያያቸው ዜጋ ከገጠማቸው ደግሞ አለቀለት:: ህይወቱን በጥይት እስከመቀጠፍ የሚያደርስ ሙሉ መብት ተሰጥቶቸዋልና::

  

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ምዕራፍ 27

የስዕል መሳያ ቀለምና የብሩሾች ዓይነቶች ከተደረደሩበት አሮጌ ጠረጴዛ ትይዩ አነስተኛ የእንጨት አልጋ አለች መስፍን አልጋዋ ላይ ጋደም ብሎ ትካዜና መረበሽ በሚፈራረቁበት ስሜት አብነትን ፍዝዝ ብሎ የሚያደርገውን ያየዋል፡፡ ከሱ አጠገብም ሁለት እስፖንጅ የለበሱ የእንጨት ወንበሮችና አንዲት አነስተኛ የመመገቢያ ጠረጴዛ ብቻ ናቸው ያሉት የቤት እቃዎች፡፡

አብነት ካናቢስ የሚባለውን የእፅ ቅጠል ፊት ለፊቱ ባለው የጠረጴዛ ልባስ ኘላስቲክ ላይ ከትንሽዬ የክብሪት ካርቶን መያዣ ውስጥ ገለበጠና የተያያዙትን ቅጠሎች በጣቱ እያፈራረሰ የእጁን ሰዓት ተመከለተ፡፡ ከምሽቱ 3፡52 ደቂቃ ብሏል፡፡

ስራ ባልያዘው የግራ እጁ ድሬድ አድርጎ ያሳደገው ፀጉሩን ከግምባሩ ላይ ወደ ኋላ መሰለ፡፡ የተያያዘውን የዕፅ ቅጠል በሚፈልገው ሁኔታ አላቆ ካበቃ በኋላ ከሸሚዙ የደረት ኪስ የኒያላ ሲጃራ የሚታሸግበትን መያዣ አወጣ፡፡ ውስጡ የነበሩትን ስድስት ሲጃራዎች ገልብጦ አልሙኒየም ልባስ ያለውን የውስጥ ማሸጊያ ወረቀት አወጣና ዘረጋጋው፡፡

ከዛም በወረቀቱ በኩል ምራቁን እያስነካ በመጠኑ ካረጠበው በኋላ አልሙኒየም የለበሰው የወረቀቱ አካል ወደ ውጪ እንዲሆን አድርጐ አጣጠፈውና የግራ እጁ መዳፍ ላይ አስቀምጦ ለአጭር ደቂቃ በቀኝ እጁ ጠበጠበው፡፡

መልሶ እኩል የሆነ አንድ እጥፋት እስኪቀረው ድረስ ፈታታውና በጐን በኩል የላይኛውን ጫፍ ጠርዝና ጠርዝ ላይ በመያዝ ወደ አፉ አስጠግቶ ትንፋሹን በረጅሙ ነፋበት፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

በቅፅበት የአልሙኒየም ልባስና ወረቀቱ ተላቀቁለት፡፡ እጥፋቱን ከፍቶ የአልሙኒየሙን ጫፍ በመያዝ ከወረቀቱ ላይ ሙሉ በሙሉ ካለ ችግር ልጦ አነሳውና ጨምድዶ ወደ ቤቱ በር ስር ወረወራት፡፡

ስሏ ወረቀት ደረቅ እንድትል እያራገፋት ቆየና በቁመቷ በኩል እኩል እያካፈለ ሶስት ቦታ ቆራረጣት፡፡ በሶስቱም ቁርጥራጮች ላይ የካናቢሱን ቅጠል አደረገባቸውና እንደ ሲጃራ ባለ ሁኔታ ጠቀለላቸው፡፡

“ስማ አብነት..... ”

“ወዬ..... ”

“ያንን ስዕል ስለህ ጨረስከው ወይስ ተውከው?”

“የቱን?”

“በቀለም መተረክ የሚል ርዕስ የሰጠኸውን ስለ ኢትዮጵያዊነት ተናጋሪ ያልከውን”

“ተውኩት... ”

“ለምን? ”

“በልቤ ውስጥ ያለውን እውነታ ቀለም ብቻውን ሊገልፀው አልቻለም፡፡ የኢትዮጵያን ታሪክ በስዕል ልትስለው ከፈለክ መጠቀም ያለብህ ንፁህ የሰው ልጅ ደምን ብቻ ነው፡፡ ከሱ በስተቀር ችሎ የሚገልፀው ሌላ ቀለም የለም፡፡ ” ከጠቀለለው ሀሺሽ አንዱን አንስቶ በመለኮስ ጭሱን በረጅሙ መማግ ጀመረ፡፡ እየማገ ከሚያስገባው ጭስ ውስጥ ቅንጣት ታህሏን እንኳ መልሳ በአፉም ይሁን በአፍንጫው እንድትወጣ እድሉን አይሰጣትም ነበር፡፡

እሳቷ ጣቱን እስክትለበልበው ድረስ አጢሶ ጨረሰና ቁራጯን ከሲሚንቶ የተሰራው የቤቱ ወለል ላይ ጥሎ ረገጣት፡፡

እንደዘወትሩ ሁሉ የእፁ ጢስ የሚፈጥርለት ስሜት ይበልጥ በሰውነቱ ከመሰራጨቱ በፊት እንዳይወጣበት “ታኮ” ብሎ የሚጠራውን አንድ ሲጃራ ለኩሶ ማጨስ ጀመረ፡፡

የስዕል ትምህርቱን ካጠናቀቀ ሶስት ዓመት አልፎታል፡፡

ሲጃራውን ጨርሶ አጠፋውና ጣቱን ወደ ጭንቅላቱ በመስደድ ጮፍሮ በወፍራሙ ከተገማመደው ድሬድ ፀጉሩ መሀከል አንደኛውን

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

በመምዘዝ እያፍተለተለ ዛሬ ሊሰራው ስለወሰነበት የስዕል ጭብጥ ማሰላሰል ጀመረ።።

ቀድሞ ርዕሱ ምን መሆን እንዳለበት አመነ።። “መጪውን ቀን መፍራት” በዝቅተኛ ድምፅ ተናገረና ከመቀመጫው ተነስቶ ሁለት ሜትር በአንድ ከሀምሳ የሚሆነውን የመሳያ ጨርቅ ወደ ወጠረበት የቤቱ ግራ ጐን አመራ።።

ኮሳሳው ሰውነቱ አንድ ሜትር ከሰማንያ ሶስት ከሆነው ቁመቱ ጋር ሲታይ ጐስቋላ ህይወትን የሚገፋ ባይተዋር አስመስሎት ይታያል።።

ቀጠን ብሎ ረዘም የሚለው የፊት ቅርፁ ላይ የደፈረሱት ትንንሽ አይኖቹ ጐልተው ይታያሉ።። ስልክክ ካለው አፍንጫው ስርም በሲጃራና በሀሺሽ ጢስ የጠቆሩ ወፋፍራም ከንፈሮች አሉት።።

ፀይመው የሚታዩት ሰርጓዳ ጉንጮቹ መቆረጥ ካቆመ ሁለት ዓመታትነ ባስቆጠረው የተያያዘ ፂሙ ተሸፍነዋል።። ፈገግ ሲል ሰፊ ክፍተት ያለው ፍንጭት ጥርሱ እንደመወየብ ብለው ይታያሉ።።
በለሆሳስ ሲራመድ የሃያ ሰባት ዓመት ወጣት ሳይሆን የአርባ ዓመት ጐልማሳ ይመስላል።።

አብስትራክት የሆነ የአሳሳሉን ዘይቤ የሚያደንቁለት በርካታ አፍቃሪዎች አሉት።። ግን ገቢውን ለመደጐም እንዲችል የመግዛት አቅሙ የሌላቸው ብቻ ናቸው።።

ሽራው ጋር እንደደረሰ አጠገቡ ካለ ጠረጴዛ ላይ አንድ ብሩሽ አነሳና በረጃጅም ጣቶቹ መሀከል እያመቻቸ አስቀድሞ በቀኙ በኩል ስዕሉ የሚጀመርበትን ዕለት ሚያዝያ 25/1994 ብሎ ፃፈ።።

ቀሪው የቤቱን አካል የያዘው ተጀምረው የተጠናቀቁ በርካታ ስዕሎች፣ የተቀዳደዱ አቡጀዲዎች፣ ለመወጠሪያነት የሚሆኑ ቀጫጭን ጣውላዎች ለቀለም መጥረጊያነት የዋሉ በርካታ ቡቱቱዎች ያልተጠናቁ ጅምር ስዕሎች እዚም እዛም ወዳድቀው ይታያሉ።።

ይቺን ጠባብ ክፍል ቤት ተከራይቶ የሚኖርበት አካባቢ ከዋናው የፖስታ ቤት መስራቤት ጀርባ በኩል አምባሳደር አካባቢ ነው።።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

ከሁሉም በላይ ፍቅርን ያከብራል፡፡ በቃ በሱ እሳቤ ውስጥ 'የተፈጥሮ ሀይል ታምቆ ያለው ፍቅር ውስጥ ብቻ ነው፡፡ በፍቅር አተያይ፣ በፍቅር አስተሳሰብ፣ በፍቅር ግንዛቤ ውስጥ ብቻ ማለፍ ቢቻል ምድራችን ከሰማይ በታች ያለች ሌላ ሰማይ ለመሆን በቻለች ነበር፡፡' ይላል፡፡

በማሰላሰል ጭልጥ ብሎ ከቆየበት ስሜት እንደ መባነን አለና ተራምዶ የመሳያው ሽራ አጠገብ ባለው ጠረጴዛ ላይ ሁለት ሻማዎችን ለኮሰ:: በምስራቅ አቅጣጫ የተሰራውን የቤቱን ጠባብ መስኮት ከፈታት፡፡

ሁለተኛውን የካናቢስ ጥቅልል አንስቶ ለኮሰና አጢሶ ሲጨርስ ለመሳል የሚያነሳሳው ድባብ ተጫጫነው ብሩሹን ጨብጦ ለፍቅር ተምሳሌትነት የሚሆነው መነሻ እያሰላሰለ ቆየና እይታውን ድንገት ከመስኮቱ ውጪ ተጓዘ፡፡

ጨረቃ ሙሉ ክብ ሆና ታየችው፡፡

"አዎ ለክብ ቅርፅ ልዩ መውደድ አለው ክብ ነገሮች በአመዛኙ መውደድን፣ ቻይነትን፣ በጐነትን መግለፅ ይችላሉ ብሎ ያምናል" ለራሱ ተናገረ ቀጭኗን ብሩሽ ከተበጠበጡት ቀለሞች መሀከል በአንደኛው ላይ አጥቅሶ የተወጠረው ሽራ ላይ ማሳረፍ ጀመረ፡፡

መስፍን አልጋው ላይ ሲቁነጠነጥ ቆይቶ የካርል ማርክስን ወፍራም ጥራዝ መፅሀፍ አንስቶ ማገላበጥ ጀመረ::

አርባ ሁለት ደቂቃዎች ሲያልፉት አብነት ከፍተኛ በሆነ የተመስጦ ማዕበላዊ መነሻው ጋር ደርሶ ነበር፡፡

"ስማ አብነት..... "

ከስድብ በማይተናነስ ቅላፄ "ምንድነው ስራ ላይ ነኝ....." ተነጫነጨ

"አንድ ያልነገርኩህ ነገር አለ"

"ምንም ነገር መስማት አልፈልግም አሁን!" አለው ትኩረቱን ሳይበታትን

"የግድ መነጋገር አለብን "

"ሰውዬ ልስራበት! ወሬ ካማረህ ውጣና ወይዘሮ እልፌ ቤት ጠብቀኝ:: ስጨርስ እመጣለሁ::" ገንዘብ የሌላቸው ቀን በዱቤ ካቲካላ የሚጠጡበት ቤት ነበር::

መስፍን ቀና ብሎ አልጋው ላይ በመቀመጥ ሲጋራ መለኮስ ሲጀምር አብነት እንደማይተወው አወቀና ብሩሽና ቀለም ማዋሀጃ አትሮኖሱን

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ጠረጴዛው ላይ ወርውሮ በማስቀመጥ እያፈጠጠበት "የሙድ ሌባ ነህ እሺ! ደባሪ! "
መስፍን ቁጣውን ከቁብም ሳይቆጥረው መናገር ቀጠለ "የትላንቱን ዜና እንዲያትምልን ያስደረግነው የጋዜጣ ድርጅት ታሸገ፡፡ ሰራተኞቹም በጠቅላላ ከያሉበት ታፍሰው ወዴት እንደተወሰዱ አይታወቅም!"
"መቼ !?"
"ዛሬ አስራ አንድ ሰዓት አካባቢ....."
"የድርጅቱ ባለቤትስ?"
"ጋሽ መርድ በአሜሪካ ያሉት የኢትዮጵያውያን ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ያዘጋጁት ስብሰባ ላይ ለመሳተፍ በአጋጣሚ ትላንትናውኑ ለሊት ነበር የተጓዙት፡፡"
"ብራቮ..... አመለጡዋቸው!"
"ምን ያመልጡዋቸዋል" አለ መስፍን
"እንዴት?"
"ሚስታቸውን እንደ ማሲያዣ አስረዋቸዋል፡፡"
አብነት በንዴት ተወራጨና "ምን ዓይነት መንግስት ነው!?..... ባል በሰራው ሚስትን፤ ልጅ ባጠፋው እናትን እየያዘ በእስር የሚያሰቃየው....."
"ማን ይጠይቀዋል ብለህ ነው..... ከፈለገ ሊገላቸውም ይችላል፡፡"
"ለመሆኑ ከመታሰራቸው በፊት ያቀረቡላቸው ጥያቄ ነበር?"
"ከሰጠናቸው ዜና ጋር የተያያዘ እንደሆነ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ነኝ..... ምክንያቱም የዛን ዕለት ለጋሽ መርድ ዜናውን እንዲሰሩበት ጥቆማውን ስሰጣቸው ከባድ አደጋን ሊያስከትል እንደሚችል ስጋታቸውን ገልፀውልኝ ነበር፡፡ እናም ምናልባት መረጃውን ከየት አመጣችሁ ለማለት ይሆናል" አለ መስፍን፡፡
"ጦሱ ገና ወደ አንተም ይመጣላ"
"ምኑን አውቄ....." አለ በረዥሙ አየር እየሳበ፡፡

"ጋሽ መርድ መጥተው ከሚታሰሩ በዛው እንዲቀሩ ቢነገራቸውስ?..... ሌሎቹ እንደሆን አንተ ስለመስጠትህ ምንም መረጃ የላቸውም፡፡"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“ጋሽ መርድ ናቸው የሚቀሩት.....! ያውም ሚስታቸው ታስረው.....! እርግጠኛ ነኝ እስካሁንም በራሳቸው ሚስት አስደውለውላቸው እንዲመጡ እያስገደዱዋቸው ይሆናል”
“እሳቸው ከመጡማ እውነታውን ተናግረው ሊያሲዙህ ይችላሉ!” አለ አብነት በጭንቀት ተውጠ፡፡
“ነገሩ ከእውቀቴ በላይ ነው፡፡” አለ ግራ በተጋባ ሁኔታ መስፍን፡፡
“የምመክርህ ከምትያዝ ለምን ስራህንም አቁመህ እንድትሰወር ነው፡፡”
“አልሰወርም”
“ለምን?”
“በሌላ በኩል ተሰወርኩኝ ማለት ሰናይት ያመጣችው የሉዊስ እቅድ በዚች አገር ላይ ተፈፃሚ ይሆናል ማለት ነው፡፡”
“ካልተሰወርክ ደግሞ ይህ መንግስት ወይም ራሳቸው የነሰናይት ሰዎች ሊያስወግዱህ ይችላሉ፡፡” ቀጠለ እያፈጠጠበት “ በዚህ ምድር ላይ ስትኖር የመጀመሪያ ዓላማህ መሆን ያለበት ራስህን በህይወት ማኖር መቻል ነው፡፡ እንድትሞት የሚያስገድዱህ አንድ ሺህ ምክንያቶችን መዘርዘር ይቻላል፡፡ እንድትኖር የሚያድርግህን ምክንያት ግን አንተው ብቻ ነህ ፈልገህ ማግኘት ያለብህ፡፡ ”
“በኔ ምክንያት እኮ ነው ሁሉ ሰው እየተጉላላ ያለው፡፡”

“ሞኝ አትሁን፡፡ ሄደህ ብትያዝ ይገሉሀል..... የአንተ አስፈላጊነት ያለ ውጤት ያበቃል፡፡ ለተወሰነ ጊዜ ተደበቅና ሁኔታውን ለማክሸፍ በድብቅ እንሯሯጥ፡፡ ያሰብነውን ከፈፀምን በኋላ ቢገሉህ እንኳ ባለ ድል ሆነህልና እንደሞትክ አይቆጠርም፡፡”
“እነ ሰናይት እንኳ ይነኩኛል ብዬ አልሰጋም፡፡ ለሚስጥሩ ማፈንገጥ ብቸኛው ተጠርጣሪ እኔ ብቻ ልሆንባቸው አልችልም፡፡ ምክንያቱም እርዳታ በሚደረገለት በአንዱ ፓርቲ አባል በኩል አፈተልኮ ነው ብለው ሊያስቡ ይችላሉ፡፡ ባይሆን በዚህ መንግስት.....”
“ጋሼ መርድ የቤትህ አድራሻ ያውቁታል?”
“ስልኬን እንጂ ቤቱን አያውቁትም”
“ያው ነው ይታወቃል ማለት ይቻላል፡፡” አለ አብነት መፍትሔ ለመሻት እየጣረ፡፡
መስፍን መናገር ቀጠለ “ሰሞኑን ከየ አንጃዎቹ በተመረጡት መሪዎች ስም የተዘጋጀ የጦር መሳሪያዎቹን የመረከቢያ ሰነድ እንደሚላክ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ሰናይት ነግራኝ ነበር፡፡ ቢያንስ ሰነዱን በእጄ አስገብቼ ነው መሰወር ያለብኝ"
"እንግዲህ እስከዛ እኔ ጋር ትቀመጣለህ"
"የተሻለ አማራጭ እስከሌለ ድረስ....." አለ፡፡
አብነት ግን አልሰማውም፡፡ ከራሱ ጋር ሲሟገት ቆይቶ ቀና አለና "ኧረ እግዚያብሔር ሆይ ምን ዓይነት የጭንቅ ዘመን ላይ ፈጠርከን?" ብሎ በምሬት አንገቱን ቁልቁል ደፋ፡፡
ጥቂት ቆይቶም ወንበር በመሳብ ከመስፍን ፊት ለፊት እየተቀመጠ "ለመሆኑ እሷ ከባህርዳር ተመለሰች?"
"አልተመለሰችም..... ዜናውን ከጋዜጣ ላይ ካነበበችው ግን እንደምትመጣ እርግጠኛ ነኝ፡፡ ቢያንስ እንኳ ትደውልልኝ ነበር ባታነበው ይሆናል እንጂ....."
"ጥሩ ሁለተኛው እርምጃችንን ከነገ ጠዋት ጀምሮ መቀጠል አለብን"
"የቱን?" አለ መስፍን
"የህቡእ አንጃዎቹን መሪዎች በመንግስት የተደረሰባቸው አስመስለን በስልክ እየነገርናቸው እንዲጠፉ ማስደረጉን"
"ግን ለምን የእውነት ለመንግስት ጠቁመን አናሲዛቸውም!" መስፍን ጠየቀ፡፡
"አይሆንም! በፊትም ተነጋግረን ተማምነንበታል፡፡ ለመንግስት ያለንን መረጃዎች በጠቅላላ ብንሰጥ እቅዱን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥሮ ለማክሰም የሚያስችል አቅምም ብቃትም ሆነ በተለይ እውነተኛ የሆነ ልባዊ ፍላጐት የለውም፡፡ ምናልባት የስልጣን ዘመኑን ለማራዘም ሲል ብቻ ለጊዜው እንዲዳፈን ሊያስደርግ ይችላል እንጂ፡፡ ምክንያቱም ራሱ መንግስት ኢትዮጵያን አንድ ለማድረግ ሳይሆን ለመበታተን ያለውን ፍላጐት ስልጣን ከያዘ ማግስት አንስቶ ዛሬም ድረስ በጉልህ እያራመደ ያለው ዓላማው ነው፡፡"
"እና እንደጀመርነው ብቻችን እንታገል?" አለ በተዳከመ ሁኔታ፡፡
"አዎ..... የዚህ ትውልድ ሀላፊነት የተጫነው በራሱ በዚሁ ትውልድ ላይ ብቻ ነው፡፡ እኛ የዚህ ትውልድ አንዱና የወቅቱ አካል ነን፡፡ ነገሮች ከአቅማችን በላይ እስኪሆኑ ድረስ በራሳችን ጥበብ እቅዱን ለማክሸፍ እንዋጋቸዋለን፡፡"
"እነሱ እኮ ብዙ ነገር አላቸው፡፡ ገንዘቡና መሳሪያው በእጃቸው ነው"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“ወንድሜ ገንዘብ ከሚያፈረጥመው ጡንቻ ይልቅ እውነተኛ የአገር እና የወገን ፍቅር የሚፈጥረው ሀይል እጅግ የላቀ ውጤት ያመጣል..... በአንድ ወቅት ላይ እነሱም እኮ መሳሪያም ገንዘብም የላቸውም ነበር። ከምንም ነው የተነሱት እናም ለዚህ የደረሱት። ሌላው ደግሞ የወያኔ ትልቁ ችግር እነሱን አርግዞ የወለደው ብሶት እና ትግል ሌላውን ማርገዝም መውለድም ያቆመ ነው ብለው ማመናቸው ነው” አለውና እያየው ቀጠለ “.....አገርን ስለመምራት ሆነ ስለ ኢትዮጵያ ታሪክ እናውቃለን ብሎ የሚኮፈሰው ይሄን መንግስትና በዙሪያው ሆነው የሚያጨበጭቡለትን አባላቶቻቸውን ተዋቸው..... ተወቃሽ እስክትሆን ድረስ ስህተትን የማይነግርህ ትውልድ ነው ከላይህ ተጭኖህ ያለው።”

በዝምታ ጥቂት ቆዩና “ጥሩ እንግዲህ ነገ ጠዋት እየደወልን እናስደንግጣቸው” አለ መስፍን።

“አዎ.....ቢያንስ ለተወሰነ ጊዜ እንዲሸሹ ማድረግ መቻል ቀላል አይደለም።” ቀጠለ አብነት ሰለ አንጃዎቹ መሪዎች እያሰበ “.....በጣም የሚያሳዝነው የነሱ ራስ ወዳድነት መገለጫ ማጣቱ ነው። ስልጣን ለመከፋፈል ሲሉ በሚፈጥሩት አስከፊ ሁኔታ ህዝቡ ደግሞ ዳቦ ለመከፋፈል ሲል እርስ በራሱ እንደሚጨራረስ ሳያውቁት ቀርተው አይደለም። ግና የወላፈኑ ፍንጣሪ ስለማይደርስባቸው ስለ ህዝብ ምን ገዶኝ በማለት እንጂ.....”
“ምን ታደርገዋልህ በተለይ በኛ ዘመን ሁሉም ነገር ቅጥ እያጣ ሄደ።”
“አዎ..... ይህን ትውልድ ለማምከን በየቦታው የማይደረግበት ነገር የለም። ገዢዎቻችን ልጆቻቸውን በአውሮፓና አሜሪካ ከህዝብ በሚዘርፉበት ገንዘብ እንደላቀው እያስተማሩና እያኖሩ እዚህ ያለው የጭቁኑ ህዝብ ልጆች ግን የጫት ቤት፣ የመጠጥ ቤት፣ የዝሙት ቤት እንደ ዳቦ ማደያ በየ አዳሩ እንዲስፋፉላቸው ይደረጉላቸዋል። እውቀታቸው እንዲዳብር አይፈለግም። የባህል ማዕከልና ቤተ-መፅሀፍን ማዘውተር እንደ ገዳይ በሽታ ተደርጐ ይሰበክላቸዋል። እንደዚህ ዓይነት ተቋሞች እንዲስፋፉ አይፈቀድም እንደውም ያሉት ጥቂቶቹም እንዲዘጉ የማይደረግባቸው ድብቅ ሴራ የለም።.....

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“.....ታዲያ እንዴት ነው ከዚህ አገዛዝ ሰውን የመሰለን ሳይሆን ሰውን የሆነ ትውልድ ማግኘት የሚቻለው?.....”
መስፍን በዝምታ ያዳምጠዋል፡፡
ቀጠለ አብነት “.....ጭራሽ ህዝቡ የሚበላው ማጣቱን፣ የሚለብሰው ማጣቱን፣ መጠለያ አጥቶ የጦዳና ህይወት መግፋቱንና ማህይምነቱን አገራዊ ሀብቶቹ እንደሆኑ አምኖ እንዲቀበላቸው ተገዷል.....

“.....በሌላ ጐን ነጋ ጠባ ጐሰኝነትና ዘረኝነት፤ ምቀኝነትና ጥላቻ ብቻ እንዲሰርፅበት ከሶስት ሺህ ዓመት በፊት ስለነበረችው ሰፊና አንድ ኢትዮጵያ ሳይሆን ባለፉት አንድ መቶ ዓመት ውስጥ ተሀድሶ አድርገውላት በእነሱ ስለተገኘችው ኢትዮጵያዊት አገር የሀሰት ስብከት እየተነገረው አድሮ ሚፈነዳ የጐሰኝነት ፈንጂ በልቡ ይቀበርበታል፡፡” አለ አብነት፡፡

መስፍን ጥርሱን በመንከስ ሲሰማው ቆይቶ “እንዲህም ሆኖ ግን ዛሬም አገሩን ከህይወቱ አስበልጦ የሚወዳት ትውልድ መሆኑን አሳይቷል፡፡ ኤርትራ ዛሬ ጫካ ፈጥሮ በተፋቸው አውሬ ሽፍቶች ሴራ ብትቆረጥም ዛሬም ድረስ የኢትዮጵያዊነት ስሜትና ገፅታዋን አላጣችም፡፡ ወደፊትም ቢሆን በፍፁም አታጣውም፡፡”
ቀጠለ “.....ሆን ብለው ወንድምን ከወንድሙ አባትን ከአማቹ ደም አቃቡት፡፡ ግና ኢትዮጵያዊነት ይቅር ባይነትም ነው:: ዛሬ ጊዜው ባይፈቅድ እንኳ መጪው ትውልድ ጉልበት ለጉልበት ተሳስሞ በሰይጣናዊ እልልታ የተገነጠለችውን ግዛት በመልአክት ሽብሻቦ ከናቷ እንደሚያዋህዳት እርግጥ ነው፡፡” አለ፡፡

አብነትም በስሜት ተውጦ አቋረጠውና “አዎ.....” አለና ለዛች ክልል መገንጠል ስኬት ተብሎ ለጦርነቱ የተመመውን አፍላ ሀይል እያሰበ “ለዚህች የሀበሻ አገር እድገት ስንት ተዓምር መስራት የሚችል የወጣት ጭንቅላት በቦምብ በፈንጅና በጥይት ተበረቃቅሶ በየአለቱ ላይ እየተፈጠፈጠ ደምና አንጐሉ ተደባልቆ ፈሰሰ..... ስንቱ ገላው ከእቶን ባልተናነሰ እሳት ተጠብሶ የከሰለ ቆሮቆንዳ መሰለ.....የስንቱ አንጀት እንደ ተተለተለ ቱባ ክር መሬት ላይ ተዘርግፎ ቀረ.....

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ስንቱ ነፍሱ ሳትወጣ በጥንብ አንሳ መንጋ ተበጫጭቆ አለቀ..... ስንቱስ እጅና እግሩን፤ ዓይኑን አጥቶላት ለዚህች ደሀ አገር ሌላ የወጣት ተጧሪ ሆኖ ቀረ..... ይሄ ሁሉ ግን ለመንግስታቶቻችን በአንድ ቲአትር ቤት ውስጥ ከሚቀርብ ምርጥ የቀልድ ተውኔት እጅግ በላቀ ሁኔታ እያሳቃቸውና እያዝናናቸው እንቅልፍ የሚያስተኛቸው ጨዋታ ብቻ ሆኖ ቀረ.....”

ቀጠለ እያሰበ “.....ይህ ሁሉ መስዋዕትንት ለልማት ቢውል ኖሮ አገራችን የአንድን ታላቅ ትውልድ መገንቢያ ባገኘች ነበር.... በጦርነቱ የወጣው ወጪ የስንቱን ወጣት መጪ ራዕይ እውን ማድረግ በቻለ ነበር..... ስንቱን ምሁር ከፍልሰትና ከስደት ባዳነ ነበር.....” በማለት እየተቀባበሉ ቢወራ ቢወሪ የማያልቀውንና ሆነ ተብሎ በገዢዎቹ የሚፈጠሩላትን የዚህች አገር የመቆርቆዝ መንስኤ እየተወያዩ የለሊቱ እኩሌታ እስኪያልፍ ቆዩ።

«««««« »»»»»»

የአብነትና የመስፍን ትውውቅ የተጀመረው በነሱ ሳይሆን በወላጆቻቸው ነበር። ሁለቱም ተወልደው ያደጉት ፈረንሳይ ለጋሲዮን እየተባለ በሚጠራው ሰፈር ነው።ሁለቱም የተገኙትም ደግሞ ከችግረኛ ቤተሰቦች ሲሆን ሁለቱም አሁን ለሚተዳደሩበት ሙያ በራሳቸው ጥረት ነው የደረሱት።

በጉርብትና የሚተዋወቁት ወላጆቻቸው ከህፃንነት ጀምሮ ቄስ ትምህርት ቤት አስገቧቸው። ከዛም የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አብረው በመማረ አጠናቀቁ። አስራ ሁለተኛ ክፍል ግን ለያያቸውና መስፍን ወደሚያዘነብልበት የጋዜጠኝነት ትምህርት ሲገባ አብነት ደግሞ ጣቶቹ የተፈጠሩት ለስዕል ነበረና የስነ-ጥበብ ትምህርት ቤት የሰጠውን ፈተና በቀላሉ አልፎ ገባና አራት ዓመታት በመማር በዲግሪ ተመርቆ ወጣ።

ተቀጥሮ የመስራት ፍላጐት ስላልነበረው ለስዕል ስራውና ለጎን ማሳረፊያነት በቂ የሆነች አንዲት ክፍል ቤት በርካሽ እየተከራየ ስራውን ቀጠለ።መጀመሪያ አካባቢ የስዕል ሙያ እጅግም

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ባልዳበረበት ኢትዮጵያ ውስጥ በሱ መተዳደሩ አስቸጋሪና ፈታኝ ሆኖበት ነበር፡፡ በኋላ ላይ ግን የኢትዮጵያን ጌጣ ጌጥና የባህል እቃዎች ለሚሸጡ ሱቆች በብራና በሸራና በእንጨት ላይ እየሰራ በሚያቀርብላቸው ባህላዊና ሀይማኖታዊ ጭብጥ ባላቸው ስራዎቹ እየተወደደ ሄደ፡፡

በእርግጥ ገቢው አሁንም ቢሆን አጥጋቢ አይደለም፡፡እንደዛም ሆኖ ደግሞ ገንዘብ አያያዝ አይችልበትም፡፡ በተለይ ሰው ተቸግርኩ ሲል አይወድም፡፡ ያለውን ገልብጦ ይሰጣል፡፡ ከዛም ለኑሮዬ የሚጎለኝ ነገር በሙሉ 'ለሙያዬ የሚከፈል መስዋዕትነት ነው' ብሎ ያምናል፡፡

««««««« »»»»»»»

ማለዳ ላይ መስፍን ነበር ቀድሞ ከእንቅልፉ የነቃው፡፡
"አብነት..... አብነት....."
"እ.....ወይ....."እየተገላበጠ መለሰ
" ተነስ....! "
"እሺ....." የተያያዘ ጮፈሬ ፀጉሩን ከፊቱ ላይ ወደ ጮንና ጮን እየመለሰ "ሰዓቱ ስንት ይሆናል?"
"አንድ ሊሞላ ነው፡፡"

ሁለቱም ከጠባቧ አልጋ ላይ ሲወርዱ ለብሰው ያደሩት ሱሪዎቻቸው መጨመዳደዱን አዩ፡፡ ፊታቸውን ታጥበው ካበቁ በኋላ ሱሪዎቻቸውን ቁልቁል በመዳፋቸው እንደመቦረሽ አደረጉና ቤቱን ቆልፈው ወጡ፡፡

የህዝብ ስልክ ለማግኘት ወደ ቀኛቸው ታጥፈው አስር ደቂቃ ያህል እንደተጓዙ የፍልውሃ መግቢያ ጋር የተንጠላጠሉ ስልኮች ጋር ደረሱ፡፡

መስፍን ሳንቲም ከቶ መጀመሪያ የተጫናቸው ቁጥሮች በትግራይ ላይ እንቅስቃሴ የሚያደርገው በርሔ ጋር ነበር፡፡ ያነሳችው ሴት "የለም" ብላ ዘጋችበት፡፡ ሁለተኛ ሂርጳ ጋር ደወለ እሱም ለትንሽ ቀደም ብሎ ወጣ ማለቱ ተነገረው፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“ሰዎቹ የጋዜጣውን ዜና አንብበው ሳይደበቁ አልቀሩም መሰለኝ” አለ የሶስተኛውን ሰው ቁጥር እየተጫነ፡፡
ስልኩ ሲነሳ “አቶ ጳውሎስ ይኖሩ ይሆን?”
“ማን ልበል?” ሴት ነበረች ጠያቂዋ
“አስቸኳይ ለሆነ የስራ ጉዳይ ተፈልጌ ነው.....”
በመጠራጠር ቅላፄ “ይ.....ጠብቁ” አለችውና ስትጣራ በስልኩ ውስጥ ተሰማው፡፡
“አቤት?”
“አቶ ጳውሎስ ?”
“አዎ..... ማን ልበል?”
“እ..... በድብቅ እያንቀሳቀስክ ስላለው ፓርቲህ እየሰለለች መረጃ ለመንግስት እያቀበለች ያለችው ሰው አደጋ ውስጥ ልትጥልህ ጥቂት ቀርቶዋታል፡፡”
“ስለ..... ስለምንድነው የምታወራው..... የምን ፓርቲ.....ለ.. ለመሆኑ ማነህ አንተ?”
“ማንነቴን አልነግርህም....”
አቋረጠውና “ልዘጋው ነው”
“ትችላለህ..... ከደቂቃዎች በኋላ ግን የፖሊስ ሰንሰለት በእጆችህ ይጠልቁልሀል”
“ልታስፈራራኝ ባትሞክር ጥሩ ነው”
“እሱን ለማድረግ መብት የለኝም”
“እሺ.....ቆይ ታውቀኛለህ?”
“በደንብ ነዋ.....የ “ህዝበ ደቡብ ነፃነት ሀይል” መስራችና አባል”
ጳውሎስ ጀርባውን ሲረጥበው ተሰማው፡፡
ቀጠለ መስፍን “.....ወደ ፍሬ ነጥቡ እንግባ ሰናይት የምትባል ሰው አደጋ ላይ ልትጥልህ ጥቂት ቀርቷታል፡፡”
“ሰናይት!”
“አዎ”
“ይ.....ይህን ስም አላው.....ቀውም”
“ፖሊሳዊ ምራመራን እያደረግኩብህ አይደለም፡፡ ግን ተጠንቀቅ..... ብትችል እርጃም አስውስድባት ወይም ራቃት” አለውና ስልኩን ጆሮው ላይ ዘጋበት፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ጳውሎስ ግን መነጋገሪያውን እንደያዘ ደርቆ ቀረ።
“ምነው ምን ሆንክ?” ሚስቱ ጠየቀችው።
“እኔንጃ.....እ.....”
አጠር ብላ ወፍራም የሆነችው ሚስቱ በትልልቅ አይኖቿ እያፈጠጠችበት “ምንድነው ያሉህ?”
እሷን ትቶ የስልኩን ቁጥሮች ማዞር ጀመረ።መስመሩ ሲከፈት “ሻለቃ ነህ?”
“አዎ.....”እንቅልፍ በተጫነው ሁኔታ መለሰለት።
“ጳውሎስ ነኝ..... ችግር ተፈጥሮብናል.....” በከምባትኛ ቋንቋ መነጋገር ጀመሩ።
ሻለቃው የአርባ ሁለት ዓመት ሰው ሲሆን በፌደራል ፖሊስ ቢሮ ውስጥ የልዩ ተወርዋሪ ሰራዊት ዋና አዛዥ ሆኖ እያገለገለ ያለና እሱም በድብቅ ለ “ህዝበ ደቡብ ነፃነት ሀይል” የሚሰራ የድብቅ ሰው ነበር።
“ምንድነው ችግሩ?” ጠየቀ ከእንቅልፉ በደንብ ነቅቶ
“ሰናይት የተባለችው ሴትዮ የመንግስት ሰላይ ሆና ተገኘች”
“ምን!?”
“ቅጥረኛ ሰላይ.....”
“አለቀልን በለኛ”
“ይመስለኛል”
“ማነው የነገረህ?”
“ከማላቀው ሰው በደረሰኝ የማስጠንቀቂያ የስልክ ጥሪ ነው”
“ምን አለህ?”
“በአጭሩ ልታሲዘኝ ጥቂት እንደቀራት ነው የገለፀልኝ”
ሻለቃው በዚህ ጊዜ “ግዳይ 200” ተብሎ በመንግስት ስለተቋቋመው ልዩ ሀይል በጨረፍታ የሰማውን አስታወሰ።
ቀጠለ ጳውሎስ “.....አሁን በቀጥታ ጠፍቼ ወደ ትግል ሰዎች መመለስ አለብኝ” አለ።
“ቆይ መጥፋት የለብህም.....” መለሰለት። ሀሊናው ግን ‘ “ግዳይ 200” የተባለው ሀይል የሚከታተለው ስራ ከዚህ ጋር የተያያዘ ይሆን?’ በማለት እያሰበ ነበር።
“እና ምን ላድርግ.....ልያዝ!?” በፍርሃት ጮሆ ጠየቀው።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“አይደለም.....ዛሬ ቅዳሜ ነው..... ልጆችህና ሚስትህን ይዘህ ከቤትህ አካባቢ ተሰውረህ ዋል። ጉዳዩ በትክክል ከተደረሰበት እንድንይዝህ የምንላከው እኛው ነን። እውነት ሆኖ መጥተን ካጣንህ ማታ ላይ ቤት ወይም ቢሮዬ ደውለህ ታጣራና ነግሬህ ትጠፋለህ። ካለበለዚያ ግን ችግር መፈጠሩን እርግጠኛ እስክንሆበት ድረስ ትቆያለህ።”
“እንዴ.....ቢይዙኝስ?”
“ነገርኩህ እንድትያዝ ከተፈለገ የሚታዘዘው የኔ ክፍል ነው። የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽን ነው ይህን የሚሰራው ቢባል እንኳ ቀድመን ስለምንሰማ እነግርህለውኝ።”
ጳውሎስ ባልተዋጠለት ስሜት “እሺ” አለ።
ቀጠለ ሻለቃው “.....ለመሆኑ ቤቷን ታውቀዋለህ?”
“የማን?”
“የሰናይትን ይቺ ውሻ?”
“አዎ.....አንዴ አብረን ሄደን አይቼዋልሁ።”
“የት ነው?”
“በድሉ ህንፃ ላይ.....አምስተኛ ፎቅ.....” ክፍሉን ጭምር ዘርዝሮ ገለፀለት።
“በጣም ጥሩ ሳትቀድመን እንቀድማታለን።”
“ለመንግስ የምትሰራ ከሆነ እኮ ጫፏ ጋር መድረስ አይቻልም”
“ዋናው መገኘቷ ነው። ከዛ የሀሰት ምክንያት መደርደር ነው።”
“ምን ልታደርግ?”
“በአንዲት ጥይት የዘላለም በድን አደርጋታለሁ” ብሎ ዛተና የስልኩን መነጋገሪያ ቦታው መለሰ። እየተቻኮለ ተነስቶ ልብሱን ማጠላለቅ ጀመረ።

  

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ምዕራፍ 28

ሰናይት ከባህርዳር ተነስታ አዲስ አበባ የገባችው ቅዳሜ አምስት ሰዓት ላይ ነበረ፡፡ የአየር መንገዱን ተጓዦች መቆጣጠሪያ መውጫ እንዳለፈች ከፊት ለፊት የተንጠላጠሉ የህዝብ ስልኮች አየችና ወደ አንደኛው በማምራት የመስፍን መስራቤት ደወለች፡፡ ጋዜጣው ዜናውን ከማን እና እንዴት አግኝቶ ማተም እንደቻለ እርግጠኛ ሆና ይሄ የምትለው ሰው ባይኖርም የመጀመሪያ ተጠርጠሪዋ ግን መስፍን ነበር፡፡

የወንድ ድምፅ “ ስራ አልገባም” አላት፡፡

“ከመቼ ጀምሮ ነው ያልገባው?”

“እ.....ከትላንት ከሰዓት ጀምሮ ነው፡፡”

“አሞት ይሆን?”

“እርግጠኛ አይደለሁም”

“አመሰግናለሁ፡፡”

ዘጋውችና ወደ መኖሪያ ቤቱ ደወለች፡፡

“ሀሎ.....” የትልቅ ሴት ድምፅ ነበር፡፡

“መስፍን ይኖራል?”

“ኧሪ ልጄ ትላንት እንደወጣ አልተመለሰም፡፡”

እናቱ መሆናቸውን ገመተችና “በሰላም ነው ግን?”

“እኔ ምን አውቄ.....ግራ ገብቶኝ ተቀምጫለሁ፡፡”

“ከመጣ መልዕክት ይነግሩኛል?”

“ምን ብዬ.....”

“ሰናይት ደውልልኝ ብልሀለች ብለው፡፡”

“በጀ”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

መነጋገሪያውን ቦታው መልሳ ጉዞ ስትጀምር አደጋ እያነጣበበባት እንዳለ ጥርጣሬዋ እየጨመረ መጣ፡፡

ሁኔታዎች ከቁጥጥሩ ውጪ ከመሆናቸው በፊት አንድ ነገር መፍጠር እንዳለባት ብትገነዘብም ጠብ የሚል የመፍትሔ ሀሳብ ማግኘት አልቻለችም፡፡

'ለማንኛውም ሁሉንም ነገር ለፒየረ ሪፖርት ማድረግ አለብኝ' ብላ አሰበች፡፡ በፋክስ የምትልክለትን ፅሁፍ ለማዘጋጀት ታክሲ ይዛ በድሉ ህንፃ ላይ ወደተከራየችው ቤቷ አመራች፡፡

እቤት እንደደረሰች ግን ፅሁፉን ከመጀመሯ በፊት ከመለመለቻቸው የአንጃ መሪዎች ጋር መነጋገር ፈለገችና የሷ ባልሆነ ስምና አድራሻ ተመዝግበው እንድትገለገልበት ከተዘጋጁላት ሲም ካርድ መካከል አንዱን አውጥታ ሞባይሏ ውስጥ በመክተት መጀመሪያ ጳውሎስ ጋር ደወለች፡፡ ስልኩ ለረዥም ደቂቃዎች እየደጋገመ ቢጠራም የሚያነሳ ሰው አልነበረም፡፡ ጥርጣሬዋ ወደ ፍርሃት እየተለወጠባት መጣ፡፡

ቀጥሎ ሂርጳ ጋር ደወለች፡፡

"ሀሎ....."

"አቶ ሂርጳን ነበር?"

"ነኝ ማን ልበል?"

"ሰናይት ....."

"እህ..... አንችው ነሽ እንዴ..... ?" ሰላምታ ተለዋወጡ፡፡ ለጥቂት ቀናት በስራ ምክንያት ከአዲስ አበባ እንደምትወጣ ነግራው ነበር፡፡

ሂርጳ "አንቺ በቀደም ጋዜጣ ላይ የተፃፈውን ዜና አንብበሽው ነበር?"

"አዎ....." አለች ሰናይት በረዥሙ እየተነፈሰች፡፡

"ምንድነው? ማነው መረጃውን ያሾለከው? ወይስ ሌላ ድርጅት ይህን ስራ የሚሰራ ተቋቁሟል ማለት ነው?"

"እኔም እንዳንተው ግራ ገብቶኛል..... ግን የገጠማችሁ ችግር ነበር? ወይም የሰማኻው ፍንጭ አለ?"

"ለነገሩ እስካሁን ደህና ነን፡፡ በግሌ ጥንቃቄ ጨምሬያለሁ፡፡" አለ ሂርጳ

"ጥሩ አድርገህል፡፡"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“የመሳሪያውን ጉዳይ ምን ላይ አደረሽልን?”
“ዛሬ እስኪ.....የሁኔታዎች ዝርዝር እጠይቃቸዋለሁ”
“ቶሎ በሉ በያቸው እንጂ”
“እሺ.....እሺ.....ለማንኛውም ወደ ማታ ደውዬ ውጤቱን እነግርሀለውኝ ምናልባት ስለ ጋዜጣው ዜና አዲስ ነገር ከሰማህ ስለ ምንጩ አጣራልኝ” ብላው ተሰነባበቱ፡፡
ቀጥሎ በርሔ ጋር ደወለች፡፡ ሴት ነበረች ያነሳችው “ሀሎ”
“አቶ በርሐ ይኖር ይሆን?”
“ማነዎት?”
“ሰናይት በይልኝ?”
በርሔ ውጪ አድሮ ገና መግባቱ ነበር፡፡ ቀርቦ “ሀሎ”
“ሰናይት ነኝ”
“ቧ.....አንቺ በሰላም ነው የጠፋሺው?”
“ነግሬህ አልነበረም እንዴ ለአንድ ጉዳይ ጉዞ እንደነበረኝ”
“ታዲያ መች እቆያለሁ አልሽኝ?”
“አጋጣሚ ስራ በዝቶ ነው፡፡”
“በጧት ላይ ደውለሽ ያጣሽኝ አንቺ ነሽ?”
“አይደለሁም”
“ቤት አላደርኩም፡፡ ስልክ ፈልጐኝ እንደነበረ ሲነግሩኝ አንቺ መስለሽኝ ነው፡፡” አለና ፋታ ሳይሰጣት ቀጠለ “ጉዳዩ ምን ላይ ደረሰ?”
“የትኛው?”
“የመሳሪያው እርዳታ ነዋ.....ከሶስት ቀናት በፊት ከአስመራ ባለስልጣናት ጋር ተነጋግሬ ነበር፡፡”
“አስመራ ሔደህ?”
“ኧረ እዚሁ አዲስ አበባ..... ከወያኔ ጋር ሚስጥራዊ ስብሰባ ነበራቸው፡፡ በዛው በሚስጥር ተገናኘንና አነጋግረውኝ ሄዱ”
“እሺ..... ምን አሉህ?”
“የወታደር ማሰልጠኛ መሬት ሊሰጡኝ ተስማምተናል”
“በጣም ጥሩ!”
“ምን ዋጋ አለው ታዲያ?”
“እንዴት?”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“ገንዘብ፣ መድሀኒት፣ ማሳሪያ.....ምናምን.....ምንም የለንም”
“ቶሎ እንዲላክላችሁ አስደርጋለሁ።።”
“ሌላ ያልነገርኩሽ..... በነሱ ወደብ እንድጠቀም ስለፈቀዱልኝ በምፅዋና አሰብ በኩል እንዲገባልን አስደርጊ”
“አስቸጋሪውን ስራ አቃለልክልን።።”
“መቼ ይደርስልናል ታዲያ?”
“እ.....ከሰዓት በኋላ ደውዬ እነግርሀለው”
“እሺ”
“ቻው” ስልኩ ተዘጋ።።

በሌላም በኩል ግማሽ የኢትዮጵያ ግማሽ የሶማሊያ ዜግነት ካለው አቡበከር መሀመድ ጋር መስራት የሚጀመርበት ሰዓት መቃረቡን አሰበች።። እንደነገራት ከሆነ የሶማሊያ ወደብ በሆነው በበርበራ በኩል ያሻውን ነገር ማስገባት እንደሚችል ነው።። ከዛም አልፎ አካባቢውን ከሚቆጣጠሩት ከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ጋር መፍጠር በቻለው የጥቅም ተስስር በኢትዮጵያ ምስራቃዊና ደቡባዊ ክልልሎች ውስጥ የፈለገውን ነገር በህገ-ወጥ መንገድ ማዘዋወር እንደሚችል አረጋግጦላታል።።
አዲስ ለተፈጠሩት እና የትጥቅ ትግል በማካሄድ የመገንጠል ጥያቄን ላነገቡት ሁለቱ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች “ኦ.ሊ.ን.” እና ለ “ህ.ደ.ነ.ህ.” ተዋጊዎች በሶማሊያ በኩል የሚገባው የጦር መሳሪያ ካለ ችግር ሊከፋፈላቸው እንደሚችል እርግጠኛ ሆናለች።።

አቡበከርን ስለ ቀጣዩና ወሳኙ ተግባራቸው በስልክ ከምታዋራው ይልቅ በአካል ቤቱ ድረስ ሔዳ ልታወያየው ወሰነች።።

ቀጣዩን የስልክ ጥሪ የጄነራል ምትኩ ነበር።። ይህ ጥሪ ከተሳካ የሷም ስራ ወደ መገባደዱ እንደሚቃረብላት አሰበች።።
ከባህርዳር ይዛ የመጣውችን የጀነራሉን ቁጥር ፈልጋ አወጣችና መደወል ጀመረች።።
ከተደጋጋሚ ሙከራ በኋላ ስልኩ ተነሳ።።
“ጄነራል ምትኩን ነበር?”
“ከየት ነው?”
“ከዚሁ ነው ከአዲስ አበባ ፈልጌያቸው ነው።።”
“እ.....እኔ ነኝ ማን ልበል?” አለ ጄነራሉ።።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

ሰናይት በቀጥታ መስመር ልታገኘው በመቻሏ በጣም እየተደሰተች “ሰናይት ነኝ”
“ሰናይት.....?ሰናይት.....?”
“ሰናይት ባህርዳር ተገናኝተን የነበርነው?”
“አላስታወስኩሽም..... ከጥቂት ቆይቶ በኋላ “አው..... አስታወስኩሽ .....ይቅርታ” ቀጠለ ቀዝቀዝ ባለ ሁኔታ፡፡ አጭር ሰላምታ ተለዋወጡና “አዲስ አበባ በመለወጥህ የተሰማኝን ደስታ ልገልፅልህ ፈልጌ ነው፡፡”
“አመሰግናለሁ፡፡.....ስልክ ቁጥሬን እንዴት አገኘሽው?”
“አምላክ ከልብ የምፈልገውን ነገር ሁሉ እንዳገኝ አድርጎ ስለፈጠረኝ ይሆናላ” በዛው ፈጥና ቀጠለች “ለደስታችን ድምቀት ምሳ ልጋብዝሃ.....”
“አልችልም..... ከአሁን በኋላም ደግመሽ በመደወል እንዳትቸግሪ..... እኔ ትንሽ ስራ የሚበዛብኝ ሰው ነኝ”
“ይቅርታ የዚህን ያህል የረበሽኩህ አልመሰለኝም ነበር፡፡” አለች የቅያሜ በመሰለ ቅላፄ፡፡
ጄነራሉም የእረፍት ስሜት አደረበት፡፡
በዚህ ቅፅበት ሰናይት ደግሞ ‘ከአሁን አሁን ስልኩን ጠረቀመብኝ’ እያለች ታስብ ነበር፡፡
“አይደለም .....ስለእረብሻ ምናምን ነገር ሳይሆን..... ስራ በጣም ይበዛብኛል”
“መቼም ምሳ ለመብላት.....”
“ለስብሰባ መሔዴ ስለሆነ ነው፡፡ ከመጣሁ ጀምሮ ለግል ጉዳዬ የሚሆነኝን ፋታ አልሰጡኝም”
“ምንም ችግር የለም፡፡ ወደ እራት ልናዞረው እንችላለን.....”
ጄነራሉ ለሰከንዶች በዝምታ ቆየ፡፡ ልብ ቀጥ የሚያደርገው የውበቷ ምስል በህሊናው ውልብ አለበት፡፡ “በነገራችን ላይ እግረ መንገድም የማዋራህ ጥቂት ጉዳይ ስላለኝ ነው ”
“እ.....ሺ....፡፡ ማታ ሁለት ሰዓት ላይ ከኦሎምፒያ ወደ መስቀል ፍላወር በሚታጠፈው አስፓልት መቶ ሃምሳ ሜትር ገባ እንዳልሽ በስተቀኝ በኩል “ብሉ ፐብ” የምትል ቤት አለች፡፡ እዛ እንገናኝ”
“ሌላ ቦታ.....”
አቋረጣትና “ሰዋራ ቤት ስለሆነች እዛ እንድንገናኝ ፈልጌ ነው፡፡”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“እሺ”

ቀጣዩ ስራዋ ለፒየር የሚላክለትን ፅሁፍ ከወቅቱ ሁኔታ ጋር እያሰባጠረች ለመፃፍ መዘጋጀት ጀመረች። አስቀድማም ስትደውልበት የቆየችው ሲም ካርድ አውጥታ በመሰባበር መፀዳጃ ቤት ሲንክ ውስጥ ጣለችውና ውሃ ለቀቀችበት።

እስክሪኘቶውን አስቀምጣ ተነሳችና ወደ መስኮቱ በመጠጋት እይታዋን በመኮቱ በኩል ወደ ሰንጋተራ መንደሮች ላከችው። የዛገ ጣሪያ ያላቸውና ቅጥ ባጣ ሁኔታ ችምችም ያለው መንደር ይታያል።መልሳ ወደ ጐዳናው አፈጠጠች። ልቧ መራዱን አላቆመም።

ወደ ጠረጴዛዋ ተመለሰችና ፅሁፉን ለመቀጠል ሞከረች። መንፈሷ ግን ‘ሂጂ’ እያለ የሚያዛት መሰላት። ግን ወዴት? መልስ አልነበራትም። የጀመረችውን ስራ መጨረስ እንዳለባት አምና መፃፊያውን አነሳች።

ሁለት ደቂቃ ያህል እንዳለፉ የዋናው በር ሲንኳኳ ተሰማትና ቁልፉ ተከፈተ። አፓርታማውን በደባልነት ያከራየቻት ሴት ነበረች። ከዱባይ ከተመለሰች አምስት ቀን ሆኗት ነበር።

“ሀይ.... ሰኒ ቤት ነሽ እንዴ?”

“ሀይ ሳምሪና..... ከሆነ ቦታ መጥቼ ደከመኝና ቤት ለማረፍ መጣሁ።”

“እኔ ራሴ እንዴት እንደከመኝ ብታይ..... ዛሬ ማታ ተመልሼ ወደ ዱባይ ስለምበር ጓደኞቼ ካልጋበዝንሽ ብለው ለሊቱን ሙሉ ሲያሽከረክሩኝ አደሩ... ኡፍ..... ” በድካም የዛለ ሰውነቷን አልጋዋ ላይ ለማሳረፍ ወደ መኝታ ቤቷ በር እየተመለከተች።

“ውይ እጠይቅሻለሁ ብዬ.....?” አለች ሳምራዊት

“ምን ?”

“ተመልሼ የምመጣው የሚቀጥለው ወር ስለሆነ የቤት ኪራይ ብር ካለሽ ብትሰጭኝ ለጉዞዬ እጠቀምበት ነበር?”

“አዘጋጅልሻለሁ።”

ሳምራዊት የመኝታ ቤቷን በር ቁልፍ ከፍታ እየገባች ንግግሯን ቀጠለች

“....ዛሬ ደግሞ ምን እንደፈለጉ አላውቅም በጊቢው ውስጥ ፖሊሶች እየተግተለተሉ ነው።”

“የቱ ጊቢ?”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“የኛው የህንፃ ጊቢ ነዋ” ብላት ወደ መኝታ ቤቷ ገብታ በሯን ዘጋችና አልጋዋ ላይ ከነልብሷ በድካም ተዘረረች።

ሰናይት የሰማችው ነገር ልክ በልጅነቷ ተገዳ ስትበላው መላ ጭንቅላቷን እያናወጠ እንደሚሰነጥጣት የበቆልት ሰናፍጭ ውስጧን አናወጠው። ደመ-ነፍሷን ተነሳችና ሳምራዊት ሳትሰማት ቀስ ብላ በፍጥነት ወደራሷ ክፍል በማምራት አንዳንድ ጠቃሚ ያለቻቸውን እቃ በጥድፊያ በማንሳት ለመፃፊያነት የተዘጋጁትን ወረቀቶች ጨምራ በመያዝ ድምፅ ሳታሰማ ከቤት ወጣች። ወደ መውረጃው ደረጃ መጓዝ እንጀመረች እይታዋ በመተላለፊያው መስኮቶች ባንደኛው ቁልቁል ወደ ጊቢው ተወረወረ። ከሃያ የማያንሱ ሙሉ ትጥቅ ያነገቡና ብረት ኮፊያ ያደረጉ የልዩ ሀይል ፖሊሶች ወደ ህንፃው መግቢያ ሲጣደፉ አየች።

ስለሷ መረጃ እንደደረሳቸው ቅንጣት ታህል አልተጠራጠረችም የምታደርገው ጠፋት። ወደፊት እና ወደኋላው እንደመመላለስ አለች። ይህን ቤቷን ከጳውሎስ በስተቀር ማንንም እንዳላሳየች አሰበች። እሱ ሊጠቁምብኝ ይችላል ብላ ለማመም የሚያስቸላት ፍንጭ ማግኘት ግን አልቻለችም። ከዚህ በላይ ስለ ጠቋሚው ሰው ማንነት ለማሰብ ጊዜው ስላልነበረ እራሷን ለማስመለጥ ማሰብ ቀጠለች።

ዝም ብላ አትወርድ ነገር ደረጃው ላይ መገናኘታቸው ነው። አሳንሰርም እንዳትጠቀም ምናልባት እየመጡበት ባይመጡበት እንኳ ታች መውጫው ላይ ጠባቂዎች እንደሚያቆሙ አሰበች።

የሻለቃነት ማዕረግ ያለውና የፌደራል ፖሊሶቹ አዛዥ እየመራቸው አንደኛ ፎቅ ላይ ደረሱ።

ከጳውሎስ የተነገረውን የቤቱን ክፍል ቁጥር እንዳልተሳሳተ እርግጠኛ ነበር። በለበሰው ፊልድ ጃኬት የውስጥ ኪሶች ደብቆ የያዛቸው እቃዎች እንዳይታዩበት እየተጠነቀቀ በችኮላ ወጣ። እንደሀሳቡ ቢሆን ኖሮ ተፈላጊዋን ሴት አድኖ በመግደል የሚስጥሩን ፍንጭ ድምጥማጡን ሊያጠፋው ያቀደው ገና በማለዳ ነበር። ከቤት ወጥቶ መስራቤቱ እንደደረሰ ግን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወደ ውጪ ሊሄዱ በመሆኑ ከቤተመንግስት ቦሌ ድረስ መንገዱን በመዝጋት ቁጥጥር የሚያደርገውን ክፍል እንዲመራ ታዘዘ።

እሱን ሲጨርስ በፌደራል ፖሊስ ዋና ሀላፊ ትዕዛዝ ተወርዋሪ ፖሊሶችን ይዞ ሌላ ግዳጅ ወጣ። እንደገናም ከህዝብ ደህንነት ሹሙ ድንገት የተጠራ ስብሰባ ላይ ከሌሎች አራት ባለስልጣናት ጋር “ግዳይ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

200" ተብሎ የተሰየመው የአዳኞች ጉዳይ ለመወያየት ለአንድ ሰዓት ተኩል ያህል መቆየት ግዴታ ሆነበት፡፡ በስብሰባው ላይም ሌላ ተጨማሪ ውሳኔ ተላለፈ፡፡

ውሳኔው ሻለቃው ካለ አንዳች ተጠያቂነት ሰናይንት ካለ ቅድመ ሁኔታ ጭንቅላቷን በጥይት መፈርከስ መቻሉን አረጋግጦለታል፡፡

እነሱ ሁለተኛውን ፎቅ ማለፍ ሲጀምሩ ሰናይት በደመ ነፍስ ወደ ኋላዋ ተመለሰችና ዞራ መሮጥ ጀመረች፡፡ ከዛም ወደ ቀኙ መታጠፊያ ጋር ደረሰች፡፡ በአለቻት ቅፅበት ህይወቷን ለማዳን ከፈለገች አንድ መላ መፍጠር ግዴታዋ ሆነ::

የሰው ቤት አስከፍታ በመግባት ልትደበቅ አሰበች፡፡ 'ቢፈትሹስ እየዞሩ' አለች ለራሷ፡፡

የህንፃው መታጠፊያ አካባቢ ለአደጋ ጊዜ መውጫ እንዲሆን በብረትና መስታውት የተሰራ በር ከበሩም አልፎ ከህንፃው የውጭኛው አካል ጋር ተያይዞ በብረት የተሰራ የመውረጃ ደረጃ ታያት:: ያላት ብቸኛ አማራጭ እሱ ነበር፡፡ ተጠጋችውና በአካባቢዋ ሰው ያለመኖሩን አረጋግጣ መስታውቱን በርግጫ መታችው፡፡ ተሰባብሮ ወደቀ፡፡ ሾልካ መውጣት ስትጀምር በርቀት የኩቴና የሚንኮሻኮሽ ብረት ድምፅ ተሰማች፡፡

በዚህ ወቅት ላይ ከጊቢው መውጣትም ሆነ መግባት በር ላይ በቆሙት ታጣቂዎች ተከልክሎ ነበር::

ሰናይት ወደ ታች ልትወርድ አሰበችና ታች የቀሩ ካሉ እንደሚያይዋት ገመተች፡፡ ወደላይ መውጣት ነው የሚሻለው፡፡ በዛው ቅፅበት የማምታቻ ሀሳብ ውልብ አለላት፡፡

የያዘቻቸውን የማይጠቅሙ ወረቀቶች በደረጃው ላይ ቁልቁል በተነቻቸቸው፡፡ከዛም በተቻላት ፍጥነት የህንፃው አናት ላይ ለመድረስ ወደ ላይ መገስገስ ጀመረች፡፡

በሻለቃው እየተመሩ የክፍሉ በር ጋር የደረሱት ታጣቂዎች ቦታ ቦታ ይዘው ትእዛዝ መጠበቅ ጀመሩ:: ሻለቃው ሽጉጡን አውጥቶ አቀባበለና በሩን እንዲያንኳኳ አጠገቡ ካሉት መሀከል ወደ በሩ የቀረበውን ታጣቂ በዓይኑ ምልክት ሰጠው፡፡

አንዱ ለማስከፈት በሩን በመዳፉ ተረተር ደጋግሞ መታው፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ቅጥ በሌለው የድፍረት ማንኳኳት የተናደደችው የሰናይት አከራይ ገና ካሸለበችበት እንቅልፏ እንደመባነን እያለች "ማነው!? ቀስ አትልም!" በቁጣ እየተነጫነጨች ተነስታ በመምጣት በሩን ስትከፍት የተነጣጠረው ሽጉጥ ተኩስ ድምፅ በህንፃው ውስጥ አስተጋባ።።

ሳምራዊት ወደኋላዋ ተዘረረች።። ከግምባሯ የሚንዠቀዠቀው ደም ፊቷን እያጨማለቀ ወለሉ ላይ መሸኳለል ጀመረ።።

ሻለቃው በስራው ውጤት በደስታና በእርካታ ተሞላ።። ፖሊሶቹ ተሯሩጠው ገቡና ክላሻቸውን በየ አቅጣጫው እያነጣጠሩ ክፍሎቹን በማየት ሌላ ሰው እንደሌለ አጣሩና አለቃቸውን እንዲገባ ነገሩት።።

ሻለቃው በቀጥታ በሩ ተከፍቶ በሚታየውና የሟች ነው ብሎ ወደ ገመተው ክፍል ገባ።። በውስጥ ኪሶቹ ደብቆ የያዛቸውን ጥቅልሎች እያወጣ በፍጥነት ማንም ሳይደርስበት መከፋፈት ጀመረ።። ጥቅልሎቹ ውስጥ በሌላ ግዳጅ ላይ አግኝቶዋቸው ደብቆ ያስቀመጣቸውና ወንጀል የተሰራባቸው ሁለት ሽጉጦች ከሁለት ከፍተኛ ጉዳት ማድረስ የሚችሉ ክላስተር ፈንጂዎች ነበሩ።። የእጁን አሻራ በአልጋ ልብሱ ጫፍ ጠረግ ጠረግ አደረገና የአልጋው ራስጌ ስር ከተታቸው።። ከዛም ለመቃኘት ያህል የግባ አስመስሎ ዙሪያውን እየቃኘ ወጣ።። ሌሎቹንም ክፍሎች እየተዟዟረ አየና "ፍተሻ ጀምሩ!" ሲል አዘዘ።።

የቤቱን እቃ ምንቅርቅሩን አወጡት።። እሱም የሚያግዛቸው ለማስመሰል ተፍተፍ ማለት ጀመረ።። መኝታ ቤቱን ሲፈትሹ የነበሩት ሁለት ታጣቂዎች ሻለቃው የደበቃቸውን የጦር እቃዎች ሰብስቦ አመጡና በኩራት አሳዩት።። እሱም በሟች ላይ "ግዳይ 200" ተፈፃሚ ለማድረግ የተጠቀመበት ዘዴ እንደሰመረለት አረጋገጠ።። የተገኙትን ሽጉጦች እና ክላስተር ፈንጂዎች ለበላይ አለቆች ወስዶ ማስረከብ.....።።

አንድ ሌላ ፈታሽ የሟችን ቦርሳ ይዞ በመውጣት ፊት ለፊታቸው መሬት ላይ ዘረገፈው።። ከውስጡ ፓስፖርት፤ ጥቂት ዶላሮች እና የኢትዮጵያ ብሮች፤ የቀበሌ መታወቂያና መጋጌጫ ቁሳቁሶች ታዩ።። ሻለቃው መጀመሪያ ፓስፖርቱን ቀጥሎም መታወቂያዋን አውጥቶ እያገላበጠ በማየት ስሟ « ሳምራዊት አለበል» እንደሚል ማንበብ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

እንደጀመረ በድንገጤ ፈዞ ቀረ፡፡ የገደላት ሰው ሰናይት ሳትሆን ሌላ ግለሰብ እንጂ....፡፡

ድንጋጤው እንዳይታወቅበት ወደ ኮሪደሩ ወጣና በሰራው ስህተት ተበሳጨ፡፡

ሌሎቹ የፌደራል አባላቶች ግን አንድ አደገኛ ተጠርጣሪ ሰው እንደሚያድኑ ነው እንጂ ሟች ተፈላጊዋ ትሁን ወይም ሌላ ሰው ምንም የሚያውቁበት ፍንጭ አልነበረም፡፡ ሬሳ አንሺና ተጨማሪ መረጃ መርማሪ አካል እስኪደርስ ድረስ በበሩ አካባቢ ሲመላለስ ቆየና ወደ ቀኝ አቅጣጫ ተጉዞ የህንፃው መታጠፊያ ጋር ሲደርስ የተሰባበረ መስታወት አየ፡፡ ወድያውኑ በዚህ እንዳመለጠቻቸው አወቀ፡፡

“ሂይ.....በፍጥነት ኑ.....ያመለጠ ሰው አለ!”

በበሩ አካባቢ ቆመው ከነበሩት መሀከል ስድስት የሚሆኑት ተሯሩጠው ደረሱለት፡፡

“በዚህ በኩል ያመለጠ ሰው አለ!” ቀድሞ ሾልኮ ወጣና ወዴት እንደሄደች ለማወቅ ምልክት ሲፈልግ ወደታች የተበታተኑ ወረቀቶች አየ፡፡ “ኑ!” ሁሉም በተሰበረው በኩል እየሾለኩ ወጡ፡፡ “እ.....ለማንኛውም ሁለት ሰው ወደ ላይ ይውጣና ይፈልግ፡፡ አራታችሁ ተከተሉኝ!” አለና ሽጉጡን መዞ በፍጥነት ቁልቁል መውረድ ጀመረ፡፡

ወደላይ የሚወጡት ሁለቱ የተቀባበለ ክላሺንኮቫቸውን አፈሙዝ እያስቀደሙ የህንፃው አናት ላይ ደረሱ፡፡ ላዩ ሜዳ ሲሆን መሀከል አካባቢ ቤት መሳይ የህንፃው አካል ቁጭ ብሎ ይታያል፡፡ አልፎ አልፎ የውሃ ማጠራቀሚያገንዳዎች እና የታጠበ ልብስ ማስጫ ብረቶች ይታያሉ፡፡ ሌላው የህንፃው ጣሪያ ግን ፀድቶ ቁልጭ ያለ ነበር፡፡

ፖሊሶቹ ተፈላጊውን ሰው በቤት መሳዩና በገንዳዎቹ ዙሪያ ፈለጉት፡፡ ግን አልነበረም፡፡ ደጋግመው ዙሪያ ገባውን ተመለከቱ፡፡

ሰናይት በዚህ ጊዜ ከህንፃው ጣሪያ ሁለት ሜትር ወደ ላይ ርቆ በመሰቀል የሚያገለግል የብረት ምጣድ ቅርፅ የነበረው ሰፊ ዲሽ ላይ በመውጣት በዮጋ እስፖርት ዳብሮ የሚተጣጠፍ ቀጭን አካሏን ለጥፋበት ተደብቃ ተኝታ ነበር ::

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“ወደዚህ ማንም አልወጣም” ከዲሹ ስር ያለው የፌደራል ፖሊስ ለባልደረባው ሲነግረው ሰማችው፡፡
ሌላኛው “ ዝም ብሎ ነው የሚያስለፋን” አለ በተሰላቸ ቅላፄ፡፡ እያወሩ ለመውረድ መንገድ መጀመራቸውን ድምፃቸው እየራቀ ሲሄድ አወቀች፡፡ እሷ ግን ለአንድ ሰዓት ያህል ካለችበት ሳትንቀሳቀስ ተቀመጠች፡፡ ሻለቃው ስለ ጉዳዩ ምንም የማያውቁ የህንፃውን ሰላማዊ ነዋሪዎች ቤት ሲያስስ በጥያቄ ሲያስጨንቅ እና ሲያተረማምስ ቆይቶ ምንም ሲያጣ እንዳመለጠቻቸው በማመን ወጥቶ ሄደ::
ሰናይት ካለችበት ወርዳ ታጥቦ የተሰጣ ረዥም የሀበሻ ቀሚስ ከነነጠላው አውርዳ በመልበስ ማንም ሰው እንዳይለያት ተሸፋፈነችና ከህንፃው ጊቢ በመውጣት በደመ ነፍስ መጓዝ ስትጀምር ማንም ልብ ብሎ ያስተዋላት አልነበረም:: አካሏ በድንጋጤ ዝሏል:: ወደ ቄራ የሚሄድ ታክሲ ተሳፍራ ስትጓዝ ጭምር ምንም አታስተውልም ነበር:: በቃ ከአካባቢው መራቅ እንዳለባት ብቻ ነው የምታስበው፡፡
ራሷን ለማረጋጋት እየጣረች ቡልጋሪያ እየተባለ የሚጠራ አካባቢ ወረደች፡፡ በዛው አካባቢ በስተቀኝ በኩል መንገዱ ዳር በሚገኝ አንድ ኬክ ቤት በረንዳ ላይ ተቀመጠችና ቡና አዘዘች፡፡
ከጥቂት ደቂቃ በኋላ እድሜው ከአስር የማይበልጥ የጐዳና ተዳዳሪ ወደሷ ቀረበና “ የዳቦ መግዣ?”
“ሂድ ከዚህ!” አምባረቀችበት፡፡
ታዳጊው ደንግጦ ወደ ኋላ አፈገፈገና መንገድ ሲጀምር ሰናይት ስሜታዊ በመሆኗ አፍራ በዙሪያዋ የነበሩትን ሰዎች አማተረች፡ ጥቂቶቹም በትዝብት እያዩት ነበር፡፡
እሷም በህሊናዋ ‘ችጋራም ህዝብ! ከችጋር በስተቀር አንድም ነገር የማይታይበት ሁላ!’ እያለች በጥላቻ መሳደብ ቀጠለች::

  

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ምዕራፍ 29

ፈጠን ያለ ምት ያለው የእንግሊዝኛ ሙዚቃ በጠባቧ ቡና ቤት ውስጥ ጮልቶ ይሰማል፡፡ ውስጥ ያሉት ጠጪዎች በአመዛኙ የጉልምስና እድሜ ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡ ራቁት ከመሆን ያልተናነሰ አልባሳት ያገለደሙ ወጣት እንስቶች የወሲብ ስሜት በሚቀሰቅስ ሁኔታ ወዲህና ወዲህ ሲመላለሱ የውበታቸው ሀይል መናፍስት ሳይቀር የሚያስቱ ይመስላሉ፡፡

እጅግ በደበዘዘ ብርሃን የተዋጠው መጠጥ ቤቱ ከግማሽ አካል እንደ መጋረጃ የተሰራላቸው መስተናገጃዎች አለው፡፡ በአንደኛው ውስጥ ጀነራል ምትኩ የአዘቦት ልብስ ለብሶ በመምጣት አንዲት እድሜዋ አስራ ዘጠኝ ዓመት የሆናት ወጣት ሴተኛ አዳሪ ጭኖቹ ላይ አስቀምጦ እያሻሸ በመሳም ይዳራታል፡፡

ቀይ አጭር ቁመናና ስልክክ ያለ ገፅታ ያላትን ወጣቷ በስስት እያያት “ዛሬስ በቀላሉ አለቅሽም፡፡”ሲያወራ ወደ ሞቅታ የገባ መሆኑ ያስታውቅበታል፡፡

“ከሌላ ቀኑ የተለየ ምን ልታደርገኝ?”

“ሁሉንም ነገር.....” ውስኪውን እየተጐነጨ መለሰላት፡፡

ቀጠለ “ለወሬ ነጋሪ እንኳ ሳላስቀርሽ እበላሻለሁ”

“እስኪ ወንድ!” ብላ ከንፈሩ ላይ ሳመችው፡፡ ተጋልጠው የሚታዩት ጡቶቿ ደረቱን ሲወጉት ሙቀቱ ጨመረ፡፡ ጣቶቹን በጭኖቿ መሀከል መስደድ ሲጀምር ፈጥና እጁን ያዘችውና “እ....እ.....ዛሬ ውድ ሆኛለሁ” በለስላሳ ቅላፄ ጆሮው ስር ገብታ በእስትንፋሷ ወላፈን ሆን ብላ እየገረፈችው ተናገረች፡፡ “ታዲያ ፍላጐቴን ታውቂው የለም እንዴ?”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“የቱን?”
“ውድ ነገሮችን መውደዴን .....”
“እ...ሀ.....ሀ.....ሀ.....” እንደ ህፃን ባለ የሚጥም ዜማ ሳቀች፡፡
ጐተታትና በተራው ከንፈሮቿን ሞጨሞጫቸው፡፡ የልቡ ሲደርስ ለቀቃትና “ለዚህ ፀባያችን ታዲያ ጥቅማ ጥቅሞችን በነፃ ማግኘት የለብንም እንዴ?”
“ነፍሴን እስክረሳት ውስኪ አስጨልጠኝ እንጂ ዓለምን በከለር ቲቪ ሳሳይህ አድራለሁ.....” አለችና ድጋሜ ከንፈር ለከንፈር ተያያዙ፡፡ ጣቶቹንም በለስላሳ ጭኖቿ ላይ እያንሸራተተ ሰደዳቸው..... አሁን ግን አልከለከለችውም፡፡
ጀነራል ከሰናይት ጋር ከያዘው ቀጠሮ በጣም ፈጥኖ በመድረሱ ከመጠጣት በስተቀር ሌላ ምንም ማድረግ ስላልቻለ እንደ ቀልድ አንድ ብሎ የጀመረው ውስኪ ወደ ሞቅታ አሸጋግሮት ነበር፡፡ ሰናይት በሰዓቷ የሱ ጠረጴዛ ያለብት ድረስ መጥታ ስትቀመጥ ከቤቱ ብርሃን መደብዘዝ ጋር ተዳምሮ ነገሮችን በትኩረት እንዲያስተውል አላስቻሉትም፡፡
ወጣቷ ጭኖቹ ላይ እንደተመጠች ነበር፡፡ “ጄነራል.....” በዝቅተኛ ድምፅ ጠራችው ሰናይት፡፡
ደንግጦ ቀና ሲል አያት፡፡ ኮስተር ለማለት እየሞከረ“ስሜ ምትኩ ነው!” አለ የሌላ ሰው ትኩረት ወደነሱ ያለማረፉን እያጣራ፡፡
ሰናይት ወድያው በስሜ ብቻ ጥሪኝ እያለት እንደሆነ ገባት፡፡ ቀጠለ በተሰላቸ ስሜት ፊቱን አጨፍግጐባት “እባክሽ ይህን ምሽት ለራሴ ብቻ ተይልኝ?” አላት፡፡ ከጥቂት ወራት ወዲህ የደረሰበት ተስፋ መቁረጥና የሞራል ውድቀት ራሱን በብዙ ነገር እንዳይቆጣጠር መንስኤ ሆኖበታል፡፡
ወጣቷ በቀስታ ከምትኩ ላይ ተነስታ በመቆም ከፓንቷ በጥቂት የምትረዝም ቀሚሷን ቁልቁል እየጎተተች ሰናይትን መገላመጥ ጀመረች፡፡
“ይቻላል ግን ትንሽ ብቻ አብረን ብንቆይ?”
ምትኩ ወደ ወጣቷ ዞረና “ለትንሽ ደቂቃ.....” ንግግሩን ሳይጨርስ ሀሳቡ ገባትና ሞላ ያለ ዳሌዋን እያውረገረገች ጥላቸው ሄደች፡፡
“እሺ ለምንድነው የምትፈልጊኝ?”
“ረጋ በል እንጂ ጄነራል”
“እባክሽ በዚህ ቦታ ጄነራል አትበይኝ..... እንደማንም ተራ ሰው ነው እየተዝናናሁ ያለሁት..... ራሴን ለአደጋ ማጋለጥ አልፈልግም፡፡”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“ይቅርታ አላስተዋልኩም ለነገሩ ትኩረት ባለማድረጌ ነው፡፡”
አስተናጋጁ ሲመጣ ውስኪ እንዲያመጣላት አዘዘችውና ለምትኩም እንዲቀዳለት በምልክት አሳየችው፡፡ የጄነራሉን የሞቅታ ስሜት ስላስተዋለች በቀጥታ ወደ ዋናው ጉዳይ ለመግባት እያሰበች “ያለፈ ጊዜ ባህርዳር ስንገናኝ ልትነግረኝ የፈለከው ሚስጥር ነበረህ.....”
“ተሳስተሻል!”
“እርግጠኛ ነኝ አልተሳሳትኩም፡፡ እንደምታውቀው ወደ ኢትዮጵያ የመጣሁበት ዓላማ ቀላል አልነበረም..... የአንተ የዛን ዕለት ስሜት ደግሞ ሌላ መልዕክትን ነው ያጫረብኝ፡፡ እባክህ እንደ ቅርብ ጓደኛህ እየኝና ትንሽ ሀሳቦችን አካፍለኝ?”
ምትኩ ለደቂቃ ሲያያትው ቆየና “እኔም ከአንቺ አንድ ትልቅ ነገር እፈልጋለሁ?”
“ምን?”
“ወደ ፈረንሳይ ልሔድ የምችልበትን መንገድ ሚስጥራዊና ፈጣን በሆነ ሁኔታ ካመቻቸሽልኝ.....”
“ምን ችግር አለው..... ቀላል ነው፡፡ ከዛም የተሻለ ነገር ላደርግልህ እችላለሁ፡፡
“ጥሩ.....” በረዥሙ ተነፈሰና ዊስኪውን አንስቶ ተጐነጨ፡፡ ቀጠለ “ግን ለምን አምንሻለሁ አንቺም ከነሱ መካከል አንዷ ብትሆኝስ?”
“ከነማን ?”
“ብትሆኝስ ምን አገባኝ..... እንኳን እኔን ስንቱን ገድለዋል ” አለ በስካር መንፈስ፡፡ አፍጥጦ እያያት ቀጠለ “... የአገራችን ውስጣዊ ችግር በእጅጉ እየተወሳሰበና እየተባባሰ ሔዶዋል፡፡”
“እንዴት?”
“በህዝቡም ሆነ በሰራዊቱ ውስጥ ዘረኝነት ሰፍኗል፡፡ ህዝቦች በክልላቸው ላይ እንደ ልብ የሰላምና የአንድነት አየር እየተነፈሱ መኖር አቅቷቸዋል፡፡.....

“.....ከኦሮሞ የሚመለመሉትን ካድሬና ወታደር በአማራው ላይ ይሾማቸዋል፡፡ የአማራውን በኦሮሞ፣ የደቡቡን በትግራይ፣ የትግራዩን በሶማሊ ላይ እያስቀመጠ ከክልሎቹ አብራክ ባልወጡ ወታደሮች ህዝቡን በወታደራዊ ትዕዛዝ እንዲጨፈጭፉ እያስደረገ ያለ አገዛዝ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ነው። አሁን እንኳን ሰሞኑን በወለጋ በተነሳው ረብሻ አወዛጋቢ ትዕዛዝ ከላይ ተላልፏል።"
"ምን የሚል?"
"በወለጋ ያሉት የኦ.ህ.ዴ.ድ. ጦርና አዝማቾች ህዝቡ ላይ አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስዱ የታዘዙትን ከመፈፀም ይልቅ የህዝቡን ጥያቄ ደግፈው አንጨፈጭፍም በማለታቸው እኔንና የኔን መሰል የሌሎች ክልሎችን ወታደርና አዛዦች ሰብስበው ወደዛ በማዘዋወር አገሪቷን በጦር ሰራዊት እንድንደበድባት አዘውናል" ቀጠለ ".....ይህን ደግሞ እኔ እንደ ግላዊ እምነቴ አልደግፈውም። ከኦሮሞ ብሔር አልወለድ እንጂ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ናቸው። የአገሬን ህዝብ ደግሞ የመንግስት ትዕዛዝ ስለሆነ ብቻ በጭፍን አልመታውም። እንዲመታም ተባባሪ መሆንን አልሻም።"
"አማራ ነህ አንተ?"
"ኢትዮጵያዊ ነኝ!"

"ከዚህ ቀደም እንደዚህ አይነት ተመሳሳይ እርምጃ እንዲወስዱ ታዘው ህዝብን አንመታም ብለው ከህዝብ የወገኑ በርካታ መኮንኖች በሚስጥ እየተገደሉና በሙስና ስም እየታሰሩ የፖለቲካ መቆመሪያ ሆነው አልፈዋል። የኔም እጣ ወደነሱ ሊሆን እየተቃረበ መሆኑ ይታወቀኛል። " አለ ተስፋ በሌለው ስሜት። ይህንን ሲናገር በባህርዳሩ ምሽት ላይ ሙሉ የጀነራልነት ልብሱን ለብሶ በትልቅ ሞገስ ያየችው ሰው አልመስል አላት። ቀጠለ "... ወያኔዎች ማለት..... " ስሜቱን የሚገልፅበት ቃል አጥቶ ተወራጨና "እነሱ ማለት..... ልባቸው እንደ ዓለት ሻካራ ከመሆኑ የተነሳ እነሱ እጅ ላይ ህይወት የጣለችው ሁሉ ሳይደማና ሳይገሸላለጥ በሰላም አይነሳም" አላት

"እና ምን ለማድረግ አሰብክ?"
"በቃኝ..... የኢትዮጵያ ገዢ ነኝ ብሎ መንበር ለያዘው የወያኔ ሽፍታ አካሔድና አስተሳሰብ አጉብዳጅ መሆን ሰልችቶኛል። ተስፋ የቆረጥኩት ደግሞ እኔ ብቻ አይደለሁም። በስልጣን ከኛ ላይ ካለነው አንስቶ ታች እስካለው መኮንንና ተራው ወታደር ድረስ ሁሉም ያው ሆኗል። ፖሊስን ጨምሮ የመንግስት ወታደር የተባለው ጠቅላላ እርስ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

በርሱ በጥርጣሬና በፍራቻ ነው የሚተያየው፡፡ ከሰራዊት አባልነት ቢወጣ ሌላ ህይወቱን የሚያኖርበት ሙያና እውቀት ስለሌለው ብቻ ነው በየ ካምፑ እንደ እስረኛ ተቀምጠ የመንግስት የስልጣን ዘመን እንዲራዘም የሚያስጠብቀው" አለ፡፡

ሰናይት ብዙም ሊጨነቅበት የማይገባ ጉዳይ መሆኑንና እያንዳንዱ ችግር መፍትሄ እንዳለው በተረጋጋና በልበ ሙሉነት ስትገልፅለት ቆየችና "ለመሆኑ ለወለጋው ግዳጅ መቼ እንድትንቀሳቀሱ ነው የታዘዛችሁት?" "በሚቀጥለው ሳምንት አጋማሽ....." አለና "እጅግ ሚስጥራዊ የሆነ ጉዳይን ነው እየነገርኩሽ ያለሁት..... እስካሁን ከስድስታችን ጀነራሎች በስተቀር ማንም ስለዚህ ጉዳይ አያውቅም አላት::"
"ግን ለምንድነው የማምንሽ? ማነሽ አንቺ..... ለነገሩ ሰላይ ሁኝም አትሁኝ በዚህ ቅፅበት ህይወቴን ከዚህ ሰቆቃ የሞላበት ምድር የሚነጥቅልኝ ባገኝ ምንኛ በፈቀድኩለት ነበር....." አለና መጠጡን አንስቶ ጨለጠው፡፡

ሰናይት በሷ እቅድ ውስጥ እንዴት ልትከተው እንደምትችል ስታሰላስል ቆየችና "በነገራችን ላይ ግን.....እ.....አቅሙ ቢኖርህ ይህን መንግስት የመገርሰሱ ፍላጐት አለህ?"
"አቅም ስትይ?"
"የገንዘብም የመሳሪያም....."
"ቢቻል አዎ..... እንኳን ይሄ ዓለምን የገዙት የነ ሮም እና ታላቂቱ ብሪታንያም መንግስት ተገርስሷል፡፡ የኔ ብቻ ሳይሆን በፖለቲካዊ አመለካከታችን የምንቀራበር የሁላችንም መኮንኖች ፍላጎት ነው::"
"እንዴት ባለ ሁኔታ ልታስፈፅመው እንደምትችል አብራራልኝ?"
"ሳስበው ሰራዊት መመልመልና ማሰልጠን ብሎ ነገር አያስፈልገኝም፡፡ ከዚሁ ካለው የመንግስት ሰራዊት ላይ ተቃዋሚውንና ቅሬታ ያለበትን ሁሉ ገንጥዬ እወስደውና አስታጥቄ ትግል ማስጀመር..... ወይም በሀሳብ የምግባባቸውንና በስራቸው በርካታ ሰራዊት ማዘዝ ከሚችሉት ባለስልጣናት ጋር ተነጋግሬ መፈንቅለ መንግስት በማካሔድ....."
"እ.....እ.....ከመፈንቅለ መንግስት ጦር ይዘህ መታገሉ ይሻላል::"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“ለምን?” ጠየቀ ምትኩ፡፡
“ስልጣን ብትይዝ የማንም የውጭ አገር መንግስታት ተቀባይነት አይሰጡህም” አለው፡፡ ትክክለኛው የልብ ሀሳቧ ግን ለእቅዳቸው ግብ መምታት ጦርነት ማካሔዱ እንደሚሻል ስላመነችበት ነበር፡፡ ቀጠለች “አስፈላጊውን የገንዘብና የጦር መሳሪያ ድጋፍ ሁሉ ላደርግልህ እችላለሁ፡፡”

ጄነራሉ ባልጠበቀው የሰናይት ንግግር ተገረመ፡፡ ምናልባትም ለማሰብ የፈለገው ድረስ እንዳያስብ በሚጠጣው መጠጥ ሞቅታ ውስጥ መነከሩ አላስቻለውም እንጂ፡፡
“አንቺ ነሽ የምትረጂን?”
“ሳይሆን..... ሙሉ ድጋፍ ሊያደርግልህ ከሚችል የውጪ መንግስት ጋር ላገናኝህ አቅሙ አለኝ”
ጄነራሉ ነገር ማመንዠኩን ቀጠለና ሰናይት ራሷን እንደገለፀላቸው ውጪ የኖረች ባለ ሀብት ሳትሆን ከበስተጀርባዋ ሌላ ዓላማን ያነገበች ሰው መሆን እንዳለበት እየጠረጠረ “ከግብፅ ጋር ነው?”
“አይደለችም” አለችው፡፡
ቀጠለ “ ሶስተኛ አማራጭም አይጠፋም”
“ምን አይነት? ”
“የትጥቅ ትግል ለማካሄድ ፍላጎት ኖሮዋቸው በአቅም ማጣት ምክንያት ጊዜ እየጠበቁ ከሚገኙ የተቃዋሚ ሀይላት ጋር በመጣመር ታግሎ ይህን መንግስት ማውረድ ይቻላል፡፡ ትልቁ ጥያቄ ገንዘብ ነው፡፡”
በሀሊናውም ‘ከዚች ሰው ኋላ ያለው የውጭ መንግስት ማን ይሆን?’ ሲል አሰበ፡፡ ወድያውኑም “ድጋፍ የምታደርጉልኝ ከሆነ ወደ ወለጋ ከመዘዋወሬ በፊት መሆን አለበት፡፡ እንዴ ከተጓዝኩኝ ግን እዛ ሆኜ ጉዳዩን የማስፈፀም አቅሜ ደካማ ይሆናል፡፡”
“በሁለትና ሶስት ቀናት ገንዘቡ እጅህ እንዲገባ ይሁና” አለችው፡፡
“ለመሆኑ ምን ያልህ ነው?”
“አንድ ሚልዮን ዶላር እንጀምር እና እንደ ትግልህ የእንቅስቃሴ መጠን እየጨመረ ይሄዳል” አለችው፡፡
‘ኧረ.....ጉድ!’ አለ በውስጡ፡፡ ወድያውም በብልጣብልጥ ስሌት ሀሊናውን ማሰራት እንዳለበት አመነና “ሁለትና ሶስት ጄነራሎችን

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

ከነሰራዊታቸው ለማሳደም ይቺ ገንዘብ ምን አላት፡፡ ምናልባት የአንድን ተራ ወምበዴ ጥቂት አባሎች ለመግዛትና ለማስታጠቅ ካልሆነ በስተቀር....."

"እና ምን ያህል ይሁን?"
"አቅማቸውን የምታውቂው አንቺ ነሽና ቀጥይ"
" ሶስት ሚልዮን ይሁና"
"ያንሳል..... በጣም ያንሳል..... ረቂቅ የፖለቲካ ስራ ነው የሚካሔድበት"
"ገና እኮ የጦር መሳሪያ ድጋፍ አላችሁ"
"የመሳሪያ ችግር የለብንም፡፡የአገሪቷ የመሳሪያ ማከማቻዎች በእጃችን ናቸው፡፡"
"እና ምን ያህል ይሁን?" ጠየቀች ሰናይት፡፡
"ሀምሳ ሚልዮን ዶላር"
"ከኢትዮጵያ ላይ መሬት ቆርሰህ እንድትሸጥ የተጠየክ አስመሰልከው እኮ..... ይህ ገንዘብ ነገ የአገሪቷ ስልጣን የአንተ እጅ እንዲገባ የሚደረግልህ እርዳታ ነው:: "
ቀጠለች "የውልህ..... ክፍያው ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚጨምርና ቀጣይ ነው፡፡ አሁን መጠየቅ የምትችለው ለመጀሪመያው እንቅስቃ..... ሲያችሁ የሚያስፈልጋችሁን ያህል ብቻ ነው፡፡" መጨረሻም ላይ ሰላሳ ሚልዮን ዶላር ተስማሙ፡፡
"ምናልባት አንድ ግዴታ ይኖርብህ ይሆናል::"
"ምን? "
"የምታሳድመውን ሰራዊት በአመዛኙ የምትመለምለው ከአማራ ብሔር መሀከል የተገኙትን መሆን አለበት"
"አስቸጋሪ ቢሆንም ለማድረግ እጥራለሁ"
"የዚህን ያህል ልትረሱኝማ አይገባም....." አለች ወጣቷ ሴተኛ አዳሪ በብርጭቆዋ አስሞልታ የያዘችውን ዊስኪ ጠረጴዛው ላይ በማስቀመጥ ምትኩ ላይ ተለጥፋ እየተቀመጠች፡፡
"እንዴት ልንገናኝ እንችላለን?" ጠየቀች ሰናይት::
"አንቺ ጋር ባለው ቁጥሬ ነዋ:: መገናኛ ቦታችንን እኔ እየመረጥኩ አሳውቅሻለሁ"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ሰናይት በእሺታ ጭንቅላቷን ነቅንቃ ከተቀመጠችበት እየተነሳቸች “የምሽቱ ሂሳብ በኔ ተዘግቷል” ጨብጣው መራመድ ጀመረች፡፡
ሴተኛ አዳሪዋ ሰናይትን በቅናትና በጥላቻ እይታ በዓይኖቿ እየተከተለቻት “ምን ትመስላለች?..... ባሌን ከኔ ለመንጠቅ..... ሆ...ሆ...ሆ..... ” አለች የምትኩን የቅድም የወሲብ ስሜት ድጋሜ ለማነሳሳት እየተሻሸችው፡፡
“ማን?” ከተመሰጠበት ሀሳብ ሳይወጣ ጠየቃት፡፡
“ይቺ ሲባጎ የመሰለች ገርጃፋ አሮጊት ጓደኛህ ነቻ”
ምትኩ የምትለውን አይሰማትም ነበር፡፡
ቀጠለች “መንጠባረሯ ነው..... ስታስጠላ!... ደግሞ የምሽቱ ሂሳብ በኔ ተዘግቷል ትላለች፡፡ ማን ጠየቃት እስኪ!? ” አለች በመመፃደቅ ሁኔታ፡፡

ምትኩ ከሀሳቡ አልተመለሰም፡፡ በዝምታ ጥቂት እንደቆዩ እንደበፊቱ አልሆን ብሎ በመቀዝቀዙ እየተበሳጨች “ምን አስነክታህ ሄደች?! ..... ወይስ ደበርኩህ?”
ትኩረቱን ወደሷ ለመመለስ እየጣረ ሳለ ተነስታ ጥላው ለመሄድ ስትዞር እጇን ይዞ ጮተታት፡፡
የተቀየመች ለማስመሰል እንደመመናጨቅ አለችና ወርዳ ጭኑ ላይ ተቀመጠች፡፡
ሁለቱም ወደ ቅድሙ የሽርሙጥና ዓለም መመለስ ጀመሩ፡፡

  

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ምዕራፍ 30

አቶ መርድ የአሜሪካ ግዛት በሆነችው ዋሺግንተን ዲሲ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ጉዳይ ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ተሰባስበው የጠሩትን ስብሰባ ተጋባዥ ሆነው እንዲካፈሉ በተደረገላቸው ጥሪ መሰረት ነበር የሔዱት።

በግል ጋዜጣ አሳታሚነት ስራ መንቀሳቀስ ከጀመሩ ሁለት ዓመት ሊሆናቸው ነው። በሚያወጡት ትኩስ እውነተኛና ግልፅ ዜናዎች ጋዜጣቸው በአጭር ጊዜ ውስጥ ታዋቂ ለመሆን ችሏል።

ከመስፍን ጋር ያስተዋወቃቸውም ምክንያት ይኸው በአንድ ሙያ ጥላ ስር መኖራቸው ነበር። ለበርካታ ጊዜያት ቀጥረውት አብሮዋቸው እንዲሰራ ቢለምኑትም አሻፈረኝ ብሏቸዋል። ይሁን እንጂ ግን ለጋዜጣ አምድ መሆን የሚችሉ ፅሁፎችን አልፎ አልፎም ቢሆን በደህና ዋጋ ሊገዙት እንደሚችሉ ስለገለፁለት አንዳንዴም ቢሆን ቢሮዋቸውን ከማንኳኳት አልተገታም።

ከአምስት ቀናት በፊት ነበር በኢትዮጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀስ አንድ የውጪ ድርጅት በህቡእ የሚመሩ የውስጥ አንጃዎችን መልምሎ አገሪቷን ሊበታትኗት የሚያስችል እንቅስቃሴ የጀመረ መሆኑን የሚገልፅ ፅሁፍ ይዞላቸው ወደ ቢሮዋቸው የመጣው።
አንብበውት ሲጨርሱ "ይህ ፅሁፍ እውነተኛ ነው?" ጠየቁት።
"በሚገባ እንጂ....."
"በዜና መልክ ይሰራ?" ጠየቁት እንጂ በራሳቸው ሃሳብ እየተዋጡ ነበር። በህሊናቸው እንደዚህ አይነት ዘገባዎች ለህዝብ መግለፅ በመንግስት በኩል ስለማይደገፍ ሌላ መዘዝ ይዞ እንዳይመጣባቸው እያሰቡ።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

መስፍን “ጥሩ እንደውም ባሁኑ እትም ዜናው ብቻ ይሰራና ለሚቀጥለው ሳምንት ዕትም ላይ ሙሉ የውስጥ አምድ ሰጥተውኝ በስፋት እሰራዋለሁ” አላቸው።።
“አይ.....” አሉ በቅሬታ።። በሱ የብቃት ማነስ ላይ አልነበረም ጥርጣሬያቸው
“ምነው.....?” ጠየቀ መስፍን
“ጭብጡ ስላስፈራኝ ነው.....”
መስፍን እንደዚህ ሲሆኑ አይቶዋቸው ስለማያውቅ እየተገረመ ለመናገር ሲዘጋጅ መልሰው “ይሁና የመቼው እትም ላይ እንስራው?” ጠየቁት
“የነገው ላይ.....”
“እነዚህ ጣጠኞች ደግሞ ክስ እንዳያመጡብኝ”
“በዚህ ዜና!?”
“አዎና..... በወረቀትና በአፋቸው “ነፃ ኘሬስ..... የህዝቡ የመናገር የመፃፍ መብት በኛ ተጠብቆለታል” እያሉ ይለፍልፉ እንጂ ስንቱን ፀሀፊና አሳታሚ ቁም ስቅሉን እያሳዩት አይደል እንዴ ያሉት” መስፍን ለንግግራቸው ቦታ ያልሰጠው መሆኑን ገፅታው ላይ እያስነበባቸው “አዬ..... ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ..... ነውና ተረቱ ገና ለገና የነሱን እስርና ሞት ፈርቼ ህዝቡ ማወቅ የሚገባውን ከመፃፍ አላፈገፍግም።።..... እርስዎ ፈቃደኛ ካልሆኑ..... ለሌላ አሳታሚ መስጠት እችላለሁ።።”
“መስፍን ይህን ዜና ማተም ያለመፈለጌ አይደለም” በእርጋታ መለሱለት።።
“እንደውም ዜናውን ሚዛናዊ ለማድረግና እርስዎም የተሻለ ነፃነት እንዲሰማዎት የጉዳዩን እውነተኛነት ለአንድ የመንግስት ባለስልጣን በጥያቄ መልክ ያቅርቡለትና ከሚያገኙት ምላሽ ጋር አያይዘው ያውጡት”
“አዎ..... ይልቅ ይህ ቀና መንገድ ይመስላል”
በሁለተኛው ቀን ላይ ነበር ዜናውን በተባለው ሁኔታ ላይ ምላሽ ከሰጠው የመንግስት ባለስልጣን ቃለ-መጠይቅ ጋር ጎን ለጎን አድርገው በጋዜጣቸው ላይ ያተሙት።።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

እንደፈሩት አልቀረላቸውም፡፡ መንግስት በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ትዕዛዝ አስተላለፈ፡፡

ለዚህ ስራ በህዝብ ደህንነትና በፌደራል ፖሊስ ቢሮ ስር "ግዳይ 200" ተብሎ የተቋቋመው የሚስጥር አፋኝ ሀይል ስራውን እንደጀመረ ወደ ጋዜጣ አሳታሚው ቢሮ በመሔድ ያገኛቸውን ሰባት ሰራተኞች አስሮና ከድርጅቱ በምርመራ ሰበብ ያሉትን ንብረቶች አስጭኖና ቢሮዎቹን አሳሽጐ ሄደ፡፡

አቶ መርድ ግን አሜሪካ ስለነበሩ በቁጥጥር ስር ሊያሉሏቸው አልቻሉም፡፡ የአፋኝ ሀይሉ አዛዥ የሆነው የህዝብ ደህንነቱ ኃላፊ ሚስታቸውን ለመያዣነት እንዲያገለግሉ በፍጥነት ተይዘው እንዲመጡ አዘዘ፡፡ በዛው ዕለት ተፈፀመ፡፡

ሚስታቸውና የጋዜጣው ድርጅት ሰራተኞች ወደ ማእከላዊ የምርመራ ጊቢ ተከተው ኢ-ሰብአዊ ድብደባ ተደረገባቸው፡፡ ታጣቂዎቹ በድብደባው አቶ መርድ የሄዱበትን ቦታ ከማወቅ ውጪ ምንም ጠቃሚ መረጃ ሊያገኙ አልቻሉም፡፡

አቶ መርድ ከመሔዳቸው በፊት ለማረፊያነት አስመዝግበውት የነበረው ሆቴል አድራሻ በሚስታቸው ይታወቅ ስለነበረና ይህም ለመርማሪዎቹ ስለተነገራቸው በራሳቸው በሚስትየው ስልክ እንዲደወል አስደረጉና አቶ መርድ መሆናቸው ሲረጋገጥ መንግስት ለከፍተኛ ጉዳይ የሚፈልጋቸው በመሆኑ ዛሬውኑ በተገኘው በረራ ተጠቅመው እንዲመጡ ሚስታቸውን መልዕክቱን በታዘዙት መሠረት ማስተላለፍ ጀመሩ

አቶ መርድ "ከአስር ቀን በፊት መመለስ አልችልም"

ሚስትየው ለማሳመን መሞከር ቀጠሉ፡፡

"አልመጣም!" አሉ በቁጣ፡፡ ከዛም ጥርጣሬ ወደ መንፈሳቸው መግባት ስለጀመረ "ምንድነው ችግር ካለ ንገሪኝ?.....ምንድነው?....." ሚስትየው ከዚህ በላይ መናገር አልቻሉም ሳግ የተቀላቀለ ለቅሶዋቸውን ለቀቁት፡፡

የደህንነት ሹሙ መነጋገሪያውን ቀማቸውና "ሚስትዎ በቁጥጥራችን ስር ይገኛሉ፡፡ የሳቸውን ህይወት የማትረፍ ብቸኛው አማራጭ እርስዎ ብቻ ነዎት፡፡"

"እ..... አልገባኝም..... እንዴት....."

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“ትዕዛዙን ይቀበሉ፡፡” አለና ወይዘሮዋን በጠንካራ ጥፊ አጐናቸው፡፡ የሴትየዋ እሪታ በስልኩ እያለፈ የአቶ መርድ ህሊና ውስጥ ተራወጠ፡፡ “ንግሪው እውነታውን!” ሹሙ እያፈጠጠ መነጋገሪያውን መልሶ ሰጣቸው፡፡

“መርድ.... ሊ.....ሊ.....ገሉን..... ነው.... ሰራ....ተኛ.....ቹም..... በጠቅ....ላላ..... ተይዘው.....ታስ....ረዋ”

መነጋገሪያውን መልሶ ነጠቃቸውና ወደ ረዳት ጓዶቹ በመዞር “በቂ ነው አስወጧት” ብሎ አጠገብ ወዳለው ሌላ ክፍል አስወሰዳቸው፡፡ መነጋገሪያውን ወደ አፉ አስጠጋውናም “አቶ መርድ ይመጣሉ ወይስ የመሰለንን እርምጃ በሚስትዎ ላይ እንውሰድ?”

“ቆይ..... ለምንድነው የምፈለገው?”

“ሚስጥራዊ መረጃ በእጅዎ ይገኛል፡፡ ለእርስዎ ጥቅሙ ዜናውን ሽጠ ገንዘብ መሰብሰብ ብቻ ነው፡፡ መንግስትን ግን በአስራ ሰባት ዓመት የትጥቅ ትግል ያገኘውን ዲሞክራሲያዊ ስልጣን ሊያሳጣው ይችላል፡፡ ይገባዎታል፡፡ ጥያቄው የመንበር ነው፡፡ በስልጣን ላይ የመጣ የህልውና ጥያቄ ነው፡፡ እናም ያንን መረጃ ሰጥተው ነፃ መውጣት ይችላሉ፡፡”

“የመንግስት መረጃ በኔ እጅ?”

“አዎ.....”

“የምን መረጃ ነው?”

“ቀሪውን እዚሁ እንነገግራለን፡፡ ፈቃደኛ እስከሆኑ ድረስ ሚስትዎ ፍፁም በማያሰጋም ስፍራ ሆነው እንዲጠብቁም ይደረጋል፡፡ ለራስዎም ቢሆን አስፈላጊው ጥበቃና የደህንነት ዋስትና ስለሚሰጥዎ እንዳይሰጉ..... ዛሬውኑ ቢነሱ በአቆራራጭ በረራ ነገ መግባት ይችላሉ፡፡ የመድረሻ ሰዓትዎን እንዳወቁ በዚህ ስልክ ደውለው ይግለፁልን፡፡” ብሎ የቢሮውን ቁጥር አስመዘገባቸውና “የሚያወጡት ወጪ ኪሳራ በጠቅላላ በመንግስት የሚታሰበ በመሆኑ ይከፈልዎታል፡፡”

ለረዥም ሰከንዶች በዝምታ ቆዩና በተዳከመ ቅላፄ “እሺ.....እመጣለሁ” ብለው ዘጉት፡፡

«««««« »»»»»»»

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ለረዥም ሰዓት በባዶው ክፍል ውስጥ ለብቻቸው አውርተዋል፡፡ “እዚሁ ብቀርስ?.... ደግሞ ሚስቴን ቢገድሏትስ?..... ራሴኑ..... ቢገድሉኝስ ግን ቃል ገብቶልኛል.....” አካላቸው በላብ እስኪዘፈቅ ድረስ ምጥ ላይ እንዳለች ሴት በጭንቅ ቆዩ፡፡

በስተመጨረሻ መፍትሔ መሰል ሀሳቦችን አመላለሱ፡፡ በዝምታ ተንከርፍፈው በመሔድ እጃቸውን ቢሰጡ አፍነው ያልታወቀ እርምጃን ሊወስዱባቸው እንደሚችሉ ጠረጠሩ፡፡ በዚህ ቅፅበት አንድ አማራጭ ፍንትው አለላቸው፡፡ ሀሳቡ መንግስት ባልታወቀ ምክንያት በሰራተኞቻዋውና በቤተሰቦቻቸው ላይ የወሰደውን እርምጃ እራሳቸውንም በቁጥጥር ስር ለማዋል እያደናቸው መሆኑን ለሌሎች አቻ የጋዜጣ አሳታሚ ድርጅቶች ደውለው በመንገር አየር መንገዱ ድረስ መጥተው እንዲያነጋግሩዋቸውና ጉዳዩን በየጋዜጠቻቸው በመፃፍ ህብረተሰቡ እንዲያውቀው ማስደረግ በዚህም መንግስት የከፋ እርምጃ እንዳያደርስባቸው ጋሬጣ ለመፍጠር የሚያስችላቸው ብቸኛ መንገድ ሆኖ ታያቸው፡፡

አሁን የሚያሰጋ ነገር የለም፡፡ ሻንጣቸውን አዘገጃጁና ወደ አንድ የጉዞ ወኪል ጥሪ አደረጉ፡፡ በቀጣዮቹ ሃያ አራት ሰዓቶች ውስጥ ከዋሺንግተን ተነስተው ወደ ኢትዮጵያ ለመግባት ያለው አማራጭ ተመሳሳይ መሆኑን ነገሯቸው፡፡ ሶስት የቅብብሎሽ በረራ ማድረግ፡፡ አማራጭ ስላልነበረ ከዋሺንግተን ጣሊያን ከዛም ግብፅ ከግብፅ ኢትዮጵያ፡፡ ቦታ እንዲያሲዙላቸው አስደረጉ፡፡

በመቀጠል በአዲስ አበባ ውስጥ ካሉ የግል ጋዜጣ አሳታሚ ድርጅቶች መካከል ለሰባቱ ደወሉና ጉዳዩን በመግለፅ በቀጣዩ ዕለት የቦሌው አየር መንገድ እንዲመጡላቸው አስገነዘቡ፡፡

የሁሉም ምላሽ ነግ በኔ ነውና እንመጣልዎታለን ስለያንዳንዱ እውነታም ህዝብ እንዲያውቅ እንጥርልዎታለን የሚል ነበር፡፡

«««««« »»»»»»

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

በጉዞውና ከአውሮፕላን አውሮፕላን በመገላበጥ ያሳለፉዋቸው አስራ ስድስት ሰዓቶች እጅግ አድካሚ ነበሩ።።

እሁድ ከምሽቱ አስራ ሁለት ሰዓት ሲል የአዲስ አበባው ቦሌ ደረሱ።።

በጊቢው መውጫ ላይ የቪዲዮና የፎቶ ካሜራዎችን እንዲሁም መቅረፀ ድምፆችን የያዙ የጋዜጣ አሳታሚ ሰራተኞች ካለመታከት ተጓዥ የነበረ መንገደኛ ከውስጥ ብቅ ባለ ቁጥር በትኩረት ይቃኛሉ።። ተፈላጊው ሰው ያለመሆኑ ከለዩ በኋላም እንደገና ወደ ሌላ አቅጣጫ ይዟዟራሉ።።

በዚህ መካከል በተለያዩ መገናኛ ብዙሀኖች እውቅናን ያገኙ የጋዜጣ አሳታሚ ድርጅት ሰራተኞች በበርካታ ሰዎች እይታ ውስጥ ስለገቡ በአካባቢው ላይ የሚከናወን አንድ እንቅስቃሴ ስለመኖሩ ለማንም ግምት የቀረበ እውነታ ነበር።።

በዕለቱ በቦታው በነጭ ለባሽነት የተመደቡት የህዝብ ደህንነት ሀላፊም ይህንን ተገንዝቧል።። ጉዳዩን ለማጣራት ሞክሮ ስላልተሳካለትና በሁኔታው ስላልተደሰተ ከሰዎች እይታ ሰወር አለና በመገናኛ ራዲዮ ለአለቃው አሳወቀ።።

ሹሙም በቁጣ "በአካባቢው የተሰማሩ ሰዎቻችንን በጠቅላላ ወደ አየር ማረፊያው ጊቢ እንዲገቡ አስደርግ"
"ደውለህ ንገረዋ ውስጥ ላለው የጊቢ ደህንነት"
"መጣሁ ራሴ.....እስክደርስ ድረስ የሚፈጠር ነገር ካለ በእቅዱ መሰረት እንዲተገበር ከማስደረግ እንዳትገታ"
"ታዛዥ ነኝ" ብሎ ራዲዮን እየደበቀ በሩ ላይ ወደ ሚተራመሰው ተጓዥና ተቀባይ ሰዎች መካከል ተደባለቀ።።

የበላይ ሀላፊው የህዝብ ደህንነት ዋና አዛዥ የሆነው ጐልማሳ ነው።። አለባበሱ ሲቪል ሲሆን ሁለት ባልደረቦቹን አስከትሏል።።በአስር ደቂቃ ውስጥ ነበር ከስፍራው የደረሰው።።

ሁኔታውን ሲያይ በጣም ተገረመ።። የጋዜጠኞቹ በቦታው ላይ የመገኘት ሚስጥር ነጥቡ ድረስ ባይገባውም 'የአቶ መርድ ስራ ሊሆን ይችላል' በማለት ገመተ።። በሀሳቡ አልረጋም 'ላይሆንም ይችላል ለማንኛውም.....' ብሎ በሩ ላይ ላሉት ጠባቂዎች መታወቂያውን

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

በማሳየት ከባልደረቦቹ ጋር ወደ ኢሚግራሽን ጉዳዮች ቢሮ አልፎ ገባ ። ከአምስት ደቂቃ በኋላ ሰባት የደህንነት ሰራተኞች የአየር መንገዱ ሰራተኛ መስለው ወደ ውስጥ እንዲገቡ አስደረገ።

ሁሉም የአቶ መርድ ፎቶ ታድሎዋቸዋል። በተጨማሪም ስለሰውዬው አካላዊ ገፅታ ማብራሪያ ተሰጥቶዋቸዋል። ውስኖቹ የመተላለፊያዎች ቁልፍ ቦታ ላይ እንዲቆጣጠሩና ቀሪዎቹ ወደ ማረፊያው ሜዳ እንዲዘልቁ ተደረገ።

ከግብፅ የተነሳው አውሮፕላን ለትራንዚት አርፎ መንገደኞችን ማራገፍ ሲጀምር አቶ መርድም ብቅ አሉ። ቀድሞ ያያቸው የደህንነት አባል አቅራቢያው ለነበሩት አሳወቀ።

አቶ መርድ መውረጃውን ጨርሰው ዙሪያቸውን በስጋት እየቃኙ አስፖልቱን ሊጨርሱ ሲሉ ሁለት የአየር መንገዱን ቴክኒሻን ቱታ ያጠለቁ ሰዎች ደርሰውባቸው ነበር። አንደኛው ድምፅ ለሌላ መንገደኛ እንዳይሰማ እየተጠነቀቀ "እርስዎ በዚህ ይምጡ" ትዕዛዙን በመቃወም የሌላ ሰው እይታ ውስጥ የሚያስገባ እንቅስቃሴ ሊጀምሩ ሲሉ ሁለተኛው በማያስታውቅ ሁኔታ ጥፍንግ አድርጐ ከኋላ መታጠቂያቸው ላይ ያዛቸውና "ይቀጥሉ!" ብሎ ወደሚፈልጉበት አቅጣጫ ገፉዋቸው።

"ቆይ....ቆይ.....እንጂ....."

ጥቂት እንደተራመዱ ከመንገደኞች ትኩረት ውጪ መሆናቸውን አጣሩና ገፍትረው የህንፃው ተሽካሚ ቋሚ ስር አስገቧቸው። በፍጥነት አንደኛው ሽጉጥ አወጣና አቀባብሎ ደገነባቸው።

"ይቀጥሉ!"

ሌላኛው የመገናኛ ራዲዮ አወጣና "ግዳይ 200"

"ቀጥል"

"ተይዘዋል"

"ቦታውን ግለፅ"

"ከመግቢያው በር በስተግራ በኩል ወደ....."

አቋረጠውና "እዛው ጠብቅ"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

በጥቂት ሰከንድ ውስጥ ለመንገኞች ድንገተኛ ችግር አገልግሎት እንዲሰጥ የተዘጋጀ አምቡላንስ መኪና መጣና በአቅራቢያቸው ቆመ።።
“ይግቡ”
የደህንነት አባሉ ወደከፈተው የመኪናው የኋላ በር እያመለከተ አዘዛቸው።።
ላለመግባት አቅማሙ።።
የነርስ ሽርጥ ያጠለቀውና መኪናው ውስጥ የነበረው ሰው “ተጠቀም ብልሀት” አዘዘው አባሉን።።
ሽጉጥ ደግኖባቸው የነበረው መሳሪያውን ጠበቅ አድርጉ ጨበጠና በሰደፉ የትከሻቸው ጡንቻ ላይ ደህና አድርጉ መታቸው።። ህሊናቸውን በመሳት መልክ ተዝለፍልፈው ወደቁ።።
የነርስ ሽርጥ ያጠለቀ ሰው ከሌላ አባሉ ጋር ፈጥኖ ወረደና አቶ መርድን ቃሬዛ ላይ አድርገው በመጫን ወደ መኪናዎች መውጫ በር ተፈተለኩ።። እዛም ወደ ሌላ ሽፍን መኪና ላይ አገላብጠዋቸው ጊቢውን ሲለቁ ሁለት ደቂቃ አልፈጀባቸውም።።
ጉዞው ያቀናው ወደ ማያውቁት አንድ ወታደራዊ ካምፕ ጊቢ ነበር።።
ወድያውኑ ስለ አቶ መርድ መያዝ ሳይገለፅ ባለቤታቸውና የድርጅቱ ሰራተኞች ተለቀቁ።።
ከሰላሳ ደቂቃ በኋላ አቶ መርድ ራሳቸውን ያገኙት በአንድ ጠባብ ጨለማ በዋጠው ባዶ ክፍል ውስጥ የድንጋይ ወለል ላይ ተጋድመው ነበር።።መሬቱ ውኃ ፈሶበት ስለነበር ቀዝቅዞዋቸዋል።። ተደግፈው ቀና ለማለት ሲሞክሩ አንገታቸው ስር ክፉኛ ህመም ተሰማቸው።። እንደምንም ተቀመጡና የተከናወነውን ድርጊት ለማስታወሰ ሲታገሉ የሰው ኮቴ ተሰማቸው።። ወድያውም የነበሩበት ክፍል የብረት በር ሲከፈት የተፈጠረው አዋኪ የመንፏቀቅ ድምፅ አካላቸውን በንዝረት ናጠው።።
ጊዜው መምሸቱን በበሩ በኩል በሚገባው ጭላንጭል አወቁ።። ወድያውም የሶስት ሰው ጥላ ታያቸው።።
“አቶ መርድ ተነስ” የፊተኛው ሰው በሚሻክር ድምፅ አዘዛቸው።።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

አንደኛው ገፍትሮ ከግድግዳው ጋር ለተማቸውና ሁለት እጆቻቸውን በኋላ በኩል በካቴና ጠፈነገው።።

ከዛም እየጐተታቸው ክፍሉን ለቀው ወጡ።። ማንም አይናገርም የውጪው አየር ቀዝቃዛ ነው።። ትልልቆቹ የባህር ዛፎች በንፋስ እየተገፉ በለሆሳስ ይወዛወዛሉ።። በርቀት ከሚገኙ ክፍሎች በቀዳዳ አምልጦ የወጣ የአምፖል ብርሃን ይታያል።። እንዲሁም ታጣቂዎች በርቀት አድብተው እንደቆሙ ቅርፃቸው ይታያል።።

ሰማዩም ዝም ያለ ይመስላል።።ጨረቃ የለችም።። ጉም ያልጋረዳቸው ከዋክብቶች ብርሃን በልጥፋ አልጥፋ ስሜት ይብለጨለጫሉ።።

አቶ መርድን የሚጐትተው ሰው ፈንጠር ብሎ ወደተሰራው ሌላ ክፍል ይዞዋቸው ገባ።።

ክፍሉ ከበር ውጪ ሌላ ለአየር ማስገቢያ ቀዳዳ እንኳ የውም።። አንድ አምፖል ብቻ አስቀያሚ የደበዘዘ ብርሃን ይፈነጥቃል።።

በውስጡ አንድ ጠረጴዛና ወንበር ብቻ ሲኖር በኮንክሪት ከተሰራው ጣሪያው ላይ የተንጠለጠሉ ሰንሰለቶች ይታያሉ።።

ጠረጴዛው አቅራቢያ የተለያዩ አይነት ጐማ የለበሱ ሽቦዎች፣ ዱላዎች፣ በመጠንና በቅርፅ የተለያዩ ለማሰቃያነት የተዘጋጁ ቁሳቁሶች ይታያሉ።።

የደህንነት ሹሙ አብረውት እንዲሰሩ ከተመደቡት ሁለት ወታደሮች ወደ አንደኛውና ፈርጣማ ሰውነት ወዳለው እያየ "ልብሱን አወላልቀው!" አዘዘ።።

ሁለቱንም እጃቸውን በፍጥነት ፈቱና የተባሉትን አከናወኑ።። አቶ መርድ እርቃን እስኪቀሩ ድረስ ስለተገፈፉ ሀፍረታቸውን በመዳፎቻቸው እንደመከለል አድርገው ቆሙ።።

"ስቀለው" ሹሙ አዘዘ።።

"ይዘቅዘቅ ወይስ እንዳለ?"

"ገልብጥና"

እጆቻቸውን በፊት በኩል አሰሩትና "ተቀመጥ" አላቸው ፈርጣማው ወታደር።።

"ለ....ለ....ምን።። የምትፈልጉት....."

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

አላስጨረሳቸውም ጠልፎ ወለሉ ላይ አፈረጣቸው፡፡ ከዛም እግራቸው ላይ ቁጢጥ በሚል ሰው ሁኔታ እንዲቀመጡ አድርገው በክንዳቸው መካከል ጉልበታቸውን አሳቀፏቸው፡፡ ከጠረጴዛው ስር ረዥም ክብ ቅርፅ ያለው ብረት አወጣና በቀኛቸው በኩል የጉልበታቸው መታጠፊያ አቅጣጫ በእጃቸውና በእግራቸው መካከል አቆላልፎ ከተተባቸውና ከባልደረባው ጋር የብረቱን ጫፍና ጫፍ ይዘው ወደላይ ሲያነሷቸው፡፡ ተዘቅዝቀው ተንጠለጠሉ፡፡

የብረቱን ጫፍና ጫፍ በጣሪያው ላይ ወደተንጠለጠሉት ሰንሰለቶች በማስጠጋት ቀለበቱ ውስጥ አጠለቁትና እንዳይሾልክ በማስነከሻው ቆለፉት፡፡

ሹሙ በአቶ መርድ ተቋም ይታተሙ የነበሩ ሶስት ጋዜጣዎችን ከጠረጴዛው ኪስ አወጣና በዜና መልክ የፊት ገፅ ላይ የታተመ ፅሁፍ ጮክ ብሎ ሲያነብላቸው ቆየ፡፡

መርድ ግን እጃቸው የታሰረበት ካቴና እና የተንጠለጠሉበት ብረት እያሰቃያቸው ስለነበረ ብዙም አላዳመጡትም፡፡
ሹሙ አንብቦ ሲጨርስ “ይህን ዜና ከየት አግኝተህ ነው ያተምከው?”

“አንድ ወጣት..... ሪፖርተር ነው.....የ...ሰጠኝ”
“በለው እንጂ ቆመህ ታየኛለህ!” ሹሙ ወደ ወታደሮቹ እያፈጠጠ በቁጣ አዘዛቸው፡፡

ወታደሮቹ ዕለት ዕለት እንደሚያደርጉት ሁሉ የሚያመቻቸውን ደረቅ የሽቦ መግረፊያ እያነሱ ካለ ምርጫ ጀርባቸውን፣ እግራቸውን፣ ክንዳቸውን፣ ጭንቅላታቸው..... መፍጨርጨር ጀመሩ፡፡

ለሃያ ደቂቃ ያህል መሪር የሲቃ ጩኸት እየጮሁ ቆዩ ከዛ በኋላ ግን ተደጋጋሚ ግርፋት ያረፈበት የሰውነታቸው ቆዳ መግረፊያውን ደግሞ ሲያርፍበት መሞሸለቅ ስለጀመረ አካላቸው እየደነዘዘ መጣ፡፡

ከተሞሸለቀው ገላቸው የሚፈልቀው ደም መላ አካላቸውን አርሶ ወለሉ ላይ ቦይ መስራት ጀመረ፡፡ ምርመራው በሚዘገንን ሁኔታ ሳያቋርጥ ለቀጣዮቹ አስር ሰዓት ዘለቀ፡፡ የክፍሉ ስራ ተጠናቆ ሹሙ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ሲወጣ አቶ መርድ በደረሰባቸው አስከፊ ድብደባ ራሳቸውን በተደጋሚ እየሳቱ ይነቁ ነበር።

የተወሰደባቸው እርምጃ ለምርመራው ብቻ የታቀደ ሳይሆን መንግስት የግል መገናኛ ብዙሀኖች ላይ ሲያጠራቅም የኖረውን ጥላቻና ዛቻን እውን ያደረገ ነበር።

ይሔ ሁሉ ሲከናወን አቶ መርድ በጋዜጣው ላይ ስላሳተሙት ዜና ያገኙት መረጃ የሰጣቸው መስፍን ካሳ የተባለ ግለሰብ መሆኑንና የት ይገኛል ተብሎ ለቀረበላቸወ ጥያቄ የመስራያቤቱንና የመኖሪያ ቤቱን ስልክ መስጠት ብቻ እንጂ በባለስልጣነቱ እንደታሰበው እሳቸው የጉዳዩ ባለቤትም ሆነ ተሳታፊ መሆናቸውን የሚያሳይ ወይም ጋዜጣው የተቃዋሚ ፓርቲ ልሳን ስለመሆኑ ምንም መረጃ ሊያገኙባቸው አልቻሉም።

የደህንነት ሹሙ ባገኘው ውጤት ባይደሰትም ጉዳዩ እንዳሰበው ወዴት መጓዝ እንዳለበት ፍንጭ ቢጤ አግኝቷል። 'በፍጥነት ወጣቱን ፈልጦ መያዝ ነው' ሲል እየቋመጠ ከምርመራው ያገኘውን ውጤት ለአለቃው ለመግለፅ አቀና።

ደንዳናው ገራፊ ሹሙ መራቁን ሲያይ ቆየና ወደባልደረባው ዞሮ "በሰው ጉልበት መቀለድ አይበቃቸውም እንዴ እነሱ ስልጣን ለሚያገኙበት ስራ እኛን ቀን ያለዕረፍት ለሊት ካለ እንቅልፍ እንድናድር ያደረጉናል።" አለ በምሬት።
"አሁንማ መደበኛ ስራችን ይኸው ሆኗል። እዚህ ቦታ ከተመደብኩ አራት ዓመት ሊሆነኝ ነው መለያዬ ወታደር ይባል እንጂ ሙያዬ ገራፊ ነው።" አለ ሌላኛው።

ከአስር ደቂቃ በኋላ አራት ታጣቂዎች ወደ ምርመራ ክፍሉ መጡ።

ገራፊዎቹ ዘወትር እንደሚያደርጉት ሁሉ አቶ መርድን ከተሰቀሉበት አውርደው ወጡና በሩን ከውጪ ቆልፈው በአካባቢው ለተመደቡት ሁለት ጠባቂዎች የተጠናከረ የጥበቃ ትዕዛዝ አስተላልፈው ወደ እንቅልፋቸው ሄዱ።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ለ "ግዳይ 200" ወደተከለለው እስር ቤት መውጫ በር ላይ የተመደቡት ሁለት ጠባቂዎች በብርድ ተኮራምተው ያንቀላፋሉ፡፡ ሰዓቱ ከለሊቱ አስር ከሃያ ብሏል፡፡
ወደ ምርመራ ክፍሉ ከቀረቡት አራት ታጣቂዎች መካከል አንደኛው ወደ ጠባቂዎቹ እያየ "እስረኛውን እንድትሰጡን ታዛችኋል፡፡"
"የት እንዲላክ?" ከጠባቂዎቹ አንደኛው ጠየቀ፡፡
"ግዳይ 002 ተፈፃሚ ይሁን ተብሏል"
"ምን?"
"ግዳይ 002"
"ቧ....እኛ ስለ ግዳይ 200 እንጂ አሁን ስላልከው የሰማነውም ሆነ የምናውቀው ነገር የለም፡፡"

"ስለማወቅ ያለማወቅህ ምንም የሚያገባን ነገር የለም፡፡ ከላይ የመጣ ትዕዛዝ ነው እስረኛውን ስጠን!"
ጠባቂው የክላሹን መጠበቂያ ከፈተና "ልታስመልጡት ነው!" ተፈናጥሮ ቦታ እየያዘ ደግኖበት ቆመ፡፡
"አታ.....ምን ያወራጭካል ማጣራት ትችላለህ ራዲዮ አድርግ" አለ ሊወስዱት ከመጡት መካከል አንደኛው፡፡
ሁለተኛው ጠባቂ ራዲዮኑን አነሳና ከ "ግዳይ 200" ሀላፊዎች መካከል አንዱ በፍጥነት እንዲላክላቸው ጠየቀ፡፡
ከደቂቃዎች በኋላ አንድ ሃምሳ አለቃ መጣና ትክክል መሆኑን ገልፆ እስረኛውን እንዲያወጡ አዘዛቸው፡፡

አቶ መርድ በሁለት ታጣቂዎች ክንድና ክንዳቸው ተይዞ እየተጐተቱ ወጡ፡፡ በድብደባው በደረሰባቸው ጉዳት ደማቸው በብዛት በመፍሰሱ አካላቸውን መሸከም ተስኖዋቸው ነበር፡፡

እየተጠማዘዙ ወስደው በአንድ ጉብታ በኩል ሲያወጧቸው ከመሬት ስር የተሰራ ቦታ እንደደረሱ አወቁ፡፡

ከዛም ሁለቱ ወታደሮች ከሃምሳ አለቃው ጋር ፈንጠር በማለት በሹክሹክታ ሲነጋገሩ ቆዩና መልሰው ከመሬት ስር ወደተዘጋጀ ሌላ ጠባብ ስፍራ አስገቡዋቸው፡፡ ቦታው የተስተካከለ አራት ማዕዘን ቅርፅ ያለው ሆኖ ከላይ ግን ምንም ዓይነት ከለላ የሌለው ነበር፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“ፊት ለፊት አስደግፋቸው” አለ ሃምሳ አለቃው፡፡ ከዛም ወደ አቶ መርድ እያየ “በቀረችዎ የደቂቃ እድሜዎ ውስጥ.....የሚሉን ተጨማሪ ነገር አለ?”
“እ.....ለ...ምን....ልገደ....ል ነው እንዴ?” አቅም ለማሰባሰብ እየጣሩ ጠየቁ፡፡

ታጣቂዎቹ አስደግፈው ከአስቆሙዋቸው በኋላ ስድስት ሜትር ያህል ተፈናጥረው ቆሙ፡፡

አቶ መርድ ፍፃሜ መሆኑን አወቁ፡፡ ወደ ሰማይ ቀና ብለው ቆዩና በንዴት ወደ ሃምሳ አለቃውና አራቱ ታጣቂዎች በየተራ እያፈጠጡ “እንድ ታሪክ ልንገራችሁ.....”
ቀጠለ “.....በ1960 እና 70ዎቹ በአሜሪካ ውስጥ.....ይገኙ የነበሩ ጥቁር ፖሊሶችና ጥቂት የሆኑ ጥቁር የበላይ ሀላፊዎች.....ካሉበት የኑሮ ሁኔታ በጥቂቱ ለሚልቅ የቁሳቁስና ፍርፋሪ መደለያ ከነጮቹ እየተወረወረላቸው..... የገዛ ጥቁር ወገኖቻቸውን ካለ ምንም ወንጀልና ሀጢያት በጠራራ ፀሀይ በየጦዳናው በጥይት ይጠብሷቸው ነበር፡፡.....ለሆዳቸው እየተሸጡ ጥቁር ወንድምና እህታቸውን ለስቃይ እያሳለፉ ይሰጧቸው ይሸጧቸውም ነበር፡፡..... እናንተም ዛሬ እንደዛው ናችሁ..... አንድም ለሆዳችሁ አልያም የዛፍ እንቅልፍ ለሆነው የወያኔ ስልጣን ጥም ስንቱን ንፁሀን ወገናችሁን ፈጃችሁት.....” ማለት የፈለጉትን መግለፅ ስላቃታቸው ጥርሳቸውን ነክሰው ቆዩና ስለራሳቸው መናገር ቀጠሉ

“.....በንፅህናዬ ነው የምገደለው፡፡ ይህንንም እያወቃችሁ ልትገድሉኝ ፊቴ ቆማችኋል፡፡ ጨካኞች.....ለነገሩ ለዘላለማችሁ የምታካብቱት የህሊና ስቃይ ከሞታችሁ በፊትም ይሁን በኋላ እያባነናችሁ ይኖራል.... በሉ ግደሉኝ..... ግደሉኝ!”
ሃምሳ አለቃው በጊቢው ውስጥ በተለየ ጭካኔው ይታወቃል፡፡ ይህንን መሰል ውሳኔዎችን ካለ ማንገራገር የሚያስፈፅም በመሆኑ «ገናገዙ» የሚል ቅጥያን አግኝቷል፡፡ ሁሌም የሚረሽናቸውን ሰዎች የመጨረሻ የጣር ቃል መስማት እጅግ ያዝናናዋል፡፡
“መሀይሞች!” ተሳደቡ አቶ መርድ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

“ማነው መሀይም!?” ሃምሳ አለቃው አፈጠጠ
“አንተ!.....እና ወያኔ.....እና አራጋቢዎቻችሁ..... መሀይም!”
“አታ!.....ግቻ ሽማግሌ.....በተልዕኮ ትምህርት መንግስት ያውም ከእንግሊዝ አገር በፖለቲካ ሳይንስ ዲግሪ እንዳገኝ አድርጐኛል” አለ ሃምሳ አለቃው በንዴት፡፡
“ካ...ካ...ካ...ካ....” ሳቁበት አቶ መርድ፡፡ ቀጠሉ “.....ኢትዮጵያን ልትመራልን ነዋ....ካ.... ካ.....ካ...”
“አንተ የአፍሪካን አንድነት ወደ አፍሪካ ህብረት እንዲሸጋገር ካበቁት ተሳታፊዎ መካከል እኔም በስብሰባው ላይ ነበርኩኮ፡፡” አለ ሃምሳ አለቃው በወቅቱ በስብሰባው ላይ ተሳታፊ የነበሩትን የወያኔ ባለስልጣናት ደህንነት ተሰብሳቢ መስሎ በመግባት እንዲጠብቅ የተላከ መሆኑ ሳይገባው፡፡

“አሃ....ከእንግሊዝ ተገዝቶ በመጣልህ ዲግሪ አፍሪካን አንድ ልታደርግልን.....” አሉ አቶ መርድ በስላቅ
“አፍክን ዝጋ!” ሃምሳ አለቃው አምባረቀ፡፡
“ስለምገደል የመናገሩን ዕድል ሰጥተኸኝ የለም እንዴ....”
ቀጠሉ “... ሆዳችሁ ህሊና ሆናችሁ እናም በሆዳችሁ ታስባላችሁ፡፡ በሆዳችሁ አገር ትመራላችሁ ጠባብ ብሔርተኝነታችሁም ከሆዳችሁ የመነጨ ነው፡፡ እውቀታችሁ ከነመሪዎቻችሁ ተቀብሮ እንደበሰበሰ የሬሳ ግማት ሆኗል፡፡ ብትከፍቱትም ጥንባቱ ሌላ የብሔርተኝነት ተስቦን ፈጥሮ አገር ከማፈራረስ ውጪ ቅንጣት ጥቅም የለውም፡፡

ቀጠሉ “.... ከሰው መካከል የመቀላቀያ መፈክራችሁ ግን “ነፃነት ፣ የብሄር ብሄረሰቦች እኩልነት፣ ዲሞክራሲ፣ ፍትህ፣ ነው..... ማፈሪያዎች!.....”
“ቧ.....ወዲ ሸርሙጣ..... በቃ ረሸን!” አዘዘ ሃምሳ አለቃው፡፡
የተኩስ እሩምታ ናጣቸውና መሬት ላይ ተዘረሩ፡፡

««««««« »»»»»»»

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

እሁድንና ሰኞን ቦሌ ሆነው መምጣታቸውን ሲጠባበቁ የነበሩት የጋዜጣ አሳታሚ ድርጅት ሪፖርተሮች የሁለተኛው ቀን ምሽት ላይ 'እዛው አሜሪካ ቀርተው ይሆናል' በማለት ተበተኑ።።

የ "ግዳይ 200" አደንም ቀጭኗን ፍንጭ ይዞ ሩጫውን መስፍን ወደ ተባለው ሪፖርተር ላይ ቀጠለ።።

  

የማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ምዕራፍ 31

በኘላኔታ ውስጥ ያሉት ሀያላን ገዢዎች መጪውን ዘመን ዓለምን ካለ ተቀናቃኝ በበላይነት የመምራት ትልማቸውን እውን ለማድረግ ሁሉም እንዳካበቱት የእውቀት፣ የሀብትና የስልጣኔ ደረጃቸው ፉክክራቸውን ቀጥለዋል።

በፈንቅሎ መውጣት ፍትጊያው ውስጥ ፈረንሳይ ወደላይም ወደታችም ሳትሆን ሀያላን ከተባሉት ጋር የጨዋታውን ኳስ እኩል እየተላጋች ነው።

መንግስትም ህዝቡም በየፊናው አገሩን አሸናፊ ለማድረግ ይራወጣል። የተማረው በዕውቀቱ፣ ባለሀብቱ በገንዘቡ፣ ባለስልጣኑም በሀላፊነቱ፣ ጭብጥ የማትሞላ አዲስ ሀሳብ ያለውም ተራ ሰዉ ቢሆን ሌተቀን ይሮጣል። ስራ.....ትምህርት፤ ስራ.....ምርምር፤ ስራ.....ውጤት፤ ስራ.....ገንዘብ፤ ስራ.....መጨረሻ ላይ ሁሉን ማንበርከክ የሚችል ሀይልን መቀዳጀት።

አቅም ያለው ደካማውን ይደግፋል። የቆመው የወደቀውንም ሆነ በመውደቅ ላይ ያለውን ያነሳል። ደካማው አቅም ሲያገኝ ከሱ ባስ ያለውን ይቸረዋል። ስጦታዎች ሲባሉ ገንዘብና ቁሳቁስ ብቻ አይደሉም። የተማረው ያልተማረውን እንዲማርና በእውቀት ከሱም ልቆ እንዲገኝ ያበረታታዋል፣ ይደግፈዋል። ጋሬጣዎችን ይመነጥርለታል።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

በፈረንሳይ ውስጥ ሁሉም ለፈረንሳይ እድገት ግንባታ ልትሆን የምትችል ቅንጣት ሀሳብ መክና እንድትቀር እድል አይሰጣትም። በውይይት መድረኮች ትዳብራለች። በሀሳብ ልውውጥ ጡዘት የፈንጅ ያህል እምቅ እስክትሆን ድረስ ትሞላለች። ከዛም ወደ ግቡ ትተኮሳለች። ለፈረንሳይ አንድ እድገት።

በዚህ ውስጥ የወጣትነትና የወጣቶች ሚና እጅግ ታላቅ ነው። አፍላ ወጣቶች የነገዋን ፈረንሳይ ተረካቢ ናቸውና ይከበራሉ። ይወደዳሉ። የአዲስ ግኝት መሰረትነታቸው ማጣቀሻ ሳያሻው ይታመንበታልና እንደ ውድ ሀብት ይጠበቃሉ። ሀሊናቸው አገር ሊጐዳ ወደሚችል አቅጣጫ እንዳይጓዝ በጥንቃቄ ይሞረዳል።

የመማር፤ የመስራት፤ የመናገር፤ የመፃፍ..... መብቶቻቸው ካለ ማገጃ ክፍት ነው። አራት ነጥብ በማይታወቅበት መስመር ውስጥ ሀሊናቸው እንዲወነጨፍ ተፈቅዶላቸዋል። ወጣትነት አዲስ ሀሳብ..... አዲስ ንድፍ..... አዲስ ግብ..... ለእናት ፈረንሳይ ሀያልነት..... ወጣትነት ገና እንዳልተቆፈረ የምድር ውስጥ ውድ ሀብት ነው። ይህን የሚያውቅ ስልጡን መንግስታቸው በወጣቶች ላይ እንኳን ጥይት በትር እንዲያርፍባቸው አይፈቅድም።

የማንም ሀያል አገር እድገት የመጣውም ሆነ ወደፊት እያደገ የሚሔደው መንግስታቶች ለህዝቦቻቸው በተለይ ለወጣቱና ቀጣዩ ትውልድ ፍቅር ሲኖራቸው ብቻ መሆኑን ያውቁታል። አገራዊ ባህላቸውም አድርገው ይዘውታል።

ሉዊስም አገራዊ ሀላፊነት እንዳለበት እንደማንኛውም ዜጋ ከግል ስራዎቹ በተጨማሪ በተለያዩ ተግባራት ላይ ተሰማርቶና ስራ በዝቶበት ነበር የሰነበተው። ትልልቅ አገራዊ ስብሰባዎችን በቀረቡለት ጥያቄዎች መሰረት መርቷል። የፈረንሳይ ስልጣኔና ቀጣይ ራዕይ የሚያሳዩ ሁለት ኤግዚቢሽኖችን በተባባሪነት አሳይቷል። ለፈረንሳይ ወጣቶችና ቀጣይ ትውልድ ቅርስ ሊሆኑ የሚችሉ ሁለት ግዙፍ የባህል ማዕከላትን በራሱ ወጪ ሊያሳንፅ ፊርማውን አሳርፏል።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ከዚሁ ስራ ጐን ለጐን የግሉን ስራ ከማካሔድ አልገታም፡፡ ለሱም ሲል በሩሲያ ለአስር ቀን በቻይና ለሰባት ቀን በሆንግ ኮንግ ለአራት ቀን ቆይቶ ወደ ፈረንሳይ ተመለሰው ትላንት ማታ ላይ ነበር፡፡

በቀጣዩ ዕለት ማልዶ በመነሳት ወደ ቢሮው አመራ፡፡

ፒየርም ከፓሪስ አይውጣ እንጂ ለጀመሩት ስራ ተጨማሪ ውሎችን ሲቀበልና የተጀመሩትን ፍፃሜም ሲቆጣጠር ነበር የቆየው፡፡ “የማትኖረው ኢትዮጵያ” የሚል ስያሜ ተሰጥቶት ከየ ጐሳዎቹ መካከል በህቡዕ የተደራጁ ሰዎችን በመመልመልና ግጭቶችን በመፍጠር አገሪቷ እንድትከፋፈል ማድረግ በሚል መሪ እቅድ እየሰሩ ስላሉት ስራዎቻቸው ለመነጋገር ፒየር ወደ ሉዊስ ቢሮ አመራ፡፡

ሉዊስ ቢሮው ሆኖ ለሃያ አንድ ቀናት የተከማቹና በሱ ሊከናወኑ የሚገባቸው የስራ ፋይሎችን እያገላበጠ ነበር፡፡

የቢሮው በር ሲከፈት ቀና አለ፡፡ አጭር ሰላምታ ተለዋወጡና “.....ኢትዮጵያዊቷ ሴትዮ እንቅስቃሴ ምን ላይ ደረሰ?”

“ጥሩ እያስኬደችው ነው፡፡.....እሷ ግን ለጥቂት ከሞት ማምለጧን ገለፀችልኝ”

“እንዴት?” አለ ሉዊስ እይታውን ፒየር ላይ ተክሎ፡፡

“እንቅስቃሴዋ በመንግስት ሳይደረስበት አልቀረም”

“እንዴት ሊታወቅ ቻለ?”

“እሷም አታውቀውም ፡፡ ምናልባት ከመለመለቻቸው ሰዎች መካከል በአንዱ በኩል ለመንግስት መረጃ ደርሶት ሊሆን ይችላል፡፡” በማለት ከሰናይት የተላለፈለትን መልዕክት በዝርዝር አብራራለት፡፡

“አሁንስ በምን ሁኔታ ላይ ትገኛለች?”

“ አስፈላጊውን ጥንቃቄ እንድታደርግ አዝዤያታለሁ”

ሉዊስ በዝምታ ሲያዳምጥ ቆየና “.....እንደምንም ለቀጣዩ አንድ ወር ብትቆይልን እቅዳችን እስከዛ ድረስ ተፈፃሚ የሚሆን ይመስለኛል፡፡ ከዛ በኋላ እንኳ የሴትየዋ አስፈላጊነት ያከትማል....” ብሎ “.....ለመሆኑ እዛ ያሉት የመረጃ ሰዎቻችን የሚልኩልን ሪፖርት ጥሩ ነው?”

“ከተጠበቀው በላይ!..... ኢትዮጵያ ዙሪያዋን ታውካለች በተለይ በኦሮሞ ክልሎች ላይ የተመለመሉት ሰዎች ለገዢው መንግስት ፈታኝ ሆነውበታል”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ሉዊስ በደስታ ፈገግ አለ፡፡
ቀጠለ ፒየር “አንተስ የሂድክበት ስራ የተሳካ ነበር?”
“ሁሉም በእርኪ ሁኔታ ተጠናቋል”
“የጠር መሳሪያዎቹ ተጫኑ?”
“አዎ፡፡”
“በስንት መርከብ?”
“በአምስት ግዙፍ መርከቦች”
“የመሳሪያዎቹ ብዛትና አይነትስ?”
“እንደተወያየንበት ነው የተደረገው፡፡ በብዛት የነፍስ ወከፍ የሆኑ ናቸው፡፡ ክላሺንኮቭ ጠመንጃዎች፣ መትረየሶች፣ ላወንቸሮች በቁጥር ወደ አምስት ሚልየን ይደርሳሉ፡፡ እንዲሁም ሞርታሮችእና በሞርታር መጠንና ቅርፅ የተሰሩ ርቀት ተወንጫፊ ሚሳኤሎች ይገኙበታል፡፡ የመርዝ ጋዝ ተሸካሚ ቦንቦችን ማስወንጨፍ የሚችሉ መሆናቸው በፋብሪካዎቹ ተገልያልኛል፡፡
ፒየር “አዲስ ምርቶች ናቸው?” ጠየቀው፡፡
“አዎ.....ገና መፈብረካቸው ነው፡፡ እግረ መንገድ ምን ዓይነት አመርቂ ውጤት እንዳላቸው በተግባር በኢትዮጵያ መሬት ላይ ይታያሉ ብለዋል ሳይንቲስቶቻቸው፡፡..... እነዚህ እንግዲህ ከበርካታ ጥይቶቻቸው ጋር ሲሆን ፀረ-ሰው እና ተሽከርካሪ ፈንጂዎች፣ ቦምቦችና፣ ሽጉጦች ጭምር ናቸው የተጫኑት፡፡”
“አጠቃላይ ግምታቸው በገንዘብ ቢተመን ምን ያህል ይደርሳል?”
“እ.....በእርዳታ ጥያቄያችን ሶስት መቶ ሃምሳ ሚልዮን ዩ.ኤስ. ዶላር የሚያወጣ ያገኘን ሲሆን የሁለት መቶ ሃምሳ ሚልዮን የሚሆን ከራሳችን ሂሳብ ወጪ አድርገን ገዝተናል፡፡ ከፋብካዎቹ በስጦታ መልክ በርካታ መሳሪያዎች ተጨምረውልናል፡፡”
“ይህ ሩዋንዳ ቡሩንዲ ላይ ከደረሰው ሀያና ሰላሳ እጥፍ ውጤት ማስገኘት የሚችል ብዛት ያለው መሳሪያ ነው፡፡ ኢትዮጵያን ለመበታተንም ሆነ ምናልባት ምስራቅ አፍሪካ መቼም የማትወጣው የቤት ስራ ውስጥ ለመክተት በቂ ነው ብዬ አምናለሁ” አለ ፒየር፡፡
“ምን ችግር አለ፡፡ ካልበቃ ቀጣይ ዙር ይላክላቸዋል”
“ የኛስ ድርጅት በትክክል የሚያገኘው ትርፍ በትክክል ታወቀ? ”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“ ገና ነው አልታወቀም:: በአካባቢው ላይ በሚፈጠረው መተራመስ እና ጦርነት ጥቅም እናገኛለን ብለው የሚያምኑ አካላቶች ለእቅዱ መካሳት ገና ገንዘብ እየላኩልን ነው:: እካስሁን የደረሰን የባንክ አካውንት ሪፖርት እንደሚያሳየው ወደ ሶስት ቢልዮኝ ዶላር መከማቸቱን ነው ” አለ::
“መርከቦቹንስ ከየአገሮቹ መንግስታት ነው የተከራየኸው?”
“አይ.....ዋጋ እንዲቀንስ ብዬ.....ከህገ-ወጥ አጓጓዥ ግለሰቦች ላይ ነው፡፡”
“ወደብ መቼ ይደርሳሉ?”
“እ.....” የተነሱበትን ቀን አሰበና ከስንት ቀን በኋላ እንደሚደርሱ በነገሩት መሰረት አስልቶ “የነገ ሁለት ሳምንት”
“አሁን በጉዞ ላይ ናቸዋ?”
“አዎ.....ሰሜን ሰላማዊና ህንድ ውቅያኖሶችን እየሰነጣጠቁ ይገኛሉ፡፡” ፒየር ይዞ የገባውን ፋይል እየገለፀ ከሰናይት የተላለፈውን መልዕክት አውጥቶ “.....በትግራይ ላይ ለሚንቀሳቀሰው ቡድን የጦር መሳሪያዎቹን በቅርቡ ወደ ኤርትራ እንዲቆረጥ በተደረገው ወደብ በኩል ይግባልን በማለት ጠይቋል፡፡”
“በኤርትራ?.....”
“አዎ”
“እንዴት ከነሱ ሊግባባ ቻለ?”
“በወቅቱ ስልጣን ላይ ያሉትን ሰዎች አስቀድሞ የሚያውቃቸው በመሆኑ ይመስለኛል፡፡ ዋናው ያስማማቸው ነጥብ ግን ይህ አይደለም፡፡”
“ታዲያ ምን?.....”
“የኤርትራ መሪዎች በአሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያን ሰላምና አንድነት ስለማይደግፉ ባላቸው የስልጣንና የጥቅም ክፍፍል ግጭት ምክንያት በቀላሉ ሊተባበሩት እንደፈቀዱ ነው የገለፀልን፡፡”
“አሳማኝ ነው.....ቀላል አቅጣጫን አስበዋል፡፡” አለ ሉዊስ ጥቂት ቆይቶም “.....በጣም ጥሩ ከሩሲያ የሚነሱትንና በቀይ ባህር የሚጓዙትን መርከቦች የጉዞ አቅጣጫ ወደዛ እንዲዞር በፋክስ ትዕዛዙን አሁኑኑ ማሳለፍ እንችላለን” ብሎ ማስታወሻ ሲይዝ ቆየና “እ.....መሳሪያውን ከየመርከቦቹ የሚረከቡበትን ደብዳቤዎች ለአምስቱም የህቡእ መሪዎች

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ስም ይዘጋጅና ይላክላቸዋል..... ቢበዛ በሶስት ቀን ውስጥ ሊደርሳቸው ይገባል፡፡"
"ከሱ በፊት ግን ክፍያዎች በብዛት ጠይቀዋል" አለ ፒየር፡፡
"ምን ያህል?"
"ሰናይት በአማራው ክልል ላይ የሚሰራ አንድ ከፍተኛ ወታደራዊ የመንግስት ባለስልጣን ማግኘቷን ገልፃልኛለች፡፡"
"መልካም ነው፡፡.....በሁሉም ስፍራ መንቀሳቀስ የሚችሉ ሰዎችን አሟልታለች፡፡ ከገመትኩት በላይ ፈጣን ሰው ሆና ነው ያገኘኋት"
"አዎ..... ጋዜጣ አሳታሚ ሆና በመቆየቷ ስለ አገሪቷም ሆነ የት ሄዳ ማንን በማግኘት መጠቀሚያ ልታደርግ እንደምትችል ቀድማ እንድታውቅ አስችሏታል::"
"እሺ ምን ምን ጠየቁ?" አለ ሉዊስ ማስታወሻ ለመያዝ ብዕሩን እያመቻቸ
"እ..... የአማራውን ክፍል የሚያንቀሳቅሰው ሰላሳ ሚልዮን ዶላር..... የደቡቦቹ ሀያ ሚልዮን የትግራዩና የኦሮሞው አርባ አርባ ሚልዮን..... ጠይቀዋል:: የጠየቁት በጣም ብዙ ቢሆንም ይሄ ወሳኝ ወቅት በመሆኑ ይላክላቸው:: በቀጣይነት ግን ምን ያህል እንደምንሰጣቸው እኛ ነን የምንወስንላቸው" አለ ፒየር::
ሉዊስ አጠቃላዩን አሰላና "እስካሁን ወደ ስድስት መቶ ሚልዮን ዶላር የሚጠጋ ገንዘብ ወጪ አድርገናል የአሁኑ ሲጨመር ወደ ሰባት መቶ ያልፋል..... በእቅዳችን መሰረት ከአሁን በኋላ የቀረው ወጪ ክፍያ ሁለት መቶ ዘጠና ሚልዮን የሚሆን ነው፡፡"
"ጥሩ አስኪደነዋል ከስራው አንፃር ሲመዘን" በማለት ፒየር ተናገረና የዘነጋው አንድ ጥያቄ መኖሩን አስታውሶ ".....በተጨማሪ የመድኃኒት እርዳታ እንደሚፈልጉ ተጠይቋል"
"መድኃኒት.....?"
"አዎ"
ፒየር ብዕሩን ጠረጴዛው ላይ እየወረወረ "አይሆንም በላቸው..... ከእቅዳችን ውጪ ነው፡፡" አለ ጠንከር ባለ ቅላፄ
"እንደምንችል ነግሬያቸዋለሁ፡፡"
"አግባብ አላደረክም.... በግዢ ካልሆነ በስተቀር እንዴት ማግኘት እንችላለን በማለት አስበህ ነው?" አለ በቅሬታ ተውጠ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“ረዥም ጊዜ ሰጥቼው አስቤበታለሁ፡፡”
“በነፃ ማግኘት የሚያስችለን መፍትሔ አለህ?”
“ይመስለኛል.....” ብሎ ጥቂት ቆየና “የመድኃኒቶቹ ፋብሪካዎች ተዘዋዋሪ ጥቅሞችን እንዲያገኙ በማስቻል ነው”፡፡
“በምን መልኩ?”
“የሚሰጡን መድኃኒቶች የአገልግሎት ዘመናቸውን ሊጨርሱ ከሶስት እስከ ስድስት ወር የሚሆን ወቅት የቀራቸው እንዲሆን እንገልፅላቸዋለን፡፡”
“የነሱ ጥቅም ታዲያ ምኑ ጋር ነው?”
“እነዛ መድኃኒቶች በነሱ እጅ ውስጥ እንዳሉ የአገልግሎት ዘመናቸው ቢያበቃ የማስወገዱ ስራና ሀላፊነት የራሳቸው ብቻ ነው፡፡ ለሱ ደግሞ ሌላ በጀት፣ ሌላ የሰው ሀይልና ሌላ ጊዜን መድበው ነው እንዲወድም የሚያደርጉት፡፡መድኃኒቶቹ ግን በእርዳታ ሰበብ ለአፍሪካ አገሮች ቢሰጡ ዘመናቸው ሲያልቅ የማውደሙ ስራና ሙሉ በሙሉ የተረጂዎቹ አገርና ወጪ ነው፡፡ትልቁ ጥቅም ግን እሱ ብቻ አይደለም፡፡”

ሉዊስ ነጥቡ ወዳልገመተው ሌላ አቅጣጫ እንደሚያመራ በማወቁ ገና ለማሰብ የፈቀደው ይሄኔ ነበር፡፡
ቀጠለ ፒየር “.....መድኃኒቶቹን በማቃጠልም ይሁን በመቅበር እንዲወድሙ በሚደረግበት ወቅት በከባቢው ተፈጥሮ ላይ የሚያስከትሉትን ብክለትና ውደመት በጠቅላላ በተረጂ አገሮች ላይ ይከናወናል፡፡ አውሮፓ ይህን በመሰሉ መንገዶች ብክለትን ካልቀነሰች ወደፊት ያለው ትውልድ ፈታኝ ሁኔታ ሊገጥመው ይችላል፡፡ ጠቀሜታውን በዝርዝር መግለፅ ቢስፈልግ ከፍተኛ የእፅዋት ውድመት፣ የውሃ መመረዝ ከአየር ብክለት ጋር የሚያያዙ የመተንፈሻ አካል ችግሮች የአፈር ለምነት መበላሸት ካንሰርና መሰል በሽታዎች የኡዞን መሳሳት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ ይህም በዝርዝር ይገለፅላቸዋል፡፡”
“አሳማኝ ሀሳብ ይመስላል” አለ ሉዊስ ለመጀመሪያ ጊዜ በፈገግታ ተውጠ፡፡
“ተጨማሪ የክፍያ ጥቅሞችን ሁሉ ከተረጂዎቹ አገሮች በተዘዋዋሪ ሊያዝቃቸውም ይችላል” አለ ፒየር፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“እንዴት?”
“ከሚሰጡዋቸው መድኃኒቶች መካከል አንዳንዶቹን ማውደም እንደተፈለገው ቀላል ላይሆን ይችላል። የተማረ ባለሙያና ዘመናዊ የሆኑ የማውደሚያ መሳሪያዎችን ሊያስፈልግ ይችላል። ይህ ደግሞ አፍሪካን በመሰለች ጨለማ አህጉርና መሀይም ህዝብ አማካኝነት መከናወን ስለማይችል መልሰው ለፋብሪካዎቹ ከፍለው እንዲያወድሙላቸው ሊጠይቁ ይችላሉ። በዚህም ወደ ኪሳራ እያመሩ በነበሩት መድኃኒቶች ሰበብ ከሽያጫቸው ይገኝ ከነበረው በላቀ ሁኔታ ትልልቅ ገቢዎችን ሊያስገኙላቸው እንደሚችሉም ገልፀን ልናሳምናቸውና የመድኃኒቶቹንም እርዳታ አግኝተን ወደ ኢትዮጵያ ልንልክላቸው እንችላለን።” አለ ፒየር ጨርሻለሁ በሚል ስሜት ወንበሩ ላይ ወደ ኋላ እየተለጠጠ።
“በጣም ጥሩ የመጠየቂያ ደብዳቤዎች ይዘጋጁ” አለ ሉዊስ።
“ተጠናቀዋል። ሳንነጋገርበት እንዳልከው ብዬ ነው ያዘገየሁት”
ሉዊስ ፈገግታው ሳይደበዝዝ እያየው ቆየና በእርካታ ስሜት “መልካም ነው..... እንግዲህ የፈረንሳይ መድኃኒት አምራች ፋብሪካዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ቀዳሚውን እድል እንስጣቸዋ”
“ተመሳሳይ ነው ሃሳባችን” አለ ፒየር።
የደብዳቤውን አንድ ግልባጭ እንዲያነበው ጠረጴዛው ላይ አድርጐለት ለመውጣት እየተነሳ።
“ሰናይት ቀሪውን የስራ ጊዜዋ እያለቀ መሆኑን ግለፅላትና ቀሪውን ጊዜ በጥንቃቄ እንድትጨርስ አስጠንቅቃት። ገንዘቦቹ ዛሬውኑ በፍጥነት ይላኩላት። የመሳሪያ መረከቢያዎቹም ደብዳቤዎች በሶስት ቀናት ውስጥ እንዲደርሳት ይሁን። የሚረከቡት ግለሰቦችም በደብዳቤው ላይ በሚጠቀሰው ዕለት ወደቡ ድረስ በመገኘት ለመውሰድ ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርጉ እዘዣቸው በላት።” ፒየር ትዕዛዞቹን በእሺታ ተቀብሎ ወጣ።

  

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ምዕራፍ 32

መስፍን አብነት ቤት ማደር ከጀመረ ሶስት ቀን ሆኖታል። ጠዋት ላይ ከሰናይት ጋር የተቀጣጠሩበት ቦታ ለመገናኘት ከቤት ወጣ።

ሰናይት መስፍንን በስልክ ለማግኘት የእናቱ ቤት ተደጋሚ ሙከራ ስታደርግ ቆይታ እሱም እይታ ውስጥ እንዳይገባ ተጠንቅቆ ሊጠይቃቸው ሲሄድ ትላንት አመሻሹ ላይ ነበር ያገኘችው። እሱ ወድያውኑ እንዲገናኙ ቢጠይቃትም እሷ ግን ጠዋት እንዲሆን ቀጠሮ ሰጠችው።

ዕለቱ ሰኞ ነው። ግንቦት ከገባ አምስት ቀን ሆነው። እሱ ጠዋት ከቤት ሲወጣ አብነትም ለሊቱ እስኪገባደድ ሲሰል የነበረው ስዕል በክፍሉ ውስጥ የፈጠረው የቀለም ሽታ እንዲጠፋ አውጥቶ የቤቱን ግድግዳ እያስደገፈ ለማለዳዋ ፀሀይ ሰጥቶ ፈንጠር በማለት ተቀመጠና መፅሐፍ ማንበብ ጀመረ።

ለአንድ ሰዓት ተኩል ያህል ተመስጦ ከነበረበት የመፅሀፉ ውስጥ ዓለም "ታዲያስ አብነት?" የሚል ድምፅ አባነነው ቀና ብሎ አየና "ሰላም ነሽ ቤቲ" እያፋሸከ መለሰላት መፅሀፉንም ዘግቶ "ሰዓትሽ ስንት ይላል?"

"ለአራት ሩብ ጉዳይ"

ድጋሚ አፋሸከና በቀኝ እጁ ትከሻው ላይ ከተኙት ድሬድ ፀጉሩ መካከል አንዱን ዘለላ ጎትቶ ማፍተልተል ጀመረ።

"ዛሬ ደግሞ ቆንጆ ቆንጆ ስዕል ሰርተሀል"

"ወደድሺው?"

"በጣም..... "ምድቡ ናቹራሊዝም ከሚባለው ይመስለኛል"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“አዎ.....”
“ለስሜት በጣም ቅርብ ነው.... ርዕስ ሰጥተኸዋል?”
“ፍቅር ብዬዋለሁ.....”
በዶፍ ዝናብ ውስጥ እርቃን አካል በመሆን ተቃቅፈው ወንዝ ዳር ባለ አሸዋ ላይ የሚራመዱ የሁለት ወጣት ፍቅረኛሞችን ከሚያሳየው ስዕል ላይ እይታዋን ሳትነቅል “ለምን ራቁት አደረካቸው?” ጠየቀችው፡፡
“ተፈጥሮዋችን አርቴፊሻል ቁስ ከጋረደውና ካጨናነቀው ዓለም ነፃ መኖር ስትችል ብቻ ነው እውነተኛ ፍቅር ሊኖረን የሚችለው የሚል ስሜትን ስለገለፀልኝ ይመስለኛል.....”
“ዝናቡስ?”
“እ..... እለት እለት ከተፈጥሮ በሚቸረን ፀጋ እየታጠብን ንፁህ ማንነት ማግኘት እንችላለን ይላል መሰለኝ?”
“ወንዙና አሸዋውስ”
“ዙሪያችን ውብ ህይወት አለ፡፡ እነሱ እኛን ለማኖር በቂ ናቸው.....” እይታዋን ወደሱ መለሰች፡፡
ጥቂት ሲያያት ቆየና መልሷን ሳይጠብቅ “ህይወት አርቴፊሻል በሆነ ነገር ስትከበብና ስትሞላ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ጉድጓድ ትሆናለች” አላት፡፡ አይኖቿ ከአይኑ ላይ ሳይነቀሉ በፀጥታ ስትሰማው ቆየች፡፡
እድሜዋ ከሱ እኩል ይሆናል፡፡ ክብ ፊት ስስ ከንፈሮችና ረዥም ፀጉር አሏት፡፡ ቀለሟ በተለምዶ ቀይ ከሚባሉት ትመደባለች፡፡ ልዩ ውበቷ ግን ዓይኗ ላይ ነው፡፡ትልልቅና ማራኪ ናቸው፡፡ መካከለኛ በሚሰኘው ቁመቷ ላይ ቀጠን ያለ አካል አላት፡፡
ፈገግታዋ መስህብ አለው፡፡
“ለሰላሳ ደቂቃ ያህል እንደሱ ብትቆሚልኝ ለአንድ ስዕሌ ቆንጆ ሞዴል ትሆኚኝ ነበር፡፡” እውነተኛ ስሜቱን ነበር የተናገረው፡፡
“በቃ ሁልጊዜ ያንተ ወሬ ስለ ስዕል፣ ስለ ሞዴል፣ ስለ ቀለም፣ ስለ መስመር.....”
“ማንም ሰው ነገሮችን መግለፅ የሚችለው ከራሱ ልምድ በመነሳት ነው፡፡ ምናልባት ነጋዴ ሆኜ ቢሆን ኖሮ ሱቄ ላይ እንደሱ ቆመሽ በመሸጥ በአንዴ ሚልየነር ታደርጊኝ ነበር እልሽ ሊሆን ይችላል.....”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ሊቀጥል ሲል አቋረጠችውና "ልቃወምህ አይደለም እንደዛ ያልኩህ..... ማለት በቃ ብዙ ነገሮችን ልትነግረኝ ትችላለህ....."
"ለምሳሌ.....?"
"ለምሳሌ....እንደ አንደ ሰዓሊ የምትኖርበት ልዩ ዓለም አለህ ከሰዓሊነቱ ባሻገር ግን በዚህ ዓለም ላይ እንደማንኛውም ሰው እያሰብክ የምትኖርበት ዘልማዳዊ አለም አለህ፡፡ እና እንዳንዴም ቢሆን ዘልማዳዊ ስሜት እንዲኖርህ ስለምፈልግ ነው፡፡"
"ምን ይጠቅመናል?"
"ሰዓሊነቱ የዋሻ ውስጥ ህይወት ነው፡፡ በዛ ውስጥ መኖር መቻልህ አንድ ልዩና ትልቅ ውበት ነው፡፡ በሌላ በኩልም ከብህትውትና የባሰም ፈታኝና የጭንቅ ስፍራ ነው....."
"ይሻለኛል" አላት፡፡ ቀጠለ "ዝም ብሎ ማውራት ምን ፋይዳ አለው?"
መልስ አልነበራትም፡፡ በጊቢያቸው ውስጥ ተከራይቶ መኖር ከጀመረ ከአንድ ዓመት በላይ ያስቆጠረ ቢሆንም ሁልጊዜ አዲስና ፈታኝ አይነት ነው የሚሆንባት፡፡ በጣም ትቀርበውና የዋሻ ሰው ነው ብላ የምታምነው ህይወቱን እንዲያስጐበኝት ትሻለች፡፡ ግን ያንን ለማግኘት የሚያስችሏት መንገዶች በጠቅላላ በሱ በኩል ዝግ ነበሩ፡፡
"ዛሬስ ፀጉርህን እንድነካው የተፈቀደበት ዕለት አልደረሰም?" ጠየቀችው፡፡ በተደጋጋሚ ጠይቃው አንድ ቀን ሊሆን እንደሚችል ገልፆላት በጥበቃ ረዥም ወራቶች አስቆይቷታል፡፡
ሲያያት ቆየና "ትችያለሽ!"
ባለማመን ስሜት ተውጣ ተጠጋችውና በረዣዥም ጣቶቿ ዳበሰቻቸው፡፡ ከዛም በቀስታ እየከፋፈተችው እስከ ጭንቅላቱ ቆዳ ድረስ ዋለለችበት፡፡
"ያረጀ የበርኖስ ቅድጅዳጅ ይመስላል" አለችው በቀልድ ቅላፄ፡፡
"ቢሆንም ከበርኖሱ ፍቅር ይዞሽ ለዘመናት ልመናን በፀሎት መልክ ስታደርጊ ኖረሻል" እየሳቀ መለሰላት፡፡
አብራው ሳቀችና "መቼ ነው ማሳደግ የጀመርከው?"
"አስራ አንድ ዓመት ሆኖታል"
"ሰዎች እኮ ሲያዩህ ዱርዬ ነው ይሉሀል"
"ምንድነው የዱርይነት ብያኔ?"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ቀጠለ “.....ፀጉር ማሳደግ?..... በተለይ በዚህ ዘመን ሰው የመግባቢያ ቋንቋና የግንዛቤ ድርቅ መቶታል። ለኔ የዱርዬነት ብያኔ የሚገባኝ ፀጉር ማሞፈር ሳይሆን መስራት እየቻለ የማይሰራ፣ መማር እየቻለ የማይማር፣ መልካም አቅጣጫዎችን መከተል እየቻለ ሆን ብሎ የሚወላገደው..... ሰው ነው። በአጠቃላይ ተምሮም ሰርቶም አንቱታን አግኝቶም ከሰንካላ አስተሳሰብ ያልፀዳ ሁሉ ለኔ ዱርዬ ነው። ለምሳሌ የዚህ ዘመን የኢትዮጵያ መሪዎች ዱርዬዎች ናቸው። ቋንቋቸውም የዱርዬ ነው። ምክንያቱም እንደሚወዱን እየገለፁልን ግን እያረዱን ነው። አንድ ሊያደርጉን የመጡ የአምላክ አገልጋይነታቸውን እየገለፁልን ግን እየበተኑን ነው። እናም ዱርዬዎች ናቸው።”
“ፀጉር ማሳደጉ ላንተ የሚሰጥህ ጥቅም ምንድነው?”

“አንደኛ አፍሪካዊ የነበረው ለተፈጥሮ እጅግ ቅርቡ የነበረውን የጥንቱ ሰው ማንነቴን ይገልፅልኛል። እንዲሁም የአፍሪካን ህዝብ ጮስቋላ ህይወትና ኑሮ ዘወትር በማሰብ የትግልና የመስራት መንፈስ ይለግሰኛል። በሌላም በኩል ዘመናዊነት ያልተቀየጠበትና ከተፈጥሮ የወረስኩትን ትክክለኛ ውበቴን አይበታለሁ። በሱም ውስጥ ፍቅርን፣ ነፃነትን፣ ህብረትን፣ ሰላምን፣ ደስታን፣ ዝምታን መጮናፀፍ ወደሚያስችል መንፈሳዊ ዓለም ውስጥ እንድመለስና የጥንቱን ሰው ለፈጣሪው ቅርቡ የነበረውን ሰው ፀጋ ወደሚያላብስ ዓለም ውስጥ ይመልሰኛል።.....
“.....የዘመኑ ሰው አናት ግን ዘመናዊነት በዋጠው ገህነም ተከቦ ከተፈጥሮው ርቋል አፈግንጧል። ፍቅርን ተገፏል። ነጋ ጠባ እንደ ገሞራ በጋለው አናቱ ሲጠዝ እየዋለ አሟሟቱን ሲገምድ ይውላል።.....
“.....እናም የፀጉሬ መጮፈር ለኔ ትርጉሙ ከመገለጫዎቹ የላቀ እምቅ ሀይል ነው” አላት።
“ለነገሩ እኔ ራሴ በጣም እቀናብሀለሁ” አለችውና ደግማ በጣቶቿ ደባበሰችው።
“ስዕል መሳል የጀመረከው መቼ ነው?”
“ምናልባት የቀለማትን ዓይነት ከመለየቴ የህፃንነት ጊዜ አንስቶ ይመስለኛል።”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“ህይወቱ ግን ደስ ይላል?”
“የሰዓሊነት?”
“እህ.....”
በዝምታ ጥቂት ቆየና “አዎም.....አይም.....”
“ለምን ሁለቱም ሆነ?”
“እኔንጃ..... ብዙም አይገባኝም.....”
“የምትረዳውን ያህል ንገረኝ?”
“እ.....ረቂቅ በሆነውና በማይታየው መንፈሳዊ ዓለምና በሚታየው ዓለም መካከል ያለ መልዕክተኛ መሆን ማለት ነው፡፡ ሁልጊዜ ከዛኛው ዓለም ወደዚኛው ዓለም የሚላከውን መልዕክት ለሰዎች የማድረስ ረፍት የለሽ ሀላፊነት አለበት፡፡ እናም መሳሳት ማላገጥ መሸሸ በፍፁም አትችይበትም፡፡ በቃ ሁልጊዜ ባለአደራ ነሽ ሁልጊዜ ጭንቅ ላይ ነሽ..... በዛ ላይ ብዙ አደራ እያለው ግን ምንም እንዳይሰጥ የሚመረጥ የኪነ-ጥበብ ሰው አፍሪካዊ ሆኖ ይፈጠራል፡፡”
“እንዴት?”
“በአጠቃላይ ህይወትና ኪነ-ጥበብ በአፍሪካ ምድር የተሳሰረች የመሆኗን ያህል ገሀዳዊ እይታቸውን ግን እጅግ የላላ ነው፡፡ በቃ ኪነ-ጥበብ ከህብረተሰቡ አፈንግጧል፡፡ ወይም ህብረተሰቡ ከጥበቡ አፈንግጧል፡፡ ስለዚህም የሙያው ተሰጥኦ ኖሮሽ መስራት በምትችይው አቅም ሁሉ እንዳትሰሪ ከዙሪያሽ ወዳንቺ የሚንፀባረቁት እይታዎችና ስሜቶች ሰባራነት ያግዱሻል፡፡ እናም ጭንቀትሽን ሳትተነፍሺ ዘላለምሽን እንዳስጨነቀሽና እንደታፈነ ሰው እያሰቃየሽ እድሜሽ ያልቃል፡፡ መኖርሽም ያበቃል”

“ግን ህይወትን የምታጣጥምበት እምነትህ ምንድነው?”
“ህይወት ማለት ለኔ ድቅድቅ ፅልመት በዋጠው ዋሻ ውስጥ በማይታወቅ አንድ አስፈላጊ ምክንያት ተገኝቶ ብርሀንን ለመፍጠር ሌተቀን መትጋትን የመሰለ ትርጉም ነው የሚሰጠኝ፡፡”
“እንዴት አድርገን ነው ያንን ብርሀን መፍጠር የምንችለው?”
ቀጠለ “..... መኖር ግድ ከሆነ ይህችን ተራ ጨለማና ደነዝ ዓለም ላይ በአንድ ነገር ብቻ በርተን ማለፍ እንችል ይሆናል ብዬ አምናለሁ፡፡ የመፅሀፍ ቅዱስ አስርቱ ትዕዛዛት ከተጠቃለሉበት አንዱ ህግ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

በመከወን....." ባለእንጀራህን እንደራስህ አድርገህ ውደድ" የሚለውን ብቻ..... በቃ በሱ ስር ሚልየን መልካምነትን በመከወን ፤ ለሰው ልጅ ቅን በማሰብ፣ ቅን በመስራት ነው ብርሀን ሰርተን እኛም ብርሀን ሆነን ማለፍ የምንችለው።"

ቤቲ አትሰማውም ነበር። አፍቅራዋለች። ይህን የፍቅር ስጦታዋን እንዴት እንደምታቀርብለት ነበር ህሊናዋ የሚያስበው።

በዚህ ጊዜ መስፍን የጊቢውን በር ከፍቶ ገባ።ፊቱ አመድ የተነፋበት ይመስላል። ዓይኖቹ ፈጠዋል። ድንጋጤው የሚያደርገውን አሳጥቶት አካሉን ያወራጭ ነበር።

አብነት እንዳየው ተፈናጥሮ ተነሳና "ምን ሆንክ?"

"እናቴን ፖሊሶች ይዘዋት ሄዱ!"

"ወዴት?"

"እኔንጃ..... በዛ ጉዳይ ይመስለኛል።"

አብነት በሀዘን አቀረቀረ። "እንተን ስላጡ ነው እሳቸውን የያዙት?"

"አዎ..... የጋሽ ከበደን ሚስት እንደያዙዋቸው እሷንም ለመያዣነት ነው የያዙዋት"

"የጋሽ ከበደ ሚስት ግን ተለቀዋል ብለኸኛል አይደል?"

"አዎ....."

"ጋሽ ከበደ ከአሜሪካ ተመለሱ?"

"እመጣለሁ ብለው ነበር። ሚስትየው ግን ያለመምጣታቸውን በስልክ ነግረውኛል።" አለ መስፍን።

"አሁን መፍትሔው ምንድነው?"

"እጄን ሰጥቼ እናቴንማ አስለቅቃታለሁ..... እኔን ብሎ በመጣ ጣጣ እሷ መሰቃየት የለባትም" አለ። ተስፋ በሌለው ስሜት።

"ከአንድ ሁለት ቀን በኋላ እንደ ጋሽ ከበደ ሚስት መለቀቃቸው ስለማይቀር ታግሰህ ብትሸሸግ ይሻላል። አንተ እጃቸው ከገባህ ሊያጠፉህ ይችላሉ።"

መስፍን በአሉታዊ ንቅላቱን ነቀነቀና "ፊፅሞ አይሆንም። የፈለጉትን ያድርጉኝ እንጂ እሷን ዛሬውኑ ማስለቀቅ አለብኝ" ሁሉም በዝምታ ተዋጡ። ቤቲ የንግግራቸው ሚስጥር ስላልገባት ትቁነጠነጣለች።

"እባክህ መስፍን ተረጋጋ።"

መሰፍን መልስ አልሰጠውም።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“ለመሆኑ ከሰናይት ጋር ተገናኝታችሁ ነበር?” ጠየቀ አብነት፡፡
“አዎ”
“አወቀች የናትህን መያዝ?”
“አላወቀችም አልነገርኳትም ራሴ ካልነገርኳት ማን ይነግራታል፡፡ ባዛ ላይ እሷ አወቀች ማለት ለደህንነቷ ስትል ከኛም ትሰወርብናለች፡፡”
“ራስህ እንዴት አወቅክ?”
“ከሷ ጋር እንደተለያየን ስልክ ስደውል ነው ቤት የመጡ ፖሊሶች ጠዋት ላይ እንደወሰዷት የነገሩኝ፡፡”
“ ጋዜጣ ላይ ስላስወጣኸው ዜናስ ያወቀችው ነገር አለ?”
“ የማውቀው ነገር ስለመኖሩ ደጋግማ ጠይቃኝ ነበር፡፡ እንደተመካከርነው አድርጌ ገገምኩባት፡፡ መልሴን ግን በጥርጣሬ ይመስለኛል የተቀበለችው፡፡ ያመነችኝ አይመስለኝም፡፡ ”
“ለመሆኑ እሷስ ምን ላይ እንደደረሰች ነገረችህ?”
“አዎ..... የጦር መሳሪያዎቹን የሚረከቡበት ሰነድ ከነገ ወዲያ ይደርሱሻል ተብሏል፡፡ እሱን እንኳ መስረቅ ቢቻል ቢያንስ መሳሪያውን ወደ ኢትዮጵያ እንዳያስገቡት ለማስደረግ አንዳንድ ሙከራዎችን ያስሞክረን ነበር” አለ በቁጭት
“ሰነዱን ለሷ የሚያመጣላት ማነው?”
“ክፍያዎችን የሚያስተላልፍላት አንድ ነጭ አለ” በሱ በኩል ነው፡፡
“ እጇ ላይ እንደደረሰ በአንድ ዘዴ መስረቅ ነው ያለን አማራጭ፡፡”
“እኔንጃ..... ራሷ ሰናይት ከሚገባው በላይ ተጠራጣሪ ሆናለች፡፡ እኔን እንኳ እንደ በፊቱ ልታምነኝ አልቻለችም፡፡”
“አደገኛ ጌም መሆኑን መርሳት የለብህም፡፡ ቤቷን አሳይህለው ብላኛለች ብለህ ነበር....”
“በፊት ብላኝ ነበር.....ዛሬ እንኳን ቤቷን ስልኳን ልትሰጠኝ ፈቃደኛ ያለመሆኗን ገለፀችልኝ፡፡ ስትፈልገኝ ራሷ ደውላ በቀጠሮ እንደምታገኘን ነው የነገረችኝ፡፡”
“ሁኔታዎች ድፍንፍን እያሉብን ሄደዋል፡፡ ከፊታችን ተጋርጦ የሚታየው ትልቅ አደጋ ብቻ ነው፡፡ በዛ ላይ የእማዬ መያዝ.....” አለ መስፍን በብስጭት፡፡ ቀጠለ “.....ያም ሆነ ይህ ቀሪው ስራ ከአሁን በኋላ ያንተ ብቻ መሆኑ ይሰማኛል፡፡ እኔ ዛሬን እጠብቅና ካለቀቋት ነገ ጠዋት ሄጄ እጄን እሰጣለሁ፡፡”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“ግዴለም አረፍ በልና በደንብ እንነጋገራለን” አለው አብነት በዚህ ወቅት ላይ የመስፍንን ሀሳብ ለማስለወጥ መሞከር ዋጋ እንደሌለው እያሰበ፡፡
“ለማንኛውም መስራቤት ሔጄ ደሞዜን ልቀበል፡፡ ከለቀቋት ራሴ ሂጄ እሰጣታለሁ፡፡ ካለበለዚያም አንተው ታደርስላታለህ፡፡”
“ከሰዓት ሂደህ ትቀበላለህ አሁን አረፍ በል”
“ምን ችግር አለው አሁኑኑ ሂጄ እወስዳለሁ”
“ቆይ አብረን እንሂድ እሺ.....”
“በጭራሽ አታስፈልግኝም፡፡ አሁኑኑ እመለሳለሁ” ብሎት ወደ መውጫው በር መራመድ ጀመረ፡፡
“ተጠንቀቅ እሺ”
ምንም ሳይለው ወጥቶ ሂደ፡፡
“ምን ሆኖ ነው?” ጠየቀችው ቤቲ
“እናቱን አስረውበት”
“ለምን?”
“ዝርዝሩ ረዥም ነው..... ምንም በማያውቁት የስልሳ ሰባት ዓመት አሮጊት ማሰር....ቅንጣት ታህል ሰብዓዊነት ያልፈጠረበት መንግስት....” አለ አብነት በምሬት፡፡
“ወንጀል ሰርተው ነው?”
“የምን ወንጀል?.... ኢትዮጵያን ስለመበታተን የታደቀ አንድ ሴራ የሚያጋልጥ ዜና በጋዜጣ ላይ በመፃፉ ሊያስሩት እየፈለጉ ነው፡፡”
“አሃ....እሱን ሲያጡት ነዋ እናቱን ያሰሩዋቸው.....”
“አዎ፡፡”
“ዜናው ምን የሚል ነው አንብበኸዋል?”
አብነት እንደማትለቀው ስለተረዳ የተነሳበት ተመልሶ እየተቀመጠ ፓሪስ ታቅዶ ባህር በመሻገር በኢትዮጵያ ውስጥ እየተካሔደ ስላለው እንቅስቃሴ የሚያውቀው ድረስ ዘርዝሮ ነገራት፡፡ መጨረሻ ላይም “ይቺን ፈተና የከበባትን አገር ከመጣባት ጥፋት የማዳኑ ሀላፊነት የወደቀው በዚህ በኛ ትውልድ ላይ ነው፡፡” አላት፡፡
“አቢ..... ልትፈቅዱልኝ ከተስማማችሁ ባለኝ አቅም ሁሉ አብሬያችሁ ለመስራት ፈቃደኛ ነኝ”
“ከልብሽ ከሆነ.....”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

«««««« »»»»»»

መስፍን ከጊቢው እንደወጣ በደመ ነፍስ እግሩ እንደመራው እየተራመደ ወደ አምባሳደር አቅጣጫ ነበር የተጓዘው።

በቀጣይነት ምን ቢወስንና የትኛውን እያስቀደመ የቱን ቢከተል ሁኔታዎችን ተቆጣጥሮ ማስኬድ እንደሚችል ደጋግሞ ለማሰብ ሞከረ። ግን ቅርፅ የያዘና ጥርት ብሎ ሊታየው የቻለ መፍትሄን አላገኘም። ሀሊናው በዚህ የተተረማመሰ የሀሳብ ጡዘት እንደተዋጠ ከአምባሳደር ሲኒማ ፊት ለፊት ያለውን የዋናውን የአገር መከላከያ ሚኒስት መስራቤት ሁለት ጊዜ ዞረው። በሶስተኛው ዙር ይዞት ከጠፋው ሀሳብ በአስደንጋጭ ሁኔታ ያባነነው በንግድ ባንኩ ፊት ለፊት አቅጣጫ ከሚገኘ ው የመከላከያ ሚኒስትር መስራቤት በር አካባቢ ራሱን ከእይታ ሰውር አድርጎ የቆመ አንድ ወታደር ክላሹን በሚያስፈራ ሁኔታ አቀባብሎ እየደገነበት "አታ በማዶ ተሸግረህ እለፍ! ተሸገር!" ብሎ ሲጮህበት ነበር። ቅድም በየት በኩል እንዳለፈ እንኳ ለማስታወስ ፋታ ሳያገኝ ደንግጦ ወደ ባንኩ አቅጣጫ ለመሻገር አስፓልቱ ውስጥ ሲገባ ከብሔራዊ ትያትር አቅጣጫ ወደ ቸርቸል ጎዳና የሚከንፍ ሚኒባስ ታክሲ ክላክሱን እያናባረቀበት ለጥቂት ስቶት አለፈ።

መስፍን ተሻግሮ ጥቂት እንደተረጋጋ ወዳስደነገጠው ወታደር ዞረ። ወታደሩ ኮስማና ሀውልት በመሰለው አቋሙ ሸሽግ ብሎ እንደቆመ በገዛ አገሩ ላይ «አገር ሰላም» ብሎ የኑሮውን ውጣ ውረድ ለማስፈፀም ወደ ጉዳዩ የሚያመራን ሌላ ንፁህ ዜጋ ድጋሜ ለማስደንገጥ እንደ ተናዳፊ መርዛም እባብ አድፍጦ ታየውና ተገረመ። ወድያው አይኖቹ በመከላከያ ሚኒስትሩ መስራቤት ጊቢ ውስጥ ወደ ቆመው ሰንደቅ ዓላማ ተሳቡና እይታው ባንዲራው ላይ አረፈ።

ይህን ባንዲራ ልጅ እያለ እንደሚያስታውሰው ከሆነ ማለዳ ላይ እና አመሻሽ ላይ በወታደራዊ ሰልፍና በኢትዮጵያ ህዝብ መዝሙር ታጅቦ በክብር እየተሰቀለ በክብር በመውረድ በክብር ተጣጥፎ ወደ ማደሪያው የሚያመራ ሁሌም ንፁህ ሁሌም አዲስ የሆነ የአገር ዓርማ ትዝ አለው። ወድያውም ሀሊናው ለዚህ ባንዲራ ክብርና ፍቅር ሲሉ ላለፉት ሺዎች ዓመታት ስንት ዜጋ ውድ ህይወቱን እንደከፈለለት ስንት ነገስታቶች ከስንት ጠላት ተፋልመው ከነ ሙሉ ክብሩ በማኖር ዛሬ ላይ እንዳደረሱት ታሰበው። ይህ ባንዲራ ማንም ከፃፈውና ማንም ከተናገረው ሁሉ የሚልቅ የአገር የህዝብ የአንድነት የፅናትና የነፃነትን ጣዕምና ታሪክ እጅግ በከበደና

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

በረቀቀ ጥበብ በላዩ አቅፎ የሚኖር የአገር መፅሐፍ መሆኑ ታሰበውና አፍጦበት ቀረ።

ይህ አሁን እያየው ያለው ባንዲራ ግን ቀለሙ ወይቦ ጠርዙ ተበጣጥሶና እንደ ቁጠማ ተተልትሎ ሲታይ ደርግ ተባሮ ይህን የአገር ወታደራዊ ዋና መምሪያ ለኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ሲለቅ ሰቅሎት እንደሄደ ከዛ በኋላ ላለፉት አስራ አንድ ዓመታት የተለወጠ ያለመምሰሉን አጤነ። በሌላ ባንዲራ ተለውጦም ከሆነ እንዲህ እስኪወይብ እና እኪተለተል ድረስ የማርጀቱ ሁኔታ አንድ ብቻ ነው... ሲል አሰበ። እሱም ጠቅላይ ሚኒስትሩ በይፋ እንደተናገሩት «የኢትዮጵያ ባንዲራ የጨው መጠቅለያችን ጨርቅ ነበር» እንዳሉት ይህ ባንዲራ ተለውጦ ቢሆን እንኳ በረሀ እያሉ ጨው ጠቅለለውበት የነበረውን ይሆን እንዴ እያነሱ የሚሰቅሉት ብሎ አሰበ። ይህ ባይሆንማ ስለተሸከመው ታላቅ ታሪክና ክብር ስንት የአፍሪካ አገሮች ከዚህ የነፃነት ተምሳሌት ከሆነው የኢትዮጵያ ባንዲራ ላይ እየቀዱ ሊጠሩበት ባልመረጡት ነበር።

መንገዱን ሲቀጥል ይህ መንግስት ይህን አገር እንዲህ መጥላቱና የአገሪቷን ህዝብ ህሊናና ልቦና ለማቁሰል ለምን እንደጨከነ ምንም ሊገባው አልቻለም። አስፓልቱን ተሻግሮ ወደ ጎተራ የሚጓዝ ታክሲ ውስጥ ገባና ወደ መስራቤቱ ማምራት ጀመረ። በቅሎ ቤት አካባቢ ከሚገኘው የቴሌ መስራቤት ጥቂት ዝቅ ብሎ በሚገኝ አንድ ህንፃ ውስጥ በተከፈተ የግል የመድህን ዋስትና ከፋይ መስራቤት ቅርንጫፍ ውስጥ ነበር የሚሰራው። እሁድን ሳይጨምር ላለፉት ሰባት ቀናት ወደ ስራ ገብቶ አያውቅም። አሁንም የሄደው ደሞዙን ለመቀበልና ተጨማሪ ቀናቶችን የማይገባ መሆኑን ለማሳወቅ ነበር።

ሰዓቱ አምስት ከአስር ብሏል። ከመጣበት ሚኒባስ ታክሲ ወረደና የመስራቤቱን ህንፃ ክፍት በር አልፎ ገባ። በአዳራሽ መሰሉ ሰፊ ክፍል ውስጥ ተስተናጋጅ ደንበኞች በብዛት ይታያሉ። ፊት ለፊቱ የተገጣጠሙትን የመስራቤቱ ባልደረቦች ብቻ ሰላምታ እየሰጠ ወደ ሂሳብ ክፍል አመራና በመግባት "ደህና አረፈድሽ?"
"ታዲያስ መስፍኔ....." አለችው።
"ደሞዝ ወጥቷል?"
"ሶስት ቀን ሆኖታል....የት ጠፍተህ ነው?"
"ጥቂት ቀናት ረፍት ወስጄ ነበር"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

የመፈረሚያ ቅፅ እየሰጠችው "አስተዳደር ክፍሉ ከመጣ እንዲያነጋግረኝ ስለምፈልግ ላኪው ብለውኛል"
"ማን.....እኔን?"
"አዎ"
"ለምን?"
"እኔንጃ"

መስፍን በሀሳብ ተዋጠ፡፡ በመሄድና ያለመሔድ መሀከል ሲያመነታ ቆየና 'አልሔድም' ሲል ወሰነ፡፡ ምክንያቱን ለማጣራት ያህል ግን ቢሮ የምትጋራው ሴት ባልደረባውን አንድ አፍታ ገብቶ ሊያናግራት ፈለገ፡፡

ደሞዙን ተረከበና ከክፍሉ ወጥቶ ወደ ግራ በመታጠፍ አዳራሽ መሰል ወደሆነው ሰፊ የመስተናገጃ ክፍል ገባ፡፡ በመስታወትና በስስ ኮምፔልሳቶ ከተከፋፈሉ ጠባብ ቢሮዎች መካከል አስራ ሶስት ቁጥር የተለጠፈበትን በር ከፍቶ ገባ፡፡
"መስፍንዬ....." ባልደረባው ነበረች፡፡ በድንጋጤ እያፈጠጠችበት "መስፍኔ....ለምን መጣህ..... ፖሊሶች ይፈልጉህል እኮ ነው..... ምን አድረገህ ነው?"
"የትኞቹ ፖሊሶች?"

እይታዋን በግማሽ ኮምፔልሳቶና ከግማሽ በላይ በመስታወት በተሰራው የቢሮው መከፋፈያ ግድግዳ በኩል ወደ ደንበኞች መስተናገጃ አዳራሽ እየሰደደች "እነዛ ሶስቱ ሰዎች አንተን ፍለጋ እዚህ መዋል ከጀመሩ ዛሬ ሁለተኛ ቀናቸው ነው፡፡"
ወጥመድ ውስጥ መውደቁን እያሰበ "የትኞቹ ናቸው?"
"እነዛ...."ብላ ጥቁር ኮት የለበሰውና ሰማያዊ ጂንስ ጃኬት የለበሰው...."
ከሶስቱም አዳኞቹ እይታ ጋር አይን ለአይን ተጋጥሞ ተፋጠጡ፡፡ ቀጠለች ".....አስተዳዳሩም በነሱ ምክንያት መሰለኝ ከመጣ ያነጋግረኝ ብለዋል"
"ምክንያቱ ምን ይመስልሻል?"
"ሰዎቹ ናቸዋ.....በከባድ ወንጀል እንደምትፈለግ ነው የነገሩዋቸው"
"ቻዎ....." አላትና ወደ ቀጣዩ ቢሮ የሚያሳልፈውን የውስጥ በር በመክፈት ገባ፡፡ ከእይታቸው ለመሰወር እየሞከረ፡፡ ክፍሉ ሙሉ ግድግዳው የተሰራው በኮምፔልሳቶ ብቻ ስለነበር ለጊዜው እንዳሰበው

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ከእይታቸው ከልሎታል። የለበሰውን ነጭ ሽሚዝ በፍጥነት አውልቆ ከቀበቶው ውስጥ የነበረውን ጥቁር ቲሸርቱን እያስተካከለ ሸሚዙን "ይቀመጥልኝ" አላቸው ውስጥ ላሉት ሁለት ሴት ሰራተኞች። ከዛም በውስጥ በር ድጋሜ ወደሚቀጥለው ክፍል አለፈ። የዚህኛው ክፍል ግድግዳ ሙሉ መስታውት ብቻ በመሆኑ ወደ አዳራሹ ያሳያል።

ሲዞር ሶስቱም ሰዎች ወደሱ ቢሮ ሲገቡ አያቸው። በፍጥነት ወደ አዳራሹ የሚመልሰውን በር ከፍቶ ወጣና ወደ መውጫው መራመድ ቀጠለ። በሩን ከማለፉ በፊት ግን ጥቁር ኮት ለብሶ የነበረው ሰው ተመልሶ ወጣና ዙሪያውን ሲያማትር ተያዩ።

በሩን አልፎ ወደ ግራው በመታጠፍ በረዣዥም እርምጃዎች ጉዞ ቀጠለ። አስር ሜትር ያህል ሳይርቅ ሶስቱም ወጥተው ሲከተሉት አያቸው።

አንደኛው ሰው ቀይ ቀለም አንቴና ያላት ተንቀሳቃሽ የመገናኛ ሬድዮ አውጥቶ ለአለቃው እንዳገኙት ገለፀ። መስፍን ድርጊቱን በለዘብታ ዞር እያለ ከማየት አልተቆጠበም።

የስልኩን መልዕክት እየተቀበለ የነበረው አባል "እንዳትይዙት እስከመጨረሻው ድረስ ተከትላችሁ የት እንደሚገባ እዩት። በፍጥነት ተጨማሪ የሰው ሀይል ይገፍ እከተላችኋለሁ። መሳሪያ መታጠቁ ስለማይቀር አደጋ እንዳይጥልባችሁ ተጠንቀቁ" አለ የራሱን ድብቅ እቅድ እያሰበ።

ቀጠለ ".....ወዴት ነው እየሄዳችሁ ያላችሁት?"

"አራተኛ ክፍለ ጦር አቅጣጫ በስተግራው መስመር ላይ"

"የንግድ ታርጋ የለፈጠ ነጭ ላንድክሩዘር ይዘን ስለምንመጣ ቀድማችሁ ካያችሁን አስቁሙን"

ሻለቃ ደርበው ጋፈሮ የፈለገ ቢሆን የመስፍን ከነ ህይወቱ መያዝ አይፈልገውም። ምክንያቱም መስፍን ቢያዝ በምርመራ ወቅት ሊያወጣቸው ከሚችላቸው አደገኛ መረጃዎች መሀከል ጳውሎስ ኩንቴን የማጋለጡ ስራ አንዱ ነው። የጳውሎስ መያዝ ደግሞ የሻለቃውን ተባባሪነት ይፋ ሊያወጣው ይችላልና።

ከጠረጴዛው መሳቢያ ሽጉጡን አወጣና የጥይቱን ካርታ ከቶ አቀባበለው። በተጨማሪ ሁለት የጥይት ካርታዎችን ይዞ እየተጣደፈ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ከቢሮው ወጣ፡፡ አንድ ሾፌርና አንድ ነጭ ለባሽ አባሉን አስከትሎ ወደተነገረው አቅጣጫ መክነፍ ጀመረ፡፡

«««««« »»»»»»

መስፍን በፍጥነት እየተራመደ ወደ ኋላ ዞር አለ፡፡ ሶስቱም ሰዎች የሉም፡፡ ደግሞ ዙሪያውን ቃኘ፡፡ ማንም የለም፡፡ 'ጠፋሁባቸው እንዴ?' ራሱን ጠየቀ፡፡ እንደመቆም አለና ድጋሜ አይቶ አስፓልቱን በማቋረጥ ወደ ፒያሳ የሚሄድ ታክሲ አስቁሞ ገባ፡፡

ሚኒባሱ መንቀሳቀስ ከመጀመሩ በፊት በወያላው ተደጋጋሚ ጥሪ አንድ ሌላ ሰው ገባ፡፡ ጉዞ ሊጀምሩ ሲል አንድ ሰው አፏጭቶ አስቆመው፡፡ መስፍን ደነገጠ፡፡ ሰውዬው ደርሶ ሲገባ መስፍን በገቢናው የሾፌሩ የውስጥ መመልከቻ መስታወት አየው፡፡ ሰማያዊ ሸሚዝ ያረገና ክራቫት ያሰረ ሰው ነው፡፡ 'ሌላ ሰው ነው' ብሎ በረኽሙ ተነፈሰ፡፡ ከአንድ ደቂቃ ጉዞ በኋላ መገናኛ ሬድዮ ጥሪ ሲተላለፍ ታክሲው ውስጥ ተሰማ፡፡

ሰማያዊ ሸሚዝ የለበሰው ሰውዬ ጋር ነበር፡፡ አውጥቶ አየውና ሳያነጋግረው ዘጋው፡፡ ጥሪው ተደገመ፡፡ ሰውዬው ከፊት ባለው ወንበር ታዳኙ ሰው ስለነበረ ባናግር ይሰማኛል የሚል ግምት ስላለው ነበር ለማነጋገር ያልደፈረው፡፡ ደግሞ ሲዘጋበት ደግማ ጥሪ ማሰማት ቀጠለች፡፡ በንዴት አወጣትና "አቤት....."
"አዎ..... አስቸጋሪ ነው..... አዎ....."
ሲያዳምጥ ቆይቶ "..... ስታልፉ አይቻችኋለው..... ተላልፈናል .....ብቻዬን..... በሌላ መኪና....."
ምልልሶቹ በመስፍን ህሊና ደዋወሉ፡፡ 'ንግግሮቹ መካከል የጮደሉት ቃላቶች ምን ሊሆኑ ይችላሉ?' ራሱን ጠየቀና እንደ አንድ ጋዜጠኛ አስተሳሰብ እንዲተካ ቢሰጠኝ ብሎ
'....አዎ..... አስቸጋሪ ነው..... አዎ'
'ምኑ ነው ያስቸገረው?' ራሱን ጠየቀና አስከትሎም
'እንትና ነህ?.....'
'አዎ'
'ለምን ዘጋህብኝ ራዲዮኑን?'

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

'አስቸጋሪ ነው'
'ምኑ..... ለመነጋገር ነው ቦታው አመቺ አይደለም?'
'አዎ'
በቃለ ምልልስ መልክ ሞልቶ ጨረሰና 'ሊያስኬድ ይችላል' አለ ለራሱ።።

መሻለኪያ ጋር ሲደርሱ የባቡር ሃዲድ የሚያቋርጥበት ጋር ሲደርሱ የሚያልፍ ባቡር መንገዱን ስለዘጋው አስቆማቸው።። መስፍን ማሰብ አላቆመም።። 'ስታልፉ አይቻችኋለው..... ተላልፈናል .....ብቻዬን..... በሌላ መኪና.....' በሚለው ምልልስ ውስጥም የተረገዙትን መልዕክት መመላት ጀመረ።።
'ስታልፉ አይቻችኋለው'
'የት ጋር ናችሁ?'
'ተላልፈናል'
'ከማን ጋር ነህ?'
'ብቻዬን'
'አብረውህ የተመደቡት አባሎችስ?'
'በሌላ መኪና.....'

መስፍን በተሰላቸ ሰው ስሜት ተንጠራርቶ በመዞር ሰውዬውን ሲያይ በቅፅበት አይኖቹ በመገናኛ ሬድዮኑ ላይ አረፉ።። ቅድም ከሶስቱ መካከል አንደኛው ሲነጋገርበት ያየው አይነት ቀይ ቀለም አንቴና ያላት ነች።።

መንገድ ተከፈተና ታክሲው ጉዞ ቀጠለ።። የሚከተሉት ሶስት ብቻ እንዳልነበሩ አመነ።።

የሴንትጆሴፍ ትምህርት ቤትን አልፈው መብራቱ ላይ ቆሙ።። በሰፊው ከተዘረጋለት ወጥመድ እንዲያመልጥ የሚያስችለውን ሀሳብ ማመንጨት አልቻለም።።

መልሶ ደግሞ 'ተከትለው ያዙኝም አልያዙኝም ለእናቴ ስል እጄን መስጠቴ አይቀርም' ሲል አሰበ።።

ታክሲው ግዮንና እስታዲዮምን አልፎ የጋንዲ መታሰቢያ ሆስፒታል ፊት ለፊት እንደደረሰ "ወራጅ" አለና ሂሳቡን ሰጥቶት ወረደ።። ባለራዲዮኑም ሰው እዛው ጋር ወረደ።።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

የወረደበት መስመር ላይ በቀኝ በኩል በሚገኝ አንድ ኬክ ቤት በረንዳ ላይ ተቀመጠ።።
ቀልጠፍ ያለ ወጣት አስተናጋጅ መጥቶ ጨበጠው።። ከዚህ በፊት ከአብነት ጋር አዘውትረው የሚጠቀሙበት ቤት በመሆኑ ይተዋወቃሉ።። አስከትሎም "ፔፕሲ አምጣልኝ"
"ቀዝቃዛ ወይስ....."
"እና አፍልተህ ልታመጣው ነው?!"
የሚከታተለው ሰው አጠገብ ባለ ሌላ ኬክ ቤት በረንዳ ላይ ተቀምጦ በሬድዮው መነጋገር ጀመረ።። ሰፊ ርቀት ስላላቸው እንቅስቃሴውን ከማየት ውጪ ምን እንደሚል አይሰማውም።።
ከአምስት ደቂቃ በኋላ ሁለት ሰዎች ከታክሲው ወረዱና አንዱ መስፍን ባለበት ሌላኛው ባለሬድዮው የተቀመጠበት ኬክ ቤቶች በረንዳ ላይ ተቀመጡ።። መጀመርያ የተከታተለው ሰው ሰው መስፍን እንዳወቀው ከእይታው ከተረዳ ቆይቶ ነበር።። ያዘዘውን ማኪያቶ ሳይጨርስ ተነሳና ቆሞ የነበረ ላዳ ታክሲ በኮንትራት መልክ ተነጋግሮ ወደ አምባሳደር መስመር ጉዞ ሲጀምር መስፍን በግርምት አስተዋለው።።

መጀመሪያ ነፃ የወጣ መስሎት ነበር።። ጉዳዩን በጥልቅ ሲያስበው ግን ክትትሉ በማያውቀው ሌላ ሰው እንደተለወጠበት አመነ።። ዙሪያውን አየ።። በአካባቢው ላይ የቆሙ፣ የሚሄዱ የተቀመጡ ሰዎች በርካታ ናቸው።። እሱን የሚከተሉት ግን የትኞቹ እንደሆኑ አያውቃቸውም።። እነሱ ግን ያውቁታል።። ተበሳጨ ከቁጥጥር ውጪ ሆኖ ሊገነፍል በሚተናነቀው ስሜት እይታውን ከወዲህ ወድያ እያቅበዘበዘ ቆየና በዚህ ዕለት ተግዶም ይሁን ወዶ እንደሚያዝ አመነ።።

የቀረው ተግባር አንድ እንደሆነ አሰበ።። ለአብነት ደውሎ ሁኔታውን መንገር ብቻ።። ስልክ ከመደወሉ በፊት ሌላ ሀሳብ መጣለት።።

በሰናይት የተመለመሉት የህቡዕ ቡድኖች፤ የመሪዎቻቸው ስምና የስልክ ቁጥሮችን ለአብነት ሊሰጠው እንደሚገባ ተረዳ።። እዛው ሆኖ መፃፉ አደጋ እንዳለው እያሰበ ተነሳና ወደ ኬክ ቤቱ ሽንት ቤት

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

አመራ። በዚህ ጊዜ ሁለት ሆነው ከታክሲ በመውረድ ተለያይተው ከተቀመጡት ነጭ ለባሾች መካከል እሱ በነበረት ኬክ ቤት የተቀመጠው ሰው ተነስቶ ተከተለው።

መስፍን ገብቶ በሩን ከውስጥ ቆለፈና ለራሱ በሚቀለው መንገድ በማስታወሻ ደብተሩ ላይ አዘበራርቆ ከፃፋቸው መካከል እየመረጠ በወረቀት ላይመግልበጥ ጀመረ። አሁን ሌላ ሀሳብ መጣለት። ወረቀቱን ለአስተናጋጁ ሲሰጥ እይታ ውስጥ ከገባ መልዕክቱ ለአብነት ከመድረሱ በፊት ሊያዝ ይችላል ሲል አሰበና ለሰከንዶች ሌላ አማራጭ ሲያውጠነጥን ቆይቶ ደሞዝ ከተቀበለው ብሮች መካከል አዲስ የአስር ብር ኖት አወጣና አሰፈላጊ የሆኑትን ስሞች አድራሻዎችና ስልኮች ፃፈበት። ከዛም ኪሱ የተከማቹትን መረጃ ሊሆኑ የሚችሉትን ወረቀቶች በጠቅላላ ጨምድዶ በሽንት ቤቱ ቀዳዳ ከተታቸውና ብሩን አጣጥፎ ወደ ቦታው ተመለሰ።

ጥቂት ቆይቶ ተነሳናም በስተቀኙ በኩል ወዳለችው ሱቅ አምርቶ አብነት ጋረ ስልክ መደወል ጀመረ።
ሲገናኙ "አቢ ዛሬ መያዜ ነው። ሁሉም ነገረ ያበቃ መሰለኝ" አለው ዝቅተኛ በሆነና ተስፋ በቆረጠ ቅላፄ
"እንዴት?"
"ከመስራቤት አጠመዱኝ.....በአሁኑ ወቅት የማላውቃቸው ሰዎች እየተከታተሉኝ ይመስለኛል"
"የት ነህ ያለኸው ልምጣ"
"አብረን እንድንጠፋ ነው?....." ቀጠለ "ይልቅ መያዜ አይቀሬ ከሆነ ሻይ የምንጠጣበት ካፌ እነዛን አድራሻዎች አስተናጋጁ ጋር አስቀምጥልሀለው..... ቀሪውን ስራ ያለህን አቅም በመጠቀም የመጨረሱ ፈታኝ ሀላፊነት በአንተ ላይ ወድቋል"
"ምንድነው በቀጣይ ማድረግ ያለብኝ?"
"እኔንጃ በተቻለህ አቅም በተለይ የጦር መሳሪያዎቹን የመረከቢያ ደብዳቤ እጅህ እንዲገባ አድርግ። መውሰድ የሚገባህ እርምጃ ሁሉ ፈፅም..... ህሊናዬ ማሰብ እያቃተው ነው።"
"ለምን ነገሮችን....."

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

መስፍን አላስጨረሰውም "ቻዎ" ስልኩን ዘጋበት፡፡ ወደ ኬክ ቤቱ በመመለስ ያዘዘውን ለሰላሳ ተጐነጨ፡፡
አስተናጋጁን ጠርቶ አስር ብሩን አውጥቶ በግልፅ ሰጠው፡፡
አስተናጋጁ ብሩን ተቀብሎ የሽርጡ ግራ ኪስ ከተተውና አጠገቡ እንደቆመ የሚመልስለትን ብሮች ከቀኝ ኪሱ እያወጣ ማስተካከል ሲጀምር መስፍን ዝግ ባለና በማይሰማ ቅላፄ "አብነት አሁን ይመጣል" አለው፡፡

"ምን ልንገርልህ ታዲያ?"
"አሁን የሰጠሁህ አስር ብር ላይ የተፃፈ መልዕክት ስላለው በሌላ የአስር ብር ኖት ለውጠ እንዲወስድ ነግረህ ስጠው"
"አሁን የሰጠኸኝ ብር ላይ...." አለና አውጥቶ ለማየት እጁን ወደ ኪሱ ሲሰድ
"እንዳታወጣው!" በጠረጴዛው ስር በጫማው እየረገጠ አዘዘው፡፡
"ለምን?"
"ሰው እንዳያይህ ፈልጌ ነው.....ውስጥ ገብተህ ታየዋለህ አሁን መልስ ስጠኝ"

በእሺታ መልሱን ቆጥሮ ሲሰጠው አንድ ብር ጉርሻ ተወለት፡፡

መስፍን ተነስቶ ወጣና ወዴት መሔድ እንዳለበት ሳይመርጥ ዝም ብሎ ወደ ጋንዲ አቅጣጫ አስፓልቱን ቀጥታ ተሻገረ፡፡ ከዛም ወደ ግራ አቅጣጫ በመታጠፍ በጋንዲ ሆስፒታልና በቀይ መስቀል መስራቤት አጥሮች መካከል የምትገነጠውን አስፓልት በመያዝ በፍጥነት መራመድ ጀመረ፡፡

በዚህ ቅፅበት ነጩ ላንድክሩዘር መኪና የኬክ ቤቱ ትይዩ ደርሶ ቆመ፡፡

ሻለቃው ዘሎ ወረደና አካባቢው ላይ የመደባቸውን አባሎች ለማግኘት ሲራወጥ ቆየ ሊሳካለት አልቻለም፡፡ ብስጭቱ ናረ፡፡ ወዴት ሊሄዱ እንደሚችሉ መገመት አልቻለም፡፡ የመስፍን ያለመወገድ በተራዘመ ቁጥር ሁሉ የ "ህዝበ ደቡብ ነፃነት ሀይል" ህቡዕ ፓርቲ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ህልውናና ሚስጥር አደጋ ውስጥ እየገባ እንደሚሔድ ብቻ ነበር የሚያስበው፡፡
የመገናኛ ራዲዮኑን አወጣና "ምድብ ሶስት ምድብ ሶስት" መቀበያውን ከፈተ "ግዳይ 200 ቀጥል"
መስፍንን እየተከተሉት ካሉት ሁለት ሰዎች መካከል አንደኛው ነበር የራዲዮኑን መልስ የሚሰጠው፡፡
"የት ናችሁ?" ጠየቀ ሻለቃው፡፡
ቦታው እንደተነገረው ዘሎ መኪናው ውስጥ ገባና "አስነስተህ ዙር!" ሾፌሩን በጩኸት አዘዘው፡፡ ከዛም ራዲዮኑን ወደ አፉ በማስጠጋት "ሰውዬው አለ?"
"አዎ..... የመሰወር እንቅስቃሴ ማድረግ የሚፈልግ መሆኑን ከሁኔታው ያስታውቃል"
"እንዳይጠፋባችሁ!"
"እሺ....." አለና አፍታ ሳይቆይ "ሂደ..... ዘለለ!..... ዘለለ! ጐይቶም ተከተለው ተከተለው....."
ሻለቃው በቁጣ የሚሆነውን እያጣ "ነግሬያለሁ..... እንዳያመልጣችሁ.....!" አለ የሰሙት አልመሰለውም "ምድብ ሶስት!..... ምድብ ሶስት....!" መስመሩን ለማግኘት ሞከረ፡፡
መኪናው ዞሮ እየጋለበ መገንጠያው ጋር ሲደርስ
"በዚህ ታጠፍ!" ሾፌሩን አዘዘው እነ መስፍን በገቡበት መንገድ እያመላከተው፡፡

ሾፌሩ በድንገተኛው ትዕዛዝ ምላሽ ሲሰጥ መኪናው መንገዱን ስቶ የእግረኞች መሂጃ ላይ ለመውጣት አንድ መንገደኛን እንደ ኳስ ጠልዞት በማለፍ ከሆስፒታሉ ግንቡ ጋር ተጋጨ፡፡ ማንም ከቁብ አልቆጠረውም የኋላ ማርሽ አስገብቶ መስመሩን በመያዝ ወደታዘዘበት ተፈተለከ፡፡
ወድያው ሁለት ተከታታይ ተኩሶች አካባቢውን አወኩት፡፡
በአምስት ሰከንድ ውስጥ ሻለቃውን የጫነው መኪና ተኩሱ የተነሳበት ቦታ ደረሰ፡፡
መስፍን በፍጥነት እየተራመደ ሳለ ለእጅና መረብ ኳስ መጫወቻነት ከተዘጋጀችው ትንሿ ሜዳ ውስጥ የደጋፊ ሰዎች ጩኸት

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ተሰማው፡፡ ወድያው አንድ ሀሳብ ተከሰተለት፡፡ ዘሎ በመግባት ከህዝቡ ጋር ተቀላቅሎ ማምለጥ፡፡ አላመነታም፡፡ ብዙም ርዝመት ወደሌለው የአጥሩ ግንብ ላይ ለመውጣት መንጠላጠል ጀመረ፡፡ ይሄኔ ሁለት ሰዎች ወደሱ ለመድረስ ሲሮጡ አያቸው፡፡

ግንቡ ላይ ወጥቶ ወደ ውስጥ ከመዝለሉ በፊት ግን ወደሱ ታልመው ከተተኮሱት ጥይቶች መካከል በሁለተኛዋ ጀርባው ላይ ተመታ፡፡

በመዝለል ፈንታ እንደተግፈተረ ሰው ወደውስጥ ወደቀ፡፡ ለመነሳት ሞከረ አልቻለም፡፡

በተኩሱ የተደናገጠው ህዝብ በትርምስ ወደ መውጫው በር ሩጫ ጀመረ፡፡

መስፍን በጀርባው ተዘርሮ አይኑን ገለፀ፡፡ የቀትሯ ፀሀይ ቁልቁል ታየዋለች በግማሽ ደስታና በግማሽ ቅሬታ ተውጦ ስለሷ ማሰብ ጀመረ፡፡ እሱ እየቀረባት ወይም እሷ ወደሱ እየቀረበች መሆኑ ይሰማዋል፡፡ 'አታቃጥልም' አለ ለራሱ፡፡

እንዲከታተሉት የተመደቡት ሁለቱ ሰዎች ተከታትለው በግንቡ ላይ እየዘለሉ ገቡ፡፡ ሻለቃውም አብሮት የነበረውን አባል እንዳስከተለ በመኪናው ላይ በመንጠላጠል ግንቡን ወጥቶ በመከራ ወደ ጊቢው ዘሎ ወረደ፡፡ ሾፌሩ መኪናውን በዋናው በር በኩል አዙሮ ደረሰ፡፡

መስፍን ልብሱን እየራሰ የሚወርደው ደሙን ለመግታት መዳፉን ጥይቷ የበሳችው ቀዳዳ ላይ ለመድፈን በሚጥር ስሜት ይታያል፡፡

ሻለቃው ውስጡ በደስታ ተጠመቀ፡፡ ሌላ ጥይት ለመስፍን ህይወት አስፈላጊ እንዳልሆነ ተረድቷል፡፡ ደስታውን መደበቅ ባለመቻሉ ፈገግ አለ፡፡

"ሂወቱ ልታልፍ እኮ ኖው.....ቶሎ ሆስፒታል.....ቢኬድ....." ተኩሶ የመታው ወታደር በፀፀት ቅላፄ ተናገረ፡፡

ሻለቃው እይታውን ከመስፍን ወደ አባሉ እየመለሰ "በሒሊኮፕተር ቢነሳ እንኳ ሆስፒታል መድረስ ቀርቶ ጊቢውን ሳይለቅ ይሞታል" አለው በፈገግታ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ተኳሹ ሽጉጡን ከሽንጡ ስር አውጥቶ ሳሩ ላይ ወረወረውና ጭንቅላቱን በሁለት እጆቹ ይዞ "ፈጣሪ ምን ቀን ወታደር ቤት የከተትከኝ!" አለ በምሬት። ይህንን በመሰሉ ግዳጆች ላይ የሰው ህይወት በሱ ሲያልፍ ለአምስተኛ ጊዜ መሆኑን እያሰበ።

ሻለቃው አፈጠጠበትና "አሁን በተናገርከው የወታደርን ክብር በሚያንቋሽሽ ቃልህ ግምገማ ላይ ቀርበህ ግለ ሂስ ታወርድና ከዛ ደህና ቅጣት እሰጥሀለው" አለው በዛቻ ስሜት።

  

ያማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ምዕራፍ 33

“በአፍሪካ ውስጥ ፓርቲ ማለት ፍቺው ይህ ነው፡፡ በህዝብ አመካኝተህና ለህዝብ ተቆርቋሪ መስለህ ስልጣንን በብልጠት መጨበጥ፡፡ ከዛም ሌላው ሲያደርግ እንደኖረው ሁሉ ፈላጭ ቆራጭ ሆነህ እስከቻልከው ድረስ ጨፍልቀህ እየበዘበዝክ በመግዛት ጊዜህ አብቅቶ በባለተራው ከመንበሩ እስክትገፋተር ድረስ ተንደላቀህ መኖር” አለ ሂርጳ በዙሪያው ያሉትን ስድስት ሰዎች በየተራ እየተመለከተ፡፡

ስብሰባውን የሚያካሂዱት በወለጋ ክፍለ ሀገር ነቀምት ከተማ ውስጥ በስተምዕራብ አቅጣጫ በሚገኘው መንደር በአንድ ዝነኛ ነጋዴ ሰው ቤት ውስጥ ነበር፡፡
“የኦሮሞ አርበኞች ንቅናቄ” ብለው በሰየሙት ፓርቲ ውስጥ አመራሮችን በበላይነት የሚሰጡ ባለስልጣኖች ናቸው፡፡ እያንዳንዳቸው እንደየመጡበት ክፍለ ሀገር ከድል በኋላ የሚኖራቸው ስልጣን ላይ ለመወያየት ነበር ዛሬ የተሰባሰቡት፡፡

ስብሰባውን የሚመራው ሂርጳ በመሆኑ ንግግሩን ቀጠለ “እኛ ኦሮሚያዎች ነን እንጂ ኢትዮጵያዊዮች አይደለንም በመሆኑም አገራችንን ራሳችን ነን ማስተዳደር ያለብን” የጅማው ሰው አቋረጠውና “ህዝባችን ኢትዮጵያዊ አይደለንም የሚለው አቋማችንን አይቀበለውም፡፡እኛ ኢትዮጵያዊ አይደለንም ብለን ህዝቡን በማነሳሳት ወደ ትግል እንግባ ብንል ምንም ያህል ተከታይ ማፍራት አንችልም፡፡ ከሱ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ይልቅ እኛ ተገንጥለን የራሳችንን አገርና መንግስት መፍጠር አለብን ብንለው ነው ሊታለልልን የሚችለው፡፡"
"አዎ" አለ ከአርሲ የመጣው፡፡

"ይቻላል" አለ ሂርጳ ቀጠለ ".....እምቢ ካለም አናቱን እንደ እባብ እየቀጠቀጥን ኢትዮጵያዊነቱን በኦሮሚያዊነት እናጠምቅለታለን፡፡ ቀላል ነው ስልጣኑ ብቻ አንዴ በእጃችን ይግባ!" ሁሉም ሳቁ፡፡

እሱም አብሮዋቸው ሲስቅ ቆየና "እንዳቀድነው ሆኖ ኦሮሚያን ማስገንጠል ከቻልን የምንይዘው የስልጣን ወንበር በምን ውሳኔ እናስቀምጠው?" ጠየቀ፡፡

ከባሌ የመጣው ሰው እድል እንዲሰጠው ጠየቀና "ለአንድ የስልጣን ቦታ አንድ ሰው ይጠቆምና የተጠቆመውን ሰው በድምፅ ብልጫ እናሳልፈው ወይም እንጣለው" አለ፡፡

የሀረሪው የኢሉባቡሩና የሸዋው ሰዎች ፊት ላይ ቅሬታ ታየ፡፡ ከዛም በተለያየ አገላለፅ ግን በተመሳሳይ ሀሳብ ሶስቱም "በተባለው መሰረት ከተሰራ የትውውቅ መደጋገፍ ስለሚፈጠር ድምፅ መስጠቱ ላይ አድልዎ እና ድጋፍ ሊኖር ይችላል" አለ ሀሳቡ በሀረሪው ነው የቀረበው፡፡

"እሺ ሌላ መንገድ?" ሂርጳ ጠየቀ፡፡
ከአንድ ሰዓት ውይይት በኋላ የስልጣን ክፍፍሉ በእጣ እንዲሆን ተወሰነ፡፡

በመጀመሪያው ዙር እጣ የጅማው ሰው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ የሀረሪው የገንዘብ ሚኒስትር፣ የባሌው የኦሮሚያ ፕሬዝዳንት፣ የአርሲው መከላከያ ሚኒስትር፣ የወለጋው ጠቅላይ ሚኒስትር፣ የኢሉባቦሩ ባህል ሚኒስትር፣ የሸዋው የንግድ ሚኒስትር ተባሉና አበቃ፡፡ ግን ገና በርካታ ያልተያዙ ክፍት የስልጣን ቦታዎች ነበሩ፡፡
"ገንዘብና ስልጣን አይጠገብም..... ለምን ደርበን አንይዝም?" ሂርጳ ጠየቀ፡፡
ሁሉም ሀሳቡን ደገፉት፡፡ ሁለተኛ ዙር ሶስተኛ ዙር እየተባለ መንበርን ተባለቱለት፡፡ ብለታው ሲያበቃ የአርሲው ሰው "ወያኔም

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ብትሆን አሁን አገር የምትመራው እንደኛው ጫካ ተኧሹማ በመግባት ነው፡፡" አለ፡፡
"ወደ ግብጣ ስነ-ስርዓቱ እንለፋ?" ሂርጳ ጠየቀ፡፡
"አዎ..... ስልጣን የሚፀናው በግብጣ ሲደምቅ ነው" አለ የሸዋው ሰው፡፡
"በደስታ" አሉ ቀሪዎቹም በአንድ ድምፅ፡፡ ከውጭ አገር መንግስታት ለፓርቲው ድጋፍ እየተባለ ከሚላከው ገንዘብ ላይ እኩሌታው ለግላቸው ጥቅምና መዝናኛነት ነበር የሚውለው፡፡ ለዕለቱ ተብሎ በተያዘው ወጪ መሰረት የተዘጋጀውን የምግብና የመጠጥ ብፌ ለማንሳት ሲሄዱ ለስስታቸው ብቻ ሶስት ሰርገኞችን ማጋባት የሚችል የምግብ መዓትና መጠጥ እንዲዘጋጅ ነው የተደረገው፡፡ ክራቫታቸውን እያላሉ ሰፈሩበት፡፡

««««««« »»»»»»»

በዚሁ ዕለትና ሰዓት ከዛው ከነቀምት ከተማ በስተደቡብ አስር ኪሎ ሜትር ወጣ ብላ በምትገኝ አንዲት የገጠር መንደር አለች፡፡

በውስጧ ጐስቋላ ህይወትን ለረዥገ ዘመን የተሸከሙ በርካታ ገበሬዎች ከነቤተቦቻቸው ይኖሩባታል፡፡ ከነዋሪዎቹ መካከል ጐጆ ቀልሰው ግማሽ እድሜያቸውን እዚህ ያሳለፉ አንድ የዘጠና ሰባት ዓመት አዛውንት ሰውዬ በመጨረሻ ላይ የወለዷቸውን ሁለት ልጆቻቸውን በአንድ ረዥም የዋርካ ዛፍ ስር አስቀምጠው ታሪክ እየነገሩዋቸው ነበር፡፡

" ሁሉንም ነገር እንደ እድሜ አከናውኖ ማለፍ መቻል ብልህነትም ብልሀትም ነው፡፡ ተፈጥሮም ከኛ የምትሻው ብቸኛ ግዴታችንም እሱ ነው፡፡ እንደ እድሜ መስራት፤ እንደ እድሜ ማፍቀር፤ እንደ እድሜ ጎላፊነትን መውሰድ እንደ እድሜ መሆን ያለብንን ነገር ሆነን መገኘት፡፡ እኔ ዛሬ የደረስኩበት እድሜ እንዳደርግ የሚፈቅድልኝ አሁን ለእናንተ እያደረኩ ያለሁትን እንዳደርግ ብቻ ነው፡፡ እውነተኛውን ታሪካችንን በተለይ የአይን ምስክር ሁኜ ያለፍኩባቸውን ተቀጣዩ ትውልድ ማሳወቅ ነው ጎላፊነቴ፡፡ በናንተ እድሜ ላይ ግን እንደ እናንተ ለአገሬ ተዋግቻለሁ፡፡ ልዋጋ ስወጣ ግን የምዋጋበትን እውነተኛና ትክክለኛ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ምክንያት አውቅ ነበር። ያኔ ሞቼ ቢሆን እንኳ ለከንቱ ግለሰቦች ዓላማ ማሳኪያነት በከንቱ እንደ ሞተ ሰው ተቆጥሬ አልቀርም ነበር..... "

ትክ ብለው ሁለቱንም በየተራ እያዩዋቸው ቀጠሉ "..... በአገሬ ላይ ለመጣ ጠላት አገሬን ወክዬ ነበርና የተዋጋሁት ብሞትም ኖሮ ሞቴ የሰማእት ነበር። ዝም ብሎ ለአንድ ግለሰብ ዓላማ አስፈፃሚነት እንደ ሞተ ሰው ሳይሆን ዋጋና ክብር የሚሰጠው ትውልድና አገርን ሁሌም ሲያኮራ የሚኖር ጀግንነት ሆኖ በታሪክ እና በህዝብ ልቦና ውስጥ ታትሞ የሚኖረው..... "

የመጨረሻው ልጃቸው እድሜው ሰላሳ ሁለት ዓመት ሲሆን የሱ ታላቅ ደግሞ ሰላሳ አምስት ሆኖታል። ሁለቱም ትዳርና ልጆች አሉዋቸው። በወቅቱ በተፈጠረው የፖለቲካ ስብከት ተታለው የ "ኦሮሞ አርበኞች ነቅናቄ" ስር በመግባት ለመታገል ቆርጠዋል። አዛውንት አባታቸው ደግሞ ይህን አልፈቀዱትም። ምክንያቱንም ሊያስረዱዋቸው ነበር አንደ ኦሮሞ ህዝብ ባህል እና እንደ ኦሮሞነታቸው ትልቁ ዋርካ ስር ይዘዋቸው የሄዱት።

ታናሽየው ልጅ በእጁ ሽፋናቸው ነትቦ የውስጥ ገፃቸው የተገነጣጠሉ ሁለት መፅሀፎችን ይዟል። መፅሀፎቹ የወያኔ መንግስት ስልጣን ከያዘ በኋላ የኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ የአገሪቷን ዜጎች በተለይ የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ላይ በጠላትነት በማነሳሳት በመካከላቸው መከፋፈልን ፈጥሮ በመበታተን እያዳከመ ከፋፍሎ ለመግዛት እንዲያመቸው ታስቦ የተዘጋጀና ለፕሮፖጋንዳ ፍጆታ ካዋላቸው መፅሀፍቶች መካከል «ኦሮሚያን በፈረቃ እና የቡርቃው ዝምታ» የሚሉት ነበሩ። ቡልቻ እነዚህ መፅሀፎች እጁ ከገቡ ጀምሮ ደጋግሞ አንብቧቸዋል። ከመፅሀፍ ቅዱስ ጭምር አስበልጦ ይወዳቸዋል።

አዛውንቱ ነጭ ከሆነው ኩታቸው ጋር የሚመሳሰለውን ረዥም ሪዛቸውን ቁልቁል እየዳበሱ "ንገሩኝ እስኪ ጠመንጃ አንግባችሁ ወደ ጦርነት የምትሔዱትበትን ዓላማ?"
"ኦሮሚያን ነፃ ለማውጣት ከአባቶች የተረከብነው አደራ ስላለን" አለ ትልቁ ልጃቸው።

አዛውንቱ ፈገግ አሉና ረጋ ባለውና ነዛሪ ግርማ ባለው ቅላፄያቸው "አንተስ?" አሉት ትንሹን ልጃቸውን።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“እሱ ነገረህ እኮ አባባ.....”
“እንግዲህ ከአባታችሁ የተረከባችሁት አደራ ካላችሁ አባታችሁ እኔ ነኝ አይደል?”
“አዎ.....” አሉ ሁለቱም፡፡
“ታዲያ መጀመሪያ እኔን ስለ ኦሮሞ ህዝብ የትግል ታሪክ ንገረኝ ብላችሁ ጠይቃችሁኛል?”
“አላልንም” አለ ቡልቻ ወደ ታላቅ ወንድሙ እያየ

“ለመሆኑ ምን እያሉ ነው ስለታሪክ የሚነግሯቹ?” ጠየቁ
“ኦሮሚያ የኢትዮጵያ አካል ያለመሆኗንና በአማራ ንጉሶች ተይዘን በቅኝ ግዛት በግድ እንድንተዳደር መደረጋችንን ነዋ... ” አለ ቡልቻ
“ለመሆኑ የኦሮሞ ነገስታቶች በአማራ ክልል ያውም በጎንደር ውስጥ ነግሰው ላልተቋረጠ አንድ መቶ አመት ገደማ አብዛኛውን የአገሪቷን ክልል እንዳስተዳደሩ ነግረዋቹ ያውቃሉ?” ሁለቱም ልጆች ሰምተው ስለማያውቁት አስገራሚ ታሪክ እየተገረሙ ዝም አሉ፡፡

ቀጠሉ አዛውንቱ “ለምንድን ነው ይህንን ለኦሮሞ ህዝብ መንገር የማይፈልጉት? ” ብለው ጥቂት በሀዘን እንደመተከዝ ብለው ቆዩና ቀጠሉ “እስከ አፄ ቴዎድሮስ ለዚች አገር የተበታተነ አገዛዝ መሰባሰብ ጦርነቶች ድረስ ኦሮሞዎች የአማራን ሙሉ ግዛቶች ጭምር እንደ አንድ አገር ሰብስበው በመያዝ አስረዳድረዋል፡፡ በኋላም አፄ ሚኒልክ ያንኑ የተበጣጠሰ መሳፍንታዊ አገዛዝ ሰብስበው አገሪቷን በጠቅላላ ወደ አንድነት ለማምጣት ሲሞክሩ በርካታ አመፆች ጎልተው መውጣት ቀጠሉ እንጂ ጭቆናም ሆነ አመፅ በፊተኛውም ሆነ በኋለኛው አገዛዞች ውስጥ በመላው አገሪቷ የነበረና የቀጠለ እውነታ ነው፡፡ ጥንትም ሁሉም አየገሪቷ ህዝብ በየወቅቱ ገዢዎች አማካኝነት በሚሾሙት አስገባሪዎችና አስተዳዳሪዎች ሲጨቆን እና ሲያምፅ ነው የኖረው፡፡ ሁሌም ትግል እና ፀብ ነበር፡፡ ይህ ለአገራችን ታሪክ አዲስ አይደለም እናንተን ለማወናበድ እና ለማሳሳት ስለፈለጉ ነው እንጂ.....” አዛውንቱ የልጆቻቸውን የዋህነት ፊታቸው ላይ ሲያነቡ ቆዩና ሳቅ አሉ፡፡

ሁለቱም ልጆች መልስ መስጠት አልቻሉም፡፡ ቀጠሉ “የውሃ ጥፋት ከሚባለው የዓለማችን ታሪክ በኋላ ወደ አፍሪካ ስለፈለሱ ህዝቦች ሲወሳ አገራቹ ኢትዮጵያ ናት ዋናዋ ሆና የምትጠቀሰው፡፡ ይህም እንደ ወቅቱ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

እያደገ ከሄደው የህዝቡ መጠን እየተስፋፋ ከግብፅ ጫፍ አንስቶ እስከ የመን ባህረ-ሰላጤ እንዲሁም ቀይ ባህርን ተሻግሮ የአረቦቹን ግዛት ሁሉ እስከማስተዳደር የደረሰ እንደነበር ቀደምቱ ታሪካችን ይመሰክራል። ለምን ይዜን አይነግሯችሁም?..... "

"..... ይህ በጥበበኝነቱ በስልጣኔው እና በሀይለኛ ጦረኝነቱ ገናና የነበረው ህዝባችን በተለያየ ምክንያት እየተሰናከለ ወደ ኋላ በመቅረትና ተበታትኖ በመስፈር ቆይቶ ከቅርቡ ጥንታዊ ታሪካችን ውስጥ ኢትዮጵያ ወደሚባለው ግዛት ተጠቃለለ። ሀበሻ ወይም ድብልቅ ህዝብ የሚለው ስያሜያችንም ከታሪካችን የወረስነው ነው እንጂ ከየትም የተሰጠን አይደለም። ይህ ሲሆን እንግዲህ ህዝቦች ተበታትነው በኖሩበት የመካከለኛው ዘመናችን ውስጥ እያንዳንዱ ህዝብ በወቅቱ ለህይወቱ በቀለለው መልኩ የየራሱን ቋንቋ የአኗኗር ዘዬ አለባበስ አመጋገብ ባህል ቤት አሰራር ማህበራዊ እና አስተዳደራዊ ህግጋቶችን እየፈጠረ አስፋፍቷል። የብሔረሰብ መፈጠር ምክንያቱ ይሄ ነው እንጂ ከሰማየ ሰማያት አንዱ ከሌላው ተለይቶ የተሰጠው ልዕለ ማንነት አይደለም። እንደዛ ቢሆንማ የሰው ልጅ ሁሉ እኩል ነው ባላልንም ነበር.....

"..... ጥንት ጉንት ተብለን ስንጠራ በኖርንበት ዘመን የነበረን ግዛት አገር ወዳድ ባልነበሩ ገዢዎች እና በውጭ መንግስታ ሸር እና ደባ ተቆራርጦ ሄዷል። ዛሬ ሱዳን የኛ አይደለም ሶማሊያ የኛ አይደለም ከቅርቡ ታሪካችን ብናይ እንኳ ጅቢቲ ሄዳለች ኤርትራም እንደዛው..... በሀሰት የኢትዮጵያ አይደለችም ተብላ ከተቆረጠችው ኤርትራ ውስጥ የሚገኘውና በብዛቱ ገናና የሆነው የሀማሴን ብሔር ምንጩ ጎንደር ነበር። ከጎንደር ፈልሰው በመሄድ እዛ የከተሙ ኢትዮጵያውያን ናቸው። ህዝቡም ጥንተ ኢትዮጵያዊ አገሪቷም የኢትዮጵያ ነበረች። ዛሬ ጉራጌ የሚባለው ብሔር ጥንት ከትግሬ ፈልሶ ወደ ደቡብ የወረደ ህዝብ ነው። ራሳቸው ሀማሴኖች ፈልሰው ወደ ምስራቅ በመውረድ ዛሬ ሀረር የምልነውን ስፍራ መስርተዋል። ይህ ሁሉ የሚያሳየን ኢትዮጵያዊነት ላይ ላዩን ሲሮጥባት የሰማንያ የተለያዩ ብሔረሰብ ቋንቋ ባህልና ስርዓት መገኛ መሆኗን ሲሆን ወደ ጥልቁ ምንጯ ቢገባባት ግን ይህ ሁሉ ብሔር ከሚያለያየው ይልቅ ወደ አንድነት ጫፍ የሚያደርሰው ማንነቱ የሚበልጥ ፅኑ መሰረት ያለውና በጥልቅ የተዋሀደ አንድ ህዝብ መሆኑን ነው....." አሉ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ቀጠሉ “..... ሁላችንም ዘመን እና ሁኔታ እንድንቆም በፈቀደልን ቦታ ላይ ሆነን ተከባብረን ተዋደን ተዋህደን አብረን እየደማን አብረን እያለቀስን አብረንም እየሳቅን አብረን ድል እያደረግን ኖረናል። ሌላው የሚገርመው የአገራችን እና የህዝባችን ታሪክ ደግሞ ከአንዱ ቦታ ፈልሶ ሌላ ቦታ ከትሞ በዝቶና በልፅጎ ከሚኖርበት ቦታ ላይ በተለያዩ የህይወት ውስብስብ ምክንያቶች እየተንቀሳቀሰ እንደገና ከሌላው ጋር እየተገናኘ እየተጋባ እየተዋለደ በደም በስጋ በዘር በባህል በሀይማኖት ተደባልቋል። በናንተ ዘመን በህዝብ ትግል እና መስዋእትነት ዘውድ የጫነው መሪያቹ አደባባይ ላይ ቆሞ በተረጋገጠና በሚታይ ማስረጃ የዓለም ሊቃውን የፃፉትን ሁሉ ዘንግቶ «ኢትዮጵያ ያላት የመቶ ዓመት ታሪክ ነው ሌላው ሁሉ ተረት ተረት ነው » አለ። አሳሳች ደቀ መዝሙር ነው! ዓላማው አይታወቅምና በጥንቃቄ ተመልከቱት.... ለነገሩ አትፍረዱበት የናንተ ዘመን ህሊና ጠቧል መሰለኝ የዕለት የዕለቱን እንጂ ጥንቱን እና ነገን ከዛሬው ጋር እያመዛዘነ ማሰብ አልቻለም። ለዚህ ነው ለሆዱ ያደረ የበዛው። የሱም ህሊና ማሰብ እና መሸከም የቻለው የመቶ ዓመት ታሪክ ብቻ ነው። ከዛ ከላቀ አንጎሉ ይታወካል ይታመማል እና ነው። እውነቱ ግን የዚህች የአገራቹ ታሪክ ምድርን የሚያህል ብራና ተዘጋጅቶ ቢፃፍ እንኳ ማለቁንም እንጃ..... ” አሉ በሀዘኔታ ስሜት ተውጠው

“እና ኢትዮጵያ የማናት ከማነው ነፃ የምትወጡት? ወይስ ይህ አገር የማነው ለማነው የምትተውት? ” አሉ ሁለቱንም በየተራ እያዩ

“ የኦሮሞ የትግል ታሪክ የሚጀምረው ከአፄ ሚኒሊክ ወቅት ጀምሮ ነው ብለው ሊያሳምኗቹ ቢሞክሩ እንኳ ትግሉ የገነነው የመሳፍንታዊ ስርዓቱ እንዲቀጥል በሚፈልጉ ግለሰቦች ምክንያት ነው። ችግራቸው አገር ወደ አንድነት ከተሰባሰበች እነሱ ስልጣን ሊነጠቁ መሆኑ ስለሚያውቁ ነበር። ሌላው እንግዲህ ከአንደነት በውኋላ ለንጉሱ ግብርን በማስገበሩ ሂደት ላይ እንደሌሎቹ የኢትዮጵያ ግዛቶች ሁሉ በኛም ህዝብ ላይ አቅም ያላገናዘበና ይፈፀም የነበረው በደል እንዲቆም ነበር። እናም አፄያዊ የሆነውን ስርዓት ለመጣልና የአፄውን አስገባሪዎች ለማጥፋት በወቅቱ ተደጋጋሚ የሆኑና የተበታተኑ የትግል ሙከራዎች ተደርገዋል። ” አሉ በብትራቸው መሬቱን እየጫሩ።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“እ..... እኔ በራሴ ከደረስኩበት እና ከማውቅ ውስጥ ልንራችሁ..... ከ1930 ዓ.ም ጀምሮ የነበሩት በርካታ ተቃውሞዎች ላይ ተሳትፌያለሁ.....”
ቡልቻ ወደ ታላቁ ዞረና “እይ እንግዲህ አባታችን ትግል ላይ መሳተፍ ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ያለውን ብናስበው እንኳ ከሀምሳ ዓመት በላይ ነው”
“እሱማ ብዙም የጠነከረ አይደለም እንጂ ከዛም በፊት እሳተፍ ነበር፡፡.....”
“ታዲያ ለምንድነው እኛን ወደ ትግል አትሒዱ ብለህ የምትከለክለን?” ኡንዴ ጠየቀ፡፡
“የእናንተ የትግል አቅጣጫ በጣም የተሳሳተ ስለሆነ ነው”
“እንዴት?” አለ ኡንዴ፡፡
“አያችሁ ልጆቼ ከኛ በፊት አፄ ሚኒሊክን በመቃወም ሲታገሉ የነበሩት አያቶቻችንም ሆኑ ከዛ በኋላም የተነሳነው እኛ በጠቅላላ እንታገል የነበረው እንደ እናንተ ላለ ክፉና አጥፊ ዓላማ አልነበረም”
“እኛ ምን አጠፋን እናንተ ያወረሳችሁንን የነፃነት ትግል አንግበን ነው ነፃ ለመውጣት የተነሳነው፡፡” አለ ቡልቻ ወደ ታላቁ እያየ
አዛውንቱ ለዛ ያለው ሳቃቸውን ሲስቁ ቆዩና
“የሀሰት ወሬዎችን ሳይሆን እውነተኛና ሚስጥር እንደሆነ እንዲጠፋ እየተደረገ ስላለው ታሪካችሁ ፈልጋችሁ ስሙ..... ቃሌ እውነት ነው፡፡ ስለ እውነትም ስል የማውቀውን ከአባቶቼና አያቶቼም እንደናንተ ጐረምሳ ሳለሁ የተነገረኝ ታሪክ ሁሉ ዛሬ እነግራችኋለሁ” አሉ አይናቸው እንባ እያረገዘ፡፡
ቀጠሉ “.....ሌላው ሁሉ ቢቀር እንኳ ራሴ በአካል የተሳተፍኩበትን የትግል ታሪክ ያየሁትና የኖርኩበት በመሆኑ ስለእውነተኛነቱ ምዬ ልነግራችሁ እችላለሁ፡፡” አሉ በምስጠት ሁኔታውን እያስታወሱ፡፡
ቀጠሉ “.....የኦሮሞ ህዝብ ለአፄው አልገዛም ብሎ በየጫካው እየሸፈተ ሲዋጋ መሪ ዓላማው ከኢትዮጵያ ተገንጥሎ ለመውጣት አልነበረም፡፡ ምክንያቱም ኢትዮጵያ ከኢትዮጵያ ላይ ልትገነጠል አትችልምና ነው፡፡ የዛን ዘመን ተቃውሞውና ትግል የባሪያ አሳዳሪ ስርዓቱ አስመርሮኛል፤ አምባገነናዊ አገዛዙ ሰብሮኛል፤ እናም ያንን የፊውዳል

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ስርዓት ከአናቴ ላይ ገርስሼ መጣል አለብኝ፤ እኩልነት ማስፈን አለብኝ በሚል ፍላጐት ብቻ ነበር የሚታገለው፡፡.....

“.....ይህንን ደግሞ በወቅቱ ራሱ አማራውም ከንባታውም ሀረሪውም ሀድያውም አፋሩም ትግሬውም ጠቅላላ የአገሪቷ ህዝብ ማለት ይቻላል ሁሉም የተማረረበትና የታገለበት እውነታ ነው እንጂ የኦሮሞ ህዝብ ላይ ብቻ በልዩ ሁኔታ ሲፈፅም የነበረ ስርዓት አይደለም፡፡ የወቅቱ ጥያቄና ዓላማው ማንም የማንም ጌታ ማንም የማንም ባሪያ ሳይሆን በእኩል ኢትዮጵያን የሁላችን አድርጐ መኖር ነበር.....

“..... ዛሬ ወያኔ አጣማና አሳስታ የምትነግራቹ የኤርትራም ሆነ የትግራይ ህዝብ ጥያቄ ራሱ መገንጠል አልነበረም፡፡ ከቀደሙት ወቅቶች ሁሉ እጅግ ገኖ የወጣው የወቅቱ አመፅ በ1930ዎቹ ዓ.ም የሚጀምረው የትራይ ባላባቶች ጥያቄና ንጉሰ ነገስቱ ላይ ያቀረቡት የተቃውሞ ምክንያት በወቅቱ የትግራይ ገዢ የነበሩትን ራስ መንገሻ ስዩምን አንስተው ፊታውራሪ አለማየሁ ጠናን ማስቀመጣቸውና ይህን አዲሱን ገዢ ተከትሎ የመጣው የአስተዳደር በደል እንዲሁም የገበሬውን አቅም ያላገናዘበ የግብርና የብዝበዛ ጉዳይ እንዲሁም ከነበረው ስርዓት ጋር ተያይዞ የመጣው የፊውዳሉ ጭቆናና እንግልት ነበር፡፡ የህዝቡም ሆነ የባላባቱ ጥያቄ ግን የአስተዳደር ለውጥ፤ ፍትህ እና እኩልነት ነበር እንጂ ወያኔዎቹ እንደሚሉት በአገሪቷ ከአንድም ቦታ የመገንጠል ጥያቄ ተሰምቶ አያውቅም.....

“..... ጣሊያን እኮ ኢትዮጵያን ስትወር በአፄ ሚኒሊክም ሆነ በአፄ ኃይለስላሴ ጊዜ በመላው ኢትዮጵያ ውስጥ የነበሩት ባላባቶች እና መላው ህዝብ የውስጥ ችግሮችን ሁሉ ትተው መጀመሪያ የዘመቱት በዚች አንዲት አገር ላይ በመጣ ጠላት ላይ ነበር፡፡ እኔም አንዱ አርበኛ ሆኜ ለሶስት ዓመታት ሽፍቼ ከጠላት ጋር ስዋጋ ኖሬያለሁ፡፡ ስንቱ የኦሮሞ ጀግና ኢትዮጵያ አገሬ ብሎ ከጠላት ጋር ጉሮሮ ተናንቋል፡፡ ልጅና ሚስቱን ጥሎ ሄዶ ኦሮሚያ ብሎ ሳይሆን ለኢትዮጵያ ሞቷል፡፡.....” አሉ በሽመል ከዘራቸው መሬቱን እየመቱና የሚያስታውሱትን ለመቀጠል እየተመቻቹ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

ቀጠሉ “.....ሌላው ለዘመናት የታየው የአገራችን እውነት በትግልም ይሁን በእድል ወደ ስልጣን የመጣው አልካ ወይም ገዢ እንዲሁም ከዛ ስርዓት ተጠቃሚ የሆነው ወገን እስከ ምዕአት ቀን ድረስ ስልጣን ለሌላ አሳልፎ መስጠት ያለመፈለጉ ሲሆን ይህም ለብዙ ህዝብ መጨፍጨፍ መሰደድ እና መደህየት ምክንያት ሆኗል። ያልተቋረጠ አገር ያወደመና ወደ ኋላ ያስቀረ ተከታታይ አመፅንም ቀስቅሷል። ይህ ችግር ዛሬም ቀጥሏል። በዚህ ምክንያት ነው እኛም ወጣት እያለን በ1955 ዓ.ም. ይመስለኛል..... የኦሮሞ ልጆች ተሰባስበን በአንድነት እየተረዳዳን የምንታገልበትን ማህበር መሰረትን። ያኔም ቢሆን አላማችን የፊውዳሉን አገዛዝ መጣል እንጂ ኦሮሞን መቆራረጥ፣ ማስገንጠል የሚል የለበትም ነበር።

“ታዲያ የአሁኑ የመገንጠል ጥያቄ ከየት የተፈጠረ ነው?” ትልቁ ጠየቀ።
“የአሁኑ የመገንጠል ጥያቄማ አያቶችና አባቶች እኛም የታገልንለት መሪ ዓላማ እንዲያስቱ በተነሱ ወጠጤ ሰዎች ጭንቅላት ውስጥ የተፈጠረ የጨቅላ ህፃን አስተሳሰብ ነው።”

ቀጠሉ “.....ዛሬ ስለ ኦሮሞ የትግል ታሪክ ሲነሳ ለእናንተና እንደእናንተ ላሉ ምንም የማያውቁ ወጣቶች የሚነግሯቸው ኦሮሞ ጥንትም የኢትዮጵያ እንዳልነበረችና በጉልበት እንደተያዘች ስለዚህም መገንጠል አለባት እየተባለ ነው። ይህ ፍፁም ሀሰት ነው። ኢትዮጵያ የኦሮሞ ነች። ኦሮሞም የኢትዮጵያ ነች። አማራውም ትግሬው አፋሩም ሶማሌም ኢትዮጵያ ናቸው። ኢትዮጵያዊነት የሁላችን ነው.....”

“ታድያ ለምንድን ነው በግድ ነው የተያዝነው የሚሉት?” ቡልቻ ጠየቀ

“መሳት የሌለባቹ እውነታ... ማንም ቢሆን ብቻውን እንደፈቃዱ ሲያዝበት የነበረውን ክልል ይቅርና ቁራጭ መደብም ብትሆን ለሌላ አዛዥ አሳልፎ መስጠት አይፈልግም። ከዛ ውጪ እንግዲህ እውነተኛው ታሪክ እንደሚነግረን ጅማ አባ ጅፋር ግዛቱ የኢትዮጵያ መሆኑን ካለ አንዳች ጦርነት በደስታ ነበር ያሳወቁት። ወለጋን ሜጫና ቱለማን

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ቤኒሻንጉልን ቦረናን ነቀምትን ታች ኢሉባቡር ድረስ ይገዙ የነበሩት የወቅቱ መሳፍንቶች እነ ጆቴ ቱሉ እነ ኩምሳ ሞረዳ እነ ሼህ ሆጀሌ ለኢትዮጵያ ጥንታዊው አንድነት ተባባሪ ሆነው ሲቆሙ በክልላቸው ላይ ምንም አይነት ጦርነት አልነበረም። ቢኖር እንኳ ይህ ነው የሚባል እንዳልነበር ዘመኑን የደረሱበት አባቶቻችን ነግረውናል። በእርግጥ ወደ አሩሲ ሲዳሞና ከፋ ሲጓዙ ዛሬ ለናንተ ተጋኖ የሚነገረውን ያህል ባይሆንም የአከባቢው መሳፍንቶች ስልጣን የነሱ ብቻ እስከሆነ ድረስ በተበታተነ ደካማ አገዛዝ አገሪቷን ለማስቀጠል ካመፁት ጋር ተደጋጋሚ ጦርነት መካሔዱን ሁላችንም እናውቃለን.....

" ...የሀረር ገዢ የነበረው አሚር አብዱላሂም በመጀሪያ ቢያምፅም አፍታም ሳይቆይ ጥሎ ስለሸሸ የሀረር ህዝብ ጥንታዊቷ ኢትዮጵያ በመሳፍንቱ ምክንያት ከመፈረካከሷ በፊት ወደነበረችው አንድነት እንድትመለስ ፈቃዱን መስጠቱን ነው ከአባቶቻችን እየተነገረን ያደግነው። እንደውም በወቅቱ በጦርነት ከደረሰው ጉዳት ይልቅ በየወቅቱ በድንገት በሚከሰቱ ተፈጥሮዋዊ ወረርሺኝ ድርቅና ንዳድ ምክንያት በህዝብና በከብቶች ላይ ከፍተኛ ጉዳትና ጥፋትን እያስከተለ ያልፍ ነበር። ከዛ ውጪ ወደ ታች እየተበተነ የወረደው የጥንታዊው ኢትዮጵያ ህዝብ እስከ ነጭ አባይ ወንዝ መነሻ ድረስ የኛ አገር እና ግዛት እንደነበር ዛሬ እናንተን እያሳሳቱ ያሉ መሪዎቻቹ ጭምር በደንብ ያውቁታል" አሉ

".....እናም ልጆቼ የዛሬ የትግል መሪዎቻችሁ የስልጣን ጥማት እንዳሳበደው ውሻ አድርጓቸዋል። በየዕለቱ እየፈጠሩ የሚነግሯችሁ የሀሰት ታሪክ ነውና ደቀመዛሙርቶቻቸው ሆናችሁ ለግል አላማቸው ስኬት እንዳትሰየፉ ነው የአባትነት ምክሬ....." አሉ።
"እሺ በየቦታው ያሉት የኦሮሞን ነፃነት አራማጅ ፓርቲዎችስ የተፈጠሩት እንዴት ነው?" ትልቁ ጠየቀ።
"ቅድም እንደነገርኳችሁ በ1955 ዓ.ም. በሚጫና ቱለማ ያ የኛ ማህበር ከተመሰረተ በኋላ በማህበሩ ውስጥ የመሪነቱን ቦታ ለመያዝ ፍትጊያ መፈጠር ጀመረ።በዛም ያልተሳካላቸው የስልጣን ጥመኛ ግለሰቦች እያፈነገጡ በመውጣት በኦሮሞ ህዝብ ስም የተለያየ ማኅበር እና ፓርቲዎችን መመስረት ጀመሩ...

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“ ወድያውም ወደ ሶማሊያ ግዛት በመሄድ ከሶማሊያ መንግስት እርዳታና ድጋፍ በመጠየቅ ኢትዮጵያን ሊያፈራርሷት ሞከሩ። ሶማሊያም በግርግሩ በመጠቀም ከኢትዮጵያ መሬት ላይ የምስራቁን ክፍል ቆርጣ ለመውሰድ ትፈልግ ስለነበር በአገሪቷ ላይ ተቃዋሚዎችን መቀበል ማደራጀት እና ማሳመፅ ቀጠለች። ከነሱ ስርም ሌሎች በተመሳሳይ መንገድ እየተገነጠሉ በመውጣት የኦሮሞ ህዝብና መሬት ላይ የሚያስከትለውን አስከፊ ጉዳት በቸልታ እያለፉ ለራሳቸው የስልጣን መቆናጠጫነት በሚያመቻቸው መልኩ ታሪክ እና ባህላችንን አንጋደው እየፃፉ በሱም ዓላማዎችን እየቀረፁ እናንተ ያላችሁበት እዚህ ዘመን ላይ ደረሱ። ሶማሊያ ኢትዮጵያን ሁለቴ ወራ ምስራቁን ክፍል ለማስገንጠል ሞክራ አልሳካ ሲላት ተቃዋሚ እያስታጠቀች ልታበጣብጠን ሰትሞክር የኖረችው አገር ዛሬ ያለችበትን ሁኔታ አስተውሉ። የደረሰባት ጉዳት እንደ መልካም ባህላችን እና ጎረቤትነታችን የሚያሳዝነን ቢሆንም የኛን አገር እገነጣጥላለሁ ብላ እራሷ አራት ቦታ ለመገነጣጠል በቅታለች። ኢትዮጵያን የነካ ቅጣቱ ከሰማይ ጭምር ይወርድበታል። ” አሉ።

“.....እናም እነዛ የመጀመሪያዎቹ የማህበሩ መስራቾች በተለያዩ ምክንያት እንደኔ ከማህበሩ እንዲባረሩ እየተደረገ ግማሹም እየሞቱ ሲመናመን ተረካቢ ነን ባዮች አጠቃላዩ ተግባራቸው የአገዛዝ ስርዓትን መገርሰስ ሳይሆን አገርን መገዝገዝ ወደሚለው ተለወጠ። ይኸው ዛሬ ለናንተ ትግል ማለት አገር መገንጠል ተብሎ ተነግሯል። እናም ልጆቼ ዙሪያውን ሳታገናዝቡ እሳት ውስጥ ገብታችሁ አትማገዱ” አሉ።
“አባ... ” አለ ቡልቻ ቀጠለ “ግን እኮ ስርዓቱና ገዢዎቹ ሁሉ አማሮች ብቻ ነበሩ ያን ጊዜ ”

አዛውንቱ ፈገግ ብለው በየተራ እያዩዋቸው “ለዚህ ነው ታሪካችሁን ከስር መሰረቱ እወቁ የምለው... በፊውዳሉ ስርዓት የኦሮሞን ህዝብ ማንም ከአገዛዙ አላገለለውም። አስረጅ ከፈለጋችሁም ይኸው..... ጎጃምን ይገዙ የነበሩት ንጉስ ተክለሀይማኖት፤ ከወሎ ንጉስ ሚካኤል መሀመድ፤ በአፄ ምኒልክ ጊዜ የጦር ሚኒስትርና የንጉሱ ልዩ አማሪካ ሆነው አገር እስከማገልገል ከፍተኛ ስልጣን የደረሱት ፊትአውራሪ ሀብተጊዮርጊስ እና

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ራስ ጎበና ዳጩ ከኦሮሞ የተገኙ ኢትዮጵያዊ ነበሩ፤ ጎንደር ወሌ ብጡል፤ ሀረር ራስ መኮንን እያልንን ብዙ ሰዎችን መጥራት እንችላለን፡፡ እንዲሁም የአፄ ቴዎድሮስ ሚስት ንግስት ምንትዋብ የአፄ ምኒልክ ንግስት ጣይቱ የአፄ ኀይለስላሴ ሚስት ኦሮሞዎች ነበሩ "

" ፊትአውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ኦሮሞ ነበሩ? " ቡልቻ በአግራሞት ጠየቀ
" አዎ..... ስማቸው ከመለወጡ በፊት ቆሌ ዲነግዴ ነበር የሚባሉት፡፡ በአፄ ሀይለስላሴም ዘመን እነ ጀነራል ታደሰ ብሩ፤ ጀነራል ደምሴ ቡልቶ፤ ረጋሳ ጅማ..... ፊት አውራሪ ገረሱ ዱኪ፤ ፊት አውራሪ ገለታ ቆሪቾ ልጅ ጃገማ ኬሎ.... እንደ ሌሎቹ የአገሪቷ ጀግኖች ከፋሺስት ጋር ተዋግተው በነፃነት እንድንኖር ያስቻሉን ሌሎችም ከፍተኛ የኢትዮጵያ ባለስልጣናት ኦሮሞች ነበሩ፡፡ አንዳቸውም ግን እኛ ኢትዮጵያዊ አይደለን እንገንጠል ብለው አልጠየቁም፡፡ ሁሉም ለአንዲት አገር አብረው ሲሰሩ ኖረዋል፡፡ የጣሊያን ፋሺስት በዛ ጦርነት ወደ አንድ ሚሊዮን የሚሆን ኢትዮጵያዊ ሲጨፈጭፍ መላው የአገሪቷ ህዝብ ነው የዛ ግፍ ሰለባ የሆነው፡፡ መከራውም የአርበኞቹ ትግልም ድሉም የመላው የአገሪቷ ህዝብ ነው የነበረው፡፡ እንደ ህዝብ የኛ ችግር ሆኖ ዛሬም ድረስ አገራችንን እያበጣበጠ ያለው የመደብ ልዩነት እና የአድሎዋዊ አገዛዝ ስርአት ችግር ነው እንጂ እንደ አገር እናንተን እንመራለን ብለው የተነሱት በጥባጮች ሳይመጡ በፊት የአንድነት ችግር እና ስጋት በኢትዮጵያ ላይ አይታወቅም ነበር፡፡ " አሉ፡፡

ልጆቹ የእውነተኛው ታሪክ ሚስጥር እየሰረፀባቸው ወጣ በዝምታ ተውጠው የአዛውንት አባታቸውን አንደበት ከማስማት አልተገቱም፡፡

ቡልቻ የነተበ ሀሳብ የያዙትን ሁለቱን የነተቡ መፅሐፍቶች ሳያስበው በሬት ላይ አስቀምጦዋቸው ኖሮ ያልታሰበ ጠንካራ ንፋስ መጣና ገፆቻቸውን እየበታተነ ወሰዳቸው፡፡
ቀጠሉ እሳቸውም "……የኦሮሞን ህዝብ ለነበረበት አስከፊ ችግር ዳርጐት የቆየው የአፄዎቹ ስርዓት ብቻ አልነበረም፡፡ ከገዛ ብሔሩ የተፈጠሩ ግን ብሔራቸውን ለሆዳቸው ሲሉ ክደው የሌላን ብሔር የስያሜ ካባ በመልበስና መልሰው የገዛ ወገኖቻቸው ላይ ተሹመው በመሔድ ህዝቡን እያሰቃዩት፣ እየጨፈጨፉትና እየበዘበዙት የኖሩት

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

የራሳችን የኦሮሞ ባንዳዎች ናቸው፡፡ የናንተ የትግል አለቆች ግን ነጋ ጠባ ነፍጠኛ ህዝብ እያለ ከአማራ ወገኖቻችን ጋር ሊያተራርዷችሁ ይታገላል፡፡..... አገራችን ያኔም ሆነ ዛሬ የአስተዳደር ለውጥ ነው የሚያስፈልጋት ሌላ ምንም ችግር የለብንም፡፡ "

ቀጠሉ " ..... በእድሜዬ ያስተዋልኩትን ታላቅ ነገር ልንገራችሁ..... አምላክ የበኩር ልጄ ብሎ አስበልጦ የመረጣትን እስራኤልን እንኳ ስንት ጊዜ ለባርነት አሳልፎ ሲሰጣት የኛ ኢትዮጵያ ግን ለማንም ሳትገዛ በነፃነት ኖራለች፡፡ ሁለተኛ የበርካታ ጎሳዎችና ብሔሮች መገኛ ሆነናል፡፡ ሶስተኛው በተለያዩ ሀይማኖቶች ባህሎች ቋንቋዎች ውስጥ በአንድነት ተዋዶ እየተጋባና እየተዋለደ የመኖር ጥበብን አካብቷል፡፡ አራተኛው የበለጠ አንድ አድርጎ ሳንደፈር አሸናፊ እንደሆንን እንድንኖር ያስቻለን በየትኛውን አቅጣጫ አገራችን ሊያጠቃ የመጣ ጠላት ላይ በህብረት እና በማይረታ ሀያል ቁጣ ለነፍሱ ሳይሳሳ ሆ ብሎ ተነስቶ ድል የማድረግን ፀጋ ከአምላኩ የተቀበለ ህዝብ ነው፡፡ ታድያ ይህን ልዩ የክብር ፀጋ ለምን ጠብቃቹ ለማኖር አቃታችሁ.....? አገርን ነፃ ለማውጣት እኮ እንደ አገር ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ እንደ ብሔር ወይም እንደ ግለሰብ ማሰብ ከጀመራችሁ ያኔ ነፃ እናወጣታለን ብላችሁ የተነሳችለሁላትን አገር እንደ ባቢሎን ማፈራረስ ነው የሚሆነው ፍፀሜው፡፡..... "

".....ስለዚህም ለኦሮሞ ህዝብ ህይወትና ኑሮ ማማር ምላሽ የሚገኘው ከመገንጠልና ከጦርነት አይደለም፡፡ ይልቅም ከመወያየት ከመደጋገፍ ከመፋቀሩ ላይ ነው፡፡..... እንዲሁም ከጥንት ጀምሮ ኦሮሞ ከመላው የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ጋር ተጋብቷል፡፡ ተዋልዷል፡፡ የማይበጠስ የዘር ግንድ ትስስርን ፈጥሯል፡፡ በባህልም በቋንቋም በሀይማኖትም ተዋህዷል.... በእኩይነት የመገንጠል ሀሳብ ይከናወን ቢባል እንኳ እንዴት ነው ሊሆን የሚችለው? የሰው ስንጠቃ ሊካሄድ ነው ወይስ ተዓምር መፍጠረ የሚያስችል እፅ አለ?

".....አትሳሳቱ የናንተ እናት አማራ ነች፡፡ ነገ ከነገ ወዲያ የናንተ ልጆች ከትግሬ ከአፋር ከሀዲያ..... ከወደዱት ሊጋቡና ሊዋለዱ ይችላሉ፡፡ ታዲያ ይህን እያወቃችሁ ዛሬ የመሰሪዎችን የመገንጠል

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ዓላማ የምትደግፉት ለምንድነው? መጪው የእልቂት ዘመን እንዲሆን?"

ሁለቱም በአሉታ ጭንቅላታቸውን ነቀነቁ፡፡
"ወያኔዎቹም ሆኑ እናንተን ለነፃነት እናዋጋለን ብለው የተነሱት አስገንጣዮች በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥም ሆነ በኢትዮጵያ መሬት ላይ መቃብር የሌላቸው መቃብር ቆፋሪያን ማለት ናቸው፡፡ አትሳሳቱ፡፡ አትከተሏቸው፡፡ ሆዳምና ከሀዲዎች ናቸው፡፡" አሉና ጥቂት በተመስጦ ቆይተው"..... እንግዲያስ ቃሌን አክብራችሁ እንደሰማችሁ የኢትዮጵያ አምላክ ይባርካችሁ፡፡ ፍቅርን ሰላምን አንድነትን ይስጣችሁ..... ልቦናችሁን ያብራላችሁ.... እውነተኛ የአገር ፍቅር ስሜት ካላችሁም ከገዛ ወንድሞቻችሁ ጋር ተታኩሳችሁ ደም መፋሰሱ ይቅርባችሁ..... የቦዘኑ በሬዎቻችሁን ጥመዱ በዚች ለም መሬት ላይ እረሱ..... በእረፍት ጊዜያችሁ ስለ አገራችሁ ታሪክ ተማሩ..... ነገና ከነገ ወዲያ ኢትዮጵያ በናንተ አንድነት በናንተ ትስስር የምትደምቅና የምትኮራ እንድትሆን አድርጓት" አሉ አዛውንቱ፡፡

ሁለቱም ቀናዊ በሆነ ስሜት ምርቃቱንና አደራውን ተቀብለው አሮጌ አስተሳሰባቸው በአዲስ አጥበው ወደ ቤት መመለስ ሲጀመሩ "ቡልቻ ይዘኃቸው የነበሩት መፃፍኾስ?" ጠየቀ ኡንዴ ወደ ታናሽ ወንድሙ እያየ፡፡
"ንፋስ ያመጣቸው ሀሳቦችን ስለያዙ ንፋስ ወሰዳቸው" አለው፡፡

  

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

ምዕራፍ 34

ተክለአይ ቀኑን አሰልቺ በነበረ ስብሰባና በተለይ «ግዳይ 200» የሚል ስያሜ በተሰጠው የወቅቱ ፈታኝ ተልእኮ ትዕዛዝ ሲሰጥና ውሳኔ ሲያስተላልፍ ነበር የዋለው። አመሻሽ ላይ ከቢሮው ወጥቶ ወደ ቤቱ ሲያመራ ከመዳከሙ የተነሳ የእለቱን የመጨረሻ የስራ ሪፖርት ጭምር ሳያነብ ወጣና ወሎ ሰፈር መንግስት ለብቻው እንዲኖርበት ወደ ሰጠው ባለ አንድ ፎቅ ዘመናዊ የግል ቤቱ አመራ።

ቤት እንደደረሰ ሳሎን ተቀምጦ በሀሳብ ነጎደ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ምንም ባልገባው ምክንያት ህይወቱ ትርጉም አልባ ሆኖበታል። በኑሮው ምንም አልጎደለበትም። ሀብት በቤቱ ካዝና መቀመጥ ከሚቻለው በላይ ፈሶለታል። እንደውም ከመብዛቱ የተነሳ በአራት የውጭ አገር ባንኮች ውስጥ በሚስጥር አከማችቷል። በስልጣኑ ያሻውን ማድረግ የኖረበት ከመሆኑ የተነሳ ማሰር፤ መፍታት፤ ማፈናቀል፤ መቅጣት፤ ማባበር ባስ ሲልም እስከ መግደል ይችላል። ይህ ሁሉ ግን ከባዶነት ስሜቱ ሊያወጣው አልቻለም።

ሶፋው ላይ ተቀምጦ ብላክ ሌብል ዊስኪ ያለ በረዶ በጠርሙሱ እየጠጣ ሲጋራውን ማጨስ ቀጠለ። ሰዓታት ነጎዱ። የጠርሙሱ ውስኪ ሊጠናቀቅ ጥቂት ቢቀረውም ሞቅ እንኳ አላለውም። "መስከር ካቆምኩ ዓመታቶች አለፉኝ እኮ" ብሎ ለራሱ በንዴት አጉረመረመ። ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ሲል ቲቪውን ከፈተው። «ኢቲቪ ዜና» አሰምቶ ጨረሰ። «ወቅታዊ መግለጫ...» አሰምቶ ጨረሰ። «ወቅታዊ ሪፖርት...» አሰምቶ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ጨረሰ:: «ወቅታዊ ጥንቅር...» አሰምቶ ጨረሰ:: ሁሉምን «ወቅታዊያን...» ጨረሰ..... ጨረሰ..... ጨረሰ..... ጨረሰ.....::

ከፍተኛ ባለስልጣናት፤ ሚኒስትሮች፤ የምክር ቤት አባላት፤ የክልል ከንቲባዎች፤ በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. ስር የተካተቱ ፓርቲ ባለስልጣናት፤ የወታደራዊ ክፍል አዛዦች፤ አጫፋሪ ፤ አቃጣሪ..... ይታያል ያልፋል..... ይታያል ያልፋል..... ይታያል ያልፋል..... ለራሱ ለተክለአይ ስርጭቱ አታካች እና አሰልቺ ሆነበት::

ሁሉም ባለስልጣናት አይን ውስጥ የህዝብ ንቀት እና ጥላቻ ይነበባል:: የታወኩና በጥርጣሬ ስሜት የተዘፈቁ፤ ምንም የገዢነት መንፈስ የማይታይባቸው፤ የደነገጡ፤ በፍርሀት የታፈኑ፤ ልበ-ሙሉነት የጎደለቸው፤ አንዳንዶቹ እንደውም ገና ከእስር የተፈቱ፤ ከሆስፒታል አምልጠው የወጡ፤ ሌሎቹ ከፊት መሳሪያ ተደግኖባቸው የሚናገሩ ይመስላሉ:: ሌላው የሚገርመው ሁሉም የአንድን ፈተና የመልስ ወረቀት ኮርጀው የመጡ ይመስል የሚናገሩት ነገርና የቃላት አጠቃቀመቸው ጭምር ከጠቅላይ ሚኒስትሩ የየእለት መዝገብ የተቀዳ ነው::

ይህም አንድ ደራሲ የመፅሐፉን ገፀ-ባህሪያት እንዳሻው አድርጎ እንደሚቀርፃቸው ሁሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩም እያንዳንዱን የአገሪቱን ባለስልጣን እንደ ወደዱት አድርገው ቀርፀዋቸዋል:: ከሀያው ነፍስ ቢፈጠሩም የተጠረቡ ድንጋዮች ሆነዋል:: ሁሉም አንድ አይነት ናቸው:: ሁሉም የሳቸው ገደል ማሚቶ ናቸው:: እንደ መፅሀፍ ቅዱሱ ኤሳው የራሳቸውን ኦርጂናልነት ለሆዳቸው ሲሉ ሸጠዋል:: ሁሉም አሰልቺ ናቸው:: ሁሉም ይደብራሉ:: ሁሉም ላይ ህዝብን እና አገርን የሚያስጨንቅ አዚም ሰፍሮባቸዋል::

እነሱም ታፍነው አገሪቷን አፍነው ይዘዋታል:: በተለይ የአዲስ አበባ ታፍናለች:: አየሩ፤ ፀሀዩ ፤ መንገዱ፤ እንቅስቃሴው ፤ ብቻ ሁሉም ነገር ምን እንደሆነ በማይታወቅ ውጥረት እንደታፈነ ያስታውቃል:: ሰዎች በማይታወቅ ሁኔታ ይታፈናሉ፣ ይደበደባሉ፣ ይታሰራሉ፣ ይገደላሉ:: ህጋዊ ባልሆነ አካሔድ ድንገተኛ ፍተሻ ይካሔድባቸዋል:: በገዛ አገሩ ህዝብ የባዳነት ስሜት እንዲሰማው ተገዷል:: ለመውጣት መግባቱ ዋስትና አጥቷል:: መንግስት አስቸጋሪ በሆነ ማዕበል ከወዲህ ወዲያ እየተላጋ ህዝቡን ማላጋት እንደጀመረ ያስታውቅበታል::

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

በስሩ የሚተዳደሩ መገናኛ ብዙሀኖች ነጋ ጠባ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችን ሲያብጠለጥሉ ሲኮንኑና ሲያንቋሽሹ ውለው ያመሻሉ በተለይ በኦሮምኛ ቋንቋ የሚተላለፉት የራዲዮና የቴሌቪዥን ስርጭቶች "ኦ.ነ.ግ." እና "ኦ.ብ.ነ.ግ" ስለሚባሉት ፓርቲዎች አሸባሪነት አውርተው ሊጠግቡ ተስኖዋቸዋል።

እንደዚህ አይነት አድራጐቶችን የፖለቲካው ምሁራኖች "ውድቀት ሲቃረብ የሚፈጠር ክስተት ነው" ይሉታል። ስልጣን ላይ ያለው መንግስት የተፈጠሩበትን የችግር ጉድፎች ከራሱ ገላ ላይ አፍሶ እያነሳ ተቃዋሚ የሆኑበት የፖለቲካ ድርጅቶች ወይም የሌላ መንግስት አገሮች ላይ ወርውሮ በመለጠፍ "እዩ ቆሻሻነታቸውን" እያለ እዳሪ እዳሪ የሚል ስብከቱን ከልካይ በሌለበት ስልጣኑ ያንበለብለዋል።

ተክለአይ ይህንኑ የምሽቱን የቲቪ ስርጭት በታከተ ስሜቱ ሲከታተል ቆይቶ እንቅልፍ እንደማይወስደው እርግጠኛ ሲሆንና ቤቱ የመቃብር ያህል ሲከብደው አብራው የምታድር ሴተኛ አዳሪ ለማምጣት ተነስቶ ወጣ። በዛው እየዞረ ሲጠጣ አምሽቶ ሴት ይዞ ተመለሰ።

ጠዋት ገና ጎህ እንደቀደደ ወሎ ሰፈር አካባቢ ከመንገድ ላይ ያመጣትን ሴተኛ አዳሪ ያገኛት ቦታ አውርዷት ወደ ቢሮው አመራ። ቢሮው ሲደርስ በሚያሰቃየው አንጎበር እና ራስ ምታት እየፋሸከ ሲጋራ ለኮሰና ሲቀመጥ ጠረጴዛው ትላንት በመሰላቸት ሳያየው ትቶት የወጣውን የ«ግዳይ 200» ሪፖርት ላይ አይኖቹ አረፉ። ወድያው ነበር ሀላፊነትን ከተረከበው የመረጃና የህዝብ ደህንነት ሹሙ ጋር ከእሰጥ አገባ ያልተናነሰ ንትርክ በስልክ ማድረግ የጀመረው።

በስለላ ሰዎቻቸው የሚደረጉት ክትትሎችና የተደረሱባቸው መረጃዎች በጠቅላላ ስሜት አልሰጠውም ድንገት ያስቆጣው ጉዳይ የተከሰተው ግን የመስፍንን ሞት ማወቁ ነበር። ወድያውኑ የደህንነት ሹሙ ቢሮው ድረስ እንዲመጣ ካዘዘው በኋላ ትዕግስት አጥቶ በመቁነጥነጥ ጥበቃ ጀመረ።

በዚህ መካከል ብዕር ያነሳና ባዶ ወረቀት ከፊቱ በማድረግ የመጣለትን ሀሳብ ለመፃፍ ይሞክራል። ግን የሚፈልገውት ሀሳብ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ለኩሶ የመተርከሻው ከንፈር ላይ እንዳስቀመጠው ሲጃራ ጢስ እየተበታተነ ይጠፋበታል።።

የደህንነት ክፍሉ ዋና ኃላፊ የቢሮውን በር ከፍቶ ገባ።።

ካለ ምንም ቅድመ መግቢያ የቃላት ልውውጥ "እንዴት አንድ መረጃ ከመስጠቱ በፊት መስፍን የተባለውን ሰው ገደላችሁት?" ፊቱን አጨፍግጎ ጠየቀው።።

"በአጋጣሚ በቦታው ላይ የተመደቡት የሰለጠኑ አባሎቻችን አልነበሩም።። ስህተቱ የተፈጠረው ለዛ ነው"
"እነማናቸው?"
"ከፌደራል ፖሊስ የተወሰዱ የክትትል አባሎች....."
"በቃህ....." እያፈጠጠበት ንግግሩን ቀጠለ ".....የተገኘውን ፍንጭ በጠቅላላ አጠፋችሁት።።"
የደህንነት ሹሙ አቀርቅሮ ቀረ።።
"ተናገር ምንድነው ቀጣይ መፍትሔው የተገኙ ማስረጃዎች ወይም አድራሻ መሰል ፍንጭ ሰጪ ነገሮች አሉ?"
"ምንም አልተገኘም።።"
"ምኑ ሞኝ ነውና ይዞ ይዞራል....."

"ግል ማጎደሮቹን አሰባሰብክ?"
"አዎ..... በህፃንነቱ ከተማረበት ትምህርት ቤት አንስቶ አሁን ይሰራበት እስከነበረበት መስራቤት ድረስ ያሉትን ሁሉምንም ያገላበጥኩኝ ቢሆንም ወዴትም ሊያራምድ የሚችል መረጃ ሊገኝበት አልተቻለም"
"በተገደለበት ሰዓት የክትትሉ የበላይ አዛዥ የነበረው ሰው ማነው?"
"በፌደራል ፖሊስ ስር ያለና የተወርዋሪ ክፍሉ ዋና አዛዥ የነበረ አንድ ሻለቃ።።"
"ብሔራዊ ቲአትር አካባቢ ባለ አንድ ህንፃ ላይ ተካሔደ ያላችሁኝ ክትትልስ?"
"በራሱ በሻለቃው ነበር የተመራው"
"ለመሆኑ ብሔሩ ምንድነው?"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“የደቡብ ክልል ተወላጅ..... ለነገሩ ልምድ ያለውና በእድሜም በሰል ያለ መሆኑ ማህደሩ ላይ ተገልጧል።”
ተክለአይ ‘በታማኝነት በኩል የኦሮሞ ተወላጅ ከሚሆን ደቡብ መሆኑ ይሻላል’ አለ በህሊናው። ቀጠለ ‘.....ቢሆንም ግን ከራሴ ብሔር የሚበልጥ ማንም ታማኝ ሊኖረኝ አይችልም’ ሲሉ አስቦ “ከአሁን ጀምሮ የመዋቅር ለውጥ አድርግ”
“እንዴት?”
“የክትትሉ ስራ በጠቅላላ በራስህ መሪነት እና በሰለጠኑ የደህንነት አባሎች ብቻ ይከናወን። ለከባድና ለተመሳሳይ እርምጃ ተጨማሪ የሰው ኃይል ሲያስፈልግህ ብቻ የፌደራል ወታደሮችን እሱንም በራስህ አዛዥነት ብቻ መጠቀም ያለብህ። እንዲሁም ፌደራሎችን ከመረጃ ውጪ አድርጋቸው። ጥብቅ በሆነ ሚስጥርና ረቂቅ ክትትል በራስህ ብቻ ይከናወን።”

“የሰላይ ሀላፊዎችንስ?”
“ሁሉንም!” በዝምታ ሲያየው ቆየና ጠረጴዛውን በመዳፉ ተረተር ንግግሩን አስከትሎ እየተመተመ “በተጨማሪ ደግሞ በእያንዳንዱ ከፍተኛ ባለስልጣናት፤ የምክር ቤት ሰዎችና አጠራጣሪ እንቅስቃሴ ያላቸው አባሎች ላይ በሰውም ሆነ በመሳሪያ በተቀናጀ ሁኔታ ሚስጥራዊ ክትትል ይደረግባቸው።”
“ጀምረናል እሱንማ..... ዘጠና ከመቶ በሚሆኑት ባለስልጣናት ላይ ስለላውን ከጀመርን ቆየን እኮ”
“በጣም ጥሩ የምትደርስበትን ሁሉ ማወቅ ይገባኛል”
“እሺ” ብሎ ወጣ።

ካለፉት ጥቂት ቀናት ወዲህ በተለያየ ጥብቅ ጉዳይ እየተጠሩ ወደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ እየገቡ የሚወጡት ባለስልጣናት ቁጥር ጨምሯል። አንዳንዶቹ በስልጣን ተዋረድ በቀጥታ እሳቸውን ማግኘት የማይችሉ ቢሆኑም እንኳ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ትእዛዝ እንዲገቡ ይደረግ ነበር። ሁሉም ገብተው ሲወጡ ግምባራቸው ላይ ያጤዘውን ላብ በድንጋጤ ሞዥቀው እጃቸውን ሲያወርዱ አጢዞ ከነበረው ግምባራቸው ላይ የሆነ አይነት አስፈሪ ጭካኔ ይነበባል።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

አብዛኞቹ በሌላኛው እጃቸው ላይ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ በቀጥታ የተረከቡትና ትዕዛዝ የተላለፈበት ነጭ ወረቀት ይዘው ይታያሉ። በዛች በተጌጠች ቀላል እና ተራ በምትመስል ነጭ ወረቀት ላይ የሰፈረው ትዕዛዝ መተግበር ሲጀምር ግን ከሰላ ሰይፍ የባሰን ሰቆቃን ነበር አስከትሎ ወደ ህዝብ የሚደርሰው።

  

የማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ምዕራፍ 35

ሰናይት የሁኔታዎች ከቀን ወደ ቀን አስፈሪና አደገኛ እየሆነ መምጣት እጅግ አስግቷታል። ሁኖም የስራው በርካታ ክፍል መጠናቀቅ ደግሞ ከፊት ይኖረኛል ብላ ላሰበችው የቅንጦት ህይወት አጓጊን ተስፋን እያሳያት ስራውን ባላት አቅም ሁሉ ፀንታ ማጠናቀቅ ንደሚገባት ህሊናዋ ግድ ብሏታል።

ይህም በመሆኑ ያደራጀቻቸው ህቡእ ፓርቲዎች ለስራቸው ማከናወኛ የጠየቋትን ገንዘብ እነ ሉዊስ ባገናኟት ሰው አማካኝነት ወደ አገር ውስጥ አስገብታ እንደየጥያቄዎቻቸው በማከፋፈል ጳውሎስ የሚመራውና በደቡብ የኢትዮጵያ ክልል ላይ ለተቋቋመው ፓርቲ የተመደበው ገንዘብ ብቻ ነበር እጇ ላይ የቀረው።

እነሉዊስን ከሁሉም ይልቅ ያረካቸውናትልቅ ውጤት ያመጣል ብለው ያመኑበት ደግሞ በአማራው ክልል ላይ ሊንቀሳቀስ የተስማማው ጄነራል ምትኩ ሲሆን ከሱ ጋር ለመስራት ፈቃደኛ የሆኑና ለማጥቃት ዝግጅታቸውን ያጠናቀቁ ሁለት ሙሉ የጀነራልነት ማዕረግ ያላቸውና ሶስት ሙሉ ኮለኔል ስልጣን ያላቸው ሰዎችን ማግኘቱን መግለፁ ነበር። የባለስልጣቱ የስራ ክፍልም በተለያየ ካምፕ ውስጥ በመሆኑ እንዲሁም ከአየር ሀይል፤ እግረኛ ሰራዊት፤ ከብረት ለበስ ተሽከርካሪ ዋና መምሪያዎች ውስጥ የተውጣጡ ለእቅዱ ጥሩ ውጤት ማስገኘት የሚችሉ መሆናቸውን አረጋግጠላቸዋል።

ሌላው ክፍያውን ሲቀበል በተጨማሪ አብሮ የገለፀላት ጉዳይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ድንገት በጠሩት ስብሰባ ምክንያት በተጨማሪ ጥቂት ቀናት የሚቆይ ሲሆን ይህ ከፍተኛ የሆነ ሚስጥራዊ ስብሰባ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

እንደተጠናቀቀም ወደ ወለጋ ግዛት አስከትሎ ከሚሔደው የጦር ሰራዊት ጋር እንደሚከዳ በአሳማኝ ሁኔታ አስረድቷታል።።

መገናኛ አካባቢ የተከራየችው ቤቷ ሆና ይህንኑ ሀሳብ እየመላለሰች ስታብሰለስል ቆየችና በእጇ ላይ ያለውን የደቡብ ክልል ክፍያ ለመስጠት ስልኩን አንስታ የምክር ቤት አባል ወደሆነው ጳውሎስ ቤት መደወል ጀመረች።።

ሰዓቱ ከቀኑ ሰባት ብሎ ነበር።። ምሳውን አዘውትሮ ቤት የመመገብ ልምድ እንዳለው ታውቃለች። አልተሳሳተችም ስልኩን ራሱ ጳውሎስ አነሳው።። " አቶ ጳውሎስ እንደምን ዋልክ?"
"ደ....ደህና ማነህ?" ጳውሎስ ጠየቀ
"ሰናይት....."
"ሰናይት!? "
"አዎ.....ምነው..... ደነገጥክ?"
".....አይ..... ደህና ነኝ" በጳውሎስ አስተሳሰብ በበድሉ ህንፃ ውስጥ ከተወሰደው እርምጃ በኋላ እስከመጨረሻው ስለምትሰወር አላገኛትም ብሎ ነበር።። እንደገና ሰላምታ ከተለዋወጡ በኋላ ሰናይት "ድምፅህ ላይ ሰላም ያለህ አትመስልም ተረብሿል"
"እንዴት?"
"ማለት..... የደነገጥክ.....ወይም..... ያመመህ ትመስላለህ .....?"
"ድንጋጤ አይደለም..... ከባለቤቴ ጋር ትንሽ ተጋጭተን ስንጨቃጨቅ ነው የደወልሽልኝ..... ለዚህ ይሆናል።" የፊጠራ ምክንያት ሰጣትና "ምነው ጠፋሽ?..... በሰላም ነው...?"

"ችግር ገጥሞኝ..... መንግስት ሊይዘኝ ሞክሮ ነበር ግን አልተሳካላቸውም ተአምር በሚባል ሁኔታ አመለጥኳቸው።።" አለችና በቀጥታ ወደ ጉዳዩ በማምራት "ያለፈ ጊዜ ለፓርቲያችሁ ማጠናከሪያ የጠየከው ክፍያ ተልኮላችኋል"
"ምን ያህሉ ተላከልን?"
"ሃያ ሚልየን ዶላሩ"
"መቼ መውሰድ እችላለሁ?" እንዴት ሊያምናት እንደሚችል ግራ ተጋብቶ እየተጠራጠረ ጠየቃት፡ በህሊናው 'ወጥመድ ይሆን' እያለ በማሰብ።።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“እንደተመቸህ.....” ቀጠለች ሰናይት “.....የጦር መሳሪያዎቹ በፈጣን በመርከብ ተጭነው በጉዞ ላይ ናቸው፡፡ ከጥቂት ቀናት በኋላ የሚደርሱ ይመስለኛል፡፡ የመረከቢያ ደብዳቤው በአንተ ስም ነው የተፃፈው፡፡”
አቋረጣትና “ከማነው የምረከበው?”
“በምትፈልገው መልኩ ሁኔታዎች ይመቻቹልሀል.....”
“በየት በኩል ነው የሚገባው?”
“በሶማሊያ ወደብ..... አብረን ስለምንሔድ ዝርዝሩን በወቅቱ እነግርሀለው፡፡ የመረከቢያ ደብዳቤውን ግን እጄ እንደደረሰ አስረክብሀለውኝ..... ፓርቲያችሁን ህዝበ ደቡብ ነፃነት ሀይል ንቅናቄ ወክለህ አንተና የመረጥካቸው ሰዎች አብረውህ መገኘት ይችላሉ፡፡ አሁን ገንዘቡን ቅድሚያ መውሰድ ትችላለህ ”
“እሺ ጥሩ ነዋ.....”
በዚህ ቅፅበት ወደ ሰናይት የሚመጣው የስልክ ምልልስ ውስጥ ነፋስ የገባበትና የሚቆራረጥ “ጢን...ጢን....ጢን” የሚል ድምፅን ከጳውሎስ ንግግር ጋር እየተቀላቀለ ማሰማት ጀመረ፡፡ የእንደዚህ ዓይነት ክስተቶች ዋና ምክንያት ስልኩ ባልታወቁ አካላቶች የመጠፈፍ ምልክት መሆኑን ከፈረንሳይ ከመምጣቷ በፊት የጥቂት ሳምንታት ስልጠና ውስጥ መማሯን አስታወሰች፡፡ የስልኩ መስመር እንዲጠለፍ በሚገጠሙት መሳሪያዎች ላይ በሚፈጠረው ተራ ችግር ወቅት የሚሰማ ድምፅ ነበር፡፡
“ጳውሎስ!” በጠንካራ ቅላፄው ጠራችውና “ይሰማሀል?”
“ምኑ?”
“እርግጠኛ ነኝ ስልኩ ተጠልፏል”
“ምን!?”
“በፍጥነት ቤትህን ለቀህ ጥፋ!” አለችውና መነጋገሪያውን ወርውራ ዘጋችበት፡፡ በስልኩ መስመር ላይ የሚገጠመው የጠለፋ መሳሪያ የሚያገለግለው ንግግርን ለመስማት ብቻ ሳይሆን የደዋዩንም ሆነ የተደወለበትን ስልኮች አድራሻም አመልካች የሆነ ዘመናዊ ሲሆን ይህንን የስለላ ስራ በሁሉም ባለስልጣናት፤ የምክር ቤት አባላትና፤ በመንግስት ተቃዋሚነት የሚጠረጠር ማንኛውም ግለሰብ ላይ ክትትል እንዲያደርጉ በበርካታ ሚልዮን ዶላር ክፍያ ሚስጥራዊ ኮንትራት

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ወስደው ከኢትዮጵያ ህዝብ ደህንነት የሚስጥር ሰዎች ጋር የሚሰራው አንድ የጀርመን ድርጅት ነበር።።

ሰናይት በፍጥነት ስልኩን ወርውራ በመነሳት የተከራየችው ቤት ውስጥ የነበሩትንና ሚስጥር ይገኝባቸዋል ብላ የገመተቻቸውን ሰነዶች፤ ላፕቶፕ እና እጇ ላይ የነበረውን ለጳውሎስ የሚሰጥ በርካታ ገንዘብ በጠቅላላ አነስ ባለ ሻንጣ ቀረቀበችና ከገንዘቡ ጋር ከፈረንሳይ እንዲልኩላት ያስደረገችውን ድምፅ ማፈኛ የተገጠመለትን ሽጉጥ አውጥታ በማቀባበል ከተከራየችበት ጊቢ በፍጥነት ወጣች።።

«««««««« »»»»»»»

ጳውሎስ በሰማው ነገር ከመደናገጥ ውጪ መውሰድ የሚገባውን እርምጃ ማወቅ አልቻለም።። ሚስቱንና ልጆቹን መዘገጃጀት የሚገባቸው ነገሮችን በቀላሉ አሰባስቦ እንደ ነጠላ ሰው ሹልክ ማለት ለሱ ከባድ ነበር።።

ደቂቃዎች ነጐዱ።። ከተቀመጠበት ቦታ ሳይነሳ የቤቱ በር ተንኳኳ።። ሚስቱ ተራምዳ ስትከፍተው እሱ እንደፈዘዘ ተቀምጠ ቀረ።።

ቡኒ ቀለም ያለው ሙሉ ሱፍ የለበሱና ደንደን ያለ የጨዋ ሰው ገፅታና አቋም የሚታይባቸው ሁለት ሰዎች ሲሆኑ አንደኛው በተለሳለሰ አንደበት "አቶ ጳውሎስ ይኖር ይሆን?"
"ማነህ ልበለው?"
"ከመንግስት ምክር ቤት የመጣሁ ባልደረባው ነኝ"
"ግባ....." አለችው በሩን እስፍታ እየከፈተችለት።።
እንደሚያውቀው ሰው በጥሩ ሁኔታ ጨበጠውና "ለአንድ ደቂቃ ብቻህን ላነጋግርህ እፈልጋለሁ"
"ይቻላል" አለውና ለሚስቱ በአይኑ ግቢ የሚል ትዕዛዝ ሰጣት።።
"እ..... በምክር ቤት አባሎች ላይ አሸባሪ ፓርቲዎች ግድያና አፈና እየፈፀሙ ስለሆነ መንግስት ፀጥታው ጥብቅ ወደ ሆነ ስፍራ መኖሪያችሁን ሊያዘዋውርላችሁ ፈልጓል"
ጳውሎስ ቀጥ ልትል የነበረች ትንፋሹን በረዥሙ ለቀቃት "ለ.....ለኛ ሊለወጥ?" ድንጋጤው ያስታውቅበት ነበር።።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

“አዎ.....ከዛ በፊት ግን አብረን ወደ ቢሮ እንሔድና ስለምትመርጡት የመኖሪያ ስፍራ ከሚመለከተው ሰው ጋር ትነጋገራለህ”

“ምን ችግር አለው፡፡” እምቢታውን ምን ሊያስከትልበት እንደሚችል አስቦት በመፍራቱ ብቻ እንጂ መሔዱ እየቀፈፈው ኮቴን ለበሰና ሚስቱን ተሰናብቶ ወጣ፡፡ ህንፃውን ወርደው እንደጨረሱ ሶስት ሰዎችን የጫነ ቶዮታ ላንድ ክሩዘር መኪና ቆሞ እየጠበቃቸው ስለነበረ ገብተው ጉዞ ጀመሩ፡፡ የመኪናው የጐን መስታውቶች በጠቅላላ ጥቁር መከለያ ተለጥፎባቸው ስለነበረ ከውስጥ እንጂ ከውጭ ወደ ውስጥ አያሳዩም፡፡

««««««« »»»»»»»

በዛው ቅፅበት በሀይሌ ገብረስላሴ ጐዳና ላይ በከፍተኛ ፍጥነት የትራፊክ መብራት እየጣሰች ትግሰግስ የነበረች አንድ ዘመናዊ ነጭ መርሰዲስ መኪና በተሰጣት አድራሻ መሰረት ሰናይት ወደ ተከራየችበት ቤት አቅጣጫ ታጥፋ መግባት ጀመረች፡፡

የለጠፈችው ታርጋ የዲፕሎማቲኮች መስራቤት በመሆኑ ማንም ሰው የኤምባሲ መኪና ነች ብሎ ነበር የሚያስበው ፡፡

ሰፊው የብረት በር ጋር ለመድረስ ሃምሳ ሜትር ያህል ሲቀራት አቆመች፡፡ በውስጡ የነበሩት ሶስት ሰዎች በፍጥነት ወረዱ፡፡ኘሮተኮሉን የጠበቀ አለባበስ ለብሰዋል፡፡ አንደኛው መኪናው አካባቢ ፈንጠር ብሎ ሲቆም ሁለቱ ግን ወደ ብረት በሩ ጊቢ ደረሱና ለማስከፈት የደውሉን መጥሪያ በአቅራቢያው ያለው ሰው ተጫነው፡፡ ዘበኛው ከፈተና የማያውቃቸውን ሰዎች በየተራ እያጠና “አቤት?”
“የቤቱን ባለቤት ማግኘት እንፈልጋለን?”
“ግቡዋ ወደ ውስጥ አሉ.....” አለ ዘመድ ቢጤ ይሆናሉ ብሎ እያሰበ፡፡

የቪላው በረንዳ ጋር ሲደርሱ ቆሙ፡፡ ሁለቱም በህሊናቸው የሚጠብቋት ሴት ጐልመስ ያለች ነጋዴ መሳይ ፖለቲከኛ ግለሰብን ነበር፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

እርጅና ያጐሳቆላቸው ባልቴት በሚያሳድጓት የዘመዳቸው ልጅ እየተመሩ ወጡ።።

በዚህ ጊዜ አንደኛው የደህንነት ሰው "ባለቤት እሳቸው ናቸው?"

"አዎ.....እኔ.....ነኝ" መለሱ አሮጊቷ።።

"ሌላ ሴት የለም?"

"ምን ዓይነት ጥያቄ ነው እኛ ብቻችንን ነው የምንኖረው።።" አሉ አሮጊቷ

"ቤቱን መፈተሽ እንፈልጋለን!?"

"ለምን ተብሎ!?" አሮጊቷ በጠንካራ ስሜት ጠየቁ።።

"ፖሊሶች ነን።። ወንጀለኛ ሰው ደብቃችሁ አስቀምጣችኋል"

"ወግዱ ወዲያ!?.....ምን ይላል ይሄ.....እኔ ነኝ ደባቂ.....!?" ቁጣቸው እየገነፈለ መለሱ።።

"በፈቃደኝነት ካላስፈተሻችሁን ልናስገድዳችሁ እንችላለን" አለና የመገናኛ ራዲዮኑን ከኪሱ አውጥቶ በመክፈት "ግዳይ 200" በማለት ተጣራና "ኪራይ ሰብሳቢዋ ሴትዮ ችግር እየፈጠረችብን ነው....." በማለት ሁኔታውን ለአለቃው ገለፀና ጠንከር ያለ ትእዛዝ ተቀበለ።።

ከዛም ሁለቱም የተቀባበለ ሽጉጣቸውን መዘው መጠበቂያውን ከፈቱና ወደ ቤቱ መግባት ሲጀምሩ አሮጊቷ ወጣቷና ዘበኛው በድንጋጤ ደርቀው ቀሩ።።

ቤቱ ውስጥ የሚታዩት እቃዎች እድሜ ጠገብ መሆናቸው ያስታውቃሉ።። አባሎቹ እያንዳንዱን ክፍል ሲያስሱ ቆዩና ወደ ሳሎኑ በመመለስ አንደኛው "ይህ ፎቶ የማነው?" ጠየቀ ግድግዳው ላይ በትልቅ ፍሬም ተሰቅሎ ወደሚታየው ወጣት ሴት ፎቶ እያመለከተ።። "ልጄ" አሮጊቷ መለሱ።። ሁለቱም የደህንነት አባሎች እሷ ነች ተፈላጊዋ በሚል ስሜት ደመደሙ።።

"የት አለች አሁን?"

"አመሪካን ነዋ"

ሁለቱም ኩምሽሽ አሉ።። የአንደኛው አባል ጥርጣሬ ወደ ዘበኛው አዘነበለ።።

"ከሃያ ደቂቃ በፊት ስልክ ከዚህ ቤት ደውላ የነበረችው ሴት ማናት?"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

“እረግ..... ሴት የሚባል የለንም.....” ብለው ሲያስቡ ቆዩና “.....ያቺ ተከራይቱን ትሆን እንዴ?” አሉ አሮጊቷ፡፡
“ተከራይ አላችሁ?”
“አዎ.....በስተጀርባ ክፍል”
አባሎቹ ሽጉጣቸውን እያስተካከሉ ከቪላው በስተግራ ጐን ወደተሰራው የተቆለፈ ክፍል ተራመጡ፡፡ ደርሰው በበሩ መስታውት ለማየት ሞከሩ፡፡
ከዛም መስታውቱን በሽጉጡ ሰደፍ መስበር ጀመሩ፡፡
አሮጊቷ “ኡ....ኡ....ዝም ብለሀ ታያለህ ቤቱን ሲሰባብሩት?” ወደ ዘበኛው እያፈጠጡ መጮኽ ጀመሩ፡፡

የእድሜው ድባብ ተጭኖ ያሳሳው ድምፃቸው ሶስት ሜትር ያህል እንኳ ርቆ ለቆመ ሰው አይሰማም ነበር፡፡
ዘበኛው ዱላውን ለስንዘራ ሲያመቻች አንደኛው ሽጉጡን ዞሮ ደገነበት፡፡ እንደ ሀውልት ደርቆ ቀረ፡፡ድጋሜ ወደ አሮጊቷ ዞሮ ሲደግን ጭጭ አሉና መሬት ላይ ወደቁ፡፡
ወጣቷ ግን በፍርሀት ከመርበትበት ውጪ የሚከናወነውን በዝምታ ታያለች፡፡
አንደኛው በተሰበረው መስታውት በኩል ዘሎ ገባና ክፍሉን አተረማምሶ ባዶውን ወጣ፡፡
ከዛም ወደ ዘበኛው ተራምዶ በማፍጠጥ “ከቤት የወጣችው ስንት ሰዓት ላይ ነው?”
“እናንተ ተመድረሳችሁ ጥቂት ቀድሞ”
“ወዴት ሄደች?”
“እኔ ምን አውቄ..... ብቻ ትልቁን ሻንጣቸውን ይዘው ነበር፡፡ አስፋልቱ ድረስ ወዛደርም ስለሌለ ልሸኞት ትላቸው አከላከለውኝ ራሳቸው ይዘው ኼዱ”
“ሁልጊዜ በዚህ ቤት ነው የምታድረው?”
“አይ..... በሁለትም በሶስትም ቀን አንዴ ብቻ እንዳሻቸው ነው” አሉ ዘበኛው የሚያውቁትን እውነታ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ራዲዮ ይዞ የነበረው አወጣና የተነገረውን ነገር በሙሉ አለቃው ለሆነው የደህንነት ክፍሉ ዋና ሀላፊ አሳወቀ፡፡

ተጨማሪ አባሎች ተልኮላቸው በአካባቢው ላይ ጥብቅ አሰሳ እንዲደረግ አዘዘና እስኪላኩላቸው ድረስም አካባቢውን እየተዘዋወሩ በመቃኘት እንዲቆዩ ተነገራቸው፡፡ ምናልባት ቢያዩዋት እንኳ ተቻኩለው ሳይሟት የምትሄድበትን ፤ የምትገባበትን ፤ የምትገናኛቸውን ሰዎች አጠቃላይ እንቅስቃሴ ብቻ እንዲያስተላልፉ ጨምሮ አዘዛቸው፡፡ ሾፌሩም አካባቢውን ለቆ ለጥርጣሬ የማያጋልጥ ስፍራ በመሆን እንዲጠብቃችሁ ንገሩት አላቸው፡፡

አባሎቹ ስሟን ጨምሮ ልዩ ምልክት ሊሆናቸው የሚችላቸው ነገሮች በጠቅላላ ከዘበኛው ወሰዱና ወጡ፡፡

በዚህ ወቅት ላይ ሰናይት ሻንጣውን በአስፓልቱ አካባቢ ያለ አንድ አልቤርጐ ቤት ተከራይታ ቆለፈችበትና ወደ ቪላው በመመለስ ሁኔታውን ለእይታ የማያጋልጠው ስፍራ ላይ ቆማ ትከታተል ነበር፡፡

ሁለቱ ሰዎች ከጊቢው ሲወጡ እሷም ወደ አልቤርጐ ተመለሰችና ሻንጣውን አውጥታ ታክሲ በመኮናተር ሩዋንዳ አካባቢ ወደ ተከራየችው ቤት ተፈተለከች፡፡

ሀሊናዋ 'ከዚህ ዕለት ጀምሮ በፍፁም እዚህ አካባቢ እንዳትገኝ!' ብሎ እያስጠነቀቃት ነበር፡፡

«««««««« »»»»»»»

ጳውሎስ በቁጥጥር ስር መዋሉን ያወቀው የገባበትን መኪና የውስጥ አካል በማየት ነበር፡፡ የተራቀቁ የመነጋገሪያ መሳሪያዎች ተገጥመውለታል፡፡ እንዲሁም ኮምፒውተር መሳይ መሳሪያና ከዚህ ቀድሞ አይቶ የማያውቃቸው ውስብስብ መገልገያዎች የመኪናው የኋላ ክፍል ውስጥ ተገጥመውለታል፡፡

በመሳሪያዎቹ የኮድ ንግግር ማስተላለፍና መቀበል የመንገዶች አቅጣጫ ማንበብ እንዲሁም ለማመን በሚያስቸግር ፍጥነት መረጃዎችን ከጠለፋ ነፃ በሆነ ስጋት መለዋወጥ የሚያስችሉ ነበሩ፡፡

ይህን እያሰበ መኪናው መስቀል አደባባይ ጋር ደርሶ ወደ እስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን በመታጠፍ የተለመደውን የመስራቤቱን

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

መመላለሻ መንገድ መያዝ ሲገባው ቀጥታ ወደ ላጋር መስመር ማምራት ጀመረ፡፡ በትትክልም መያዙን ማወቅ ቻለ፡፡

መኪናው ውስጥ የነበሩት ሰዎች በጠቅላላ ተመሳሳይ ሰዓት ማሰራቸውን ተመሳሳይ ቀለበትና ቀበቶ ማጥለቃቸውንም አየ፡፡ ምን ሊሆን እንደሚችል ባይገባውም ምክንያት እንዳለው ግን ከመገመት አልተገታም፡፡

ሰዓቶቹ የፎቶግራፍ ማንሻ መሆን የሚችሉ እንዲሁም በቀለበቶቹና በቀበቶ በብረቶች ላይ በተገጠሙት ረቂቅ የመገናኛ መሳሪያዎች አማካኝነት ምስልና ድምፅ እየቀረፁ መኪናው ውስጥ ወዳለው ኮምፒውተር በሞገድ በማሻገር የሚያሳዩ ነበሩ፡፡

ጳውሎስ የሚወስዱት ቦታ ከደረሰ በሚወሰድበት ምርመራ በርካታ ሚስጥሮችን ለመናገር እንደሚገደድ አመነ፡፡ ሚስቱና ልጆቹ የሚታገልለት ፓርቲ ታሰቡት፡፡

ያለው አማራጭ ሲዘጋጅ በኖረው መሰረት አንድ መሆኑን አመነ፡፡ እጁን እያዋዛ ወደ ታጠፈው የኮቱ ኮሌታ ሰደደና ሽንቁር መሰል ቀዳዳ ውስጥ ጣቱን አስገብቶ በካኘሱል የታሸገች መድሀኒት በማውጣት ወደ አፉ ውስጥ ወረወራት፡፡

በዚህ ቅፅበት ያየው የደህንነት አባል በጠንካራ ቡጢ ጐን አገጩን አጐነው፡፡ ሀሳቡ መድሀኒቱን ለማስተፋት ነበር፡፡

ጳውሎስ ግን የሳናይድ መርዝ የያዘችውን ካኘሱል በመንጋጋዎቹ መካከል ጨፍልቆዋታል፡፡ ወድያው አረፋ እያስደፈቀው አንድ ደቂቃ ባልሞላ ቅፅበት ህይወቱ አለፈች፡፡

«««««««« »»»»»»»»

ሰናይት ሩዋንዳ አካባቢ ወደ ተከራየችው ቤቷ ደርሳ ጥቂት እንደተረጋጋች ተራ የሆኑ ልብሶችን ለዋወጠችና በቀጣዩ ምን ማድረግ እንዳለበት ማሰብ ጀመረች፡፡

እስኪመሽ ድረስ ከቤት አልወጣችም፡፡ ማታ ላይ በዚህ ቤት ማደሩ በራሱ ለደህንነቷ አስፈሪ ሊሆን እንደሚችል አመነች፡፡ አንድ መልካም አማራጭ መስሎ የተሰማትን መንገድ ስታስብ ቆይታ ‘በህይወቴ ውስጥ ሳይሆን በኑሮዬ ውስጥ አንድ ሰው ማስገባት፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ወይም ወደ አንድ ሰው ኑሮ ውስጥ መግባት አለብኝ' አለች፡፡ ቀጠለች 'ለሽፋን ይጠቅመኛል..... ግን ያ ሰው ከየት ይገኛል?' ረዥም ሰዓት አሰበችበት፡፡ ወንድ ላይ ካላትና አብሯት ባደገው ጥላቻ ምክንያት ወደ ወንድ መቅረቡን ገና ስታስበው ሊያስታውካት ተናነቃት::

በመጨረሻ ላይ ማህበራዊ ህይወቱ ከድህነት ጋር ተዳምሮ እጅግ ወዳቆራኛቸው አካባቢዎች ውስጥ መደበቅ እንደሚሻላት አሰበች፡፡ ተራ መንደሮች አካባቢ መቆየት እንዳለበት ተሰማት፡፡ እዛ ከሔደች በቀላሉ የአንዱ ሰው ኑሮ ውስጥ ገብታ መሸሸግ ስትል አሰበች፡፡

ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ሲሆን አተኩሮ ላላያት ሰው ወንድ ሊያስመስላት የሚችል አለበባስ ለብሳ ኮፍያና መነፅር በማድረግ ከዝርዝር ብሮቹ መካከል ጥቂት መቶ ብሮችንና ሽጉጧን ብቻ ይዛ ከቤት ወጣች፡፡ በተኮናተረችው ታክሲ ፍላሚንጐ እየተባለ የሚጠራው አካባቢ ድረስ መጣችና አስቁማ ወረደች፡፡

በአጠቃላይ ከተማዋ ውስጥ ሰላም ያለው ድባብ መራቁን ብዙ ሁኔታዎች ይናገራሉ፡፡

ማታ ማታ እየተዝናኑ ሲያመሹ በየመንገዱ ላይ ይታዩ የነበሩ ሰዎች ቁጥር ቀንሷል፡፡ መኪናዎች በጊዜ ወደየ ማደሪያቸው ይከተታሉ፡፡ የፖሊሶችና የመንደር ሚሊሺያ ታጣቂዎች ቁጥር ጨምሯል:: ወታደራዊ እንቅስቃሴዎች በመዲናዋ አካል ውስጥ ይታያሉ፡፡

ሰናይት አስፓልቱን ተሻግራ በኢ.ሰ.ማ.ኮ. ህንፃ ስር ወደ ላይ በምትመልሰው ቀጭን አስፓልት መራመድ ጀመረች፡፡ ወደ ኤግዚቢሽን ማዕከል የጀርባ በር የሚታጠፈው ቦታ ስትደርስ ቀጥታውን የምትታየውን ቀጭን ኮረኮንቻማ መንገድ ይዛ ገባች፡፡

ይህን ሰፈር ከዚህ ቀደም በወሬ ታውቀዋለች፡፡ ሽርሙጥቾና ሰካራሞች ይበዙበታል፡፡ የሰፈሩ ስም ከምን በመነሳት እንደተሰየመ ባይገባትም "ዲሲ" በመባል ይታወቃል፡፡ በፖሊስ የሚታደኑት ማጅራት መቺዎች፣ ኪስ አውላቂና በህገወጥ ስራ ለሚታደኑ ወንጀለኞች መሸሸጊያ ዋሻነት በከፍተኛ ሁኔታ ያገለግል እንደነበር ጋዜጣ አሳታሚ ሆና በሰራችባቸው ወቅቶች ስለ ሰፈሩ ይደርሷት ከነበሩት

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

መረጃዎች ታውቃለች። አንድም ቀን ግን መጥታበት ሆነ የሚያስመጣት ሁኔታ ይፈጠራል ብላ አስባ አታውቅም ነበር።

መንደሩ ችምችም ያለና ጐስቋላ ነው ውስጥ ውስጡን ከጨርቆስ እና ወደ መስቀል ፍላወር ከሚወስዱት መንገዶች ጋር ይገናኛ ል። ሰናይት በቀስታ ወደ ውስጥ መግባቷን አላቆመችም። በሌላም በኩል ይህ መንደር ለመዲናዋ አባል የጐዳና አይነትን የመከራ ሕይውት ለሚገፉ ሰዎች ከስሙኒ አንስቶ ሃምሳ፤ ሳንቲም፤ አንድ ብር፤ ሁለት ብር በሚደርስ ክፍያ ከሰሌን ጀምሮ እስከ ሳር ፍራሽ መኝታን በሚያከራዩ የአካባቢው ነዋሪዎች መተዳደሪያና መኖሪያ በመሆን ያገለግላል።

የመቃብር ጉድጓድ ይመስል በአልጋ ስፋትና ቁመት ተለክተው በሳጥን ቅርፅ የተሰሩ ቤቶች በብዛት ሲኖሩ ከውስጣቸውም እንደየ ሴተኛ አዳሪዎቹ ምርጫ የሚበሩ አረንጓዴ ቢጫና ቀይ አምፖሎች የደበዘዘ ብርሃናቸውን ይረጫሉ።

ውስኖቹ የምሽቱን ቅዝቃዜ ለመቋቋም ፏ አድርገው ያቀጣጠሉትን ከሰል በሁለት እግሮቻቸው መካከል ከተው..... ይሞቃሉ።

የእንስቶቹን ብዛትና ዓይነት ከዚህ ቀደም በተመሳሳይ መልኩ ገጥሞት ያየ ማንም ሰው 'የአገሪቷ ሴቶች መጨረሻቸው ሽርሙጥና ይሆን እንዴ' እያለ ራሱን መጠየቁ አይቀርም ስትል አሰበች።

'የነዚህኑ ተመሳሳይ አካባቢዎች መርካቶ ሰባተኛ በሚባለው ሰፊ ግዛት፣ በአውቶቡስ ተራ ዙሪያ፣ በአራት ኪሎ፣ በፒያሳው ዶሮ ማነቂያ፣ በገዳም ሰፈር፣ በጣሊያን ሰፈር፣ በእቴጌ መስክ ቁልቁለት ላይ፣ በጨርቆስ፣ በቂራ በግ ተራ፣ በካዛንቺስ፤ ቺቺኒያ .....

'እነዚህ እንግዲህ በየ ቡና ቤቱ ውስጥ ካሉትና በደረጃም፣ በመልክም፣ በኑሮም፣ የመጨረሻው እርከን ላይ የደረሱ ሽርሙጦች ናቸው። ለነገሩ የጭፈራና የትልልቅ ቤቶቹ በቀጣይነት ወደ ቡና ቤት ከዛም የመጨረሻ እርከን ላይ እየዘቀጡ ሲወረዱ የሚቀበሏቸው እነዚህን የመሰሉ ስፍራዎች ናቸው' ስትል አሰበች።

የመንደሩ መካከል እዚህ አካባቢ ሊሆን ይችላል ብላ እየገመተች ወደ አንዲ ልጅ እግር መሳይ ሴተኛ አዳሪ ቤት ገባች።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ሴተኛ አዳሪዋ በደበዘዘው የቤቱ አምፖል ወደ ገባው ደንበኛዋ ለማየት እየሞከረች "ጊዜያዊ ነው አዳር?" ጠየቀችው ኩራት በሚመስል ቅላፄ በልቧ ግን 'ፈጣሪዬ እርዳኝ ጥሎኝ እንዳይሔድ' እያለች ፡፡ ገፅታዋ ጭንቀቷን ሙሉ በሆነ ሁኔታ አይግለፀው እንጂ ጥቁምታን ይሰጥ ነበር፡፡
"እ....አዳር....." አለቻት በተጠቀመችው አለባበስ ኮፍያና መነፅሯ ምክንያት ወንድ ትሁን ሴት እንዳልለየቻት ተረድታ፡፡
"አስራ አምስት ብር ትከፍላለህ?"
"እከፍልሻለሁ፡፡ በሩን ዝጊው፡፡" ቅላፄዋን የወንድ እያስመሰለች ተናገች፡፡
"መጀመሪያ ክፈላ"
"እሰጥሻለሁ ሰው እንዳያየኝ ዝጊዋ....."
"አልዘጋውም..... የልብህን ካደረከኝ በኋላ ገፍትረከኝ ልትሔድ....."
ሰናይት ወድያው እናቷን ያሰቃዩ የነበቱት ወንዶች ትዝ አሏት በሀሊናዋ 'ዛሬም ድረስ እንደሱ ይደረጋል ለካ' አለችና ከኪሷ ድፍን የሀምሳ ብር ኖት መዛ ሰጠቻት፡፡
"በል ጫማህን አውልቀህ ወደ ላይ ውጣ"
"መጀመሪያ በሩን ዝጊዋ!"
"ወደላይ ካልወጣህ በሩን አታዘጋውማ....."

የውስጡን ጥበት አስተዋለችና እስኪከር ጫማዋን አውልቃ እግሯን በማየት ሴት መሆኗን እንዳትለይ እየተጠነቀቀች አልጋው ላይ በመውጣት ጥጉን ይዛ ተቀመጠች፡፡ ከአልጋዋ የሚፈጠረው ሲጥሲጥታ የናቷን አልጋ አስታወሳት፡፡
በሩን ዘግታ ሽጐረችውና አጠገቡ በመቀመጥ ጫማዋን ማውለቅ ስትጀምር በዝምታ አስተዋለቻት፡፡እድሜዋ ከሃያ ሶስት አይበልጥም፡፡ ቀላ ያለው ፊቷ ረዘም ያለ ነው፡፡ የተመጠኑ ቆንጆ አይኖችና ከንፈር አሏት፡፡ አፍንጫዋ ግን ጠማማ ነው፡፡ በድብደባ የተሰበረ መሆኑን ገመተች፡፡ ቁመናዋም የተመጠነና የተስተካከለ ነው፡፡ በኑሮ ፈተና የታሸው የአካሏ ቆዳ ግን በብልዝ መበላሸት ጀምሯል፡፡
ከላይ የለበሰችውን ልብስ አወላልቃ በመጨረስ የጡቷን መያዣ መፍታት ስትጀምር "ቆይ.....ቆይ...." አለቻት፡፡ "ስምሽ ማን ይባላል?"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“መንበረ”

ከዚህ ውጪ ሌላ ምን ልትላት ወይም ልትጠይቃት እንደምትችል ማወቅ ተሳናት፡፡ ከሰዎች ጋር ሊኖራት የሚገባው ጤነኛው ተፈጥሮዋዊ ትስስር በአንድ የልጅነት ወቅቷ በመበላሸቱ ተቆጨች፡፡ ጥቂት በዝምታ ቆየችና ራሷን የተረጋጋና ትክክለኛ ሰው ለማስመሰል እየጣረች “ሳንነካካ መተኛት እንችላለን አይደል?”

“ማለት የፈለከው አልገባኝም፡፡”

“በቃ ልብሶችሽን ልበሺና ተኚ፡፡ እኔም እንደዚሁ እተኛለሁ፡፡”

“ምነው አስጠላሁህ?” በተሰበረ ስሜት ጠየቀችው፡፡

“አይደለም አይደለም..... በቃ የመጣሁት ዝም ብዬ ተኝቼ ማደር ስለፈለኩኝ ብቻ ነው፡፡”

ወጣቷ ንክ ቢጤ ይሆናል ስትል ገመተች፡፡ ቀጠለች ንግግሩን “.....ማለት ከፈለግሽ እኔ በግርጌሽ እተኛለሁ፡፡”

ምን አገባኝ በሚል ስሜት አየችውና የማንም ሰካራም እና ትፋታም መጫወቻ ሳትሆን ለማደር በመቻሏ ፈጣሪዋን እያመሰገነች ቢጃማዋን አጥልቃ እንደ ነገሩ እያበራ የነበረውን ቀይ አምፖል መብራት አጥፍታ ተኛች፡፡

ወጣቷ ወድያው ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ሲወስዳት ሰናይት ግን እንቅልፍ ስላልወሰዳት አስሬ ስትገላበጥ ያልበላት አካሏን ስታክ ስምንት ሰዓት ከሃያ ሞላ፡፡ ድንገት አካባቢው በአንዲት ሴት ጩኸት ተናወጠ፡፡

“ምንድነው!?” አለች ሰናይት በድንጋጤ

“እንግዲህ አንዱ በድቷት አልከፍል ብሎ ይሆናላ.....”

ጥቂት ቆይቶ ሌላ ጩኸት..... ንግግሮች አልፎ አልፎ ከርቀት ይሰማሉ “.....በይው በጠርሙስ..... ኮቱን አስቀሪበት..... ደግሞኮ ባለትዳር ነው ቀለበት አጥልቋል..... የትልቅ ሰው ቅሌታም.....”

ሰናይት በምትሰማቸው ቃላት እየተገረመች “ለመሆኑ ዛሬ ብቻ ነው ወይስ.....”

ከእንቅልፏ በቅጡ ሳትባንን “እንደውም ዛሬ ቀዝቀዝ ብሏል ሌላ ቀን የደቂቃ ፋታ የለም፡፡ በየቦታው በአንድ ጊዜ ሁለትና ሶስት ጩኸት ይሰማል”

“ለመሆኑ አንቺን ገጥሞሽ ያውቃል?”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“እኔ ከሌላዋ ሽርሙጣ በምን እለያለሁ!” መለሰችላት በምፀት
“ስትጮኹባቸው ግን ይከፍላሉ?”
“አዎና..... ቅሌታቸውን ሰው ተሰብስቦ እንዳያይባቸው ሲሉ ሂሳቧን ከፍለው ሮጠው ይጠፋሉ።።”
ስለሁኔታው ስታስብ ቆየችና “በአዲስ አበባ ነው ተወልደሽ ያደግሺው?”
“አይደለም”
“የት ነው ታዲያ?”
“ምን ይሰራልህል?”
“ለጫወታ ያህል እንጂ .....”
“ከናዝሬት ነው የመጣሁት።።”
“ቤተሰቦች አሉሽ?”
“የሉኝም እናቴም አባቴም ሞተዋል። አንድ ታናሽ ወንድም ነበረኝ በአሁኑ ወቅት ግን የት እንደሚገኝ አላውቅም። በረንዳ አዳሪም ሆኖ ይሆናል።”
“ለምን ሌላ ስራ ላይ አልተሰማራሽም ከዚህ.....?”
“በትምህርትም እስከዚህም ስላልገፋሁኝና ተያዥ ስለሌለኝ ማንም ሊቀጥረኝ አልቻለም።።”
“እስከስንት ተምረሻል?”
“አልተማርኩም ማለት ይቀላል..... እስከ አራት”
“የሚረዳሽ አጥተሽ ነው ያቋረጥሽው?”
“አዎ..... ቤተሰቦቼ እያሉም ቢሆን ድሆች ነበርን” አለች በሀዘን ስሜት ተውጣ።።

“በዚህ ስራ መተዳደር ከጀመርሽ ምን ያህል ጊዜ ሆኖሻል?”
‘ሶስት የመከራ ዓመታት’ ልትለው አሰበችና “ሶስት” አለች።።
‘ኤድስ ይዟት ይሆን?’ ስትል ሰናይት ሯሷን ጠየቀች።።
“የሚረዳሽ ብታገኚ ግን ይህንን ስራ ለመተው ትፈልጊያለሽ?”
“ምን ጥያቄ አለው.....በየምሽቱ የሚተኙኝ ወንዶች በጠቅላላ እናስተምርሻለን፣ ስራ እናሲዝሻለን፣ አንዳንዱማ አገባሻለሁ ሁሉ ይለኛል።። ግን ሁላቸውም ውሸታሞች ናቸው።። የሚፈልጉትን ሲፈፅሙብኝ ካደሩ በኋላ ይሄዳሉ በዛው ይቀራሉ።። እንደው በማዬ ሞት

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

አንተም እደዛ እንዳትለኝ:: ውሸት ሰልችቶኛል:: ቃል ገቡልኝም አልገቡልኝ፤ ዋሹኝም አልዋሹኝም ስጪኝ እንዳሉት አድርጌ ነው ለሊቱን ሙሉ እስክታመም ድረስ ገላዬን የምሰጣቸው:: " አለች በምሬት፡፡

ሰናይት በዝምታ ተዋጠች፡፡ ወድያውም ወንዶች ላይ ያላት ጥላቻ ተቀሰቀሰና በቀል አማራት:: የለሊቱን አብዛኛውን ሰዓት መንበረ በውጣ ውረድ ስለተሞላው ህይወቷ ስትነግራት በዝምታ እየሰማች በየመሀከሉም ከርቀት የሚሰሙ ጩኸትና ንትርኮች እየሰሙ ቆይቶ አስር ሰዓት አካባቢ ሁለቱም ተዳከሙ፡፡

መንበረ ድንገት "አንተ ግን መክፈልህ ካልቀረ ለምን ማድረግ አልፈለክም?"አለች::

"ጠዋት እነግርሻለሁ:: አሁን እንተኛ ቻዎ::" ብላት እንቅፍ እንደወሰደው ሰው ማንኮራፋት ጀመረች:: በህሊናዋም ጠዋት ሲነሱ ከበሏ ጋር ተጣልታ ከቤት የወጣች ሴት መሆኗን እና ዘመድም ሆነ መሔጃ ስለሌላት እሷ ጋር በመምጣት ያደረች መሆኑን ልትነግራት ወሰነች::

እንደዚህ ባለ አካባቢ ማደሩ ግን በተከራየችው ቤት ወይም ትልቅ ሆቴል ውስጥ ከማደር የተሻለ መረጋጋትን ፈጠረላት::





ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ምዕራፍ 36

በርሔ እይታውን ከኋላውና ከፊቱ እየመላለሰ አካባቢውን ቃኝቶ ካበቃ በኋላ ወደ አንዲት ጠባብ የአልኮል መጠጥ ቤት ፈጠን ብሎ ገባ።

ቤቷ ከተክለሃይማኖት ቤተ-ክርስቲያን ከፍ ብሎ በአደባባዩ ወደ ግራ በመዞር በርበሬ ተራ እየተባለ ወደሚጠራው አካባቢ በሚያደርሰው አስፓልት ላይ ሁለት መቶ ሜትር ገባ ብሎ በስተቀኝ በኩል ትገኛለች።

ከውጭም ሆነ ከውስጥ ምንም ዓይነት መስህብ የሌላት መናኛ ትመስላለች። መደርደሪያዎቿ በአመዛኙ በቪኖ የተሞላ ነው። አሮጌ አግዳሚ ወንበሮችና የተላላጡ የእንጨት ጠረጴዛዎች ዙሪያዋን ተቀምጠዋል።

በርሔ ወደ ባንኮኒው አለፈና "ጂን" አላት ውስጥ ላለችው ሴት አሳላፊ። አለባበሷ ሆነ የፀጉር አሰራሯ የትግሬ ባህልን የተከተለ በመሆኑ የብሔሩ ተወላጅ መሆኗን ይመሰክራል።

አንዴ ተጐነጨና ድምፁን ቀነሰ አድርጐ "አሉ?" ጠየቃት። በአይኖቿ አዎ አለችው። በባንኮኒው መግቢያ ዞሮ ገባና በስተግራ በኩል ከዕይታ ተከልላ ባለችው አንድ ሜትር በስልሳ ሳንቲም በምትሆነው መሹለኪያ አልፎ ወደ ውስጠኛው ክፍል ገባ።

በውስጡ የተነጠፈ አልጋ አሮጌ የልብስ ሳጥን ወንበርና ጥቃቅን የቤት ቁሳቁሶች ነበር ያሉባት። የልብስ ሳጥን መሳይዋ የተቆለፈችበትን ቁልፍ መክፈቻ የት እንደምትቀመጥ ያውቃል። ወደ አንደኛው የግድግዳው መዓዘን ተጠግቶ መክፈቻዋ ከተሻጠችበት

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

የግድግዳው ስንጥቅ ውስጥ አወጣትና ተንጠልጣዩን ቁልፍ ከፍቶ የሳጥኑን ክዳን ወደላይ አነሳው።።

ውስጡ የልብስ ማስቀመጫ እንዲመስል ያህል ጥቂት ልብሶች እና አንድ ትልቅ ብርድ ልብስ ተጣጥፎ ተቀምጦበት ነበር። በፍጥነት አወጣጣውና የሳጥኑ ወለል የሚመስለውን ጣውላ ጎትቶ ከፈተው። አንድን ሰው ዘና አድርጎ ወደታች የሚያስወርድ ረዥም መሰላል በደበዘዘ ብርሃን ይታያል።። የሚያነክስ እግሩን አስቀድሞ ገባና ቁልቁል በመውረድ የሳጥኑን ክዳን መልሶ ዘጋው።። በዚህ ጊዜ አሳላፊዋ ገባችና ያወጣቸውን ልብሶች ሁሉ መላልሳ እንደነበረው ቆለፈችበት።።

መሰላሉን ወርዶ ሲጨርስ ሌላ ጠንካራ የሆነ ዝግ የብረት በር ጋር ደረሰ።። በሩን ማንኳኳት የአደጋ መጥቷል ምልክታቸው ስለሆነ ሳይነካው አለፍ አለና የኮርኒሱና የግድግዳው መገናኛ ስር የተቀመጠችውና በቀላሉ የማትታይ መቆጣጠሪያ ላይ ጣቱን አሳርፎ ተጫናት።። በዚህ ጊዜ ውስጥ ያሉት ሰዎች ጋር ለዕይታ አመቺ ስፍራ ላይ የተገጠመችው ትንሽዬ ቀይ አምፖል በራችና ጠፋች።።

የራሳቸው ሰው የሚሰጠው ምልክት በመሆኑ ውስጥ ካሉት መካከል አንደኛው ተነስቶ ከፈተለት።።

በዚህኛው ክፍል ግን በደንብ የሚፈነጥቅ መብራት በርቷል።። ወለሉ ውብ ምንጣፍ ለብሷል።። አራት ወንዶችና አንዲት ሴት ሶፋ ላይ ተቀምጠው ውስኪያቸውን እየጠጡ ያወጉ ነበር።።

በክፍሉ አንድ ጥግ ላይ የኢንተርኔት መስመር የተገጠሙላት አንድ ኮምፒውተርና የፋክስ ማሽን ተቀምጠዋል።።

በርሔ መሆኑን እንዳዩ ከተቀመጡበት ተነስተው ሰላምታ ሰጡት።።

“ቀጠሮ እንዳልበደልኩ እርግጠኛ ነኝ” አለ በትግሪኛ

“አዎ.....” መለሰለት አንደኛው።።

ሁለቱ ወንዶች በእድሜ የሚመጣጠኑ ይመስላሉ።። ቢበዛ ከሃምሳ አይልቁም።። አካላዊ ግዝፈትና ቁመናቸው በተደላደለ ህይወት ውስጥ እንዳሉ ይመሰክራል።።

ሁለቱም ደግሞ ሙሉ ኤርትራዊ ዝርያ ያላቸው ቀንደኛ የ“ሻዕቢያ” የሚስጥርና የስለላ ሰዎች ሲሆኑ በህገወጥ መንገድ በሱዳን

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

ድንበር በማቋረጥ ወደ ትግራይ ከገቡ በኋላ እዛ ባሉ ሰዎቻቸው አማካኝነት የኢትዮጵያዊነት ማስረጃዎችን በማሰራት እስከ አዲስ አበባ ዘልቀው እንደማንኛውም የትግራይ ብሔረሰብ ተወላጅ በነፃነት በንግድ እንቅስቃሴ ከለላነት የሚሰሩ ጠቃሚ ሰዎች ነበሩ።።
“ጉዳይህ ከምን ላይ ደረሰ?” ጠየቀው አንደኛው ሰው።።
“እያለቀ ሂዷል።። የጦር መሳሪያዎቹ በሁለት ሳምንት ውስጥ ይደርሳሉ ተብሏል” በርሔ መለሰና የተቀዳለትን ዊስኪ ለመጐንጨት አነሳው።።
“የትኛው ወደባችን ለስራህ እንደሚያመችህ ወሰንክ?”
“በትግራይ ሰሜን ምስራቃዊ አቅጣጫ አመቺ ክፍተት እንዳለ እዛ ያሉት ሰዎቼ ገልፀውልኛል።።”
“ስለዚህ ምፅዋ ትሻላለቻ?” ሁለተኛው ሰው ነበር።።
“አዎ.....”
“ይህንን የኤርትራ መንግስት ሙሉ በሙሉ ሊተባበራችሁ እንደሚፈልግል ድጋሜ ፈቃደኛ መሆኑን አሳውቋል” አንደኛው ሰው በኩራት መንፈስ።።
“እናመሰግናለና.....”
“ያለፈ ጊዜ መላው ትግራይን የሚያካልል ጥቃት ለማካሔድ አንድ እቅድ እየነደፍን ነው።። ብለኸን ነበር።።”
የሁለተኛው ሰው ጥያቄ ሲሆን
“አዎ.....”
“መቼ እንዲካሔድ ወሰናችሁ?”
“ከአስራ ስድስት ቀን በኋላ”
ሰውዬው እለቱን ሲያሰላ ቆየና ቀጠለ “ግንቦት 20 ማለት ነው?”
“አዎ.....” በርሔ እያያቸው ቀጠለ “በዕለቱ ስልጣን የጨበጡበትን ቀን የሚያከብሩበት ስለሆነ ከጭፈራ ውጪ የሚያታያቸው ነገር አይኖርም።። ስለዚህ ልል የቁጥጥር ሁኔታ ስለሚኖር ጥሩ ውጤት ያስገኝልናል።።”

“ጥቃቱ ምን ላይ ያነጣጠረ ነው?”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

“የህ.ወ.ሓ.ት. አባል የሆኑ ባለስልጣናትን በጠቅላላ ከክልሉ መሪዎች አንስቶ እስከ ቀበሌ ሊቀመንበሮች ድረስ ያሉትን ለማስረሽን የታቀደ ነው።።”
“ብቃት ያለው የሰው ኃይል አላችሁ?” አንደኛው ሰው ጠየቀ።።
በርሔ በዚህ ጊዜ በዝምታ ተውጠ ቆየና “አዎ ግን አብዛኛዎቹ የሰለጠኑ አይደሉም።። ገድለው ለመሞት የተዘጋጁ ናቸው።።”
ሁለቱ የ “ሻዕቢያ” ሰዎች ተያዩና አንደኛው “ስልጠና እንዳንሰጥላችሁ የቀሩት ቀናቶች ጥቂት ናቸው።።” አለ።።
“ያለፈ ጊዜ ጠይቄያችሁ የነበረው የሰው ሀይል እርዳታ ጥያቄዬ ምን ውሳኔ ሰጣችሁበት?”
ሁለቱ ሰዎች ድጋሜ ተያዩና አንደኛው ሰው “የወታደር እርዳታን በተመለከተ ተክለእግዚ ጥቂት ይሰጣቸው ተብሎ በመሪያችን እንደተወሰነ ነግሮኝ ነበር..... እስኪ ስንት እንደታዘዘ ድጋሜ ልጠይቀው.....”

ተነስቶ በክፍሉ በስተቀኝ በኩል ወደ ቆመ አንድ ረዥም ማቀዝቀዣ ፍሪጅ አመራ።። በሩን ከፈተው።። ውስጡ እንደማንኛውም ዓይነት ፍሪጅ ሲሆን የለስላሳና የአምቦ ውሃ መጠጦች እንዲሁም የተቆራረጡ ስጋዎች ተቀምጠውበታል።።
ትንሽዬ ቁልፍ ከኪሱ አወጡና በበሩ የታችኛው አካል ላይ ቀዳዳ ፈልጎ ከተታትና ሲያዞራት አንዱ በር እንደገና ሁለት ቦታ ተከፈተ።።
በውስጡ ለረዥም ርቀት የሚያገለግል የመገናኛ ራዲዮ የተገጠመለትና ማቀዝቀዣ መስሎ ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ የተደረገ ማሽን ነበር።።
በላይ በኩል የሞገዱን አካሄድ የሚያሳይ የቴሌቪዥን መስኮት የመሰለ መስታወት አለው።።
መከፋፈቻ ቁልፎቹን ሲጫናቸው ቆየና ማዳመጫውን ጆሮው ላይ አድርጎ መነጋገሪያው ወደ አፉ በማስጠጋት
“ዳህላክ 56.....ዳህላክ56”
“ቀጥል” የሚል መልስ መጣለት።።
“የዚህ ወር አስረኛ አጀንዳ ላይ ነኝ” የመለያ ኮዱ ነበረች።።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

“እሺ ቀጥል.....”
“የሰው ሀይል ጥያቄው ምን ምላሽ ተሰጠው ነው ያልከኝ?”
ይኼኔ በማሽኑ ላይ ካሉት መብራቶች መካከል ቀዩ ብልጭ ድርግም በማለት ምልክት ማሳየት ጀመረ።።
መስመሩን ለመጥለፍ የሚጥር የጠላት ራዲዮ መስመር መከፈቱን ጠቋሚ ነበር።።
ሰውዬው መልስ ከመምጣቱ በፊት ፈጠን አለና “አስር ሰከንድ ጠብቅ!” ብሎ ሌሎች ቁልፎችን መከፋፈት ጀመረ።። የሞገዱን አቅጣጫ በሌላ መስመር ላይ ካስገባው በኋላ የበፊቱ መስመር ውስጥ ሀሰት የሆነ አደናጋሪ መረጃ የተቀዳበትን የሚቆጣጠረውን ቁልፍ ከፈተው።።
ቀዩ መብራት ጠፋ።።
“ዳህላክ 56.....”
“ቀጥል”
“የሰው ሀይል ጥያቄው.....”
አቋረጠውና “አይሰማም”
“ምዕራብ አቅጣጫ 0.431 የሚለው መስመር ውስጥ ግን.....” ደጋግሞ በመንገር ተስተካከለና ጥያቄውን አቀረበለት።።
“ጠብቅ አንዴ.....” የሚል መልስ መጣለትና ከግማሽ ደቂቃ በኋላ “500 ቀይሕ እንባባ ተፈቅዶላቸዋል።።”
“አመሰግናለሁ።።”
ማዳመጫና መናገሪያውን ቦታው መልሶ ቁልፎቹን በማጠፋፋት ማቀዝቀዣውን እንደነበረ ቆላልፎ በመመለስ እየተቀመጠ “ቀይሕ እንባባ ከተባሉት የኛ ምርጥና ታማኝ ወታደሮች መሀከል 500 ያህሉ እንዲያግዟችሁ ተፈቅዶላችኋል።።”

“ቀይሕ እንባባ..... ከዚህ በፊት በስም አውቃቸዋለሁ.....” ብሎ በርሔ ጥቂት ሲያስብ ቆየና “.....ከሻዕቢያ ሌላው ወታደር ልዩ የሚያደርጋቸው ምንድን ነበር?” አለ ከአመታት በፊት የሰማውን ማንነታቸውን ለማስታወስ እየጣረ
አንደኛው ሰው ውስኪ ተጐነጨና “ቀይሕ እምባባ የሚባለው ወታደራችን 1969 ዓ.ም. በተቋቋመ ልዩ ማሰልጠኛ ውስጥ እንዲደራጁ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

የተደረጉ ናቸው፡፡ ውጪ ተወልደው ወደ ማሰልጠኛው እንዲገቡ የተደረጉት ምልምሎች እድሜያቸው አስር ዓመትና ከዛ በታች የነበሩ ናቸው፡፡.....

“.....እንዲሁም በትግል ላይ ሁለት እጅ ወይም ሁለት እግር ተቆርጠው በየካምፑ ውስጥ የነበሩ የሻዕቢያ ሰራዊቶች ከሴት ታጋዮች እንዲወልዱ በማስደረግ ህፃናቶቹ በዛ ካምኘ ውስጥ ገብተው እናትና አባታቸውን ጨምሮ ከማንም የውጪ ሰው ጋር እንዳይገናኙ ተደርገው ነው ያደጉት.....

“.....ግማሾቹም ከተለያዩ የኤርትራ ግዛቶች በህፃንነት እየታፈኑ እንዲመጡ ስለተደረጉ የማን ልጅ እንደሆኑ እንኳ አያውቁትም፡፡ በነበሩበት ካምኘ ውስጥ ከልጅነት ጀምሮ በጦር መሳሪያዎች እየተጫወቱ አድገዋል፡፡ ከስር ጀምሮ ስለ ወታደራዊ ግዳጅ እንዲያውቁና እንዲማሩ ስለተደረገ ችሎታቸው የላቀ ነው፡፡ በተጨማሪም ዕለት ዕለት ስለ ኤርትራዊነት እና የዝርያ የበላይነት፤ በተያያዥ መልኩም ስለ አማራው ብሔር ጠላትነትና አውሬነት ከሚተነፍሱት አየር ጋር እየማጉት እንዲያድጉ ስለተደረገ ኤርትራዊነት ማለት ለነሱ የዓለም ቁጥር አንድና ምርጥ ዘር ማለት ነው፡፡ አማራነት ደግሞ በተለይ ኤርትራን ለማጥፋት የተፈጠረ አውሬ ነው ለነሱ፡፡ ስለዚህም አማራ ሲባል ይንገሸገሻሉ ቀጥሎም ለቀሪው የኢትዮጵያ ግዛቶች ስር የሰደደ ጥላቻ እየታጨቀባቸው እንዲያድጉ ስለተደረገ ይህን አገር ለማጥፋት የሚያደርጉት እሽቅድድም በጣም ይገርምሀል.....” አለ አንደኛው ሰው በኩራት፡፡ ቀጠለ “.....ዛሬ ግማሾቹ ጐርምሰዋል፡፡ አሁን ድረስ ከሰው ጋር ተቀላቅለው መኖር የማይችሉ ድንጉጥ የጫካ እንስሶች ናቸው፡፡እናትና አባታቻችሁ ማነው ስትላቸው በብዙኛ መልሳቸው “ሻዕቢያ” ይሉሀል፡፡ ታዲያ እንዴት ያሉ ታማኝ ተፋላሚዎች መሰሉህ.... አንተ ከማንም ይልቅ ለእናትህ ሙት ብትባል እንደምትሞተው ሁሉ እነሱም ለሻዕቢያ ፍፁም ማፈግፈግ የሌለበት ፍልሚያን ያደርጋሉ፡፡.....”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

በርሔ በአድናቆት ሲያዳምጥ ቆየና "እኔም ወደፊት ከትግራይ ነፃነት በኋላ እነሱን የመሰለ ሰራዊት አቋቁማለሁ፡፡" አለ፡፡ ቀጠለ "..... ይህን ሁሉ ለፈቀዱልኝ ባለስልጣናት ሁሉ እና ለመሪያችሁ በጭቁኑ የትግራይ ህዝብና በፓርቲዬ ስም ወደር የሌለው ምስጋናዬን አቅርቡልኝ"
"ምንም አይደል..... ይህን ሁሉ የምናደርገው ላንተ ብለን ብቻ እንዳይመስልህ፡፡ ኤርትራ ለሃምሳ ዓመታት በባርነትና በጦርነት ስትደማ እንደኖረች ሁሉ መላዋ ኢትዮጵያም ያ እጣ እንዲደርሳት እና መበታተን መገነጣጠል አለባት ብለን ስለምናምን ነው፡፡ እናም ገና ብዙ እርዳታ እናደርግልሀለን፡፡" አለው አንደኛው ሰው ፍፁም በሆነ የጥላቻ ስሜት፡፡
"ጥሩ.....እ.....ወደእናንተ አገር የምገባበትን የድንበር መሻገሪያ ደብዳቤዬን አስጨርሳችሁ አስመጣችሁልኝ?"
"አዎ....." አለና ሁለተኛው ሰው ከኪሱ ውስጥ የተጣጠፈ ደብዳቤ አውጥቶ ሰጠው፡፡
በአንድ የአገሪቱ ከፍተኛ ባለስልጣን ስምና ፊርማ የተዘጋጀ ሁሉንም ነገር ለማስፈፀም የሚችልበት ሀይል የሚያሰጠው ደብዳቤ ነበር፡፡
ሁለተኛው ሰው በርሔ ደብዳቤውን አንብቦ እስኪጨርስ ጠበቀና "በትክክል የምትመጣበትን ዕለት ከገለፅክልን ድንበር ላይ አጃቢና መኪና ተዘጋጅቶ እንዲጠብቅህ ልናስደርግ እንችላለን፡፡"
"አሁን እርግጠኛ አይደለሁም፡፡ የጦር መሳሪያውን መረከቢያ ደብዳቤ በሁለትና ሶስት ቀናት ውስጥ እጄ እንደገባ ነው ላሳውቃችሁ የምችለው፡፡" ቀጠለ በርሔ ".....አዲስ አበባ የምትቆዩ ከሆነ ደውዬ አሳውቃችኋለው፡፡"
"አዎ እንቆያለን ገና ከኢትዮጵያን ተገንጥለው ለመውጣት እና ለነፃነታቸው የሚታገሉ ብዙ ፓርቲዎችን ለመመስረት እና ለማደራጀት ሰፊ እቅድ ይዘን ነው አሁን የተመለስነው፡፡" አለ ሁለተኛው ሰው፡፡
"እዚህ ውጤት ላይ ከደረስኩኝ እኔም ለወያኔ መንግስትም ያበቃለት መሆኑን የሚገልፅ ደብዳቤ እፅፍለታለሁ፡፡" አለ በርሔ ሁለቱ ሰዎች ሀሳቡን ባይደግፉትም ተቃውሞም አልነበራቸውም በራሱ የውስጥ ጉዳይ ለሚያካሔዳቸው ተግባሮች ብዙም ደንታ ስላልነበራቸው፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

እንዲሁ ብቻ አንደኛው ሰው "እንዴት ነው ለነሱ እንዲደርስ የምታስደርገው?" ግድ በሌለው ስሜት ጠየቀ፡፡
"እፅፍና አሜሪካ ላሉት ሰዎቼ እልከዋለሁ....." ብሎ ንግግሩን አቋረጠ፡፡ በህሊናውም ወደ ትግል ሲገባ አብረው ከገቡት አባሎች መካከል አንዱና የቅርብ ጓደኛው ከጥቂት ሳምንታት በፊት ባልታወቀ ሰው የመኖሪያ ቤቱ ውስጥ ተገድሎ መገኘቱ በሌሎች አባሎች ሲገለፅለት ከተፈጠረበት ድንጋጤና ቁጭት ያልተናነሰ ስሜት አሁንም አካሉን ወረረውና ለበለጠ ጥላቻና በቀል እያነሳሳው ተወራጨ፡፡
ጥቂት ተረጋግቶም ንግግሩን ቀጠለ "በአሜሪካ ያሉት ሰዎቼ ደግሞ መልሰው ለኢትዮጵያ ኤምባሲ ይልኩታል፡፡"

ከምሽቱ አራት ሰዓት እስኪሆን ድረስ በተለያዩ ርዕሶች ላይ ሲያወጉ ቆዩና ሶስቱ ሰዎች ለመሔድ ሲነሱ በርሔም ተነሳ፡፡ አንደኛው ሰው ግን አብራቸው የቆየችውንና ጐልመስ ያለ እድሜ ያላትን ሴት እያቀፈ ተሰናበታቸው፡፡

የወጡት በገቡበት በር አልነበረም፡፡ በቤቱ ውስጥ ለውስጥ አልፈው አጠገብ ወዳለ የሌላ ቡና ቤት ምድር ቤት ስር ደረሱ፡፡

ቦታው ከቡና ቤቱ የእቃ ማስቀመጫ መጋዘን ክፍል ጋር የሚያገናኝ በር አለው፡፡ አንደኛው ሰው ከኪሱ ቁልፍ አወጣና ከፍተው ገቡ፡፡

ውስጡ በመጠጥ ጠርሙሶች፤ በተሰባበሩ ወንበር ጠረጴዛና ሳጥኖች ተሞልቷል፡፡ ከየጨለማው ስርቻ ውስጥ አይጦች ሲራወጡ ይሰማል፡፡ አልፈው በደረጃው ወደ ላይ ወጡና ሌላ በር ከፍተው ወጡ፡፡በሚታየው ቀጭን መታጠፊያ እየተጠማዘዙ ብቅ ሲሉ ከግራና ቀኝ በኩለ የአልቤርጐ ክፍሎች ያሉበት አካባቢ ደረሱ፡፡

እየተጓዙ ወደ ዋናው ቡና ቤት የሚያስገባውን የውስጥ በር ከፍተው ገቡ፡፡ ከትንንሽዬዎቹ ደብዛዛ አምፖሎች የሚፈነጠቀው ብርሃን ሰዎችን በቅጡ እንዳይተያዩ የሚያግድ ነበር፡፡

አንደኛው ሰውዬ በርሔን ውጪ ድረስ ሸኝውና የግሉ ወደሆነውና ከዓመት በፊት ወደገዛው ቡና ቤቱ ሁለቱን ሰዎች ይዞ ተመለሰ፡፡

«««««««««« »»»»»»»»»

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

በዚሁ ዕለትና ሰዓት በአዲስ አበባ ጐተራ አካባቢ ባለ አንድ የግል መጠጥ ቤት ውስጥ አራት ሰዎች "ህዝበ ደቡብ ነፃነት ሀይል" ስለተሰኘው ፓርቲያቸው ቀጣይ ስራ እያወጉ ለረዥም ሰዓት ቆይተው ውይይታቸውን ወደ ማጠናቀቁ ሲቃረቡ "በትላንትናው ዕለት ስለተሰዋው ጳውሎስ ኩንቴ የሀዘን ፅዋችንን እናንሳ" አለ አንደኛው።።
በፌደራል ፖሊስ ስር የተወርዋሪ ክፍሉ ዋና ሀላፊ የሆነው ሻለቃ ደርበው በሀዘን ቅላፄ "እንደሚሞት ታውቆት ነበር" አለ።።
"እንዴት?"
"ከጥቂት ቀናት በፊት በፍርሀት ተውጦ ሰናይት ስለተባለችውና ስለምትረዳን ሴትዮ ገልፆልኝ ነበር።።"
"ምን ብሎ?"
"የመንግስት ቅጥረኛ እየመሰለችኝ መጥታለች ብሎኝ ነበር"
አንደኛው ሰው ተጨባጭ መረጃ በሌለው አባባሉ ሳይሳብ
"ለማንኛውም እሱ አንዴ አልፏል..... በሌላ በኩል ይህ ወቅት ለኛ ትልቅ ደስታን ሰጥቶናል።። በኛ ፓርቲ ውስጥ የሚያገለግሉ ሁለት ሰዎቻችን በዲኤታ ሚኒስትርነት ማዕረግ የመንግስት ከፍተኛ ባለስልጣን ሆነው ተሹመውልናል።። ይህ ቀላል አይደለም።። ነገ ከገነ ወዲያ በሚሰጡን መረጃ የደቡብ ክልላችንን የማስገንጠሉን ዓላማ እንዲፋጠን ያስችሉልናል።።" አለ ብርጭቆውን አንስቶ በስሜት እየጨለጠ።።

  

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ምዕራፍ 37

ከጃማይካ ግዛት ኪንግስተን በተባለችው ከተማ የተወለደው ቦብማርሊ "አፍሪካን ዩናይትድ" እያለ የተጫወተውና ታላቅ ራዕይ ያለው ዜማውን አብነት በዝግተኛ ድምፅ ከፍቶታል።

እይታውን ስለ ኢትዮጵያ አንድነት ሊገልፅበት አስቦ የጀመረው ስዕሉ ላይ ተክሏል። አንድነትም ከፍቅር ይመነጫልና የፍቅርን ተምሳሌታዊ መገለጫ በምን ዓይነት መስመርና ቀለም ውስጥ መግለፅ እንደሚችል ሲያስብ ቆየና በአራት ማዕዘን ውስጥ ማስፈር ፈለገ። አራት ማዕዘን ደግሞ ብዙ ጊዜ ፍርድ ቤቶች፣ ወህኒ ቤቶች፣ የሬሳ ሳጥን፣ የመቃብር ጉድጓዶች፣ የህግ መወሰኛ ምክር ቤቶች..... ምርጫው ጭፍን የሆነ ስሜትን ፈጠረበት "የአደጋና የፈተና መገለጫ" አለ።

ሶስት ማዕዘን ቅርፅ ውስጥ እንዴት ማሳረፍ እንደሚችል ማሰብ ቀጠለ። ወድያውም የግብፅ መቃብር ፒራሚዶች እና ጥንታዊ የመሰየፊያ ስፍራዎች አሰራር በህሊናው ታዩት። "ሞት ጠሪ ቅርፅ" አለ በለሆሳስ።

ክብ ቅርፅን አሰበ። የቤተ-ክርስቲያናት የመስኒዶች ጉልላት፣ ሁሉን ቻይ የሆነችው ቸር ምድር፣ እናት ፀሀይ፣ የፍቅር ማሰሪያ ቀለበት..... "ክብ ከማይታየው የባዶነት መገለጫነት ይልቅ የሚታይ በርካታ በጐ ገፅታዎች አሉት" አለና በምን አስታኮ መግለፅ እንዳለበት ብዙም ሳይጨነቅ በቀስተ ደመና ሀምሳያ በህብር ቀለማት ውብ አድርጐ መሳል ጀመረ።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ከዛም "ይህ የዋናው ጭብጥ ማረፊያ አቃፊ መደብ ይሆናል" የቦብ ማርሊ ከነፍስ ጋር ጥምረት መፍጠር የሚችል ጥልቅ ዜማ በዝቅተኛ ድምፅ መዝፈኑን ቀጥሏል።

አብነት የመሳያ ብሩሹን አስቀመጠና በወፍራሙ እንደ ሲጃራ የተጠቀለለውን የካናቢስ ዕፅ አንስቶ ለኮሰና በረዥሙ መማግ ጀመረ። አይኖቹ ጢሱን እየተከተሉ ወደ ላይ ወጡ። ይህም ዕፅ እሱ በአጭር ቃል "ጋንጃ" እያለ ይጠራዋል። ሆኖም ግን ቃሉ ከውጭ የተወሰደ ቋንቋ በመሆኑ ወደ ራሱ ቋንቋ ሲመለስ በሚሰጠው ውብ ስሜት "እፀ-ጥበብ" ብሎ ቢገለፀው ይመርጣል።

ወደ ኋላ ሰብስቦ አስሮት የነበረውን ድሬድ ፀጉሩን ፈታና ግራና ቀኝ ጭንቅላቱን እያወዛወዘ በታተነው። መታሰሩ አስጨንቆት እንደነበረ ያወቀው እያዳንዱ የፀጉሩ ግምደት ባሻቸው አቅጣጫ ተፈታተው ሲንጠለጠሉ ነበር።

አጢሶ እንደጨረሰ ለደቂቃ በዝምታ ካለበት ሳይንቀሳቀስ ተቀመጠ። ህሊናው ድንገት ስለ መስፍን ማሰብ ጀመረ። መስፍንን ከልብ የሚወደው ጓደኛው ነበር። መገደሉን ከሰማ ዛሬ ሶስተኛ ቀኑን ይዟል። የፈጠረበትን የመንፈስ ስብራት መቋቋም እስኪያቅተው ድረስ በሀዘን ሰምጦ ነው የሰነበተው።

የክፍሉ በር በቀስታ ተንኳኳ።

"ማነው?"

"እኔ ነኝ አቢ....." ቀጭንና ዝቅተኛ የሆነ የሴት ድምፅ ነበር። ቀጠለች "ስራ ላይ ነህ.....? ረበሽኩህ.....?"

መልስ ሳይሰጣት ተነስቶ ከፈተላት። ቤቲ ነበረች። ወደ ውስጥ ስትገባ "በሩን ዝጊው ብርሃን የሚባል ነገር ማየት አልፈልግም" አላት

ሁለት ሻማዎች ሊስልበት ከወጠረው ሽራ ግራና ቀኝ በኩል እንደሚበሩ አየችና ዘጋችው።

በሻማው ብርሃን ፊቱን ስታየው ደነገጠችና "ይህን ሶስት ቀን ምን ሆነህል?"

"እኔንጃ ምን ሆኛለሁ?" መልሶ ጠየቃት አልጋው ላይ እንድትቀመጥ በእጁ እየጠቆማት።

"ያመመህ ትመስላለህ..... ደሞም ከሳ ብለሀል....." ይህን ብቻ ገለፀችለት እንጂ የለበሰው ልብስ ላይ ከእጁና የመሳያ ብሩሾቹ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ማፅጃነት ሲጠራርግ የሰነበተው ቀለም አሻጐርጕሮ እብድ አስመስሎት እንደነበረ እያየችው፡፡ አይኖቹም ደፍርሰው ጐድጉደዋል፡፡ ከንፈሩ ደርቆ እንደ መሰነጣጠቅ ብሏል፡፡ የቤቱ ውስጣዊ ድባብም ለሷ እይታ አዋኪ መንፈስን ፈጠረባት፡፡
አብነት ሲያያት ቆየና "ያመመህ ትመስላለህ ነው ያልሺኝ....." በምፀት ቀጠለ ".....ለኔ እንደሚገባኝ በአፍሪካ ውስጥ እያለ ጤነኛ ነኝ ብሎ የሚያስብ እሱ በትክክል ህሊናው ተዛብቷል፡፡ የታመመ መሆኑን የሚያውቅ ግን ጤነኛ ነው፡፡"
"ምን..... ያጋጠመህ ችግር አለ?"
"አዎ! የነፃነት እጦት! የሰላም እጦት! የፍቅር እጦት!" መዳፉን እየጨመቀ በጠንካራ ቃላት መለሰላት፡፡
ጥምጥም ብላበት ያጣውን ፍቅር ልትሰጠው ተመኘች፡፡ የሱ ህሊና የሚፈልገው ፍቅር ግን ያታዊ አልነበረም፡፡
ቀጠለ "የበቀደሙን ልጅ ታስታውሺዋለሽ?"
"ያ በፖሊሶች እናቱ ተያዙበት ያልከኝ ጓደኛህ?"
"አዎ.....ተሳካላቸው ገደሉት፡፡"
"ገደሉት!?"
"አዎ..... በጥይት ጠበሱት!" አላት ውስጡ በሀዘን እያረረ ".....ዝም ብለሽ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን ሁኔታ ስታስተውይ በገዛ አገርሽ ላይ የባዳነትና የባይተዋርነት ስሜት ነው የሚሰማሽ፡፡ ወይ አንደኛውኑ በቁርጡ ስደት ይሻል ይሆን?..... አዎ ተሰደሽ ይችን አገር ለቀሽ ብትወጪ በስደት ህይወትና በሰው አገር ውስጥ እዚህ ያጣሽውን በራስ የመተማመን መንፈስ ፍቅርና ሰላምን በቀላሉ ልታገኚው የምትችይ መስሎ ነው የሚሰማሽ..... ሰው እንዴት በገዛ አገሩ የዜግነት ቢቀር እንኳ የሰውነትና የሰብአዊነት ዋስትናውን ይገፈፋል?" አለ በቀጭኑ የወረደች እንባውን እየጠረገ፡፡
"ምን ለመጠቀም ብለው ምንንስ ለማግኘት ብለው ገደሉት?"
"ፍላጐታቸውማ የስልጣን ዘመናቸውን ለማስረዘም..... የተሸከመቻቸውን ታንኳ በሰው ደም ላይ ካልሆነ በስተቀር ሰላም ባለበት ሰማይና ሰላም ባለበት አገር መቅዘፍ የምትችል አይመስላቸውም..... የሚበሉት እንጀራ በሰው ደም ተቦክቶ ካልተጋገረ የሚጠግቡ አይመስላቸውም..... ስልጣን ላይ መሆናቸውን ለማረጋገጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ሲሉ ብቻ የሰው ደም በየአደባባዩ ሲፈስ ካላዩ አመኔታ የላቸው.....ህሊናቸው፣ እጆቻቸው፣ አፎቻቸው በጠቅላላ በንፁሀን ደም ተበክሏል.....” አላት፡፡
“ምን ይሆን ግን የሰው የፍላጐቱ ገደብ.....ስልጣን ሲይዙ ገንዘብ..... ገንዘብ ሲይዙ ምንዝር..... ትርጉም ሲያጡበት ስየፋ.....” አለች ሰናይት፡፡

አብነት ሳቅ አለና “ሞኝት.....ለሰው የፍላጐቱ መጨረሻ ማለት ዘላለሙን ሲፈልግ መኖሩ ነው፡፡ ለሁሉ ነገር እና ፍላጎት ገደብ ራስሽ ካልሰጠሽው የሰው ልጅ ተፈጥሮ እንደ አውሬ ነው፡፡ የባለስልጣኖቻችንም ችግር ገደብ የለሽ በቃኝን የማያውቁ ግብስብሶች መሆናቸው ነው፡፡” ብሎ እይታውን ከስዕሉ ሽራ ወደሷ ሲመልስ የሷም ጉንጮች በእምባ ርሰው ነበር፡፡
“ጓደኛህ አንዴ ሞቷል፡፡ አንተ ምንም ማድረግ ስለማትችል አርፈህ ቁጭ በል እሺ፡፡” አለችው በጥልቅ የፍቅር ስሜት እያየችው፡፡
“አልተወውም ! እኔም እስከመጨረሻው ድረስ እገፋበታለሁ፡፡”
“አንተንም ይገድሉሀል እኮ.....” እምባዋ እንደ አዲስ መውረድ ጀመረ፡፡
አብነት ገፅታዋን ሳይሆን ህሊናዋን ለማንበብ እየጣረ “በህይወትም አልደሰትም፡፡ በመሞትም አልከፋም፡፡ ሁለቱም ለኔ ትርጉም የለሾች ናቸው፡፡ ልዩነታቸው የይዘት ሳይሆን የቅርፅ ነው፡፡ ማለትም በህይወት ውስጥ በሚጨበጥ አካል ትኖሪያለሽ ወይም በሞት ውስጥ በማይጨበጥ አካል ትኖሪያለሽ፡፡ ሁለቱም ጋር ግን ያው ትርጉም የለሹ የመኖር ሂደት ይቀጥላል፡፡”
“እቢ.....በቃ ወሰንክ ማለት ነው? ይገሉሀል እኮ.....”
“ሞቻለሁ፡፡ ቆሜ መሄዴን አትይ! ይህ ስርዓት እና አገዛዝ እኔን እና የኔን ዘመን ትውልድ በጠቅላላ በቁም ገሎናል፡፡ ሞቻለሁ! አንዴ የሞተ ሞትን ድጋሚ አይፈራም፡፡ የመስፍን ትግል የግሉ አላማ አልነበረም፡፡ ይችን ብኩን አገር እየመጣ ካለው አስከፊ ጥፋት መታደግ ነበር፡፡ እኔም ያንን ትግል እቀጥላለሁ፡፡ ለዚህች አገር ህይወቴን እከፍላለሁ፡፡ ” አላት፡፡
ስታስብ ቆየችና “እኔም የሆንከውን ሁሉ እሆናለሁ”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

ሊከለክላት አልፈለገም፡፡ ይልቅም ፍላጐቷ ከልብ የመነጨ እውነተኛ ስሜት መሆኑን ጠየቃት፡፡ አረጋገጠችለት፡፡ አመናት፡፡
“ከየት አቅጣጫ ስራውን እንጀምር?” ጠየቀችው፡፡
“መነሻዎቻችን በጠቅላላ የስልክ ቁጥሮች ብቻ ናቸው፡፡” ብሎ በአስር ብር ኖት ላይ ፅፎ የተወለትን ማስታወሻ አውጥቶ አሳያት፡፡
“የዛችን የመሳሪያውን መረከቢያ ታመጣለች ያልካት ሴትዮ አድራሻ ግን ታውቀዋለህ አይደል?”
“የሷንማ ስልኳንም አናውቀውም” አላት፡፡
ስታስብ ቆየችና “ከዚህ በፊት ከጓደኛህ ጋር ለብዙ አመታት አብረው ይሰሩ እንደነበረ ነግረኸኛል”
“አዎ..... የጋዜጣ አሳታሚ በነበረችበት ጊዜ ነዋ፡፡”
“በዛን ወቅት ላይ አብረዋቸው የተነሱትና አንተ የምታውቀው ፎቶግራፍ የላቸውም?”
“እኔንጃ..... ምናልባት መስፍን ቤት ከሔድን ልናገኘው እንችል ይሆናል ግን ምን ይጠቅማል?”
“ይጠቅማል፡፡ ሌላ የተሻለ አማራጭ ስለሌለን መጀመሪያ ሄደን እናምጣ” አለችው፡፡
አብነት ያሰበችው ባይገባውም አላገዳትም፡፡
“አብረን ስንወጣ ቤተሰቦቼ እንዳያዩን ቀድሜ ልሂድ” አለችና በሩን ከፍታ በጊቢው ውስጥ ማንም እንደሌለ በማጣራት ወጣችና ወደ ጊቢው መውጫ መራመድ ጀመረች፡፡

አብነትም ልብሱን በመቀያየር ፀጉሩን መልሶ አያያዘና ጥቁር የሹራብ ኮፊያ አጠለቀበት፡፡ ከዛም በሩን ቆልፎ ወጣ፡፡

ወደ ዋናው ፖስታ ቤት በሚያደርሰው አስፓልት ታጥፈው ጉዞ ጀመሩ፡፡ መስቀለኛው ጋር ሲደርሱም ወደ ላይ ታጠፉና የፒያሳን ታክሲ ይዘው ሄዱ፡፡ ከዛም ፈረንሳይ ለጋሲዮን፡፡

መኖሪያ ቤቱ ጋር ሲደርሱ የተተከለው የለቅሶ ድንኳን ገና አልፈረሰም፡፡ በውስጡ በርካታ ሀዘንተኞች ተቀምጠው በዝምታ ይቆዝማሉ፡፡

እነሱም መጀመሪያ ያደረጉት ከሀዘንተኛው ጋር ለመመሳሰል ገብተው ጥቂት መቀመጥ ነበር፡፡ ከዛም አብነት ከመስፍን ታናሽ ወንድሙ ጋር አይን ለአይን ሲጋጭ “ና” የሚል ምልክት ሰጠው፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

የሃያ ሶስት ዓመት እድሜ ያለው ወጣት ትከሻው ላይ ያደረገው ጋቢ እያስተካከለ መጥቶ አጠገቡ ቁጭ አለ።።
“በረታችሁ?” ጠየቀው አብነት።።
“አዎ.....”
የመስፍን እናት በውስጠኛው ጫፍ በኩል ከሌሎች እኩዮቻቸው ጋር መሬት ላይ በተነጠፈው ምንጣፍ ላይ ተቀምጠው ያንቀላፋሉ።። በጥቂት ቀናት ውስጥ ክፉኛ ገርጥተዋል።። መስፍን እንደተገደለ ነበር እሳቸውን ከእስር የፈቷቸው።።
አብነት ለወጣቱ ብቻ በሚሰማ ቅላፄ “ከመስፍን መኻታ ክፍል የሆነ እቃ እንድትሰጠኝ ፈልጌ ነበር?”
“ምን?”
“ፎቶዎች ናቸው?”
“ከአንተ ጋር አብሮ የተነሳውን ነው?”
“አይደለም.....እ..... አብረን ገብተን እንምረጥ? በምልክት አታውቀውም ብዬ ነው።።”
“እሺ.....ና....” አለውና እየመራው ወደ ቤቱ ውስጥ ገቡ።።
“ምን አድርጐ ነው የገደሉት?” ወጣቱ አብነትን ጠየቀው።።
“እ.....ኔንጃ.....ለእናንተ አልነገሩዋችሁም?”
“ሬሳውን የሰጡን ፖሊሶች ለእድርተኛው ያወሩት.....የዝርፊያ ወንጀል ፈፅሞ ሊያመልጥ ሲል ተገደለ ነው ያሉት።። እናንተም ልጆቻችሁን እንዲህ እንዳይሆኑ ጠብቁዋቸው ብለው ማስተማሪያ ነው ያደረጉት።።” አለ።። ቀጠለ “.....እኔ ግን መስፍን ይሰርቃል ብዬ አላምንም..... ስራ እያለው.... አንተም ታውቃለህ” አለ ወጣቱ በሲቃ።።
“አይዞህ።። ፈጣሪ አንዴ ቀኑን ወስኖለታልና ነው።። ማንም ሰው ደግሞ ከተወሰነለት ዕለት እና እንዲሞት ከሚዘጋጅለት ምክንያት ማምለጥ አይችልም ብለህ ነው ማሰብ ያለብህ”
ወጣቱ የሰጠውን ሁለት አነስተኛ የፎቶ አልበሞች ሲያገላብጥ ቆየ።። የቤቲ ግምት ትክክል ነበር።። መስፍንና ሰናይት የጋዜጣውን ህትመት የጀመሩበትን ዓመታዊ በዓላቶች ሲያከብሩ አብረው የተነሱትን አራት ፎቶዎችን አገኘ።።
ሰናይት በጉልህ የምትታይበትን ሁለቱን አወጣና “እነዚህ ናቸው።።”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

“በቃ ሌላ አትፈልግም?”
“አዎ አመሰግናለሁ፡፡” አለና ተመልሰው ወጡ፡፡ ድንኳኑ ውስጥ ጥቂት ሲጫወቱ ቆዩናም መፅናናትን ተመኝተውላቸው ሄዱ፡፡
“አገኘህ?” ቤቲ ጠየቀችው፡፡ ሁለቱንም አውጥቶ አሳያት፡፡
“አሁን ምን መሰለህ ማድረግ ያለብን.....እ.....” ሀሳቧን በእንጥልጥል ገታችውና “ቆይ.... በመጀመሪያ መሳሪያ የመረከቢያው ደብዳቤ መቼ ይመጣል ብሎ ነበር የነገረህ?”
“ከሶስት ቀን በኋላ ማለት.... ትላንት መጥቶ ሊሆን ይችላል ወይም ዛሬ ካለበለዚያ ግን በእርግጠኝነት ነገ ነው፡፡”
“ሰናይት ደብዳቤው እንደመጣላት ስልካቸው በአንተ እጅ ላሉት ሰዎች እየዞረች ታድላለች ማለት ነው?”
“እንደዛ መሰለኝ የምታደርገው፡፡”
“ዛሬውኑ የአንዱ ሰው ቤት በራፍ አካባቢ ተደብቀን መጠበቅ ይኖርብናል፡፡” አለች፡፡
“የማንንም አድራሻ አናውቅማ፡፡”
“የሆነ ዘዴ እንፈልግ..... ቀጥታ ደውለን የቤታቸው አድራሻ የት አካባቢ እንደሆነ ብንጠይቃቸውስ?”
“ለምንድነው ካሉን ምን ምክንያት እናቀርባለን?..... በዛ ላይ ደግሞ በድብቅ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ሰዎች ስለሆኑ ይብሱኑ ደንግጠው ሊሰወሩ ይችላሉ፡፡”
“እሺ..... አንደኛው ሰው ጋር ሰናይትን መስለን እንደውልና ዛሬ አንድ ላይ ምሳ ለመብላት በዛውም ስለ መሳሪያወቹ መረከቢያ ወረቀት ለመወያየት ቀጠሮ እናሲዝ፡፡ ከዛም የቀጠሮው ቦታ ሄደን በመደበቅ ልናገኘው እንችላለን፡፡ ግዴለህም የሚሰራ ዘዴ ነው፡፡” አለችና የእጅ ሰዓቷን እያየች “እንደውም አሁን አምስት ሰዓት ስለሆነ ጥሩ ነው፡፡”
አብነት ከሷ ሀሳብ የተሻለ አማራጭ ስላልነበረው ተስማማ፡፡
መጀመሪያ በርሔ ጋር ደወሉ፡፡ ቤቲ ነበረች ሰናይትን መስላ አነጋጋሪዋ
“ሀሎ”
“አቶ በርሔን ነበር?”
“ማን ልበል?” የወንድ ድምፅ ነበር፡፡
“ሰናይት ነኝ”
“ሲመጣ መደወልዎን እነግራለሁ፡፡ አሁን ወጣ ብሏል፡፡”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“እ.....ማለት.....” አቋረጠች ንግግሩን
“ተጨማሪ መልዕክት ካለዎት.....”
“በቂ ነው እንደዛ በለው፡፡” ብላ ስልኩን ዘጋችው፡፡
ወደ አብነት ዞረችናም “እቤት የለም አሉኝ፡፡”
“ሆን ብለው ይሆን?”
“አልገባኝም፡፡”
“ሌላኛው ጋር ሞክሪ”
ሂርጳ ጋር ደወለች፡፡
“ሀሎ”
“አቶ ሂርጳ ይኖራሉ?”
“አዎ.....ማን ልበል?”
“ሰናይት ነኝ”
ከጥቂት ቆይታ በኋላ ሂርጳ ቀረበ፡፡ ቤቲ የሰናይን የድምፅ ቅላፄ ምን አይነት እንደሆነ ባታውቅም የሴትነት ጥበቧን መጠቀም ጀመረች፡፡ “አቶ ሂርጳ?”
“አዎ፡፡”
“ሰናይት ነኝ”
“ እንደምን ነሽ..... እደውላለሁ ብለሽ ምነው ጠፋሽ?”
“አልነበርኩም..... ለዛ ጉዳይ ስሯጥ.....”
ሂርጳ ተጨማሪና አደናጋሪ ጥያቄ እንዲያቀርብላት የሚያደርግ ፋታ ሳትሰጠው “ሁሉንም ነገር ለምን ምሳ እየበላን አንነጋገርም?”
“ጥሩ ነው..... እቤት ነይና.....”
አቋረጠችውና “እስኪ እኔ ልጋብዝህ ዘሬ?”
“ተይ ባክሽ..... በዚህ ሰሞን ወያኔ ከተማውን እያመሰችው ስለሆነ ብዙም ከቤት ወጣ ወጣ ማለት ትቻለሁ፡፡”
“አንተ በመረጥከው አካባቢ መሆን ይቻላል?”
“አይ.....እንቢታዬ የንቀት እንዳይመስል እንጂ.....” በቅሬታ እንደሚናገር ያስታውቅ ነበር፡፡ ቀጠለ “.....እሺ ዝባድ ሆቴል እንገናኝ”
“የቱ ጋር ነበር?”
“ጳውሎስ ሆስፒታልን አለፍ ብሎ ነዋ..... እዛው የኔ ሰፈር”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“እሺ..... ልክ ስድስት ሰዓት ላይ እንገናኝ” አለችውና አንድ ምልክት መጠየቅ እንዳለባት አስታውሳ “ከቀደምከኝ የቱ ጋር ነው የምትቀመጠው፡፡ ለጥንቃቄ ስትል የምታደርገው የቦታ ምርጫ እንዳያጠፋፋን ብዬ ነው፡፡”
“የማስይዘው ቦታ አይታወቅም..... ፊቴን ሸፈን ለማድረግ ጥቁር መነፅር አደርጋለሁ፡፡”
“እሺ..... እየመጣሁ ነው በቃ፡፡” ስልኩን ስትዘጋው ፊቷ ላይ ላብ አቸፍፎ ነበር፡፡
የሆቴሉን ስም እንዳትረሳው በህሊናዋ ደጋገመችውና
“እንሂድ ተሳክቷል” አለች፡፡
ከፒያሳ አስኮ በሚለው ታክሲ ተሳፈሩና ለረዳቱ የሆቴሉን ስም በመንገር ሲደርሱ እንዲያስቆሙላቸው አዘዘው፡፡
ቦታው ላይ ለስድስት አስር ጉዳይ ሲል ደረሱ፡፡ ባለ አራት ፎቅ የሆነ ህንፃ ነው፡፡ አካባቢው የፀዳ ሲሆን የመኪና ማቆሚያው ስር ጥቂት መኪናዎች ይታያሉ፡፡
“እዚህ ውስጥ እኮ ነው” አላት፡፡
“ምን ችግር አለው ታዲያ”
አለባበሱን ተመለከተ፡፡ አዲስ ባይሆንም የሚያሳጣው አልነበረም፡፡ ካኪ የጨርቅ ሱሪ በርካታ ዓይነት ደማቅ ቀለማት ያሉት ዥንጉርጉር ሸሚዝ ክፍት ክፍት የሆነ ጫማ፡፡
እሷን አያት፡፡ ደረቷን ለዕይታ ያጋለጠ ነጭ ከኒቲራ ከጥቁር ኮትና አጭር ቀሚስ ጋር ውብ ከሆነ ባለ ጥልፍልፍ የገመድ ጫማ ጋር፡፡ በማስያዣ ተይዞ የነበረው ፀጉሯን ስትለቀው በትከሻዋ ዙሪያ ተበትኖ ውበቷን አጎላው፡፡ አብነትም እሷ ከሱ የበለጠ መስህብ እንዳላት አስተዋለ፡፡
ቀጥሎ ያደረገው እጁን ወደ ኪሱ መስደድ ነበር፡፡ ለሚገለገሉት ነገር የሚጠየቀውን ክፍያ ማወቅ አለበት፡፡ በኪሱ ያለውን ገንዘብ አወጣ፡፡ ሁለት ባለ አስር ብር እና ባለ አንድ አንድ ኖት፡፡
ቤቲ ስሜቱ ስለገባት “ገንዘብ በቂ የሆነ ይዣለሁ” አለችው፡፡ የመግቢያውን በር አልፈው ወደ መመገቢያ አዳራሹ የሚያደርሰውን ደረጃ መውጣት ሲጀምሩ አንድ ሰው ከኋላቸው መጣና በፈጣን

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

እርምጃ አልፎዋቸው ገባ፡፡ ተራ የሆነ ሰማያዊ ጃኬትና ግራጫ የጨርቅ ሱሪ ለብሷል፡፡ በአይኑ ላይ ጥቁር መነፅር ሰክቶ ነበር፡፡

ቤቲ አብነትን ነካ አደረገችውና በዝቅተኛ ድምፅ "ይሄ ነው መለሰኝ"

"ውስጥ ስንገባ ሌላ ሰው ከሌለ ነው እርግጠኛ መሆን የምንችለው፡፡"

ትክክል ነበረች በስተግራ በኩል በሚገኘው ሰወር ያለ ቦታ ጥንድ ከሆኑት ሰዎች ሌላ ብቻውን የተቀመጠው እሱ ብቻ ነበር፡፡ አምቦውሃ በማዘዝ ለአንድ ሰዓት ያህል ጠበቀ፡፡

እነሱም ለሱ እይታ እምብዛም ባልተጋለጠ ጠረጴዛ ተቀምጠው ጥሩ ምሳ ተመገቡ፡፡

ሰባት ሰዓት ሲል የአምቦውሃውን ሂሳብ ከፍሎ ወጣ፡፡ እርምጃው ከቅድሙ ይበልጥ ፈጣን ሲሆን በጥቂቱ ንዴት መሳይ ገፅታም ይታይበት ነበር፡፡ እነሱም ሂሳባቸውን ዘግተው በመውጣት በመካከላቸው ሊኖር የሚገባውን እርቀት እያስተዋሉ ተከተሉት፡፡

ሂርጳ ወደ ቀኝ ታጥፎ ሃምሳ ሜትር ያህል ከተጓዘ በኋላ አስፓልቱን ተሻገረና ወደ ግራ ታጥፎ በኮረኮንቻማ መንገድ ገባ፡፡ የአንድ ብረት በር ጊቢ ጋር ሲደርስ ቁልፍ ከኪሱ በማውጣት ከፍቶ ሲገባ አዩት፡፡

ቀጣዩ ስራቸው በዛው አካባቢ ሰዋራ ስፍራ ላይ ሆነው የሰናይትን መምጣት መጠባበቅ ሆነ፡፡

  

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ምዕራፍ 38

ሰናይት ያለፉትን ሁለት ቀናት በጳውሎስ መኖሪያ ህንፃ አካባቢ ክትትል ብታደርግም ምንም ፍንጭ ማግኘት አልቻለችም። ይህም ሁኔታዎች ወደ አደገኛ ደረጃ ላይ መድረሳቸውን እንድትገነዘብ ስላስቻላት የመረበሽ ስሜቷ በእጅጉ እያየለ ሄዷል። አንዳንድ ጊዜ እንደውም ይህን የጀመረችውን አደገኛ ስራ እስከመጥላት ትደርሳለች።

ሚሊቴሪ የለበሰ ፖሊስ ባየች ቁጥር አንበሳ እንዳየች ሚዳቋ ሮጣ ስርቻ ስር መወተፍ ይሻታል። የምታያቸው የከተማው ፖሊሶች በጠቅላላ እሷን ለማደን ብቻ የተሰማሩ ሀይሎች እስኪመስላት ድረስ ፈርታቸዋለች።

ከዚህ ሁሉ አስቀያሚ ስሜቷ ጋር ስትታገል ትንሽ እንድትረጋጋ የሚያደርጋት ነገር ቢኖር ግዳጇን ለመፈፀም ከሁለትና ሶስት ሳምንት የማይበልጥ ጊዜ የቀራት መሆኑን ስታስብ ብቻ ነው።

ከዛም የረብጣ ሚልየን ዶላር ባለቤት ትሆንና ደስታው..... ፈሽታው ተግተልትለው በመምጣት ያጅቧታል።

«ዲሲ» በሚባለው አካባቢ መንበረ ቤት ማደር ከጀመረች ሶስት ቀን ሆኗታል። እስከ ትላንትናው እለት ምሽት ድረስ ሰናይት ሌት መሆኗን መንበረ አላወቀችም ነበር። ማታ ላይ ስትነግራት ለጊዜው ብትደነግጥም ወድያው ተረጋጋች። በዛው አያይዛም ከቧሏ ተጣልታ የተሸሸገች መሆኑን ገለፀችላት። መንበረ በጣም አዘነችላት። ከራሷም ታሪክ በወንዶች የደረሰባትን በደል አንዳንዱን ነገረቻት። በጥሩ ሁኔታ እየተግባቡ በመሄዳቸው ሌላ ቦታ መቀየር ሳያስፈልጋት የምትፈልገውን ያህል ጊዜ ከሷ ጋር መቆየት እንደምትችል መንበረ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ነገረቻት። ሰናይትም የዋህነቷን እያስዋለች እናቷን ለማስታወስ ስለተገደደች ሀዘን ቢጤ ይሰማት ጀምሯል።

መንበረ ስላለችበት አንገሽጋሽ ህይወትና በየ ዕለቱ በምትኖርበት ሰፈር ውስጥ የሚከሰተውን አሳዛኝ ሁኔታ እያወጋችላት አያይዛም በአካባቢው ላይ ያሉት ወጣቶች ተስፋቸው እንደጉም እየተበታተነ ሞራላቸው አብቦ ሳያፈራ በለጋነት ጫጭቶ ሲጠፋ እያየች እሷ ለነሱ እንደምታዝን ነገረቻት። ሰናይት ደግሞ መልሳ ለራሷ የሚታዘንላት ፍጡር መሆኗን እያሰበች ለሊቱን ያሳልፉ ነበር።

መንበረም ያለፉትን ሶስት ቀናት ገበያ መጣ አልመጣ ፤ ሰክሯል አልሰከረም፤ ያሳምመኝ ይሆን ወይስ አይሆን..... ከሚሉት አስቀያሚ ሀሳቦች ተላቃ ለእለት ወጪዋና ለቤት ኪራይዋ የሚያስፈልጋትን ገንዘብ በቀላሉ ማግኘት ስለቻለች ሰናይን በመልካም መንፈስ ተቀብላታለች። ህይወቷ ስላልፈቀደችላት እንጂ ላልተወሰነ ጊዜ የተጐዳው ስሜቷ እስኪጠግን ድረስ ከወንድ ጋር ወሲብ ባትፈፅም ትመርጣለች።ይህን ደግሞ ከሰናይት ማግኘት ችላለች።

ወድያው ሌላ ስጋት ተከሰተባት። ሰናይት ስትገባና ስትወጣ በጉረቤቶቿ እንዳትታይባት ነበር። ምክንያቱም ከሴት ጋር መተኛት ጀመረች ብለው ስሟን በግረሰዶማዊነት እንዳይበክሉባት በጣም ፈራች። ፍርሀቷን ግን በውስጧ ይዛ ዝም አለች።

በሶስተኛው ቀን ጠዋት ላይ ከእንልፏ መንበረ ቀድማ ተነሳችና "ሰዓት ገና ነው ተኚ" ብላት ተነሳች።

ልክ ነበረች። ገና አስራ ሁለት ሰዓት ይል ነበር። ሰናይት ግን ለስሙ አልጋ ውስጥ ትሁን እንጂ በእለቱ ስለምትፈፅመው ሁለት አደገኛ ስራዎች ስታስብ ነበር ለሊቱን ካለ እንቅልፍ ያሳለፈችው።

መንበረ ለባብሳ የግብር ውሃ በመያዝ ወጣችና ተጣጥባ ተመለሰች። ከዛም አነስተኛ ዘምቢል አንጠልጥላ ወጣች።

ጥቂት ቆይታ ስትመለስ ስድስት እንቁላል አራት ዳቦ የችርቻሮ ዘይትና ሽንኩርትን ከሻይ ቅጠልና ስኳር ጋር ገዛዝታ ነበር።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

አንድ አጭር እርምጃ በማታራምደው ቤቷ ውስጥ ገብታ በሩን ዘጋችና ከአልጋው ስር ቡታጋዝ ጐትታ በማውጣት ለኩሳው ስራዋን ቀጠለች፡፡

ሰናይት ቀና ብላ አየቻትና "በጥዋቱ ራበሽ እንዴ?"
"ዛሬ ቁርስ ልጋብዝሽ ብዬ ነው፡፡"
ደንግጣ "ለማ.....ለኔ?"
"አዎ"
"ምን ስላደረኩልሽ?"
"ደስ ስላለኝ....." አለች፡፡
አስተውላ እያየቻት 'እድሏ ለምን እዚህ ውስጥ ጣለቻት?' ስትል አሰበ፡፡ ቀጠለች 'እድል..... ምንድነው ግን ሚስጥሯ?.....አንዳንዱን ሰው በሚጓዝበት አቅጣጫ ሁሉ እየቀደመችው ትጠብቀዋለች፡፡ ውስኑን ደግሞ ከኋላው ትከተለዋለች፡፡.....አንዳንዱን ሰው ደግሞ እሷን እየተከተለ ይጓዛል፡፡ አብዛኛው ሰው እና የስኬት እድሉ ግን ልክ እንደ ተመሳሳይ ዋልታ ማግኔት እድሜ ልክ እንደተገፋፉ ይኖሩና ሰውዬው በስተመጨረሻ ላይ ተሸናፊ ሆኖ ይወድቃል.....' አለች በሀሊናዋ፡፡ '.....የዚህች ልጅም ዕድል እንደ ማግኔቶቹ ይሆን?' ራሷን ጠየቀች፡፡
"እንደዚህ እያየሽኝ ስለምንድነው የምታስቢው?" ጠየቀች የእንቁላሉን ቅርፊት ሰብራ አስኳሉን ወደ ሰሀን ውስጥ እያፈሰሰች፡፡
"እ.....አይ..... ስለራሴ ነው፡፡"
ጠባብሳ ስትጨርስ "ወደዚህ ጋር ጠጋ በይና ፊትሽን ላስታጥብሽ" አለች የመታጠቢያ ሰሀኑን እያመቻቸች፡፡
"ቢቀርብኝ ችግር የለውም ነበር፡፡"
"ምን..... የሸርሙጣ ግብጥ ስለሆነ መናቁ ነው? ወይስ ተፀይፈሽኝ....."
በሀዘን የተዋጠ ንግግሯን አቋረጠቻትና "አይደለም..... መንበረ እውነቴን ነው..... እንደውም ራሴ እታጠባለሁ፡፡ የውሃውን ጣሳ አቀብይኝ"

አየቻትና ጨፍግጐ የነበረው ፊቷ እንደ ዕለቱ ማለዳ በተስፋ ብርሃን የተሞላ መሰለ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ሰርታ ስትጨርስ የተፈረፈረውን እንቁላል በሳህን አድርጋ ዳቦዎቹን በዙሪያው በማስቀመጥ አቀረበችላትና "በይ ብይ....."
"ነይ ጠጋ በያ....."
"ለራሴ ድስቱ ውስጥ አስቀርቻለሁ"
"በፍፁም አይሆንም፡፡ ከዚህ ጋር ነው መብላት ያለብሽ!" ቁጣዋ አስደነገጣትና በክርክር አልዘለቀችም፡፡ ለሁለቱም ሻይ ቀድታ የአልጋው ጠርዝ ላይ ተቀመጠች፡፡ በዝምታ መብላት ጀመሩ፡፡
"እንዳንዴ.....ወንዶችን ስታይ በሚሰሩት ስራ ፍፁም ይቅርታ እንዳታደርጊላቸው ትገደዳለሽ" አለቻት፡፡
ሰናይት ሀሳቡን የተቀበለች በማስመሰል ጭንቅላቷን ነቀነቀችላት እንጂ ስለምግቡ ነበር የምያስበው፡፡ ይህንን ምግብ እንዴት ባለ ሁኔታ ባገኘችው ገንዘብ ገዝታ እንደጋበዘቻት ስታስብ ስጋዋን ጠብሳ ያቀረበችላት ያህል ተሰማትና አልዋጥሽ ብሎ ተናነቃት፡፡
"ብይ እንጂ ምግቡን ምን አፍሽ ውስጥ ታንገዋልይዋለሽ?"
"እሺ...." አለቻት ሰናይት በሻዩ እያወራረደች፡፡
በህሊናዋ ቀጠለች 'በህይወቷ ውስጥ የገባሁት ለመሸሸጊያነት ብዬ እንደሆነ ብታውቅስ?' ራሷን ጠየቀች፡፡
ጥቂት ጮራርሳ "በቃኝ" አለቻት፡፡
"ግማሹን እንኳ አልበላሽም እኮ....."
"እውነቴን ነው በቃኝ"
አነሳስታ አስታጠበቻት፡፡ ከአልጋው ወረደችና ፀጉሯን እንደማስተካከል እያደረገች ልብሷን ለባብሳና ጫማዋን አጥልቃ ጨረሰች፡፡ በተኛችበት ግርጌ በኩል ፍራሹን ገልፃ ሽጉጧን በማውጣት ወገቧ ስር ስትከት መንበረ አየችና በድንጋጤ ሽሽት እያለች "ፖሊስ ነሽ እንዴ?"
"አዎ..... ምነው ደነገጥሽ?"
"አይ..... እንዲህ መሳሪያ..... ሳይ አልወድም እፈራለሁ፡፡"
"አይዞሽ..... ማታ እመጣለሁ ቻዎ....." ብላት ልትወጣ ስትል
"ቆይ ውጭውን ላጣራልሽ ስትወጪ ሰው እንዳያይሽ፡፡"
"ተይው ባክሽ..... ማንስ ቢያየኝ ምን አገባው፡፡"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ዝም ብላ አየቻት፡፡ በሀሳቧ ግን ርቃ ነበር፡፡ ሽርሙጣ ቤት አድሮ በልበ ሙሉነት ሰው አየኝ አላየኝ ሳይል የሚወጣ ደምበኛ በስድስት ወር ውስጥ አንዴ እንኳ እንደማያጋጥማት እያሰበች፡፡

ሰናይት ከዛ መንደር ወጥታ ወደ ፊላሚንጐ አመራች፡፡ ከዛም ቦሌ የሚለውን ታክሲ ይዛ ወሎ ሰፈር ለመድረስ ጥቂት ሲቀራት ወረደች፡፡

በወረደችበት ስፍራ ትይዩ ላይ በብዛት የ “ኢ.ሀ.አ.ዴ.ግ” ባለስልጣናት፣ ካድሬዎችና የምክር ቤት አባሎች የሚኖሩባቸው ረዣዥም ህንፃዎች ላይ ስታፈጥ ቆየችና ወደ ጳውሎስ ኩንቴ ቤት መግባት እንዳለበት ለመጨረሻ ጊዜ ወሰነች፡፡ ያለፉትን ሁለት ቀናት በዚህ መልኩ እሱን ጥበቃ ብታሳልፍም ምንም ፍንጭ ልታገኝ አልቻለችም፡፡ አስፓልቶቹን ተሻግራ ወደ ህንፃው ጊቢ እያለፈች ዙሪያዋን ደጋግማ ቃኘች፡፡ ከዛም ወደ ህንፃው በመግባት እርምጃዋን ወደ አሳንሱሩ ስትቀጥል

“ይቅርታ የኔ እመቤት ማንን ፈልገው ነው?” ከዚህ በፊት አይታው የማታውቅ የህንፃው ጠባቂ ጠየቃት፡፡

“ሶስተኛ ፎቅ ላይ ለአጎቴ መልክት ለማድረስ ነው፡፡ አታውቀኝም እንዴ ሁሌ እመጣለሁ እኮ አብሬው፡፡ እንደውም ስመለስ አብረን እንወጣና ታየዋለህ” ብላ ልብ የሚሰርቅ አይናፋር ፈገግታ አሳይታው መልስ ሳትጠብቅ አልፋው ገባች፡፡

የአሳንሰሩ በር ሲከፈትላት ገብታ የምትፈልገውን ፎቅ ቁጥር ተጫነቸው፡፡

አሳንሰሩ መውጣት ሲጀምር ሽጉጧን አውጥታ አቀባበለችና ድምፅ ማፈኛው በትክክል መጥበቁን አረጋግጣ መጠባበቂያውን ከፈተችው፡፡ ያሰበችውን ከመፈፀም ውጪ ሌላ ምንም አማራጭ እንዳልነበራት አምናለች፡፡

በዚህ አደገኛ ሙከራ ውስጥ አንድም ስኬታማ በመሆን ለቀጣዩ ስራዋ ጋሬጣ የፈጠረባትን ሁኔታ ትጠርገዋነች፡፡ አልያም በዚህ ሙከራ ልትያዝም ሆነ ልትገደል እንደምትችል አስባበታለች፡፡

አሳንሰሩ ደረሰና መውጫውን ከፈተላት፡፡ መተላለፊያዎቹ ሰው አልባ ነበሩ፡፡ በቀስታ እየተራመደችና ዙሪያውን እያየች የጳውሎስ ቤት በራፍ ላይ ደርሳ ቆመች፡፡ የጥንቃቄ ጥቁምታ ለማግኘት ያህል ጆሮዋን ወደ በሩ አስጠግታ ከውስጥ ድምፅ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ለመስማት ሞከረች፡፡ የሚያወራ ሰው አልነበረም ሰዓቷን አየች፡፡ ገና ከጠዋቱ አንድ ሰዓት ላይ ያመለክት ነበር፡፡
በቀስታ በሩን አንኳኳችው፡፡
“ማነው?” የሴት ድምፅ ዘግይቶ ምላሽ ሰጣት፡፡
“እኔ ነኝ”
“ማን?”
“መልዕክት እንዳደርስ ተልኬ ነው የመጣሁት” ከዚህ በፊት አንድ ሁለቴ ያየቻት በመሆኑ እንምታስታውሳት ብትገምትም በዚህ ወቅት ላይ ግን ስለሷ የሚኖራትን መንፈስ ለማወቅ ስላልቻለች ማንነቷን በግልፅ ማሳወቅ አልፈለገችም፡፡
“አልከፍትም ማነሽ አንቺ!?” በቁጣ ጠየቀች፡፡
ገና ከጅማሬው በሰላም የመግባባቱ ጉዳይ ገደል እንደገባ ታሰባት፡፡ ትክክለኛ ማንነቷንም መግለፁ ለሚፈለገው ውጤት እንደማይጠቅም አመነችና “ከመንግስት ምክር ቤት ስለባለቤትሽ የመጣልሽን የደብዳቤ መልዕክት ልሰጥሽ ነው፡፡”

ወድያው ተራምዳ ከፈተችውና ገና የሰናይትን ፊት ስታይ ለባለቤቷ መገደል መንስኤ ከዚህች ሴት ጋር ጀምሮት የነበረው ሚስጥራዊ ግንኙነት መሆኑ ታወሳትና በሩን በመወርወር ልትጠረቅምባት ስትል እግሯን አስቀድማ በሩ ስር ቸከለችባት እና አገደቻት፡፡ ወድያውኑ ገፍትራት ገባችና በሩን ስትዘጋው የጳውሎስ ሚስት ለመጮኽ አፏን ከፈተች፡፡ ሽጉጡን አውጥታ በተከፈተው አፏ ትክክል ደገነችባት፡፡ እግሮቿ በፍርሀት እየራዱ አፍጥጣባት በዝምታ ታያት ጀመር፡፡
“ዝም ከአልሽ ጫፍሽን አልነካውም!” በሀይለ ቃል ተናገረቻት፡፡
“እ.....ሺ.....ሺ....” በረዥሙ መለሰች፡፡
“ባለቤትሽስ?”
“ ገድለውታል“
ሰናይት ለደቂቃ ደርቃ ቀረች፡፡ የገመተችው ትክክል ነበር፡፡
የጳውሎስ ሚስት ሳግ እየተናነቃት በዝምታ ማልቀስ ጀመረች፡፡ ሰናይት የቤቱን ዕቃ ያስተዋለችው ይሄኔ ነበር፡፡ ምንቅርቅሩ ወጥቷል፡፡ ሁለት የተሸከፉ የጉዞ ሻንጣዎች ግን ሶፋ ላይ ተቀምጠው ይታያሉ፡፡
“ማነው ቤቱን እንደዚህ ያደረገብሽ?”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“እሱን..... የገደሉት.....ፖሊሶች.....ናቸው።።” አለች ማልቀስ እየጀመረች።።
“መቼ?”
“ትላንትናም ዛሬ ለሊትም መጥተው.....ነበር.....”
“አታልቅሺ።። አልነካሽም።። ልጐዳሽ አይደለም የመጣሁት።።” አለቻት የደገነችባትን ሽጉጥ ዝቅ እያደረገችው።።
የመረጋጋት መንፈስ እስኪታይባት ጠበቀችናም “ባለቤትሽ አሁን የት ነው ያለው? ማለት ፈሳው?”
“ለምርመራ ሄዷል እንዳሉኝ እስካሁን አልሰጡኝም።።”
“እንሰጥሻለን ብለዋል?”
“አዎ.....ዛሬ ከሰጡኝ ይገፍው አገሬ እገባለሁ” አለች።።
ሰናይት የሻንጣው ዝግጅት ለሱ መሆኑን አወቀች።።
“ለመሆኑ ገንዘብ አለሽ?”
“ለመሳፈሪያ ይበቃኛል።።”
በዝምታ ጥቂት ቆየችና “እኔ የምፈልገው አሁን አንድ ነገር ብቻ ነው ከአንቺ”
ምን በሚል እይታ አየቻት።።
“ህዝበ ደቡብ ነፃነት ሀይል የሚባል የድብቅ ፓርቲ በነ ጳውሎስ መሪነት መቋቋሙን እንደገለፀልሽ አንዴ አጫውቶኝ ነበር።።” አለቻት።። የምትነግራትን ከፍተኛ ሚስጥር በቀላሉ ያለማመን ፅኑ እምነት ቢኖራት እንኳ አስተሳሰቧ ላይ ቀድማ ተፅዕኖ ለማሳደር የፈጠረችው ሀሳብ ነበር እንጂ ከጳውሎስ ጋር ይህን መሰል ርዕስ አንስተው አያውቁም።።
“ለ.....ለኔ.... በፍፁም.....አላውቅም”
“ለምን ትዋሺኛለሽ።። እኔ የዛ ፓርቲ አንዱ አባል ነኝ”
“አላውቅም።።” መንዘፍዘፏ እንደ አዲስ ተነሳባት።። ሆኖም የበፊቱና የአሁኑ ፍራቻዎቿ መካከል ልዩነት እንደነበረው ሰናይት በማጤኗ ልትደብቃት መፈለጓን አወቀችባት።።
“መጀመሪያ የምፈልገውን ልንገርሽ.....” አለቻትና በልቧ እንዲሳካላት ፈጣሪዋን እየተማፀነች “.....እዚህ አዲስ አበባ ውስጥ ከጳውሎስ ጋር ሆኖ የፓርቲውን እንቅስቃሴ የሚመራ የአንድ ሰው አድራሻ ብቻ እንድትሰጪኝ ነው የምፈልገው።።”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

“አላውቅም..... አልኩሽ እኮ.....”
“ቅጥረኛ የመንግስት ሰላይ አይደለሁም..... የፓርቲውን እንቅስቃሴ ትደግፊዋለሽ፡፡ እኔ ደግሞ ፓርቲው ከውጭ መንግስታት ድጋፍ የሚያገኝበትን ሁኔታ የማመቻችለት ሰው ነኝ፡፡”
“አላ.....ውቅም..... ፖሊሶችም ስለዚህ ጉዳይ አንስተው ጠይቀውኝ ነበር”
በተለያዩ መንገዶች ልታሳምናት ብሞክር አልቻለችም፡፡ የተናደደች አስመስላ ተወራጨችና ሽጉጧን መልሳ ደገነችባት፡፡ እጥፍጥፍ ብላ መሬት ላይ ወደቀች፡፡ በዚህ ጊዜ አንደኛው ህፃን ልጇ ከእንቅልፉ ተነስቶ አይኖቹን እየጠራረገ ከጓዳ ብቅ አለ፡፡
ዞራ ወደ ልጇ በማፍጠጥ “እቢ.....ግ....ባ ግባ!” ጮሀ አዘዘችው፡፡ የደነገጠው ህፃን ግን ሮጦ መጥቶ ተጠመጠመባት፡፡
ሰናይት ሽጉጡን ከሷ ላይ ወደ ህፃኑ ጭንቅላት ደገነች፡፡
“ባክሽ ልጄን አትግደይብኝ..... እኔን....እኔን በይኝ.....” የልጇን አካል ጨምቃ በጉያዋ ስር ለመሸሸግ እየጣረች ተማፀነች፡፡
“አንቺን አልፈልግም፡፡ ህፃኑን ግን እገድለዋለሁ!”
እግሯ ስር ወድቃ ጫማዋን የመላስ ያህል እየሳመች በፊቷ ገፅ እያበሰች “እኔን.... እኔን... ቀደመሽ ግደይ.....”
“ድምፅሽን ቀንሺ!”
“እሺ.....”
ህፃኑ ያልተለመደ አይነት የሆነበትን ትዕይንት በዝምታ ሲያይ ቆየና እናቱን ጨምቆ በመያዝ ማልቀስ ጀመረ፡፡
ቀጠለች “በይ ንገሪኝ ወይም የልጅሽን ሬሳ ለማንሳት ተዘጋጂ” አለችና የተቀባበለው ሽጉጡን ደግማ አቀባበለችው፡፡
መጀመሪያ የተጐረሰችው ጥይት ተወርውራ ወጣች፡፡ ድርጊቱ ስነ-ልቦናዋን ለመስረቅ አስባ የፈፀመችው ነበር፡፡
“እሺ..... አትግደይው.....ቆይ.....” ፈጥና ከወለሉ መነሳት ጀመረች፡፡
“ቶሎ በይ..... ቶሎ በይ!”
ወደ መፅሀፍ መደርደሪያው ሮጠችና በደህንነቶቹ ፍተሻ ወቅት ከተበታተኑት መካከል ወፍራም ጥራዝ ያለው ኢንሳክሎፒዲያ የመሰለውን መፅሀፍ አነሳች፡፡ ገፁን እየከፋፈተች ተበታትነው የተቀመጡ ቁርጥራጭ ወረቀቶችን በማውጣት ቁጥሮቹን እያገላበጠች ፅፋ ሰጠቻት፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“የማን አድራሻ ነው?”
“የሻለቃ ደርበው ጋፈሮ”
“የት ነው የሚሰራው?”
“ፌደራል ፖሊስ ውስጥ”
“ቤተሰብ አለው?”
“እዚህ የሉም ገጠር ናቸው፡፡”
“ይህ የግል ቤቱ አድራሻ ነው?”
“የኪራይ ቤቶች በሰጠው ቤት ውስጥ ነው የሚኖረው፡፡”
“ስንት ሰዓት ላይ ብሔድ አገኘዋለሁ፡፡”
“ያው ከስራ ሰዓት ውጪ ነዋ..... አንዳንዴ ግን ስራ ከበዛበት መስራቤት ነው የሚያድረው፡፡”

ወረቀቷን ኪሷ ከታ በዛው የተጨባበጠ ብር አወጣችና በውስጡ የነበሩትን ድፍን ባለ አንድ ሺህ ዶላር ኖቶች ለይታ እየሰጠቻት “መምጣቴን ለአንድ ሰው ትንፍሽ እንዳትይ!”
“እሺ” አለች ቶሎ ቤቱን ለቃላት እንድትወጣ እያሰበች:: በሩን ከፍታ አንገቷን በማስገግ አጣራችና ማንም ያለመኖሩን ስታውቅ ወጥታ መሄድ ጀመረች:: የጳውሎስ ሚስትም ልጇ ላይ ተጠምጥማ እንደገና ማልቀስ ጀመረች::

ሰናይት ወርዳ መውጫው ጋር ስትደርስ ለዘበኛው “አጎቴ ተኝቷል አብሬሽ አልወርድም አለኝ:: በኋላ ተመልሼ ስመጣ ታየዋለህ” ብላ ድጋሜ አማላይ ፈገግታ አሳይታው ወጣች::

በቀጥታ ኮንትራት ታክሲ በመያዝ ቦሌ ሩዋንዳ ወደተከራየችው ቤቷ አመራችና ወደ ፈረንሳይ የምትልከውን ሪፖርት ስትፅፍ ቆይታ ለመላክ ጨረሰች::

ምሳ ሰዓት እየተቃረበ ሲመጣ ከጳውሎስ ሚስት ባገኘችው አድራሻ መሰረት የሻለቃው ቤት ወደሚገኝበት አካባቢ ጉዞ ጀመረች፡፡ ቤቱ የታነፀው ከቴሌ መድሀኒያለም ወደ መገናኛ መስመር የሚመልሰውን አስፓልት በመያዝ አንድ ኪሎ ሜትር ያህል ገብቶ ነበር፡፡

ካለ ብዙ ድካም አገኘችው፡፡ የድሮ ስራ ሆኖ ደህና መስህብ ያለው መለስተኛ ቪላ መሳይ ቤት ነው፡፡ የጊቢው አጥር አንድ ሜትር ቁመት ባለው ደንጊያ ተገንብቶ ተጨማሪ አንድ ሜትር በጌጥ የተሰራ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ብረት የተቀጠለበት ነው፡፡ በብረቱ በኩል ጊቢው ለዕይታ እንዳይጋለጥ ቆርቆሮ ተደርቦበታል፡፡

ሰናይት ከቤቱ ፊት ለፊት በሚገኝ ኬክ ቤት በረንዳ ላይ ተቀምጣ ማኪያቶ በማዘዝ ስለምትወስደው ቀጣይ እርምጃ እያሰላሰለች ለግማሽ ሰዓት ያህል ቆየች፡፡

በዚህ ጊዜ አንድ ነጭ ቅብ የተቀባ ላንድ ክሩዘር መኪና መጣና በበሩ አቅራቢያ ቆመ፡፡

ወድያው በሰናይት ህሊና ውስጥ አብዛኛዎቹ የመንግስት ሰዎች በተመሳሳይ ላንድ ክሩዘር መኪና የመጠቀማቸው ጉዳይ ታሰባት፡፡ስለ ሁኔታው እያሰላሰለች ተጨማሪ ጊዜ መግደል አልፈለገችም፡፡

ትኩረቷን አሰባሰበችና ሰውዬውን በዕይታ መከታተል ጀመረች፡፡

ብቻውን እየነዳ የመጣው ሰው ወረደና የጊቢውን በር በቁልፍ ከፍቶ ገባ፡፡

ሰናይት ትርታዋ ጨመረ፡፡ ግና ግዴታዋ መሆኑን አሰበችና በረዥሙ ተንፍሳ በመነሳት ሂሳቡን ከፍላ ወጣች፡፡ ጭር ያለውን አስፓልት ተሻገረችና ገርበብ ተደርጎ የተተወውን የጊቢውን በር ገፋ አድርጋ ገባች፡፡

ውስጡ ሳር በቅሎበታል፡፡ ያልተረገጠ ሳር በመሆኑም ሻለቃው ለብቻው ስለመኖሩ ተጨማሪ ማስረጃ ሆነላት፡፡

የቤቱ መግቢያ ጋር ደርሳ በቀስታ አንኳኳች፡፡

“ማነው?”

“እኔ.....ነኝ”

በሩ ሲከፈት ሻለቃው በርካታ ወረቀቶችን ይዞ ለመውጣት የተዘጋጀ መሆኑ ያስታውቅበት ነበር፡፡

ሰናይት ከዚህ በፊት ትውውቅ ያላቸው አስመስላ ጠበቅ ባለ ስሜት ሰላምታ ሰጠችው፡፡ ድርጊቱ በትክክልም የሻለቃውን ስሜት በመያዝ አፍራሽ ሀሳብ እንዳይከሰትበት ጠቀማት፡፡ ሻለቃው ፈገግ እንዳለ “የት እንደምንተዋወቅ ግን ለማስታወስ አልቻልኩም፡፡”

“አዎ..... በእርግጥ በአካል አንተዋወቅም፡፡ ጳውሎስ ግን.....”

ሻለቃው ገና ስሙን ሲሰማ የያዘውን ወረቀት ለቀቀው፡፡ እጁን ወደ ሽጉጡ ማህደር መስደድ ሲጀምር ሰናይት ቀድማው አውጥታ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

አገጩ ስር ደገነችበት፡፡ እየገፋች ወደ ሳሎኑ ቤት አስገባችውናም ሽጉጡን ወሰደችበት፡፡ “ምንም አይነት ሙከራ ብታደርግ እገድልሀለው!” አለችው፡፡ የሻለቃው ፊት ወድያውኑ በፍርሀት ላብ ረጠበ፡፡
“ተምበርከክ!..... እነቃነቃለሁ ብትል እርምጃ ከመውሰድ አንዳች ሀይል አያግደኝም፡፡”
ሻለቃው ከመፈፀም ውጪ አማራጭ አልነበረውም፡፡
“ምንድነው የምትፈልጊው ከኔ?”
“ምንም፡፡ ይልቅ አንተም ሆንክ ህዝበ ደቡብ ነፃነት ፓርቲ ከኔ ብዙ ነገር ይፈልጋል፡፡ ጳውሎስ ሞተ ማለት የኛ ትግል እና ዓላማ ከሸፈ ማለት አይደለም፡፡ እኛ አብረን መቀጠል እንችላለን፡፡ አሁንም አንተን መግደል ወይም ማጥቃት ቢሆን ዓላማዬ እካስሁን መቆየት ባላስፈለገኝ ነበር፡፡ የምፈልግህ ስራውን አብረን እንድንቀጥል ብቻ ነው፡፡ ይዤ የመጣሁትን ጠቃሚ ነገር ልሰጥህ እፈልጋለሁ.....”
ሻለቃው በዝምታ ያያት ጀመረ፡፡

“ያደረከው በሙሉ ትክክል ነው፡፡ አንተም ሆንክ ጳውሎስ ለህዝበ ደቡብ ነፃነት ሀይል በድብቅ ስትሰሩ የቆያችሁ ታማኝ ሰዎች መሆናችሁን አውቃለሁ፡፡ ዛሬ እሱ ለዓላማው ተሰውቷል፡፡ ሆኖም ግን አንተም እንደሱ አጉል አሟሟት መሞት እንደማትሻ አውቃለሁኝ.....”
አለችው በተረጋጋ መንፈስ
ቀጠለች “.....በሌላ መልኩ ግን ለዓላማችን መሳካት ስንል እያንዳንዳችን መስዋዕትነትን እስከ መክፈል ድረስ መስራት ይገባናል..... ለምሳሌ እኔ ከአስር ቀን በፊት በበድሉ ህንፃ ላይ በተከራየሁበት ቤቴ ውስጥ የመግደል ሙከራ ተደርጕብኝ ነበር፡፡ ግን አመለጥኩ....”
አቋረጣትና “ሰናይት የትምባይው አንቺ ነሽ!?”
“አዎ”
የዛን እለቱን ስራ የመራው ሰው እሱ መሆኑን ካወቀች ትገድለኛለች ብሎ አሰበና ፍርሀቱ ባሰበት፡፡
ቀጠለች ሰናይት “.....አሁንም ባላሰብኩትና ባለወቅኩት ሰዓት ልገደል እችላለሁ፡፡ የሚያስጨንቀኝ ግን የኔ መሞት አይደለም ስገደል

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ይዤው ወደ መቃብር የምወርደው ማስረጃና ሚስጥር ግን ቀሪ ሆነው ለዚህ ዓላማ የሚታገሉ አባሎችን ሊጐዳ ይችላል፡፡"

ሻለቃው በፍርሀት እየራደ ሞት እንደዚህ የሚያስፈራ መሆኑን ለመጀመሪያ ጊዜ ማሰብ ጀመረ፡፡

"እኔ የትም አልሄድም፤ የትም አልሸሸግምም አሁንም እንደበፊቱ ልረዳችሁ እፈልጋለሁ፡፡ ጳውሎስ ሞተ ማለት ዓላማው ተኮላሸ ማለት አይደለም፡፡ ከጥቂት ቀን በኋላ ወደብ የሚደርስ የጦር መሳሪያ የጫነ መርከብ በጉዞ ላይ ይገኛል፡፡ ጳውሎስ ባይሞት ኖሮ ራሱ ሔዶ እንዲረከበው ተስማምተን ነበር፡፡ ዛሬ እሱ ባይኖርም አንተ አለህ፡፡ ይህን ለትልቅ ዓላማ የተንቀሳቀሰ መሳሪያ አንተ በቦታው ተገኝተህ በመረከብ ለታጋዮቻችሁና ለህብረተሰቡ እንድትሰጥልን ልጠይቅህ ብቻ ነው ቤትህ ድረስ የመጣሁት?"

"እውነትሽን ነው የምታወሪው?"

"ለምን እዋሻለሁ?"

"እኛ ማለትም እኔም ሆንኩኝ ጳውሎስ ወደ መጨረሻው አካባቢ የደረሱን መረጃዎች የወያኔዎች ሰላይ መሆንሽን ነው" አለ ሻለቃው በራሱ የሃሳብ ግጭቶች እየተናጠ፡፡

"ራሴን የመንግስት ሰዎች ሊገድሉኝ ነበር እያልኩህ!..... እየዋሸሁ አይደለም፡፡ አቅሙ ካለህ በዕለቱ ተወስዶ ስለነበረው እርምጃ ድርጊቱን ከፈፀመው ክፍል አጣራ፡፡ በዕለቱ ቤቱን በደባልነት ያከራየችኝ ሴትዬ እኔን ለመግደል መጥተው በነበሩት ፖሊሶች ተገድላች " አለች ሰናይት ሻለቃው ስለ ዕለቱ ሁኔታ ምንም የማያውቅ መሏት፡፡

ሻለቃው በረዥሙ ተነፈሰ፡፡ የእፎይታ ነበር፡፡ በሱ የተመራ ግዳጅ እንደነበረ ያለማወቋ በመጠኑ እንዲረጋጋ አደረገው::

"የጦር መሳሪያውን የመረከቢያው ደብዳቤ ዛሬ እጄ ይገባል ነገ አምጥቼ እሰጥሀለው፡፡ መሳሪያው በሶማሊያ በርበራ ወደብ በኩል ገብቶ የምትፈልገው የኢትዮጵያ ደቡብ ክልል ድረስ እንዲጓጓዝ አስደርግልህ እና አንተ ቦታው ተገኝተህ እንድትረከብ አመቻቻለሁ:: ከዛም በፊልጋችሁት መንገድ መገልገሉ የናንተ ፈንታ ነው፡፡"

"እንዴት በበርበራ ገብቶ ሊደርሰን ይችላል?"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“ሁሉምንም ነገር አመቻችቼላችኋላው፡፡” አለችና ረዥም ደቂቃ ስለ ሁኔታው ስትገልፅለት ቆየች፡፡
ሻለቃው ሙሉ በሙሉ እንዳመነበት ካረጋገጠች በኋላ “አሁን ከፈለክ ልትገደለኝ ትችላለህ ሽጉጥህን እንካ” ብላ የቀማችውን የራሱን ማካሩቭ ሽጉጥ መለሰችለትና ደግናበት የነበረውን የራሷን ሽጉጥ ወገቧ ስር ሻጠችው፡፡ ድርጊቱ ሻለቃው ላይ የበለጠ አመኔታን ፈጠረበት ፡፡
“መነሳት ትችላለህ”
“ለመሆኑ አድራሻዬን እንዴት ለማግኘት ቻልሽ?”
ሰናይት የተሻለ መልስ መስጠት እንዳለባት አሰበችና “ጳውሎስ በተደጋጋሚ ከሌሎች አባሎች ጋር ላስተዋውቅሽ አድራሻቸውም ይኑርሽ እያለ ይጠይቀኝ ነበር፡፡ በወቅቱ አስፈላጊ ስላልመሰለኝ አልሰማሁትም ነበር፡፡ የአንተን ግን ከሚስቱ ነው የተቀበልኩት፡፡ አላውቅም ብላ ላለመናገር በጣም አስቸግራ ነበር፡፡ አስፈራርቼ ነው የተቀበልኳት፡፡” አለችው ስሜን ለማንም ትሰጣለች ማለት ነው ብሎ እንዳይሰጋ፡፡

ሻለቃው ተነስቶ የተንበረከከበት ጉልበቱ አካባቢ የነካውን አቧራ አራግፈና የተበታተኑትን ወረቀቶችን ሰብስበው ሲወጡ ለደህንነቱ ሲል የጳውሎስ ሚስት ላይ ከፍተኛ ፍራቻና ጥርጠሬ ስላደረበት አንድ እርምጃ መውሰድ እንዳለበት እያሰበ ነበር ፡፡
“ደብዳቤውን ነግ ማታ አምጩና ስጭኛ?”
“ይቻላል.....”
“ወደ ከዛንቺስ ከሆንሽ ልሸኝሽ እችላለሁ”
“እሺ.....” ብላ መኪና ውስጥ እንደገባች ቀረቤታቸውን ይበለጥ ለማድረግ “ምሳ አብረን ብንበላስ?” አለችው፡፡
“ማለቂያ ወደሌለው የግምገማ ስብሰባ እየሄድኩ ስለሆነ አልችልም፡፡” ሰዓቱን አየና “እንደውም ረፍዷል፡፡.....ነግ ማታ እራት ግን ይመቸኛል፡፡”
“ጥሩ ስልክህን ስጠኝና እንደዋወላለና ”
“ እሺ ” ብሎ ይነግራት ጀመር፡፡

«««««««« »»»»»»»»

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ሰናይት ከቀኑ ስምንት ሰዓት ሲል ያመራችው ወደ ሂርጳ ቤት ነበር፡፡ ከታክሲው ወርዳ በመሻገር ኮረኮንቻማውን መንገድ መግባት ስትጀምር ከመዞሪያው አካባቢ ባለች አንዲት አነስተኛ ሱቅ መስኮት ላይ ለስላሳ ይዘው የቆሙ ሁለት ወጣቶችን ጉዳዬ ብላ አላየቻቸውም፡፡
"ፎቶውን ስጠኝ!" አለችው ቤቲ አብነትን
አብነት ፈጥኖ አቀበላት፡፡ ያለፈችውን ሴትና ፎቶውን በየተራ ስታይ ቆየችና "ፀጉሯ ከማጠሩ ውጪ ራሷ ነች" አለች፡፡
ሰናይት ቀጥታ ወርዳ የሂርጳን ቤት በር አንኳክታ በማስከፈት ስትገባ አዩዋት፡፡
ሁለተኛው የክትትል ድል በአንድ ቀን ውስጥ ተፈፃሚ ሆነላቸው፡፡

«««««««« »»»»»»»

ሂርጳ ሰናይትን እንዳያት "አንድ ሰዓት ሙሉ ጮልተሽኝ ትጠፋለሽ እንዴ?" አለ በቅሬታ፡፡
"የምን ጉለታ አመጣህ?"
"ይቅርታ መጠየቅ ይገባሻል!"
"ለምን? ስለምንድነው የምታወራው?" አለችው ግራ ተጋብታ
"ምን ሆንሽ..... ሆቴል እንገናኝ ብለሽ ቀጥረሽኝ....." ሀሳቡን አንጠልጥሎ ተወው፡፡
"መቼ?" የተረሳ ቀጠሮ የነበራት መስሏት እየደነገጠች ጠየቀች፡፡
"ጠዋት ደውለሽ ዛሬ ምሳ ልጋብዝህ አላልሽኝም?"
"እኔ?"
"ምን ሆነሻል?"
"በፍፁም እኔ ዛሬ አልደወልኩልህም"
በሂርጳ ላይ ሌላ ድንጋጤ ተፈጠረ፡፡
"ምንድነው ጉዳዩን አብራራልኝ እስኪ?"
ሂርጳ የሆነውን ሁሉ በዝርዝር ነገራት፡
"አንዷ ጓደኛህ እየቀለደችብህ ነበር ማለት ነው፡፡"
"እ...! እ...! እንደዚህ ዓይነት ቀልድማ የለም፡፡"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“ ሌላ ምን ሊሆን ይችላል?.....”
“የአንቺን ስምና የኔን ስልክ የሚያውቅ ሰው በኔ በኩል የለም..... የሆነ አይነት ያልተለመደ ነገር ነው:: በእርግጠኝነት ይህ ነው ብሎ መናገር የማይቻል”
ሰናይት በህሊናዋ ‘ መስፍን ይሆን ? እሱ ደግሞ መሞቱን በስልክ ከሰማሁ ሶስት ቀን ሆኖኛል’ ስትል አሰበች::
“ግራ ያጋባል” ቀጠለች “ይልቅ የመሳሪያው መረከቢያ ደብዳቤ ዛሬ እጄ ይገባል:: ማታ አምጥቼ እሰጥሀለው::”
ሂርጳ በእንጥልጥል የተተወው የቀጠሮ ጉዳይ ውስጥ ውስጡን እያሳሰበው በተነገረው ነገር ተነስቶ በደስታ ጨበጣት::
ለአንድ ሰዓት ያህል ስለተለያዩ ጉዳዮች እያነሱ ሲያወሩ ቆዩና “ማታ ደብዳቤውን አመጣልሀለውኝ” ብላው ለመሄድ ተነሳች::
የጊቢውን በር አልፋ ስትወጣ ሀሳቧ ሂርጳ ቀጥሮት ስለጠፋው ሰው ማንነት ማሰላሰል ጀመረ:: አያይዛም ራሷን ጭምር በአደገኛ ሁኔታ እየተከተለ ያለ አንድ ሀይል መኖሩን በተመስጠ እያሰላሰለች መንገዷን ቀጠለች:: ስለ ተከታዮቹ ማንነት ግን ከፈጣሪና ከባለቤቶቹ ውጪ ለመገመት የሚያስችል ፍንጭ እንኳ አልነበራትም::
ወደ ፒያሳ የሚመለስ ሚኒባስ አስቁማ ተሳፈረች:: በዚህ ጊዜ በርቀት ሲከተሏት የቆዩት አብነት እና ቤቲ ላዳ ታክሲ አስቁመው በኮንትራት መልክ ተስማሙና “ሚኒባሱን ተከተለው” አዘዘው አብነት::
የማዘጋጃ ቤት የላይኛው አጥር በኩል ሚኒባሱ ቆመና የጫናቸውን ሰዎች በጠቅላላ አራገፋቸው::
አብነትና ቤቲም በመውረድ ሰናይትን በሃያ ሜትር ርቀት ክትትላቸውን ቀጠሉ::
ሰናይት አደባባዩ ጋር ስትደርስ ወደ ቀኝ ተጠመዘዘችና ሰዓቷን እያየች በቀጠሮዋ ትክክለኛ ሰዓት ላይ የሚፈለገው ቦታ መድረስ መቻሏን እያሰበች አስፓልቱን ተሻግራ “ፖስታ ቤት” “ሜክሲኮ” “ቄራ” በሚል ሚኒባስ ታክሲ ተሳፈረች:: ታክሲው ቶሎ አልሞላ ብሎ ቢያዘገያትም ቅር አልተሰኘችም:: ምክንያቱም በተቻላት አቅም እንቅስቃሴዎቿን ሁሉ ብዙ ህዝብ ቢመገለገልባቸው ትራንሰፖርቶች እና ቦታዎች ማድረጓን ለእይታ የመጋለጥ እድሏን እንደሚያጠብላት አውቃለችና::

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

የሚከተሏት ወጣቶችም ሌላ ታክሲ ኮንትራት ይዘው የበፊቱ አይነት ትዕዛዝ አዘዙት፡፡

ሚኒባሱ የዋናው ፖስታ ቤት ጋር ደርሶ መስቀለኛውን መንገድ ከመሻገሩ በፊት አቆመና አንድ ሰው አወረደ፡፡ እነ አብነት ሰናይት መሆኗን እንዳወቁ እነሱም አስቁመው ወረዱ "የኛ ሰፈር ደግሞ ምን ትሰራለች? ማንን ለማግኘት ነው እዚህ?" አለች ቤቲ፡፡

ሰናይት ወደ ፖስታ ቤት ተሻግራ በቀኝ በኩል ሚዞረው አስፓልት መንገድ በመታጠፍ ጉዞ ቀጠለች፡፡

ህሊናዋ የሚያስበው የጦር መሳሪያውን የመረከቢያ ደብዳቤው አሁን በተያዘለት ቀጠሮ መሰረት እጇ ከደረሰ ዛሬ ማታና በነገው ዕለት አድላ መጨረስ እንዳለበት ነበር፡፡

ድጋሜ ወደ ፖስታ ቤት መግቢያ ተሻግረችና ቀጥታውን በማለፍ ወደ ቀኝ በምትጠመዘዘው ቀጭን አስፓልት ቁልቁል መውረድ ጀመረ፡፡

የቴሌኮሙኒኬሽን ዋና መስራቤት የመኪና ማቆሚያ የሆነውን የጊቢ አጥር ጨርሳ ሃያ ሜትር ያህል እንደተጓዘች ሰዓቷን ደጋግማ አየች፡፡ ዘጠኝ ከሰላሳ ይላል፡፡የቀጠሮው ሙሉ ሰዓት ይህ ነው፡፡

አንድ ሽንጣምና ግዙፍ የሆነ ሞተር ብስክሌት ከታች ከአምባሳደር መናፈሻ አቅጣጫ የአስፓልቱ መታጠፊያ በኩል አዋኪ ድምፁን እያሰማ ወደ ላይ ሲመጣ ታያት፡፡ የለጠፈው የውጭ አገር ታርጋ ነው፡፡ የሚሾፍረው ሰው ፈረንሳዊው ነበር፡፡ በሞተሩ ግራና ቀኝ ክፍል ላይ የጫናቸው ቁሳቁሶች አገር ጦብኚ አስመስሎታል፡፡

በስተግራው በኩል ካሉት አነስተኛ ሆቴሎች መሀከል ስማቸውን እያነበበ በማለፍ አንደኛው ጋር ሲደርስ ሞተሩን አቆመና መውረድ ጀመረ፡፡

ሰናይትም ስታየው ተሻገረችና ተጨባበጡ፡፡ ነጩ ጥብቅ ያለ ሰማያዊ ጂንስና ቡኒ ቆዳ ጃኬት ለብሷል፡፡ ጫማው የጉዞ ነው፡፡ አይኑ ላይ አቧራ መከላከያ ብሎ የሰካውን ሰፊ የሆነ ጥቁር መነፅር እያወለቀ በፈረንሳይኛ "ውስጥ እንግባ" አለችው፡፡

"እቸኩላለሁ"

"ደብዳቤው ተላከ?" ጠየቀችው

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“አዎ.....” አለውና ከሞተሩ ቀኝ በኩል ካለው ኪስ ጥቁር የሆነ አዲስ ሳምሶናዊት ሻንጣ ማውጣት ጀመረ፡፡
አብነትና ሰናይት እያንዳንዱን እንቅስቃሴ በርቀት ሲከታተሉ ቆዩና “እርግጠኛ ነኝ ሻንጣው ደብዳቤውን የያዘ ነው፡፡” አላት አብነት፡፡
“ምንድነው ማድረግ ያለብን?”
“በዚህ ዕለት እጃችን እንዲገባ ካላስደረግን ትበትነዋለች”
“እኮ በምን መንገድ.....?” አለች፡፡ “እንስረቃቸው?”
“አይደለም..... በፖሊሶች መጠቀም እንችላለን” አላትና በቀኝ በኩል የአንድ ሱቅ መስኮት ላይ ወደታየው የስልክ መደወያ ሮጠ፡፡
ከኪሱ የማስታወሻ ደብተሩን እያወጣ “የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽነር የቢሮ ስልክ ነው” አላትና ተቀምጦ እየቃመ ወደ ነበረው ባለ ሱቁ “ይህን ቁጥር ደውልልኝ.....” ነገረው፡፡
ቁጥሩን ተቀብሎ ደወለለትና “ይጠራል እንሳው” ብሎት ተመልሶ ወደ ጫቱ ተቀመጠ፡፡
“ሀሎ.....”
“የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽነር ቢሮ?”
“አዎ..... ምን ነበር?”
“ኮሚሽነሩን ቢያገናኙኝ የምሰጠው አንድ ጥቆማ ነበር”
“ይጠብቁ” አለችው የኮሚሽነሩ ፀሀፊ፡፡
ጐርናና ድምፅ “ሀሎ”
“ሀሎ..... ከባድ የሆነና አገር የሚጐዳ ወንጀል እየተፈፀመ በመሆኑ በፍጥነት ደርሳችሁ አንድ መፍትሔ እንድትፈጥሩ ለመጠቆም ነበር፡፡”
“ምንድነው ጉዳዩ?”
“ያለፈ ጊዜ በአንድ የግል ጋዜጣ ላይ ታትሞ በነበረና በህቡዕ የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶችን በተመለከተ ጥያቄ ቀርቦልዎት መልስ የሰጡበትን ጉዳይ ያስታውሱታል?”
“የቱ?”
“የአገሪቷን ብጥብጥ ለመፍጠር.....”
አቋረጡትና “አስታወስኩት.....” በድንጋጤ ድምፃቸው እየሰለለች፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“እንቅስቃሴው በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል፡፡ ለዚህ ዓላማ የሚንቀሳቀሱ ግለሰቦች በዚህ ሰዓት ትልቅ ጠቀሜታ ያለው ሰነድ እየተለዋወጡ ናቸው፡፡”
“አሁን!?”
“አዎ”
“የት ቦታ?”

ስፍራውን ከነግለሰቦቹ መለያ ጋር በጥንቃቄ ገለፀላቸውና ድጋሜ እንደሚደውልላቸው ገልፆ ስልኩን ዘጋው፡፡
ሂሳቡን ከፈለና “ቤቲ ይህን አካባቢ እንልቀቅና ታች ማዞሪያው ጋር ሆነን እንከታተል፡፡”
“በቃ በጉዳዩ ፖሊስ ገባበት ማለት ነው?” ጠየቀችው፡፡ ከአሁን በኋላ ሀላፊነቱን ለመንግስት ሰጥተው ወደራሳቸው የግል ዓለም ሊመለሱ መስሎዋት በደስታ ተውጣ ፡፡
“ገና ምኑ ተጀመረና ነይ ይልቅ.....” በፍጥነት እየተራመዱ አልፈዋቸው ወደ አምባሳደር መናፈሻ አቅጣጫ ወረዱና ከመጠምዘዛቸው በፊት አካባቢውን የአደጋ ምልክት በሆነ የፖሊስ መኪና ሳይረን ጩኸት የምትረብሽ አንዲት ሀዩንዳይ ከአምባሳደር መስመር መጥታ ወደ ተባለው ቦታ ታጠፈች፡፡ ጐኗ ላይ “ፖሊስ” የሚል ፅሁፍ ተፅፎባታል፡፡

ውስጧ ሁለት ክላሽ የጨበጡ እና ሁለት ነጭ ለባሽ አባሎች ይታያሉ፡፡

ፈረንሳዊው ሞተሩን በማስነሳት ላይ ነበር፡፡ ሰናይት ሳምሶናዊቱን ይዛ አጠገቡ ቆማለች፡፡ ዞረና ከታች እየከነፈች በመጮህ የምትመጣው መኪና ሲያይ በድንጋጤ ዞረበት፡፡
“ወደኛ ነው መሰለኝ!” በፈረንሳይኛ ጮሆ ተናገረ፡፡
“ውጪ! ውጪ!” አላት፡፡

ሰናይት ሞተሩ ላይ ወጥታ ከመቀመጧ በፊት መኪናዋ ደረሳ የሞተሩን ቂጥ በመግጨት አንሸራታ ጣለችው፡፡ ሞተሩ ግን አልጠፋም፡፡ ፈረንሳዊው በነፍስ አውጭኝ ቅፅበት አነሳውና ሰናይትን ጭኖ ሞተሩን በመመንጨቅ ጉዞ ሊጀምር ሲል አንዱ ነጭ ለባሽ ተወርውሮ ሰናይት ላይ ተጠመጠመባት፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ፖሊሶቹ በዋናው አገር መከላከያ ሚኒስቴር እና ከፊት ለፊቱ በሚገኘው የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን መስራቤቶች አካባቢ ላይ ቅኝት እንዲያደርጉ በእለቱ የተመደቡ ተወርዋሪ የፌደራል አባላቶች ነበሩ። ኮሚሽነሩ በመገናኛ ራዲዮን በተላለፈላቸው ትዕዛዝ መሰረት ሰዎቹን ከነነፍሳቸው ይዘው ማስረከብ እንጂ እንዳይገድሉዋቸውም ታዘው ነበር።

ሰናይት በዮጋ ትምህረቷ ላይ ከጥቃት ራስን እንዴት መከላከል እንደሚቻል በተማረችው መሰርት ከኋላዋ አጥብቆ ተጠምጥሞባት ጎትቶ ሊጥላት ከሚታገላት ፖሊስ ራሷን ለማላቀቅ ብትሞክርም አልቻለችም። አንድ እጇን ወደ ሽንጧ ሰደደችና ድምፅ ማፈኛ የተገጠመለትን ሽጉጥ መዛ ተኮሰችበት። ሰውዬው ደረቱ ላይ ተመታና ሚዛኑን ስቶ ከላይዋ ተንሸራተተ ግን አለቀቃትም። ሞተሩ መሔድ ጀምሯል። ደገመችና ተኮሰችበት። አካሉ ከሷ ላይ ቢላቀቅም በሁለት እጆቹ ሳምሶናዊቱን ታቅፎ መሬት ላይ ወደቀ። እጆቹ ግን የያዙትን አልለቀቁም። ሰናይት የሳምሳናዊቱን እጆታ ይዛ እየጐተጓቱ ጥቂት ሜትር ያህል ሄዱ።

በዚህ ጊዜ ሀዩንዳዋ ውስጥ የነበሩት ሌሎች ታጣቂዎች አስደግንጠው ለማስቆም ክላሺንኮቭ ጠመንጃቸውን ወደ ሰማይ እያንጣጡት ጀመሩ።

ሰናይት ልታስለቅቀው በምታደርገው ትግል፤ በሞተሩ ሀይልና ሻንጣውን በያዘው ፖሊስ ጉትቻዎች ሚዛኗን ስታ በመንሸራተት ለመውደቅ ጥቂት ሲቀራት የሞት ሞቷን ተወራጭታ ከመውደቅ ለጥቂት ተረፈች።

ራሷን ከመውደቅ ለማዳን ያስቻላት ብቸኛ አማራጭ ግን ሳምሶናዊቱን ለቃ በእጇ የፈረንሳዊውን ወገብ መያዟ ነበር።

ታጣቂዎቹ ወደ ሰማይ ባደረጉት ተኩስ ባለሞተሩ እንደማይቆም ሲያዩ አከታትለው ወደ ሞተሩ ተኮሱ። በልምድ የዳበረው የፈረንሳዊው አነዳድ ግን ከኢላማ ውጪ ስላደረጋቸው ሳይመቱ አመለጡ።

ሲቪል ለባሹ ሳምሶናዊቱን አጥብቆ እንደጨበጠ ህይወቱ አለፈች።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ሀዩንዳዋ መኪና ሞተሩን ለመከተል ብትጓዝም በመኪናዎች መካከል እየተሽሎከሎከ የተፈተለከው ሞተር ግን በየት እንዳለፈ እንኳ ለማወቅ የተቻለው ከአንድ ኪሎ ሜትር ባልበለጠ ርቀት ውስጥ ሲሆን ከዛ ቀጥሎ የት እንደገባ ሳይታወቅ ጠፋ።።

ተኩሱ ወደተደመጠበት አካባቢ የተሯሯጡ ቀለም የተቀቡ የመከላከያና የፌደራል ፖሊስ ተጨማሪ መኪናዎች እየተግተለተሉ ጮረፉ።። ስፍራውም በፖሊስ፣ በፌደራል ፖሊስ፣ በወታደሮች እና በደህንነት አባሎች ተጨናነቀ።።

ነጭ ቀለም የተቀባ ላንድ ክሩዘር መኪና በቦታው የደረሰው ከሁሉም ዘግይቶ ነው።። በውስጡ አራት ሰዎችን ጭኗል።። ከአራቱ አንዱ የህዝብ ደህንነት መስራቤት ዋና ሀላፊና ከተክለአይ ቀጥተኛ ትእዛዛትን የሚቀበለው የፌደራል ፖሊስ ዋና አዛዥ ሲሆን በእጁ ሁለት የመገናኛ ራዲዮኖችን ይዟል።።

በዚህ አካባቢ እየተከናወነ ስለነበረው ሁኔታ በፖሊስ ኮሚሽኑ በኩል በመገናኛ ራድዮኑ ነበር የተነገረው።። ራሱ ቦታው ላይ ሆኖ ተፈላጊዎቹን ሰዎች በቁጥጥር ስር እንዳያውል በስራ ምክንያት አራተኛ ክፍለጦር ጊቢ ስብሰባ ላይ ነበር።። ስለዚህም በአቅራቢያው ለተመደቡ አባሎች መውሰድ ያለባቸውን እርምጃ ገልያላቸው ወደ ቦታው እንዲሄዱ አዘዘ።። እሱም ስብሰባውን አቋርጦ በስፍራው እስኪደርስ ሁሉም ተግባር ባልጠበቀው አቅጣጫ ተከናውኖ ቆየው።።

አብነት የታችኛው መዞሪያ ላይ ቆሞ የተፈፀመውን ድርጊት ሲከታተል ቆየና ለቀጣዩ እርምጃው ምን መከወን እንዳለበት ሲያስብ ነጩ ላንድ ክሩዘር ሲያልፍ ተመለከተው።። በውስጡ ሁለት የመገኛ ራዲዮን የያዘውን ሰውዬ ከዚህ ቀደም በቲቪ እና ፎቶውን በተለያዩ ጋዜጣዎች ላይ አይቶታል።።

ይህ ባለስልጣን ከዚህ ቀደም አብነት ከሌሎች በአርት አብረውት ከተመረቁት ጓደኞቹ ጋር በጋራ የስእል ኤግዚቢሽን በኤግዚቢሽን ማእከል ሊያሳዩ ተነጋግረውና ኪራይ ከፍለው ለእንግዶች መጥሪያ ከበተኑ በኋላ አደራሾቹ ለፌደራል ሰራዊት ጊዜያዊ ማረፊያነት ስለሚፈለግ ፕሮግራማችሁን ሰርዙት ብሎ በስልጣኑ በማሰረዝና ለዝግጅቱ የመጡ የሰዓሊያኖች በርካታ ስራ በዝናብ እንዲበላሽ አስደርጎባቸዋል።።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

በወቅቱ ሰውዬውን ለማግኘት ሞክረው ፈቃደኛ ባለመሆኑ በአካል ባያገኙትም በስልክ ግን አብነት በተደጋጋሚ አናግሮት "ኢትዮጵያ መንግስት ወታደር እንጂ ሰዓሊ አይደለም የሚያስፈልገው ! ቀለም ጨርቅ ላይ መለቅለቁን ተዉና እኛ ጋር መጥታቹ ወታደርነት ተመዝገቡ:: በተለይ ለመከላከያ ሰራዊታች የፈንጅ አምካኝ አባላት እጥረት አለብን:: ኑና ተመዝገቡ!" ብሎት ስልኩን ድጋሜ እንዳይደውልበት አስጠንቅቆት ዘግቶበታል:: በዚህም ምክንያት የዚህ ባለስልጣን ስልክ አብነት ጋር ይገኝ ነበር::

አብነት ወድያው የደህንነት ባለስልጣን ራሱ መሆኑን ለየው:: ከእንቅስቃሴው እና ከሚያሳየው ድርጊት ይህንን ግዳጅ በዋናነት የሚመራው እሱ እንደሚሆን ገመተ:: ሀሳብ መጣለት::

ቤቲ ድርጊቱ ወደ ተፈፀመበት ቦታ እንዳፈጠጠች ደርቃ ቀርታለች::

አብነት ስለ ሳምሶናዊቱ እያሰበ ነው::

ወድያው መዞሪያ ላይ ወደ ሚገኝ አንድ ሱቅ አምርቶ የባለስልጣኑን ስልክ ከማስታወሻው ደብተሩ ላይ በማውጣት ደወለ::

"ማነህ አንተ?"

"የደህንነት አባል ነኝ....."

"ምን ፈለክ? "

"ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ለኮሚሽነሩ ጥቆማውን የሰጠሁት እኔ ነበርኩ:: ክትትሉ በናንተ እንደሚደረግ ዘግይቶ ነው መረጃ የደረሰኝ:: ጊዜ የለም አሁንም ቀጣይ ጥቆማ አለኝ..... የማዛችሁን በፍጥነት ማከናወን አለባቹ:: ዛሬ ሁሉም ሰዎች በቁጥጥር ስር የሚውሉበት ቀን ነው::"

"የት ነው ያለኸው አንተ"

"በክትትል ላይ ነው ያለሁት::" አብነት በርቀት ሁለቱንም የመገናኛ ሬድዮ በአንድ እጁ ይዞ በሌላኛው በሞባይ ስልኩ እያዋራው መሆኑ ይታየዋል::

"ክፍልህ የት ነው? "

" ዋ..... አሱን ለመነጋገር በቂ ጊዜ አለን አሁን ጥቆማውን ተቀበለኝ..... አገር በመበጥበጥ ወንጀል የተጠረጠሩ የህቡዕ ፓርቲ አባሎችን በመከታተል ላይ ነኝ::" ቀጠለ አብነት በቁጣ "..... ከአምስት ደቂቃ በፊት በኔ ጥቆማ ነው ሊፈጠር የነበረውን ችግር ደርሳችሁ ያረገባችሁትና ከፍተኛ ሚስጥር የያዘው ሳምሶናዊት ያገኛችሁት::"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“የምን ሳምሶናዊት?”
“ከአመለጡዋችሁ ሁለት ሰዎች ላይ ያስጣላችሁት ነዋ.....”
ሹሙ ዙሪያውን አይቶ ወደ ሳምሶናዊቱ እየተራመደ “ቀጥል አሁን ” አብነት አውቆ ዝም ሲለው “ምንድነው? ቀጥል እንጂ” አለ ተንሰፍስፎ፡፡
“አሁን በምትገኙበት አካባቢ ላይ የምትፈልጉዋቸው በርካታ ሰዎች ከአንድ ሰዓት በኋላ ይሰበሰባሉ፡፡”
“እዚህ?”
“አዎ..... አቅራቢያ ቦታ ላይ.....”
“ለምንድነው የሚመጡት?”
“በሳምሶናዊቱ ውስጥ ያሉትን ማስረጃዎች ለመከፋፈል” ሹሙ በዚህ ጊዜ “ቆይ አንዴ..... ጠብቅ እሞ..... ” አለና ስልኩን ከአፉ ራቅ አድርጎ “እንተ እሱን ሳምሶናዊት ወደዚህ አምጣው!.....” አለ ለቦርሳው የተሻለ ጥበቃ እንዲደረግለት አጠገቡ የነበሩትን አባሎች እያዘዘ፡፡
“ቀጥል....” አብነት እያንዳንዱን ሁኔታ በርቀት ይከታተላል፡፡
“እና በመጀመሪያ አንድ ከባድ ማስጠንቀቂያ ልሰጣችሁ እፈልጋለሁ፡፡ ሳምሶናዊቱ በራሱ ቁልፍ ካልተከፈተ የሚፈነዳ ፈንጅ የተገጠመለት በመሆኑ እንዳይነካካ ከፍተኛ ጥንቃቄ አድርጉ፡፡” አለ አብነት ያሰበውን ከመሞከሩ በፊት ከፍተውት ሰነዶቹን እንዳበይበታተኑ በማሰብ፡፡

ሹሙ በሰማው ማስጠንቀቂያ ደንግጥ አለና ከሳምሶናዊቱ ለመራቅ በማያስታውቅ ሁኔታ ተራመደ፡፡
“ቁልፉ ማን ጋር ነው ያለው?”
“እንደነገርኩዎ ከአንድ ሰዓት በኋላ አምስት ከፍተኛ የሆኑ ህቡዕ ፓርቲ ሀላፊዎች ይመጣሉ፡፡ ቁልፉም ያለው እነሱ እጅ ነው፡፡”
“እዚህ ከደረሱ በኋላ ሳምሶናዊቱን ከማንና በምን አይነት መንገድ ነው የሚረከቡት?”
“ወደ አምባሳደር መናፈሻ ተመልሳችሁ ስትወጡና ወደ ዘውዲቱ ሆስፒታል የሚታጠፈውን አስፓልት ታገኙታላችሁ፡፡”
“እሺ.....”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“ልክ እንደታጠፋችሁ ከዘውዲቱ ሆስፒታል አጥር ጋር የሚያገናኝ ወንዝ አለ፡፡”
“አዎ አውቀዋለሁ፡፡”
“በቃ የዘውዲቱ ሆስፒታል አጥር ጫፍ ለመድረስ ጥቂት ሲቀረው ማዘጋጃ ቤት ያስቀመጠው አንድ የደረቀ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ትልቅ የብረት ገንዳ አለ የተፋፋቀ ቢጫ ቀለም ነው የተቀባው፡፡ በቀጥታ ሳምሶናዊቱን ወስዳችሁ እሱ ውስጥ ጣሉትና በቅርብ ሜትር ርቀት ላይ አካባቢውን በነጭ ለባሾች አስጠብቁት፡፡ አምስቱ ሰዎች በቀጠሮዋቸው ሰዓት መሰረት በመኪና አንድ ላይ ይመጡና ከገንዳው ውስጥ አውጥተው ሲወስዱት እጅ ከፍንጅ ልትይዟቸው ትችላላችሁ፡፡”
ሹሙ በማመንና ባለማመን ስሜት ተከፍሎ በዝምታ ሲያዳምጥ ቆየና “ለምንድነው በቆሻሻ ገንዳ የሚቀባበሉት?”
“እርስ በእርስ ስለማይተማመኑ ሁሉም በአንድነት በተመሳሳይ ሰዓትና ቦታ ተገናኝተው ሊረካከቡ ነው የተስማሙት፡፡ የመረካከቢያ ብቸኛው መንገድን አሁን የተናገርኩት ብቻ ነው፡፡ ”
ቀጠለ አብነት “.....እኔ ከነሱ ጋር የነሱ ሰው መስዬ ለመንግስት የምሰራ አባል ነኝ፡፡ አሁን ሰዎች ወደኔ እየመጡ ስለሆነ መልሼ እደውላለሁ፡፡ ምንም ስህተት እንዳይፈፀም፡፡ ይህንን ተግባር ፈፅማችሁ እነሱን በቁጥጥር ስር እንዳዋላችሁዋቸው ደግሞ ሌላ ጥቆማ እሰጣችኋለው፡፡”
“እሺ ጌታዬ.....” አለ ሹሙ፡፡
አብነት ስልኩን ዘጋው፡፡ ሂሳቡን ከፈለና “ነይ ቶሎ በይ”
“ወዴት?”
መልስ ሳይሰጣት ወደ ሽራተን የሚወስደውን አቅጣጫ ተከትሎ በፍጥነት መራመድ ጀመረ፡፡
ሹሙ በአካባቢው ላይ ያሉትን ሚሊቴሪ የለበሱ ፖሊሶች እና ወታደሮችን ከነመኪናዎቻቸው ወደየ ሰዋራ ቦታዎች ተበትነው የደፈጣ ጥበቃን በዙሪያው እንዲያደርጉ አዘዘ፡፡
ሳምሶናዊቱን በሚያስቀምጥበት ገንዳ አካባቢና በዙሪያው ደግሞ ቁጥራቸው ሀያ የሚደርስ የታጠቁ ሲቪል ለባሾችን አሰማራ፡፡
የጥበቃውን ሁኔታ በሚገባ አቀናጅቶ ከፈፀመ በኋላ መኪናው ውስጥ በመግባት ወደተባለው ገንዳ አመራና ተጠግቶ በማቆም ወረደ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

የሰውን ትኩረት እንዳይስብ ተጠንቅቆ ከገንዳው አራት ክዳኖች መካከል አንዱን ከፍቶ ሳምሶናዊቱን ከመክተቱ በፊት ተመለከተ፡፡ ከጥቂት ካርቶን እና ወረቀቶች በስተቀር ቆሻሻ የሌለው ሲሆን በዙሪያው ተጣብቀው ከደረቁት ቆሻሻዎች የሚነሳው ግማት ግን አንጐል ይበጠብጣል፡፡

በግማቱ ምክንያት ምራቁን አስፓልቱ ላይ እየለጠፈ በመኪናው አብሮ ተጭኖ የመጣውና አባል ጠራና “ውስጡን ግባና ፈትሸው!” ሲል አዘዘው::

ሲቪል የለበሰው ታጣቂ በፍጥነት ዘሎ በመግባት ወረቀት እና ካርቶኖቹን ሲያተረማምስ ቆይቶ ግማቱ እያጥወለወለው በመውጣት “ከቆሻሻ በስተቀር ምንም የለም ” አለ:: ወድያው ወደ ወንዙ አቅራቢያ ዞሮ ማስታወክ ጀመረ:: ሹመ በንቀት እያየው ሳቀበትና ሌላ አባል ጠርቶ “ሳምሶናዎቱን ገንዳ ውስጥ በጥንቃቄ አስቀምጠው!” አለ

የታዘዘው አባል ሳምሶናዊቱን ከተተውና ክዳኑን ዘግቶ ወደ መኪናው ተመለሰ፡፡ ወድያው መኪናውን አስነስተው በመናፈሻው በኩል በሚገኙ ካፌቴሪያ በር ላይ አቁመው የተባሉትን ሰዎች መጠባበቅ ጀመሩ::

አብነት ያዘዘውን መፈፀሙን እንዳረጋገጠ መስቀለኛውን አስፓልት ተሻግሮ ወደ ሽራተን ሆቴል የሚያደርሰውን ዳገትማ መንገድ ተያያዙት፡፡ ከዛም በሆቴሉ አቅጣጫ ተሻገሩ፡፡
የሆቴሉ የታችኛው አጥር ድንበር ጋር ሲደርሱ “እንቺ እዚህ ጋር ትጠብቂኛለሽ”
“የት ልትሔድ?”
“ሳምሶናዊቱን ይዤው ልመጣ”
“እንዴት?”
የሆቴሉ ታችኛው አጥር ድንበር ጋር ሲደርስ ቆም አለና “ጠብቂኝ!” ጫን በሚል ቅላፄ ነገራትና ከእግረኛው መሂጃው መንገድ በዘንባባዎቹ መሀከል አልፎ ወደ መኪና መሂጃው አስፓልት ኮሪደሩ ጋር ለመድረስ ጥቂት ሲቀረው ቆመ፡፡

በተለምዶ ፊት በር እየተባለ ከሚጠራው ሰፈር አንስቶ በሽራተን ሆቴል በር አቅጣጫ በማድረግ ቁልቁል የአስፓልቱን የጐርፍ ፍሳሽ እየተቀበለ በማንሸራተት ከዘውዲቱ ሆስፒታል ጀርባ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

የሚገኘው ትልቅ ወንዝ ውስጥ የሚያስገባ ሰፊ ትቦ መቀበሩን ያውቃል።

በኮሪደሩ አቅራቢያ ወደ ተቀበረው ትቦ ቁልቁል የሚያስገባ መውረጃ ሲኖረው ይህም መውረጃ በትልልቅ ክብ ቅርፅ ባላቸው ክዳኖች ተዘግቷል። አንዳንድ የአካባቢው ህፃናት እና ጎዳና ተዳዳሪዎች በዚህ በሆቴሉ የታች አጥር ድንበር አቅራቢያ የሚገኘውን የትቦ ክዳን ከፍተው በመግባ በትቦው ውስጥ ለውስጥ ተጉዘው በወንዙ በኩል እንደሚወጡ አይቷል።

ባለፉት ቀናቶች ውስጥ ደግሞ ቂጡ የተነደለ የቆሻሻ ገንዳ በማዘጋጃ መስራቤት የቆሻሻ ማንሻ መኪና መጥቶ የዘውዲቱ አጥር አቅራቢያ ሲቀመጥ የዚህ ገንዳ ቂጥ የአንዱ ትቦ ክዳን ላይ በማረፉ የጐዳና ተዳዳሪ ህፃናትም መጀመሪያ ወደ ገንዳ ው ቀጥሎም የትቦውን ክዳን በመክፈት እየገቡ ሲጫወቱበት ተመልክቶ አዝኗል።

ዛሬ ግን አጋጣሚ የሚባል ነገር የለም ሁሉም ነገር ጥቅም እንዳለው አምኗል።

ድጋሜ ወደ ቤቲ ዞረና "መጣሁ ጠብቂኝ" ብሎ ብረቱን የቱቦ ክዳን ከፍቶ ገባና ዘጋው። ማንም አላየውም። ከዛም በፍጥነት አጎንብሶ ወደ ታች አቅጣጫ ጉዞ ጀመረ። የአንድ ሜትር የዙር ስፋት ያለው ትቦ እምክ እምክ ይገማል።

ውስጡ ጨለማ ነበር። በርቀት በርቀት ላይ ግን ዘርዛራ የሆነ የውሃ ማስገቢያ ክዳኖች በተከደኑበት በኩል ብርሃን ሲገባ ይታያል። መጠነኛ የሆነ ቆሻሻ ውሃ እየተሸኳለለ ወደ ወንዙ አቅጣጫ ይወርዳል።

የሚፈልገው ቦታ ላይ መድረሱ የክፍለ አገር ጉዞ ያህል ራቀበት። እየተሳሳተ ሌሎች ክዳኖች ጋር በደረሰ ቁጥር ገፍቶ ለመክፈት ይሞክራል። ብዙዎቹ ግን በአስፓልቱ ጥገና ወቅት ጠርዛቸው ሬንጅ ስለለበሰ አይከፈቱም። አልከፈት ባሉት ቁጥር ሁሉ ቦታው ገና መሆኑን እያሰበ ቁልቁል ወረደ። መጨረሻ ላይ የሚፈለገውን የቱቦ ክዳን አገኘው። ለመክፈት ሲሞክር ብዙ አላታገለውም። ምክንያቱም በዚህ ክዳን በኩል ለመግባት ህፃናቶች በተደጋጋሚ እየከፈቱ ይዘጉት ስለነበረ ነው።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

አብነት በፍርሃት እየራደ በተከፈተው የቱቦ ክዳን በኩል ወደላይ ወጣ። ከዛም በተነደለው የቆሻሻ ገንዳ ቂጥ ውስጥ ብቅ አለ። ሳምሶናዊቱ ጠርዝ ላይ ተቀምጧል። ተንጠራርቶ እጆታውን ጨበጠና በገባበት በኩል ተመልሶ ወረደ። ከዛም የትቦውን ክዳን እንደነበረው ዘግቶ ወደላይ አቅጣጫ መሮጥ ጀመረ።

ጉልበቱ ተንጠፍጥፎ ያለቀ እስኪመስለው ድረስ ተዝለፈለፈ። ተጣጥሮ በመገስገስ ሲገባ ቦታው እንዳይጠፋበት ምልክት ያስቀመጠበት የቱቦ ክዳን ጋር ደረሰ።

መክፈት ሲጀምር ቤቲ አገዘችው።

"ተቀበይኝ"

የምታየውን ማመን አቃታት። እየተርበተበተች ሳምሶናዊቱን ተቀበለችው። እየተሳበ ወጣና ክዳኑን መዝጋት ሲጀምር በዚህ ቱቦ ውስጥ እየገቡ ከሚጫወቱት የጦዳና ተዳዳሪ ታዳጊዎች መካከል እድሜያቸው ከአስራ አምስት የማይበልጥ ሁለቱ አብነትን ቆመው አዩት።

"ጥፋ ከዚህ!" ጮኸባቸው።

ድርጊቱን የለመዱት በመሆኑ ብዙም ሳይስባቸው ወደታች መውረድ ጀመሩ።

"ሂጂ አንቺ..... እደርስብሻለሁ" አላት።

ኮፍያው ቱቦ ውስጥ በመውደቁ በድሬድ ፀጉሩ በልብሱና የፊቱ ገፅ ላይ የተጠረጉት ጭቃና ቆሻሻ በትክክል ያበደ ሰው አስመስሎታል። ኮቷን በማውለቅ ሳምሶናዊት ቦርሳውን እንዳይታይ ሸፈነችበትና ቀድማ አስፓልቱን ተሻግራ መጓዝ ስትጀምር አብነትም ለመሔድ ተነሳ። ባልና ሚስት የሆኑ አገር ጐብኚ የጃማይካ ተወላጆች ከሆቴሉ ወጥተው ቁልቁል እየወረዱ ነበር። አብነት አላያቸውም። ወንዱ ጃማይካዊ ወደ ሚስቱ ዞረና "ፀጉሩ በጣም ያምራል..... ግን ንፅህና ይጐድለዋል።" ብሎ ያነጣተውን ካሜራ በማስተካከል አብነትን በጐን በኩል አቅርቦ ፎቶ አነሳው። እሱ ግን አላያቸም።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

የደህንነት ሹሙ የተባለው ሰዓት አልፎ ለተጨማሪ ግማሽ ሰዓት ይመጣሉ የተባሉትን ሰዎች ለመያዝ እንደቋመጠ በርቀት ሲንቆራጠጥ ቆየ፡፡
'አንድ መረጃ ደርሷቸው መቅረታቸው ይሆናል' ብሎ አሰበ፡፡
የመገናኛ ራዲዮን አውጥቶ በአካባቢው ላይ የተሰማሩ ሀይሎች እንዲበተኑ አዘዘና ወደ ገንዳው መራመድ ጀመረ፡፡ ደርሶ ክዳኑን ሊከፍት አለና የቅድሙ ሽታ ታውሶት አንዱን የበታች ባልደረባውን በመጥራት ሳምሶናዊቱን እንዲያመጣ አዘዘው፡፡
ገብቶ ሲፈልግ የቆየው አባል "የለም!" አለ፡፡
"ምን ታወራለህ?....." ብሎ በመጠጋት ዙሪያውን ሲያይ ሻንጣው ያለመኖሩን አጣራ፡፡ አጥወለወለው፡፡ ወደ ወንዙ እንኳ አላደርስ ብሎት ሲጠጣ የቆየውን ሁለት ብርጭቆ ስፕሪስ ጁስ ከላቆጠ ሁለት ቦምቦሊኖ ኬክ ጋር በላዩ ላይ ማስታክ ጀመረ፡፡ መናፍስት ካልሆነ በስተቀር ሰው በአካባቢው ዝር እንዳላለ ቆሞ አይታል፡፡ ነገሮች ህልም መሰሉት፡፡
ራሱን ወይም አይኖቹን ከመጠራጠር ነፃ ሊሆን ግን አልቻለም፡፡ የመገናኛ ራዲዮኑን ከፈተና "ግዳይ 200....." ደግሞ ተጣራ፡፡ ከመከላከያ ሰራዊት ለዚህ ግዳጅ ዝግጁ እንዲሆን የተቀናጀውን ክፍል እንዲመራ ኃላፊነት የተሰጠው ኮነራል ጥሪው ለሱ መሆኑን እንዳወቀ "ቀጥል" አለ፡፡
"ከፍተኛ ወንጀል ተፈፅሟል ከአሁን ጀምሮ የሰራዊቱ ሀይል አብሮን መስራት አለበት"
"የት ጋር ነው ቦታው?"
"ከመከላከያ ሚኒስትር ወደ ሽራተን ሆቴል በሚወስደው አካባቢ ላይ"
"ምን እርምጃ ይወሰድ?"
"በአካባቢው ያሉት ወጣቶች በጠቅላላ እየታደኑ ከየቤታቸው ይጫኑ!"
"ወዴት?"
"እስኪለገፅ የተባለውን አድርግ!"
"አሁኑኑ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡"
ወድያውኑ በየአቅጣጫው ረጭሯምና አስፈሪ የሆኑ የጦር ሜዳ ካሚዎን መኪናዎች እያጓሩ ደረሱ፡፡ በላያቸው ሙሉ ትጥቅ ያነገቡ ወታደሮችን ጭነው ነበር፡፡ ከዛ ቅፅበት ጀምሮ በአካባቢው ላይ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

የተገኘም ይሁን የአካባቢው ወጣት የሆነ ሁሉ ኢሰብአዊ በሆነ መንገድ በመሳሪያ ሰደፍ እየተፈነከተና እየተደበደበ ታፍሶ ለህብረተሰቡ ወዳልተገለፀ ስፍራ መጋዝ ጀመረ፡፡

እንደታጠበ ሸማ ድህነት ጨምቆ የመከራ ሀሩር ላይ ያሰጣቸው የሚመስሉት የአካባቢው እናቶችም ቅስማቸው ቅጭም ብሎ በመከራ ያሳደጓቸው ልጆቻቸው በሚዘገን መልኩ በወታደር እና ፌደራል ፖሊስ አባላቶች እየተጨፈጨፉ ሲታፈሱ በማየት በደረታቸው አስፓልቱን እያሰሱና ማህፀናቸውን ጨብጠው ልጅ ያፈራበትን ቀን እየረገሙ እንባ ተራጩ፡፡ በዘመኑና በአገዛዙ ነፍሳቸው እስኪኮታኮት ድረስ አዘኑ፡፡

  

የማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ምዕራፍ 39

በአምስቱ ካሚዮን መኪናዎች ተጠቅጥቀው የተጋዙት ሰዎች “ታጠቅ” በሚባለው የጦር ማሰልጠኛ ጊቢ ተራገፉ። ያመጧቸው ካሚዮኖችም ሌላ ትዕዛዝ ተቀብለው ከጊቢ ወጡ።

ሰዓቱ ከምሽቱ አንድ ከሃያ ብሏል። በረጣሹሞቹ የባህር ዛፍ፣ የጥድና የዝግባ ዛፎች መካከል የሚነፍሰው ነፋስ አጥንት ድረስ ሰርስሮ ይገባል።

የጅብ ጩኸት ከየተራራው ላይ ዙሪያውን ይሰማል። የታፈሱት ወጣቶች ከተዘረገፉበት ሰፊ ሜዳ ትይዩ በድንጋይ የተሰሩ ሰፋፊና ረጣሹም አዳራሽ መሰል ቤቶች በብዛት ይታያሉ።

የጥበቃው ወታደሮች ሙሉ ትጥቃቸውን አንግበው ሁለትና ሶስት በመሆን በጊቢው ውስጥ ሲዘዋወሩ ይታያሉ።

ድንገት ታፍሰው የመጡት በጠቅላላ በሽብር ተውጠዋል። ለምን እንደተያዙና ወደዚህ ስፍራ እንደመጡ የሚያውቅ የለም። በእድሜ አስር ዓመት ከሚሆነው ታዳጊ አንስቶ ወጣቶች፤ ጐልማሶች እና ሽማግሌዎች ጭምር ይገኙበታል። አብዛኛዎቹ ግን ከሃያ እስከ ሰላሳ አምስት ዓመት የሚሆናቸው ናቸው። አብዛኛው የአከባቢው ነዋሪ ወጣት ሲሆን ከስራ ወደ ቤት የሚያመሩ፤ ከትምህርት ቤት የሚመለሱና በአካባቢው ሲተላለፍ የተገኙም አሉበት። ሁሉም በፍርሃትና ግራ በመጋባት የሚሆነውን በመጠበቅ ላይ ሳሉ በርቀት የካሚዮኖቹ ድምፅ መስማት ጀመረ።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

መኪናዎቹ እነሱ ከተቀመጡበት አካባቢ መቶ ሜትር ላይ ሲደርሱ እየቆሙ ሞተራቸውን አጠፉ፡፡ ሁሉም የገመቱት በሁለተኛው ዙር ታፍሰው የመጡ ሰዎች ይሆናሉ ብለው ነበር፡፡

የመጫኛቸው የኋላው መዝጊያ ተከፍቶ መውረድ ሲጀመር ግን ድንጋጤያቸው ናረ፡፡

አምስቱም ካሚዮኖች የፌደራል ፖሊስ ሰራዊቶችን ነው ማራገፍ የጀመሩት፡፡ ወርደው ሲያበቁ በአንድ ቦታ ላይ እንዲሰባሰቡ ታዘዙና በአዛዡ መመሪያ ተሰጣቸው፡፡

ጥቂቶቹ ክላሺንኮቭ ጠመንጃቸውን እንደታጠቁ በተመረጡ ቦታዎች ላይ ተበታትነው ታፋሾቹን በመክበብ ቆሙ፡፡

ሌሎቹ ደግሞ ወደ ታፋሾቹ ቀረቡና ተነስተው እንዲቆሙ በማዘዝ በሃያ ረድፍ ከፋፍለው አሰለፋቸው፡፡ ከዛም ወደ ተለያዩ አዳራሾች ይዘዋቸው በማምራት አስገቡዋቸው፡፡

የየአዳራሾቹ ወለል አቧራው እንደ ጢስ ይበናል፡፡ ሁሉም ማሳልና ማስነጠስ ጀመረ፡፡ በየጥጋጥጉ የተነቃቀሉ እንጨቶች ጣውላዎችና ቁርጥራጭ ብረቶች ርቀት ላይ ከተንጠለጠሉት ፍሎረሰንት መብራቶች በሚወጣው ብርሃን አማካኝነት ይታያሉ፡፡ አዳራሾቹ የውስጥ ግድግዳቸው መፈራረስ ጀምሯል፡፡

እያሰለፉ ያስገቡዋቸው የፌደራል ፖሊሶች የየቡድኑ መሪ ባሻቸው መንገድ ተጠቅመው ምርመራውን በመፈፀም እንዲያመጡ የታዘዙትን መረጃ ለማግኘት በመጀመሪያ ወደ ሁሉም አዳራሾች ለገቡት ታፋሾች ያቀረቡላቸው ጥያቄ አንድ አይነት ነበር፡፡ “በሰፈራችሁ ላይ ከፍተኛ ሚስጥር የያዘ የመንግስት ሻንጣ ተሰርቋል፡፡ የወሰደ ካለ ስለማይጠቅመው ይመልስ፡፡ ሌላ ሰው ሲወስድ ያየ ካለ ደግሞ ይንገረን” የሚል፡፡

የታፈሰው ወጣትና ጐልማሳ ሁሉም ግራ ተጋብቶ እርስ በእርስ ከመተያየት ውጪ ሊሰጥ የሚችለው መልስ አልነበረውም ፡፡

የልዩ ሀይል አባሎቹ እርምጃ እንዲወስዱ ታዘዙ፡፡ በየቦታው የወዳደቀውን እንጨትና ብረት እንደ ዱላ እያነሱ በሰው አካል ላይ ካለ ርህራሄ ያሳርፉት ጀመረ፡፡ አዳራሾቹ በጩኸትና በዋይታ መናወጥ ቀጠሉ፡፡ በአገኙት እቃ ያገኙት ሰው አካል ላይ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ያሳርፉበታል፡፡ ጭንቅላት፣ ቅልጥም፣ ጐድን፣ አከርካሪ፣ ግንባር፣ ክንድ..... ምርጫ የለም፡፡ ደም እንደ ውሃ ፈሰሰ፡፡

የህዝብ ደህንነቱ መስራቤት ዋና አዛዥ በንዴት እንደበገነ እዛው ታጠቅ ጊቢ በሚገኝ ቢሮ ውስጥ ተቀምጦ ከምርመራው የሚመጣለትን ውጤት ትዕግስት ባጣ ሁኔታ ይጠብቃል፡፡

ስልክ ደውሎ ያሳሳተውን እንደ ጅል ያቄለውን ሰው ከደረሰበት እንዴት አድርጐ በመበቀል ስሜቱን ሊያረካ እንደሚችል ግራ ገብቶታል፡፡ ሀሊናው ‘በእሳት ማቃጠል..... በዘይት መጥበስ..... ቤተመንግስት ጊቢ ላሉት አንበሶች መወርወር.....’ ብቻ ሁሉም እርካታን ሊያጐናፅፉት የሚችሉ አልመሰለውም፡፡

ኢ-ሰብአዊ የሆነው ድብደባ እስከ እኩለ ለሊቱ ስድስት ሰዓት ድረስ ቀጠለ፡፡ እስካሁን ምንም የተገኘ ነገር አልነበረም፡፡

አዛዡ ከፊቱ ባለው ጠረጴዛ ላይ ካስቀመጣቸው ሁለት የመገናኛ ራዲዮ መካከል የአንዱን መስመር ተከፈተና
“ግዳይ 200.....ግዳይ 200” ተጣራ፡፡
“ቀጥል.....ምንድነው?”
“ጌታዬ ሁለቱ ግለሰቦች ያመለጡበት ሞተር ብስክሌት ተገኝቷል፡፡”
“የት ተገኘ.....ፍንጭስ አለው!?”
“ራስ መኮንን ድልድይ አቅራቢያ ላይ ነው፡፡ ሙሉ በሙሉ በእሳት ተቃጥሏል”
“ማነው ያቃጠለው!?”
“አይታወቅም፡፡ ምናልባትም ራሳቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡”

አዛዡ በሌላ በኩል ለአደና እንሞክርበታለን ያለው አማራጭ ይህ ነበርና ተስፋው ከሞተሩ ጋር አብሮ ተቃጥሎ ሲጠፋ ታሰበው፡፡ ሰዎቹ ፈፅሞ ዱካቸውን እየጣሉ የማይሔዱ አደገኞች መሆናቸውንም አመነ፡፡

ክትትሉ በማንኛውም መንገድ እንዲቀጥል በማዘዝ ራዲዮኑን ዘግቶ እንዳስቀመጠው የቢሮው በር ተንኳኳ፡፡
“ማነው.....ግባ.....”

ሁለት የልዩ ሀይሉ አባሎች ድሪቶ ያንጠለጠሉ ሁለት እድሜያቸው ከአስራ አምስት ዓመት የማይልቁ ታዳጊዎችን ይዘው ገቡ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

የአንደኛው ታዳጊ ጭንቅላት ተፈንክቶ የሚፈሰው ደም ፊቱን በመሸፈን ልብሱ ላይ መፍሰስ ጀምሯል። የሁለተኛው ደግሞ የፊቱ ግማሽ ገፅታ በአሰቃቂ ሁኔታ አብጦ ሊፈርጥ የደረሰ እስኪመልስል ድረስ ከፍተኛ ድብደባ ተፈፅሞበታል። ከንፈሩም በአንደኛው አቅጣጫ ተሰንጥቆ ደም ይፈሰዋል።

ሁለቱም ወደ ቢሮው እንደደረሱ መቆም አቅቷቸው ወለሉ ላይ ወደቁ።

"ምንድናቸው?" አለ አዛዡ።

"ሻንጣውን የያዘው ሰው ከቱቦ ውስጥ ሲወጣ አይተነው ነበር ነው የሚሉት" አለ አንደኛው አባል እየተቅለሰለሰ።

"የምን ቱቦ አመጣችሁብኝ!?" በቁጣ ጠየቃቸው።

"ስለጉዳዩ ራሳቸው እንዲገልፁ ነው ያመጣናቸው።" አለ ሁለተኛው አዛዡ ወደ ልጆቹ ዞረና "የምን ቱቦ ነው?"

"እዛ..... ከሽራተን ወረድ ብሎ ከሚገኝ ትቦ..... ውስጥ..... አንድ ፀጉሩን እንደ ራስታዎች ያሳደገ ሰውዬ ጥቁር ሻንጣ..... ይዞ በመውጣት ለአንዲት ሴትዮ..... ሲያቀብል አይተናል" አለ ፊቱ ያበጠው ታዳጊ ድምፁ ገና በለጋ እድሜ መጠቀም በጀመራቸው ሲጃራ ጫትና አደንዛዥ ዕፅ ምክንያት ጐርንኗል።

"እንዴት ሊሆን ይችላል.....? እኛ ያስቀመጥነው ታች ወንዙ ጋር በሚገኝ አንድ ገንዳ ውስጥ ነው።"

ታዳጊው ያበጠ ፊቱን እያሻሸ በየዕለቱ በቱቦዎቹ ውስጥ ለውስጥ የሚያደርጉትን ጨዋታ ገለፀለት። ስላላመናቸው በአካባቢው ላይ ለነበሩት ተወርዋሪ አባሎች እውነታውን እንዲያጣሩ በመገናኛ ሬድዮኑ አዘዘ። በዚህ ጊዜ ነበር ገንዳው የተቀመጠበት መሀከል ቦታ ላይ የቱቦ ክዳን የሆነ ብረት መኖሩን ያስታቁት።

በቦክስ ጠረጴዛውን ደልቆ ተነሳ። በጠባቧ ቢሮ ውስጥ እየተንቆራጠጠ ቆየና "ሰውዬው ምን ዓይነት ነው?" ጠየቃቸው።

"እንደ ራስታዎች ፀጉሩን ያሳደገ....."

"ሴቷስ!?"

"እ.....ቀይ.....ሆና....እ....አንድ ዓይነት በአንድ ዓይነት ልብስ የለበሰች.....እ...."

አዛዡ አቋረጠውና "ፊቷ ላይ ልዩ ምልክት የለባትም?"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“እ..... እኔንጃ”
ወደ አባሎቹ ዞረና “ምርመራውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ ንገሩዋቸው፡፡ ሌላ ጥሩ ፍንጭ ይገኝ ይሆናል፡፡” ብሎ አዘዘና አንደኛውን መገናኛ ራዲዮ በማንሳት ከፌደራል ፖሊስ እና ከደህንነት መስራቤቱ ጋር የሚያገናኘውን መስመር በመክፈት “ግዳይ 200”
“ይቀጥሉ.....”

“በአዲስ አበባ ውስጥ የሚገኙ ፀጉራቸውን እንደ ራስታዎች ያሳደጉ ሰዎች በጠቅላላ በቁጥጥር ስር እንዲሆኑ”
“ኢትዮጵያዊያኖችን ብቻ ነው ወይስ የውጭ ዜጋዎችን ጭምር?”
ከመስራቤቱ ጋር ከሚያገናኘው ራዲዮ የመጣለት ጥያቄ ነበር፡፡
“ሁሉንም!”
“የውጭ ዜጋዎችን መያዝ የዲፕሎማሲ ችግር አይፈጥርብንም?”
“መጀመሪያ መኖር ሲቻል ነው ስለ ዲፕሎማሲ የሚታሰበው.....” ቀጠለ “..... የምንፈልገውን ሰው ካገኘነው ቀሪዎቹን በስህተት ይዘን ስላጉላላናቸው ይቅርታ ጠይቀን እንለቃቸዋለን..... ያለው አማራጭ ይህ ብቻ ነው፡፡ በፍጥነት አደናው ይጀመር በሆቴሎች ጭምር!..... ትዕዛዙ ደግሞ በመላው የአዲስ አበባ የፖሊስ ጣቢያዎቹ አሁኑኑ ይተላለፍ” አለ፡፡

ልጆቹን ይዘው ከገቡት አባሎች መካከል “አንዱ እነዚህን ምን እናድርጋቸው?”
“ለድጋሜ ማስረጃነት ስለምንፈልጋቸው ሙሉ ማንነታቸውን እዚህ ጋር ፃፍልኝ” ብሎ ፎርም መሰል ወረቀት ለአንዱ የፌደራል ፖሊስ አባል ሲሰነዝር እኔ መፃፍና ማንበብ አልችም ጌታዬ” አለ፡፡
ለሌላኛው አባል ሲሰነዝር ተቀብሎት ፎርሙን ለመሙላት እየተዘጀ ወደ አንዱ ታዳጊ ልጅ ዞረና “ስምህ ማነው?!”
“ዲፊንጮ”

“ምን ማለት ነው ዲፊምጮ?! ” ፌደራሉ ጠየቀው መፃፉን አቁሞ እያሾፈበት መስሎት ለመማታት እየተሰናዳ
“ስሜ... ነው...” ታዳጊው በፍርሀት መለሰ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ዋናው ጎላፊ ጣልቃ ገባና "አታ እውነተኛ ስምህን ተናገር እሞ...!" አለ በቁጣ
"ሁሉም እንደዛ እያለ ነው የሚጠራኝ ሌላ ስም የለኝም"
"ምን ማለት ነው?
"ድፍጥጥ አፍንጫ ማለት ነው" አለ ጓደኛው ጣልቃ ገብቶ
የሚፅፈው አባል "እድሜህ ስንት ነው?!"
"አስራ አራት"
"ብሔርህ ምንድነው?!"
"ኢትዮጵያ"
"ዝጋ...!!! " አምባረቀ ጎላፊው። ቀጠለ በቁጣ "... ወዲ ሽርሙጣ ኢትዮጵያ የሚባል ማንነት የለም! ገባህ...?!" ታዳጊው ምን ለማለት እንደተፈለገ አልገባውም ስለፈራ ብቻ "እሺ" አለ። ቀጠለ ጎላፊው "አባትህ ምንድነው?!
"አላውቀውም አባቴን "
"የእናትህስ ብሔር?! "
"እሷንም አላውቃትም። አንድ የሚለምኑ ሴትዮ ናቸው ከመንገድ ላይ አገኘሁህ ብለው ያሳደጉኝ" አለ ታዳጊው ድጋሜ እንዳይቀጠቅጡት እየተርበተበተ።

"ያሳደገችህ አሮጊትስ ብሔሯ ምንድነው?!"
"እኔንጃ.... ምንም ሳይነግሩኝ ነው ያለፈው አመት የሞቱት..... ግን እንደኔ ኢትዮጵያ ይመስሉኛል ምክንያቱም ምንም ዘመድ የላቸውም ነበር። አባዲና ነው ሬሳቸውንም ከመንገድ ላይ የወሰደው።"
"አባዲና ይብላህ ሀድጊ?! ጠማማ! " ብሎ ተሳደበ ጎላፊው።
ፎርሙን ሲሞላ የነበረው አባል ወደ አለቃው ዞረና በፍርሀት እያየ "ብሔር የሚለው ላይ ምን ልሙላበት? "

"ምን እኔን ታፋጥጣለህ?! ልጂ መሰለህ እንዴ? ትግሬ ማለት ፈለክ! ዶዶቦች! አማራ ብለህ ፃፍበት" ብሎ ቀና ሲል አንደኛው ፌደራል ፖሊስ ከአማራ ክፍል የመጣ በመሆኑ ቅሬታ ፊቱ ላይ ሲታይ አነበበና "ኦሮሞ በለው!" ብሎ እንደተናገረ ሲፅፍ የነበረው አባል ኦሮሞ ስለነበር ፊቱ ላይ ስስ የሆነች ንዴት ተነበበች። ጎላፊውም ስለገባው "ቦቃ የለውም! ብሔር

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

የለውም በለው!" አለ በንዴት። ከዛም ወደ ታዳጊው ዞረና "እንክርዳድ! " ብሎ ተሳደበ።

ለሊቱ በቅጡ ወደ ንጋት እንኳ ሳይቃረብ በአሰቃቂው ድብደባ ብዛት የአስራ አንድ ሰዎች ህይወት ማለፉ ታወቀ። ሆኖም ግን ምርመራው ይበልጥ ተጠናክሮ እንዲቀጥል በአዛዡ ተገለፀ።

  

ያልተሸጠ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ምዕራፍ 40

ቤቲ ሳምሶናዊት ሻንጣውን እንደያዘች ከላይ የለበሰችውን ተደራቢ ልብስ አውልቃ ሽፈነችበት እና መንገዷን በመቀጠል ቀድማው ነበር ቤት የደረሰችው። ጥቂት ደቂቃ ዘግይቶ አብነትም ገባ። ከጥቂት ሰዓት በኋላ በአከባቢው ላይ በተጀመረው አፈሳ የተገኘው ህዝብ ሁሉ ከመንገድ ላይ ሲለቀም አብነት ድካሙን ለማርገብ የቤቱ ወለሉ ላይ በጀርባው ተንጋሎ ተኝቶ በረዥሙ እየተነፈሰ ነበር።

ቤቲ ከራሳቸው ቤት መጥታ የአብነት ክፍል ገባችና ወለሉ ላይ እንደተጋደመ አየችው። ይበልጥ እየወደደችው እንደሄደች ተሰማት። ድፍረቱን፣ በህሊናው መጠቀም መቻሉን፣ ላመነበት ነገር መስዋዕት መሆኑን፣ ፈጣን ሀሳብ ፈጣሪነቱን..... በአንድ ቀን ውስጥ ስለሱ የማታውቃቸውን ብዙ ነገሮችን ልታያቸው ቻለች። እነዚህ በፊት ከምታውቀው ማንነቱ ላይ ሲጨመሩበት እሷ የሱ መሆንን ብቻ ሳይሆን ራሷ እሱን ሆና መፈጠርን እጥብቃ ተመኘች።

የክፍሉን በር ዘጋችና ሻማዎቹን በመለኮስ መብራቱን አጠፋችው። አብነት አያያትም። ሁለቱንም አይኖቹን ጨፍኖ ከስፍራው በምናብ ጉዞ ርቋል።

የተገማመደው ፀጉሩ በጭንቅላቱ ዙሪያ ወለሉ ላይ ተበታትኗል።

"አቢ....." ጠራችው።

አይኖቹን ገለፀ። ".....ተነስ እንጂ ከመሬት ላይ....." ፍፁም በተዋጣለት ውብ ቅላፄ ተናገረችው።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“ምን..... ምን.....አልሽ?” እንድትደግምለት ስለፈለገ ጠየቃት፡፡
“ተነስ ከመሬቱ ላይ.....”
“አቤት..... ድምፅሽን ብስለው እንዴት ድንቅ ነበር.....”
“ድምፅ ደግሞ ይሳላል እንዴ?”
“አዎ.....ለኔ ግን የሶስት ሰው እድሜ ቢሰጠኝ እንኳ የአንቺን ድምፅ ስዬ መጨረስ የምችል አይመስለኝም” አላት እውነተኛ በሆነ ስሜት ተውጦ፡፡ እጆቹን ጨብጦ እያወዛወዘ ከተንጋለለበት ቀና ብሎ ተቀመጠ፡፡ እይታውን ፊቷ ላይ ተክሎ ገፅታዋን ሳይሆን ህሊናዋን እንደሚያነብ ዓይነት በተመስጦ አያትና “.....እስካሁን ካጋጠሙኝ እንስታት መሀከል የሚለይሽ አንድ ልዩ ነገር ያለሽ ይመስለኛል.....”
“ምን?”
“እኔንጃ.....መናፍስት ይወቁት፡፡ እኔ አቅሙ የለኝም.....”

ቆማ ከነበረችበት ስፍራ ተራመደችና አጠገቡ ወለሉ ላይ ተቀመጠች ለደቂቃ እንደተፋጠጡ በዝምታ ቆዩ.....በዝምታ ተነጋገሩ..... እኩል አንገት ለአንገት ተቃቀፉ፡፡ በጣቶቿ የፀጉሮቹን መካከል እየፈለፈለች ገባች፡፡ እየጨበጠች..... እየጨመቀች ..... ዳበሰቻቸው፡፡በለሆሳስ ከንፈራቸው ተሻሹ፡፡ ተሳሳሙ፡፡ ከዛም ተጣብቆ ቀረ..... ልብሶች እየወለቁ ተወረወሩ፡፡ የሰውነቱን ሙቀት ማንም ወንድ ላይ አጋጥሟት የማያውቅ ዓይነት ሆነባት፡፡ ለብ ያለ ውሃን በገንዳ ውስጥ ሞልቶ እንደ መተኛት ዓይነት.... እጆቹ ባልወደቁት ሉል መሳይ ጡቶቿ ላይ አረፉ..... በስሱ ቀለም ሊቀባቸው እንደሚሻቸው ስዕሎቹ በቀስታና በእርጋታ ዳበሳቸው፡፡.....
‘አቤት አለም እንዲህ እንዳለ ለዘላለም በቆመች’ አለች ቤቲ በህሊናዋ፡፡ የነበረው ነገር ሁሉ ተረሳ፡፡ ፀጉሮቹን እየጐተተች እንደፎጣ አካሏን ዳበሰችበት.....ዝቅ ብሎ ውብ ጡቶቿን ሳመላት፡፡
“አቢ.....እስከመጨረሻው.....ው.....አት....ተወ.....ኝ.....”ስትል አይኖቿን ጨፍና እንደ ህፃን ተናገረች፡፡

በምላሱ ጫፍ ደረቷን..... አንገቷን..... ከንፈሯን.... ጆሮዋን.... ዳሰሳቸው፡፡ ህሊናዋን መሳት እስኪቀራት ድረስ አስደሳች ንዝረት ከፀጉር ጫፏ እስከ እግሯ ጥፍር ድረስ አንቀጠቀጣት፡፡ የተከፈቱ ጭኖቿ መካከል ገባ፡፡.....

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

በህይወቷ እንደሱ ያለ ድንቅ የወሲብ ሰው አልገጠማትም፡፡
“በነፍሴ ውስጥ እንዴት ያለ ህያው የሆነ ውብ ስዕልን እንደሳልክልኝ በቃላት መግለፅ ያቅተኛል.....” አለችው፡፡
“እኔን ደግሞ በትንሹ እንደ ዓለማዊው ሰው ማሰብ እንድችል ስላደረግሽኝ ደስታዬ ወደር አጥቷል፡፡”
“እንዴት ነበር የምታስበው?”
“እኔንጃ.... ከዓለማዊው ሰው ያነሰ ወይም የበለጠ.....”
“እንደዓለማዊው ሰው ማሰብ እንዴት ነው?”
“ተያይዶ መፋቀር ከዛም መተቃቀፍ ከዛም መሳሳም ከዛም.....”
“አንተ አፍቃሪ አይደለህም እንዴ ታዲያ?”
“እንስታትን በፍቅረኛ መስፈርት የማፍቀር ችሎታዬን ግን ካጣሁት ቆይቼ ነበር፡፡”
“ፍቅር ጅል ስላልሆነ እስከመጨረሻው ፈቶ አለቀቀህማ..... እኔና አንተን መልሶ አገጣጠመን.....”
“ጅሉ እንግዲህ አንቺ ወይ እኔ ብንሆን ይሆናላ”
መልስ አልሰጠችውም፡፡ ጥብቅ አድርጋ በማቀፍ አካሏ ላይ አጣበቀችው፡፡
“ቤቲ ሰውነቴም ሆነ ፀጉሬ ምን እንደሚመስል ግን አይተሽዋል?.....እግረ መንገድ የቴቦውን ቆሻሻ ሳፀዳ ቆይቼ የወጣሁ መስያለሁ”
“ውስጥህ ግን ከማንም በላይ ንፁህ ስለሆነ በሱ ተጋርዷል፡፡” አለችው ከበፊቱ አጥብቃ እያቀፈችው፡፡
“ነገሮችን የምታስቢበት አቅጣጫ የሚደነቅ ነው፡፡ ይልቅ ልቀቂኝ.....” አቋረጠችውና “ከምን አንፃር?” ጠየቀችው፡፡
“እ..... ብዙ ጊዜ ስገምት ከአንድ ሰው ስነ-ምግባር ሰባ በመቶ የሚሆነውን ድርሻ ያ ሰው የተፈጠረበትንና የኖረበትን ህብረተሰብ ገላጭ ያደርገዋል፡፡ አስተሳሰብ ግን ያ ሰው የግሉን የማስተዋል ማንነቱን የሚያሳይበት የማንነቱ መገለጫ ነው፡፡”
“ስለዚህ በምግባርና በአስተሳሰብ መሀከል የሰፋ ልዩነት አለ ማለትህ ነው?”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“አዎ.....በእርግጥ እጅግ በጣም አልፎ..... ’አልፎ ምግባር ከአስተሳሰብ ሊፈጠር ይችላል፡፡ በሚያመዝን መልኩ ግን ብዙ ሰዎች በሚያስቡት አቅጣጫ ምግባራቸውን ማረቅ አይችሉም፡፡”
“እንደምሳሌ ብትጠቅስልኝ?”
“ይቻላል፡፡ እ.....ሰው እንዳይሰርቅ፤ እንዳይዋሽ፤ እንዳይገድል..... በሀሳብ ደረጃ እየሰብኩ በምግባሩ ላይ ግን ራሳቸው ቀንደኛ ውሸታም ሌባና ገዳይ ሆነው ይገኛሉ፡፡ በአስተሳሰብ ደረጃ ሰው የሱስ ተገዢ መሆን የለበትም እያሉ ምግባሩ ላይ ግን አጫሾቹ ጠጪዎቹ አመንዝራዎቹ ራሳቸው ናቸው፡፡”
“አንተ ግን በአስተሳሰብም በምግባርም አንድ ዓይነት ሰው ነህ.....በቃ የምታስበውን የህይወት አቅጣጫ በምግባርህ ታሳየዋለህ”
“አመሰግናለሁ” አላት ስሜት በሌለው ቅላፄ፡፡
“እውነቴን ነው፡፡ እያሾፍኩ አይደለም..... ይልቅ አንድ ችግር አለብህ?”
“ምን?”
“አስተሳሰቦችህ ስለማይጨበጡ ምግባርህም እንደዛው ሆኖ ይታያል..... ሰው በቀላሉ አውቆህ አብነት እንደዚህ ነው ሊልህ አይችልም፡፡”
“ለኔ ግን እኔ ማለት ቀጥ ያልኩና በአንድ አቅጣጫ ላይ እየተጓዝኩ ያለሁ ቀላል ሰው ሰው አድርጌ ነው ራሴን የማየው፡፡”
“ለምንድነው ታዲያ አስቸጋሪ የምትመስለው?”
“ምናልባት ሰዎች እኔን አይተው ሊያውቁኝና ሊረዱኝ የሚፈልጉት በራሴ መንገድ እያለሁ ሳይሆን እኔን ካለሁበት አውጥተው በራሳቸው አስተሳሰብ በራሳቸው አካሄድና አቅጣጫ ውስጥ ከከተቱኝ በኋላ ሊረዱኝ ይጥራሉ፡፡ ያኔ የማልጨበጥ ዓይነት መስዬ እታያቸዋለሁ፡፡ ዝም ብለው ግን በራሴ መንገድ ውስጥ እንዳለሁ ቢያዩኝ ልክ እንደ ሪያሊስቲክ ስዕል ፍጥጥ ብሎ በሚታይ ሁኔታ ውስጥ ያገኙኛል፡፡” አላት፡፡

“እንግዲህ እኔም ማየት እንደሚገባኝ አድርጌ አላየሁህም ማለት ይሆናላ.....” ቀጠለች ጥቂት ቆይታ “.....አሁን እዚህ ብዙ ጊዜ የምትመጣው ጓደኛዬ ስታይህ እብድ ነገር ነው ትልሀለች፡፡”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

አብነት በረኸሙ ሲስቅ ቆየና ከዛም "የእብደትን መነፅር አጥልቃ ስለምታየኝ ይሆናል፡፡"
እየጐሻሸመች ታግለችው፡፡ድጋሜ ከቅድሙ በማይተናነስ አዲስ ስሜት ወሲብ አደረጉ፡፡

ጨርሰው ጥቂት ዕረፍት ከወሰዱ በኋላ አብነት ወለሉ ላይ ጥሏት እየተነሳ "ኧረ ገና ስንት ስራ ይጠብቀናል ገላዬን መታጠብ አለብኝ፡፡"
"አሁንማ እኔንም አቧራ በአቧራ አድርገኸኛል....." ብላ ተነስታ ስትቆም እርቃኗን አያት፡፡ ሰፋ ያለው ትከሻዋ፣ የወገቧ ቅጥነት፣ የዳሌዋ ግዝፈት፣ የእግሮቿ ውበት..... ድጋሜ ወደ ወሲብ እንዳይገባ እይታውን ከሷ ላይ ነቀለ፡፡ እሷ ግን ያልዳበረ ሰውነቱን በስስት እያየች ቆየችና "እቢ..... ትንሽ ወፈር እንድትል ሀሳብ ቀንስና ምግብ ብላልኝ....."
ሀሳቧን ማስለወጥ ፈለግና "እስኪ ሳምሶናዊቱን ሻንጣውን ከፍተን እንየው የት አደረግሺው? " አላት፡፡
ተራምዳ ካስቀመጠችበት አነሳችና ሁለቱም አልጋው ጠርዝ ላይ ተቀመጡ፡፡

ስድስት ክፍሎች ባሉት ተሸከርካሪ የቁጥር ኮድ መቆለፊያ ያለው ዓይነት ነበር፡፡
"መክፈቻ ስለሌለው እንስበረው" አለችው፡፡
"ይከፈታል..... ወረቀትና እስክሪፕቶ ብቻ....." ያዘዛትን ሰጠችው፡፡
ከዛም ተሸከርካሪዎቹን ቁጥሮች እየገፋና በጐን ጠርዝ በኩል ክፍተት የጢን ቀዳዳ እስኪመጣለት እያዟዟረ ቀዳዳውን ሲያገኘው ቁጥሩን ፃፈ፡፡ የስድስቱንም በዚህ መሠረት ፅፎ ጨረሰና ከያንዳንዱ ቁጥር ላይ አምስት አምስት በመቀነስ የመጣለትን ቁጥር ደርድሮ ጨረሰ፡፡ በዛ ቁጥር መሠረት የሻንጣውን ቁጥር አዟዙሮ አስተካከለና ማስነከሻውን ቁልቁል ሲጫናት የሻንጣው የላይኛው ክፍል ተፈናጥሮ ተከፈተ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ቤቲ ስታየው ቆየችና ተንጠራርታ ከንፈሩ ላይ ሳመችው። በውስጡ በአራት አራት ገፅ የተያያዙና በአምስት ሰዎች ስም በእንግሊዝኛ ቋንቋ ለየብቻ የተዘጋጁ ነበሩ። የሉዊስ ተቋም ይህ ደብዳቤ የመጨረሻውና ለየ አስገንጣዮቹ የፖለቲካ ፓርቲ ዋና መሪዎች በቀጥታ ይደርሳሉ ብሎ ስላመነና በቀጣይነትም ሰናይትን ከመሀል አገናኝነት አስወጥቶ በራሱ የግንኙነት መስመር መስራት ስለፈለገ የተቋሙን ሙሉ አድራሻ ከአስፈላጊ ዝርዝሮች ጋር አካቶ ያዘጋጀው መሆኑን አዩ። ተጨማሪ ደብዳቤ አወጣ። ይኸኛው ለሰናይት የተላከ መሆኑን ስሟን አንብቦ አወቀ።

"የምንፈልጋቸው ሰነዶች በጠቅላላ እጃችን ገብተዋል" አላትና ትርጉሙ በትክክል ባይገባቸውም እያንዳንዱን አነበቡት። በዚህም አራት መርከብ ሙሉ የጦር መሳሪያ ከጫኑት ውስጥ አንደኛው በምፅዋ ወደብ የሚራገፍ ሲሆን ለትግራይ ግዛት አስገንጣዮች የሚሰጥ ነው። ሁለቱ መርከቦች ደግሞ በሶማሊያ የበርበራ ወደብ በኩል ለደቡብ እና ለኦሮሞ ግዛት አስገንጣዮች ይሰጣል። የአንደኛው መርከብ መሳሪያ ለአማራው ክልል የሚሰጥ ሲሆን የሚራገፈውም የሱዳን አማፂያኖች በድብቅ በሚጠቀሙበት ወደብ ላይ መሆኑን ይገልፃል። እንዲሁም የጉዞና ሌሎች ዝርዝር ሁኔታዎች በግልፅ ያልተቀመጡላቸው ሁለት ሌላ መርከቦች መኖራቸውን ያመለክታል።

ሁሉም መርከቦች የያዙትን ለማስረከብ በየታዘዙበት ወደብ ላይ የሚደርሱት ግፋ ቢል አምስት ቀን ልዩነት መሆኑን ለሰናይት በተፃፈላት ደብዳቤ ላይ ተገልጿል። ዕለቱም በኢትዮጵያ አቆጣጠር ግንቦት አስራ አራት እና አስራ አምስተኛው ቀን ሰዓቱም ከለሊቱ ስድስት ላይ ነው ይላል።
አብነት አንብቦ ሲጨርስ "ግንቦት ከገባ እኮ ዛሬ..... ስድስተኛ ቀኑ ነው።" አላት።
ቤቲ "ሰዎቹ ጊዜው አጭር ስለሆነ ሌላ የመረከቢያ ደብዳቤ አዘጋጅተውላቸው ሊልኩ ስለሚችሉ ምንድነው ማድረግ ያለብን?" አለች በፍርሃት።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ቀጠለች ዝም ሲላት "....በፎቶ ኮፒ ለመንግስት ብንሰጥ መንግስት ጉዳዩን ተከታትሎ ሊያከሽፍባቸው አይችልም?"
"እንደሱ ብናስብማ ደብዳቤውን ከመንግስት እጅ ለማስወጣት ምን አስለፋን ነበር..... ግፋ ቢል መንግስት ደብዳቤዎቹ ላይ ስማቸው የተፃፉትን ግለሰቦች እያደነ ሊይዝ፣ ሊያስር፣ ሊገድላቸው ይችላል። ግን የውጪውን ድርጅት እንቅስቃሴ ሊያስቆመው አይችልም። መሳሪያዎቹንም በየወደቡ ላይ እንዳይራገፉ የማስደረግ ስልጣን የለውም። ስለዚህም የፈረንሳዩ ተቋም ሌሎች ተገንጣዮችን አደራጅቶ ድጋሜ በመመልመል ዓላማውን ሊያሳካ ይችላል።" አላት።
"ታዲያ ምን እናድርግ?"
ሲያስብ ቆየና "አሜሪካ ከሶስት ዓመት በፊት ዲቪ ደርሶት የሄደ አንድ ሰዓሊ ጓደኛ አለኝ ከሁለት ወር በፊት በፃፈልኝ ደብዳቤ ላይ አንድ ነገር ገልፆልኝ ነበር።"
"ሊጠቅመን ይችላል?"
"እርግጠኛ አይደለሁም..... ግን ላሳውቀው።"
"ስለ ምንድነው የፃፈልክ?"
"እ..... በአፍሪካ አንድነት ዙሪያ የሚንቀሳቀስ በጥቁሮችና ጃማይካዎች ህብረት የተቋቋመ አንድ የህቡዕ ድርጅት ውስጥ አባል እንዳደረጉት የሚገልፅ ነው።"
"ብናሳውቃቸው ሊረዱን ይችላሉ?"
"የሚሉንን እናያለና..... እንደነገረኝ ከሆነ በአፍሪካ አንድነት ትግበራ ላይ የሚያምኑ በርካታ ኢትዮጵያውያኖች ጭምር አባል እንደሆኑ ገልፆልኝ ነበር " ቀጠለ ከተቀመጠበት እየተነሳ "ገላዬን ልታጠብና አሁኑኑ ኢ-ሜል እናደርግላቸዋለን።"
"እኔም ልለቃለቅና አብረን እንሂዳለን" ብላው ልብሷን መለባበስ ጀመረች።

ታጥቦ ጨረሰና በሩን ከፍቶ ሲወጣ የቤቲን እናት ጊቢ ውስጥ ቆመው አገኛቸው። "የት ልትሄድ ነው በዚህ ሰዓት ሰዉ ሁሉ ተመንገድ እየታፈሰ ነው! በል ተመልሰህ ወደ ክፍልህ ግባና መብራትህን አጠፋፍተህ ተኛ" አሉት በእናትነት ስሜት እያዩት።
"እየታፈስ?! "

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“አዎና ማን ቀራቸው..... ህዝቡን ሁሉ አግዘውታል ”
“እሺ አልወጣም ” አላቸውና ወደ ቤት ተመልሶ በመግባት ረዥም ሰዓት ቆየ። ያሰበውን እሰካላደረገ ድረስ ግን ህሊናው የማያርፍ ተፈጥሮ ስላለው አልጋው ላይ ሲቁነጠነጥ ቆየና ዘሎ ተነሳ። ሰዓቱ መሸቶዋል። የቤቲ እናት ወደ ቤት መግባታቸውን ተደብቆ አጣራና ከቤቲ ጋር ተሸሽገው ከጊቢ ወጡ።

የማታዋ ጀንበር ጠልቃ በፋንታዋ ጨረቃ በአጤ ሚኒልክ ቤተ-መንግስት አናት ላይ ሙሉ ክብ ሆና እየወጣች ነበር። ሰዓት ሲጠይቅ አንድ ሰዓት ሊሞላ ጥቂት እንደቀረው አወቀ። መንገዱ ላይ ሰው የሚባል አይታይም። አልፎ አልፎ የፖሊስ ፓትሮል በፍጥነት ሲያልፍ ይታያል።
“አቢ ነገ ብንልከውስ ውጪው በጣም ያስፈራል። ደግሞ ሊይዙንም ይችላሉ ” አለችው።

“በጭራሽ አይሆንም ዛሬውኑ ነው ማሳወቅ ያለብኝ። ጊዜ በሰጠናቸው ቁጥር ምን ሊፈጠር እንደሚችል አይታወቅወም ”
በምሽቱ ብርሀን ውስጥ አተኩራ ስታየው ውሳኔውን እንደማይቀይር ተረዳች። “እሺ በዋናው አስፓልት አንሄድም ና በዚህ ውስጥ ወስጡን አቋርጠን አምባሳደር ፊልም ቤት ጋር እንወጣለን ” ብላው በመንደሯ ውስጥ እየመራችው ደረሱ። በመጀመሪያው ዙር አፈሳ በርካታ ህዝብ ሲያግዙ የነበሩት የፌደራል ፖሊስ አባላት አስፓልቱ ላይ አይታዩም። የአገር መከላከያ ሚኒስትር በር ላይ የታጠቁ ጠባቂዎች መሳሪያቸውን ወድረው ከርቀት ይታያሉ።

ሀራምቤ ሆቴል ሰው አውርዶ ወደ ፒያሳ ያመራ የነበረ ላዳ ታክሲ ድንገት ከታች ሲመጣ አብነት አየውና አፏጭቶ በማስቆም ፈጥነው ገቡ። ወዴት እንደሚሄዱ ሲጠይቃቸው “ኢንተርኔት ማግኘት ፈልገን ነበር የምታውቅ ክፍት ቦታ ውሰደን ” አለው።
ከአስራ አምስት ደቂቃ በኋላ ኢንተርኔት ሊያገኙ ወደ ሚችሉበት ቦሌ አካባቢ አደረሳቸው። ጉዳዩን በዝርዝር ፅፈው አሜሪካ ላለው ጓደኛው በኢ-ሜል ላከለት።
ሲጨርሱ “መልሱን ነገ ያሳውቀናል” አላት። ባይሳካ ግን በቀጣይነት ምን ምድረግ እንዳለበት ማወቅ አልቻለም።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

በታክሲ ቤታቸው ድረስ ተመለሱ። ቤት ሲደርስ ግን ሁለት ጊዜ ከአሜሪካ ስልክ ተደውሎለተ እንደተፈለገ በቤቲ እናት ተገለፀለትና ቆጣ ብለው " እንዳትወጣ ፖሊሶች ይይዙሀል ብየህ አልነበረም?"
"አዎ ግን የግድ ስልክ የምደውልበት ጉዳይ ነበረኝ " አላቸው በጥፋተኝነት ስሜት። "በል ደግመህ እንዳትጣ ፖሊሶቹ አብደዋል። ሰዉን እንዴት እየቀጠቀጡ ሲጭኑ እንደነበር ስላላየህ ነው። በሰፈሩ አንድ ሰው የቀረ እንዳይመስልህ "
"እሺ " አላቸው።
"አንቺስ የት ነበርሽ? " አሏትና መልሷን ሳይጠብቁ "እንደው መቼ ይሆን ተዉ ስንላቹ የምትሰሙን?..... እንደው አምላክ ልቦና ይስጣቹ እኛም በናንተ ጭንቀት አለቅን..... እንደው እመብርሀን እነዚን ክፉ ደግሞ መቼ ይሆን የምታነሺልን" አሉ በመንግስት እየተማሩ።
ወድያው ሶስተኛ የስልክ ጥሪ ለሁለት ሰዓት አምስት ጉዳይ ሲል ደረሰው።

ኢ-ሜል ያደረገለት ጓደኛው መሆኑን ሲያውቅ "ፈፅሞ በዚህ ፍጥነት መልዕክቱን በማንበብ ትደውላለህ ብዬ አልጠበኩም።"
"አጋጣሚ መስመር ላይ ነበርኩ....." አለውና ሰላምታ ተለዋወጡ።
ቀጠለ የአሜሪካው ሰው "በጣም አስደንጋጭ ጉዳይ ነው። ለበላይ ሰዎች አሳውቄያለሁ"
"እና ምን ወሰኑበት?"
"የዋናዎቹ ደብዳቤዎች ግልባጭ በፋክስ አሁኑኑ ይላክልን ብለዋል።"
"አሁኑኑ?"
"አዎ!"
"እሺ የፋክስ አድራሻችሁን ስጠኝ?"
መዝግቦ ሲያበቃ "ደብዳቤውን ይገፍ እስከምደርስ ግን ፋክስ ማድረጊያ ቤቶቹ ከተዘጉ ነገ ጠዋት መሆኑ ግዴታ ነው።"
"በፈጠረህ ፍጠን!"
"እሺ ቻዎ።" መነጋገሪያውን ቦታው ላይ መለሰ።
ከአከራዮቹ ሳሎን ቤት ለመውጣት ሲነሳ ኢ.ቲቪ የምሽቱን የአማርኛ ስርጭት ጀመረና ጋዜጠኛው "የእለቱን ዜና ማሰማት እንጀምራለን...." እንዳለ የቤቲ እናት "እረዲያ ወጉ አለወቀረብህ እቴ... የእለቱን ስድብ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ማሰማት እንጀምራለን አትሉም...” ብለው ጆሮዋቸው በምሽት ክፉ ከመስማቱ በፊት ተነሱና ነጠላቸውን እያጣፉ ወደ መኝታ ክፍላቸው መራመድ እንደጀመሩ ጋዜጠኛው “አርቆ ማሰብ የተሳናቸው ጥገኛና ትምክህተኛ ህዝቦች ፀረ-መንግስት መሆናቸው ተገለፀ። ” የሚለው መግቢያ ጆሮዋቸው ጥልቅ አለ። “እግዚኦ ፈጣሪ ከነዚህ ሰዎች መቼ ደግ ደጉን የምታሰማን ” ብለው ለመተኛት ወደ ውስጥ ገቡ። አብነት ከመውጣቱ በፊት ለቤቲን በአይኑ “ነይ” የሚል መልክት ሰጥቷት ወጣ።

“ምን አሉህ?”

በዝርዝር ነገራትና “..... ብር እንድታበድሪኝ እፈልጋለሁ”

“ምንም ችግር የለውም” ብላ ሁለት የመቶ ብር ኖቶች ከቤት አምጥታ ሰጠችው።

የፋክስ አገልግሎት ሰጪ ቤቶች ለመዝጋት ሲዘገጃጁ ደረሰና የሁሉንም ደብዳቤዎች ግልባጭ አሻገረላቸው።

ቤት ተመልሶ ከተረጋጋ በኋላ ጋንጃውን በወፍራሙ ሸበለለና በእርጋታ ማጤስ ጀመረ። ለሊቱንም በመልካም እንቅልፍ አሳለፈው።

ጠዋት ከእንቅልፉ ያባነነው የበሩ መንኳኳት ነበር።

“ማነው?”

“እኔ ነኝ ቶሎ በል” አለችው ቤቲ።

ከፍቶላት ገባች። ፊቷ በድንጋጤ ላብ አቸፍቸፎበታል። በዝምታ ስታየው ቆየችና ከንፈሩን አጥብቃ ሳመችው።

“ስሜትሽ የተረበሸ ይመስላል.....”

“ጌቱ.....” አለችው።

“የቱ ጌቱ?”

“የኔ ወንድም ፖሊሱ.....” በተቆራረጠ ቅላፄ መናገር ጠቀለች “ስራ አድሮ ገና አሁን እቤት....መግባቱ ነው።”

“ምን ሆነ ታዲያ?”

“ለሊት በስራ ላይ እያሉ..... በከባድ ሚስጥር..... የሚጠበቅ ተብሎ የተላለፈላቸው ትዕዛዝ ደረሰን አለ።”

“ምን የሚል?”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“የሆነ ጥቆማ ሳይደርሳቸው አልቀረም፡፡ ፀጉራቸውን ያሳደጉ ኢትዮጵያውንም ይሁን የውጪ አገር ዜጋዎች እንዲያዙ ትዕዛዝ ተላለፈልን አለ፡፡”
“ምን!?” ደርቆ ቀረ፡፡
“አንተን እንደማይዝህ ለማዬ ሲያወራ ሰምቼዋለሁ፡፡ ሌሎች የሚያውቁህ አባሎች ካሉ ግን ዛሬን አያውሉህም አለ፡፡”
ከአልጋው ተነስቶ በሀዘን እየተራመደ ለቀለምና ብሩሽ ማስቀመጫነት የሚጠቀምበት ጠረጴዛ አጠገብ ካለ ደረቅ ወንበር ላይ ዘፍ አለ፡፡

ቤቲም ወደሱ ተራመደችና እናት ልጇኝ እንደምታደርገው ዓይነት ጭንቅላቱን ሆዷ ላይ አስደግፋ አቀፈችው፡፡
“ሌላስ ምን ነገረሽ?”
“እኛ ቤት ተከራይቶ እንደሚኖር የሚያውቁ ሌሎች ፖሊሶች አሁን በቡድን ሀላፊው ከተነገራቸው መምጣታቸው አይቀርምና መንገድ ላይ እንዳይያዝ.....ፀ....ፀጉሩን....ቆርጦ.... ከሰፈር መሰወር..... አለበት፡፡”
ቃሉ እየዘገነናት ሁሉንም ነገረችው፡፡ ከአስር ደቂቃ በኋላ ቤቲ ከኋላው ቆማ እንደ ዓይኑ ብሌን የሚሳሳለት ረዣዥም የተገማመደ ድሬድ ፀጉሩን ከስሩ በመቀስ መንግላ ወለሉ ላይ ከመረቸው፡፡በመካከላቸው የሞት ያህል ዝምታ ሰፍኖ ቆየ፡፡
“ለመኖር አስፈላጊ የነበረው አካሌ ተቆርጦ ተጣለ” አላት በሀዘን ተውጦና አይኖቹን መሬት ባሉት ፀጉሮቹ ላይ ተክሎ፡፡

ቤቲ ማልቀስ ፈለገች፡፡ ግን የሱንም ጥንካሬ መግፈፍ መስሎ ተሰማትና ሀዘኗን ዋጥ አድርጋ የተቆረጡ ፀጉሮቹን ከመሬት ላይ ለቃቅማ በማንሳት በአሮጌ ወረቀት ጠቀለለችውና ይዛው ወጣች፡፡
ቆይታ ስትመለስ “ምን አደረግሺው?” ጠየቃት፡፡
“ቆሻሻ ውስጥ ጣልኩት”
‘አከተመ’ አለ በሀሊናው፡፡ ቀጠለ ‘የተቆረጠው እስኪያድግልኝ ሌላ አስራ አንድ ዓመት..... በፍፁም ትዕግስቱ አይኖረኝም’
“በል ተነስ ለተወሰኑ ቀናቶች ሌላ ቤት ተከራይተህ ትቀመጣለህ” ብላ የተያያዙ የመቶ ብር ኖቶች ኪሱ ውስጥ ወሸቀችለት፡፡ መልሳ “ ቆይ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ፀጉርህን ቅባት ልቀባለህ" ብላ ከራሷ አመጣችና ቀብታና አበጥራለት ስታበቃ "ቆንጆ አፍሮ ሆነልህ" አለችው፡፡

"አዲስ ነገር ካለ ወደ በኋላ ደውዬ እጠይቅሻለሁ፡፡"
"እኔ ራሴ ያለህበትን ማወቅ ስለምፈልግ አዲስ ነገር ባይኖረኝም ደውልልኝ እሺ?"
"እሺ"
"ይሄን ሳምሶናዊት እኛ ቤት እደብቀዋለሁ፡፡" ብላ አነሳችው፡፡

አልተቃወማትም፡፡ ወጣና በሩን ቆልፎ ጉዞ ቀጠለ፡፡

እንደወጣ የኢንተርኔት አገልግሎት የሚሰጥበት ቤት አመራና የራሱን የኢ-ሜል አዲስ አድራሻ ከፈተ፡፡ ከዛም እየታደነ መሆኑን በአሜሪካ ላለው ጓደኛው አሳወቀው፡፡ ከአንድ ሰዓት ተኩል ቆይታ በኋላ አሜሪካ ካለው ጓደኛው መልስ ደረሰው፡፡ መልሱ ላይ ተደብቆ ሊቆይ የሚችልበት አድራሻ አብሮ መጥቷል፡፡

ቦታው ሲ.ኤም.ሲ. እየተባለ በሚጠራው በአዲስ አበባ ምስራቃዊ ዳርቻ ላይ የሚገኝ ሰፈር ነው፡፡

በአካባቢው የውጪ አገር ዲኘሎማቲክ ሰራተኞች ይበዙበታለ፡፡ አብነት ሲደርስ ቤቱ ከገመተው በላይ ዘመናዊ ሆኖ አገኘው፡፡ ፈራ ተባ እያለ አስከፍቶ ገባ፡፡ ቤቱ አዲስና ባለ አንድ ፎቅ ሲሆን ተከራይቶ የሚኖርበት ሰው "በአፍሪካ አንድነት ድርጅት" ውስጥ የሚሰራ ጥቁር የደቡብ አፍሪካ ተወላጅና በአሜሪካ ውስጥ በህቡዕ ለሚንቀሳቀሰው የጥቁሮች ህብረት ተቋም አባል ነበር፡፡

ለሱም ከአሜሪካ መልዕክቱ በስልክ ደርሶት ነበርና አብነትን ከማግኘቱ በፊት ወደ ስራ አልሔደም፡፡ ሲገናኙ ሞቅ ባለ የወዳጅነት ስሜት ተቀበለውና የራሱ የሆነ መታጠቢያ ያለውን የመኝታ ክፍሉ ተዘጋጅቶለት የቆየው መሆኑን ነግሮት አሳየው፡፡ በመኝታ ክፍሉ ኢንተርኔት የተገጠመለት ኮምፒውተር ጭምር የያዘ ነበር፡፡ ምግብም ሆነ የሚፈልገውን ቁሳቁስ ከቤት መጠቀም እንደሚችል ገለፀለትና ወደ ስራ መሔድ እንዳለበት አሳውቆት ወጣ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

በጊቢው ውስጥ አንድ የፅዳት አንድ የጥበቃና አንድ ምግብ አብሳይ ሴት ሰራተኞች ብቻ ናቸው ያሉት፡፡
ጥቂት ተረጋግቶ ለሰናይት ስልክ በመደወል አገኛትና "አዲስ ነገር አለ?" ጠየቃት፡፡
"አቢ እግርህ ከጊቢ እንደወጣ ፖሊሶች ሊፈልጉህ መጥተው ነበር" አለች እየተንሰፈሰፈች፡፡
"እና ምን አሉ?"

"ከሁለት ሳምንት በፊት ለቀክ የሄድክ መሆኑን ነገርናቸው፡፡"
"ዝም ብለው ሄዱ?"
"ያው ወዴት እንደሄድክ ቢጠይቁንም አናውቅም ስላልናቸው ሄዱ፡፡"
ቀጠለች "ለመሆኑ የት ነው ያለኸው?..... እንዳይዙህ....."
"አሜሪካኖቹ ጥገኝነት አሰጥተውኛል" አለ እያሾፈ፡፡
"አትቀልድ....."
ጉዳዩን በዝርዝር ነገራት፡፡ የስልኩን ንግግር ስትጨርስ ቤቲ በደስታ ሰክራ ዘለለች፡፡
"አገር እንዲህ እየታመሰ ምንድነው ታስራ እንደ ተፈታች ጥጃ እንዲህ የሚያስቦርቅሽ?" አሏት እናቷ፡፡
ዘላ ሳመቻቸውና "እማዬ እንደዚህ ወቅት በህይወቴ ደስተኛ ሆኜ አላውቅም" አለች በእቅፏ እየተጠመጠመችባቸው፡፡
"ወግጅ ወድያ ለፍዳዳ! " አሏት እቅፏን እያስለቀቁ፡፡

«««««««« »»»»»»»»

በዕለቱ ከቀኑ ስድስት ሰዓት እስኪሆን ድረስ ከአዲስ አበባ ዙሪያ ሀምሳ ስድስት የሚሆኑ የተለያዩ አገር ዜግነት ቢኖራቸውም ድሬድ ፀጉራቸው እየታየ ታፈሱ፡፡ እንዲሁም ሰባ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ባለ ድሬዶች ከተገኙበት ሁሉ እየተያዙ ወደ ማዕከላዊ እስር ቤት ታጐሩ፡፡
እያንዳንዱ እስረኛ ለየብቻ ምርመራ እየተወሰደ ጉዳዩ ከተገለፀለት በኋላ ሻንጣውን እንዲያስረክብ ጥየቃ ተጀመረ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ከቀኑ ሰባት ሰዓት ከአርባ አካባቢ ተራ ደርሶት የገባው ጃማይካዊ አስደንጋጭ ምላሽ ሰጣቸው፡፡
“በትላንትናው ዕለት ከቀኑ አስር ሰዓት አካባቢ ከባለቤቴ ጋር አርፈንበት ከነበረው ሽራተን ሆቴል ወጥተን ወደ ታች ስንጓዝ አንድ እንደነሱ ፀጉሩን ያሳደገ ሰው ከትቦ ውስጥ ለአንዲት ሴት ሻንጣ አቀብሎ ሲወጣ አይተናል” አለ፡፡

ቀጠለ “.....በመጀመሪያ የአይምሮ ህመምተኛ መስሎን ነበር፡፡ በኋላ ላይ ግን ወጥቶ የቱቦውን ክዳን መዝጋት ሲጀምር ሁኔታውን በርቀት አይተናል፡፡ ትኩረቴን የሳበው ግን ውብ ፀጉሩ ነበርና ለሚከውነው ተግባር ሳልጨነቅ ከትከሻው በላይ የፊቱን የጐን ገፅታ ጨምሮ ፎቶ አንስቼዋለሁ” አለ፡፡
“በዚህ ካሜራ?” ጠየቀው ቃሉን እየተቀበለው ያለው የህዝብ ደህንነት በልደረባ በሚያስተረጉምለት ሰው አማካኝነት፡፡
“አዎ.....ፊልሙ ስላላለቀ አልቀየርነውም ገና”
“የሱን ፎቶ ብቻ ቆርጠን እንውሰድና ቀሪውን ብንሰጥህስ?”
“ትችላላችሁ፡፡” አለ ጃማይካዊው ካሜራውን ጠረጴዛው ላይ እያደረገ፡፡
ከሰላሳ ደቂቃ በኋላ የአብነት ፎቶ ተባዝቶ በከተማዋ ውስጥ ላሉ ፖሊስ ጣቢያዎችና የደህንነት ሰራተኞች ተበተነ፡፡

««««««««« »»»»»»»»»

የቤቲ ታናሽ ወንድም የሆነው ጌቱ ከደጅ እየሮጠ ገባና “ወይኔ.....ወይኔ....” አለ በጩኸት፡፡
“ምነው?” አሉት እናቱ ደንግጠው፡፡
“ተከራዩ.....”
“የቱ?”
“ይሄ እኛ ጋር የነበረው ሰዓሊ.....” ቤቲ ከውስጥ ወጣችና ደርሳባቸው ጉዳዩን ማዳመጥ ጀመረች፡፡
“ምን ሆነ?” አሉ የናትነት ሆዳቸው እየራደ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“እሱን ይዞ ያመጣ ፖሊስ የማዕረግ እድገትና የገንዘብ ሽልማት ይሰጠዋል ተባለ” ብሎ ፎቶውን ከኪሱ አወጣና እያሳያቸው “አመለጠኝ!” አለ ቁጭት በተቀላቀለበት ሀይለ ቃል፡፡

የቤቲ እግሮች በድንጋጤ ተርበተበቱ፡፡ ያስተዋላት ግን አልነበረም፡፡

“አንተ ተው እንደዚህ ስልጣንና ገንዘብ ወዳድ አትሁን” አሉት እናቱ፡፡

“ግን ብታገኘው ለጥቅም ብለህ ታሲዘው ነበር?” ቤቲ ጠየቀችው፡፡

“እንክት አድርጌ ነዋ!”

በጥፊ አጮለችው፡፡

“ምን ያማታሻለ!” ደነፋ፡፡

ታላቁ ብትሆንም እናታቸው ከመካከላቸው መሆናቸው በጀ እንጂ በአደረገው የፖሊስ ጫማ እግሯን ሊከሰክሰው እያሰበ ነበር፡፡

“ከላይ እስከ ታች ድረስ አገሪቷን ደደብ እየገዛት በየት በኩል ትደግ!?” አለች ቤቲ በንዴት፡፡ በሌላ በኩል ፎቶው እንዴት ሊገኝ እንደቻለ እየተገረመች፡፡ ያላስተዋለችው ሌላ ጥያቄ ከተፍ አለባት፡፡ ‘የኔስ ፎቶ ተገኝቶ ይሆን?’ የሚል፡፡

“ጌቱ.....በናትህ አንድ ነገር ልጠይቅህ?”

“በአፍንጫሽ ቁሚ!” ብሏት ወደ ጊቢው መውጫ በር መራመድ ጀመረ፡፡

  

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ምዕራፍ 41

አፈሳው በተካሄደበት ምሽት መላዋ የአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ የሚገኙት መጠጥ ቤቶች ሱቆች እና አንዳንድ የህዝብ አገልግሎት መስጫ ተቋማቶች ያለ ወትሮዋቸው በጊዜ ተዘጋጉና በየመንገዱ ላይ የሚታዩት ገዢውን ፓርቲ በስልጣን የማስቆየት ህልውና የሚያስጠብቁ ሙሉ ትጥቅ የታጠቁ ወታደሮች፤ የፌደራል እና የህዝባዊ ፖሊስ አባላቶች ብቻ ሆኑ::

በቀጣዩ እለት የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በትላንትናው እለት ካለ ምንም ጥፋት በአከባቢው ሲተላለፉ ከመንገድ ላይ ታፍሰው ባልታወቀ ስፍራ የታሰሩት የዩኒቨርስቲው ተማሪዎች እና ሌሎችም ንፁሀን ዜጎች ካለ ምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ እንጠይቃለን በማለት፤ የሰሩት ወንጀል ቢኖር እንኳ ጉዳዩ የአገሪቷ ህገ-መንግስት በሚያዘው መሰረት በፖሊስ ተጣርቶ እና በፖሊስ ቁጥጥር ስር ቆይተው በፍርድ ቤት መታየት እንዳለበት በመግለፅ የጠየቁት እስኪተገበር ትምህርታቸውንም እንደማይቀጥሉ አስታወቁ::

የዩኒቨርስቲውን ጊቢ እንዲጠብቁ ከተመደቡት የፌደራል ፖሊሶች በተጨማሪ ሌላ ሀይል ወደ ጊቢው እንዲላክ ታዘዘና ተማሪዎቹ ያነሱት ጥያቄ ወደ ህዝብ ጆሮ ከመድረሱ በፊት አፍነው ወደ ትምህርት ክፍላቸው እንዲገቡ በሀይል ያስገድዷቸው ጀመር:: ይህም ግጭትን መፍጠር በመጀመሩ ፖሊሲቹ ተማሪዎቹን በዱላና በሰደፍ መቀጥቀጥ ቀጠሉ:: ሆኖም ቀን በመሆኑ እንደልብ መደብደብ አልቻሉም::

የጊቢውን በር ዘግተው መውጣትም ሆነ መግባት ከልክለው ቀኑን እንደምንም አሳለፉ በኋላ ከምሽቱ አምስት ሰዓት ሲሆን ተጨማሪ ሰራዊት በወታደራዊ መኪናዎች እየተጫነ ወደ ጊቢው እንዲደርስ ተደረገና ለሊቱን ሙሉ ተማሪዎችን በየክፍላቸው ሰብረው በመግባት ሲቀጠቅጡ አደሩ:: በዚህ መካከል ግን የገዢው ፓርቲ ቤተሰብ ልጆች እና ደጋፊዎች

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

የነበሩት በድብቅ ከጊቢው እንዲወጡ ስለተደረገ ሌላው ተማሪ ላይ የደረሰው ኢ-ሰብአዊ ድብደባ አላገኛቸውም።

ለሊቱን ሙሉ ሲወሰድባቸው ባደረው እርምጃ ምክንያት ቅስማቸው ተሰብሮ በቀጣዩ እለት ወደ ትምህርታቸው ይመለሳሉ ብሎ ያመነው ገዢው መንግስት ያሰበው ሳይሳካ ቀረ። ተማሪዎች ወደ ትምርት አንመለስም ብለው በአንድ አቋም ከመፅናታቸው በተጨማሪ አመፁ እንደ ሰደድ ወድያውኑ በመስፋፋት ወደ አራት ኪሎ ዩኒቨርስቲ ወረደ። ቀጥሎም ወደ ሁለተኛ ደረጃ የከተማዋ ትምህርት ቤቶች እየተዛመተ በመሄድ ከትግራይ ክልል ዩኒቨርስቲ በስተቀር በመላው አገሪቷ ላይ የሚገኙት ዩኒቨርስቲዎች ለተወሰደው እርምጃ መልስ ከመንግስት እንደሚፈልጉ በማስታወቅ ትምህርታቸውን አቋረጡ።

መንግስት ግን ጉዳዩን እንደመንግስት በማስተዋል እና ለወገን ተቆርቋሪ በሆነ ሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ከመሞክር ይልቅ በየ ወታደራዊ ካምፖች አስቀምጦ በህዝብ ገንዘብ ሲቀልባቸው የነበሩትን የጦር ሰራዊቶችን ግማሹን የፖሊስ ልብስ በማስለበስ ግማሹንም በወታደራዊ ልብሳቸው ተማሪውን እና የተማሪውን ጥያቄ የሚደግፍ ማንኛውን የአገሪቷን ዜጎች እንደ እባብ እንዲቀጠቅጥ ብሎም በጥይት እስከ መግደል ትእዛዝ ሰጥቶ ህዝብ ላይ አሰማራቸው።

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ተሟጋች ድርጅት ሁኔታውን ለተለያዩ ዓለም ዓቀፍ ተቋማት በተደጋጋሚ ማስታወቅ እና አገሪቷ በህገ-ወጦች አገዛዝ ስር መውደቋን መወትወት ጀመረ። ትኩረቱም የዓለምን ዓይን መሳብ ጀመረ።

ገዢው የወያኔ ፓርቲ ሁኔታዎች ከቁጥጥር ውጭ እየወጣ በመሆኑ መርበትበቱ አልቀረም። የማእከላዊ ፖሊት ቢሮ አባላሎች በስብሰባ ተጨናንቀዋል። በየቦታው፤ በየመስራቤቱ ፤ በየጥጋጠጉ..... ስብሰባ ፤ ስብሰባ፤ ስብሰባ..... በእርግጥ ጉዳዩ የዓለም አቀፉ ህብረተሰብ ጋር መድረሱ ወያኔን ይህን ያህል አላሰጋውም። ምክንያቱም ኢትዮጵያ የሮም ኮንቬንሽን ፈራሚ አገር ባለመሆኗ «የዓለም አቀፍ ወንጀለኞች ፍርድ ቤት» ሊከሳቸው እንደማይችል ያውቁታል።

የነሱ ጭንቀት የሆነው ከአውሮፓ ህብረትና መንግስታት፤ ከዓለም ባንክ እና ከበርካታ የእርዳታና ፈንድ አድራጊ ተቋማት በደሀው የኢትዮጵያ ህዝብ እና በዚች ደሀ አገር ስም የሚቀበሉትን ከዛም ወደ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ግል ኪሳቸው የሚከቱትን በቢልየን የሚቆጠር ገንዘብ እና ጥቅማጥቅም ሊያሳጣቸው የሚችል መሆኑ ነበር።

ይህም በመሆኑ በአገሪቷ ህዝብ ላይ ለሚወሰደው እርምጃ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለሚነሱ ጥያቄዎች በሰላ አንደበት አደናጋሪ መልስ ለመስጠት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሁሉም የላቀ ስራ በዝቶባቸው ነበር። ሆኖም ግን ለሁሉም ጥያቄ መልስ ለመስጠት እና በቀጣይነት ህዝቡን ነጣጥሎ ለመምታት፤ አፈናን እና ጭቆናን እንደፈለጉ ለማካሄድ የሚያስችለው አጀንዳ ተረቆ አበቃ።

በዚህም አገሪቷ በምትከተለው አቀርቋሪ ፖሊሲ ምክንያት ስራ ፈት እና ስራ አጥ ሆነው ለመብታቸው የሚታገሉትን ወጣቶች ለመምታት «አደገኛ ቦዘኔ» የሚል ሽፋን ተለጠፈባቸው።

ራሱ ገዢው ፓርቲ መልምሎ ስልጣን ላይ ካስቀመጣቸው በኋላ እንደ ፓርቲው ፈቃድ ለመመራት አሻፈረኝ ያሉትንም ሆነ እንደ ህዝብ ለማሰብና ለመስራት የተነሳሱትን ለማጥቃት «ሙስና!» የሚል ህግ-ማነቆ ወጣላቸው።

በሰላማዊ ትግል ለአገር እድገት የሚበጅ መፍትሄ እናመጣለን ብለው ቢሮ በመክፈት በጠረጴዛ ዙሪያ ትግል በመጀመር እና የሚያነሷቸው ሀሳቦችም ሆኑ ጥያቄዎች የህዝብ ጥያቄ መሆኑን ለማሳየት በሰላም ሰላማዊ ሰልፎችን በሚጠሩና ህዝብን ለበጎ ዓላማና አንድነት የሚያስተባብሩ የተቃራኒ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ለማጥቃት፤ ለመበታተን ፤ለማሰር እና ለመግደል እንዲችሉ «ህገ-መንግስቱን በሀይል ለመናድ የተደራጁ ህገ-ወጦች» በማለት....

ራሳቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ የህዝብ ምክር ቤት ውስጥ በተደጋጋሚ ባደረጉት ንግግር ላይ እንደገለፁት ድልም ይሁን ፍትህ በሰላማዊ መንገድ እንደማይመጣ ባስረገጡት መሰረት «ከወያኔ ጋር የትጥቅ ትግል ካልሆነ በስተቀር ምንም አይነት ሰላማዊ ድርድር ማድረግ አይቻልም » ብለው ፊታቸው ወደ ጠመንጃ የመለሱት ፓርቲ አባላትን እያደኑ ካለ ፍርድ ችሎትና ካለ ምህረት ለመስቀል «የአሸባሪዎች አባላት!» እያሉ

ስደትን አልሞክርም ብለው አገራቸው ከምትበላው ፍዳ አብረው መብላትን በመምረጥ በኢትዮጵያ ቀርተው ስለ ፍትህ፤ ስለ ዲሞክራሲ፤ ስለ እኩልነት እና አንድነት ሌተ-ቀን መንግስትን የሚሞግቱ እና ህዝብን የሚያስተምሩ ምሁራንን ከስራቸው ለማፈናቀል፤ መኖሪያ ለማሳጣት፤ ሞራላቸውን ለመጣልና ክብራቸውን ለማንቋሸሽ «የፌውዳል ስርዓት

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ናፋቂዎች! የደርግን ስርዓት ቅሪቶች! ትምክህተኞች! አድርባዮች!» የሚል ጥላሸትን በማንተቻው ላይ እየለጠፉ መድረሻ በማሳጣት

የአገሪቷን ኢኮኖሚ ለመለወጥ ጥሪታቸውን አሟጠው የሚሰሩ ባለ ሀብቶችን ለመዝረፍ እና ለመውረስ ብሎም እያዳከሙ ለማክሰም «በህገ-ወጥ መንገድ ለመክበር የቻሉ» እያሉ በማስፈራራት

በዩኒቨርስቲና መሰል ከፍተኛ የትምርት ተቋማት የሚነሱ አገር አቀፍ ጥያቄዎችን ለማፈን እና እነዛን የህዝብ ድምፅ አሰሚዎችን ወህኒ ለማበስበስ « አመፅ በአገሪቷ ላይ ማነሳሳት! የቀለም አብዮት ማነሳሳት! እና አገር መክዳት!» በሚሉ አደገኛ ተጠየቅ ውስጥ በመዝፈቅ

በአንዳንድ ነቃ ባሉ የገበሬዎች አካባቢ የሚነሱትን የገበሬዎቹን የመሬት ጥያቄ ለማዳፈን እና መሬታቸውን በጉልበት እየነጠቁ እንደፈለጉ ለመቸብቸብ በ«አገር ልማት» ስም እያፈናቀሉ መሰረት እና ርስት አልባ በማድረግ ስለ መብቱ እንዳይሟገት እያጋዙት

የወቅቱን ሁኔታና እውነታ እያስነበቡ ያስቸገሩ ጋዜጣዎችን ለመዝጋት እና ጋዜጠኞችን ለማሰር «የአሸባሪዎች ልሳን! የህገወጦች ተባባሪ! አመፅ ቀሽቃስ!» ብሎ ለመወንጀል የሚያስቸሉ የመላው አገሪቷን ህዝብ በታትኖ እያዳከሙ አደህይቶ ለመምታት የሚያስችሉ ህጎችን በፍጥነት አርቅቆ እራሱ እያፀደቀ አሰራጨ።

በማንኛውን መልኩ መንግስት በህገ-ወጥ ይዞ እንዳሻው ለሚያንገላታቸው ዜጋዎች በዓለም አቀፉ ህብረተሰብ እና በሰብአዊ መብት ተሟጋቾች ለሚነሱት ጥያቄዎች ከላይ ካሉት ምክንያቶች አንዱን እየተለጠፈ፤ የጠያቂዎቹንም አመለካከት በሰላ የሀሰት አንደበት ለማምታታት በመቻሉ «ግዳይ 200» የተባለው የአፈና ተቋምም በአገሪቷ እና በህዝቡ አናት ላይ እንዳሻው ተደላድሎ ከተመ። ልዕለ-ሀያል የሆነና ገደብ የለሽ ስልጣን የተሰጣቸው እነዚህ የአፈና ቡድን አባላቶች ተጠሪነታቸው በቀጥታ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ብቻ በመሆኑም ሲያስሩ፤ ሲሳደቡ፤ ሲደበድቡ፤ ሲነጥቁ ፤ ሲገድሉ..... «ለምን?» ብሎ ለመጠየቅ ስልጣን ያለው አካል በመታጣቱ «የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጣቶች» የሚል ቅጥያ ስም በራሳቸው በወያኔ አባላቶች ተሰጣቸው።

  

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ምዕራፍ 42

“አ.....አዎ.... ተ...ኩስ.. በለው.... በ...ለ..ለው... አ...እግሬን መታ...ኝ.... አል..ቻ...ልኩም ....ኡ .....ኡ..... አልቻ....ልኩም...”
“ሰናይት!ሰናይት!” መንበረ ከእንቅልፏ ቀስቅሳ አባነነቻት፡፡
“ምነው!?....ምን ተፈጠረ!?” በድንጋጤ ቀና እያለች ጠየቀቻት፡፡ ፊቷ በላብ ተዘፍቋል፡፡
“አሞሻል እንዴ በጣም እያቃዠሽ ነበር” አለቻት ቀና ብላ እያየቻት፡፡

ከመጀመሪያው ዕለት አንስቶ ስታደርግ እንደበረው በግርጌዋ በኩል ነበር ዛሬም የተኛችው፡፡ አስፈሪውን ቅዠት ያየችው ገና ሽለብ እንዳደረጋት ሲሆን ሰዓቱ ከለሊቱ ዘጠኝ ብሏል፡፡
“አ....እጅሽን እጅሽን.....” አለቻት ሰናይት በስቃይ ድምፅ፡፡

መንበረ ደንግጣ ተደግፋው ከነበረው እግሯ ላይ የነበረው አጇን አነሳችና መብራቱን በማብራት “ምን ሆነሻል?” ብርድ ልብሱን ገለጠችውና ለእይታ አጋለጠችው፡፡ ሰናይት ከግራ ጉልበቷ መታጠፊያ ላይ የደረቀ ደም ይታያል፡፡ ለብሳ የተኛችው ሱሪዋም ጉልበቷ ላይ ተጣብቆ ነበር፡፡
“ምንድነው የሆንሽው?..... ማታ ወደኔ ስትመጪ ዱርዬዎች ደበደቡሽ?” ደንግጣ ጠየቀቻት፡፡ ማታ ያለወትሮዋ አምሽታ መግባቷን እያስታወሰች፡፡
“አይ.....ቀን ላይ መንገድ ስሄድ መኪና ገፋ አድርጐ ጣለኝ” በማለት ዋሸቻት፡፡

አደጋው የተፈጠረባት ግን ሳምሶናዊት ቦርሳውን ለማስጣል በፈጠረችው ግብግብ ወቅት ላይ ነበር፡፡
“እና መኪናው ተያዘ?”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

“አይ.....አመለጠ”
“ሱሪሽን አውልቂና በንፁህ ጨርቅ ልሰርልሽ ”

ጥቂት እንደማመንታት አለችና አወለቀች፡፡ የተላጠው ጉልበቷ ላይ ተጣብቆ የነበረው ሱሪዋ ሲላቀቅ መድማት ጀመረ፡፡ መንበረ ከአልጋው ወርዳ ቡታጋዝ በመለኮስ ጥቂት ውሃ ከጨው ጋር ለብ ማድረግ ጀመረች፡፡

ሰናይት በራሷ ሃሳብ ተውጣ መነሻና መድረሻ በሌለው ዝብርቅርቅ ስሜት ውስጥ ተውጣ በአይኗ ግን መንበረን ትከታተላለች፡፡ ሊያመልጡ የቻሉበትን ተዓምራዊ ቅፅበት ድጋሜ በህሊናዋ ታያት፡፡ ማብቂያ የሌለው ይመስል የነበረው የክላሽ ተኩስ በህሊናዋ ድጋሜ አስተጋባባት፡፡ እንዴት ፖሊሶች ሊደርሱባቸው እንደቻሉ ግን ለማምት የሚሆን ፍንጭ እንኳ ማግኘት አልቻለችም፡፡

ደብዳቤውን ያመጣላት ፈረንሳዊ አካባቢውን ለቀው እንደወጡ በአቆራራጭ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ፒያሳ ደርሶ በደመ-ነፍስ ወዴት መንዳት እንዳለበት ሳያስተውል የአራት ኪሎን መንገድ ተያያዘው፡፡

ራስ መኮንን ድልድይ ጋር ሲደርስ በሚነዳው ሞተር ቢክስሌት አማኝነት ሊያዝ እንደሚችል ታወሰው፡፡ በወቅቱ ከጊዜው ውጥረት አማካኝነት የመጣለት መፍትሔ አንድ ብቻ ነበር፡፡

በራስ መኮንን ድልድይ በስተግራ በኩል የምትገነጠልና ብዙም ግርግር የሌለባት ቀጭን አስፓልት እይታው ውስጥ ገባች፡፡ እዞረና በአስፓልቱ መቶ ሜትር እንደተጓዘ አቁሞ “ውረጅ!” አላትና ሰናይትን እሱም ወረደ፡፡

ከዛም ከቤንዚን ጋኑ ወደ ካርብራተሩ ነዳጅ የምታስተላልፈውን ጐማ ነቀለና በሞተሩ ወሳኝ ክፍሎች ላይ ነዳጁን አፈሰሰበት፡፡ቀጥሎም መሀረብ መሳይ ጨርቅ ከኪሱ አወጣና በጋኑ ጭንቅላት በኩል ወደ ውስጥ በመንከር አንደኛውን ጫፍ በጥንቃቄ በእሳት አያያዘው፡፡ ከዛም በፍጥነት ከአካባቢው መራቅ ጀመሩ፡፡ ከአንድ ደቂቃ በኋላ እሳቱ በመላው የሞተሩ አካል ላይ ተሰራጨ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“ፍጠኝ ከአካባቢው እንጥፋ” አለና በረጭኹም እርምጃ ቁልቁል መመለስ ጀመሩ፡፡”

ጥቂት ቆይቶም መጠነኛ ፍንዳታ ተሰማና የቤንዚኑ ጋን ተወርውሮ በረረ፡፡

የዋናው አስፓልት ጫፍ ጋር እንደደረሱ “እንግናኛለን ደህና ሁኝ ብሏት” ወደ ፒያሳ መመለስ ሲጀምር ሰናይትም ተሻገረችና የአራት ኪሎ ታክሲ አስቁማ ተሰወረች፡፡

ይህንን ሂደት ስታሰላስል ቆይታ ከሀሳቧ ያባነናት የመንበረ ጥያቄ ነበር፡፡

“የመኪናው ታርጋ እንኳ አልተያዘም?”

“ተይዟል.....ግን ማን እሱን ፍለጋ ይሯሯጣል ብዬ ተውኩት፡፡”

ውሃው መሞቁን አረጋገጠችና ገዝታው ያልተጠቀመችበትን ነጭ አንሶላ ከሳጥኗ አወጣች፡፡ ሰናይት አይታ እንዳትከለክላት ጀርባዋን ሰጥታት ያስፈልጋል ብላ የገመተችውን ያህል በአንደኛው ጫፍ በኩል ቀደደችና ቀሪውን መለሰችው፡፡

ቅዳጁን እንደገና ሶስት ቦታ ቀደደችና በአንደኛው ከጨው ጋር ለብ ያለው ውሃ ውስጥ እየነከረች የሚደማውን ቁስል እስኪፀዳ ድረስ አጠበችላት፡፡ ከዛም ከአንድ የመዳኒት መቋጠሪያ ፕላስቲክ ውስጥ አምፒሲሊን አወጣችና ካፕሱሉን በመክፈት ዱቄቱን ቁስሉ ላይ አፍስሳ ደመደመችበት::

ቀጥሎ እጇን አደራረቀችና ሁለተኛውን ቅዳጅ ጨርቅ በቁስሉ ስፋት ልክ አጣጥፋ በላዩ አስቀመጠችበት፡፡ በሶስተኛው ቅዳጅ እንዳይንሸራተት አድርጋ በጥሩ ሁኔታ አሰረችላት፡፡

ይህ ሁሉ ሲሆን ሰናይት በህሊናዋ ስለ ሌላ ነገር ነበር የምታስበው፡፡ ‘ከአሁን በኋላ በምንም ዓይነት ሁኔታ ዋስትና ያለው እንቅስቃሴ አይኖረኝም..... በዛ ላይ አንድ የደህንነት አባላቸውን ገድዬባቸዋለሁ..... ይህ ደግሞ ክትትሉትን ይበልጥ እንዲያጠናክሩበት ነው የሚያደርጋቸው.....’ መለስ ትልና ደግሞ ‘ለነገሩ ሊነጋ ሲል ይበልጥ ይጨልማል አይደል የሚባለው.....ወደ ፍፃሜው እየተቃረብኩ ስለሆነ ይሆናል ፈተና የበዛው’ ብላ ራሷን ታበረታታ ነበር ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

‘.....አንድ ጊዜ የመሳሪያው ርክክብ ቢፈፀም እኔም ስራዬን ጨረስኩ ማለት ነበር....። ግን ሳምሶናዊቱን እንዴት አድርጌ ከመንግስት ማሰረቅ እችል ይሆን?..... መንግስት ምን ሊያደርግ አስቦ ይሆን?..... ለነገሩ ምን አስጨነቀኝ ሌላ ፅፈው እንዲልኩልኝ ማስደረግ እየቻልኩ' በሚሉ ሀሳቦች መካከል እየዋዠቀች ቆየች።

“ዛሬ ሌላ የሆነ ችግር እንዳጋጠመሽ ታስታውቂያለሽ” አለች መንበረ ስራዋን ስትጨርስ።
ሰናይት ደንግጥ አለችና “ምን መስያለሁ ንገሪኝ እስኪ?”
“እኔንጃ ማታ ከመጣሽ ጀምሮ ዝም ብለሽ ብንን ብንን ትያለሽ..... በዛ ላይ ፊትሽ ራሱ በአንድ ቀን ጠቁሯል በአጠቃላይ ጤነኛ አትመስይም።”
ፈገግ ለማለት እየሞከረች “ስለመሰለሽ ነው እንጂ በጣም ደህና ነኝ።”
“እኔ ለክፉት ወይም ላሳቅቅሽ ፈልጌ አይደለም እንደሱ ያልኩሽ። ችግር ካለ እኔ ጋር ተደብቀሽ መቀመጥ ትችያለሽህ። ከፈለክሽም ቀን ቀን ተኝተሽ እየዋልሽ ማታ ማታ ወጣ ብለሽ መመለስ ትችያለሽ።”
በእውነተኛ ስሜቷ ነበር የምትነግራት።
ርህራሔዋ፤ አሳቢነቷና ግልፅነቷ ከመቼውም ገኖ ታየባት።
“በይ ብርድ እንዳይመታሽ እግርሽን አስገቢና ተኚ።” ያዘዘቻትን ፈፀመች ከሳጥኗ ጋቢ አውጥታ ስትደርብላት
“አረ..... ሙቀቱን አልችለውም አንቺው”
“አሞሻል ዝም ብለሽ ተኚ”
“መንበረ ሙች ካስፈለገኝ እነግርሻለሁ አንቺው።”
አንስታ አጣጠፈችውና “እሺ ራስጌሽ አድርጊው ስትፈልጊ ትጠቀሚበታለሽ።”
ተቀበለቻትና በጐን በኩል እያስቀመጠችው “በይ ተኚ” አለቻት።
በቀጣዩ ቀን ተኝታ አረፈደች። ከሰዓት በኋላ ወደ ፒየር የምትልካቸውን መልዕክቶች ጨራርሳ ሩዋንዳ አካባቢ ወደ ተከራየችው ቤቷ ተመለሰችና ምንም ያህል ደቂቃ ሳታባክን ገላዋን በመታጠብ ልብሶቿን ቀይራና ወፈር ባለ ሰማያዊ ቀለም ኘላስቲክ መያዣ ተጠቅልሎ በኘላስተር ዙሪያውን የታሸገ አነስተኛ እቃ ይዛ ወጣች።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ሽጉጧ እንዳይታይ በቀኝ ጎኗ በኩል እያስተካከለች ጉዞ ጀመረች፡፡ ማታ ላይ ወደ መንበረ ቤት ስትገባ በጥሩ ፈገግታ ተቀበለቻት፡፡ ዘወትር እንደምታደርገው ሁሉ ጫማዋን አውልቃ አልጋው ላይ ወጣች፡፡ ምሽቱን እየተጫወቱና እየተሳሳቁ አሳለፉት፡፡ ሊተኙ ሲሉ ሰናይት በዝግታ ሁለት ባለ አስር ብር ኖቶች አውጥታ ዘረጋችላት፡፡

መንበረ በትካዜ ስታያት ቆይታ "የምትሰጭኝ ገንዘብ ሰርቼ ያመጣሁት ሳይሆን አታልዬ የምቀማሽ መስሎኛል አሁንስ" አለች ለመቀበል ቅር እያላት፡፡

ሰናይት 'የምትሰሪው ስራማ ከምታገኚው ክፍያ በላይ መሆኑን ብታውቂ ኖሮ.....' ብላ አሰበችና

"ግድ የለሽም ባይሆን ሌላ ቀን ታልፊኛለሽ፡፡"

ምንም አማራጭ የሌለው ብቸኛ የእንጀራ መብያ መንገዷ ስለሆነ አጥብቃ አልተከራከረችም፡፡ ሰናይት ብሩን እንደሰጠቻት ቀን በኘላስቲክ መያዣ ጠቅልላ የያዘችውን እቃ እያወጣች "ይህንን ነገር ሰው በፍፁም የማይደርስበት ቦታ ደብቀሽ እንድታስቀምጪልኝ እፈልግ ነበር?"

"ምንድነው?"

"እቃ..... ለሌላ ሰው ምንም የማይጠቅም፡፡ ለኔ ግን በጣም አስፈላጊ የሆነ....."

"ምንም ችግር የለውም፡፡" ብላ ተቀበለቻት፡፡

ሌላ በፖስታ የታሸገ ደብዳቤም አወጣችና እየሰጠቻት "ይህንንም አብረሽ ታስቀምጪውና አንቺ ጋር መምጣቴን ድንገት አቋርጬ ለሶስት ቀናት ያህል ከጠፋሁ ፖስታውን ከፍተሽ ታነቢውና በውስጡ ያለውን ትዕዛዝ ካለ ፍራቻ ትፈፅሚያለሽ፡፡"

መንበረ በሀዘን እንዳቀረቀረች ተቀበለች፡፡

"ምነው ቅር አለሽ?"

"አይ..... አላለኝም፡፡" የውሸት ፈገግ ለማለት እየሞከረች፡፡ በውስጧ ግን 'ምን ዓይነት ሞኝ ናት?..... ድሮስ ቢሆን ማን ሽርሙጣ ቤት ገብቶ እስከመጨረሻው ድረስ መቅረት ይፈልጋልና' ሰናይት ከተናገረቻቸው መካከል አንዱ ሀረግ ደግሞ አቃጨለባት፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“.....መምጣቴን ድንገት አቋርጬ.....”
ቀጠለች ለራሷ መናገር ‘.....ይሄኔ ለባልነት መሆን የሚችል ጥሩ ሰው ተዋውቃ ይሆናል። አቤት ታድላ!’ አለች በቅናት።

ቀጣዩን ቀናቶች ብዙም ፋይዳ በሌላቸው እንቅስቃሴዎች ተከባ አሳለፈች።

የጦር መሳሪያውን የመረከቢያው ደብዳቤ ድጋሜ ተሰርቶ ከአንድ ቀን በኋላ እንደሚደርሳት የተገለፀላት ቢሆንም እስካሁን ድረስ ሳይመጣላት ሁለተኛው ቀን መጋመስ ጀመረ። ችግሩ ግን ከነሉዊስ ሳይሆን ገንዘብና እቃ የሚያስተላልፍላቸው ሰው ሊፈጠርበት በነበረው አደጋ ምክንያት ደንግጦ በመሰወሩ ምክንያት ነበር።

  

የማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ምዕራፍ 43

ሉዊስ እንደተበሳጨ ነበር ቢሮው የደረሰው። አጠቃላይ ሁኔታው ድብልቅልቁ የወጣበት መስሏል። ክራቫቱ ላልቶ ወደ ግራ ተንጋዷል፣ ኮቱ ተጨማዷል፣ ፀጉሩ ተንጨፍርሯል። ቢሮው እንደደረሰ ያንጠለጠለውን አነስተኛ ሰነድ መያዣ ሻንጣ ጠረጴዛ ላይ ወርውሮ ወደ ፒየር ቢሮ አመራ።

ፒየርም እንዳየው ኮምፒውተር ላይ የሚከውነውን ስራ አቁሞ "አው ሉዊስ..... ተንቀሳቃሽ ስልክ ላይ ላገኝህ ደጋግሜ የሞከርኩት ጥሪ የተሳካ አልነበረም።"
"አዎ..... ዘግቼው ስለነበር ነው።"
"ከሁለት ቀን ተኩል በላይ ወደ አሜሪካ ተጉዘህ ያደረከው ቆይታ ከእቅዳችን ውጪ ነበር። ምክንያቱ ምንድነው?"
"ድንገተኛ የሆነ ጥሪ ደርሶኝ ነው።"
"የሂድክበት ጉዳይ ተሳካ ታዲያ?"
"የአንድ ቢልየን ዶላር ኪሳራን አስከትሎ....."

"ምን!?"
ሉዊስ በዝምታ እያየው የጠረጴዛው ጠርዝ ላይ ተቀመጠ።
"ምንድነው የተጠፈረው አደጋ!?" አለ ፒየር ግራ ገብቶት።
"በኢትዮጵያ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው ኘሮጀክታችንን የሚያደናቅፉ ሀይሎች ተነሱብን።"
"እነማናቸው?"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“በአሜሪካ ውስጥ በጥቁሮች የተቋቋመ አንድ የወመኔ ቡድን”
“በጥቁሮች!?”
“አዎ.....።።”
“እንዴት ሊያውቁት ቻሉ?”
“ጉዳዩን በግልፅ ሊያሳውቀን የሚችል መረጃ ለማግኘት ብዙ ሞክሬ ነበር አልተሳካልኝም። አፍሪካን አንድ እናደርጋለን ብለው የሚቃዡ የጥቁሮች ስብስብ ተቋም ነው”
“ህጋዊ እውቅና አላቸው?”

“ይህ ነው የሚባል አይደለም። የገንዘብ ድጋፍ ለማሰባሰብ እና በምስራቅ አፍሪካ አካባቢ ሊፈጠሩ የሚችሉትን ቀውሶች ቀድሞ መቆጣጠር የሚያስችል ድጋፍን ለማሰባሰብ የጠሩት ሰላማዊ ሰልፍ መኖሩን እንደሰማሁ ጉዳዩ ከኛ ፕሮጀክት ጋር ተያያዥነት ይኖረው መሆኑን ለማጣራት ነበር የሄድኩት። እንደፈራሁትም አልቀረም ስለ እኛ እቅድ አንድ አይነት መረጃ ሳይደርሳቸው እንዳልቀረ ግን አውቄያለሁ። ” አለ ሉዊስ። ቀጠለ እያሰበ “.....ፕሮጀክታችንን ለማክሸፍ የሚያስችላቸውን ከፍተኛ የሆነ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ጥሪዎችን ለጥቁር አሜሪካውያኖች እየበተኑ ነው።”
“ ከቡድኑ ሀላፊዎች ጋር ተገናኝተህ ነበር?”
“ሌላው ችግር እሱ ነው። ማን እንደሆኑ አይወቁም። ቋሚ ቢሮ የላቸውም። የወደፊቱ እቅዳቸው ራሱ ለነጭ ህዝብ ህልውና ሳያሰጋ የሚቀር አይመስለኝም። በዛ ላይ ጥብቅ በሆነ ሚስጥር የተደራጁ ይመስለኛል።”
“እና አንድ ቢልየን ዶላሩን ለምንድነው ለመክፈል የተጠየከው?.....” መልስ ሳያገኝ ራሱ ቀጠለ ፒየር “.....እንቅስቃሴያችንን እንድናቆም ጉቦ ክፈለን ብለው አስጠየቁህ?”
“ቢሆንማ ጥሩ ነበር.....”
“ሌላ ምን ሊሆን ይችላል?”
“በርካታ የጥቁር ተወላጆች ሆሊውድ ውስጥ ያሉ ትልልቅ የኪነ-ጥበብ ሰዎቻቸው ሳይቀሩ ድርጅቱ ላቀረበው የእርዳታ ጥያቄ ድጋፍ ለመስጠት ፈቃደኛ ሆነዋል። በተለይም በዋሺንግተን፣ በቺካጐና ኒውዮርክ ውስጥ ከሚኖሩት ውስጥ አብዛኞቹ .....ማለት ይቻላል።”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ፒየር በንዴት ጠረጴዛው ላይ አቀረቀረ፡፡ ጥቂት ቆየናም “የፈለገው ያህል ቢራወጡ ሊያቆሙን አይችሉም!”
“እሱ እንዳይሆን ነው ክፍያውን መስጠት ግድ የሆነው.....” ቀጠለ ሉዊስ “.....የነዛ ሱሰኛ ባሪያዎችን ህሊና ወደፊት ላሉት አስራ አምስት ቀናት ያህል መስረቁ በጣም ጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል አመንኩ፡፡”

“እንዴት?”
“በዋሺንግተን ቺካጐና ኒውዮርክ ከተማ ውስጥ ያሉትን ህገ-ወጥ የአሺሽ መሸጫ ሱቆችና ማጨሻ ቤቶችን በጠቅላላ በገንዘብ በመያዝ ነፃ አገልግሎትን ለአጫሾች በፈለጉት መጠን እንዲሰጧቸው በማድረግ፡፡”
“ኮኬይን እና ሄሮይናቸውን ?”

“አዎ..... አየህ እነዛ ደደብ ጥቁሮች አሸሹን በነፃ አግኝተው ማጤስ የሚችሉበትን መንገድ ከፈጠርንላቸው መላ ትኩረታቸው ወደዛ ይሰረቅና ሙሉ ጊዜያቸውን በሱ ላይ ያሳልፋሉ፡፡ በተለይ ለድጋፍ የተጠራው ሰላማዊ ሰልፍ ላይ እንዳይገኙ ለማድረግ ነው፡፡ እናም በድርጅቱ የተደረገላቸውን ጥሪ የሚያስታውሱበት ሽራፊ ሰከንድ ስለማትኖራቸው አንድም ባሪያ ከጐናቸው አይገኝም፡፡” አለ ሉዊስ፡፡
“አንድ ቢልየን ዶላር.... ለአስራ አምስት ቀን.....” ፒየር በቁጭት ቀጠለ “.....ለምንድነው አስራ አምስት ቀን እንዲሆን የወሰንከው ቀኑን ብታሳጥረው ኖሮ ቀላል የማይሰኝ ገንዘብ ማዳን እንችል ነበር፡፡”
“በጉዞ ላይ ያሉትን የጦር መሳሪያዎች እስከዛ ድረስ ኢትዮጵያ ተጠቃለው ሊገቡ እንደሚችሉ ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡ መሳሪያዎቹ ደግሞ አንዴ የህዝቡ እጅ እንዲደርሱ ከተደረገ የዛ ቡድን እርምጃ ተዓምር ቢፈጠር እንኳ እቅዳችን ማክሸፍ አያስችለውም፡፡ በኢትዮጵያ ምድር የሩዋንዳንና ቡሩንዲ ካለበዚያም የሶማሊያ የእርስ በእርስ ጦርነቱም መጀመር ካለ አንዳች እንቅፋት ተከዋኝ ይሆናል፡፡ ለኛም የእቅዳችን ፍፃሜ ይሆናል፡፡” አለ ሉዊስ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“ጥሩ ነው ዘዴው.....” ቀጠለ “ታዲያ የአንድ ቢልየን ዶላሩን ክፍያ ለማነው ሰጥተህ የመጣኸው?”
“በዋሺንግተን ቺካጐና ኒውዮርክ ውስጥ ህገ-ወይ የአሺሽ መቸብቸቢያና ማጨሻ ቤቶችን በበላይነት ከሚቆጣጠሩት ማፊያዎች መካከል ጥቁሮችን የሚያስተዳድር አንድ ታዋቂ ሰው አለ፡፡”
“ምንድነው ቀለሙ?”

“ጥቁር አሜሪካዊ.... ከመላው የዩናይትድስቴትስ ግዛት አንስቶ በደቡብ አሜሪካና አውሮፓ ድረስ ያሻውን መፈፀም የሚችል አሸባሪም ነው፡፡ በኢንተር ፖልና በኤፍ.ቢ.አይ መዝገብ ላይ ሰፍረው ከሚታደኑት ቁጥር አንድ ተፈላጊ ወንጀለኞች ተርታ ውስጥ ገብቷል በዚህ ወቅት ላይ፡፡”
“በራሳቸው ሰው መጠቀምህ ጥሩ ነው፡፡” አለና ጥቂት ደቂቃዎች ቆይቶ “እኔም አንተ የሂድክበት ሰዓት ላይ ኢትዮጵያ ካሉት ሰዎቻችን አስደንጋጭ ዜና ደረሰኝ፡፡”
“ከሰናይት?”
“እና ገንዘብ ከሚያስተላለፍልን ሰውዬያችን”
“ምንድነው?” አለ በነገሩ እየተሳበ፡፡
“ለመሳሪያው መረከቢያ የተላከው ሰነድ ከነሻንጣው ተወሰደ፡፡”

ሉዊስ ፊቱ እንደ ሬሳ ገረጣ፡፡ ለደቂቃዎች እንዳፈጠጠበት፡፡ ቆየና
“መጀመሪያ ላይ በመንግስት ሰዎች ነበር... በዛው ዕለት ምሽት በድጋሜ በተላከልን ዘገባ ደግሞ ባልታወቁ ግለሰቦች በረቀቀ መንገድ ከመንግስት መሰረቁ ተነገረን፡፡”
“አስደንጋጭ ነው!.....ለመሆኑ የሰረቁት ግለሰቦች በአሜሪካ ውስጥ እንቅስቃሴ ከጀመሩን ሰዎች ጋር ግንኙነት ያላቸው ይመስልሀል!?” ሉዊስ ጠየቀ

“እንዳንተው ነኝ ምንም መልስ መስጠት አልችልም፡፡” አለ ፒየር በቀዝቃዛ ስሜት፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“የፈጣሪ ያለህ.....” ሉዊስ ድንጋጤው አልበረደለትም። ቀጠለ “ይህ ሁኔታ ወዳላሳብነው ውስብስብ አቅጣጫ እያመራብን ይመስለኛል።”
“ሁሉም ነገር ቅድም እንዳልከው የሚወሰነው የጦር መሳሪያዎቹ የኢትዮጵያን ድንበር መሻገር ሲችሉ ብቻ ነው። ለሱ ደግሞ ከስድስት ቀን ያነሰም ጊዜ ሊበቃው ይችላል።”
“ታዲያ ለሰናይት ደግመህ የመረከቢያ ደብዳቤውን ላክላት?” ጠየቀ ሉዊስ።

“መጀመሪያ የተፈጠረውን ነገር ለአንተ ማሳወቅ ስለነበረብኝ አላኩላትም። ደጋግሜ በስልክ ላገኝህ የሞከርኩት ለዚሁ ጉዳይ ነበር። ዛሬ ተጠናቆ ነገ ጠዋት ላይ መላክ ይቻላል።”
“ነገን ማለፍ የለበትም ጊዜ የለም.....”

“ይኸውና ድጋሜ መዘጋጀት ጀምሯል።” ብሎ ያለቁለትን ወረቀቶች አንስቶ አሳየው።

  

የማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ምዕራፍ 44

በደቡብ አቅጣጫ በሚገኘው የቺካጐ ግዛት ውስጥ በተገነባው ሃያ ፎቆች ባሉት አንድ ህንፃ አናት ላይ ሶስት ጥቁር አሜሪካውያኖች ከሁለት ኢትዮጵያውያኖች ጋር ተቀምጠው ሀሳቦችን በማላተም ወደ ሚፈልጉት አንድ ነጥብ ላይ ለመድረስ መወያየት ከጀመሩ ሁለት ሰዓት ሆኗቸዋል፡፡

ጊዜው ከምሽቱ ሶስት ሰዓት ብሏል፡፡

የሶስቱ አሜሪካውያኖች ሰዎች እድሜ ከሃምሳዎቹ እስከ ስልሳ ባሉት ዓመታት መካከል ነው፡፡ ሲጃራ እያጨሰ ያለው ሰው ከመካከላቸው ባለው ነጭ ጠረጴዛ ላይ ያሉትንና ከኢትዮጵያ የተላኩትን ወረቀቶች እያገላበጠ ቆየና "ጉዳዩን ለማስፈፀም ቢያንስ ሁለት መቶ ሚልየን ዶላር እንደሚያስፈልግ ተነግሮናል" አለ በተለይ ወደ ኢትዮጵያውያኑ እያየ፡፡

በከተማው ውስጥ በሚገኝ አንድ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካ ሌክቸር የሆኑት ፕሮፌሰር ፍሬሰንበት ሀይሉ መነፅራቸውን እያስተካከሉ" የሚከፈለውን ዋጋ ሁሉ ከፍለን ይህንን አደገኛ ጥፋት ካላቆምን ለዛ ሁሉ ዓመታት ስንደክምበት የኖርነው እቅዳችን ትርጉም አልባ ሆኖ ነው የሚቀረው" አሉ

ከጎናቸው የነበረውና ፔንታጎን ውስጥ በከፍተኛ የስልጣን ደረጃ የሚሰራው ዶክተር ስዩም ሀሳባቸውን በመደገፍ "በቢሮዬ በኩል የሚደርሱኝ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ምስራቅ አፍሪካ ላይ የሚነሱትን ብጥብጦች በፍጥነት ማክሸፍ ካልተቻለ የሶተኛው የዓለም ጦርነት መቀስቀሱ በፍፁም የማይቀር መሆኑን ነው፡፡ ይህ እየተፈራ ያለው ጦርነት ከተቀሰቀሰ ከሁሉም በላይ አፍሪካና ህዝቦቿ ናቸው

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

እንዳያንሰራሩ ሆነው የሚጠፉት። የአፍሪካን የውስጥ ችግሮች መፍታት እንደዚህ እልህ አስጨራሽ ሆኖብን እያየን ማንም የማይረባ ተቋም ሌላ ተጨማሪ ችግር ይዞብን ሲመጣ በዝምታ ማየት የለብንም። " አለ
"ዶክተር ችግሩ ይህ ሁለት መቶ ሚልየን ዶላር.....በዚህ ጥቂት ቀናት ውስጥ ከየት ሊመጣ ይችላል?" አለ ሌላኛው ጥቁር አሜሪካዊ ሁለተኛው ሰው።
"በቅስቀሳው ምን ያህል ገንዘብ መሰብሰብ ቻለ?" ጠየቀ ሶስተኛው።
"ሃምሳ ሁለት ሚልየን ዶላር....." ሲጃራ የያዘው ሰው መለሰና ተነስቶ ከነሱም ብዙ ወደ ማይርቀው የህንፃው ዳርቻ በማምራት ቁልቁል በመብራት ያሸበረቀውን ጎዳና እያየ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ማሰብ ቀጠለ።

ዋና መሪያቸው እሱ ነበር። ስሙ ጆንስ ቴይለር ይባላል። በፖለቲካ ሳይንስ የፒ.ኤች.ዲ. ዲግሪውን ከያዘ ሰባት ዓመት ሆኖታል። "አፍሮኢዝም" የሚል መጠሪያ የሰጡትን የህቡዕ ፓርቲ በድብቅ በአሜሪካ ውስጥ አደራጅቶ መምራት ከጀመረ ሃያ ሰባት ዓመት ሆኖታል። በዛን ጊዜ እድሜው ገና ሃያ ዘጠኝ ዓመት ነበር።

የመጀመሪያ ዲግሪውን አግኝቶ ወደ ስራው ዓለም ለመግባት ባደረገው ጥረት ውስጥ ጥቁርነቱ እንደ ጎዶሎነት ተቆጥሮበት በዘረኝነት መድሎ ተገፍቶ ተስፋ በቆረጠ ወቅት ላይ እያለ በአንድ ጓደኛው በኩል "አፍሮኢዝም" የሚል ስያሜን የያዘና መላው አፍሪካን ጨምሮ በመላው ዓለም ላይ ተበትነው ያሉትን ጥቁር ህዝቦችን አሰባስቦ መሰረታቸው ወደ ተገኘበት አፍሪካ በመመለስ እንዴት ወደ አንድነት ግዛት ማምጣት እንደሚቻል የሚተነትነው የፖለቲካ ንድፈ ሀሳብ እጁ የገባው።

በርካታ ጊዜ ደጋግሞ ካነበበው በኋላ አዲስ በሆነው ንድፈ ሀሳብ በእጅጉ ተሳበ። ወደ ተግባርም ሊለውጠው ወሰኖ ተነሳ። በመጀመሪያዎቹ ወቅቶች ላይ ብዙ ጥቁር ጓደኞቹ ሳይቀር ሀሳቡን በመቃወማቸው ለማሳመን በእጅጉ ተቸግሮ ነበር።

በዚሁ ሁኔታ ውስጥ ተስፋ ሳይቆርጥ ባደረገው ትግል ሊያፈራቸው የቻላቸውን ጥቂት ሰዎች አሰባስቦ ፓርቲውን በድብቅ መሰረተ። የሂደቱን የመጨረሻ ውጤት ለማየት ትዕግስት

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

አስጨራሹን የትውልድ ጥበቃን ማድረግ እንዳለበት ቢያምንም ባለፉት ሃያ አምስት ዓመታት ውስጥ ግን ችግሞቹን በመላው የዓለም ግዛት ላይ መትከል ችሏል። ደጋፊ አባላቶቹንም ከመቶ ሺዎች ወደ ሚልየን አህዞች አድገዋል።

ጆንስ ከህንፃው ጫፍ ፓርቲውን አብረውት ወደሚመሩበት ሁለት ሰዎች ተመለሰና እልህ በተናነቀው ስሜት "እኛ ጥቁሮች ዘርና ቀለም ሳንለይ በመልካም ለቀረበን ሁሉ ወንድም መሆን የሚቻለንን ያህል ለአጥፊዎቻችን ምህረት የለሽ ጠላትም መሆን እንደሚቻለን ማሳየት አለብን።" አለ።

በዚህ ጊዜ አራተኛው ባልደረባቸው የህንፃው አናት ላይ የሚያስወጣውን በር በመክፈት ስድስት ጠባቂዎቻቸውን አልፎ ሲመጣ አዩት።

በእድሜው ወደ አርባዎቹ መጀመሪያ ላይ ይሆናል። ግዙፍ ቁመናና አስፈሪ የፊት ገፅታ አለው። ሲያያቸው ከመቼውም ጊዜ በተለየ ሁኔታ የፊቱ ገፅታ በፈገግታ ደምቆ በራ።
አጠገባቸው ደረሰና "እንዴት ናችሁ..... ወንድሞች?" አላቸው ሁሉንም በአንድነት።
ቀጠለ "ችግራችን እልባት አግኝቷል!"

"ምን ዓይነት?" ፕሮፌሰሩ መነፅራቸውን እያወለቁ ጠየቁ።
ቀጠለ ካርል ".....በሚደነቅ ሁኔታ የምንፈልገው ድርጅት ራሱ የአንድ ቢልየን ዶላር ክፍያ ያለውን ስራ አምጥቶ ሰጠኝ" አለ።
ሶስቱ አሜሪካውያኖች በተዘበራረቀ ስሜት ተያዩና ወደሱ እያፈጠጡ "ምን አድርግ ብሎ ሰጠህ?" ጆንስ ረጋ ባለ ሁኔታ ጠየቀው።
ካርል ከሉዊስ ከራሱ ጋር ተገናኝቶ የተቀበለውን ስራ ነገራቸው።
"ነጮቹ አፍሪካን ሰላም ለመንሳት ሲሉ የማይከፍሉት መስዋዕት የለም ማለት ነው!?" ዶክተሩ በንዴትና በሲቃ ቃላት ተናገረ።
"ክፍያውስ?"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“ከአንድ ሰዓት በፊት ወደ ባንክ ሂሳቤ ገቢ ተደርጓል፡፡” እኔም ክፍያው ገቢ እስኪሆንና እርግጠኛ እስክን ድረስ ነበር ሳልነግራቹ ለመጠበቅ የተገደድኩት፡፡ ”
“በራሱ ገንዘብ ስራችንን መቀጠል እንችላለና.....” አለ ጆንስ፡፡

“በሚገባ” ካርል መለሰ፡፡ ካርል በዋሺግንተን በቺካጐና በኒውዮርክ ግዛቶች ውስጥ በአሺሽና በጦር መሳሪያ ዝውውር ህገ-ወጥ ንግድ ገናና የሆነ ዝና ያለውና ለመንግስት ተቆጣጣሪ አካላቶች የመናፍስት ተፈጥሮ ያለው ይመስል ሊይዙት ያልቻሉት ፈጣንና ብልጥ የሆነ ግለሰብ ነው፡፡

“አፍሮኢዝም” በተባለው ፓርቲ አባል ሆኖ መስራት ከጀመረ ሶስት ዓመት ሆኖታል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከፓርቲው አጋሮቹ እየተደረገለት ባለው ገለፃ የአሺሽ ንግድ በአሜሪካ ውስጥም ይሁን ከአሜሪካ ውጭ ባሉት አገሮች ከነጮቹ ይልቅ ጥቁር ወንድሞቹን በስፋት እያጠቃ ያለ በመሆኑና ለወደፊቱ የፓርቲው ግብ ትልቅ እንቅፋት ፈጣሪ በመሆኑ የንግድ ሙያውን በሌላ እንዲለውጥ ለማስደረግ ሀሳቦችን መሰንዘር ከጀመሩ ሰንብተዋል፡፡

እራሱም በጉዳዩ ላይ እያመነበት ስለመጣ በከፍተኛ ደረጃ ያካሂድ የነበረውን እንቅስቃሴ በእጅጉ ቀንሷል፡፡ በአመዛኙም ወደ ማቆሙ አዘንብሎ በርካታ ድርጅቶች ውስጥ አክሲዮን መግዛት ጀምሮ ነበር፡፡ ስሙና ዝናው ግን ከበፊት ደረጃው ገና ዝቅ አላለበትም፡፡ ሉዊስም ህንን ሰው በአካል አግኝቶ ለማነጋገር እልሀ አስጨራሽ የነበረ ስምምነቶችን መካከል ላይ ካሉ አገናኝ ደላሎች ጋር የፈፀመ ሲሆን ቀላል ያልነበረም ገንዘብ ከስክሷል፡፡ ከባድ የነበረው ግን አመኔታ አግኝቶ መገናኘቱ ሲሆን መጨረሻ ላይ ተሳክቶለታል፡፡ ያላወቀው ትልቁ ሚስጥር ግን ይህ ሰው «አፍሮኢዝም» ለተባለው የጥቁሮች ነፃ አውጪ ተቋም ዋና አባል መሆኑን ነበር፡፡

“የስራ ክፍፍላችን ይነገረንና ብቃት ያላቸው አባሎችን ይዘን እንሰማራ፡፡” አለ ዋልተር በሲቃ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

የ«አፍሮኢዝም» የመጀመሪያ መስራች የሆነው ጆንስ ሌላ ሲጀራ ለኮሰና "በአንተ የሚታቀፈው ቡድን አንድ በቀጥታ ወደ ፈረንሳይ ያምራ" አለው ወደ ዋልተር እያየ፡፡
"በጣም ደስ ይለኛል..... በዛች ቅድስት አገር ላይ ይህን ሁሉ የሚያደርገውን ሰውዬ በአካል ላገኘውና ልቀጣው እፈልጋለሁ!"
"ስሜታዊ አትሁን፡፡ ጥቂት ክፍተት ጥለህለት ከቀደመህ ራስህን አመድ ያደርግሀል" አለው ጆንስ በእርጋታ፡፡
"ግዴለም እሱን በጊዜው እናየዋለን፡፡....."
ወደ ሁለተኛው ሰው ዞረናም " ፒተር የአንተ ስራ የሚከብድ ሊሆን ይችላል፡፡ በውቅያኖስ ላይ ያሉትን መሳሪያ የጫኑ መርከቦችን ማደን ነው፡፡"
"ችግር የለውም፡፡ በአሜሪካ ባህር ሀይል ውስጥ ለአስራ አምስት ዓመት ማገልገሌን አትርሳ፡፡ ሌላው ምርጡ አጋጣሚ በቅርቡ ሳወዲ አረቢያ ውስጥ ለሚገኘው የአሜሪካ ጦር ሀይል ተመድበው የተላኩ የራሳችን አባሎች ስላሉን ዛሬውኑ አገኛቸውና ምን ሊረዱን እንደሚችሉ አነጋግራቸዋለሁ፡፡ ስራው አስቸጋሪ እንደማይሆን ተስፋ አለኝ፡፡" አለ በልበ ሙሉነት፡፡

"በኔ የሚመራው ቡድን ሶስት ወደ ኢትዮጵያ ነው የሚጓዘው፡፡"
ካርል ማርጐት "እኔስ?" ጠየቀ፡፡
"አንተ ገንዘቡን በማምጣት በኩል የሰራኸው ስራ ከሁላችንም በላይ ያደርግሀል፡፡ ምክንያቱም ገንዘቡ ባይገኝ ኖሮ በጣም ከባድ ይሆንብን ነበር፡፡ በሁለተኛው መልኩ ለደህንነት በማያመቹ ቦታዎች ላይ አሰርተንህ እንድናጣህ አንፈልግም፡፡ አንተን ለመያዝና ለመግደል እግረ መንገዱን ስልጣን ለማግኘት የሚፈልግህ የፕላኔታችን ፖሊስ ሁሉም ነው፡፡ ይህ ማለት ግን ሀላፊነት የለብህም አይደለም፡፡ በማዕከላዊነት እዚሁ ትቀመጥና ከሶስቱም ቡድኖች ለሚላክልህ የአቅም ድጋፍ ጥያቄ ምላሽ ትሰጣለህ፡፡ እንዲሁም በውቅያኖሶቹ ላይ ለሚሰራው ስራ ከዚህ ሆነህ አስፈላጊውን ሁሉ ትከውናለህ፡፡" አለው ጆንስ፡፡

"የኔ ቡድን ዛሬውኑ ወደ ፈረንሳይ በረራ ያድርጉዋ?" ጠየቀ ዋልተር፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“አዎ....በዘገየን ቁጥር ሁሉ ሁኔታዎች እየከበዱና እየተወሳሰቡ ሊሄዱብን ይችላሉ፡፡ ሁላችንም አሁኑኑ እንነሳ” አለ ጆንስ፡፡ ከዛም ወደ ኢትዮጵያውኑ ፕሮፌሰር እና ዶክተር እያየ “እናንተ ከኔ ጋር አዲስ አበባ ብትሄዱ ብዙ ነገር ታግዙኝ ነበር፡፡ ግን እዛ ስትገቡ የአገራቹ መንግስት ከያዛችሁ ወደ ወህኒ ያወርዳችኋል፡፡ ስለዚህ እዚሁ ሆናችሁ በሌላ በሌላ ስራ ትረዱናላችሁ፡፡”

ሁሉም በወንድማማች ስሜት ተቃቀፉና ለሚጠብቃቸው ጦርነት አብሮዋቸው የሚጓዘውን አባል ወደ ማቀናጀት ተመለሱ፡፡

  

የማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

ምዕራፍ 45

ዋናው ቢሮውን ብራስልስ ላይ ያደረገውና «የዓለም ዓቀፉ የግጭት ጥናት ተቋም» ወደ አስፈሪ ብጥብጥ እና ትርምስ እያመራች ስላለችው ኢትየጵያ በድህረ-ገፁ ላይ እና በሚያሳትማቸው ወቅታዊ የጥናት ውጤት መፅኤቶች እና ጋዜጦች ላይ ተደጋጋሚ ፅሁፎች ማቅረብ ጀመረ::

በጉልህ እየተፃፉ መውጣት የጀመሩት ጥናቶች «በፈንጅ ላይ የቆመች አገር ኢትዮጵያ!» በሚል ርዕስ ስር ስለ አገሪቷ ያወጣቸው ፅሁፎች ሁለት አይነት ምልከታን ለዓለም አቀፉ ህብረተሰብ የሰጠ ሲሆን በዚህ የአፍሪካ ቀንድ ክልል ላይ ይነሳል ተብሎ ከተገመተው አደገኛ አገር አቀፍ ብጥብጥ በስተጀርባ የማይነጥፍ ጥቅም እናገኛለን ብለው ያቀዱ በርካታ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ለግጭቱ ፈጥኖ መጀመር የሚሆነውን የማቀጣጠያና የማገዶ ሀሳብና ቁሳቁስ በስውር እና በይፋ እያቀበሉ ግጭቱን አኩብኩበው መጠባበቅ ጀመሩ::

ሁኔታው ለ«ሉዊስ ወኪሎች» ተቋም በድብቅ እርዳታን ካደረጉለት መንግስታት እና ድርጅቶች እንዲሁም ግለሰቦች አመኔታን እና ምስጋናን ያተረፈለት ሲሆን ግጭቱን ለማባባስና ይፈጠራል ተብሎ የታሰበውን የእርስ በእርስ ጦርነት አይቀሬ ለማድረግ ከዚህ ቀደም በሊዊስ ለፕሮጀክቱ ማስፈፀሚያ የገንዘብ ጥያቄ ቀርቦላቸው በወቅቱ ሀሳቡን ያላመኑበት ሁሉ የብራስልሱ ቢሮ ከሰጠው መግለጫ በኋላ ከተጠየቁት በላይ የሆነ ገንዘብን ለሉዊስ ተቋም በስውር መለገስ ጀመሩ::

ይህም ሉዊስ አሜሪካ ሄዶ እዛ ያሉ ጥቁሮች ሊያደርጉ ያቀዱትን የተቃውሞ ሰልፍ እና የሱን እቅድ ለማክሸፊያነት የሚያስፈልገውን ገንዘብ ሊያሰባስቡ ያቀዱትን ስራ ለማሰናከል ለ«ማፊያዎች» ከፍሎ ከመጣውን አንድ ቢልየን ዶላር በሶስት እጥፍ የላቀ ገቢ ማግኘት አስቻለው::

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

አሁን ለሊዊስ ሁሉም ነገር ከአቀደው በላይ በሆነ ውጤት ወደ ማብቃቱ እየተቃረበ መጣ። በግዙፍ መርከቦች የተጫኑት የጦር መሳሪያዎች የአፍሪካ ቀንድ ላይ ሲራገፉ የሚፈጠረውን ወጤት እጁን አጣጥፎ በመቀመጥ እያየ ይዝናናል።

አብነት ሲኤምሲ ተደብቆ እንዲቀመጥ የተደረገው ዲፕሎማቲክ ቤት ሆኖ እዛ ካለው ጓደኛው ጋር ከአሜሪካ ዛሬ ይገባሉ የተባሉትን ሰዎች በመጠባበቅ ላይ እያለ ስልክ ተደወለና የሚመጡት ነገ እንደሆነ ተነገረው። እሱም ቤት ተቀምጦ መዋል ስላልፈለገ ወጣና ወደ መገናኛ ታክሲ ተሳፍሮ መጓዝ ጀመረ። በሚኒባሱ ውስጥ ያሉት ተሳፋሪዎች በጠቅላላ ሰሞኑን በመላው ከተማዋ ውስጥ እየተካሄደ ስላለው አፈሳ ነበር የሚያወሩት።

ዩኒቨርሲቲዎች እና የሁለተኛ ደረጃ ትምርት ቤቶች እንደተዘጉ ናቸው። መላው የከተማዋ ነዋሪም ተማሪዎቹ ያነሷቸው ጥያቄዎች አግባብ መሆናቸውን በመግለፅ ሙሉ ድጋፍ እየሰጡ ሲሆን መንግስትም ሁኔታውን ለማፈን በየአቅጣጫው አፈሳውን አጧጡፎታል። ከየስፍራው እየተጫነ ያለው የህብረተሰብ ክፍል ወደ ሰንዳፋ፤ ዝዋይ፤ ሽዋሮቢት እንዲሁም በከተማው ውስጥ ባሉና ለማሰር አመቺ በሆኑ ማጎሪያዎች እየተጋዘ ሲሆን ከሚታፈሱት መካከል ወዴት እንደሚወሰዱ የማይታወቁ እና በዛው ደብዛቸው ጠፍቶ እንዲቀር የሚደረጉ በርካቶች ነበሩ።

መንግስት ግን ምንም እንዳልተፈጠረ በማስመሰል ከተማዋ ውስጥ የሚታዩት አንዳንድ ክስተቶች በ«አደገኛ ቦዘኔዎች» ስብስብ አማካኝነት የተፈጠረ ተራ ክስተት በመሆኑ «በማያዳግም ሁኔታ» ችግሮችን በቁጥጥር ስር ማድረጉን ባገጠጠ ሀሰት በየ-መገናኛ ብዙሀኑ በአሰልቺ ሁኔታ መወትወቱን ቀጥሎበታል።

አብነት የመገናኛ አደባባዩን በመሻገር ከተሳፈረበት ታክሲ ወረደና በስተግራ በኩል ወደሚገኝ አንድ ካፌቴሪያ ገብቶ ቡና በማዘዝ ሲጋራ አውጥቶ ለኮሰ። በተስተናጋጆች በተሞላው ጠረጴዛ መካከል ከአንዱ ወደ ሌላው እያለፈ የተቀላጠፈ መስተንግዶ የሚሰጠው ሽምሱ ለአብነት የታዘዘውን ቡና እያቀረበ ጠረጴዛውን ለሚጋራው ሌላ ተስተናጋጅ "ዛሬ ንዴት ዱዳ አድርጎሀል..... ምንድነው የሆንከው?" አለው በሻይ እና በምሳ ሰዓት አዘውትሮ እየመጣ ለሚጠቀም አንድ የአከባቢው የመንግስት መስራቤት ሰራተኛ። ጎልማሳው ሰውዬ አቀርቅሮ እያነበበ የነበረውን አዲስ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ዘመን ጋዜጣ እየወረወረ “እንዴት መንግስትን የሚያህል አካል ዘልአለም ውሸት ለህዝብ ይናገራል?..... ህዝብ ደደብ ይመስላቸዋል እንዴ?” አለ ለማን አንደሚናገር እንኳ ሳይለይ
ሽምሱ እየሳቀበት “በጋዜጣው ነው የተበሳጨኸው?”

“ይሄ ዜና በቀጥታ የኔን መስራቤት እንደውም የኔን ቢሮ የሚመለከት ዘገባ ነው የያዘው:: ግን እንዳለ ውሸት ነው:: ” አለ
“ግርምሽ ሞኙ..... ማወቅ ያለብህ ዋና ነገርኮ መንግስት የሚያሳትማቸውን ጋዜጣና መፅኤት ስታነብ የተቀባበለ ሽጉጥ ጠረጴዛህ ላይ አስቀምጠህ መሆን አለበት::”
“ለምን?” አለው አብነት
“በምታነበው ውሸት ተበሳጭተህ ከምታብድ ወይም መንግስት አንተ ያላልከውን በአንተ ስም እየፃፈ ስምህን በህዝብ ከሚያስጠፋ ይሻልሀል አንተ ራስህን በጥይት ብታጠፋ ” ብሎት በግርማ ብስጭት እየሳቀ ወደ ሌላ ጠረጴዛ አለፈ:: እዛም ሄዶ ሁለት ሆነው በመቀመጥ ሳፊ ወተት እየጠጡ ከነበሩ ሰዎች ጋር መጨቃጨቅ ቀጠለ:: ሁለቱምን ሰዎች አዲስ አበባ ከገቡበት ወቅት ጀምሮ ያውቃቸዋል::

ሁለቱም ሰዎች በ1983ዓ.ም የወያኔ ሰራዊት አገሪቷን ሲቆጣጠር ከበረሃ የገቡ «ታጋዮች» ሲሆኑ ከዛ ወቅት ጀምሮ በአከባቢው ላይ ባሉ የመንግስት መስራቤቶች ውስጥ ያለ እውቅትና ችሎታቸው በከፍተኛ ሀላፊነት ደረጃ ላይ በመስራት ላይ ይገኛሉ::
ሽምሱ በግብር ክፍያ ከስሮ ጫት ቤቱን እስከተዘጋበት ጊዜ ድረስ እሱ ጋር እየመጡ በማይከፈል ዱቤ ሲቅሙ ኖረዋል:: ከዛም በአካባቢው የተለያዩ ምግብ ቤቶች ውስጥ እየተዘዋወረ በአስተናጋጅነት ሲሰራ እነሱም ምግብ ቤቶችን ሲያዳርሱ፤ ምሽት ላይም ለቢራ ጭለጣ ሲመጡ ከረጅም አመታት ጀምሮ ያውቃቸዋል::
አንደኛው ሰው የሆነ ነገር ሲናገረውና ጓደኛው ጥርሱን እየገለፈጠ ሲስቅበት አብነት አየ:: ምን እንዳለው ግን አልተሰማውም::

ሽምሱ ፊቱን ቅጭም አድርጎ ወገቡን እየያዘ “ እናንተም ሆናቹ አለቆቻቹ ከጫካ ስትገቡ የማናውቃቹ መሰላቹ..... እ? ንገረኝ ካልክ እነግርሀለው..... እሺ..... ኩሽና ተሰቅሎ በጭስ የደረቀ ጨው የሌለው ቋንጣ የሚመስል ገጣባ አይደል እንዴ ትመስሉ የነበሩት.....? አሁንማ በምግብ እና በድራፍ ብዛት መኳንንት መስላችኋል:: የሚያሳዝነው....”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ሁለቱንም በየተራ እያየ ቀጠለ "... ገላቹ ምንም ቢያምርበት ታዲያ ህሊናቹና አመለካከታቹ ግን ቋንጣ እንደሆነ ቀርቷል። የምግብ ብዛት መኳንንት ያስመስል ይሆናል እንጂ ሊቃውንት አያደርግም።!" ብሎዋቸው ትቶዋቸው ሄደ።

ቀስ እያለ አካባቢው የፌደራል ፖሊስ አባላቶችን በጫኑ ላንድ ክሩዘሮች መጥለቅለቅ ጀመረ። እነዚህ የፌደራል ፖሊስ ልብስ እንዲለብሱ ከተደረጉት መካከል አብዛኞቹ ከመከላከያ ሰራዊት ውስጥ ተዘዋውረው ፖሊስ በመምሰል እንዲሰሩ የታዘዙ ጭምር ነበሩበት። አብዛኞቹ ገፅታቸው መጣጣ ሲሆን ከሚጠብቁት ፓርቲና ከመሪዎቻቸው ውጪ አንድም ነገር እንዲያስቡ ስለማይፈቀድላቸው፤ እንዲሁም ስለ ህይወት፤ ስለ ሰው ልጅ ክቡርነት እና ልዕልና ያላቸው የተምታታ እውቀትና አመለካከት ሳቢያ ሁሉም ፊታቸው ላይ የኑሮ ቁጣ፤ ጥላቻ፤ ተስፋ የለሽነት፤ አይረቤነት ይታይባቸዋል። አይኖቻቸው ድልህ በርበሬ መስለው ሰው ላይ ደም እንደጠማው አውሬ ይጉረጠረጣሉ። ሁሉም ሙሉ ትጥቅ ታጥቀዋል።

ወድያው ከርቀት የማያቋርጥና የቅብብሎሽ የተቃውሞ የመኪና ክላክስ ጩኸት እየተስፋፋ መጣ። ለዚህ ተቃውሞ መነሻ ምክንያት የሆነው መገናኛ ከመድረሱ በፊት ሾላ ገበያ እየተባለ ወደ ሚጠራው አካባቢ በሚያደርሰው መንገድ ላይ በሚገኝ አንድ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የተፈጠረው ክስተት ነበር።
የሰባተኛ ኤ ክፍል ተማሪዎች አራተኛ ክፍለ ጊዜ እንደተጀመረ አማርኛ የሚያስተምሯቸው መምህር ወደ ክፍል ገቡና በስጭት በስጭት እያሉ "ትላንት እንድትፅፉ የታዘዛቹትን ግጥም ፅፋቹ መጣቹ!?" ጠየቁ በቁጣ የአብዛኛው ተማሪ ምላሽ ዝምታ ነበር። እያንዳንዱን ተማሪ እያስወጡ መፃፍ አልቻልንም ያሉትን እጃቸውን በአለንጋ ገርፈው እያንበረከኩ ተራው አንድ የአስራ አንድ አመት ተማሪ ጋር ደረሰ።
"አንተስ?"
"ፅፌያለሁ....."
" ና ውጣና አንብብ! ደደቦች ሁላ!"
ከክፍሉም ሆነ ከዓመቱ አጠቃላይ የተማሪዎች የእውቀት ውድድር ከፍተኛ ውጤት በማምጣት ሁሌም ተሸላሚ የሆነው ተማሪ ከተቀመጠበት ተነስቶ የፃፈውን ግጥም ለማንበብ ወጣ።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“ርዕሱ የማይሞላ ክፍት የስራ ቦታ ይላል:: ” አለና ማንበብ ቀጠለ

«ይፈለጋል.....
ጠብ-መንጃ የሚያነግት
የሚወድ ጭንቅላት
ሲተኩስ የማይስት

መስፈርት.....
መፃፍና ማንበብ የማይችል
ለእውቀት የማይቸኩል
የሚታመን ላጎረሰው
ለሌላው ቅንጣት ደንታ የሌለው

ተፈላጊ ብቃት.....
ህይወት ህይወት ነው ብሎ ያመነ
ሰውና በረሮን በእኩል መስፈርት የተመነ
አገርን ሳይሆን አለቃውን ለመጠበቅ የሚተጋ
«ድንበር ባንዲራ ህዝብ» የሚሉትን የሚቀስፍ
የሚወጋ
ተቀንሶ የተሰጠውን መብት፤ ደግሞ ቀንሶ የሚሰጥ
ሞኝ የማይሉት፤ ወይ ብልጥ

የስራው ቦታ.....
ወጥቶ አደር
ሩዋንዳ፤ ቡሩንዲ፤ ሱማሌ ፤ ቤርሙዳ፤
ማርስም ቢሆን የሚቀጠር
የትም ወድቆ የሚቀበር
ለማን? ለምን? እንዴት? ብሎ ማይጨነቅ
ስለራሱም ስለማንም ምንም ነገር የማይጠይቅ
አንጎሉ ተመጦ ቢደፋ የማይገርመው
ለመግደል እውቀት እንደማያሻ የገባው
በደመ-ነፍሱ ተወልዶ ደመ-ነፍሱን ያደገ
በሰዋዊ ህሊናው ላይ አውሬያዊነትን የደነገገ

ይፈለጋል.....
ይሂድና ይቀጠር

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ጥበብና ፍቅር
ሰላምና ፍትህ፤ በሌለበት የኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ መንደር:: »

ተማሪው የፃፈውን ግጥም አንብቦ ጨረሰና የሚሰጡትን መምህራዊ አስተያየት ለመስማት ወደሳቸው ሲዞር ባልወለደ አንጀታቸውና ሰፈድ በሚያህለው ላባም እጃቸውን ማጅራቱ ላይ ለተሙለት:: ገና አቅሙ ያልፀናው የአስራ አንድ አመት ታዳጊ ወደፊቱ ተደፋና ከፊት ለፊቱ ከነበረ ዴክስ ጠርዝ ጋር በፊቱ ተላተመ:: ወድያው ነበር አንቱ ተቀጭቶ ህይወቱ ያለፈው::

አስተማሪው እንደ ሌሎቹ ከፍተኛ የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. ባለስልጣናት ከውጭ አገር ዩኒቨርስቲዎች በተልእኮ ትምህርት ስም በገንዘብ ተገስቶ የሚመጣ ዲግሪና ማስትሬት ባይዘጋጅላቸውም በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ አባልነታቸው ብቻ ከሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ እንደ ሌሎቹ በርካታና መለስተኛ የአገሪቱ ባለስልጣናት «ተምረዋል» ለማስባል ብቻ ተመርቀው ካለ ብቃት እንዲያስተምሩ የተፈቀደላቸው መምህር ወደ ትምህርት ቤቱ ግቢ እንዲገቡ የተደረጉበት ዋና ምክንያት ሌሎቹን መምህራንንም ሆነ አጠቃላይ የትምህርት ቤቱን እንቅስቃሴ እየሰለሉ ወደ ታዘዙበት አካል መረጃ እንዲሰጡ ነበር::

ሰውዬው በክፍሉ የተነሳውን የተማሪዎች የድንጋጤ ጩኸት እና ትርምስ በዱላ ዝም ለማሰኘት ድብደባቸውን ሲቀጥሉ ተማሪዎች ከክፍሉ እግሬ አውጭኝ እያሉ በመውጣት ሲጯጯሁ ወሬው ተዛመተና ጊቢው ታመሰ:: ሁኔታውን የሰማው የአካባቢ ምድብ ተወርዋሪ ፌደራል ፖሊስ ትምህርት ቤቱን ከቦ ህፃናቱን መደብደብ ሲጀምር የአከባቢው ነዋሪ ግልብጥ ብሎ ወጥቶ «ልጆቻችን አለቁ!» እያለ ከፖሊስ ጋር ይፋለም ጀመረ:: የህዝቡ ቁጣ ወድያው በመላው አዲስ አበባ ተስፋፋ:: በሌሎች በርካታ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችም ተመሳሳይ የፍርሀት እና የውጥረት መንፈስ እንደ ሰደድ መዳረስ ጀመረ:: ፖሊስም ካለ ምክንያት በየ መንገዱ አፈሳወና ድብደባው አጧፋ::

አብነት ሁኔታው እየተካረረ ሲመጣ ድንገት እጃቸው ላይ እንዳልወድቅ ብሎ ስለሰጋ በእልህ ሲቃ እየነፈረ ወደ ተደበቀበት ቤት መመለስ ጀመረ::

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ምዕራፍ 46

ሰናይት ቀን ላይ በተደጋጋሚ ጀነራል ምትኩን በቢሮውም ሆነ በሞባይል ስልኩ ላይ ልታገኘው ደጋግማ ሞክራ ስላልተሳካላት እንደ ቤተክርስቲያን ሳይሳለማት ወደ ቤቱ ከማይከተትበት መጠጥ ቤት ልታገኘ ው ሄደች:: እንዳሰበችውም ገና ሳይመሻሽ አንዲት ወጣት ሴተኛ አዳሪ ጭኑ ላይ አስቀምጦ እየተዳራ ውስኪውን ሲጠጣ አገኘችው:: ሲያያት ደንግጦ ልጅቷን ከላዩ አስነስቶ አባረራትና "ሰናይት....."

"ሰላም ዋልክ አቶ ምትኩ..... በስልክ ደጋግሜ ላገኝህ ሞክሬ ነበር::"

"አላወቅሽም እንዴ....."

"ምኑን?"

"ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. ነኝ ብሎ የተሾመው ባለስልጣን ጠቅላላ ለመንግስት ቀንደኛ ተቃዋሚ ለሆኑ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅት በስውር ሲሰሩ ስልካቸው እየተጠለፈ ስንቱ ተይዞ ወህኒ ወረደ..... " አላት

"ተው እንጂ....!?"

"ወላዲትን!.... እኔም ለዛ ብዬ ነው ማንኛውንም ግንኙነት በስልክ ከማድረግ የተቆጠብኩት"

"እንዴት ነው ግን አጠቃላይ አሁን መንግስት ያለበት ሁኔታ?"

"በጣም ፈርተዋል:: ህዝቡን እንዴት መልሰው ማረጋጋት እንዳለባቸ ግራ ተጋብተዋል:: ያው ፖለቲካ ሲባል ግማሽ ጎኑ ምናልባትም ከዛ በላይ ውሸት ማውራት ነውና ህዝቡን የውሸት ተስፋ ለማጠጣት ተዘጋጅተዋል:: "

"ምን በማለት? "

"በግብርና መር የአገሪቷን ኢኮኖሚ እናስመነጥቃለን የሚለው ማታለያ ከሽፏል:: አሁን ደግሞ ለአዲስ አበባ ህዝብ ኮንዶሚነም ቤት እየሰራን

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

በነፃ እናዳርሳለን ብለው የህዝብን አንጀት በመብላት ድጋፍን ለማግኘት አዲስ እቅድ ነድፈዋል "
" እውነት ያንን የሚያደርጉ ይመስልሀል? "
"ሞኝ ነሽ ልበል? በነፃ አይደለም ላዲስ አበባ ለትግራይ ህዝብ አይሰጡም! እነሱ በዚች አገር እና በህዝቡ ንግድ ነው የተያያዙት:: የቻለ ገዝቶ እየገባ ኪሳቸውን ያደልባል:: ያልቻለ ጎዳና ላይ ይጣላል:: በተለይ ለአዲስ አበባ ህዝብ ባላቸው ስር የሰደደ ጥላቻ ምክንያት ህዝቡ ቤት አልባ ሆኖ በችግር አፈር ሲግጥ ማየትን ይፈልጋሉ:: ያም ሆነ ይህ በሱ አንድ ሶስት አመት አጭበርብረው ከቆዩ በኋላ ውሸት መሆኑ ሲደረስበት አባይን ገድበን ኢትዮጵያን እናበለፅጋለን የሚል አጀንዳ አስቀምጠዋል... "
" እሱንስ ማከናወን የሚችሉ ይመስልሀል? "
" ከጀርባ ያስቀመጡት በግድቡ ምክንያት የሚዘርፉት ሀብት ስላለ ነው እንጂ በትክክል ለአገር ከመቆርቆር እንዳልሆነ በየስብሰባውና ግምገማው ከማየው በመነሳት እርግጠኛ ሆኜ መናር እችላለሁ..."

ቀጠለ "...ደግሞ በሱ አንድ ሶስት ዓመት አጭበርብረው ይቆዩና ከኡጋዴን ዘይት በማውጣት አገሪቷን የአፍሪካ ቱጃር እናደርጋታለን ብለው ሌላ ሶስት ዓመት፤ ደግሞ እሱ ሀሰት መሆኑ ሲደረስበት ጅቡቲን ለማስመለስ ከፈረንሳይ ጋር መደራደር ጀምረናል ይላሉ፤ ደግሞ እሱ ሲደረስበት ሌላ ምክንያት እየተፈላሰፉ በመዋሸት ስልጣንን መራዘም ነው እቅዳቸው" አላት::

ሰናይት ስትስቅ ቆይታ "ግን ህዝቡ ይህን ሁሉ ውሸት የሚቀበል ይመስልሀል? "

"የኢትዮጵያ ህዝብ ንፋስ ወደነፈሰበት ነው..... ተስፋ እና የተስፋ ዳቦ ይወዳል ምናልባት አንድ ቀን ካልተለወጠ በስተቀር:: ኢትዮጵያ ማለት በነፃነት ኖራ የማታውቅ ነፃ አገር ነች:: "
"ግን እዳሰቡት ባይሄድላቸውስ? "

በስላቅ ሲስቅ ቆየና "በነባር የወያኔ አባላት ዘንድ አንድ የተለመደች አባባል አላቸው ለመሞት ባለን ቁርጠኝነት ከመላው የኢትዮጵያ ህዝብም ሆነ ከሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ሁሉ እኛ እንበልጣለን ይላሉ::

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ስለዚህም ማንም ከኛ ስለማይሻል በግድም ይሁን በውድ ሁሉም ለኛ እንደተገዛ ይኖራል ብለው ያምናሉ።"

ሰናይት እየተገረመች "የአንድ ተራ አሸባሪ አቋምም ተመሳሳይ ነው። ለሞት ባለው ቁርጠኝነት ነው አጥፍቶ የሚጠፋው። ራሱን በገመድ የሚሰቅልም፤ መርዝ ጠጥቶ የሚሞተውም ሁሉ ለሞት ባለው ቁርጠኝነት ነው። ለሞት ቁርጠኛ መሆን ከመቼ ጀምሮ ነው ደግሞ የጥንካሬ መስፈርት እና መገለጫ የሆነው?"

"ተያቸው ባክሽ እነሱ የሚሉት ማለቂያ የለውም" አላትና "የኛም እቅድ አሁን ሊጀመር ነው። ሁሉንም ነገር በጥብቅ ሁኔታ አደራጅቼ ጨርሻለሁ። የጀመርነው ስብሰባ ነገ ይጠናቀቃል ተብሏል። ከነገ ወድያ ወደ ወለጋ ማምራታችን የማይቀር ነው በዛው ያሰብነው ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል" ብሎ አረጋገጠላት።

  

የማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ምዕራፍ 47

ከአሜሪካ የተነሳው የቡድን አንድ አባላት በጆንስ መሪነት በቀጣዩ ዕለት ማለዳ አዲስ አበባ አውሮፕላን ማረፊያ ደረሱ።።

ብዛታቸው አስራ አንድ ሲሆን ሰባት ወንዶችና አራት ሴቶችን አቅፏል።። አየር መንገድ ሂዶ የተቀበላቸው በአፍሪካ አንድነት ድርጅት ውስጥ የሚሰራውና አብነትን ደብቆ ያስቀመጠው የሚስጥር ሰዋቸው ነበር።።

ጥቁር ቀለም ባለው አዲስና ዘመናዊ መርሴዲስ እና የአየር መንገዱ መውጫ ላይ ከሚቆሙት ሀዩንዳይ ታክሲዎቹ መካከል ሶስቱን ተኮናትረው ሲ.ኤም.ሲ. አካባቢ ወዳለው መኖሪያ ቤት ተጉዘው ደረሱ።።

አብነት ሳሎን ተቀምጦ በክፍሉ ውስጥ ባለው ኮምፒውተር አማካኝነት በኢንተርኔት የሚሰራጩ ዓለም አቀፍ ዜናዎችንና መልዕክቶችን እየፈለገ ያነብ ነበር።።

የሳሎኑ በር ተከፍቶ እንግዶቹ መግባት ሲጀምሩ ኮምፒውተሩን አጠፋና ወደ መኝታ ክፍሉ ለመግባት ተነሳ።። እየተራመደ እይታውን በጥቁር አሜሪካውያኖቹ ላይ ሲሰድ

“አቢ!” የሚል ጥሪ ከነሱ መካከል ከአንዱ ሰው ሰማ።። የጠራው ሰው እጆቹን በስፋት ከፍቶ እቅፉ ውስጥ ሊያስገባው ወደሱ መራመድ ሲጀምር አብነት አላመነም።።

“እዮቤ!”

አንዱ በሌላኛው እቅፍ ውስጥ ገብቶ ተጨማመቁ።። በአዲስ አበባው ዩኒቨርስቲ የስነ-ጥበብና ዲዛይን ትምህርት ቤት አብሮት ስዕል

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

የተማረው እና ከጥቂት ዓመታት በፊት የዲቪ እድል ደርሶት ወደ አሜሪካ የሄደ ጓደኛው ነበር።።

በአሜሪካ ውስጥ በድብቅ በተቋቋመው የጥቁሮች ፓርቲ ውስጥ አባል እንዳደረጉት ፅፎ የነገረውና ኢትዮጵያን ከመጣባት አደጋ እንዲታደጓት ከፓርቲዎቹ መሪዎች ጋር ያገናኘው እርሱ ነበር።።

"ተስማምቶሀል..... ሙያህን ለወጥክ እንዴ?" አለው አብነት።።

"ያው መቼም እዛ ስትሔድ መልክህ ይቀላል።። ስጋህ ይሞላል።። የመስራት እድሉ ሰፊ ነው።። ከሰራህ ደግሞ ጥሩ ትኖራለህ እንጂ ስዕል መሳል አላቆምኩም።።" መለሰለት ኢዮብ።።

ቀጠለ ".....ይህ ሁሉ ግን ስጋዊ ፍላጐትን ከማሳካት አንፃር እንጂ ህሊናዊና ሞራላዊ ወደሆኑት ስሜቶችህ ስትመጣ ግን ከዕለት ዕለት ባዶ እየሆንክ የምትሔድበት አገር ነው።። ኢትዮጵያዊ ወዝና ባህልን ከተፈጥሮ ጋር ሊኖርህ የሚገባው የፀዳ ቁርኝትን..... ብዙ ነገርህን እዛ ታጣዋለህ።። በአጠቃላይ ህይወትህ የሚሞላው በቅራቅሞቦና አርቴፊሻል በሆኑ ነገሮች ብቻ ነው።።.....ዋው ፈጣሪ አፍሪካን ለአስከፊ ድህነት ባይመርጣት ኖሮ ከዛ አገር በእልፍ እጥፍ የሚልቅ ያልተበረዘና ውብ የሆነ የተፈጥሮና የባህል እሴት ያላት ምድር ናት..... በቃ እዛ ገንዘቡ አለ ተፈጥሮው ግን የለም።። እዚህ ደግሞ ተፈጥሮው አለ ገንዘቡ ግን የለም።።" አለ።።

"ህይወት በተቃርኖ የተሞላች ናት የሚባለው ለዚህ አይደል" ኢዮብ ወደ እንግዶቹ እያመለከተ "ና ተዋወቃቸው ወንድሞችን....."

አብነት ቃሉ ደስ አለው።። 'ምናለ ዓለም በጠቅላላ የወንድማማችና የእህትማማች ስሜቱ ቢኖረው' ሲል ተመኘ።።

ኢዮብ እነሱ ወደተቀመጡበት ሶፋ አቅፎት ተራመደና "ይህ ወንድማችን ነው በኢትዮጵያ ላይ የታቀደውን እቅድ እንድናውቀው የረዳን"

ጆንስ በአክብሮት ፈገግ አለና "ትልቅ ውለታ ሰርተሀል።። በመጀመሪያ ለራስ ቀጥሎ ለአገርህ ቀጥሎም ለአፍሪካና ለጥቁር ህዝብ በሞላ....." በስሜት ጨብጦ እጁን ወዘወዘው።።አብነት ለሁሉም ሰላምታ ሰጠና ጨረሰ።።

"ና አጠገቤ ተቀመጥ" አለው ጆንስ ።። ተቀመጠ።።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

“ስምህ ማነው?”
“አብነት”
“እኔ ጆንስ ቴይለር እባላለሁ፡፡ ሲጃራ ታጨሳለህ?” ከኪሱ ለግብኛ እያወጣለት ጠየቀው፡፡
አብነት አጫሽ ቢሆንም አዎ ማለት አልፈለገም፡፡ ስሜቱ ከአክብሮት ይምጣ ከይሉንታ አልተረዳውም፡፡
ጆንስ ከመያዣው አንዱን በማውጣት ለራሱ ለኮሰና “.....ወደ መጣንበት ጉዳይ እንመለስና የነዛን ሰዎች እኩይ እቅድ እንዴት ልትደርስበት እንደቻልከ ንገረኝ?” አለው፡፡
የሁሉንም እንግዶች ስሜት የሳበ ጥያቄ በመሆኑ በዝምታ ማዳመጥ ጀመሩ፡፡ ሀሳቡን በትክክል እንዲረዱት በእዮብ አስተርጓሚነት ማስረዳት ጀመረ::
አብነት ህሊናው ላይ ቀድሞ ድቅን ያለበት የመስፍን ገፅታ ነው፡፡ በሀዘን ፈዞ ቀረ፡፡ ሁሉንም የደረሰበት በመስፍን በኩል ነውና፡፡ ሁኔታውን ካወቀበት ዕለት አንስቶ እዚህ ቤት እስከመጣበት ዕለት ድረስ ያሳለፋቸውን ተግባራት በሙሉ ዘረዘረለት፡፡
“አብራህ ስትሰራ የነበረችው እህታችንስ?” ጠየቀው ጆንስ፡፡
“እቤቷ ነው ያለችው፡፡”
“እሷን እንዴት አልያዟትም?”
“እንደነገረችኝ የኔ ፎቶ ብቻ ነው ለጊዜው በእጃቸው የገባው፡፡ ከደረሱባት ግን እሷም ብትሆን የሞት እጣ ነው የሚደርሳት፡፡”
“ልንረዳት ይገባናል ችግር ውስጥ ከመግባቷ በፊት” አለ ጆንስ፡፡
“በምን መልኩ?”
“እ.....አስቤበት አሳውቅህለው፡፡.....ደግሞም ላያት እፈልጋለሁ ግን.....” አብነት አቋረጠውና “ቤቱን ታውቀዋለች ደውዬ ልጠራት እችላለሁ፡፡”
“እዚህ?”
“አዎ.....”
“አሳይተህት ነበር?”
“አይ.....በምልክት ነገርኳት፡፡ እነሱ ቤት የነበሩኝን የስዕል ስብስቦቼን እና የመስሪያ እቃዎቼን ማንም በሌለበት ሰዓት እንድታመጣልኝ ጠይቄያት ስታመጣልኝ በሱ ምክንያት ነው ቤቱን ያወቀችው፡፡”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“ጥሩ.....የምትመጣበትን ዕለት እነግርህና ትጠራታለህ፡፡”
“እሺ.....” አለ አብነት፡፡

ጆንስ አብረውት ወደመጡበት አባሎች ዞረና “መውሰድ ስላለብን እርምጃ እንወያይ” አላቸውና የሁሉንም ትኩረት ያዘ፡፡

በቀጣዩ ዕለት የጊቢው ሁለት ሰራተኞች ከደሞዛቸው ውጪ ጉርሻ ተሰጥቶዋቸው “ለሁለት ሳምንት ረፍት አድርጉ፡፡” በሚል ምክንያት እንዲሰናበቱ ተደረገና ምግብ ማብሰሉን ዕዳቱንና ጥበቃውን ጨምሮ የጊቢው እንቅስቃሴ በጆንስ ሰዎች ተያዘ፡፡

«««««««« »»»»»»»»

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ውስጥ የሚሰራው ሰዋቸው ለነጆንስ ከፊት ለፊቱ በስተቀር ጥቁር መስታወት የተገጠመለትና ብርማ ቀለም የተቀባ ስምንት ሰው መጫን የሚችል ቼቭሮሌት መኪና አምጥቶ ሰጣቸው፡፡

ታርጋው የግል የተለጠፈበት ነበር፡፡ ከጓደኛው ነው የተዋሰው ለዕለቱ ግዳጅ የተሰናዱት ሶስት ወንዶችና አንዲት ሴት በጆንስ ሾፋሪነት እና በአብነት አቅጣጫ ጠቋሚነት ወደ ሂርጳ ቤት መጓዝ ጀመሩ፡፡

ሶስቱ ወንዶች የአዲስ አበባ ማስተር ኘላን መስራቤት በኮንትራት ያስመጣቸው የውጭ አገር ዜጋ ሰራተኞች መሆናቸውን የሚገልፅ መታወቂያቸውን ደረታቸው ላይ አንጠልጥለዋል፡፡ ተጨማሪ የማወናበጃ ደብዳቤዎችንና ሰነዶችን አዘጋጅተዋል፡፡ እንዲሁም ለቦታ ልኬት የሚያስፈልጉ ዘመናዊ ሜትሮችን ኘላን መሳይ ወረቀቶችን ይዘዋል፡፡

መኪናው የሂርጳን ቤት ሊያሳይ የሚችልበት ርቀት ስፍራ ላይ እንዲቆም ተደረገና ክትትሉን አብነት ከዚህ ቀደም በተጠቀመበት ዓይነት ተመሳሳይ ዘዴ ጀመሩ፡፡

የ“አሮሞ ነፃነት ንቅናቄ” መስራችና መሪ ከሆኑት ውስጥ አንዱና ዋነኛው ሂርጳ ሁለት ጊዜ ከጊቢው እየወጣ ሲገባ አይተውታል፡፡ መያዝም ይችሉ እንደነበረም ተረድተውታል፡፡ ዋናዋ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ሰው ግን ሰናይት ናት፡፡ እሷ ወጥመዳቸው ውስጥ እስክትገባ ድረስ ሂርጳ ላይ ምንም ዓይነት እርምጃ ለመውሰድ አልፈለጉም፡፡ ምክንያቱም ሰናይትን የማጥመጃ ብቸኛ መንገዳቸው ሂርጳ ነው፡፡ ሂርጳ ከሌለ ደግሞ ሰናይትም እንደማትኖር ያውቁታል፡፡ ምናልባት ይህ እስኪሳካ ሳምንትም ወርም ክትትል ማድረጉ ምንም አማራጭ የሌለው መንገድ ነው ብለው አምነውበት ነበር፡፡

አብነት ከኪሱ የቴኘ ካሴት አወጣና ከተፈው፡፡

የቦብ ማርሊ "አፍሪካን ዩናትድ" የሚለው የሬጌ ዜማ መሰማት ጀመረ፡፡

ጆንስ ፈገግ አለና "ትወደዋለህ ይህን አቀንቃኝ?"

"ከማንም ድምፃዊ በላይ..... አጭር የነበረች እድሜውንና ችሎታውን በሙሉ ስለ አፍሪካ አንድነት፣ ስለ ነፃነትና ስለ ፍቅር ለዚህች ለኛ አህጉር በሙዚቃ እንደተዋጋ ነው ሀይወቱ ያለፈው፡፡"

"አዎ....." አለ ጆንስ፡፡ ቀጠለ በተመስጦ ".....የኛም ትግል ሀላፊነት ከነሱ የተረከብነው ትልቅ አደራ ነው....."

"እ.....ስለፓርቲያችሁ በጥቂቱ ልትነግረኝ ፈቃደኛ ነህ?"

"አዎ....."

"ስሙ ማን ይባላል?" ጠየቀ አብነት፡፡

"አፍሮኢዝም"

"ፍቺ ይኖረው ይሆን?"

"ግልፅ ነው፡፡ አፍሮ የሚለው ቃል አፍሪካን ወካይ ሲሆን ኒዝም የምትለዋ ቃል ደግሞ የአፍሪካን አንድነት እውን ለማድረግ የሚያስችል አዲስ የፍልስፍና አቅጣጫን የሚተነትን ፅንሰ ሀሳብ መኖሩን ለመጠቆም ነው፡፡"

"መቼና በማን ተፈለሰፈ?"

"እ.....1967 በአሜሪካ ነው፡፡ የፅንሰ ሀሳቡ ፈጣሪ ኢትዮጵያዊ ሲሆን ስሙ ሳሙኤል ታ.በ. ይባላል፡፡ በአካልም ሆነ በፎቶ አናውቀውም፡፡ ልናገኘው ሞክረን ነበር ምን እንደሆነ ሳይደረስበት ተሰውሮ መቅረቱን ብቻ ነው ልናውቅ የቻልነው፡፡ ንድፉን ፅፎ እንደጨረሰ በአሜሪካ አገር ትምህርቱን ለመከታተል ለመጣ አንድ ኢትዮጵያዊ ጓደኛው ላከለት.....

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

".....የዚህ ታላቅ የፅሁፍ ንድፍ እጄ ላይ ሊገባ የቻለው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ በዛን ወቅት ላይ እኔ ከዛ ኢትዮጵያዊ ጋር በአንድ ዩኒቨርስቲ የፖለቲካ ሳይንስ ተማሪዎች ነበርን፡፡ በዩኒቨርስቲው ውስጥ ያለነው ጥቁሮች በጣም ጥቂት ስለነበርንና በዘር መድልኦ ከፍተኛ ጫና ይደረግብን ስለነበረ በጣም እንቀራረብ እንተጋገዝ እንዋደድ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት ላይ ነው ፅሁፍ ለሱ የተላከለት፡፡ እሱም እንድናነበው ጥቁር ለነበርን ጥቂት ጓደኞቹ ሰጠን፡፡ መጨረሻ ላይ የፅሁፍ ጥራዝ በኔ እጅ ቀረ፡፡ እናም ደጋግሜ የማንበቡ የማገናዘቡ እድል ተፈጠረልኝ፡፡"
"ምንድን ነበር አጠቃላይ ጭብጡ?" ጠየቀ አብነት፡፡
"አፍሪካን አንድ መንግስት እናድርጋት ነው፡፡"
"በምን መልኩ?"
"መሪ ሀሳቡ....." ንግግሩን ቆም አደረገና ሲጃራ አውጥቶ እየለኮሰ በረዥሙ ምጐ ጢሱን አስወጣና "..... "ቅድመ አያቶቻችን አሁን ወዳሉበት የአሜሪካ ግዛት ለቅንጦት ኑሮና ለንግስና አልሄዱም፡፡ ለባርነት ተግዘው እንጂ፡፡" የሚል ሲሆን "አሁንም ወደ እናት ምድር አፍሪካ መመለስና በዛው መኖር አለብን" የሚል ሰላማዊ በሆነ መንገድ የሚፈፀም የትግል አስተሳሰብን ነው የሚያራምደው፡፡....."
".....ወደ አገራችን ከመመለሳችን በፊት ግን አፍሪካ እንደ አሜሪካ ባለ አንድ ሰፊ ግዛት ስር ተጠቃላ በአንድ መንግስትና ህግ የመኖር ህልውናዋ መረጋገጥ አለበት፡፡"

አብነት ሲሰማ ቆየና "ይህ ታዲያ በነ አፄ ኃይለ ስላሴ፣ በኬንያው ጆሞ ኬንያታ፣ በናይጄሪያው ኤስ ኤል አኪንቶላ፣ በጋናው ዶክተር ክዋሜ ንክሩህማ..... በተባሉትና በሌሎች የወቅቱ ቀናኢ ታጋዮች በ1960ዎቹ ከተቋቋመው ፓን አፍሪካኒዝም በምን ይለያል?"
"የልዩነታቸውን ጥያቄ እናዘግየውና የፓን አፍሪካኒዝም ትግል የተጀመረበትን ጊዜ በትክክል ታውቀዋለህ?" ጆንስ ጠየቀው፡፡
"ያው በ1960ዎቹ ነዋ....."

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“አይደለም.....” አለ ጆንስ በእርጋታ። ቀጠለ “እንተ በምትለው ወቅት ላይ ፓን አፍሪካኒዝም ህጋዊ መሰረትን ለመጣል የሚያስችል ዓለም አቀፍ ድልን የተቀዳጀበት ወቅት ነው።”
“ትግሉ ታዲያ መቼ ነው የተጀመረው?”
“በ19 ምዕተ-ዓመት አጋማሽ ላይ በአሜሪካንና በካሪቢያን ባሉ በተለያዩ አገሮች ውስጥ በሚኖሩ ጥቂት ሰዎች የተፈጠረ ሀሳብ ነው። ይህ ሀሳብ አፍሪካዊ የዘር ሀረግ ባላቸው ጥቁር የሆኑ ጥቂት የወቅቱ ምሁራን ዘንድ ተቀባይነትና ድጋፍ ስላገኘ ወደ ትግል እንቅስቃሴ ሊለወጥ ቻለ።.....
“.....በተለይ በሃያኛዎቹ ምዕተ-ዓመት መጀመሪያ ላይ አስተሳሰቡ በራሷ በአፍሪካ አህጉር የተለያዩ ግዛቶች በመሰራጨት መስፋፋቱን ቀጠለ። በዛ ትግል ወቅት በከፍተኛ ሁኔታ ለዓላማው ስኬት ከሰሩት መካከል የአሁኗ ማላዊ ዜጋ የነበረውና ዮሴፍ ቡዝ የተባለው ሚስዮናዊ በ1897 “የአፍሪካ ክርስቲያን አንድነት” በሰተኘውና ሀይማኖታዊ ስያሜን የያዘ ተቋም መስርቶ ስለ አፍሪካዊነት አስተሳሰብ አጥብቆ ቅስቀሳን በማድረጉ ሀሳቡ አህጉራዊ ቅርፅ እንዲይዝ አድርጓል....

“.....እንዲሁም የማህበራዊ ኑሮ ምሁር የነበረው ዱ.ቢ. “ክራይሲስ” የተሰኘ ፅሁፍ በማሳተምና በማሰራጨት ለትግሉ እገዛ አድርጓል። ከዛም ይህን ሀሳብ የደገፉ ምሁር ግለሰቦች 1900 ለንደን ላይ ተሰበሰቡ። ቀጥሎም 1919፣ 1921፣ 1923፣ 1927 በለንደን፣ በብራስልስ፣ በሊዝቦን፣ በኒው-ዮርክ ትልልቅ የነፃነት ጥያቄ ስብሰባዎችን አካሂደዋል። እንዲሁም ማርክስ ጋርቬይ የተባለው ጃማይካ ፕረዝደንት “የጥቁሮች ፓርላማ” የተባለ ድርጅት አቋቁሞ የአፍሪካ ተወላጆችን በማሰባሰብ “ወደ አፍሪካ እንመለስ” በሚል መሪ ሀሳብ ብዙ ታግሏል....
“.....ከነዛ ሁሉ ጥረቶች በኋላ ነው ፓን አፍሪካኒዝም የተመሰረተው። ምስረታውን በተመከለተ በተለይ ኢትዮጵያዊ አፄ ኃይለ ስላሴ ድፍረትና ጥበብ የተሞላበት ትግል ከነጮች ጋር አካሂደዋል። እሳቸው በፅናት ሀሳቡን ይዘውት ባይወጡ ኖሮ የአፍሪካ አንድነት

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

መስረታ መክኖ ይቀር ነበር። ማንምም ከቀኝ ግዛት መላቀቅ ባልቻለ ነበር። በወቅቱ ጥቁር እንደ ሰው የማይታይበት ዘመን ነበር.....

" የአውሮፓ መንግስታት ምክር ቤት ቆመው ከቆዳ ቀለም ልዩነት የፀዳ እኩልነት ምድር ላይ መስፈን እንዳለበት በድፍረት ያወጁ ታላቅ ንጉስ ነበሩ።" ብሎ እያሰበ ቆየና

".....እንዲሁም ከላይ የዘረዘርካቸው ትልልቅ ሰዎች በጠቅላላ በምስረታው ትግል ላይ የተሳተፉና የደከሙ ናቸው። በመጨረሻም የምስረታውን ውጤት በህይወታቸው እያሉ ሊያዩ የቻሉ እድለኞች ናቸው።በዚህ ትግል ላይ ግን ብዙዎቹ ቀደመው ተሰውተውለታል።" አለ ጆንስ።

አብነት በትኩረት ሲሰማ ቆይቶ "ፓን አፍሪካኒዝምን ከአፍሮኢዝም ምንድነው የሚለየው?"

"የአፈፃፀም ስልቱ ብቻ። ዓላማው ግን ያው አፍሪካን አንድ ማድረግና ማሳደግ ነው።"

"ስለ አፈፃፀሙ ልታብራራልኝ....."

አቋረጠውና "እችላለሁ።....." ጆንስ በግልፅ ስሜት ቀጠለ ".....የአፍሪካውያኖችን የዘር ሀረግ ከነጮቹና ቢጫ ህዝቦች ጋር በጋብቻም ይሁን ከጋብቻ ውጪ በሚፈጠሩ የፍቅር ጓደኝነቶች ቆይታ ወቅት ነገዶቹ እንዲካለሱ በማድረግ ነው"

አብነት የሰማውን ሲያሰላስል ቆየና "አስቸጋሪ ሀሳብ ይመስላል"

"ግን መተግበር ተችሏል።"

"እንዴት?"

"ይህን ፅንሰ ሀሳብ በመቀበል የአፍሮኢዝም ፓርቲ በአሜሪካ በ1975 በድብቅ እንዲቋቋም ካደረግን በኋላ በቀጥታ ወደ ትግበራው ነው የተገባው። በርካታ አፍሪካውያኖች ከነጭ ነገዶች ጋር ጋብቻ ፈፅመው ልጆች ወልደዋል። ከጋብቻ ውጪም እንደዛው። ሂደቱ ቀጠለ በአውሮፓ በኢስያና በሩቅ ምስራቅ አገሮች ሳይቀር ፍጥነቱ ከጠበቅነው በላይ ተባብሶ ዛሬ በዓለም ላይ አፍሪካዊ ዝርያ የተደባለቀባቸው በሚልዮን የሚቆጠሩ ታዳጊዮችንና ወጣቶችን ማግኘት ችለናል።"

"የልጆቹ የተካለሶ ውልደት ታዲያ ምን ያመጣው ጥቅም አለ?"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“ፅንሰ ሀሳቡ ትውልድን የመፍጠር ስራ ነው፡፡ ትውልድን ፈጥረህ ውጤቱን ማየት የአምስትና አስር ዓመት ስራ አይደለም፡፡ ረዥም ጊዜን ፅናትን ትዕግስትን ይሻል፡፡ “.....የኛ አዲስ ልጆችም ዛሬ ገና ናቸው፡፡ ውጤታቸው የሚታይበት ጊዜያቸው ገና ነው፡፡”
“እንዴት?”
“መጀመሪያ ከ1975 ጀምሮ እስካሁን ያለውን እድሜ አስበው.....” ጆንስ ፋታ ሰጠውና ቀጠለ “.....በዛው ዓመት የተወለዱት እንኳ እድሜያቸው ቢሰላ ገና በወጣትነት ውስጥ ያሉ ናቸው፡፡ ይህ እድሜ በአመዛኙ በትምህርት ዓለም ላይ የሚነጉድ እንጂ ሀሳብ አቅጣጫ ይዞ ህሊና መሆን ስላለበት ነገር ሰክኖ የማመዛዘን ደረጃ ላይ የማይገኝበት የለጋነት ወቅት ነው፡፡.....
“ሁለተኛው ምክንያት ይቀጥላል.....” አለና ሲጃራ አውጥቶ መለኮስ ጀመረ፡፡
አብነት በጣም አጫሽ መሆኑን እያሰበ ማዳመጡን ቀጠለ “.....ሁለተኛው ይህ እድሜ ሀብት የምታካብትበት አይደለም፡፡ ብዙ ጊዜ ፅንሰ ሀሳቦችን ለመተግበር ስትነሳ ደግሞ ከፍተኛ ሀይል፣ እውቀትና ሰው ከሌለህ ቢያንስ የገንዘብ ክምችት ሊኖርህ ይገባል፡፡ በተለይ አፍሪካን የተመለከተ ሲሆን.....”
“እሱ ላይ ልክ ነህ” አለ አብነት፡፡

“.....ሶስተኛውና ዋናው እድሜው ጠቃሚ ለሆኑ የስልጣን እርከኖች እንዲታጩ፤ የዓለምንና የፖለቲካን ሚስጥራት በብስለት እንዲያውቁ የሚያደርጋቸው አይደለም፡፡ አየህ እነዛ ታዳጊዎችና ወጣቶች ከጥቂት ዓመታት በኋላ በየተወለዱበት አገር ከፍተኛ እውቀት ስልጣንና ሀብት ሊጨብጡ ይችላሉ፡፡ ያን ጊዜ የአፍሪካን አንድ መሆን ጥያቄ በግልፅም ይሁን በድብቅ ማንሳትና ማራመድ ይችላሉ.....
“.....በዛን ወቅት እነሱም በአንድ የመጠቃለሏን እቅድ መንግስታቶቻቸውን በማሳመኑ በኩል፤ ለእቅዱ የሚያስፈልገውን ገንዘብ በመቸር በኩል፤ ያሉበትን አገር ልምዶችን በመስጠት በኩል.....ስፍር ቁጥር የሌለው እገዛን ለአፍሪካ አህጉር መስጠት ይችላሉ፡፡ በግልፅ እገዛ ማድረግ ባይቻላቸው እንኳ የስለላ ስራዎችን ጨምሮ የካበቱ ሀያላን አገሮች የተነሱበትንና የደረሱበትን እንዲሁም

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

በቀጣይነት አፍሪካን ለመጨፍለቅ ያሏቸውን የእቅዶች ሚስጥር በማውጣት በማኮላሸት አፍሪካ መከተል ያለባትን አቅጣጫ በመጠቆም፤ በፖለቲካው በኢኮኖሚውና በማህበራዊው ዘርፍ ከመዳህ ሊላቀቅ ያልቻለው አቅሟን አዳብረው በጡንቻ የፈረጠሙች በማድረግ ለእቅዱ መሳካት ይሰራሉ።።"
አብነት ሲያስብ ቆየና "እሁን ያሉት የአፍሪካ መሪዎች በዚህ ጉዳይ ላይ እየሰሩ ስለመሆናቸው ነጋ ጠባ ይደሰኩራሉ.....እንደውም የድረጅቱን ስያሜ ከ "አፍሪካ አንድነት" ወደ "አፍሪካ ህብረት" ለውጠውታል።።"

ጆንስ የብግነት ሳቅ ሳቀ።። ጥርሱን ነክሶ "እነዚህ የሆዳም፣ የመሀይምና የአሳማ ጥርቅሞች ናቸው አፍሪካን አንድ የሚያደርጉት!?..... ሩቅ ምን አስኬደህ የወቅቱ የኢትዮጵያ ገዢዎች ተመልከት።። በየጊዜው ስለ አፍሪካ አንድነት እየታገልን፣ እያለቀስን፣ እየሞትን ነው በማለት በዓለም መገናኛ ብዙሀኖችና በየ አዳራሹ የቋንቋ አደራደሩን አሳምሮ ሲቀጥፍ ይውላል።። በሌላ በኩል ግን ኤርትራን አስገነጠለ።። ነገ ትግራይንም የማስገንጠሉ እቅድ እንዳለው እናውቃለን።። ቀጥሎም ሶማሌን፣ አፋርን፣ ኦሮሞን..... እያለ ለመበታተን ከሃያ ዓመት በፊት የቀረፀው "ማኒፌስቶ" እንዳለው እናውቃለን።። እንደሱ ዓይነት እልፍ መሪዎች ናቸው ዛሬ ስልጣን ላይ ያሉት።።ውሻ ይመስል ከነጮች እግርና ቂጥ ስር የማይጠፉ።። አፍሪካን በየ አንድ አንድ ሜትሩ ሸንሽነው እየቸበቸቡ ያሉ አውሬዎች!....."
አብነት ጆንስ በኢትዮጵያ ውስጣዊ ሁኔታዎች ላይ ያለው በሳል እውቀት እየገረመው ገፅታውን ፈታና አሰር በማድረግ አይኖቹን አፉ ላይ ተክሎ ያዳምጣል።።

ቀጠለ ጆንስ ".....የአፍሪካን ድህ ህዝብ ለመዝረፍ ለመበዝበዝ ነው ሌተቀን እንቅልፍ አጥተው የሚጨነቁት እንጂ የህዝቦቻቸውን ህይወት ላለማጐሳቆልና ኑሮዋቸውን ለማሻሻል አይደለም።። በፍፁም አይደለም!..... ምሳ አብረው ከበሉት አጋራቸው ጋር እራት ላይ ጦር ሲማዘዙ ነው የምናያቸው..... ቦርጭና ጫንቃቸውን እያደለቡ ህዝቡን እርስ በእርስ በማጋጨትና በማፋጀት የስልጣን ዘመናቸውን ከማራዘም

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

በስተቀር ሌላ ምን ቅዱስ የሆነ ህልም ምን ቀና የሆነ ራዕይ አላቸው?..... ህዝብ ሲማር የነሱ መሀይምነት ይገለጣልና ህዝብን ማስተማር፣ ማሳወቅ፣ ማፋቀር አይሹም..... አፍሪካን ከዕለት ዕለት ወደ ባሰ አዘቅት ያጠለቋት የነጮች ጫማ ስር ተነጥፋ የትቢያቸውና የጉድፋቸው ማራገፊያ እንድትሆን ያደረጓት እነሱ ናቸው፡፡.....ለሰሩትም ሆነ ለሚሰሩት ሀጢያት ገሀነም ተወርውረው ፍፃሜ ለሌለው ዘመን ሲቃጠሉ መኖር አለባቸው፡፡....." ብሎ ጥቂት ቆየና

".....በብቸኝነት ምንም መፍጠር ያልቻሉ እውነተኛ የአፍሪካ ልጆችና ታጋዮች አልፎ አልፎ ከመካከላቸው ብቅ ሲሉ ይታያሉ፡፡ ለዚህም የደቡብ አፍሪካው ኔልሰን ማንዴላ ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ስማቸው ዛሬ በተዳፈነውና ነገ ይፋ በሚወጣው የአፍሪካ ታሪክ ውስጥ አብሮ ሲዘከር ይኖራል፡፡" አለ ጆንስ
አብነት የጆንስን ትንታኔ በዝምታ ሲያዳምጥ ቆይቶ "እነዛ ከነጮች ጋር እንዲካለሱ የተደረጉት ህፃናት የአፍሪካዊ ዝርያ ቅልቅል በመሆናቸው በበታችነት ስሜት ወደ ባሰ ጥፋት ሊያመሩ ቢችሉስ በማለት አስባችሁ ነበር?" ጠየቀው፡፡
ጆንስ ፈገግ አለና "አዎ..... ለብዙ ጊዜም ተነታርከንበታል፡፡ በእርግጥ እጅግ ጥቂቶቹ የምትለውን ዓይነት ችግር ሊፀናወታቸው ይችል ይሆናል፡፡ ግን ወቅታዊ ስሜት ነው፡፡....."

እይታው ከፊት ለፊት በሚታየው የሂርጳ ቤት ላይ ይትከል እንጂ በህሊናው ግን ርቆ ተጉዞ ነበር፡፡
ቀጠለ ከህሳብ እይታዎቹ እየባነነ ".....አፍሪካ ምን የሚያሳፍር አፈጣጠር አለባት? በስነ-ባህል..... በስነ-ተፈጥሮ....በታሪክ፣ በቀደምት ስልጣኔ፣ በተፈጥሮ ሀብት..... ምን ጐደሎነት አለባት? ያላትን መጠቀም እንዳትችል ካደረጓትና በዝብዘው ለበዝባዥ አሳልፈው ከሰጧት መሪዎቿ በስተቀር..... ነጮቹም ቢሆኑ ይህን ያውቁታል..... አፍሪካዊ ሆነው ባለመፈጠራቸው የሚቆጩ እልፍ ናቸው.....

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“.....እናም ደግሞ ብዛት ያለው ህዝብ በቀጣይነት እየተዋለደ በመሔድ የተወላጆቹ ቁጥር ከተበራከተም ያነሳኸው የበታችነትና የጥፋት ስሜት ፈፅሞ አይከሰትም፡፡ ይልቅ ሊያመራ የሚችለው በትክክል ሁሉንም የሰው ዝርያዎች ያዋህደ አለማቀፋዊነትና አንድነትን በዚህኛው ፅንሰ-ሀሳብ መነሻነት እየተፈጠረ እንደሚሄድና የዓለም ህዝብ በአንድ አስተዳደርና ህግ ስር በሰላም በፍቅር በደስታ በእኩልነት መኖር እንደሚችል ይሰማኛል፡፡”

“ከተሳካ ጥሩ ነው፡፡ መልካም ጐኖቹ ይበዛሉ፡፡” አለ አብነት
“በፍፁም አትጠራጠር፡፡ በርካታ ጥቁር ምሁራኖች እና የአፍሪካን አንድ መሆን በእውነተኛ ስሜታቸው የሚደግፉና አብረውን የሚታገሉ ነጭ ጓደኞቻችን ጭምር እቅዱን ተቀብለውታል፡፡ እነዚህ የዛሬዎቹ ህፃናቶችና ወጣቶች ነገ በየአደባባዩ የተሻለ ሰብዓዊነት፣ የተሻለ መተሳሰብ፣ የተሻለ መግባባትና አንድነትን በቀላሉ በዓለም ህዝቦች ህሊና ውስጥ ማስረፅ የሚያስችል እምቅ ሀይል ያላቸው ናቸው፡፡ ከነሱ መካከል የዘር ግንዳቸው ወደሆነችው አፍሪካ መጥተው መኖር የሚፈልጉም ሆነ፣ በተወደዱበት አገር የሚኖሩት ልጆቻችን በአንዱ አይናቸው የነጭ አገራቸውን በሌላኛው ደግሞ የጥቁር አገራቸው አፍሪካን ይጠብቃሉ፡፡ አንድ እጃቸው ላሉበት አገር ሲሰሩ በሌላኛው ለአፍሪካ የሚተጉ ትውልዶች ይሆናሉ፡፡

“.....ለአፍሪካ እነሱ ሲደርሱላት በምድሯ ላይ ድንበር የሚባል ነገር አይኖርም፡፡ ጥንትም ቢሆን አምላክ ድንበር እንዲኖር አላዘዘም፡፡ ከተፈጥሮ ህግጋት እየሸሸ ላለው የዘመኑ ሰው መሪና አስተማሪ ይሆኑታል፡፡ ከአፍሪካ ቀጥሎም አንድ የሆነች ዓለምን ይፈጥራሉ፡፡ ከዛም በኋላ የሰው ልጅ እንዳሻው እየተጓዘ መኖር ይችላል፡፡ አውሬ የሆኑ መንግስታቶች ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ የከለሏቸው ድንበሮች እንደ ባቢሎን ግንብ ፈራርሰው ይጠፋሉ፡፡ ምድር ሰላምና ፍቅር የሰፈነባት ትሆናለች ሰማያዊውን ነገትም ተስፋ ማድረግ እናቆማለን ምክንያቱም ከሱ የማይተናነሰው ገነታዊ ህይወትን በነዛ ልጆች ራሳችን መፍጠር እንችላለንና፡፡”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“አፍሮኢዝም” አለ አብነት በስሜት ቀጠለ “መቼ ይሆን ያ ጊዜ?” ጠየቀ፡፡
“በቅርቡ እንደርስበታለን፡፡ እኛ ባንደርስበትም ልጆቻችን ይደርሱበታል፡፡ እሱም ባይደርስበት ልጁ ይደርስበታል፡፡ መሰረቱ ዛሬ ተተክሎዋል፡፡ ሰንሰለቱ ብቻ ነው እስከ ፍፃሜው ሳይበጣጠስ መጓዝ ያለበት፡፡ ይህም የእያንዳንዱ አፍሪካዊ ሀላፊነት ነው፡፡ ለአፍሪካ አንድ መሆን እውቀቱን ክብሩን ሀብቱን ህይወቱን እየከፈለ ሌላው ቢያቅተው አንድነትን እየሰበከ፤ ህሊናዊ አደራውን እየተወጣ ነው ማለፍ ያለበት፡፡” አለ ጆንስ

“ፍልስፍናው.....ማለትም የአፍሮኢዝም ፅንሰ ሀሳብ ለምንድነው በዓለም ላይ በይፋ ያልተለቀቀው?” ጠየቀ አብነት፡፡
“ዓለም እስካሁን ድረስ ከዘረኝነት አስተሳሰብ አልፀዳችም፡፡ እናም ዘረኝነታቸውንና የበላይነታቸውን አስጠብቀው መኖር የሚሹ አውሮፓውያን ኢስያውያን አሜሪካውያን የአፍሪካን አንድ መሆን ፈፅሞ አይፈልጉም፡፡ እንቅስቃሴያችንን ካሳወቅናቸው ደግሞ ፍርክስክሳችንን አውጥተው ያጠፉናል፡፡.....

“.....አንድ ምሳሌ ልሰጥህ እችላለሁ” ብሎ ሲጀራ ለኮሰና ደጋግሞ በመማግ “.....ያኔ የፓን አፍሪካኒዝም ትግል ሲጀመር የአላማው ፍፃሜ አፍሪካን በአንድነት አዋህዶ በአንድ ጥላ ስር እንድትኖር ማስቻል ነበር፡፡ እናም ይህን እቅድ ፍፃሜው ድረስ ሳያመራ እንዲኮላሽ ያደረጉት ነጮች ናቸው፡፡ እነሱን በየስብሰባውና የውስጥ ጉዳዮች እንዲሳተፉ በመደረጉ በረቀቀ ጥበባቸው ወደ ትልቅ ደረጃ ያደረሱትን ታላላቅ መንግስታቶች እርስ በእርስ አናከሷቸው፡፡ ይባስ ብለው የውስጥ እሳት ጫሩባቸው፡፡ ታላቁ ራዕይም መክኖ ቀረ፡፡ ዛሬ ድረስ የአፍሪካን ህዝቦች እርስ በእርስ እያስጨረሱ ያሉት ጦርነቶች የዛ ቅሪቶች ናቸው፡፡.....

“.....በወቅቱ እንቅስቃሴው ነጮችን ጣልቃ ሳያስገባ የተካሔደ ቢሆን ኖሮ ግቡን ይመታ ነበር፡፡ ያም ሆነ ይህ ዛሬ የአፍሮኢዝም ልጆች

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

በዓለም ላይ በእውቀት፣ በህይወት ልምዶች፣ በሀብት፣ በስልጣን እየካበቱ ሄደዋል።።በቅርቡ አፍሪካ አንድ ትሆናለች።።" አለ በብሩህ ተስፋ ተውጠ።።

"ልጆቹ ለምን ዓላማ እንደተካለሱ ያውቁታል?"
"ሁሉም ጊዜያቸው ሲደርስ እንዲያውቁት ይደረጋል።። እስከዛ ግን ከህፃንነት ህሊናቸው አንስቶ በአፍሪካዊ አባታቸው ወይም እናታቸው ተገቢው እነፃ እየተደረገላቸው ነው በማደግ ላይ ያሉት።።"
በዕለቱ ሰናይት ወደ ሂርጳ ቤት ባለመምጣቷ ክትትሉ ያለ ውጤት አብቅቶ ወደ ቀጣዩ ቀን ተዘዋወረ።።

  

የማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

ምዕራፍ 48

ተክለአይ በንዴት እንደጦፈ ግዳይ 200ን በዋናነት የሚመራው የህዝብ ደህንነት ሀላፊ ላይ አፍጥጦ “የት አለ ተያዘ ብለህ የነበረው ሳምሶናዊት ቦርሳ? ” አለ። ቀጥሎም ሌሎቹን እያየ።

“ ሰዎቹ መልሰው ወሰዱት”

“ሰራዊት አስከትለህ እንደፈለክ በምታዝበት ከተማ ላይ መልሰው ወሰዱት ስትል አታፍርም! ”

“ዋ! በቃ ከአቅማችን በላይ ሆነ ሰራዊቱ የቻለውን ሰርቷል። የቻልነውን ያህል ህዝብ ከየተገኘበት አፍሰን ምርመራ አድርገናል። ገርፈናል ሌላም ሌላም..... አድርገናል። ሰርተናል! መወቀስ የለብንም! ”

“የተገኙ ፍንጮችስ? ”

“አሉ ግን ገና እየሰራን ነው..... አሁን መልሰን ከተማዋን ለማረጋጋት እየታገልን ነው..... በተለይ ዩኒቨርስቲዎችን”

ተክለአይ መፍትሄ ይሰጡት ይመስል ሀጎስ እና ወዲ ሀለፎምን በየተራ እየተመለከተ ቆየና “ዝምብለን እኮ ነው ዩኒቨርስቲ፤ ኮሌጅ፤ ቅብጥርሴ ፤ ምናምን እያልን የምንደክመው! መንግስት ዝም ብሎ ገንዘቡን ለነሱ ይከሰክሳል። ህዝቡን በቀበሌና ወረዳ እያደራጁ እዛ እንዲማር ከተደረገ ይበቃው ነበር። ዋ!..... የኢትዮጵያ ህዝብ ማለት እኮ ሽንፍላ ነው ስንት ዓመት ሙሉ ተነገረው አይሰማም! ታሪክ፤ አንድነት፤ ቅርስ፤ ባህል..... ከሚለው አስተሳሰቡ አጥቦ ማንፃት አልተቻለም ” አለ በንዴት። የሁሉም ተሰብሳቢዎች አስተሳሰብ ተመሳሳይ ስለነበር ማንም አልተቃወመውም።

  

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ምዕራፍ 49

በሶስተኛው ቀን ክትትል ነበር ተፈላጊዋን እና ዋናዋን ሰው ያዩዋት "ጆንስ ጆንስ....." ከኋላ ወንበር ላይ የተቀመጠው ሰው ተጣራና "ማነው ወደ ጊቢው የሚገባው?" ጠየቀ ወደ ሂርጳ ቤት እያመለከተ "ራሷ ሰናይት ናት!" አብነት ፈጥኖ መለሰ።።
ጆንስ ሰዓቱን አየ።። ከገመተው በላይ መሄዱን አወቀ።።
"ሂዱ..... መኪናውን በሩ ጋር አስጠግተን እንቆምላችኋለን" አላቸው ጆንስ።።
ሶስቱ ወንዶችና አንዲ ሴት የያዟቸውን የቅየሳ ቁሳቁሶች እያንጠለጠሉ ከመኪናው ወረዱ።።
ሂርጳ ቤት ጋር እንደደረሱ ኢዮብ ቀድሞ በሩን አንኳኳና ሲከፈት "የአቶ ሂርጳ ገመዳ ቤት ነው?"

"አዎ....." ሚስቱ በጥርጣሬ እያየች መለሰች።።
ደረታቸው ላይ ያንጠለጠሉትን መታወቂያ እያሳያት "ከማስተር ኘላን መስራቤት የመጣን መሀንዲሶች ነን።። እነሱ የውጭ አገር ዜጋዎች ናቸው።። የቦታ ካርታችሁን ወይም ደብተራችሁን ማየት ፈልገን ነበር።።" አላት።።
ሁሉንም በየተራ ካስተዋለች በኋላ የመረጋጋት ስሜት እየታየባት "ራሱን ታነጋግሩታላችሁ ገባ በሉ....." ብላ የጊቢውን በር ዘጋችው።።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

አራቱም ገብተው የቤቱ በረንዳ ጋር መጠበቅ ጀመሩ። እንዳሰቡት ጊቢው የሚጠበቅ አልነበረም። አራቱም በፍጥነት አውጥቶ ለመጠቀም በሚያስችላቸው ቦታ የታጠቁትን ድምፅ ማፈኛ የተገጠመለት ሽጉጥ እንዳይታይባቸው በተሻለ የመረጋጋት ስሜት ነካኩት።

ሂርጳ ወጣ። ሲያዩት እሱም ምንም ዓይነት ጥንቃቄን ያላደረገ ነበር። ለሚስቱ የጠየቋትን ድጋሜ ለሱ አቀረቡለት።
"ካርታ የለውም ደብተር ነው ያለው።" አለ
ሁለቱ አሜሪካውያኖች የአካባቢውን ካርታ ያነሱበት የሚመስልና ውስብስብ መስመሮች የሞሉበትን ሰፊ የፕላን ወረቀት ገልፀው በእንግሊዝኛ መነጋገር ጀመሩ። ለማወናበጃነት እንዲያገለግላቸው የያዙት ኘላን መሳይ ነገር ነበር።
"ልታሳየን ትችላለህ?" አለው ኢዮብ።

ሂርጳ ካለ ጥርጣሬ "እሺ" ብሎ ወደ ቤቱ ተመለሰ።
ኢዮብ በእግሩ ጫፍ እየነጠረ ቀድሞ ወደ በሩ ተጠጋና በአይኖቹ ተከተሉኝ ትዕዛዝ ሰጣቸው። ሁሉም ሽጉጣቸውን አወጡና በወታደራዊ ስልት ቤቱ ውስጥ ገቡ። ቀድማ ሴቷ ወደ ሳሎኑ ስትወረወር ሁሉም ተከተሏት። እዚህ ውስጥም እንዳሰቡት ብዛት ያለው ሰው አልነበረም።

ሰናይት ብቻዋን ተቀምጣለች። ሂርጳ ከጓዳ አልተመለሰም። ሰናይት በቅፅበት ገብተው ሽጉጥ የደገኑባትን ሰዎች ስታይ ምን ማድረግ እንዳለባት ተምታቶባት ቆመች። ጭንቅላቷ ውስጥ ያ የምትጠላው ሰናፍጭ የፈሰሰባት ይመስል እየሰነፈጠና እየለበለበ አንቀጠቀጣት። ደመ-ነፍሷን ሽጉጧን ለመምዘዝ እጇን ወደ ወገቧ አቅራቢያ ስትሰድ ሴቷ ባልጠበቀችው ፍጥነት ተሽከርክራ በሰለጠነችበት የቴኳንዶ ጥበብ በጫማዋ ተረከዝ ጉሮሮዋን ለመምታት ሰደደች። ሰናይትም ከዮጋ ጋር አያይዛ በሰለጠነችው መሰረት ተንሸራታ አመለጠችና ወደኋላ በማፈግፈግ ሽጉጧን ለማውጣት ሞከረች። ከኋላ በኩል ግን ያላየችው ምት አረፈባት። ወለሉ ላይ ተዘረረችና ጥቂት

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

አጓርታ ህሊናዋን ሳተች፡፡ የመታት ሰውዬ ፈጥኖ ተጠጋትና ታጥቃው የነበረውን ሽጉጥ አውጥቶ ወሰደባት፡፡

ሂርጳ ከውስጠኛው ክፍል ብቅ ያለው የቤት ባለቤትነት ደብተሩን እያነበበ ነበር፡፡ ወደሳሎኑ ገብቶ የሰናይትን ወለሉ ላይ መውደቅ ገና ከማየቱ በሽጉጥ ሰደፍ አቅል የሚያስት ምት ማጅራቱ ላይ አረፈበትና እሱም ወለሉ ላይ ተዘረጋ፡፡

ሁለቱንም እጆቻቸውን ወደ ኋላ በመመለስ በካቴና አሰሯቸው፡፡ ከሂርጳ ቀበቶ ስር ረዥም ኮልት ሽጉጥ አገኙበት፡፡ ከዛም ሴቷና ኢዮብ ቀድመው በመውጣት ማንም በጊቢው ውስጥ ያለመኖሩን አጣሩ፡፡ ኢዮብ የቤቱን ግድግዳ እየታከከ ወደ ጓሮው ሲያይ ቅድም በሩን የከፈተችላቸው ሴት ሰራተኛ መሳይ ከሆነች ሌላ ሴት ጋር ጤፍ ትነፋለች፡፡ በአካባቢያቸው ህፃናት ይጫወታሉ፡፡

በፍጥነት ተመለሰና ሰዎቹ እንዲወጡ አዘዛቸው፡፡ሁለቱ አሜሪካውያኖች ሰናይትንና ሂርጳን በማጅራታቸው ላይ ተሸክመው ወጡ፡፡

የጊቢውን በር ከፍቶ ውጪውን ቃኘ፡፡ መኪናው በሩ ስር ደርሶ ቆሟል፡፡ ምንም የሚያሰጋ ነገር አልነበረም፡፡ ሰዎቹን በጐን በር ጫኗቸውና ገብተው ጉዞ ጀመሩ፡፡

«««««««««« »»»»»»»»»

ለ “ህዝበ ደቡብ ነፃነት ሀይል” ተጠሪ እንዲሆን በሰናይት የተጠየቀውና በፌደራል ፖሊስ ስር የተወርዋሪ ክፍሉ ዋና አዛዥ የሆነው ሻለቃ ደርበው ስራ አምሽቶ ነበር ወደ ቤቱ ያመራው፡፡

በወቅቱ ሁኔታ እንዳልጋለጥ ብሎ ስለሰጋ የሚጥል የሚያነሳው ጉዳይ ሁሉ ግራ ገብቶት ሰንብቷል፡፡ ያለው ብቸኛ ማደናገሪያ በስራው ላይ በርትቶ መታየት ስለነበረ ሰሞኑን በርካታ ግዳጆች ላይ በመሳተፍና ጥንካሬውን በማሳየቱ ከአለቃዎቹ የቃላት ምስጋናን አትርፏል፡፡ እሱ ብቻ ነበር ትንሽ እንዲረጋጋ ያስቻለው፡፡

በተለይ ሳምሶናዊት ሻንጣው ከመንግስት እጅ መሰረቁ በእጅጉ አስደስቶታል፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

በሌላ በኩል መንግስት ሻንጣውን ወሰደ ብሎ በማመን እንዲበተን ያስደረገውን ባለ ጐፈሬ ወጣት ፎቶ ይዞ ነው የሚንቀሳቀሰው፡፡ይህ ወጣት በከተማዋ ውስጥ በተበተኑት በአስር ሺዎች በሚቆጠሩ የደህንነትና የፖሊስ አባሎችም ያለመያዙ ሌላ ተዓምር ሆኖበታል፡፡

ሻለቃው ከሌሎች አባሎች ጋር ስለ ወጣቱ ሲወያይ “ጃማይካዊው የተሳሳተ መረጃ ሳይሆን አይቀርም የሰጠው” ያለው የአንደኛው አባል ንግግር ታወሰው፡፡

ሻለቃው ሁሉም ነገር ዝም ያለ መሰለው፡፡ዝምታው ግን የጤነኝነት ይሁን ውስጣዊ ሴረኝነት ሊታወቀው አልቻለም፡፡

በነዚህ ሀሳቦች እየተብሰለሰለ ጥቂት ቆየና ተጐንጭቷት የመጣው ዊስኪ ስሜት ሳትቀዘቅዝበት ወደ መኝታው አመራ፡፡

በቀጣዩ ዕለት ማለዳ ላይ ወደ ስራ ለመግባት ተነስቶ ልብሱን ማጠላለቅ ጀመረ፡፡ ሰዓቱ ገና ከንጋቱ አስራ ሁለት ይል ነበር፡፡ የዕለቱ ተረኞችን ለመደልደል እንዲችል ቀድሞ በመግባት ዝርዝሮችን ማገላበጥ እንዳለበት አስቦ ነው የተነሳው፡፡

ፊቱን ታጥቦ ፀጉሩን እንደነገሩ አበጣጠረና ኮልት ሽጉጡን ጐኑ ላይ ሻጥ አድርጐ ከቤት ወጣ፡፡ ላንድ ክሩዘር መኪናው ጊቢ ውስጥ ቆሟል፡፡ የቤቱን በር ቆለፈና በረንዳውን መውረድ ሲጀምር ከየት እንደመጣ ፍፁም ያላስተዋለው ሰው በቀኝ በኩል ጭንቅላቱ ላይ ሽጉጥ ደገነበትና “ቁም!” ትዕዛዙ በእንግሊዝኛ ነበር፡፡

በደመ ነፍስ የሚያየውን ከድርጊቶች በመነሳት ገምቶ አልተነቃነቀም፡፡

ከፊት ለፊቱ ማራኪ ሴት ወደ እሱ ስትራመድ አያት እሷም ሽጉጥ ይዛለች፡፡ ጥብቅ ያለ ሱሪና ጥቁር አጭር ቆዳ ጃኬት አድርጋለች፡፡ ጫማዋ የተጓጉች ይመስላል፡፡ በፈገግታ ቀረበችው፡፡ ለመናገር አፉን ሲከፍት ተሽከርክራ በጫማዋ ጫፍ ጐሮሮው ላይ መታችው፡፡ ወድቆ አጓራና ህሊናውን ሳተ፡፡

ውጪ ቆሞ የነበረው ቼቭሮሌት መኪና ወደ ጊቢው እንዲገባ ተደረገና ሻለቃውን ሽጉጡን አስፈትተውና ወደ ኋላ አስረውት የመኪናው ወለል ላይ ወረወሩት፡፡ ሴቷ ከሾፌሩ አጠገብ ገባች፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ሰናይት የኋላ በር አካባቢ ከያቆብ ጋር ተቀምጣለች፡፡ ሁለቱም እጆቿ በካቴና ከወንበር ጋር ታስረዋል፡፡ ስራ ላይ የነበሩት ሁለቱ ወንዶች ሻለቃውን በጫኑበት በር ገቡና እንዳይረግጡት እየተጠነቀቁ ተቀመጡ፡፡መኪናው ጉዞ ቀጠለ፡፡

«««««««« »»»»»»»»

የሰናይት መያዝ እንደገመቱት በሌሎች ታዳኞች ላይ የሚደረገውን ፍለጋ አቀለለው፡፡ሶማሊያዊና ኢትዮጵያዊ ድብልቅ የሆነው አቡበከር መሀመድ ጫቱን ሲቅም ውሎ ለአዳሩ ተጨማሪ ጫት ለመግዛት ከቤቱ ሲወጣ ተከተሉት፡፡

ከሩዋንዳ ወደ ቦሌ መንገድ የሚያወጣውን አስፓልት ይዞ ዋናው መንገድ ጋር ለመድረስ ጥቂት ሲቀረው ሁለት ማንነታቸውን የማያውቃቸው ሰዎች በመሳሪያ አስገድደው ቼቭሮሌቱ ላይ ጫኑት፡፡ራሱን ያገኘው በአንድ እስር ቤት መሳይ ክፍል ውስጥ ተቆልፎበት ነበር፡፡

በአማራውና በትግራይ ክልል ላይ እየተንቀሳቀሱ ያሉትን ሰዎች ለመያዝ በቀጣዩ ዕለት ቀጠሮ ተያዘ፡፡

«««««««««« »»»»»»»»»»

በአማራው ክልል ላይ የመንግስት ወታደሮችን አስከድቶ እቅዱን ለማስፈፀም ስራውን የተቀበለው ጄነራል ምትኩ ግን በቀላሉ ሊገኝ አልተቻለም፡፡

ሰናይት ጋር የነበረው አድራሻውም የስልክ ቁጥሩና የሚጠጣበት መጠጥ ቤት ብቻ ነበር፡፡

የሚሆነውን ከመጠበቅ ውጪ በምትኩ ላይ ለጊዜው ምንም ዓይነት እርምጃ መውሰድ እንደማይችሉ አሰበና ወደ ቀጣዩ ሰው አመሩ::

በዚሁ ዕለት ማታ ሶስት ሰዓት ላይ ቼቭሮሌቱ መኪና ከጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ወደ ተክለሀይማኖት ቤተ-ክርስቲያን የሚያደርሰውን አስፓልት ቁልቁል መውረድ ጀመረ፡፡ በትግራይ ክልል ላይ የሚሰራው በርሔ አብርሃ አዘውትሮ ከሚያመሽበት መጠጥ ቤት

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ሲወጣ በማያውቃቸው ሰዎች መታፈኑን እንጂ ወዴትና ለምን እንደሚወስዱት አያውቅም ነበር።።

ህሊናው ያመነው ግን 'በመንግስት የደህንነት ሰዎች ተያዝኩ' የሚለውን ነበር።።

የታጠቀውን ሽጉጥ በአርቴፊሻል እግሩ ላይ ካጠለቀው ቀበቶ ውስጥ አውጥቶ ለመጠቀም እንቅስቃሴ ሲጀምር በሽጉጥ ሰደፍ ተመቶ ወለሉ ላይ ተዘረረና ህሊናውን ሳተ።።

በሁለት ቀናት ውስጥ በቴኳንዶና በአፈና በቂ ስልጠና በወሰዱ የ "አፍሮኢዝም" አባሎች በአማራ ክልል ላይ ከሚሰራው ጄነራል በስተቀር ቀሪዎቹን በጠቅላላ በቁጥጥር ስር አዋሉዋቸው።።

ጆንስ የተያዙትን ሰዎች ለየብቻ በተዘጋጀ ክፍል ቆለፈባቸው።። ስናይትንም ለማረፊያነት ወደ ተዘጋጀው ጠባብ ክፍል ወስዷት በሩን ቆልፎባት ሄደ።።

ከዛም ብስለት በታከለበት አኳሀን ስለ ቀጣዩ ስራው በእርጋታ ማሰብ ጀመረ።።

  

ያማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

ምዕራፍ 50

መንበረ ደጋግሞ አስነጠሳት፡፡ ዛሬ ቁም ስቅል የሚያስበላ ጉንፋን እንደሚይዛት አምናለች፡፡ አብሯት ያደረው ሰው ማታ ሲግፈው አምሽቶ የመጣውን ካቲካላና ጠጅ ደረቷና አልጋዋ ላይ ሲያስመልሰው ነው ያደረው፡፡

የሽርሙጥና ህይወት አንገፍግፏታል፡፡የአስር ዓመታት ያህል ርዝማኔ የነበረው መስሎ የተሰማት ለሊቱ በመከራና በጭንቅ ነጋ፡፡ ስትገላበጥ ጭልጥ ባለ እንቅልፍ ተይዞ ያንኮራፋ የነበረውን ሰውዬ አባነነችው፡፡ ተንጠራርቶ አካሉን አፍታታና እጆቹን ወደ ብልቷ ሲሰድ ታወቃት፡፡

“እንዳትነካኝ!”

ልትከላከለው ስትሞክር ወገቧን ይዞ ወደራሱ ጐተታት፡፡

“ልቀቀኝ!” እልህና እምባ እየተናነቋት ጮኸችበት፡፡

“ምን....አ...ጠፋሁ?” የአፉ ግማት ሰነፈጋት፡፡ ይባስ ብሎ ከንፈሯን ለመሳም እየተጠጋት አሞጠሞጠ፡፡

“ለሊቱን ስትጫወትብኝ አደርክ፡፡ በቃህ ልቀቀኝ!”

“አለቅሽም፡፡.....ገ...ንዘ..ቤን ከፍ...ዬሽ... እኮ...ነው....፡፡” ቃላት ይሰባብራል፡፡

ድምፁ ጐርናና ነው፡፡ እጁን አውጥቶ ፀጉሯ ላይ አሳረፈና አጥብቆ ጐተታት፡፡ በድመት ተይዛ እንደምትንገላታ ድምቢጥ ያህል ተሰማት፡፡

“አ.....ል....ቀ...” ማለት የፈለገችውን ሳትጨርስ አፏ ውስጥ እንደ ኩበት የደረቁት ወፋፍራም ከንፈሮቹን ሰገሰገባት፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

እምባዋ በጆሮ ግንዶቿ በኩል ያለማቋረጥ ቁልቁል መፍሰስ ጀመረ፡፡ ሰውዬው ስሜት አልሰጠውም፡፡ ተገልብጦ ላይዋ ወጣና ጭኖቿን ፈልቅቆ ገባ፡፡ ተስፋ ስለቆረጠች ብዙም አልታገለችውም፡፡ በሚያሰቃያት ሁኔታ ወሲብ መስራት ጀመረ፡፡.....

ጉልበቱ የጅብ ነበር፡፡ እንደ አውሬ ጨፈረባት፡፡ ልትቋቋመው ስላልቻለች ስቃዩን በእምባዎቿ በማካካስ እንዳሻው ብላ ተወችለት፡፡ ከረዥም ደቂቃ በኋላ የልቡን አድርሶ ጨረሰና ከላይዋ እየተነሳ “እንደ...ጨዋ....ሴት... መለ....መ....ን ትፈልጊያ....ለሽ....እንዴ ....ሽ.....ሽርሙጣ....ነሽ እ...ኮ....ì” አላት በስላቅ፡፡

ሃምሳ ቦታ ብትፈነክተው ሁሉ የምትበቀለው አልመስልሽ አላት፡፡ አፍጥጣ እያየችው ብቻ ታነባለች፡፡

ተነስቶ ልብሱን ማጠላለቅ ጀመረ፡፡ እድሜው ሰላሳ ሰባት ነው፡፡ ፊቱ ሰፊ ሆኖ ብልዝና ጠባሳ የበዛበት፡፡ ጥርሶቹም ጠቋቁረው መሸራረፍ ጀምረዋል፡፡ አካሉ ግን ግዙፍ ረዥምና ያልተጐሳቆለ ዓይነት ነው፡፡ የነተበ ቡኒ ኮቱን አጥልቆ ሲጨርስ በተኛችበት ቁልቁል እያያት “ዓመል..... ቢኖ...ርሽ... ኖ...ሮ..... ቋሚ ደንበኛሽ...እሆን....ልሽ ...ነ...በር..፡፡ ግን ካሉሽ.....ነገሮ...ችሽ ...በጠ....ቅላላ.... እኔ ጋር የቀ....ረው..... ም...ን...ሽ እ....ንደሆነ ታውቂ...ያለሽ.....? አስቀያሚ ትዝታዎችሽ ብቻ፡፡” አላት እያፌጠጠባት፡፡

ቀጠለ “....በዚህ....ዓ...ለም...አይደለም ዳግም....በሌላ....ዓለም መፈጠ....ር....ቢኖ...ር እንኳ ....አንቺን.....ለሰ...ከንድ ሽራ.....ፌ ላገኝሽ....ሳይሆን....ላስብሽ አል....ፈቅድም...፡፡ገባሽ!?”

ቀና አለችና በሲቃ “በተራ ቃላት ብታዋርደኝ ወራዳነትህን ነው ያሳየሽኝ እንጂ አልነካሽኝም!”

በጥፊ አጮላት፡፡ ልትታገለው ሞከረች፡፡ ደግሞ ጠንካራ ጥፊ አሳረፈባት፡፡ ኩርምት ብላ አቀረቀረች፡፡ ከዛም በእግሩ ላብ እና አቧራ እንደ ቁርበት የቆረፈዱና ቀዳዳ የሆኑ ክፉ ጠረን ያላቸው ካልሲዎቹን አድርጎ ጫማውን በማጥለቅ “ሽርሙጣ!” ብሎ ተፋባትና በሩን ሀይለ በተሞላበት ሁኔታ ከፍቶ ወጣ፡፡

“ምን ዕለት ይሆን የተፀነስኩት?” አለች በምሬት፡፡ ቀጠለች በውስጧ ‘አቤት....አምላክን ሀያል ያሰኘው ፈጣሪነቱ ብቻ አይደለም፡፡ የሰው

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ልጅ ሲሰቃይ ለማየት የሚጨክን ጥሩ ጥንካሬ ያለው መሆኑ ጭምር እንጂ.....' አለች፡፡ወንድ የተባለውን ፍጡር እንዴት መበቀል እንደሚገባት ማሰብ ጀመረች፡፡

ወድያው ግን የሰናይት ሁኔታ ድቅን አለባት፡፡

ቤቷ መምጣት ካቆመች ዛሬ አራተኛ ቀኑ መሆኑ ትዝ አላት፡፡ ባህሪዋ የጨዋ፣ ልስላሴው የድመት፣ የሰውን ስሜት የመረዳትና የመጠበቅ ችሎታዋ በህሊናዋ ተግተለተሉባት፡፡ ማንነቷን አስረስታ የሙሉ ሰው ስሜት እንዲሰማት የምታደርጋት ብቸኛ ሰው እሷ ብቻ መሆኗ ታወሳት፡፡
'ግን ለምን ቀረች?' ራሷን ጠየቀች፡፡

'ሽርሙጣ በመሆኔ አይደል?.....ደግሞም ልክ ናት... ሽርሙጣን እንኳን ባዳ ዘመዷስ መች ይፈልጋታል' አለች፡፡ በተሰበረው ስሜቷ መንስኤ ከእድሜዋ ላይ ሃያ ዓመት የተቀነሰባትና አሁኑኑ የምትሞት መሰላት ሆኖም አልጠላችውም፡፡ ምክንያቱም ከዚህ ምድርና ከህይወት ቶሎ መላቀቅ እንዳለባት እያሰበች፡፡

ቀና ብላ ግዳግዳው ላይ የተንጠለጠለችውን መስታውት በማውረድ ፊቷን አየችው፡፡ ሰውዬው በሁለት ጥፊ ያነደደው የቀኝ ጉንጯ እንደማበጥ ብሎ አይኗንም አበልዞታል፡፡

እብጠቱና ብልዙ እስኪድንላት ቢያንስ ለሶስት ቀን ማንም ወንድ ሲያያት በሽተኛ ስለምትመስለው እንደማይተኛት አሰበች፡፡

በሌላ በኩል የቤት ኪራይ ምግብ እና ለተለያዩ ወጪዎች ደግሞ ገንዘብ ያስፈልጋት ነበር፡፡ እልህና ብሶት እያወራጫት ማልቀስ ቀጠለች፡፡

ሰዋዊ ስሜቱን ያልተገፈፈ ሰው ፈለገች፡፡ ሰዋዊ ፍቅር የሚሰጣት ሰው ፈለገች፡፡ የእናት ዓይነት ፍቅር እሱን ብታጣ..... የወንድም አይነት ፍቅር እሱን ብታጣ..... የእህት አይነት ፍቅር እሱን ብታጣ..... የዘመድ አይነት ፍቅር እሱን ብታጣ.... የወገን አይነት ፍቅር..... ግን ሁሉም የሉም፡፡ 'በዚህ ምድር ላይ እናት ብቻ ነች ልጇን ከነ ቁስሉ፣ ከነ እዳሪው፣ ከነ ምናምኑ.....በንፁህ ልብ ማፍቀር የምትችለው፡፡' እያለች በሀሳብ ስትብሰለሰል ቆየችና እናቷ ናፈቀቻት፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

እሷን ግን ዳግም ልታገኛት እንደማትችል ታወሳት፡፡ እንባዋ መንታ ሆኖ እየተደራረበ መውረድ ቀጠለ፡፡ ብታገኛት አንገቷ ላይ ጥምጥም ብላባት ምን እንደምትላት ማጉተምተም ጀመረች “እማዬ..... ሽርሙጣ ሆንኩልሽ.... ድሮ እንደዛ የምትወጂኝ ህፃን ልጅሽ ዛሬ ለራሴና ለሰው መሰናከያ ሆኜ በሀጢያት ማጥ ተዘፈቅኩልሽ.... እማዬ..... ነገ አንቺ ወደ ገነት ስትገቢ እኔን እግዚያብሔር ገሀነም ይወረውረኛል.... ይህን ቀድመሽ ብታውቂ ትወልጂኝ ነበር?....እሙ.... ናፈቅሺኝ እኮ.....” ለእናቷ ተምሳሌትነት ብርድ ልብሱን ጭምቅ አድርጋ በማቀፍ ተንሰቀሰቀች፡፡

እንባዋ ጉንጮቿን እየለበለባቸው ሲወርድ ተሰማት፡፡ ራሷን ይብስ ጠላች..... ገላዋን ጠላች..... ህይወትን ጠላች.....፡፡

ከአሁን በኋላ በየትኛውም አቅጣጫ በዚህ ምድር ላይ ስኬታማ ልትሆን ብትችል እንኳ አንድ ህያውና ቅን የነበረው ትልቅ መንፈሳዊው አካሏ ከውስጧ ተቆርጦ መሞቱን አወቀች ‘.....ህሊናዬ በህይወት የስቃይ መጠጥ ጠንብዞ ምን ማድረግ እንዳለበት ስቷል ተበላሽቷል’ አለች፡፡

ቀጠለች ‘.....አዎ እኔ ከአሁን በኋላ በሰዎች መካከል ሰዎች ሲስቁ አብሬ እስቅ ይሆናል እንጂ ሳቅ ለኔ ትርጉም የለሽ ነው፡፡ በደስተኛ ሰዎች መካከል እገኝ ይሆናል እንጂ የደስታን ጣዕም የማውቅበት ስሜቴ ሞቷል፡፡ በሚፋቀሩ ሰዎች መካከል ብገኝም ፍቅር ለኔ ሚዛኑ የማይታወቅ ጨለማ ሀይል ነው፡፡ ህዘንስ ምንድነው?..... ህይወትስ ምንድነው? እውነት መድኀኒያለም ለእንደኔ አይነቷ ሰው ሞቷል?!.....’ በማለት አልጋዋ ውስጥ ጭብጥ ብላ ለረዥም ጊዜ ቆየች፡፡

ጥፊው ያረፈበት የፊቷ ገፅ በኩል ህመሙ ሲብስባት የመታትን ሰውዬ አስታወሰችው፡፡ ወድያውም በአካሏ ውስጥ ጥሎባት የሄደው የዘር ፈሳሹ ታሰባት፡፡ ዘገነናት፡፡ ተፈናጥራ ከመኝታዋ ወረደችና ተጣጠበችው፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ማልቀስ አላቆመችም፡፡ የሰውነትን ለዛ ያላጣ የሰው ፍቅር ናፈቃት፡፡ ለሷ ጥሩ ከነበሩት ሰዎች መካከል የቅርብ ጊዜ ትዝታዋ ሰናይት ብቻ ነበረች፡፡ ናፈቀቻት፡፡ ግን አጠገቧ አልነበረችም፡፡ አጠገቧ ያለመኖሯ ደግሞ እሷን የመፈለግ ስሜቷን አባባሰው፡፡ የገጠማትን ሁሉ ልትነግራት ተመኘች፡፡ ወድያው ግን 'ድጋሜ ላትመጣ ሄዳለች ከአሁን በኋላ....' ብላ አሰበች፡፡ እሷ ጋር ትታ የሄደችውን እቃና ንግግሯን አስታወሰች፡፡

"አንቺ ጋር መምጣቴን ለሶስት ተከታታይ ቀናት ያህል ካቆምኩ ፖስታውን ቀደሽ አንብቢው፡፡ የሚያዝኽንም ካለ ፍራቻ ፈፅሚ፡፡" የሚለው ንግግሯ፡፡

ዛሬ አራት ቀን ሆኗታል፡፡ ተነሳችና ሳጥኗን ከአልጋው ስር ጐትታ አወጣችው፡፡ ክዳኑን አንስታ ፖስታውንና እቃ የተጠቀለለበትን ላስቲክ አወጣች፡፡ ፖስታውን ስትቀደው ከውስጥ ትንሽዬ ወረቀት አገኘችና አወጣችው፡፡ በአንድ መስመር ላይ "ከዚህ ህይወት ወጥተሽ መኖር አለብሽ፡፡ ላስቲኩን ፍቺው" ይላል፡፡ እየሰባበረች አነበበችውና ግራ በተጋባ ስሜት የላስቲኩን እሽግ ፈታች፡፡ ሌላ ወረቀት ላይ አጭር ፅሁፍ ሰፍሯል "ይህ አንድ መቶ ሺህ የአሜሪካን ዶላር የአንቺ የግል ሀብት ሆኗል፡፡ ህይወትሽ ተለውጧል ከአሁኑ ጀምሮ" ይላል፡፡

ገንዘቡን አገላበጠችው አየችው፡፡ የሚሰማትን ስሜት ግን ለማወቅ አልቻለችም፡፡ እምባዋ መውረድ አላቆመም፡፡

  

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ምዕራፍ 51

ጆንስ ለአራት ተከታታይ ቀናት በኢትዮጵያ ውስጥ በህቡዕ የሚመራ ፓርቲን በትግራይ፣ በኦሮሞ፣ በደቡብ ክልል ላይ የመሰረቱት ግለሰቦችን ለየብቻ ሲያነጋግር ቆየ።።

ከሶስቱም በዋናነት የተረዳው ጉዳይ ይህ ከውጪ የሚመጣው እርዳታ ከሁሉም ተደብቆ የደቡብ ለሱ ብቻ፣ የኦሮሞውም እንደዛው፤ የትግራዩም በአንድ ሀብታም ግለሰብ የተደረገለት ድጋፍ መሆኑን ነበር የሚያውቁት እንጂ አንደኛቸው ስለሌላኛቸው ምንም መረጃ የላቸውም።።

የሶማሊው ተወላጅ የሆነው አቡበከር ደግሞ የጦር መሳሪያ በሶማሊያ በርበራ ወደብና ግዛት በኩል አስገብቶ ወደ ኢትዮጵያዎቹ ሀረር እና ደቡብ ክልል ላይ በማሻገር የሚያፍሰውን ገንዘብና ከመጣው የጦር መሳሪያ ላይ በደረጃ ተቀንሶ ሶማሊያ ለሚገኙትና በወንድሞቹ ለሚመራው የጐሳ አንጃዎች እርዳታ ማሰጠት መቻሉን ብቻ ነው የተረዳው።። ከዛ ውጪ የሚፈጠረው ነገር በጠቅላላ ጉዳዩ ያለመሆኑንም ለጆንስ በግልፅ አስቀመጠለት።።

በዚህ መካከል በአማራው ክልል ላይ ሊንቀሳቀስ የተስማማውን ጄነራል ስሜት ብቻ ነበር ለማወቅ ያልቻለው።።

በቀጣዩ ቀን ከሰዓት ላይ አምስቱ ሰዎች ለየብቻ ተቆልፎባቸው ከነበሩበት አስወጥቶ በሳሎኑ እንዲሰባሰቡ አስደረገና ሰናይትንም አስመጣት።።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ሶስት ኡዚ መሳሪያ ያነገቱ የጆንስ ሰዎች በበሩና መስኮቱ አካባቢ ቆመዋል፡፡

ሌሎች ሁለት ታጣቂዎች የጊቢውን ዙሪያ ይቆጣጠሩ ነበር፡፡ አብነትም መጨረሻ ላይ ከጓዳ ወጥቶ ተቀላቀላቸውና ተቀመጠ፡፡ “ተዋወቁ” አላቸው ጆንስ ሲጃራ አውጥቶ በመለኮስ ከፊት ለፊታቸው እየተቀመጠ፡፡

የሁሉም ገፅታ ላይ ወደ ሞት የሚጓዝ ሰው የሚያሳየውን ዓይነት ተስፋ መቁረጥ ስሜት ነበር የሚያነበው፡፡

ሁሉም በተናጠል ሰናይትን ያውቋታል፡፡ሆኖም እንደማይተዋወቅ መስለው ተጨባበጡና ስም ተለዋወጡ፡፡ሰናይት ከሁሉም ይበልጥ መደናገጧ በፊቱ ላይ ባቸፈቸፈው ላብ ይታወቅበታል፡፡

ጆንስ ጮላ ባለ ቅላፄ “እናንተ ሁላችሁም አንደኛችሁ ስለ ሌላኛችሁ አታውቁም፡፡ ግና ሁላችሁም በሰናይት የተመለመላችሁ የዓላማ መምቻ መሳሪያ ነበራችሁ” አለ፡፡

አራቱ በጉምጉምታ ተዋጡ፡፡ ሰናይት ዓይኗ ፈጠ ዝም እንዳለች ወደ ጆንስ ታያለች፡፡ ሻለቃ ደርበው ከህፃንነቱ ጀምሮ ክልላቸው ላይ ሀይማኖትን ሽፋን እያደረጉ ለማይታወቅ ዓላማ ከሚመጡ ሚስዮናውያኖቹ ጋር ስላደገ እንግሊዝኛ ቋንቋን ለመግባባት የሚያስችል ያህል ያውቅ ነበር፡፡

በርሔም በሱዳንና አሜሪካ ኗሪ በነበረበት ወቅት ጠንቅቆ ተለማምዷል፡፡ አቡበከር እና ሂርጳ በትምህርት በመታገዝና በልምድ ለመግባቢያነት የሚሆን በቂ እውቀት ነበራቸው፡፡

በአጠቃላይ በክፍሉ ውስጥ ያሉት ሰዎች ለመግባባት ችለዋል፡፡ እገዛ ሲያስፈልግ እዮብ በየመሀከሉ እየገባ ያስተረጉም ጀመር::

ቀጠለ ጆንስ “.....እስኪ መጀመሪያ አንቺው ራስሽ የቀጠረሽ ድርጅት ማን እንደነበረ ለነዚህ ሰዎች ብትገልጭላቸው....”አላት ወደ ሰናይት ዞሮ::

“የሲ.አይ.ኤ. ተቋም፡፡”

አራቱ ሰዎች ድጋሜ በመገረም አጉረመረሙ፡፡

“ሰናይት ተሳስሰሻል” አላትና ቀጠለ “....በፈረንሳይ ውስጥ የሚገኝና በሲ.አይ.ኤ. ስም የተጠቀመ ሌላ ድርጅት ነው ሲያሰራሽ የቆየው፡፡”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“ምን ማስረጃ አላችሁ?” አለች ሰናይት ግራ በተጋባ ሁኔታ።።

ጆንስ ፈገግ አለና በእርጋታ ተነስቶ በስተቀኛቸው በኩል ኮምፒውተር ተቀምጦበት ከነበረው ጠረጴዛ ላይ በርካታ ወረቀቶችን አነሳና

“ሂርፓ....ገመዳ” ተጣራ።።

“እኔ ነኝ”

ባለ አራት ገፅ ወረቀት እየሰጠው “ለአንተ የተላከ ነበር”

“ደርበው ጋፈሮ”

እጁን ዘረጋለት።። ከጄነራል ምትኩና ከከማል በስተቀር ለሁሉም የተላከውን የጦር መሳሪያ መረከቢያውን ትክክለኛ ደብዳቤ አድሎ ካበቃ በኋላ

“በየግዶቹ ላይ ያረፈውን አርማ የመስራቤት ስምና አድራሻዎቹ ስር የተፃፈውን አገር ተመልከቱት” አላቸው።።

“ሳምሶናዊት ቦርሳውን ከመንግስት ያሰረቃችሁት እናንተ ነበራችሁ!?” አግራሞት በተሞላበት ሁኔታ ጠየቀ ሻለቃው።።

“አዎ.....” አለ ጆንስ።።

ሌሎቹ ግን በሁኔታው ይበልጥ ግራ እየተጋቡ ነበር የሄዱት።።

ቀጠለ ጆንስ “ ሉዊስ ወኪሎች የተባለ ድርጅት ነው የቀጠረኝ።።” አላት ሰናይትን።። ከዛም ፓሪስ ላለው ጉዳይ ከተጓዘው ቡድን የተላከለትን ዲስኬት አወጣ።። ዲ.ቪ.ዲ ውስጥ ከተተውና ከፈተው።። “የማትኖረው ኢትዮጵያ” በሚል ስያሜ በሉዊስ የተነደፈውን አጠቃላይ ፕሮጀክቱን የሚያጋልጥ ፊልም ሰላሳ አምስት ኢንች ማሳያ ባለው ትልቅ ቴሌቪዥን ላይ መታየት ጀመረ።።

ለአንድ ሰዓት ከሃያ ደቂቃ ሁለት ጊዜ ደግመው እዩት።።የሁሉም የፊት ገፅታና ስሜት በእጅጉ ተለውጦ ነበር።።

“ቧ..... ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ነው እኛን ወደ ጦርነት እንድንገባ የሚረዱን?” ጠየቀ በርሔ ሰናይት ላይ አፍጠጠ።።

“አዎ.... እንዳያችሁት ከስድስት ቢሊየን ዶላር በላይ ነበር በእናንተ ስም እርዳታ ሲሰበስቡ የቆዩት።።” አለ ጆንስ።።

“አንቺ..... እኔ ነኝ የምረዳችሁ አላልሽኝም!?” በርሔ ደግሞ ሰናይትን ጠየቀ።።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

“ራሷ ለብዙ ሚስጥሮች እንግዳ በመሆኗ ተዋት” አለ ጆንስ በርሔን በእርጋታ፡፡

“እኔ የማይገባኝ ነገር....” ሻለቃው ጆንስን እያየ ቀጠለ
“.....ሀያላን መንግስታቶች ይህንን ያህል ፈንድ አዋጥተው ለዚህ ኘሮጀክት መተግበር እንዲውል በማድረጋቸው የሚያገኙት ጥቅም ምንድነው?” አለ፡፡
“ዝርዝሩ ማለቂያ የለውም.... ዋናው ጉዳይ ግን ካዋጡት የበለጠና እጥፍ ገቢን መልሰው ማግኘት የሚያስችላቸው ስለሆነ ነው.... የእድሜዬን አብዛኛውን ክፍል ያሳለፍኩት በአፍሪካ ዙሪያ በተለይ በኢትዮጵያ ላይ የታሪክ ምርምር ሳካሂድ ነው፡፡ በቅርቡ ተከታታይ ክፍል ያላቸው ግዙፍ ጥራዝ መፅሐፍ ማሳተሜ አይቀርም” አለና የለኮሰውን ሲጃራ አጥፍቶ ቀጠለ
“.....የነሱ የሀብትና የሀያልነት ህልውና ከጥንትም ጀምሮ የተገነባው በአፍሪካ ድህነትና በሷ ላይ በሚያካሔዱት ዝርፊያ ነበር.....፡፡ በርካታ ማስረጃዎችን ማንሳት ይቻላል፡፡
“.....ለምሳሌ ሃያኛዎቹ ክፍለ ዘመናት ድረስ ከሁለት አገሮች በስተቀር በሌሎቹ ላይ ቀኝ ገዢዎች በርካታ ዝርፊያዎችን በአፍሪካ ውስጥ ሲያካሔዱ ኖረዋል፡፡ ኢትዮጵያ ብቻ ናት ነፃነቷን አሳልፋ ሳትሰጥ የኖረችው፡፡”
“ ላይቤሪያስ? ” አለ እዮብ ጣልቃ ገብቶ

“የላይቤሪያ በቅኝ ግዛት ያለመያዝ ራሱን የቻለ ምክንያት ነበረው፡፡ ከአፍሪካ ይጋዙ በነበሩት ባርያዎች ጉልበት ላይ ብቻ ተጭኖ የኖረው ስርአት ወደ ኢንዱስትሪው ስልጣኔ ሲያድግና በርካታ ስራዎች ከባሪያዎች ጉልበት ወደ ማሽን ስራ በመዘዋወራቸው ምክንያት ነጮቹ አዲስ ውሳኔ እንዲያስቀምጡ ተገደዱ፡፡ ውሳኔው በተይ ጉልበታቸው ተመጦ አልቆ እድሜያቸው ለገፋ፤ ይሰሩ በነበሩት አስቸጋሪ ስራ ምክንያት ለተለያዩ የማይድን ህመም የተዳረጉ እናም በአንዳንድ ስፍራዎች ከአስፈላጊው መጠን በላይ ተከማችተው እንደ ሸክም የተቆጠሩ አፍሪካውያኖችን ከነሱ መኖሪያ ስፍራ ማሸሽ ስለፈለጉ ብቻ፤ ጉልበታቸውን እና እድሜያቸውን መጠው ሲያበቁ እየመለሱዋቸው ላይቤሪያ ውስጥ ያከማቿቸው ጀመረ.....

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

"... በዚህ ዋና ምክንያት ላይቤሪያ ላይ የተቃጣባት የወረራ ጥቃት ባለመኖሩ ሲሆን ኢትዮጵያ ግን ላለፉት ሺህ ዓመታት ክንዱን ሊያሳርፍባት ያልሞከረ የአውሮፓ መንግስት አልነበረም።

".....ግን ጀግና በሆነው ህዝቧ መስዋዕትነት በፍፁም ለወራሪ ያልተገዛች ብቸኛ አገር መሆኗን ለዓለም መንግስታትና በባርነት ሲማቅቅ ለመቶዎች ዓመታት ለተገዛው ጥቁር ህዝብ አሳይታለች። በዛ ጨለማ ዘመን ውስጥ ጥቁር የቆዳ ቀለም ያለው ሁሉ እንደ ሰው በማይቆጠርበት ወቅት፤ የሰለጠነና ዘመናዊ መሳሪያ ታጥቆ የመጣን የነጭ ሰራዊት በባዶ እጅ ተዋግታቹ ያሸነፋቹ ህዝቦች ናቹ። በሌላው ጥቁር ህዝብ እይታ አይነኬ መስሎ ይታመን የነበረውን የነጭ የበላይነት ያዋረዳቹና ጥቁር ህዝብ ነጭን ተዋግቶ ማሸነፍ እንደሚችል ለሌላው ቀሪ የአፍሪካ ህዝብና ከዛም አልፎ ለካሪቢያን አገሮች እንዲሁም ለሌሎች በባርነት ሲማቅቁ ለኖሩ አህጉራት ሳይቀር በነፃነት ውስጥ መኖር እንደሚቻል የሚያሳየውን የመጀመሪያውን በር የከፈታቹ ታላቅ ህዝቦች ናቹ። ዛሬ አገራቹን እንድንኮራባትና ስሟ በክብር እንዲጠራ የሚያደርጋት አንዱ የታሪክ ቅርሷ ይህ ነው።" አለ ጆንስ በተመስጦ።

ቀጠለ ".....አንድ አህዛዊ መረጃ ልንገራችሁ" አለና ስለዚህች የጥቁር ህዝብ ምድር ታሪክ ለአስርት ዓመታት ሲያጠና ከቆየው ላይ እየቀነጨበ ጀመረ
"አፍሪካ 30 ሚልዮን ካሬ ኪሎ ሜትር ስፋት ያላት አህጉር ነች። ይህች አህጉር 19ኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ድረስ መሬቷ የህዝቦቿ ወይም የራሷ ሀብቶች አልነበረም። እንግሊዝ 9 ሚልዮን ካሬ ኪ.ሜ. የሚሆነው ምድሯን በቀኝ ግዛት ይዛው ትበዘብዘው ነበር። ይህ ስፋት የራሷን የእንግሊዝን አገር በ35 እጥፍ ይልቅ ነበር.....

".....ፈረንሳይም እንዲሁ 9 ሚልዮን ካሬ ኪ.ሜ. የሚሆነውን ሰፊ መሬት ስትገዛው ቆይታለች። ይህም የፈረንሳይን 17 እጥፍ ያህል ሲሆን ጀርመን ደግሞ ወደ 3 ሚልዮን ካሬ ኪ.ሜ. ይጠጋል። ጣልያን 1.6 ሚልዮንካሬ ኪ.ሜ. ነበራት። ቤልጅየም 2.3 ሚልዮን የሚሆን

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

መሬትን፤ ፖርቹጋል 2.3 ሚልዮን ካሬ ኪ.ሜ. እንዲሁም ስፓኝም ሰፊ ግዛት ነበራት፡፡ በአጠቃላይ በ1900 እ.ኤ.አ. ላይ የአፍሪካ ክልል ከሆነው መሬት ላይ 90.4 በመቶ የሚሆነው በቀኝ ግዛት የተወረረና ለመቶ ዓመታቶች ሲበዘበዝ የቆየ ነበር፡፡ይህ ወቅት ለአፍሪካ አንድ አባባልን ጥሎላት አልፏል፡፡"
"ምን የሚል?" አብነት ጠየቀ፡፡
"ነጮች ወደ አፍሪካ ሲመጡ መፅሀፍ ቅዱስ ነበራቸው፡፡ አፍሪካውያንም መሬት ነበራቸው፡፡ አሁን ግን መሬት ያላቸው ነጮች መፅሀፍ ቅዱስ ያላቸው አፍሪካውያኖች ሆኑ፡፡" የሚል ነው፡፡
".....ከያዟቸው መሬቶች ላይ የራሷን የአፍሪካን ህዝቦች በመሳሪያ እያስገደዱ በፅንሷ ያሉትን ኘላቲኒየም፣ አልማዝ፣ ወርቅ፣ ኮባልት፣ ኒዩቢየም፣ አንቲሞኒ፣ ሊቲየም፣ ማንጋኒዝም፣ ኩፐር፣ ዚንክ፣ ባክሳይድ፣ ቆርቆሮ፣ ዩራኒየም፣ የአረብ ብረት፣ ነዳጅ እናም ህዝባችንን..... እየዘረፉ ወደ አገራቸው በማስጫን ትልልቅ ኢንዱስትሪዎችን ከፈቱ፡፡ ዛሬ ድረስ የሚመኩባቸውና ላሉበት ስልጣኔና ሀያልነት መሰረቱ የአፍሪካ ሀብት ነበር.....

".....አፍሪካዊ ምሁር የነበረው ደብሊው ዱቦይስ ከትቦልን ያለፈው መረጃ ላይ እንደሚያሳየን በዛን ወቅት አፍሪካ ሊሰራ የሚችል ሀያል ክንድ የነበረው አንድ መቶ ሚልየን ህዝቦቿን በባርነት ዝውውር ወቅት እንዳጣችው አስፍሮታል፡፡ ለባሮቹ ማጓጓዣ ይውሉ በነበሩር መርከቦች ላይ እንደ ጭድ ጠቅጥቀው በመጫን ሲወስዷቸው ወደ ሚጋበዙት አገር ከነ ህይወታቸው የሚደርሱት ከአስሩ ሁለቱና አንዱ ብቻ ነበሩ፡፡ ስምንቱ ግን ጭካኔ በተመላበት ሁኔታ መርከቡ ውስጥ በጥይት ተመተው አልያም ወራት በሚፈጀው ጉዞ ላይ በአየር በምግብና በውሃ እጦት ለህልፈት እየበቁ በየውቅያኖሶቹ ላይ የሻርክ ቀለብ ሆነው ይቀሩ ነበር፡፡" አለ በሀዘን፡፡

".....ዛሬ በአሜሪካና በአውሮፓ ያሉት እንደኛ ያሉ ጥቁር ህዝቦች የተራፊዎቹ ዝርያዎች ነን፡፡.... እኛ ወደ እናት ምድር አፍሪካ ለመመለስ ስንታገል ያ የግዞት ዝውውር በዚህ ዘመን ላይ በአሜሪካ ቅርፁን ለውጦ ዲቪ በሚለው ጥበባዊ ንድፍ በመተካት አፍሪካ ዛሬም

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

በስንት መስዋዕትነት ያስተረማረቻቸው ልጆቿን እያጣች ነው፡፡" አለ ጆንስ፡፡
የቤቱን ውስጣዊ እንቅስቃሴ ከሚቆጣጠሩት መካከል ወደ ውስጠኛው መግቢያ በር ቆሞ የነበረው ኢዮብ በጆንስ ንግግር አናቱ በዱላ የተመታ ያህል ተሰማው፡፡ እሱም ከጥቂት ዓመታት በፊት በ "ዲቪ" ነበርና አሜሪካ የገባው፡፡
ጆንስ ቀጠለ ".....ዛሬ በአውሮፓ ያሉት ትልልቅ ባንኮች ተዝቆ የማያልቅ ሀብት ያካበቱት በአፍሪካ ላይ በተካሔደው ወረራና ዝርፊያ ነው፡፡"

ሁሉም በተመስጠ ነበር የሚያዳምጡት፡፡ ሻለቃው ድምፁን ሞረደና "ያለፈው ነገር ሁሉ በአሳዛኝ ሁኔታ ተፈፅሟል፡፡ አሁንስ ለምንድነው አፍሪካን ሰላም ለመንሳት የሚጥሩት?"
ጆንስ ተነስቶ በለሆሳስ ወደ መስኮቱ እየተራመደ መመለስ ጀመረ "ዛሬም ቢሆን የመኖራቸው ሀልውና ከአፍሪካ አናት ላይ አልወረደም፡፡ አፍሪካ ከማንኛውም አህጉራት የላቀ የማዕድን ክምችት አላት፡፡ የነሱ ኢንዱስትሪዎች ዛሬም ቢሆን በከፍተኛ ሁኔታ የሚንቀሳቀሱት ከአፍሪካ በሚላኩ ጥሬ እቃዎች ነው፡፡ አፍሪካ አቅምና ስልጣኔ አግኝታ የራሷን ሀብቶች በራሷ አህጉራዊ ኢንዱስትሪዎች እያስነገባች ብትጠቀም የሀያልነታቸው ጉዳይ ያከትማል፡፡ ይህ ደግሞ መልሶ ከሺህ ዓመታት በፊት ወደነበሩበት ከአፍሪካ የባሰ ድህነት ውስጥ ይጥላቸዋል፡፡....."

".....በመሆኑም አፍሪካ ሰላም ሆና እንድታድግና እንድትለማ አይሹም፡፡ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ እርስ በእርስ እያጠዛጠዟትና እያፋጇት መኖር አለባቸውና ነው፡፡ በዚህ ላይ በአሁኑ ወቅት የዓለማችን ትልቁ የንግድ ምርት የጦር መሳሪያ ነው፡፡ እነሱ እንደሆነ እርስ በእርስም ይሁን ከሌላ ጋር አይዋጉም፡፡ ያመረቱዋቸውን መሳሪያዎች ለመሸጥ ደግሞ ዘወትር በመራወጥ ላይ ናቸው፡፡ እናም ይህች አህጉር ከራሷ ከርሰ ምድር ተጭኖ በሂደው ማዕድኗ ተመልሶ ማጥፊያዋ ይመረትበትና ወደሷ ይላካል....."

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“..... በጥቅሉ ለነሱ የጦር መሳሪያቸው መጣያ አፍሪካ፤ጊዜ ያለፈባቸው መራዥና አደገኛ መድሀኒቶች ማቃጠያ አፍሪካ፤ አገልግሎታቸውን ጨርሰው ፀረ-ተፈጥሮ የሆኑ ኬሚካሎችና የኒኩልየር ዝቃጮችን መቅበሪያ አፍሪካ፤ በህክምናና በየምርምር ማዕከሎቹ የሚፈበርኩዋቸውን በሽታዎች መሞከሪያ የአፍሪካ ህዝብ....አፍሪካ ማለት ለነሱ በሌላኛው መልኩ ሰፊ የቆሻሻ ገንዳ ስትሆን ህዝብጅ ደግሞ በገንዳው ውስጥ የተራቡ ትላትሎች ናቸው፡፡ ይህ ታዲያ እውነተኛ የሆነ የአገራዊነት፣ የተቆርቋሪነትና የአንድነት ስሜት ካላችሁ ሊያሳዝናችሁ በቂ አይሆንም!?” አላቸው ቀስቃሽ በሆነና ሀይል በተሞላ ስሜት ተውጠ፡፡ ዓይኖቹም እምባ ማቀርዘዝ መጀመራቸው አስታወቀ፡፡

ቀጠለ “.....ከቀኝ ግዛት ብዝበዛቸው በአባቶቻችን ትግል ነቅለው ከወጡ በኋላም በዘመናት ውስጥ ወቅቱን እየጠበቀ የሚፈነዳ የግጭት ፈንጅን ቀብረውብን በመሄዳቸው አንሶ ዛሬም በአካል እየመጡ እርስ በእርስ የሚያባሉንና የሚያፋጁን ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ እንጂ እውነት ለትግራይ ወይም ለኦሮሞ ወይም ለኤርትራ ወይም ለሁቱና ቱትሲ..... ህዝብ አዝነውና ተቆርቋሪ ሆነው አይደለም፡፡ በተመረዘ ነፃነት ካባ የሸፈኑት የአፍሪካን ህዝብና ውድቀት ጥፋት ስለሚሹት እንጂ..... የአፍሪካን አንድነት ፅንሰ ሀሳብ እስከመጨረሻው እንዳይፈፀም ወደ እቶን ወርውረው ዶጋ አመድ አድርገው ማስቀረት ስለሚፈልጉ እንጂ.....”

ስሜቱን መቋቋም አልቻለም ጆንስ፡፡ ሶፍት አውጥቶ በጉንጩ ላይ መንከባለል የጀመረው እምባው ፂሙ ስር ከመስረጉ በፊት ጠረገው፡፡

በዚህ ቅፅበት የአምስቱ ሰዎች የበፊት ዓላማና የትግል እንቅስቃሴ ማዕበል እንደመታው የአሸዋ ቁልል እየተንሸራተተ መበታተን ጀምሮ ነበር፡፡

“የማይጣፍጥ እውነት ልንገራችሁ.... በቅኝ ግዛት አትያዙ እንጂ የቅኝ ግዛት ተፅእኖ ሰለባ ሆናችኋል፡፡ ምክንያቱም የአብዛኞቻቹ እምነት፤ አመለካከትና ድርጊት ሙሉ በሙሉ ቅኝ ተይዘው ከነበሩ የአፍሪካ አገር

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

መሪዎች ምንም የተለየ ሊሆን አልቻለም። ይህም በዓለም አገሮች እይታ «የነፃነት አገር እና የነፃነት ህዝብ ተምሳሌት» የሚለው መልካም መልካቹን ካሳጣቹ ሰነባብቷል። ሌላው ያልገባቹ እውነታ በመገነጣጠላቹ ብቻ የምትመኙት ሰላምና ብልፅግና እንዲሁም የመኖር ዋስትና ይመጣ ከመሰላቹ ተሳስታችኋል.....

"ጠላቶቻቹ ምእራባውያኑም ሆኑ በውስጥ ጉዳያቹ እጃቸውን እያስገቡ የሚያተራምሷቹ አረቦቹ ተገነጣጠላቹም አንድ ሆናቹም ከዚህ ከናንተ መሬት ላይ የሚያገኙት ጥቅም እስካለ ድረስ መቼም ሰላም አይሰጧችሁም። መቼም!!! " ብሎ በየተራ እያያቸው ቀጠለ.....

" የነሱ ጉዳይ የናንተ ነፃነት እና ሰላም አይደለም። እናንትን በተለያየ መንገድ እያዳከሙ ጥቅምና ዓላማቸውን ካለ እንቅፋት ማስጠበቅ መቻል ብቻ ነው። እንደውም ተገነጣጥላቹ ትንንሽዬ ስትሆኑላቸው በሻርክ አፋቸው እናንተን ለመዋጥ ይበልጥ ይቀላቸዋል። እውነት እላችኋለው እንደውም ቀና በል፤ ጎምበስ በል፤ ተኛ፤ ተነስ፤ የሚሉ አሳፋሪና ተራ ትእዛዛትን ሁሉ ተገዳቹ እከመቀበል ተደርሳላቹ። እስኪ እንደ ህዝብ መሪና እንደ አገር አስተዳደር ሀላፊ ሆናቹ አስቡት። ያለፈውን ሁሉ በቅን ልቦና፤ በመቻቻል፤ በይቅርታ አሳልፎ እንደ አገር በመፅናት በአገር ላይ የመጣን ጠላት እንደ አገር አንድ ሆኖ መታገል ይበልጥ ላለመጠቃት ያስችላል። ግዙፍ አገር እና ብዙ ህዝብ መሆን ለውጭ ጠላት ያስፈራል። ከብዙ ህዝብ ብዙ እውቀት፤ ብዙ ጥበብ፤ ብዙ ሀይል፤ ብዙ ጉልበትና ብዙ ምርጥ ውጤት ለአንድ አገር ይሰለፋል። ይህም ይበልጥ ያስከብራል። አይነኬ ያስደርጋል.....

" ሌላው ዋናው ጉዳይ አንድ ብሔር ተገንጥሎ ወጥቶ አገር ሲሆን ምዕራባውያኑም ቀጣዩን ምእራፍ ከፍተው ማስተግበር ይጀምራሉ። እሱም ብሔርን ወደ ጎሳ መከፋፈል ጎሳንም ወደ ቤተሰባዊ የዘር ሀረግ ወደ መሰነጣጠቅ ይቀጥላል። ጦርነቱና እልቂቱ መቼም ቢሆን ማቆሚያ የለውም። ፍፃሜው ግን ህዝብ ያልቃል። ትውልድ ይሞታል። ከዛም አገር ትሞታለች። ጠላቶቻቹ ግን መኖር ይቀጥላሉ..... ሶማሊያን እዩ..... ኤርትራ በመገንጠሏ ያወራችውን ሰላምና ብልፅግና አገኘች?! ሩዋንዳስ ከዛ ዘግናኝ እልቂት ምን አተረፈች?! እጅና እግራቸውን የተቆራረጡ ተስፋ የለሽ ህፃናትን ተሸክሞ ለምእራባውያኑ መሳቂያና ለማኝ ሆኖ መቅረት ብቻ ነው.....

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“ ትላንት የራሱን መልክ ይዞ ሄዷል። ነገን ውብ ለማድረግ ዛሬን ማቆንጀት መቻል አለባቹ። ነገን የፍቅር ለማድረግ ዛሬን የመዋደድ ማድረግ ያስፈልጋል። ነገን የመከባበር ለማድረግ ዛሬን የይቅርታ ቀን ማድረግን ይጠይቃል። የነገው ማንነት ሁሌም የሚገነባው በዛሬው መሰረት ላይ ብቻ ነው። ፍቅር ምንም ዋጋ አያስከፍልም ጥላቻና ቂም ግን የሚያስከፍሉት ጠንቅና መዘዝ እንዲሁም ከሚያስከትሉት ጦስ ጋር የሚያበቃው የምፅአት ቀን ብቻ ነው....

“ ስለትላቱ ቀን ቆሻሻነት ስታወሩና የዛገ ሰይፋችሁን ከተቀበረበት በማውጣት ስትጨራረሱበት ዛሬንም የባሰ በሰው ልጅ ደም አሳድፋችሁት ታልፉና የነገው ትውልድ ደግሞ በባሰና በበሰበሰ የማንነት ግማት ላይ ራሱን ተስፋ የለሽ ሆኖ እንዳያገኘው ተጠንቀቁ። ተቀብሮ የዛገውን ሰይፍ ከነበቀል እሳቤው ጋር እዛው ተውት ይበስብስ..... ይጥፋ..... ሰይፍ ከሚያመጣ ውጤት ይልቅ ፍቅር የሚያመጣው ለውጥ የበለጠ ታላቅ ዋጋ አለው። ዘላለማዊም ሆኖ መኖር ይችላል። ሁላችሁም..... ሁላችንም አንድ ነን። ሁላችንም ባለፈው የመከራ እሳት እኩል ተጠብሰናል። እኩል ተበላልተናል። እባካችሁ እዚህ ጋር ይብቃ። ፊታችን ለፍቅር ይብራ። ልባችን ለፍቅር ይስራ።”

ጆንስ በአስፈሪ ዝምታ ተውጦ ሁሉንም በየተራ አስተዋላቸው። መጨረሻ ላይ ሂርጳ ላይ ዓይኖቹን ሰደረና “በኢትዮጵያ ውስጥ በተለይ ኦሮሞ ብሔረሰብ መሪ ነን ባዮች ሁልጊዜ ስለ ብሶትና መገንጠል በዓለም መገናኛ ብዙሀኖች ሲያወሩ እሰማለሁ። ነጮቹም ይህን ስሜት ዘወትር እያነሳሱትና እያወሳሰቡት እሳቱን በማራገብ ሲያባብሱት አያለሁ። ይህ ለምንድነው የሆነው?” አለው ሂርጳን በዝቅተኛ ግን ውስጣዊ ግለት ባለው ስሜትና ቅላፄ።

ሂርጳ እንዳቀረቀረ ቆየና “እኛማ የነፍጠኛው ስርዓት በኦሮሞ ላይ ያደረሰው ግፍና በደል በታሪክ መፅሀፎች ላይ ተፅፎ ስናነብ በእጅጉ ለበቀል ስሜት ያነሳሳናልና ነው።” አለ።
“ማነው የታሪኩቹን መፅሀፍ ሲፅፍ የኖረው?”
“የአውሮፓ ፀሀፊዎች እናም በጥቅም ተገስተው አውሮፓውያኑ እንደሚፈልጉት እያደረጉ የፃፉላቸው የኛው ሰዎች ጭምር ናቸው።”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“ከፀፊዎቹ በስተጀርባስ?” ጆንስ ድጋሜ ጠየቀ፡፡
“የአገራቸው መንግስት ነዋ” አብነት ሁሉም ዝም ሲሉ መለሰ፡፡
“አዎ..... በአመዛኙ በገዢዎቻቸው ትዕዛዝና ተፅዕኖ ስር ሆነው ነበር የሚፅፉት፡፡ ገዢዎቻቸው ደግሞ ቅድም እንዳልኩት የአፍሪካ ህዝብ ስነ-ልቦና ላይ ነቀርሳና ጠባሳ የሚፈጥር ስራዎችን ነው ሆነ ብለው ሲያስሩ የኖሩት፡፡ የፈጠራ ሀሳቦችን ነው እውነት አስመስለው በታሪክ ስም ያፃፉልን፡፡ እሱም ከቀበሩብን ፈንጂዎቻቸው መካከል አንዱ ነበር፡፡ ይኸው ወቅቱን ጠብቆ መፈንዳቱን ጀምሯል፡፡.....

“.....በሌላ በኩል እውነት ይሁን ብለን ይህን የታሪክ ድርሳን እንቀበለው፡፡ ከዛሬ ሃምሳና መቶ ዓመታት በፊት የነበሩት ነገስታቶች ጥሩ ጐን የነበራቸውን ያህል እኩይ ነገርም ነበሩዋቸው፡፡ ይህ የማይካድ ሀቅ ነው፡፡ እናም የገዢነት ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ ሲሉ ያሻቸውን አድርገው አለፉ እንበል፡፡ ዛሬ ላይ ግን እነሱ ወይም አገዛዛቸው የለም፡፡ ይህ ሌላ ዘመንና ሌላ አስተሳሰብ የሞላበት ወቅት ነው፡፡ ታዲያ እናንተ ከዛሬ መቶ ሁለት መቶና ሶስት መቶ ዓመታት በፊት የተካሔደውን በአብዛኛው ያልተካሄደውንም የሀሰት ጉዳይ ነጮቹ ፈልፍለው አሳድገውና አግንነው ሲሰጧችሁ የጦርነት ሰይፍ መምዘዙ እውነተኛ አገርና ህዝብ ወዳድ ሊያስብላችሁ የሚችል ይመስላልችኋል?”
ሂርጳ ምላሽ አለነበረውም፡፡

ጆንስ ቀጠለ “.....የግጭታችሁ መነሻዎች ሁሉ የትላንትና ያረጁ ጠባሳዎች እንጂ የዛሬ ምቶችና ትኩስ ቁስሎች አልነበሩም፡፡.....
“.....የዛን ዘመን ገዢ ነገስታቶች አማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ስለነበሩ ብቻ ዛሬ አማራው ህዝብ ላይ እየሰረፀባችሁ ያለው ጥላቻ ፍፁም አግባብነት የሌለው ነው፡፡ ቆም ብላችሁ የሁለቱን ጐሳ ህዝቦች ብታዩዋቸው ፍቅር ነው ያላቸው፤ አንድነት ነው ያላቸው፤ህብረት ነው ያላቸው፡፡ መሪና አዋቂ ነን ባዮች እናንተ ግን በሌለና ባልነበረ እውነታ ላይ ኖረ ብላችሁ ብትነሱ እንኳ እንደ ዳዊትና ጐልያድ ዘመን ጦርነት ታሪክ ሆኖ በቀረ ሃሳብ ላይ ቤንዚን እያርከፈከፉባችሁ ክብሪት እየጫራችሁ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ህዝቡ እንደ አዲስ ከማፋጀት በስተቀር ምን ቦታ ምን እውነታ አላችሁ?.....
“.....አማራው ያኔም የአማራ ገዢዎች በነበሩበት ወቅትም ይሁን ዛሬ ህዝቡም ይሁን ገበሬው ከስም በስተቀር አንዳች ያገኘው ጥቅም የለው፡፡ እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ህዝብ በረሃብ በመሀይምነት በበሽታ እየማቀቀ ከመርገፉ ውጪ..... እስኪ በዓይናችሁ ፊት ያለውን ግርዶሽ አንሱት እውነታዎችን አመዛዝናችሁ አስተውሉ፡፡ ጥንትም ይሁን ዛሬ ህዝቡ ጮስቋላ ነው፡፡ ከናንተ የተለየ የተደረገለት ጥቅም አልነበረም፡፡ ዛሬም የለም፡፡ ኢትዮጵያ ስትራብ አብሮ ይራባል፡፡ ኢትዮጵያ ስትጠግብ አብሮ ይጠግባል፡፡ እንደማንኛውም ህዝብ፡፡ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ ግን አንድ የሚያደርገው ልዩ የሆነውና ልቡ ውስጥ የሚቃጠል የአገር ፍቅር ስሜቱ ነው፡፡”

ሂርጳ በላብ እየራሰ ነበር፡፡ ንግግሩ ግን የሁሉንም ህሊናና የጠበበ አስተሳሰብ ነክቷል፡፡ ሁሉም የሚሰሙት ከዚህ ቀደም ቦታ ያልሰጡትን የማንነታቸውን ገፅታ ነበርና፡፡
ጆንስ ቀጠለ “.....ዛሬ የግጭታችሁ መንስኤዎች በጠቅላላ ህልም መሳይ ትዝታዎች ናቸው፡፡ ባላወቃችሁት ሁኔታ የነጮች ወይም የነጭ ቡችላ ከሆኑት ከፋፋይ ገዢዎቻችሁ ተፅእኖ ስር ስለወደቃችሁ ልቦናችሁን መክፈትና ማስተዋል ተስኖዋችኋል፡፡ አሁን እየፈፀማችትና ልትፈፅሙት እየተዘጋጃችሁት የነበሩት ነገሮች በጠቅላላ ራሱ ለቀጣዩ ትውልድ ሌላ እልቂትና ቂምን የሚያተርፍ፤ የብቀላ በትርን አውርሶ የሚያልፍ ነው፡፡.....

“.....የኢትዮጵያ የጀግንነትና ለቅኝ ገዢዎች ያለመንበርከክ ታሪክ የአማራ ወይም የትግሬ ወይም የአፋር ብቻ አይደለም፡፡ የመላው ሰማንያ ብሔረሰብ የአንድነትና የትግል ውጤት እንጂ፡፡ በኢትዮጵያዊነታችሁ የምትግባቡዋቸው አንድ ሺህ እውነታዎች እያሏችሁ እንዳሉ ቢተው እንኳ ምንም ጥቅምም ጉዳትም የማያመጡትን አስር የማይሞሉ የልዩነቶችን ነጥቦች እየተተባተባችሁበት በመሳሪያ ትቆራቆዙበታላችሁ፡፡ በሱም የስልጣን

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

መኾገር፤ የህዝብና የአገር አንገት አንቀው ገዢዎቻችሁ የቆይታ ዘመናቸውን ታራዝሙላቸዋላችሁ፡፡" አለ በሲቃ ቅላፄ፡፡

ቀጠለ "....እናንተ በምታራምዱት አስተሳሰብና ኋላ ቀር ንድፍ አፍሪካ ወደ ባሰ ድህነት ጥፋትና ምድረ በዳነት ትዘግጣለች፡፡ ይህ ነው ትርፏ፡፡ ሌላው የአውሮፓ ኢስያና አሜሪካ ግዛት ወደ አንድነት እየተጠቃለለ ሄዷል..... ባለፉት ዘመናት ኮሚኒስትና ኤምፔሪያሊስት በመባል የሚታወቁት ተቀራኒ ርዕዮተ ዓለማትን ሲያራምዱ የኖሩ አገሮች እንኳ ዛሬ አቋማቸውን በማለዘብ ወደ አንድነትና የመመሳሰል አቅጣጫን እየያዙ በመጡበት ሰዓት ላይ ከነሱ እያየን መሄድ አቅቶን ነጋ ጠባ ስለ ግንጠላና ፍልሚያ እንሮጣለን፡፡....

".....ብልጠቹ ነጮች ግን ዛሬ ከመቼውም ጊዜ በተለየ ሁኔታ ተቀራርበዋል፡፡ የመጠሪያ ስያሜያቸውን እንኳ ሳይቀር ምዕራባውያኑ የተቀራራቡ ስሞች መጠቀም ጀምረዋል፡፡ እንዲሁም "በኢንዱስትሪ ኋላ ቀርና የበለፀጉ አገሮች" በማለት ይጠቀሙበት የነበረውን ሀረግ ዛሬ "የሰሜንና የደቡብ ግንኙነቶች" በሚሉት አቀራርበዋቸዋል፡፡ ነገ ደግሞ አንድ ሆነው በአንድ የጋራ ስያሜና ግዛት ለመጠቃለል በሚስጥር እየተጉ ይገኛሉ፡፡ ይህ የሚያሳየው በዚህ ዘመን ላይ አንድነት ምንም አማራጭ የሌለው የአቅም፤ የብልፅግና፤ የስልጣኔና የክብር መሳሪያ መሆኑን ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ የአውሮፓ አገሮች ህብረት ወደ አንድነት መለወጡ ሁነኛ ማሳያ ሊሆን ይችላል፡፡ ልበ ድፍን ባትሆኑ ኖሮ ይህን ማየታቹ ብቻ በራሱ በቂ ነበር፡፡ " አለ በየተራ እያያቸው፡፡

ቀጠለ ".....እናንተ ደግሞ አስርና ሀያ ሚልዮን የሚሆን ያውም ገና ያልተማረና ድቅድቅ ፅልመት እና ድህነት ውስጥ ያለን ህዝብ ይዛችሁ መገንጠል በሚል ኋላ ቀር ፈሊጥ ትታገላላችሁ፡፡ ይህ ፍፁም የሆነ ስህተት ነው፡፡ እኛ አፍሪካውያን ስለ ድህነት፣ ስለ ረሃብ፣ ስለ በሽታ፣ ስለ አንድነት ነው ማሰብ ያለብን ወይንስ ዛሬም እንዳለፉት በርካታ ዘመናት ስለ ጦርነት፣ ስለ ክፍፍል፣ ስለ ዘር መድልአና ጭሰኝነት እንሩጥ!?..... አይበቃም ባለፈው ጉዞዋችን ያካበትነው

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ስብራት!?..... መማር አንችልም ካለፈው!?..... ያለፉት ትውልዶች ተዋጉ ተጨራረሱ ተበጣጠሱ ግን ለአፍሪካና ለኛ ምን አተረፉልን!?..... ጥቅም አልባ ጥላቻን ቅስም ከሰበረ ድህነትና መሀይምነትን ብቻ.....” አለ በታከተ ስሜት።።

ቀጠለ “.....ዛሬ በስነ-ልሳን ላይ ከሚደጉት ጥልቅ ጥናቶች ላይ እየተገኙ ያሉት ውጤቶች ለበርካታ ሺህ ዘመናት አፍሪካ የነበራትን የባህል የዘርና የአንድነትን ውህደቶች እያሳዩ ይገኛሉ።። እነዛ የነገድ ትስስሮች ደግሞ ከመሰረቱ አንስቶ ዛሬም ድረስ ውህደታቸው ሳይፈራርስ በከፊልም ቢሆን እንደተጠበቁ የሚገኙት በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ ነው።።” አለ ጆንስ

በንግግሩ መሀከል ጥርሱን ነክሶ ፈገግ አለና ቀጠለ “.....ኢትዮጵያ ግን በዚህ ወቅት አንድ የሆነ ብሔራዊ ቋንቋ የሌላት አገር ሆናለች።። ከቋንቋው ጋር በተያያዘ ሁኔታ ስለ ትምህርት ፖሊሲያችሁ በጣም የሚያሳዝነኝ ነገር አለ” አለና እይታውን ወደ ወለሉ በመትከል በዝምታ ተውጦ ቆየ።።
አብነት ሲቁነጠነጥ ቆየና ዝምታው ሲረዝምበት “ችግሩን ብትነግረን.....”አለው በዝግታ።።

“.....ትምህርት በኢትዮጵያ ውስጥ “በአፍ መፍቻ ቋንቋ” በሚል ሰበብ በአገሪቷ ውስጥ በአምስትና ከዛም በላይ በሆኑ ቋንቋዎች እየተሰጡ ነው ያሉት።። እንዲሁም በየ ክልሉ ላይ የስራ ቋንቋ በየጐሳው ቋንቋ መሠረት እንዲካሔድ እየተደረገ ነው።። ጉዳዩ ላይ ላዩን ሲታይ የክልሎቹን ህብረተሰብ ለመጥቀም የተደረገ በጐ ስራ ሊመስል ይችላል።። ችግሩ መርዙን መርጨት የሚጀምረው ግን ከሃያና ከሰላሳ ዓመታት በኋላ ነው።። ለምሳሌ በክልሉ ቋንቋ ትምህርቱን ያጠናቀቀ አንድ ወጣት አገሬ በሚላት በመላው የኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ እንዳሸው እየተዘዋወረ ስራ መስራት አይችልም።። ምክንያቱም የደቡብ ኦሮምኛን ወይም አማርኛን አልያም ትግሪኛን አይችልምና ነው።። ሌላውም እንደዛው።። አንዱ የአንዱን ስለማይችል ደግሞ ባለበት ጠባብ ስፍራ ላይ ተገድቦ መቅረቱ ግዴታው ይሆናል።።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

በሁሉም ክልሎች ላይ ይህ በሚከሰትበት ወቅት አገር አቀፋዊ በሆነ መልኩ ሊያስተሳስራቸው ይችል የነበረውን አንድ ትልቅ ቅርስ ያሳጣቸዋል፡፡....

".....ሁሉም በሩን ዘግቶ በራሱ ክልል ላይ እንዲቀመጥ ሲደረግ ደግሞ ለምን ተገንጥዬ የራሴን መንግስት አልመሰርትም ወደሚል ጭፍንና ኋላ ቀር ስሜት ውስጥ ለመግባት ይገደዳል፡፡ ይህ የቋንቋና የትምህርት ፖሊሲ ራሱ የኢትዮጵያን አንድነት ለመከፋፈል በገዢዎቻችሁ ሆን ተብሎ የታቀደ ሴራ ነው፡፡" አለ ጆንስ በስሜት መዳፎቹን ጨብጦ፡፡
ሁሉንም እያየ ቆየና ".....የናንተ ገዢዎች እናንተን የመከፋፈል መሰሪ ዓላማ ለማካሔድ እንጂ፡፡"

ከሁሉም ይልቅ ሂርጳ ፊት ላይ የቅሬታ ስሜት ይታየበት ነበር፡፡ ጆንስም ሁኔታውን ተረድቶታል፡፡ ፈገግ አለና "ኢትዮጵያ በአፍሪካ ውስጥ በብቸኛነት የምትጠቀምበት የራሷ የሆኑ ሆሔያት እያሏት የነጮቹን ተውሶ ማምጣቱ ለምን አስፈለገ?" አለ ለኦሮምኛ ቋንቋ ከላቲን የተወረሰውን እያሰበ፡፡
ቀጠለ ".....ወንድሞች ነጮች በአፍሪካ ላይ የሚያካሔዱት ጦርነት የህዝብና የማዕድን ዘረፋ ላይ ብቻ ያነጣጠረ አይደለም፡፡ የባህልና የቅርስ ውድመትንም በስፋት እያካሔዱ ናቸው፡፡ በዘመናት ዕድሜ ታሽተውና ተቀርፀው እዚህ የደረሱ የአፍሪካ የባህልና የቅርስ ሀብቶችን በአርቴፊሻል ወረርሺኞቸው እንዲጠፉ ወይም በነሱ ተፅዕኖ ስር እንዲወድቁ እያደረጓቸው ነው፡፡ በማንኛውም ነገር ይህ ጥቁር የአፍሪካ ህዝብ የነሱ ጥገኛ ሆኖ እንዲኖር ይፈልጋሉ፡፡ ለዚህም በአማካሪነት የውስጥ ጉዳዮቻችን ላይ እያስገባናቸው በሆሄያቶቻችን ላይ እንኳ እስከመወሰን ደረሱ፡፡ ለዚም የኦሮምኛ ቋንቋ በላቲን ተፅዕኖ ስር ወደቀ፡፡.....

".....ምናልባት በዚህ ዘመንና የስልጣኔ ደረጃ የኢትዮጵያ ሆሄያት ጥበቱ አላሰራ ብሎ ቢያስቸግር እንኳ በምርምር ማዕከላት እንዲዳብርና እንዲያድግ ማድረግ በተቻለ ነበር፡፡ ግን ተቆርቋሪነት

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ያለው ገዢ ታጣ እንጂ፡፡.....ዛሬ ዓለምን ለመቆጣጠር የሚጥረው የእንግሊዝኛ ሆሄ በአንድ ወቅት ላይ የራሱ ጥበትና ድክመቶች ነበሩበት፡፡ ግና በተናጋሪዎቹ ያላሰለሰ ጥረት፣ ምርምርና ግኝት ለዚህ በቅቷል፡፡ የኢትዮጵያ ሆሄም በኦሮምኛ እንዲያመች ማስደረጉ አቅቶዋቸው አይደለም ከላቲን እንዲወረስ ያስደረጉት..... በዛ ላይ የቋንቋና የሆሄያት እድገት እንደ አገሪቷ የስልጣኔና የምርምር ሁኔታ ሊፈጥንም ሊጓተትም ይችላል፡፡ በራሱ ማደግና መበልፀግ ይችል ነበር፡፡....

“.....ወደፊት እንደ አስፈላጊነቱ በትክክል የኢትዮጵያ ሆሄ ሊዳብር የማይችል መሆኑ ከአገሬው አብራክ በተገኙ የበቁ ምሁራኖች ጥናትና ምርምር እንዲሁም በህዝቡ ታምኖበት ለአዲስ ሆሄ ቦታ እንዲለቅና ሙዝየም እንዲገባ ማድረግ እየተቻለ ዛሬ ከባዶ ሜዳ ተነስቶ በሚልዮን የሚቆጠር ታዳጊ ተማሪና የአገር ተረካቢ ወጣት ህልውና ላይ ከጫካ በመጡ ሽፍታ መሪዎች መወሰኑ ፍፁም አግባብነት የሌለው ነው፡፡”
ከረዥም ደቂቃዎች በኋላ ሻለቃው “ምንድነው በቀጣይ መከናወን ያለበት?” ጠየቀ፡፡
ጆንስ ድካም ባለዘበው ስሜት “መጀመሪያ በማንኛውም ሂደት ውስጥ በአንድነት እመኑ፡፡ ሌላውን ችግር ሁሉ በመወያየት መፍታት እንደሚቻል በጥልቅ አስተውሉ፡፡ በመወያየት ውስጥ ሚልዮን የሀሳብ ፍጭት ይነሳሉ፡፡ በየትኛው የዓለም ግዛት ደግሞ ሀሳቦች ካልተጋጩ፤ ሀሳቦች ካልተፋጩ አዲስ የእድገት ምዕራፍ አይፈጠሩም፡፡.....

“.....የሀሳብ ግጭቶች ወደ ጦር መሳሪያ መዘዛ ማምራት የለባቸውም፡፡ እሱ ቢሆንማ የመጨረሻው መፍትሔ አሜሪካውያኖች፣ አውሮፓውያኖች.....ዛሬ ሀያል የተሰኙ አገሮች በጠቅላላ እርስ በእርስ ተጨፋጭፈው በተጨራረሱ ነበር፡፡የሀሳብ ግጭቶች የትም ያሉ ናቸው፡፡ ከነሱ ውስጥ እውነታ ይፈልቃል፡፡ በእውነታው መተማመን ላይ ይደርሳል፡፡ የተማመናችሁበት የእውነት ዓላማ ደግሞ ጠቅላላ የአገሬው ህዝብ አስከትላችሁ ያሻችሁትን ተራራ መናድ የሚያስችል ሀይል ታገኛላችሁ፡፡ እና የጦር መሳሪያን የመጨረሻ መፍትሔ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

አድርጋችሁ አትነሱ፡፡ አንዳንዴም በመተላለፍ ችግሮችን መፍታት እንደሚቻል ከሀያላኖቹ አገሮች ተማሩ፡፡...

“..... የአንድ አገር ህዝብ ማለት ለአንድ አዕምሮ የሚሰራ መላው የሰውነት አካል ማለት ነው፡፡ ከሰውነታችን አንዱ ሲታወክ ሌላውም በትክክል መስራትም ሆነ መኖር አይችልም፡፡ አትሞኙ የአንድ አካል መጉደል ለሌላው ሁሉ ጠንቅ ነው፡፡ የናንተም ውበት እና ሀይል አንድነታችሁ ነው....
“.....አንድነትና ህብረት ሲኖር የትም ቦታ ሀይል አለ፡፡ ታላቋ ሶቭየት ከመበታተኗ በፊትና በኋላ ያለችበትን ሁኔታ አጢኑ፡፡ ጀመርኖች ሲዋሀዱ ዓለም ላይ ያሳደሩትን የሀያልነት ተፅዕኖ አመዛዝኑ፡፡ እንዲሁም በጠላትነት ሲተያዩ የኖሩት ሰሜንና ደቡብ ኮሪያዎች በጣልቃ ገብ አገሮች እየተጓተተባቸው እንጂ ወደ አንድነት ለመጠቃለል ስምምነቶችን መፈራረም ጀምረዋል፡፡ አንድነት ካለ ፍቅር አለ፡፡ እንሱ ሲኖሩ ደግሞ ሁሉም ነገር አለ፡፡ በዚህች ምድር ላይ ያለው የሰው ልጅ በጠቅላላ ስለ አንድነት ያለው እውቀትና ፍላጐት ተመሳሳይ ቢሆን ኖሮ ምድርን ገነት ማድረግ በቻልንና ሰማያዊውንም ገነት ገና በይመጣል ተስፋ ባልጠበቅን ነበር፡፡ በጦርነትና በክፍፍል እድገት መቼም አይመጣም፡፡ ስልጣኔ መቼም አይመጣም፡፡ ጦርነት የእድገት በር መክፈቻ ቢሆን ኖሮ ኢትዮጵያ ከዓለም ቁንጮነት አልፋ ጋላክሲን በተቆጣጠረች ነበር፡፡ 'ስለ ጦርነት አስከፊ ገፅታ ማንስ ከኢትዮጵያ ምድርና ህዝብ ልቆ ሊያውቅ ይችላልና?.....” አለ ሲጀራ አውጥቶ እየለኮሰ፡፡

“ሳያችሁ በአሜሪካ ግዛት ውስጥ እንዳሉት ጥቁር አፍሪካውያን ጋር ትመለሳላችሁ፡፡” አለ በርሔ ጆንስና ሌሎቹን እያየ፡፡
“ስለ ማንነታችሁ እስከአሁን አልነገርከንም፡፡”
“በቀጣዩ ዕለት ስለ እያንዳንዱ እንቅስቃሴያችን እነግራችኋለው፡፡” መለሰለት ጆንስ፡፡ እንደደከመው ያስታውቃል፡፡
ቀጠለ “.....ወደየ ክፍሎቻችሁ መሄድ ትችላላችሁ እኛ ለእናንተ ፍቅር አለን፡፡እንደ አንድ ቤተሰብ አስቡን፡፡” ንግግሩ የሁሉንም ልብ ኮረኮረው፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

የዕለቱ የጆንስ ተግባር ሙሉ በሙሉ ባይባልም እጅግ በላቀ ሁኔታ የሰዎቹን የተሳሳተ አካሔድና የአስተሳሰብ አቅጣጫ ማስለወጥ የቻለ ነበር።
በቀጣዩ ዕለት ጆንስ ስለ "አፍሮኢዝም" አመሰራረትና ዓላማ ቀኑን ሙሉ ሲገልፅላቸው ዋለ። መጨረሻ ላይም እያንዳንዳቸው በዚህ ተግባር ላይ ተሳታፊ በመሆን ለስኬቱ ምን ምን መስራት እንደሚችሉ እውነተኛ በሆነና አሳማኝ በነበረ መልኩ ሲገልፅላቸው አመሸ።

በዚህ ዕለት አስተሳሰባቸውን ሙሉ በመሉ መለወጥ መቻሉንም አረጋገጠ።

በቀጣዩ ቀን ረፋድ ላይ ድጋሜ ተሰባሰቡ። ሙሉ የሆነ ቤተሰባዊ መተሳሰብንም መለዋወጥ ቻሉ። የቤቱ በረንዳ ላይ ተሰባስበው ከተቀመጡበት ስፍራ የበርሔ ንግግር ጮልቶ መሰማት ጀመረ። "ወድሞቼ አገሬን ስበድል ቆይቻለሁ። ይቅርታን ማግኘት ከቻልኩ ልክስ ቃል እገባለሁ።" አለ በተሰበረ እውነተኛ መንፈስ።

ጆንስ ዓይኖቹ በእምባ ተሞሉ። "ሁላችሁንም እወዳችዋለሁ። እኛ ጥቁር ህዝቦች እኩል የሆነ የስቃይ ሸክም የተጫነብን ወንድማማቾች ነን።" አለ ተነስቶ ወደ በርሔ እየተራመደ።
"አዎ..... ሲሆን የነበረው ሁሉ የተሳሳተ እንደሆነ አምኛለሁ። ለእውነተኛው የኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን የአፍሪካ አንድ መሆን ትግል ላይ ለመሳተፍ ሙሉ ህይወት ጊዜና እውቀቴን ሁሉ እሰጣለሁ።" አለ ሂርጳ ተነስቶ በመራመድ ወደ በርሔና ጆንስ እየተጠጋ።

"በፊትም ቢሆን እንድንገነጠልና መገንጠል ጥቅም እንዳለው የሰበኩን ነጮች ነበሩ..... በየዋህነት አምነናቸው ነበር።እውነት አሸናፊ ነውና የነሱን አመጣጥ እውነት ፈረካክሳ ጣለችው። ዛሬ በስራዬ ተፀፅቻለሁ።" አለ ሻለቃው።
"ሁላችንም ወደ እሳት ልናንደረድረው የነበረው ህዝብ የዋህነትና ፀሎት ነው ከታላቁ ጥፋት ያዳነን።" አለ ሂርጳ።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ጆንስ ፈገግ አለና “ኢትዮጵያ ቅዱስ ምድር ነች፡፡ መፅሀፍ ቅዱስም “ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚያብሔር ትዘረጋለች” በማለት ገልያታል፡፡ ከሚወነጨፉባት እልፍ ጥፋት የምትድነው ለሀይማኖቱና ለአገሩ ለወገኑ ፍቅር ያለው የተቀደሰ ህዝብ የተገኘባት በመሆኗ ነው፡፡” አለ፡፡

የሁሉም ዓይኖች ወደ አቡበከር ዞሩ “ገንዘብ ለማግኘት ስል ብቻ ነበር ያደረኩት፡፡ እነዚህ ሁሉ ጉዳዮችና ሚስጥሮች ከጀርባ መኖራቸው ፈፅሞ አላስተዋልኩም፡፡ ደግሜ በዚህ መሰል ተግባር ላይ ላለመሰማራት ቃል እገባለሁ፡፡ ለወንድሞቼም የሶማሊያን ችግር ምን እንደሆነ መንገር የሚያስችለኝ ጥሩ እውቀት አግኝቻለሁ፡፡ ማን ያውቃል ለሶማሊያ ሰላም መምጣት መንስኤ እኔ ልሆን እችላለሁ፡፡ የጦርነትን ጥቅምና ትርፍ ለህዝቡ እሰብካለሁ፡፡ ኢትዮጵያና ሶማሊያንም እንደ ጥንቱ ተዋህደው መኖር እንዲችሉ እተጋለሁ፡፡” አለ፡፡

“ያ በአማራው ክልል ላይ ሊንቀሳቀስ የተስማማው ጀነራል በዚህ ቦታ ተገኝቶ በነበር....” አለ ጆንስ ጉጉት ባጀበው ስሜት፡፡
“እኔንጃ.....” አለች ሰናይት፡፡ “.....በእናንተ መቅናቴን ብቻ ነው የማውቀው፡፡ እንጂ የሀገር ፍቅር..... የእናት ፍቅር.... ለኔ ምን ዓይነት እንደሆኑ አላውቃቸውም” አለች በተዘበራረቀ ስሜት ውስጥ ያሳለፈችውን የልጅነትና የወጣትነት ትርጉም የለሽ ህይወቷን እያሰበች፡፡
“ፍቅራችንንስ ወደሽዋል?” ጆንስ ግራ ተጋብቶ ጠየቃት፡፡
“መግለፅ ከሚሳነኝ በላይ!..... ከልጅነት ጀምሮ እንደ እናንተ ዓይነት ፍቅር ማግኘት ብችል ኖሮ.....” እምባዋ በጉንጮቿ ላይ ተሸኳለሉ፡፡ ጆንስ አብሯት አነባ፡፡

አብነትን ጨምሮ ሰባቱም ሰዎች ለደቂቃ ተቃቀፉ፡፡ እውነተኛ በሆነ ጥልቅ ስሜት አንድነታቸውን በፍቅር አፀኑ፡፡

ሰናይት ስላለፈችበት የህይወት ታሪኳ ዘረዘረላቸው፡፡ ይህን ስታደርግ በህይወቷ ለመጀመሪያ ጊዜዋ ነበር፡፡ ለምን በዚህ ተግባር ላይ ልትሳተፍ እንደቻለችም ሁሉም ተረዱላት፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

በዕለቱ ታላቅ ግብዣ እንዲደረግ ተወሰነ፡፡ አብነትና ኢዮብ በመኪና በመሄድ ሶስት የሰላም ተምሳሌት የሆኑ ነጫጭ በጐችን በመግዛት ከሚገፍላቸው ወጣት ጋር ይዘው ተመለሱ፡፡ በጐቹ ታርደው ካበቁ በኋላ እዛው ደጅ በብረት ምጣድ ላይ በባህላዊ መልኩ እንዲጠበሱ ተስማሙ፡፡

ሁሉም ሰዎች በስራው ላይ ተሳታፊዎች ነበሩ፡፡ ግማሹ ስጋውን ይበልታል፡፡ ግማሹ የሚጠበስበትን ቦታና ማገዶ ሲያዘጋጅ ቀሪዎቹ አስፈላጊውን ቁሳቁስ ሲያቀብሉ ጆንስ በቁምጣና በሰደርያ ብቻ ሆኖ ሁሉም ጋር እየገባ ሲያግዛቸው ቆየ፡፡ በነገሩ አግራሞት የያዛቸው አንዷ ሴትና አንድ ወንድ ግን በረንዳው የነበሩት ወንበሮች ላይ ተቀምጠው ዊስኪ በበረዶ እየጠጡ ያዩዋቸዋል፡፡ በመካከሉም ፎቶ ያነሷቸዋል፡፡

ጆንስ ሂርጳን፣ ሻለቃውን፣ ከማልንና በርሔን ጠርቶ “ወደየቤተሰቦቻችሁ ስልክ በመደወል ሰላም መሆናችሁን መንገር ተፈቅዶላችኋል፡፡” አላቸው፡፡

ከሰናይት በስተቀር ሁሉም ስልክ ወደሚያገኙበት ሳሎን መራመድ ጀመሩ፡፡ ሰናይት ግን ማንም የላትም ነበርና እነሱ ከየ ቤተሰቦቻቸው ጋር ሲያወሩ በተመስጦ አየቻቸው፡፡ ጆንስ ትከሻዋን መታ አድርጐ አባነናትና “አይዞሽ አትዘኝ” አላት፡፡

ጥብሱ በልዩ ሁኔታ ተዘጋጀ፡፡ አራጁን ጨምሮ ሁሉም በኢትዮጵያ ባህል መሰረት በአንድ ሰፊ ገበታ ዙሪያ ተቀመጡ፡፡ ኢዮብ ድንገት አጨብጭቦ የሁሉንም ትኩረት ሰበሰበና “እኔ በአማራነቴ የጠፋውን ጀነራል ቦታ እንደተካሁ ተደርጐ ይታሰብልኝ” አለ፡፡

ሁሉም በእኩል ስሜት አጨበጨቡለት፡፡ ክርስቲያኖች “በስመ-አብ.....” እስላሞቹም “ቢስሚላሂ.....” ብለው አንዱን ማዕድ እንደየ ሀይማኖታቸው ባረኩት፡፡

“አብነት ያለፈ ጊዜ ያልከኝን ታስታውሰዋለህ?” ጆንስ ጠየቀው፡፡

“ምኑን?” እየጐረሰ ጠየቀው፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“ኢትዮጵያ የሁለቱን ሀይማኖት ህዝቦች በወዳጅነት በማኖር የሚስተካከላት የለም ያልከኝን”
“አዎ..... ይኸው” ወደ ማዕዱ እያሳየ፡፡ ቀጠለ “.....አንድን ማዕድ አብሮ ባርኮ ከመብላት የበለጠ ምን ምስክር ያስፈልጋል!?” አለ፡፡
“አዎ.....የሚያኮራ ትልቅ ማንነታችን አንዱ መገለጫ ነው” አለ ጆንስ በደስታ ሲቃ፡፡

በፍቅር እየተሳሳቁ ተመግበው ጨረሱ፡፡ ምሽቱንም እየጠጡና እየተዝናኑ በደስታ አሳለፉት፡፡
በቀጣዩ ዕለት አረፋፍደው ሲነሱ ሁሉም ውስጥ አንድ የበቀል ስሜት እየተንቀለቀለ ነበር፡፡
ከቁርስ በኋላ ሁሉም በሳሎኑ ተሰባሰቡ፡፡ ሁሉም በሀሳብ የተግባቡ መስለዋል፡፡

ከጥቂት ዝምታ በኋላ “ የሉሢስ ወኪሎች የተባለው ተቋም አስፈላጊውን ቅጣት መቀበል ይገባዋል.....” አለ በርሔ፡፡
“እኔም እቦታው ሔጄ የታዘዝኩትን ለመፈፀም ፈቃደኛ ነኝ” አለ ሂርጳ፡፡

ሌሎቹ ከመናገራቸው በፊት ጆንስ ጣልቃ ገባና “ሁሉንም ለኛ ተውት.....” መናገር የፈለገውን አቋረጠና ጥቂት በዝምታ ቆይቶ ወደ ሌላ ንግግር ተዘዋወረ፡፡ “አሁን ከእናንተ የምንፈልገው ነገር ህዝባችሁን ስላወቃችሁት እውነታ ሁሉ እንድታሳውቁልን ብቻ ነው፡፡ ህዝብ ማመር አለበት፡፡ ከአንድነት ቀጥሎ የአንድ አገር ትልቁ ሀብት የተማረ ሀብረተሰብ ነው፡፡ ትምህርት የሁሉም ነገር አገልጋይ መሳሪያ ነው፡፡ ጨለማን ወደ ብርሃን ይለውጣል፡፡ ከሰሃራ በረሃ ውሃን ማውጣት ያስችላል፡፡ በስሜትና ደቡብ ዋልታዎች ጫፍ መኖር የሚያስችልን እውቀት ይሰጣል፡፡ ነገና ከነገ ወዲያ በፀሀይና በኘሉቶ ላይ የሚያስፈነጨንን ሚስጥር ሊያሳውቀን ይችላል፡፡ መማር ሁሉም ነገር ነው፡፡ ከትምህርት የሚገኘው ጥቅም ልክ እንደ ዘልዓለማዊነት የማይነጥፍ ነው፡፡ እስከ እዚህ ድረስ ተብሎ በገደብ የሚቀመጥ አይደለም፡፡.....

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“.....ለህዝቡ ሁልጊዜ መሳሪያ መማዘዙ መፍትሔ እንደሌለው እንድታስረዱት ነው የምንጠይቀው፡፡ ህዝብ የአውሬ መሪዎች የዓላማ ማስፈፀሚያ እቃነቱ ማብቃት እንዲኖርበት እንድታስረዱት ነው የምንፈልገው፡፡ ህዝባችሁ በመንግስት ሲበደልና በሚካሄድባችሁ የአገዛዝ ስርዓት ሲማረር ካለ ጦር መሳሪያ ካለ ደም መፋሰስ መንግስትን በሰላም መዋጋትና ድል ማድረግ እንደሚችሉ አሳውቁዋቸው፡፡ ወይም በፍርሃት ተውጠው ከመጣባቸው የጥፋት ቀውስ ለመሸሽ ወደ ዋሻ መሰደድ እንደሌለባቸው ይወቁት...

...የመጣው አደጋ ፍፃሜው ላይ ከመድረሱ በፊት በመንግስታቸው ላይ ግፊት በማድረግ፤ አልገፋ ቢል እንኳ የተሻለ ሰላማዊ አስተሳሰብንና አንድነትን አንግበው፤ ህዝባዊነትን አዳብረው ከተንቀሳቀሱ ገፍተው መጣለ እንደሚችሉ አሳውቁዋቸው..... እናንተም ለነዛ ትግሎች መሪ ሁኑ የአፍሪካ ልጅ የሆኑት ማርቲን ሉተር፣ ኔልሰን ማንዴላን የህንዱን ጋንዲን....አርአያ ተከተሉ፡፡ ካለ መሳሪያና ጦርነት መብትን ማስከበር ማሸነፍም እንደሚቻል ተረዱት... እወቁት....፡፡ በዚህ ዘመን ላይ እኮ ከመሳሪያ የበለጠ ሀይል ያለው ህዝብ ጋር ነው፡፡ ተመልከቱ የሰለጠኑት አገሮችን አካሄድ..... አስር ቀን ባልሞላ አገር አቀፍ የስራ ማቆም አድማ በመምታት ብቻ እኔ ነኝ ያለ አምባገነን መንግስትን ከስልጣን ማውረድ እንደሚቻል በዓለማችን ታሪክ ተይቷል፡፡ ” አላቸው በየተራ እያያቸው፡፡ ገፅታው ላይ የትኩስ አብዮተኛ ሰው እንጂ የተሰላቸ የትግል አርበኛ አይመስልም ነበር፡፡

ቀጠለ “....አገራዊ ህጐቻችሁን አሻሽሉዋቸው፡፡ ለሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ምንም ፋይዳ የሌለው ኋላ ቀር የሆነውን “የራስን መብት በራስ መወሰን እስከመገንጠል” የሚሉትን ነፃነት መሳይ ግን ከፋፋይ ደንቦቻችሁን ፋቁዋቸው፡፡ በነሱ ቦታም “የራስን መብት አብሮ መወሰን እስከ መዋሀድ” በሚሉት ለውጡዋቸው፡፡.....

“.....በዚህ ዘመን ለተበላሸ አገዛዝ ሽሽት አገርን ቆርጠ መጣል አይደለም መፍትሔው፡፡ አገር ካንሰር የያዘው እግር አይደለም፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

መሪዎቻችሁ ካንሰር መሳይ በሽታ እናሲዘው ቢሉ እንኳ አገርና ህዝብ ካንሰር ሊይዘው አይችልም፡፡ ምናልባት ሊድን በማይችል ሁኔታ በዚህ በሽታ የተያዘ እግር ብቻ ነው በዚህ ዘመን ይቆረጥ ቢባለ ዓለም አቀፉ እሳቤ የሚደግፈው፡፡.... ኢትዮጵያዊ ነን ብላችሁ ታምናላችሁ!?..." በየተራ እያያቸው ጠየቀ

ቀጠለ " ብትሆኑ ባትሆኑ ማን ስለእናንተ ደንታ ይሰጠዋል!?..... ማንም! በዚህ ግዜ ላይ እኮ የኢትዮጵያ ህዝብ እረኛ እንደሌለው መንጋ ሆኗል፡፡ ማንም የሚጠብቀው፤ ማንም ሀላፊነት ወስዶ የሚንከባከበው አካል የለም፡፡ አንተው እራስህ ነህ ፤ አልቺው እራስሽ ነሽ በዚህ እብድ ዘመን ላይ የራስና የአገር ጠባቂ መሆን ያለባቹ! የአንድነታቹ ጠባቂ መሆን ያለባቹ! የኢትዮጵያዊነታችሁን ክብር እና እሴት የመጠበቅ ሀላፊነት ያለባቹ፡፡ መሪዎቻቹ እንደሆን ከስግብግብነታቸው ብዛት የተነሳ እንኳን እናንተን እና አገሪቷን ኢየሱስ ተመልሶ ወደ ምድር ቢመጣ ለገንዘብና ለሆዳቸው ሲሉ ድጋሜ አሳልፈው ከመሸጥ ወደ ኋላ የማይሉ ይሁዳዎች ናቸው፡፡ አትሞኙ.....

".....እያንዳንዱ ዘመንም የየራሱን እሳቤ እምነቶችና ትውልዶችን ያፈራል፡፡ እያንዳንዱም ሰው ሊገመገም ከተፈለገም በራሱ ዘመን መነፅር ውስጥ ሊታይ ይገባዋል እንጂ መቶና ሁለት መቶ ዓመት በፊት የተከወኑ ድርጊቶችን፣ ስርዓቶችንና ሰዎችን ከዛሬው ሁኔታ ጋር አይቶ ለማመዛዘን መሞከሩ በተለይ ጥንቃቄ ከጐደለው ወደ ማቃረኑና ማቃቃሩ ከማንደርደር በስተቀር ዋጋ እንደሌለው እወቁት.....

".... ትላንት በተሳሳተው መንገድ ተጉዛቹ ስለ መገንጠል ሰብካቹ ወዳሳሳታችሁት ህዝብ ተመለሱና አንግባችሁት የነበረው ዓላማ ልክ እንዳልነበር ንገሯቸው፡፡ በእርግጥ ይህን ስታደርጉ ሁኔታዎች ቀላል እንደማይሆኑላቹም እወቁት፡፡ ወደ ተሳሳተው የቀድሞ አላማቹ ተስበው በገቡት በራሳቹ ዓባሎች ጓደኞች ዘመዶችና ቤተሰቦቻቹ ጭምር ከፍተኛ ተቃውሞ ሊጠብቃቹ ይችላል፡፡ ምክንያቱም የተበላሸን ነገር ማስተካከል እንደማበላሸት ቀላል አይደለምና፡፡ ባስ ካለም መገለል መደብደብ መታሰር መሰደድና መሞት ጭምር ሊጠብቃቹ ይችላል፡፡ ይሄ ዓለምን የሚያተራምስ የፖለቲካ የስልጣንና የጥቅም ጉዳይ በመሆኑ ብዙ አደጋ ሊገጥማቹ ይችላል.....

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

"..... የምትከፍሉት ዋጋ ግን በጠቅላላ በአገራቹ በህዝባቹ በአንድነታቹና በታሪካችሁ ውስጥ ህያው እንዳደረጋቹ ይኖራል። አይደም የናንተ በመከራና በቋፍ ላይ ያለች አገር ይቅርና በሰላም እና በዲሞክራሲ ውስጥ ነው የምንኖረው ብለው የሚደሰኩሩት ህያላኖቹ ምእራባውያን አገሮች ጭምር ህልውናና ሉዓላዊነታቸው የሚፀናው ዛሬም ድርስ እየተከበረና እየኖረ ያለው በንፅህ ዜጎቻቸው ውድ የህይወት መስዋእትነት ክፍያ ብቻ ነው። እናንተም ለመላው አፍሪካና ለጥቁር ህዝብ ስቃይ ማብቃት የነፃነት ታጋይ እና ምስራች ተናጋሪ ሁኑ እንጂ የአስገንጣዮች ታጋይነታቹ ያብቃ። የናንተ የትግል አቅጣጫ መስተካከል ብቻ ነው የህዝብን እምባ የሚያቆመው! ለአገርም አንድነት ለምትመኙት ሰላም እና ብልፅግናም የሚበጀው" ቀጠለ ሁሉንም እያየ "... እኛ የውጭውን ሀይል ካስቆምንላቹ እናንተ ደግሞ የአገራቹን ችግር በራሳቹ ትግል ፍቱት። ሊበታትኗቹ የሚታገሉትን መሪዎቻቹን ከመንበሩ ነቅላቹ በማንሳት ወደ መቃብር ሸኟቸው። ፋና ሆነቹ በመቅደም የዚህን ህዝብ ተስፋ አክሙለት ልቦናውን ፈውሱለት። ከብርሀን መንገዱ አታሰናክሉት። አርሶ ይጨድ ነግዶ ያትርፍ ተምሮ ይወቅ ሰው በአገሩ ላይ እንደፍላጎቱ ሆኖ ካልበለፀገ ምን ተስፋ ይኖረዋል? ከስልሳና ሰባ ለማታልፍ የሰው ልጅ እድሜ በራስ ወዳድነት ተባልታቹ ህዝብን አታባሉት። ህፃናት ተወልደው ባገራቸው ላይ አድገው ቤተሰብ መስርተው አክብረው ተከብረው የሚያረጁባት የሰላም ግዛት ፍጠሩ። ጦርነትና ስድት ይብቃ እኛም ወደ እናት አፍሪካችን እንመለስ። " አላቸው ጠንከር ባለ ቅላፄ።

"እሺ..... የሉዊስ ተቋም ጉዳይ ለናንተ ከተተወ በአማራው ክልል ላይ ሊንቀሳቀስ ሰላሳ ሚልዮን ዶላር ወስዶ በመስራት ላይ ያለው ጄነራል ጉዳይ ምን ይሁን?" አለ አብነት።።
"እኛ ልንይዘው ካልቻልን የመንግስት ወታደር ሊያስከዳ እንቅስቃሴ ላይ መሆኑ ለምን አይጠቆምበትም?" ኢዮብ ሃሳብ አቀረበ።።

"ይህን እኔ በቀላሉ ልፈፅመው እችላለሁ" አለ ሻለቃ ደርበው።።ቀጠለ "..... ከነ ተባባሪዎቹ ላሲዘው እችላለሁ"
"አዎ..... ከሚከሰተው ጥፋትና እልቂት እሱ ቢያዝና ህዝብ ቢተርፍ ነው የሚቀለው" አለ ኢዮብ።።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ጆንስ ጄነራሉ ተይዞ በመንግስት እርምጃ ከሚወሰድበት ሊያድነው ቢችል ነበር የሚመረጠው፡፡ ሆኖም ከጊዜው እጥረትና አደገኛነት አንፃር የተሻለ ሀሳብ መፍጠር ስላልቻለ “ቀጥልበት” አለው ሻለቃውን አያይዞም “የጠር መሳሪያውን የጫኑት መርከቦች ጉዳይ ምን ላይ እንደደረሰ ለማወቅ አልተቻለም፡፡”
“የሚረከባቸው ሰው ካላገኙ እንደጫኑ ይመለሳሉ አይደለም እንዴ?” ጠየቀ አብነት፡፡
“አይመለሱም፡፡”
“እና ምንድነው የሚያደርጉት?” ደግሞ ጠየቀ፡፡
“ከፈረንሳይ ከተላከልኝ መልዕክት ውስጥ.....ተረካቢዎቹ መርከቦቹ ወደብ በደረሱ በአምስት ቀናት ውስጥ ቀርበው ካልተረከቡ የጦር መሳሪያዎቹን ለፈለጉት ሌሎች አገሮች የመሸጥና የመመለስ መብት እንዳላቸው ተዋውለዋል መርከበኞቹ፡፡” አለ ጆንስ፡፡
“ከተለመደው አቅጣጫ ያፈነገጠ ስምምነት ይመስላል” አለ ኢዮብ፡፡

“አዎ..... የመሳሪያዎቹ ሽያጭም ሆነ ዝውውሩ ዓለም አቀፍ ህጐችን በተፃረረ መልኩ ስለተካሄደ አዘዋዋሪዎቹ አካሎች ከተያዙ ይቀጣሉ፡፡ ስለዚህም ይህን ለመከላከል ብለው ቶሎ እንዲረከቡዋቸው ማስገደድ ፈልገው ነው፡፡” አለ ጆንስ፡፡
“ቅጣቱን እንኳ ተወው.....” አለ አብነት ቀጠለ “.....ህጉን አውጪዎቹም መሳሪያውን አምራችና ሻጮቹም አዘዋዋሪዎቹም ራሳቸው ነጮች ስለሆኑ መደጋገፋቸው አይቀሬ ነው፡፡ ይልቅ ባለመርከቦቹ ለማን ይሸጡታል እንጂ.....”አለ፡፡

“ምን ችግር አለው፡፡ በአፍሪካ ግዛት ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በጦርነት እየታመሱ ናቸው፡፡ ሶማሊያን፣ አንጐላ፣ ሩዋንዳ፣ ላይቤሪያ፣ ዛምቢያ፣ አልጄሪያ፣ ሴራሊዮን፣ ኮትዲቯዋር፣ ጊኒ፣ ሴኔጋል፣ ኮንጐ የተጋነነ አይሆንም እንጂ ራሷ ኢትዮጵያ፣ ሱዳን፣ ኤርትራ፣..... እነዚህ ሁሉ አገሮች ህዝባቸውን በጦር መሳሪያ እየማገዱት ነው፡፡ እናም ወደ አንዱ ወደብ ጠጋ ብለው ሰከንድ ባልሞላ ቅፅበት እንደ ብስኩት ቸብችበውት ይመለሳሉ፡፡” አለ ጆንስ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ከዛም ከተቀመጠበት ተነስቶ ተንጐራደደና ጥርሱን ነክሶ "በፍፁም የአፍሪካ ወደብ ላይ መራገፍ የለባቸውም!" አለ በሀይለ ቃል፡፡
ቀጠለ "....በጥይት በቂ ተገዳድለናል፡፡ ወይም ከበቂ በላይ!" ብሎ ይህንን ተግባር እንዲቆጣጠር ሀላፊነት ስለወሰደው ስለ ቡድን ሶስት ማሰብ ጀመረ፡፡
"እኛ ጥቂሮች ገና ዓለምን እንገዛታለን፡፡ እንደተጫወቱብን እንጫወትባቸዋለን" አለ ኢዮብ፡፡
ድንገት የሁሉም ዓይኖች በሱ ላይ አረፉ፡፡ የማይገባ ነገር መፈፀሙ ተሰማው፡፡

ጆንስ ጠጋ ብሎ በወዳጅነት አቀፈውና "በፍፁም አንገዛም፡፡....." ወደ ሌሎቹ እያየ ቀጠለ ".... ጥቁርነት እኩልነት ነው፡፡ ጥቁርነት ወንድማማችነትና እንድነት ማለት ነው፡፡ አንዱ እየበላ ሌላው ጦም አያድርም፡፡ አንዱ እያለቀሰ ሌላው አይስቅም፡፡ ሁሉም እኩል ነው፡፡ ጥቁርነት ማለት ፍቅር ነው፡፡ እናም ፍቅር.... ያጡትን.... የነበራቸውን ግን የጠፋባቸውን ፍቅር እናስተምራቸዋለን፡፡ በፍቅር እናጠምቃቸዋለን፡፡ እናም ሲፀዱ፤ ውስጣቸው፤ ህሊናቸውና ልቦናቸው እንደ ቆዳቸው ሲፀዳ ወንድም እናደርጋዋቸለን፡፡ ይህ ነው የኛ እምነትና ፍላጐት፡፡" አለው፡፡

  

የማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ምዕራፍ 52

ለወለጋ ክፍለ አገር በማዕከላዊነት የምታገለግለው ነቀምት ከተማ ውስጥ በተቋቋመው ጊዜያዊ የወታደር ቀጣና ላይ የታነፀው የመገናኛ ቢሮ ድንገተኛ ትዕዛዝን አዲስ አበባ ከሚገኘው ዋና መስራቤት ተቀበለ፡፡

የቀጣናው ዋና ኃላፊ የነበረው የ “ኦ.ህ.ዴ.ድ” ጄነራል ቦታውን ለ “ብ.አ.ዴ.ን” ጄነራል በልዋጭ ለቆ ወደ አማራ ክልል እንደሚዘዋወር ከተገለፀለት ሳምንታትን አስቆጥሮ ነበር፡፡

ተተኪውን ጄነራል ምትኩ ሲጠብቅ ቆይቶ ዛሬ እንደሚደርስ በተነገረው መሰረት እዛው የቀጣናው ጊቢ ሌላ ተለዋጭ መልዕክት የደረሰው፡፡

የመልዕክቱ ዋና ሀረግ “ጄነራል ምትኩ ወደ አንተ ለመምጣት በጉዞ ላይ ይገኛል፡፡ እንደደረሰ ታስሮ በከፍተኛ ጥበቃ ወደ አዲስ አበባ በመጣበት ሂሊኮፕተር መልሰህ እንድትልከው ! ” የሚለው ሚስጥራዊ ትዕዛዝ አስደንግጦታል፡፡

“ምክንያቱ ምንድነው?” ብሎ ሲጠይቅ

“ማንም ዝርዝር ጉዳዩን አያውቅም፡፡ በዕዝ ሰንሰለት የወረደ ትዕዛዝ ስለሆነ መፈፀም ብቻ ነው ያለበት”

“ታዛዥ ነኝ” ብሎ መነጋገሪያውን ቦታው በመመለስ ሂሊኮፕተሩ በሚያርፍበት ቦታ ላይ ታጣቂ ወታደሮችን በጥንቃቄ አዘጋጅቶ መጠበቅ ጀመረ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ትዕዛዙ ለወታደሮቹም አስደንጋጭ ነበር፡፡ ቢሆንም ግን ጄነራሉን ለመማረክ የጠመንጃቸውን አፈሙዝ ለሂልኮፕተሩ ማረፊያነት ወደ ተዘጋጀው ሜዳማ ስፍራው ወድረው መድረሱን መጠባበቅ ያዙ፡፡

«««««««« »»»»»»»

ጄነራል ምትኩ በሂሊኮፕተሯ ውስጥ ከአብራሪው አጠገብ ነበር የተቀመጠው፡፡ በውስጡ ያሉት ሁለቱ ብቻ ናቸው፡፡

ጄነራሉ ለመውሰድ ያሰበውን ውሳኔ ትክክለኛነት ከልብ አምኖበታል፡፡ ሆኖም ግን ቁርጥ ብሎ ያሰባት ሰዓት እስክትመጣ ድረስ መንፈሱን ሙሉ በሙሉ ማረጋጋ አልቻለም ነበር፡፡ የረዳት አብራሪው ወንበር ላይ ተቀምጦ ወደ ምእራብ አቅጣጫ በተራራዎች አናት ላይ የምትጓዘው ሂሊኮፕተር ውስጥ ሆኖ ወደ ታች የመሬቱን ዙሪያ ገባ እየቃኘ ቆየና ወደ አብራሪው እይታውን አዞረ፡፡ አብራሪው ተከስተ ገብረአብ የሚባል ገና ለጋ ምልምል ነው፡፡

በተከስተ በኩል ባለው መስታውት ላይ «ጀግናው የመከላከያ ሰራዊት» የሚል ፅሁፍ የሰፈረበት እስቲከር አነበበና ፈገግ አለ፡፡ ተከስተ የጄነራሉን ፈገግታ በስርቆት ለማየት ዞር ሲል አይን ለአይን ተጋጠሙ፡፡

“ምንድነው ጀግና ማለት? ማነው ጀግናስ?” አለ ምትኩ በሚሳለቅ ቅላፄ፡፡

“የመከላከያ ሰራዊታችን ነዋ ጄነራል”

ወድያው ምትኩ ደርግ ስልጣን ከያዘበት ወቅት ጀምሮ እስካሁኑ ድረስ በአገሪቷ የውትድርና ህይወት ውስጥ ያለፉትን ለቁጥር አታካች የነበሩ ወፈ-ሰማይ ሚች ወጣቶች የሙት መንፈስ በአስፈሪ ሁኔታ ታዩት፡፡ «ጀግና» ከሚለው ሽንጋይ ቃል በስተጀርባ በወጉ ተሰልፈው ወደ ሞት እንዲያመሩ የተደረጉት ገበሬዎች እና የገበሬው ልጆች ታዩት፡፡

ደርግ “ጀግናው ህዝባዊ ሰራዊት፤ ጀግናው የቀዩ ጦር ጥንስስ፤ ጀግናው የአየር ሀይላችን፤ ጀግናው የናደው እዝ፤ ጀግናው ሶስተኛ ብርጌድ..... ጀግናው... ጀግናው... ጀግናው...” እያለ አሞካሽቶ ለአስራ ሰባት ዓመት ህዝብን ባስጨፈጨፈ ማግስት ወደ ስልጣን የመጣው የወያኔ መንግስት ይህንኑ የማደናገሪያ ቃል እየለጠፈ “ጀግናው የመከላከያ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

ሰራዊታችን፤ ጀግናው የአግአዚ ክፍለ ጦር፤ ጀግናው ልዩ ሀይላችን፤ ጀግናው... ጀግናው...” እያለ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ እና ፕሬዝደን ኢሳያስ አፈወርቂ ጉንጭ ለጉንጭ ተሳስመው እንደ አንገት ሀብል ለተሰጣጡት መሬት ስንት ህዝብ ህይወቱን በጦርነት እንዳጣ ታሰበው::

ወድያውም ህሊናው ለሱ የሚጠይቀውን ጥያቄ ለአብራሪው መደርደር ጀመረ “ማነው ጀግና?”

“የመከላከያ ሰራዊታችን አልኩኮ ጄነራል” ቀጠለ በወታደራዊ የአክብሮት ቅላፄ ”በየግምባሩ የተሰዉና ሊሰዉ በጀግንነት ቆመው ያሉት ሁሉ...” ብሎ ከበረራ ሰዓት ውጭ ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. የሚያሳርሰው የፖለቲካ ስብከት እያመነዠከ መትፋት ሊቀጥል ሲል ጀነራሉ በቁጣ “የተሰዉ አትበሉኝ! የደርግ ሰራዊትን ጨምሮ እኛ ሁላችንም የፓርቲ ጠባቂዎች እንጂ ጀግኖችም የአገር ወታደሮችም አልነበርንም:: አይደለንምም:: ” አለው በቁጣ

አብራሪው የሚሰማውን ነገር በፍፁም ማመን እየተሳነው “አ..ልገ..ባኝ..ም» አለ

ቀጠለ ምትኩ “በደርግ ወያኔም ሆነ በኢትዮ ኤርትራ ጦርነቶች ከሁለቱም ጎራ የተፈጀው ሰራዊት ለእርድ የተነዳ በግ ነበር!”
“ጄነራል እኛኮ በባህላችን ጥፋት የሰራ ሰው ቢሆን እንኳ ከሞተ አንወቅሰውም:: አበሻ ሙታንን ያከብራል እንጂ ሙት ወቃሽ አይደልም” አለ ተከስተ እየተቅለሰለሰ:: በልቡ ግን ይህንን የጀነራሉን ንግግር ግምገማ ላይ አቅርቦ ጠንካራ እርምጃ ሊያስወስድበት እየቋመጠ::

“ዛሬ እንውቀሳቸዋ እኔና አንተ ሆነን ያንን አሮጌና ያረጀ ተረትና አባባል እንጣልና እንውቀሳቸዋ:: እንስደባቸዋ:: አዎ ደደብ ሟቾች ነበሩ እንጂ ለአገር የተሰዉ ጀግና ወታደሮች አልነበሩም:: ለሞታቸው ደሀ አገራቸውን ዋጋ ያስከፈሉ ብኩኖች ባክነው አገራቸውን ያባከኑ ሟቾች ናቸው እንጂ... ከሰላሳ ዓመት በላይ ያስቆጠረ ጦርነት እና ከሶስት መቶ ሺህ ሰው በላይ ህይወቱን ያጣበት ውጤት አልባ የነበረ እልቂት ነው! መተራረድ ነው! ቁስለኛ ሆኖ የቀረውን አታስበው::”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

"ጀነራል እኔ ንግግሮት ምንም አልገባኝም ዛሬ"
"ጀግና በሚል ካባ ተሸፍነው ራሻ ባመረተችው ተራ ፈንጂና ቦምብ፤ ጥይትና ታንክ ሲቆራረጥ፤ ሲጠበስና ሲከስል የነበር፤ ራሻ ባመረተችው ሳንጃ ሲሞሸላለቅ፤ ሲተካተክና ሲፈታፈት ያለቀ ታሪክ አልባ ሆኖ የኖረና ያለቀ ሰራዊት ነው:: የጥንብ አንሳና የጅብ ቀለብ ሆኖ የትም ወድቆ የቀር ህዝብ ነው:: በሁለቱም ተቃራኒ ግንባር እንደ አገር አንድ ሆነው አንዋጋም በማለት ለክቡር ህይወታቸው መኖር ቢያምፁ ኖሮ እነሱም ባላለቁ እንዲሁም እነሱ ለመሪዎቻቸው የግል ፍላጎት ሲሉ ብቻ በገቡበት ጦርነት እና ለሞቱበት መሳሪያ አገር ከድህነት መቀነቷ ላይ እየፈታች ለመሞቻቸው ዋጋ ባልከፈለች ነበር:: መንግስታችን ራሱ ባወጣው መረጃ መሰረት በኢትዮ ኤርትራ ጦርነት ብቻ ሃያ አንስት ቢልዮን ብር ከዚች ድሀ አገር ተነጥቆ ወደ እሳት ተጥሏል:: ይህ እሳት የበላው ገንዘብ ምን ያህል ሆስፒታል ምን ያህል ኢንዱስትሪ ምን ያህን የልማት ተቋማትን መገንባት ባስቻለ ነበር:: የስንቱን ድሀ ገበሬ ኑሮ በለወጠ ነበር.....

"... አረብ አገር ተስፋ አልባ ሆና ለቀረችው የስንት እህታችን ህይወት በታደገ ነበር:: አምስት ብር በማታወጣ መርፌ እጦት ምክንያት ስንተ እናት ከነ ፅንሷ በየ ባላገሩ ጤና ጣቢያ ባልሞተች ነበር:: ይህን ሁሉ ሳያመዛዝን ለዛ ጦርነት ተነስቶ ራሱን ያሰለፈና የታጨደው ዜጋ ሁሉ ተወቃሽ ነው:: አካሉን አጉድሎ የአገር እና የቤተሰብ ጡረተኛ ሆኖ የቀረው ሁሉ ተወቃሽ ነው:: የሞተው አንዴ ሞቶ ቢያልፉም እንኳ አገር ግን በነሱ ሞት ምክንያት ዛሬም ድረስ ሞታቸው እየሞተች፤ እነሱን ከጠበሳቸው እሳት እየተጠበሰች፤ በአሳፋሪ ሁኔታ ለምና ከምታመጣው ብር ላይ የሙታንን እዳ እየከፈለች፤ ከድህነት ወደ ባሰ ድህነት፤ ከመከራ ወደ ባሰ መከራ እያመራች እዚህ ደርሳለች:: ወደፊትም ችላ ቀና ማለቷንም እንጃ..... ጦርነት ማለት በዛፍ የተሞላ መናፈሻ ውስጥ ገባ ብሎ ንፁህ አየር እየኮመኮሙ መፅሐፍ ማንበብ ይመስላቸዋል እንዴ? " አለ

"ሙታን ቢወቀሱ ታድያ ምን ጥቅም አለው? እኛም አንመለስ ወይም እነሱም አይመጡ" አለ ተከስተ
" አስተውል! ጥሞናህን በደንብ ሰብስበህ አስተውል.... ዛሬ ላይ ሆኜ ትላንት የታጨዱትን ሰዎች የምወቅሰው ሞራል ስለሌለኝ ወይም እነሱ መልስ መስጠት ስለማይችሉ አይደለም:: አይደሉም እነሱ የዛ ጦርነት ተሳታፊና ሰለባ ሆነው ዛሬ በህይወት ያሉት ሰዎች ራሳቸው ለምን በዛ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ጦርነት እንደተሳተፉ ቢጠየቁ አንዳቸውም ምክንያታዊ መልስ መስጠት አይቻላቸውም:: እመብርሀንን እምላለሁ! መልስ የላቸውም:: እነሱን በይፋ በዚህ መልኩ መውቀሴ ዛሬም ላይ ለትርጉም አልባ ዓላማና በልቶ ለማደር ሲሉ ብቻ ወታደር ሆነው ለመሞት ተሰልፈው ተራ እየጠበቁ ያሉትን አባነን ወደ ህይወት መስመር ለመመለስ ይቻለናልና ነው"

"የመከላከያ ሰራዊቱን ነውኮ እንደዛ እያሉ ያሉት ጀነራል በዛ ላይ እርሶም ተሳትፈዋልኮ"

" ሞኝ አትሁን እኔ ጀነራል ነኝ:: ሞት ከኔ መስመር በጣም የራቀ ነው:: ከዛ ውጪ ማንም የመስመር ወታደር እና የግምባር ጎላፊ ሁሉ ጦርነቱን በግምባር ላይ የተሳተፈ ሁሉ ሞኝ ነበር:: እናም ደግሞ ሌላም ልጨምርልህ ማንንም ሊሆን ይችናል..... ዛሬ አንተና ያንተ ቢጤዎች ገና ጥሬ ስጋ ስለሆናቹ አይገባቹ ይሆናል:: በፖለቲካ አሻጥር ምጣድ ላይ ስትጠበሱና ስትበስሉ ያኔ ይገባችኋል:: ጀግና በሚለው የሀሰት ካባ ተታለው ያሉትን ሁሉ ነው:: ከፈለክም ይኸው..." ብሎ ድምፁን ከፍ በማድረግ ንግሩን ቀጠለ

"... ጀግናው የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. ሰራዊት፤ ጀግናው የኦነግ ጦር፤ ጀግናው የአርበኞች ግንባር፤ ጀግናው የአጋዴን ነፃ አውጪ ፤ ጀግናው የምናምን ወታደሮች..... ወይም ጀግናው እገሌ እያለ ገና እራሱን አዲስ ለመመስረት የሚዘጋጀው ሁሉ ሊሆን ይችላል:: ጀግናው... ጀግናው... ጀግናው.... ሁሉም ጦርነትን እስከመረጠ ድረስ ለዚህች አገር መፍትሄ አምጭዎች ሳይሆኑ የህዝብ ደም እና የአገር መቆርቆዝ የማይገዳቸው የስልጣን ጥማት ያሰከራቸው መንፈሰ እውራን ናቸው::"

ተከስተ ከአንድ ከፍተኛ የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ የጦር ባለስልጣን በማይጠበቀው ንግግር ተገርሞ ሂሊኮፕተሯ መሬት የምታርፍበትን ቅፅበት ናፍቋል::

ቀጠለ ምትኩ "እንደው አካሄዳቸውን ይሁን ብለን ብንቀበለው እንኳ ለህዝብና ለደሀው ገበሬ ከሚደግሱት የሞት ድግስ ራሳቸው ቀድመው እየተሰዉ አላሳዩንም:: ኔልሰን ማንዴላ አፓርታይድን ሲታገል እኮ ቤቱን ፤ ሚስቱንና ልጆቹን ወደ ኋላ ትቶ « ለመሞት ራሴን አዘጋጅቻለሁ» እያለና የተናገረውን በተግባር እያሳየ ነው ታግሎ ያታገለው:: ሀያ ሰባት ዓመት ሰው የማይደርስበት በውቅያኖስ በተከበበ ዓለት ውስጥ ዓለት እያስፈለጡት ሲታሰር ስለ ትግሉና ስለ ተግባሩ ያሰረውን ስርዓት እና መንግስት «ይቅርታ» አልጠየቀም:: ይህ የሱ ጠንራካና ታማኝ የትግል ስብእና ነው የሞራል ስንቅ ሆኖ ህዝቡን እስከመጨረሻው በማታገል

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

የማይገረስስ ይመስል የነበረውን የነጮች የበላይነት እንዳያንሰራራ አድርጎ ጠራርጎ ወደ መቃብር የሸኛቸው:: የኛዎቹ ጋር ሲመጣ ትግልና ሞት የገበሬና የደሀ ልጅ ነው:: ስልጣንና ረጅም እድሜ ከሚያንደላቅቅ ሀብት ጋር የጮሌ ፖለቲከኛ ብቻ ነው::"

"ይህ ያሁኑ ንግግሮት እኮ እርሶንም ይመለከታል ጄነራል" አለ ተከስተ ቁጣውን ለመሸሸግ እየታገለ

"እኔን ከሌላው ሆዳምና አቃጣሪ ምን ይለየኛል!? "

"እሺ ደርጎችስ? "

"ሁሉም ያው ነው:: ምሁር እና ተማሪን ፈጅተው፤ የተረፈውን አሰድደው እና አሸፍተው ፤ የቀረውን አፍሰው አዝምተው አገሪቷን በመሀይማን ካጥለቀለቁና ራሳቸውንም በሚኞች ላይ ካደለቡ በኋላ «ጎድ» እየተባባሉ በመጠራራት ለአገሪቷ ጉድጓድ ሲምሱ ነው ኖረው ለፍፃሜ የበቁት:: "

"እሺ ታድያ ጀግና ማነው?"

"ጀግናማ በአገር ላይ በመጣ የውጭ ጠላት እንደ አገር አንድ ሆኖ ተነስቶና ተፋልሞ መስዋእት እና ሰማእት እየሆኑ አገራቸውን አስከብረው ያለፉት እነሱ ብቻ ናቸው::"

"ወደ ድሮ ታሪክ እንዳንመለስ..... " አለ ተከስተ እጅግ የሚቀፈው የድሮውን የኢትዮጵያ ታሪክ መስማት ነበረና:: ሆኖም አልቀረለትም ቀጠለ ምትኩ "ጣልያንን በባዶ እጅ ገጥመው ያዋረዱ፤ እንግሊዝን ካለ ድል ወደ መጣችበት የመለሱ፤ ቱርክን አባረው ቀይ ባህር ውስጥ የቀበሩ፤ ደርቡሽን የተፋለሙ፤ ግብፅን ደጋግመው ሸንፈትን ያለበሱ፤ በምስራቅ ሶማሊያን አሳደው አሸዋ ላይ የቀበሩ አዎ እነሱ ናቸው ታሪክ ሁሌም የሚያውቃቸው ሁሌም የሚያነሳቸው ጀግኖች:: ሌላው ሁሉ ታሪክ የማያውቀው እንደ ሙጃ የታጨደና ሊታጨድ ራሱን በፈቃደኝነት አሰልፎ የሚጠብቅ ብቻ ነው" አለ ምትኩ::

ተከስተ ድፍረቱን አሰባስቦ " ጄነራል ለንግግሬ ይቅርታ ያድርጉልኝና ዛሬ እንደ ጠላት ነው የሚያወሩት ሁሉ"

ምትኩ ትንሽ እንደ መተከዝ ብሎ ቆየና ውጭውን አሻግሮ በማየት የሚፈልገው ሰዓት መድረሱን አረጋገጠ::

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ከዛም "አዎ" ብሎ በመመለስ ሰላሳ ሚልዮን ዶላር የያዘውን ሻንጣ ወደ እግሩ ስር ጐትቶ ቆመበት።።

ከዛም ሽጉጡን በቅፅበት አውጥቶ አቀባበለውና "አቅጣጫህን ወደ ሱዳን ካርቱም አስተካክል!" አለው ለፓይለቱ።። ትዕዛዝ አዘል በሆነ ቃላት አፈሙዙን ወደ አንገቱ ስር ደግኖበት።።
"ምን.....ሱ....ሱዳን...ለ....?" አብራሪው በፍርሃት ተንተባተበ።።
"ቀጥል!..... ካለበዚያ አናትህን ፈርክሼው ራሴ አበረዋለሁ!"
"እሺ....." አለው መስመሩን እየለወጠ።።
ጄነራል ምትኩ በህሊናው 'ከነዛ መሀይሞች ነፃ ወጣሁ' አለ ለራሱ።። ሱዳን እንዳረፈ ወደ አንዱ ጥሩ አገር የፖለቲካ ጥገኝነት ጠይቆ በመሄድ ቀሪው ህይወቱን በዚህ ገንዘብ ተንደላቆ መኖር እንዳለበት እያሰበ በደስታ ተዋጠ።።

በሌላ በኩል ደግሞ ተወልዶ ያደገባት ይችን አገር መቼ ተመልሶ ሊያያት እንደሚችል ራሱን ጠየቀ።። መልሱ አጭር ነበር 'ይሄ ሌባ መንግስት ሲወድቅ' አለው ህሊናው።።

መልሶ ይህንን ገንዘብ ለማግኘት በሰናይት ላይ የተጠቀመባቸውን አንዳንድ ተራ ብልጠቶች ማሰብ ጀመረ።።

ጥቂት ቆየናም "ተከስተ ዛሬ እኔ እያደረኩ ያለሁትን ድርጊት ሁሉም ጄነራል ሊያደርገው የሚጓጓው እና የተሳካለትም እያደረገው ያለውን ነው።። ባለ አራት ኮከብ ጀነራሉ ሳይቀር የሚያደርገውን ነው ያደረኩት።። ይህን ስልህ ደግሞ ወታደሩን ሚመሩትን ብቻም ሳይሆን ፖለቲካውንና ሲቪል ተቋማቶችን በአጠቃላይ አገሪቷን የሚመሩት ከፍተኛ ድልብ ባለስልጣናትን ሁሉ..... ሁላችንም አንድ ነን።። ሁሉም የሀሰት ነው አገር፤ ህዝብ፤ ዲሞክራሲ፤ ነፃነት ፤ እኩልነት፤ ገለመሌ እያለ የሚደሰኩረው።። ማንም እኩል አይደለም።። ማንም ነፃ አይደለም።። ወደፊትም ማንምም አይሆንም።። ይሄ አፍሪካ ነው።። እኔ ጄነራል ብሆንም አንድ ተራ ኮነሬል ከትግራይ ስለሆነ ብቻ እኔን እና የኔ አይነቶቹን ለብሄር ኮታ መሚያነት ለታይታ የገባን ባለ ስልጣናትን እንደሚፈልገው ሲያዘ ታይቷል።። አንተም ነገ እኔን ተነስ ተኛ ስላለማለትህ ምን ሙያዊ ስነምግባር ወይም አገራዊ ዋስትና አለኝ!?

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

ሁሉም የግል ጥቅሙን አሳዳጅና የግል ጥቅሙን ፈላጊ ነው። ልክ እንደኔው። ይህ የምልህ እንዲገባህ ጠንቋይ ወይም ነብይ መሆን አያሻህም የገዢው ፓርቲ ባለስልጣናት በአገር ውስጥ እና ከአገር ውጭ ያካበቱትን ንብረት ማየቱ ብቻ በቂ ነው።" አለው

ተከስት መልስ አልሰጠም። ጭንቅላቱ ላይ ስለተደገነበት የተቀባበለ ሽጉጥ ብቻ ነበር በፍርሀት ተውጦ የሚያስበው። ቀጠለ ጀነራሉ "ይህን ሁሉ የምነግርህ ተመልሰህ እንድትነግራቸው ስለምፈልግ ነው። ያገራቸው ልጅ ስለሆንክ ያምኑሀል። ከአማራው ክፍል ብትሆን ይሰቅሉህ ይሆናል። ወይም ከኦሮሞው ክፍል ብትሆን ያስሩህ ይሆናል። አንተ ግን ከራሳቸው ስለሆንክ ምንም አያደርጉህም። እኔ የማውቅን እና የማምነውን አብዛኛው መኮንን እንደሚያምነበትም ንገራቸው። ለነገሩ ራሳቸውም ያውቁታል። "

በዚህ ጊዜ ኢትዮጵያንና ሱዳንን የሚያዋስነውን ጠረፍ ማለፍ ጀምረው ነበር።
"እንዲህ ነው ራስን ነፃ ማውጣት" ብሎ አጉተመተመ።



የማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ምዕራፍ 53

እነ ጆንስ ባረፉበት ጊቢ መጠነኛ የሆነ የዝምታ ድባብ ሰፍኖበታል። እርቁ በተካሔደ ማግስት ነበር ሻለቃው፤ በርሔ፤ አቡበከርና ሂርጳ በነፃነት የጊቢው በር የተከፈተላቸው። አራቱም ወደየሚኖሩበት ሲሄዱ ሰናይት ግን ዘመድ ወይም የሚጠብቃት ቤተሰብ የላትምና እዛው ቀረች።

አብነትም እርቁ በተፈፀመ ዕለት ምሽት ላይ ነበር የስዕል ስራውን በራሱ ክፍል ውስጥ የቀጠለው። አሁን ለስራዎቹ ከመነሻ የላቁ በርካታ ተጨባጭ ጭብጦችን ማግኘት ችሏል። ሀሊናው በበርካታ ጭብጦች ተወጥሯል። ቀለማት በብሩሾቹ ጫፍ ዋጋቸውን ማግኘት ጀምረዋል።

እነ ሂርጳ ወደየቤታቸው በሄዱ በሁለተኛው ቀን ማለዳ ላይ እዛው ጊቢው ውስጥ ጠረጴዛውንና አስፈላጊ ቁሳቁሶችን በማዘጋጀት በስሜት ተውጦ ሲስል ቆየ። ጆንስ በረንዳው ላይ ተቀምጦ አንዴ የአብነትን አሳሳል ሌላ ጊዜም ከፊቱ ባለው ጠረጴዛ ላይ የተቀመጠውን ወፍራም መፅሀፍ እያገላበጠ በማንበብ ሲጃራውን ሲምግ ቆየ።

የጊቢው በር ተንኳኳ። በአካባቢው የነበረውና ከጆንስ ጋር ከመጡት መካከል አንዱ የሆነው ሰው ተራምዶ ከፈተው።

ቤቲ ነበረች። አብነትን ስታየው ፊቷ በፈገግታና በሲቃ ተሞላ። ምን እንደምታደርገው ግራ ገብቷት በዝምታ ለደቂቃ አፈጠጠችበት። አካሏን አጉልቶ የሚያሳይ ጠባብ የሆነ ቀይ አጭር ሱሪ፤ ረጅን በመጠኑ አጋልጦ ከሚያሳይ ስስ ቡዲ ላይ ዘመናዊ የሆነ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ቡኒ የቆዳ ጃኬት ለብሳለች፡፡ የተጫማችውን ጫማ ለመርገጫዋ ብቻ ተለክቶ የተሰራ ቀጭን ሶል ሲኖረው ከላይ በተጠላለፉት ቀጭን ማሰሪያዎች ባቷ ድረስ በመውጣት ይታሰራል፡፡ የእግሮቿ ጣቶች የብዙሀኑን ሴቶች የእጅ ጣት ውበት ያስንቃሉ፡፡

አብነት ከተመሰጠበት ላለመውጣት ቢፈልግም የሷ በዕለቱ በቦታው መገኘት በራሱ ፍላጐት የተደረገ በመሆኑ ዞሮ አያት፡፡
ውብ ፈገግታዋ እንደ ማለዳዋ ፀሀይ ሲሞቀው ተሰማው
“አቢ ታዲያስ?”
“እንዴት ነሽ?”

ወደሱ መራመድ ጀመረች፡፡አብነት የጀመራትን መስመር ለመጨረስ ወደ ጠረጴዛው ዞረና ቀለም አጥቅሶ ስራውን ቀጠለ፡፡

ቤቲ አጠገቡ ደርሳ እስኪጨርስ በዝምታ እያየች መጠበቅ ተያያዘች፡፡

ጆንስ ዛሬ ደውለህ እንድትመጣ ንገራት ባለው መሰረት ነበር ትላንት ደውሎ የጠራት፡፡

ቡሩሹን ማስቀመጥ ሲጀምር “ጉዳዩ ምን ላይ ደረሰ?” ጠየቀችው፡፡

መልስ ሳይሰጣት እቅፉ ውስጥ ከተታትና ወደ ሰመመን መሳይ ዓለም በሚያሻግር ሁኔታ የልብ ቅርፅ ያላቸው ከንፈሮቿን ሳማቸው፡፡
“ዷ.....ዷ.....ዷ.....” ጆንስን ከተመሰጠበት መፅሀፍ ያባነነው በሚማርክ ሁኔታ ሲሳሳሙ የሚፈጠረው የተለመደው ዓይነትና ደስታን የሚሰጠው ድምፅ ነበር፡፡ እያያቸው ፈገግ አለ፡፡

የመሻታቸው ያህል ተሳስመው እንደጨረሱ ቤቲ ደግማ የበፊቱን ጥያቄ አቀረበችለት፡፡
“ሁሉም ነገር በሰላምና በእርቅ ተጠናቋል፡፡”
“እስኪ በዝርዝር ንገረኝ.....?” በሚማፀን ቅላፄ ጠየቀችው፡፡
“መጀመሪያ ከአሜሪካውያኖቹ ጋር ላስተዋውቅሽ.....” አላትና ወደ ጆንስ መራመድ ጀመሩ፡፡

በፈገግታ ጠበቃቸውና ሲደርሱ የለኮሰውን ሲጃራ እያጠፋ ከተቀመጠበት ተነሳ፡፡
“ቤቲ ማለት እሷ ነች?” ጆንስ ቀድሞ ጠየቀ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“አዎ....” አለ አብነት፡፡

እጁን ለሰላምታ ዘረጋላት፡፡

“ከአብነት ጋር የሰራሽውን ታላቅ ስራ ሰምቻለሁ፡፡ የምትደነቂ ወጣት ነሽ፡፡”

ቤቲ እየሰማች ፈገግ ከማለት ውጪ ምላሽ አልነበራትም፡፡ አብነት አስተረጎመላት፡፡

ለግማሽ ሰዓት ያህል በተከናወኑት ጉዳዮች ዙሪያ በየተራ ሲገልፁላት ቆዩ፡፡

ከዛም ጆንስ “ምንድነው ራዕይሽ?” ጠየቃት፡፡

“መማር..... በጣም እፈልጋለሁ.....”

በመልሷ እየተደሰተ “ምን ያህል ተምረሻል?”

“አስራ ሁለተኛ ክፍል አጠናቅቄ ነው ያቆምኩት”

“ለምን አልቀጠልሽም?”

“ለዩኒቨርስቲ በቂ ውጤት አልመጣልኝም..... የግል ኮሌጅ እንዳልማር ደግሞ አቅሙ የለኝም..... በውጪ አገር ነፃ የትምህርት እድል ለማግኘት ተፃፅፌ ነበር አልተሳካልኝም” ትልሚን ወዶታል፡፡ በባህሪው ለመማር ለማወቅ የሚተጋ ሰው ያስደስተዋል፡፡

“በሌላ በኩል መንግስት አንቺንም ሆነ አብነትን እየፈለጋችሁ እንደነበረ ሰምቻለሁ፡፡”

“ አብነትን ነው፡፡ የሱን ፎቶውን ሁሉ አግኝተውታል፡፡”

ጆንስ በዝምታ ሲያስብ ቆየ፡፡ ከአብነት ጋር ስለ ቀጣዩ እቅድና ህይወቱ ተነጋግረው በራሱ በአብነት ውሳኔ የደመደሙት ጉዳይ በመሆኑ ጆንስ ስለሱ ማንሳት አልፈለገም፡፡

“አንዳንድ ነገሮችን ባመቻችልሽ ምን ይመስልሻል?”

“ማለት ምን ለማድረግ.....”

አብነት ጣልቃ ገባና “እዚህ ለመማር አሁን ያለችበት ሁኔታ ብዙም አመቺ አይሆንላትም፡፡ በአገሪቷ የትምህር ፖሊሲ እንቅፋትነት ምክንያት የፈለገችውን ዓይነት ትምህርት መርጣ እንድትከታተል እድሉን ስለማይፈጥርላት.....” ሀሳቡን አንጠልጥሎ ተወው፡፡

“ምን አማራጭ አለ?” ጆንስ ጠየቀ፡፡

“ቢቻል ለኔ ሰጥተሽኝ በነበረው ዕድል እሷን ወስዳችኋት እዛው ብትማር.....”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“ፈቃደኛ ከሆነች ይቻላል፡፡”
አብነት በደስታ ጆንስን ጨበጠውና ወደ ወደ ቤቲ ዞሮ “እንኳን ደስ አለሽ”
“አንድ ነገር ግን ቃል ላስገባት እፈልጋለሁ” አለ ጆንስ
“ምን?” ጠየቀችው፡፡
“ትምህርትሽን እንዳጠናቀቅሽ ተመልሰሽ አገርሽ እንደምታገለግይ እርግጠኛ እንድትሆኚልኝ.....”
“የኔም ፍላጐት እሱ ነው፡፡”
ጆንስ ፈገግ አለና “ስደት ማለት ኪስሽ ውስጥ የሌለን ገንዘብ የሌላ ሰው ኪስ ውስጥ ፍለጋ አገርን እና ቤትን ዘግቶ መሄድ ማለት ነው፡፡ የሌላ ሰው ኪስ ውስጥ ያለ ገንዘብ ደግሞ የራስ ስላሆነ በምፅዋት ወይም በሌብነት ብቻ ነው የሚገኘው፡፡ እናም ስትሰደጂ የምትደርሺበትን ዓላማ የማታውቂና ዝም ብለሽ አርቴፊሻል ነገርን ፍለጋ ከሆነ የነሱን የሰላም ትርፍራፊ፤ የዲሞክራሲ ትርፍራፊ፤ የስልጣኔ ትርፍራፊ፤ የፍትህ ትርፍራፊ፤ የዋስትናና ኑሮዋቸውን ትርፍራፊ ሁሉ በምፅዋት እየተቀበልሽ ወይም እየሰረቅሻቸው ያንቺ ባልሁነ ነገር ውስጥ ራስሽን እና ክብርሽን ፤ ህሊናሽን ዝቅ አድርገሽ ተዋርደሽ መኖር ማለት ነው፡፡” እሷ ግን ወደ አብነት ዞረችና
“አብረን ነው አይደል የምንሄደው?”
“እኔማ መሔድ አልፈልግም፡፡”
“እና..... አንተን ትቼ ልሔድ?” አለችው በሀዘን ተውጣ፡፡
“አዎ፡፡ ግዴታ መሆን አለበት፡፡ ተምረሽ ራስሽን ለውጠሽ ብትመጪ የወደፊቱ ደስታሽ ከእኔ ጋር መኖር የበለጠ ይሆንልሻል፡፡ እኔም የነፍስ ጥሪ አለኝ፡፡ መሳል የምችለው ህይወቴ ከምንም ዓይነት ጥገኛ ነገር ነፃ ስትሆን ብቻ ነው፡፡ ካለበለዚያ መሳል አልችልም ካልሳልኩ ደግሞ አብዳለሁ፡፡ ብወድሽም ተመልሼ የብቸኝነት ዋሻዬ ውስጥ መግባት አለብኝ፡፡”
“የስዕል ፍቅር.... ከኔ ይበልጥብሀል?” ትኩስ የእምባ ዘለላዎች በጉንጯ ላይ እየተሸኳለሉ ጠየቀችው፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“አላውቅም..... ሚሰማኝ እውነተኛ ስሜት ግን አንቺም እኔም መኖር እንዳለብን ብቻ ነው። አንቺም የራስሽን የነፍስ ጥሪ በነፃነት ኑሪያት። ያኔ ሁለታችንም ኖርን ይባላል። ካለበለዚያ እኔ ላንቺ ስሞት አንቺ ለኔ ስትሞቺ የህይወት ስቃይዋ ያይላል። ይህ ደግሞ በፈጠራ ሰው ላይ ይበረታል..... ቤቲ ከማንም በላይ እወድሻለሁ ግን አልፈልግም ራቂኝ..... አንቺ በህይወት ውስጥ እልፍ አማራጮች አሉሽ። እኔን ብትተይኝ ከሰማያዊው ገነት የፈለቀን የነፍስ ውሃ እያመጡ በማጠጣት አለምልመው ሊያኖሩሽ የሚችሉ እልፍ አፍቃሪዎች ማግኘት ትችያለሽ ....እኔ ግን የአንድ ነገር ምርኮኛ ነኝ። ወደየትም ብሔድና ብዞር ምርጫ የለኝም። አንቺ ከኔ ጋር በመሆን የሚደርሱብሽን ስቃዮች በጠቅላላ በፀጋ ተቀብለሽ መቋቋምና መኖር ትችይ ይሆናል። እኔ ከአንቺ ጋር በመሆን መሰቃየት ከጀመርኩ መሳል አልችልም አብዳለሁ። ጨርቄን ከጣልኩ ደግሞ ምን ያህል ብትወጂኝ እንኳ ያኔ ትተይኛለሽ።”
ቤቲ ከመቼውም ጊዜ የበለጠ ከሱ ጋር መኖርን ስትፈልግ ተሰማት። በትካዜ ተዋጠች።
አብነት ፈገግ አለና “ሁልጊዜ በድንገተኛ የመለያየት ሁኔታ የሚከበቡ ፍቅረኛሞች እርስ በእርስ የመፈላለግ ሀይላቸው በጣም ይጨምራል” አላት።
“እሺ....ቃ....ል ግባልኝ.....እስክመጣ ድረስ?”
“ለምን የሞኝ ስራ እንሰራለን። ያንቺ ለኔ መሆን ወይም እኔ ላንቺ መሆን በእጣ ፈንታ የተቸገረን ስጦታ ከሆነ ላንገናኝ ተባብለን ብንለያይ እንኳ የህይወት መዘውሩ ራሱ ያገናኘናል።”
የማይገለፅላት የሱነቱ ባህሪዎች መጡባት። ሁለቱ አብረው እንዲሰሩ ያገናኛቸው የፖለቲካ ጉዳይ ከመከሰቱ በፊት የምታውቀው አብነት ነበር አሁን እያወጋት ያለው።
በህሊናዋ ‘ምናለበት ስራው ተራዝሞ በነበር።’ አለች።
“ግን አገኝህለውኝ?” ጠየቀችው በዝቅተኛ ድምፅ

“መልሱ የጊዜ ጉዳይ ስለሆነ ለራሱ ለጊዜ ብንተወውስ? አሁን እኔ ስላንቺ የማስበው በአንድ አቅጣጫ ብቻ ነው። በተገኘው ጥሩ ዕድል ተጠቅመሽ ራስሽን ስትለወጪ ማየት መቻልን።”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

'አጭር ብትሆንም ያሳለፍናት አስደሳች ጊዜ እንዲሁ መረሳት አለበት ማለት ነው?' አለች በህሊናዋ፡፡

"በዚች ምድር ላይ ስትኖሪ ድርጊቶች በጠቅላላ ገጠመኞች ናቸው፡፡ ያልፋሉ ይመጣሉ ተመልሰውም ያልፋሉ፡፡..... ማስተዋል ያለብሽ ነጥብ ግን ህይወትን ድጋሜ ልታገኛት የማትችይ ክስተት በመሆኗ መኖር እንደምትፈልጊው ብቻ ለመኖር ነው መታገል ያለብሽ"
በውስጧ ላሰበችው ነገር ምላሽ በሚሆናት ንግግር ተገርማ "እንደ ነብይም ያደግርሀል ልበል?" አለችው፡፡
ዓይኖቿ በአይኑ ላይ ተተክለው፡፡ የሱ ዓይኖች ደግሞ ከአይኗ ውስጥ ያለውን ዕይታ በሚፈልግ ስሜት ሲንከራተቱባት ቆዩና
"ነገሮችን እንደገባሽ የመረዳት መብት አለሽ፡፡"
"በስመ-አብ....."አለች እይታዋን ወደ ሌላ አቅጣጫ እየሰደረች፡፡ ቀጠለች "....በሰማይ ላይ እንዳለ ጉም ነህ ትታያለህ እንጂ አትጨበጥም" አለችው አፈጣጠሩ እየተማታባት፡፡
"እያየሽኝ መደሰት ስትችይ ለምን ልትጨብጪኝ ትታገያለሽ?"
"በደንብ ላውቅህ ስለምፈልግ....."
"ያወቅሽኝን ያህል እበቃሽ ነበር.... እኔም ካንቺ የበለጠ ራሴን አላውቀውም.... እና የበለጠ ልታውቂኝ በጣርሽ ቁጥር ግን ይበልጥ እየጠፋሁብሽ ይበልጥ እየተወሳሰብኩብሽ ነው የምሔደው፡፡"
"ልክ እንደ አብስትራክት ስዕል፤" አለች በስላቅና ንዴት
ጆንስ ለረዥም ደቂቃዎች በአማርኛ ሲነጋገሩ የነበሩትን በዝምታ ሲሰማ ቆየና "አብስትራክት" የምትለዋ ቃል ጆሮው ጥልቅ ስትል "ስለ ስዕል ነው የምትነጋገሩት?" አለ፡፡
"ቀጣይ ህይወቷ ምን መምሰል እንዳለበት ነው፡፡" አብነት ቀድሞ መለሰ፡፡
"ያላትን የትምህርት ማስረጃዎች እና ፓስፖርቷን ዛሬውኑ አምጥታ ትስጠኝ" አለ ሲጃራ እየለኮሰ፡፡
ቤቲ በግማሽ ሀዘንና ደስታ "እሺ" አለች፡፡ ህሊናዋ ግን የአብነትን ለሷ ስለ መሆን እየፀለየ ነበር፡፡

«««««««« »»»»»»»»

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

በዛው ዕለት ከሰዓት በኋላ ሰናይት ጥቁር መርሰዲስ መኪና በመያዝ ሩዋንዳ ከተከራየችው ቤቱ ውስጥ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችንና ከነሉዊስ ተልኮ ሳይሰጥ በእጇ ላይ የቀረውን ገንዘብ ለማምጣት በዛውም የቤቱን ቁልፍ ለባለቤቶቹ አስረክባ ከቦሌ መስመር ወደ መገናኛ ከዛም ወደ ሲ.ኤም.ሲ. አቅጣጫ በመዞር ጉዞ ላይ ነበረች።

ህሊናዋ ስለ ቀጣይ ህይወቷ ምን መምሰል እንዳለበት በሀሳብ ተወጥሮ መኪናዋን ከገደብ በላይ ታስከንፋታለች። ተመልሳ ፈረንሳይ በመሄድ እዛ ለመኖር አልፈለገችም። በሌላ በኩልም ኢትዮጵያ እንደማትቀር በእርግጠኛነት እያሰበች 'ኑሮ አቅጣጫዋን ወደ ምን ዓይነት ገፅታ ታዞርብኝ ይሆን?' ብላ ራሷን ጠየቀች።

በእርግጥ ከነሉዊስ አገኘዋለሁ ብላ ካቀደችው በላይ የሆነ ገንዘብ እጇ ላይ መኖሩን አሰበች። ከሱ ላይ ለመንበረ የሰጠችውን መቶ ሺህ ዶላር አስታወሰችና ፈገግ አለች።

'ይሄኔ ምን እየሰራች ይሆን?' ወድያው ሀሳቧን ወደራሷ መለሰችና በቀረው ገንዘብ ካለ ችግር መኖር እንደምትችል ማገናዘብ ቀጠለች። መኪናው ይከንፋል ወደ ቤት ለመድረስ።

ሆኖም ግን ያልተረዳችው የባዶነት ክፍተት በውስጧ መኖሩ ይሰማታል። ያንን ጦዶሎነት ደግሞ እንዴት መሙላት እንዳለበት አታውቀውም።

ማታ በዚሁ ሀሳብ ስትብሰለሰል ጆንስ አይቷት ለረዥም ሰዓት ሲመክራት ነበር ያመሸው። ከተነጋገሩበት መካከል የጆንስ አንድ አባባል ታወሳት "በማንኛውም አንገሽጋሽ ወቅቶች ውስጥም ቢሆን መኖር እንዳለብሽ እመኚ። ስትኖሪ ብቻ ነው ሁሉንም ነገር መለወጥ የምትችይው" የሚል ነበር።

በዚህ ስሜት እየዋለለች ባላስተዋለችው ፍጥነት የሚያከንፋት መርሰዲስ መኪና ቤታቸው ጋር ለመድረስ ሃምሳ ሜትር ያህል እንደቀራት እንኳ ልብ አላለችም። በተቃራኒው አቅጣጫ ገልባጭ የሆነና የግንባታ እቃ የጫነ እስካኒያ መኪና በተመሳሳይ ጥፍነት

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ከፊት ለፊቷ እየመጣ መሆኑን እንኳ አታይም ሲደራረሱ ብቻ ፍጥነቷን ተቆጣጥራ ለመተላለፍ ፍሬን ፍሪስዮን ማርሽ መሪ... ሁሉንም ተጠቀመች። ግና ዘግይቶ ነበር። የመርሰዲሱ ግራ አካል ከእስካኒያው ጋር ተላተመና አስፓልቱን ስቶ ወደ ግራው አቅጣጫ እንደ ኳስ በአየር ላይ ተሽቀነጠረ። አሰቃቂ አደጋ ነበር።

ኢዮብ በጊቢው ውስጥ ሲዘዋወር ከፍተኛ የሆነ ፍንዳታ መሰል ግጭትና መንሸራተት ስለሰማ ምንነቱን ለማጣራት የጊቢውን በር ከፍቶ ጭንቅላቱን ወጣ አደረገ። ጥቁሩ መርሰዲስ መኪና ተጨረማምቶና መስታውቶቹ ረግፈው ቆሞ አየው። ሃያ ሜትር ራቅ ወዳለው ቦታ ሮጠ ሲደርስ ሰናይት መሆኗን አወቀ።

ተመልሶ ሌሎቹን ጠራና በረገፈው የግንባር መስታውት በኩል ጐትተው ሲያወጧት ከጭንቅላቷ ላይ የሚፈሰው ደም ተበክላ ነበር። ከጆንስ ጋር አራት የሚሆኑት ወደ ሐያት ሆስፒታል ሲወስዷት ቀሪዎቹ መርሰዲሱ ውስጥ የነበረውን ትልቅ ሻንጣና ቁሳቁሶች ወደ ቤት ማስገባት ጀመሩ።

በሐያት ሆስፒታል ለአራት ሰዓት ያህል ህክምና ሲያደርጉላት ከነበሩት ባለሞያዎች መካከል የበላይ ተቆጣጣሪ የሆነው ጐልማሳ ዶክተር እንግዶች ወደሚያርፉበት አካባቢ መጣና "የሰናይት ቤተሰቦች?"
"አቤት....." አለ ኢዮብ።

ዶክተሩ ሁሉም ሲከቡት የውጪ አገር ሰዎች መሆናቸውን አወቀና በእንግሊዝኛ ስለ ጉዳቷ ረዥም ገለፃ ሲያደርግላቸው ቆየና "....በማያቋርጥ የህክምና ክትትል የሚስተካከል ቢሆንም በጭንቅላቷ ላይ ከፍተኛ የሆነ ጉዳት ደርሶባታል።" አለ። ሲናገር በትህትናና በእርጋታ ነበር።
"ለሞት ያደርሳት ይሆን?" ጆንስ ጠየቀ ።
"በጭራሽ....."
"ሌላ ተፅዕኖስ?"
"እ..... ምናልባት የመርሳት ችግር ሊከሰትባት ይችላል"
ጆንስ ለደቂቃ ሲያስብ ቆየና "ህክምናውን በውጭ አገር እንድትከታተል ስለምፈልግ አስፈላጊውን ትብብር ብታከናውንልን"

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“የት አገር?”
“አሜሪካ”
“እሺ ጉዳዩን ለሚመለከተው አቅርቤ ላስወስን” አለ ዶክተሩ፡፡
ጆንስ ወደተነሳበት ወንበር እየተመለሰ ‘ከተሳካላት የወደፊት ኑሮውዋም ለመለወጥ ጥረት እናደርግላታለን በማለት እያሰበ ነበር፡፡

  

ያማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ምዕራፍ 54

እንደ ተስቦ በወረርሺኝ መልክ ስብሰባና ግምገማ ወደ አገሪቷ የገባ ይመስል ሁሉም በስብሰባ ተወጥሯል። በጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ ከፍተኛ ባለስልጣናት ስብሰባ ተቀምጠዋል.... የ"ህ.ወ.ሐ.ት" ከፍተኛ ባለስልጣናት ስብሰባ ተቀምጠዋል..... "ብ.አ.ዴ.ን" ስብሰባ ላይ ነው..... "ኦ.ህ.ዴ.ድ" ስባሰባ..... "ደ.ህ.ዴ.ግ" ስብሰባ..... ክልሎች፤ ዞን ፤ ወረዳ፤ ቀበሌ ፤ ፖሊስ፤ ወታደሩ ጭምር በያለበት ክፍል ስብሰባ.....

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በቲ.ቪ. ላይ ባስተላለፉት ንግግር ውስጥ የ"ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ስልጣን የዛፍ ላይ እንቅልፍ ነው" በሚለው ማስፈራሪያ መሰል ማስጠንቀቂያ የተላለፈላቸው የየመስራቤቱ ባለስልጣናት ትጉህ ለመባልና ስልጣናቸውን ላለመነጠቅ ሰራተኛውን ወጥረው ስብሰባ... ስራ ስብሰባ ብቻ እስኪመስል ድረስ ስብሰባ..... በስብሰባና በግምገማ ብዛት አገር ብትበለፅግ ኖሮ የኢትዮጵያ ስልጣኔ ጨረቃን በነካ ነበር። እንዳለመታደል ሆኖ የስብሰባ እና የግምገማ ብዛት አገሪቷን ወደ ማበስበስ እና ወደ ማግማት ነው ያዘቀጣት። ራሳቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ አንድ ወቅት ላይ እንዳሉት "ገምተናል....! ገምቶዋል...! " አዎ ኢትዮጵያ እንድታራምድ በተገደደችው ስርዓት ምክንያት በምድሪቷ ላይ ገምታለች። ስርዓቱ በፈጠው ዓለም አቀፍ እና አገር አቀፍ የለማኝና የልመኛ አይነት ብዛት ከሚሰደደው ዜጋዋ አስደንጋጭ ቁጥር ብዛት ጋር ተዳምሮ አመራሮቿ አግምተዋታል..... ባለበሷት የበሰበሰ አስተሳሰብ እና ድርጊት አገር ፈራርሳ ገምታለች።

የውሻዎች ቁመና፤ የፀጉር መልክ እና መጠን ምንም ቢለያይ የሁሉም ጩኸት ያው አንድ ዓይነት «ውው..ው.ው.ውውው....» እንደመሆኑ የወያኔው አገዛዝ የስብሰባ እና ግምገማ ብዛት ከወደቀው የደርግ ስርዓት ውስጥ አንድን ተመሳሳይ ድርጊት ሁሌም ያስታውሳል። እሱም «ዘመቻ» የሚለውን ነበር። ይህ አገዛዝ ሁሉን ነገር በስብሰባና

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ግምገማ ይፈታው ይመስል እንደሚያደርገው ደርግም ሁሉን ነገር በዘመቻ ይፈታው ይመስል «የሰርቶ አደር ዘመቻ፤ የላብአደር ዘመቻ፤ የቀይ ሽብር ዘመቻ፤ የመሰረተ ትምህርት ዘመቻ፤ አብዮታዊ ዘመቻ...፤ የጥጥ ለቀማ ዘመቻ፤ የደን ተከላ ዘመቻ፤ ዘመቻ...፤ ዘመቻ...፤ ዘመቻ...» ሲል ከርሞ ሳይንሳዊ እውቀት እና ሳይንሳዊ ጥበብን የሚጠይቀውን የውትድርና ተግባር በ«ዘመቻ» ስሌት ለመፍታት ሆሆሆ..... ብሎ ገባበት::

ከእግር ጥፍሩ እስከ አናት ፀጉሩ ጉድ እስኪባልለት ድረስ የዘመኑን ዘመናዊ መሳሪያ የታጠቀና አስፈሪ ቁጥር የነበረው ግዙፍ ሰራዊት በአንድ ወቅት ላይ ናቅፋ በተባለው የሰሜን ተራራ ውስጥ ብቻ ተሰባስቦ የተቀመጠን ጥቂት አማፂ መደምሰስ አቅቶት ከኤርትራ ጫፍ በ«ዘመቻ» ቁልቁል መሸሽ የጀመረ መጨረሻ ላይ የአዲስ አበባውን ምኒልክ ቤተ መንግስት ጥሎ እስከመፈርጠጥ ደረሰ::

በዛ ዘመን ላይ አገርን ያዛገው የ«ዘመቻ» ድርጊት እና ጩኸት ልክ እንደ ውሻ ጩኸት በዚህኛው አገዛዝም ጥቂት የስምና የቅርፅ ለውጥ ብቻ አድርጎ በተመሳሳይ ጩኸት «ስብሰባና ግምገማ» ተብሎ እዛው አሮጌ የአስተሳሰብ አተላ ገላ ላይ አዲስ የስም ካባ በመደረብ አገር ማበስበስ እና ማግማቱን ቀጥሏል::

አዲስ አበባን የተቆጣጠሩበትን አስራ አንደኛ ዓመት በስጋት ፤ በስብሰባና በግምገማ ነበር ያከበሩት:: በዓሉን በማስመልከት እንደምንም ብለው መላው የዓገሪቷን ህዝብ በጠቅላላ በቲቪ እና ሬድዮ አማካኝነት ስብሰባ ሰብስበውት ዋሉ:: በዋናነት ያስተላለፉት መልእክትም «ኢ.ህ.አ.ዴግ ከሌለ የብሔር ብሔረሰቦች ነፃነት የለም፤ ዲሞክራሲ የለም፤ ሰላም የለም፤ አገር የለችም ፤ በተለይ የትግራይ ህዝብ እስከመጨረሻው ካልደገፍከን ሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ ይፈጅሀል! ወየውልህ! .....» የምትለውና ከተሳካ ሆድ መብያ ካልተሳካም ቀጭን ዛቻ አዘል ማስፈራሪያ በስብሰባቸው መካከል በምትለቀቀው

« ..... ያ ሁሉ ታላፈ
ታጋይ የህዝብ ልጅ በደሙ በላቡ
ደማቅ ታሪክ ፃፈ..... »

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

በምትለው እና በህዝብ ልጅ መስዋእትነትና ደም፤ ግን ለማን እንዳለፈ በቅጡ በማታብራራው በዛች የበረሃ ዘመን መዝሙራቸው እየታጀበ ሲተላለፍ ዋለ። ስርዓቱ ስራ ፈት ፤ ስራ ፈትነቱ ድህ ያደረገው አብዛኛው የአገሪቷ ህዝብም የሚያከናውነው ጉዳይ ስላልነበረው ሰተሰብስቦ ሲያዳምጣቸው ዋለ።

ሶስተኛው የታሪክ ስህተት ሲደገምም ቁጭ ብሎ አየ። ስህተት አንድ ንጉሰ ነገስቱ ከስልጣን እንደወረዱ ብዘሀኑ የዋሆች «ይህች አገር አበቃላት!» ብለው ነበር። ይህ ስህተት ደርግ ከስልጣን መውረዱ አይቀሬ መሆኑን ሲረዳ «እኛ ከሌለን ህዝብ የለም! አገር የምትባል አትኖርም! ኢትዮጵያዊ ሁሉ ጉድህ ፈላ! ብሎ ለማስፈራራት ሞክሮ ነበር። ይኸው የኢ.ህ.አ.ዴ.ግ. መንግስትም ይህኑ መድገም ጀምሯል። ከአገር እና ህዝብ በስተጀርባ የሰው ልጅ ሰላምና አንድነት እንዲሁም ደህንነት እንደ አምላክ ፈቃድ መሆኑን ዘንግተዋል። ይህ ባይሆንማ ኖሮ እንደ ብዙኀኑ ፖለከኞች « እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይበቀል» መሻት አገሪቷ እንደ አገር ቆማ ባልተገኘች ነበር።

ተክለአይ ቢሮ ውስጥም ሰባት ሰዎች ስብሰባ ላይ ነበሩ። ተክለአይ እየተበተነ ያስቸገረው ህሳቡን ለማሰባሰብ በፍፁም የማይቻል ሆኖበታል። ግን ሰባት ከፍተኛ ባለስልጣናትን ሰብስቦ ለስብሰባ ተቀምጧል። ለውይይት ያዘጋጀውን ዋነኛ ርዕስ ለማስታወስ እየጣረ "ስለዛ እንቅስቃሴ ጉዳይ ፍንጭ ሰጪ አቅጣጫ ጠፋ ማለት ነው?" አለ ወደ ህዝብ ደህንነት ሀላፊው እያየ።

"አዎ.....። ሻንጣ ተያዘ..... መልሰው መሰረቁን። ሰራቂው አካል ማን ይሁን? ለምን ዓላማ ይስረቀው? በውስጡ ምን ዓይነት ሰነድ ይኑረው? ምንም አልታወቀም። የአንድ እንክርዳድ ተጠርጣሪ ወጣት ፎቶ በመላው ከተማዋና ቁልፍ በሆኑ የክልል ከተሞች ሳይቀር የተበተነ ቢሆንም ምንም ውጤት ሊያስገኝ አልቻለም" አለ።
ሀሳስ ጣልቃ ገባና "በዚህ ሰሞን ደግሞ አጠቃላይ ሁኔታዎች ዝም ብለዋል። የምንም ዓይነት አጠራጣሪ እንቅስቃሴ በከተማዋ ውስጥ የለም።"
"ዝምታው አስፈርቶኝ አይደል እንድንነጋገር የጠራኳችሁ።....." ቀጠለ ተክለአይ "ትላንት አንድ ጋዜጣ ላይ ምን የሚል ነገር እንዳነበብኩ ታውቃላቹ....." ብሎ በየተራ እያያቸው " የህዝብ አመፅና እሳተ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ገሞራ አንድ ናቸው፡፡ ከጥሩ ዝምታ ውስጥ ነው ድንገት ፈንድቶው የሚያጠፉት፡፡"

ወዲ ሀለፎም እና ሌሎች ሁለት ተሰብሳቢዎች በአምንታ ጭንቅላታቸውን ነቀነቁ፡፡ ቀጠለ "..... የዚህ አደግዳጊ እበላ ባይ ህዝብ ዝምታ የቦጎ ስላልመሰለን እንደምታውቁት ሰሞኑን የጠቅላይ ሚኒስትሩ ቢሮ ለከፍተኛ የውሳኔ ጉዳይ ስብሰባ ላይ ነበር የቆየው፡፡ በዚህም ከፍተኛ ወሳኔ ተላልፏል፡፡ ይህ ድንገተኛ የህዝቡ የዝምታ ጉዳይም ሁኔታዎች ወዴት እያመሩ እንደሆነ ፍንጭ አልሰጥ ስላለ አሳሳቢና አስፈሪም ስለሆነ ነው ውሳኔው የተላለፈው..." አለ ተክለአይ ቀና ብሎ የሁሉንም ፊት እያጠና፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከጣት ቁጥር እጅግም ከማይልቁና ህ.ወ.ሓ.ት.ንም ሆነ አገሪቷን በዋናነት ከሚያሽከረክሩት ጎላፊዎች ጋር ሆነው ውሳኔ ያሳለፉበትን መዝገብ እየገለፀ "የትግራይን ከኢትዮጵያ መገንጠል በይፋ ልናውጅ ተዘጋጅተናል፡፡ በዚህም ምክንያት ሁሉም የህ.ወ.ሓ.ት አባል በቅድሚያ እንዲያውቀው ታሟል፡፡ " አለ

ለዚሁ ስብሰባ ከትግራይ የመጡትና ከሳላሳዎቹ ከፍተኛ የህ.ወ.ሓ.ት ባለስልጣናት መካከል አንዱ የሆኑት ወድያውኑ "አይሆንም! " ሲሉ ተቃወሙ፡፡

የሁሉም ተሰብሳቢዎች እይታ ወደ እሳቸው አተኮረ፡፡ ቀጠሉ ገብረእግዚ "ያለፉትን አስር ዓመታት በትግራይ የተለያዩ አውራጃዎች ውስጥ ተዟዙሬ ሰርቻለሁ፡፡ እንዲሁም ትግራይን የመገንጠል ሀሳብ ላይ የክልሉ ህዝብ ያለውን ስሜት ለማወቅ ሁለት ጊዜ በመንግስት ጥናት እንዲደረግበት የታዘዘውን ስራ መርቻለሁ፡፡ ጥናቱንም ለበላይ ሰዎች አሳውቀን ነበር፡፡ ምንም ጥያቄ የሌለው ነው፡፡ ትግራይን እንገንጥል ብለን አሁን በይፋ ብናውጅ የትግራይ ህዝብ ራሱ ተነስቶ ይመታናል፡፡ አይቀበለንም ያጠፋናል፡፡" አሉ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

ይሄኔ ሀዱሽ የተባሉት ሌላኛው ተሰብሳቢ “የትግራይ ህዝብ ብቻ ሳይሆን ሌላው የኢትዮጵያ ህዝብስ በዝምታ የሚያይ ይመስላችኋል? ” በማለት ጥያቄያዊ አስተያየት ሰነዘሩ።።

ተክለአይ ይህንን ዓላማ ያለ እክል ለማስፈፀም እንዲቻል በሌሎቹ የአገሪቷ ክልሎች ላይ የታቀደውን እና ከጠቅላይ ሚኒስሩ ቢሮ የተላለፈውን ውሳኔ እያነበበ መመለስ ጀመረ “የትግራይ ነፃነት እንደታወጀ ወድያውኑ የኦሮሚያ እና ኦጋዴን ነፃነቶች ይታወጁና የየራሳቸውን መንግስት እንዲመሰርቱ ይደረጋሉ። ከላይ የትግራይ መሄድ እና ከታች የኦሮሚያ መውጣት ትምክህተኛውን ነፍጠኛ ውንና አደገኛውን አማራ ግራ የሚያጋባ ሁኔታ ውስጥ ለብቻው ስለሚያስቀረው ሳይወድ በግዱ የተዳከመና ምንም ማድረግ የማይችል ራሱን የቻለ አገር ይሆናል። ያውም ከኦሮሚያ ጋር በመሬት ጉዳይና በሌሎች ምክንያት ወደ ጦርነት ሊያመራም ስለሚችል ለትግራይ የሚያሰጋት ሁኔታ አይፈጠርም። ሌላው ከታች የኦጋዴን ከላይ የኦሮሚያ መቆረጥ ደቡብን ለብቻው ስለሚያስቀረው ሳይወድ ራሱን በራሱ በመንግስትነት ለማስተዳደር ይገደዳል። ሌሎቹ አናሳ ብሔረሰቦች እንደ እድላቸው ይሆናሉ።”

ገብረእግዚ ሲያዳምጡ ቆይተው “እኔ ግን ህዝቡ ውስጥ አብሬ ኖሬ አይቼዋለሁ ይህ የታቀደው ሀሳብ አሁን ይተግበር ከተባለ ወደ መበላላቱ እናመራለን እንጂ በፍፅም አይቻልም። እንደውም የሚገርመውን ነገር ልንገራቹ ከጊዜ ወደ ጊዜ የትግራይ ህዝብ ሀይማኖቱ ላይ እና ኢትዮጵያዊነት የሚለው አቋሙን እያጠበቀ እኛ ንም እየተቃወመ መጥቷል።” አሉ ስጋታቸው በግልፅ እየታየ። ንግግራቸው ግን ሁሉንም ተሰብሳቢዎች አላስደሰተም።

ተክለአይ ጠንከር ባለ ቅላፄ “ካልሆነ በመሳሪያ አስገድዶ ማስፈፀም ነው።”

ገብረእግዚ “ዋ... እኛ ራሳችን የተገኘነው እኮ ስለ ጦር መሳሪያ እና ስለ ጦርነት ጠንቅቆ ከሚያውቀው ከዛው ከትግራይ ህዝብ መካከል ነው። መሳሪያ ለትግራይ ህዝብ አዲስ አይደም።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

አይፈራንም:: እንደውም በስማችን መነገድ አቁሙ ማለት ሁሉ ጀምረዋ"

ሀጎስ ጣልቃ ገባና "ችግሩ የኢትዮጵያን ህዝብ ገና በበቂ ሁኔታ አጠላልፈን እና አጠላልተን አልጨረስንም:: ህዝቡ ገና እርስ በእርስ ቂም ተያይዞ አላበቃም:: እዛ አደገኛ ደረጃ ላይ እንዲደርስ ገና ብዙ መስራት ይጠበቅብናል:: ምናልባት አርባና ሀምሳ ዓመት ሊፈጅብን ይችላል:: እስከዛ ስልጣን ከኛም መውጣት ላይኖርበት ግድ ይላል" አለ

"እና ምን ይሻላል?" አለ ተክለአይ ግራ በተጋባ ስሜት

ገብረእግዚ "ጠቅላይ ሚኒስትሩን ማናገር እፈልጋለሁ:: እንዲሁም በቀጥታ እኔ ራሴ ለሳቸው ብቻ መስጠት የምፈልገው ተጨማሪ መረጃ አለኝ::!" አሉ

"ያም ሆነ ይህ እድላችንን መሞከር አለብን" አለ ወዲ ሀለፎም

"ካልተሳካና የሱማሊያ አይነት አገር አቀፍ ብጥብጥ እና እልቂት ውስጥ ከተገባስ?" አሉ ገብረእግዚ

"ካልሆነማ መቼስ አብረን አናልቅ ሁሉም እንደ እድሉ ይሆናል:: እኛም አገር ጥለን መኮብለል ነዋ::" አለ ተክለአይ

"አዎ የተሻለ ምርጫ የለንም አለ..... ይህ ዝምታ የሰላም ስላልመሰለኝ ከወዲሁ ለማምለጥ ዝግጁ ሆነን መቀመጥ እንዳለብን ልንገራችሁ ብዬ ነው፡፡"

"አዎ..... የተሻለ ምርጫ የለንም" ሀጎስ::

ቀጠለ ተክለአይ "እስከ ሰባትና አስር ትውልድ ድረስ እያንደላቀቀ ሊያኖረን የሚችል ሀብት ጨብጠናል፡፡ ለዚህ ስልጣንና ላገኘነው ሀብት ያደረሰን እድላችንን እያመሰገንን ቀሪው እድሜያችንን በዓለም ላይ ያሻን ቦታ ሁሉ ሄደን በደስታ መኖር ነው፡፡ .....ሌላ ባለተራ ደግሞ መንበሩን ይያዝና የተቻለውን ያህል ይበዝብዝ፡፡ የማይነጥፍ የሀብት ምንጭ የሆነችው ኢትዮጵያ እንደሆን ለማንም ንፉግ አይደለችም፡፡"

"አዎ...." አንድ የማእከላዊ ፖሊት ቢሮ አባል የሆነው ባለስልጣን::

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ቀጠለ ".....እኛም ሁሉን ቻይ ወደሆነችው አሜሪካ ላጥ ማለት ነው፡፡" "እኔስ በደህናው ጊዜ ሲውዲን ቤት ሰርቻለሁ፡፡" አለ ወዲ ሀለፎም "ቤት መስራት ያለመስራቱ አስጨናቂ አይደለም፡፡ እንደ ምርጫችን ከመላው አውሮፓ እስከ ሩቅ ምስራቅ ጫፍ..... ከሰሜኑ አሜሪካ እስከ ደቡብ ጫፍ..... ገንዘቡ እስካለን ድረስ የፈለግንበት መኖር እንችላለን፡፡" አለ ተክለአይ።

"ይልቅ ትዕዛዙ ይተላለፍ....." የፖሊት ቢሮው ባለስልጣን ተናገሩ።
"አዎ.... በማንኛውም ሰዓት ለጉዞ ዝግጁ የሆኑ ሄሊኮፕተሮች ከነሾፌሩ የመኖሪያ ቤታችን አቅራቢያ ዝግጁ እየሆኑ ይቁሙ። ድንገተኛ የሆነ ችግር ከመጣ የትግራን ነፃነት በይፋ አውጀን ተያይዘን እብስ..... እስከዛም የቻልነውን ያህል ገንዘብ ከዚህ ጅል ህዝብ ኪስ ማግበስበስ....." አለ ሀጎስ

ሁሉም እየተሳሳቁ በመጨባበጥ ሀሳቡን አፀደቁት፡፡

ተክለአይ ሄሊኮፕተሮች ዝግጁ ሆነው እንዲቀመጡ ለማዘዝ ለደሚመለከተው የበታች ባለስልጣን ጋር ስልክ መደወል ጀመረ፡፡

  

የማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ምዕራፍ 55

ከሶቭየት ዋና ከተማ ሞስኮ ተጓጉዞ በጥቁር ባህር ወደብ በኩል እንዲጫኑ የተደረጉት ሁለት ግዙፍ መርከቦች ሙሉ የጦር መሳሪያ በቡልጋሪያና በቱርክ መካከል ባለችው ጠባብ የባህር ሰርጥ በማለፍ ወደ ሜዲትራኒያን ተሻገሩ።

ከዛም ፊታቸውን ወደ ደቡብ አቅጣጫ አዙረው በስዊዝ ቦይ በኩል በማለፍ የቀይ ባህርን መካከለኛ ክፍል ያዙና ጉዞ ቀጠሉ።

የአንደኛው መርከብ ጭነት በሱዳን ወደብ እና የሁለተኛው ደግሞ በኤርትራ ክልል በኩል በመራገፍ ሁለቱም በተለያዩ አቅጣጫ ተጉዘው ወደ ኢትዮጵያ በመግባት በትግራይና በአማራ ክልሎች ላይ ለሚንቀሳቀሱ አንጃዎች የሚከፋፈሉ ነበሩ።

በአስራ አምስት ኪሎ ሜትር ርቀት ተከታትለው የሚጓዙት ሁለት መርከቦች ላይ ለመድረስ ሌላ ጥቃት ሰንዛሪ ሶስተኛ መርከብ በፈጣን ጉዞ ይከተላቸው ነበር። የተነሳው ከጣሊያን ደቡባዊ ጫፍ ሲሲሊ ከተባለችው ከተማ ዳርቻ ሲሆን የመርከቡ ባለቤት የታወቀ የማፊያ አለቃ ነው።

በውስጡ የአፍሮኢዝም አራማጅ የሆኑና የመርከቦቹን ተግባር ለመግታት የተዋቀሩ የቡድን ሶስት ጥቁር አሜሪካዊ አባሎችን ይዞዋል። ቡድኑ የሚመራው ፒተር ጄፈርሰን በተባለው ጥቁር አሜሪካዊ መርከበኛ ሲሆን በስሩ ስምንት ሰዎችን የያዘ ነበር።

ከሲሲሊያዊው ማፊያ ይህን ጥቃት አድራሽ መርከብ ሲኮናተሩ ለሚያካሔዱት እያንዳንዱ ግዳይ የሃምሳ ሚልዮን ዶላር ክፍያ ለመስጠት በመዋዋል ሲሆን በነሱ መርከብ ላይ ለሚደርስ ማንኛውም አይነት ጥቃት ሆነ ኪሳራ ሀላፊነትን ወስደዋል። ለዚህም ብለው

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ራሳቸውን ከማንኛውም ጥቃት ለመከላከል በጥንቃቄ ነበር ክትትላቸውን እያከናወኑ የነበሩት።

የመርከቡ ካፒቴንና ውስጣዊ እንቅስቃሴውን የሚቆጣጠሩት ሃያ አንድ ጣሊያናዊ ሰራተኞች ግን በባለቤቱ የተቀጠሩ ባለሞያዎች ናቸው። የመርከቡ ውጫዊ ይዞታ ሲታይ ለእቃ መጫኛነት የሚያገለግል መካከለኛ ግዝፈት ያለው ማጓጓዣ ቢመስልም በወለሎቹ በግዳግዳዎቹና ከአናቱ ላይ በስውር የተገጠሙ በኮምፒውተር ትዕዛዝ በመታገዝ የሚወጡና የሚገቡ አነስተኛ ሚሳኤል ማስወንጨፊያዎች ነበሩት።

ተፈላጊዎቹ መርከቦች በየትኛው ዓለማቀፋዊ የባህርና የውቅያኖስ ክልል ላይ እንደሆኑ ህዋ ላይ ከተሰቀለ ሳተላይት በሚቀበለው ምስልና መርከቦቹ ጉዞ በመጀመር ካለፉባቸው ጣቢያዎች አካባቢ ካሉት ሰዎቻቸው የስልክና የፋክስ መልዕክት ኒውዮርክ ሆኖ እየተቀበለ መረጃውን ለፒተር የሚያስተላልፍላቸው ካርል ማርጐት ነበር።

ጉዞ ከጀመሩ አንስቶ እያንዳንዱን ሁኔታ እየተቆጣጠረ ለፒተር በመገናኛ ራዲዮ የሚያስተላልፈው በኒውዮርክ ውስጥ በሚገኝ አንድ የስነ-ፈለክ የምርምር ጣቢያ ጋር በሚስጥር ከፍተኛ ገንዘብ ከፍሎ ባደረገው ስምምነት ምክንያት ነው።

ለጥቂት ደቂቃ ተቋርጦ የነበረው ግንኙነታቸው "አፍሮ ቡድን ሶስት....." በሚሉት የጥሪ ቃላቶች ቀጠለ።

"ካርል ቀጥል.... ምን አዲስ መረጃ አለ?" አለ ፒተር።

" ከኋላ እየተጓዘ ካለው ሁለተኛው መርከብ ጋር ያላችሁ ርቀት የአምስት ኪሎ ሜትር ብቻ ነው።"

"በአካባቢያችን ላይ ሌላ ጉዞ የሚያደርግ መርከብ መኖሩን ብትነግረኝ?"

"በስተምስራቅ አቅጣጫ ከናንተ አርባ አምስት ኪሎ ሜትር በመራቅ የሚጓዙ ሁለት መርከቦች መኖራቸውን ያሳያል።"

"አመሰግናለሁ....." ብሎት ራዲዮኑን ቦታው መለሰና ሰዓቱን አየ። ከለሊቱ ሰባት ከሃያ አምስት ብሏል።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

የሚጓዙበት የቀይ ባህር ክልል የነፋስም ሆነ የማዕበል ግፊት ስላልነበረው ከገመቱት በላይ በሆነ ፍጥነት ነበር የሚገሰግሱት። ሰማዩም ጥርት ብሎ የጨረቃን ግማሽ አካልና የነቁጥ ክዋክብት ብርቅርቅታን ያሳያል።

ጥቁር መስታውት የመሰለው ውሃውም የሚቀበለውን ብርሃን መልሶ እንደ አነስተኛ የውሃው ሞገድ አካሄድ በተለያዩ አቅጣጫዎች ያንፀባርቀዋል።

ፒተር በአሜሪካ ባህር ሀይል ውስጥ ሲሰራ ባካበተው ልምድ መሰረት ሰዓቱን እያየ ቆየና የሚፈልገው ላይ ሲደርስለት የመርከቡን የውስጥ መገናኛ ራዲዮ አነሳና ዋና ካፒቴኑን አስቀርቦ "በቀጣዮቹ ሃያ ደቂቃዎች ውስጥ ተፈፃሚ ይሆናል" አለው።

ካፒቴኑ አጠገቡ ወደነበሩት ረዳቶቹ ዞረና "የክፍል ኤ.ዜድ ሰራተኞች ቦታችሁን ያዙ" ሲል አዘዘ።

ስድስት ባለሞያዎች አስፈላጊውን ክንውን ወደሚካሔድበት ክፍል ውስጥ ገቡና ቦታቸውን በመያዝ የኮምፒውተ ቁልፎችን መነካካት ጀመሩ። በዚህ ጊዜ የርቀት ካሜራዎችና ሚላማ ውስጥ ማስገቢያ መነፅሮች ከተደበቁበት የመርከቡ ክፍል እንደ አንቴና ወደ ላይ እየተመዘዙ ወጡ።

በመርከቡ የግራና ቀኝ አካል ላይ በረቀቀ ጥበብ የተገጠሙት ሁለት የሚሳኤል ማስወንጨፊያ አፈሙዞች ከወለሉ ውስጥ በመውጣት በቀጫጭን ኤሌክትሮኒክስ ገመዶች አማካኝነት ወደሚታዘዙበት አቅጣጫ አነጣጠሩ።

በስዊዝ ቦይ በኩል አድርገው ወደ ደቡብ አቅጣጫ የግፅን የባህር ክልል በማለፍ በሱዳንና በሳውዲ አረቢያ መካከል ላይ የደረሱትና የጦር መሳሪያ የጫኑት ሁለቱ ግዙፍ መርከቦች ጉዞዋቸው አንዳች እንከን ያላረፈበት ሰላማዊ ነበር። አስጊ የነበሩትን ቀጠናዎች ያለ ችግር በማለፋቸው ካፒቴኑና ሌሎቹም የመከቦቹ አባላት ዘና ብለው እየተጫወቱ ጭነቱን እንዲያራግፉበት ወደ ታዘዙት ወደብ ለመድረስ የሰዓታት ጉዞ ብቻ ነበር የቀራቸው።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

አጥቂው መርከብ የሁለተኛው መርከብ ሙሉ ኢላማ ውስጥ መግባቱን በኮምፒውተሮቹ መስኮት ላይ በሚታዩት ምስሎች እንደተረጋገጠ ዋና ተቆጣጣሪው ለተኳሹ
"ቁልፍ አንድና ሁለትን አሰራ፡፡" ሲል አዘዘው፡፡

የታዘዘው ሰው ኮምፒውተሩን ለአምስት ሰከንድ ያህል በፈጣን ሂደት ቁልፎቹን ተጫናቸው፡፡ በስተግራ አካሉ ባለው አስወንጫፊ አፈሙዝ ሁለት ፍም የመሰሉ የሚሳኤል አረሮችን ሲተኩስ የመርከቡ አካል በንዝረት ተናጠ፡፡

ከሃያ ሰከንድ በማይልቅ ግስጋሴ ሁለቱም ተወንጫፊ ሚሳኤሎች የሁለተኛውን መርከብ አናት ቁልቁል ተላተሙና ከፍተኛ የሆነ ፍንዳታ ድምፆችን አሰሙ፡፡ ዳርቻ የሌለው የሚመስለው ባህሩ ግን የፍንዳታውን ድምፅ ውጦ አስቀረው፡፡ የተቀጣጠለው እሳት እየተስፋፋ ሂደና የጦር መሳሪያዎቹ የተቀመጡበት መጋዘን ጋር ሲደርስ ተከታታይ ፍንዳታዎች በማሰማት ቃጠሎው ተባባሰ፡፡ ከአስር ደቂቃ ቃጠሎ በኋላ መርከቡ ወደ ቀይ ባህር ወለል መዝቀጥ ጀመረ፡፡

ከፊት ሲገሰግስ የነበረው አንደኛው መርከብ ፍጥነቱን ጨምሮ ርቀቱን በማስፋት ጉዞ ቀጥሏል፡፡ ከኋላው እየተከሰተ ስላለው ሁኔታ ምንም መረጃ አልነበረውም፡፡

የመጀመሪያው መርከብ ሰምጦ ባህሩ ተመልሶ ወደ መጀመሪያው ዝምታ ሲዋጥ ኢላማው ወደ ሁለተኛው መርከብ ተነጣጠረ፡፡ በዛው ቅፅበት ከአዳኙ መርከብ ሁለት ሚሳኤሎች ተወነጨፉበት፡፡ እሱም በውስጡ ከነበሩት ሰዎች ጋር ለወሬ ነጋሪ አንድ እንኳ ሳይቀር እየተቃጠሉ ወደ ባህሩ ወለል በዝግታ መስመጥ ጀመሩ፡፡

በተሳካ ሁኔታ ግዳጁን የፈፀመችው መርከብ ማስወንጨፊዎቿንና የሚላማ መነፅሮቿን መልሳ ወደ አካሏ በመክተት የንግድ እቃ አመላላሽ መስላ ጉዞዋን ወደ መጣችበት አቅጣጫ ዞራ መመለስ ጀመረች፡፡

«««««««««« »»»»»»»»

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ናንጂንግ በተባለችው የቻይና ከተማ ተፈብርከው በሶስት መርከብ የተጫኑት የጦር መሳሪያዎች ተጓጉዘው እንዲራገፉ የታዘዘው በሶማሊያ በርበራ ወደብ ላይ ነው። ከዛም የአንዱ መርከብ ጭነት ለሚያበረክቱት አገልግሎት ሲባል ለአስተላላፊዎቹ የሶማሊያ አንጃዎች እንደ ክፍያ የሚሰጥ ሲሆን የሁለቱ ግን ሶማሊያን አቋርጠ ወደ ኢትዮጵያ ይዘልቅና ለደቡብ ህዝብ እና ለኦሮሞ ህዝቦች እንዲከፋፈል የታቀደ ነው።

ጉዞዋቸውን ከቻይና ባህር ጀምረው ወደ ሰላማዊ ውቅያኖስ አደረጉት። ከዛም ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመዞር ጠንከር ያሉትን የቁጥጥር ስፍራዎች በገንዘብ፤ እስከዚህ አስጊ ያልነበሩትንም በተጭበረበረ የሀሰት ሰነድ በማለፍ ህንድ ውቅያኖስ ክልል ላይ ገቡ።

በዚህ ወቅት የአፍሮኢዝም ቡድን ሶስት አባሎች የነበሩትና ከነርተር ተከፍለው ወደ ቻይና ያመሩት የተኮናተሩትን መርከብ በመያዝ የህንድ ውቅያኖስ ሰሜናዊ ዳርቻ በምትገኘው ሲሪላንካ አካባቢ በመድረስ ለመጠበቅ ነበር ሀሳባቸው።
በመሀከሉ ከኒውዮክ የሳተላይት ምስሎችን ከምድር ላይ እያነሳ የሚያሰተላልፍለት ካርል ማርጐት መልእክት መጣ።
"ቀጥል....."
"ሁለት መርከቦች ከማልዳየቭ ደሴት በስተሰሜን አቅጣጫ በምድር ወገብ መስመር ላይ 812.4 ፍሬም ውስጥ እየተጓዙ ናቸው።"
"ሶስተኛው መርከብስ?" ጠየቀ የቡድኑ መሪ።
"ከእይታ ውጭ ሆኖብናል። ምናልባት የቴክኒክ ችግር ገጥሞት ወደ አንዱ ወደብ ሳይጠጋ አልቀረም።"
"መልካም..... እንዳገኛችሁት አስተላልፉልኝ....." ብሎ የውስጥ መገናኛ ራዲዮኑን አነሳና ለዋናው ካፒቴን ትዕዛዝ አስተላለፈ። ፈጣኑን ክትትልም መረጃው በተሰጠበት አቅጣጫ ቀጠለ።

ከስድስት ሰዓታ ፈጣን ጉዞ በኋላ የተባለው ክልል ውስጥ ደረሱ። የሁለቱ መርከቦች ጉዞ አንዱ የሌላኛውን እይታ መቆጣጠር በሚያስችላቸው አጭር ርቀቶች መካከል ነበር። አብረው እየተጓዙ ስለነበሩ ሁለቱም ላይ እኩል ጥቃት መሰንዘር እንዳለበት ቢያምኑም የጥቃት ሰንዛሪዋ የማለሚያ መነፅሮች የተሟሉ ባለመሆናቸው አንዱ ከተመታ በኋላ ነበር ወደ ሌላኛው ማነጣጠር የሚችሉት።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ለአንድ ቀን ያህል በመካከላቸው ያለው ክፍተት ይሰፋ ይሆናል በማለት በርቀት እንዲከታተሏቸው አስደረገ፡፡ እንዳሰቡት የተመቻቸ ነገር ስላልተከሰተ ያለውን አማራጭ ለመጠቀም ተስማሙና በዚህ እለት እኩለ ሌሊት ላይ ከፊት የሚጓዘው መርከብ በመጀመሪያ እንዲመታ ወሰኑ፡፡

ውሳኔው በአመዛኙ የካፒቴኑን ፍላጐት ያስጠበቀ ሲሆን ያቀረበው ምክንያትም "……ሁለተኛው መርከብ በቅርበት ስላለ ካለ ችግር በፈጣን ሁኔታ ሊላማ ውስጥ አስገብተን ልንመታው እንችላለን" በማለቱ ነበር፡፡ ባልደረቦቹም ሀሳቡን ደገፉት፡፡ የአፍሮኢዝም ወኪሎች ምን ያህል ትክክል ሊሆን እንደሚችል ባያውቁትም ይህን በመሰለ ቦታና ሰዓት ላይ ብዙ መነታረክ አልፈለጉም፡፡
"መልካም..... ይሞከር....." አለ፡፡

ለተመቻቸ ጥቃት ስንዘራ የመረጡት የእኩለ ለሊት ሰዓት ሲደርስ አስፈላጊው ዝግጅት ተከናውኖ ተተኮሰበት፡፡ ከፊት ይጓዝ የነበረው መርከብ በተሳካ ሁኔታ ተመታ፡፡ ሁለተኛውን መርከብ ለመምታት የማለሚያ መሳሪያዎቹ አቅጣጫ መለወጥ ጀመሩ፡፡ ሁሉም ተከናውኖ ከመተኮሳቸው በፊት ከፊቱ በነበረው መርከብ ላይ የተካሄደውን ያየው የሁለተኛው መርከብ አዛዥ ከኋላቸው ባለው አጥቂ መርከብ ላይ አፀፋዊ ምላሽ እንዲሰጥ አስደረገ፡፡

ያስወነጨፉት አነስተኛ ሚሳኤል አጥቂውን መርከብ ሙሉ በሙሉ በማግኘት ፈንታ ከፊታቸው በቅርበት ውሃው ላይ ወድቆ ፈነዳ፡፡ ሆኖም ግን ከነዛሪው ንቅናቄው መጠነኛ ጉዳት እንዳገኛቸው አውቀው ነበር፡፡

የሁለተኛው ዙር ተኩስ ግን ከሁለቱም መርከቦች እኩል ተነሳ፡፡ ወደ አጥቂው መርከብ የተወነጨፈው ሚሳኤል ከፊቱ ላይ ደህና አድርጐ አገኘው ፡፡ የነሱ ሊላማ ግን የተሳካ ሆነና ከደቂቃዎች በኋላ መሳሪያ የጫነው መርከብ ሰምጦ በዕይታ ተሰወረ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

የጥቃት ሰንዛሪው መርከብ የአደጋ መብራትና ጩኸቱን በየክፍሎቹ ብልጭ ድርግም እያደረገ ማስተጋባት ቀጠለ። የመርከቡ ውጫዊ አካል ተቦድሶ ውሃ ማስገባት ጀምሯል።

የአፍሮኢዝም አባላቶችን ይመራ የነበረው ሰው ኒውዮርክ ካለው ሰዋቸው ጋር ተገናኝና እየሆነ ያለውን ገለፀለት። ከአንድ ሰዓት በኋላ መርከቧ ወደፊት እያዘነበለች ሄደች። ምንም ተስፋ እንደሌለ የተረዱት የመርከቡ ሰራተኞች የዋና መንሳፈፊያ እያጠለቁ ለመዝለል ተዘጋጁ። መርከቧ በፊቷ በኩል ሰርጦ የሚገባው የውቅያኖሱ ውሃ ወደ ታች እንድታዘቀዝቅ ሲጫናት ቁልቁል ወደ ጥልቀቱ መንሸራተት ጀመረች። ይሄኔ ሁሉም ነፍሱን ለማዳን ዘለሉ። መርከቧ ሰምጣ ስታበቃ አካባቢው ላይ ምንም እንዳልነበረ ሁሉ አና ሆነ።

ከትከሻቸው በላይ ብቅ ብቅ ያሉ ሰዎች ብቻ በድንጋጤ ሲንቦጫረቁ ይታያሉ።

ለሁለት ሰዓት ያህል ሳይበታተኑ ከአደጋ አዳኝ መርከቦችን ቢጠባበቁም ሳይደርሱላቸው ቀሩ። ውሃው በፊት ያልነበረ በርካታ አረፋን መስራት ጀምሯል።

ካፒቴኑ ከፍተኛ የሆነ ማዕበል ሊመጣ ሲል የሚጠቁም ምልክት መሆኑን ከዚህ ቀደም ባካበተው ልምድ አወቀና "መሞታችን ነው " አለ።

የተቻላቸውን ያህል በዋና ወደመሰላቸው ግምታዊ አቅጣጫ ለመጓዝ ታገሉ። ውሃው ዝቅተኛ ሞገድ መስራት ጀመረ። ቆየት ብሎም በዝቅተኛ ማዕበል መተካት ጀመረ። አሜሪካውያኑም ተዓምር ካልተፈጠረ እንደማይተርፉ ገባቸው። ዙሪያውን ሲያማትሩም የውሃው አስፈሪነት እያየለ መሄዱን አስተዋሉ።

"አፍሮኢዝም ግቡን ይመታል..... ለሱም ስኬት መስዋዕትነት የግድ ያስፈልጋል..... ከሰባ ሚልዮን ንፁሀን ኢትዮጵያዊ ህዝብ ፈንታ የኛ ሶስት ሰዎች መስዋእትነት ምንም ማለት አይደለም " አለ አንዱ አባል።

ከርቀት እንደ ተራራ ተቆልሎ እየተውዘገዘገ የሚመጣው አስፈሪ ማዕበል ታየ።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

‘እው.... የኛስ ሞት በውሃ ነው፡፡ ስንቱ ህፃናት እና እናቶች በእሳት ተጠብሰው ሊያልቁ ነበር.....’ ብሎ በህሊናው ለተራሱ ተናገረ፡፡

ማዕበሉ ደርሶባቸው ወደ ሰማይ ይዟቸው ተነሳና መልሶ በማውረድ በጥልቀት ዘፈቃቸው፡፡ ወደላይ ለመውጣት ተፍጨረጨሩ፡፡ ጉልበታቸው ተሟጠ ከጨርቅ የቀለሉ እስኪመስሉ ድረስ ውሃው ሽቅብ ቁልቁል እያረገ ቀለደባቸው፡፡

መዓበሉ ስራውን ቀጠለ፡፡ ለሶስት ሰዓታት ያህል ውቅያኖሱን ሲያምሰው በቆየው ከፍተኛ ማዕበል የመርከቡ ሰራተኞችን በሙሉ ገድሎ ሬሳቸውን እንደ ወረቀት ማንሳፈፍ ጀመረ፡፡

  

የማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

ምዕራፍ 56

በሰላሳ ደቂቃ ውስጥ አራት እድሜያቸው ገና ከሶስት ዓመት ያላለፉ ህፃናት እና ሌሎች አምስት በተለያዩ እድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሰዎች ጥቁር አምበሳ ሆስፒታል የድንገተኛ ህክምና መስጫ ክፍል ውስጥ ተጎተው እየተሰቃዩ ነበር። ለሚሰቃዩት ህመምተኞች ካሉበት አስጨናቂ ህመም እንዲያገግሙ በምሽቱ ተረኛ ሀኪሞች ህክምና እየተሰጣቸው ነበር።

ህፃናቱ በማያቋርጥ ተውከት ትኩሳትና የመንፈራገጥ ሁኔታ እየተሰቃዩ ሲሆን ትልልቆቹ ሰዎች የህፃናቱ ያህል ባይሆንም በአደገኛ ሁኔታ ላይ እንደሚገኙ ግን ያስታውቅባቸዋል። ሁሉም ታካሚዎች ሙሉ የላቦራቶሪ ምርመራ ከተደረገላቸው በኋላ በተገኘው ውጤት እጅግ የተደናገጡትና የተናደዱት ዶክተሮች ወደ አንድ ጥግ በመሰባሰብ መነጋገር ጀመሩ። በንግግራቸው መካከል ዋናውን ሀሳብ የያዘው ስጋት በመላው አገሪቷ ውስጥ ምን ያህል ህዝብ የተመሳሳይ አደጋ ስለባ እየሆነ እንዳለና ወደ ሆስፒታል እንኳ መድረስ ሳይችል ቀርቶ የስንት ሰው ህይወት በያንዳንዷ ሰከንድ እየተቀጠፈ እንዳለ መነጋገር ጀመሩ።

እነዚህ በአዲስ አበባ በተለያዩ አካባቢዎች ነዋሪ የሆኑት ሰዎች በደረሰባቸው ድንገተኛ ህመም ወደ ሆስፒታሉ ለመምጣት የተገደዱበት ምክንያት በተደረገላቸው የምርመራ ውጤት ላይ እንደተረጋገጠው ሁሉም ጊዜው ያለፈባቸው፤ በጤንነትና በህይወት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ መድኃኒቶችን ከተለያዩ የመድኃኒት መሸጫ ቤቶች ገዝተው የተጠቀሙ ነበሩ።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

በእርግጥ ዶክተሮቹ ሁሉም ህመምተኞች የተጠቀሙትን መድኃኒቶች ማሽጊያ ላይ እንዳነበቡት የአገልግሎት ጊዜያቸው እንዳላበቃ የሚገልፅ ቀን ያለበት ቢሆንም በመድኃኒቶቹ ላይ ባደረጉት ምርመራ ጊዜያቸው ማለፉን አረጋግጠዋል። ይህ እንዴት ሊሆን እንደቻለና ለተፈጠረው ችግርም ጎላፊነት ወስዶ ምላሽ የሚሰጥ መንግስታዊ አካል ባለመኖሩና ይህ ችግር በተደጋጋሚ እየተከሰተ እንዲሁም እየተስፋፋ በመሆኑ ምን ማድረግ እንዳለባቸው ነበር ግራ በመጋባት የሚወያዩት።

የሁሉንም ታካሚዎች ህይወት ለማትረፍ ያደረጉት ጥረት ሙሉ በሙሉ የተሳካ አልነበረም። የአንዲት ህፃን እና የአንድ አዛውንት ህይወት አለፈ። ሌሎቹን ግን መታደግ ቻሉ። የዚህን መድኃኒት ወደ አገር ውስጥ መግባት የሚያውቁና በማስገባታቸውም ቀላል ያልሆነ ገንዘብ ማፈስ የቻሉ የኢትዮጵያ ከፍተኛ ባለስልጣናት እጅ የነበረበት ሲሆን በተለይ በኢትዮ-ኤርትራ ፖለቲካና ድንበር ጉዳዮች ላይ የሚሰሩና ቁጥጥር የሚያደርጉት የወንጀሉ ዋና ተዋናዮች ነበሩ።

ይህ መድኃኒት ከፈረንሳይ ማርሴል ወደብ ላይ በመርከብ ተጭኖ ጉዞ ሲጀምር የዚህ መርከብ ጭነት ሊዊስ ወደ ኢትዮጵያ ካሰማራቸው ሌሎቹ መርከቦች በአንዳንድ ጥቃቅን እክሎች ምክንያት ትንሽ በመዘግየቱ ስለ ጉዞው የተሟላ ሪፖርት ገና ስላልተገኘና ስላልተመዘገበ በአፍሮኢዝም በተመሩት አባላት የሉዊስ እና የፒየር ቢሮ ሲፈተሽ ምንም መረጃ ባለመገኘቱ ካለ እክል ምፅዋ ወደብ ለመድረስ ቻለ።

እዛ ደርሶ ለሶስት ቀን ተረካቢዎችን ሲጠብቅ ቆይቶ ብቅ ያለ ባለመኖሩ ካፒቴኑ ሁኔታውን ከፈረንሳይ መድኃኒቱን ላስጫኑት ፋብሪካዎች አሳወቀ። ከነሱም በተላለፈለት ትእዛዝ መሰረት በአካባቢው ላይ ለቁጥጥር በሚዘዋወሩት በአሜሪካና ወይም በእስራኤል ሀይሎች ተገኝቶ ሌላ ጣጣ ውስጥ ከመግባታቸው በፊት ጭነቱን ለኤርትራውያኑ ባለስልጣናት በማሳወቅ ተነጋግረው በነፃ የተለገሳቸው መሆኑን በመግለፅ አስረክበዋቸው እንዲመለስ ታዘዘና የተባለውን ተፈፃሚ አደረገ።

የኤርትራ ባለስልጣኖቹ የተረከቡት መድኃኒት ጊዜው ሊያልፍ ጥቂት የቀረው አንዳንዱ እንደውም ያለፈበት መሆኑን ቢያውቁም የማሽጊያ ካርቶኖቹንና የአገልግሎት ወቅቱን የሚገልፀውን ፅሁፍ አጥፍቶ ገና ሶስት እና አምስት ዓመት የሚቀረው አስመስሎ በላዩ በማፃፍ ለህዝብ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ሊቸበችቡት እንደሚችሉ በማመን ከተረከቡዋቸው በኋላ ሰፊ ህዝብ እና ገበያ ወደሚገኝበት የኢትዮጵያ ግዛት ቢገባ በፍጥነት እንደሚሸጥ ስላወቁ በኢትዮጵያ ካሉት ወዳጆቻቸው ጋር በሚስጥር ተወያይተው ተማመኑ።

በጥቂት ጊዜ ውስጥ ማሽኒያው እና ቀኖቹ በሚፈለገው መልኩ ተስተካክለው በወታደራዊና ላለመፈተሽ ልዩ ፍቃድ ባላቸው የኢትዮጵያ ታርጋ በለጠፉ መኪናዎች በኢትዮ-ኤርትራ ድንበር በኩል በለሊት ተጉዘው እንዲገቡ ተደረገና ወደ አገሪቷ መዲና ገብተው እንዲሰራጩ ተደረገ። መኪናዎቹም ከሸያጩ የተገኘውን በርካታ ሚልዮን ብር እየጫኑ ወደ መጡበት እንዲመለሱ ተደረገ።

  

የማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ምዕራፍ 57

አብነት ካዛንቺስን አልፎ ኡራኤል ቤተ-ክርስቲያን አካባቢ ወደ ቴሌ መድኃኒያለም በሚገነጠለው አስፓልት በኩል ግማሽ ኪሎ ሜትር ያህል ተኪዶ በስተ-ግራ አቅጣጫ በሚገኝ መንደር በየወሩ አንድ መቶ ብር የሚከፍልባትን ጠባብ ቤት ተከራይቶ ከገባ ጥቂት ቀን ሆነው፡፡

የቤቷ ውስጣዊ ገፅታና ሁኔታ በፊት ከነበረበት ምንም የሚለያት ነገር የለም፡፡ ጆንስ ከሶስት ቀን በፊት ሰናይትንና ቤቲን ይዞ ሲሄድ እሱንም አብሮዋቸው ወደ አሜሪካ እንዲሄድ ድጋሜ ጠይቆት ነበር፡፡

የአብነት መልስ ግን ከበፊቱ የሚለይ አልሆነም፡፡ “ስፈልግ እነግርህና ትወስደኛለህ፡፡ አሁን መሳል አለብኝ፡፡ቢያንስ ውስጤ ያሉትን ሀሳቦች አውርጄና ህሊናዬን አርግቤ ነው የሚሻለኝ፡፡” በማለት በእምቢታው ፀንቶ ቀረ፡፡

ዕለቱ እሁድ ሲሆን የግንቦት ወር ወደ መጠናቀቁ ተቃርቧል፡፡ ክረምቱም በጊዜ ደርሻለሁ በሚል ስሜት ሰማዩን በየዕለቱ ማጠቋቆር ጀምሯል፡፡

አብነት ቀን ቤት ውሎ ምሽት ላይ ወጣ፡፡ የፀጉሩ መቆረጥ ለማያውቀው ቀርቶ ለሚያውቀው ሰው ሁሉ የሚያደናግር እንግዳ ገፅታ ሰጥቶታል፡፡ በየመንገድ ላይ የሚገጥሙት ፖሊሶችንም በድፍረት የሚያልፋቸው ፎቶውን አይተው ከሱ ጋር ለማመሳሰል የሚያስችላቸው ምንም ነገር ሊያገኙበት እንደማይችሉ በመረዳቱ ነው፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ወደ ካዛንቺስ የሚመልሰውን አስፓልት ይዞ በቀስታ መራመድ ጀመረ፡፡ ሰዓቱ ከምሽቱ ሁለት ከአርባ ደቂቃ ብሎዋል፡፡ ህሊናው ለሊት እየሰራ ስለሚያድረው ስዕል ጭብጥ በማሰብ ተወጥሯል፡፡
“ወንድም ዳቦ ግዛልን?”
ወደተጠየቀበት አቅጣጫ ሲዞር ሶስት የጐዳና ህይወት የሚመሩና እድሜያቸው ከአስራ አንድ ዓመት የማይልቅ ድሪቶ የለበሱ ታዳጊዎች ነበሩ፡፡
“ስንት ይበቃችኋል?” ከራሱ ሀሳብ እየወጣ ጠየቃቸው፡፡
“ያሰብከውን ስጠን አንተ” አንደኛው ፈጥኖ መለሰለት፡፡
አብነት እያወራቸው መቆየት ስለፈለገ ሌላ ጥያቄ ማቅረብ ሲዘጋጅ እይታው በኡራኤል ቤተ-ክርስቲያን ግንብ ስር ወደ ተኮለኮሉት ነዳያን የሰው ልጆች ላይ አረፈ፡፡

በርካቶቹ አብረውት ካሉት ወጣቶች ጋር እኩዮች ናቸው፡፡በየመካከሉ ግን ታዳጊዎች፣ ህፃናት፣ የጐለመሱና ያረጁም ይገኙበታል፡፡ የሚበዛው ግን ወጣቱ ነው፡፡
ግማሹ ሰብሰብ ብሎ በመቀመጥ ያወራል፡፡ ቀሪው ተኝቷል፡፡ በመበታተን ተኮራምተው የተቀመጡም አሉ.....
“ለመሆኑ የአዲስ አበባ ልጆች ናችሁ?” ጠየቃቸው አብነት፡፡
አንደኛው “አዎ” ሲል ሁለተኛው “እኔ ከአዋሳ ነው የመጣሁት እሱ ደግሞ....” አንጠልጥሎ የተወውን ሀሳብ ሶስተኛው ወጣት “ከባህር ዳር” አለው፡፡

“ለምንድነው ጐዳና የወጣችሁት?”
የሁለቱ ህፃናት መልሶች “ቤተሰቦቻችን በኤድስ ስለሞቱ ሊያኖረን የሚችል በማጣታችን” አሉት፡፡ የአዲስ አበባው ወጣት ግን “አባቴን አላውቀውም፡፡ እናቴ ግን የሰው ቤት ተቀጥራ ነው በሰራተኝነት የምትሰራው፡፡ ስለዚህ አብሬያት እንድኖር ፈቃደኛ አሰሪ ስላጣሁኝ ነው፡፡”
በየ ጥጋ ጥጉ ስር ያሉትን ታዳጊና ወጣቶች ሁሉ በህሊናው አሰባቸውና በሀዘን ተዋጠ፡፡ ‘ይህ ሁሉ ወጣት እንደ ትቢያ በየ ጐዳናው ተበትኖ ተስፋ የለሽ ህይወት ይገፋል’ ሲል አሰበ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

“በላ ግዛልን?” ጠየቀው የአዋሳው ልጅ፡፡
“እገዛላችኋለው፡፡”
መስቀለኛውን መብራት ከመሻገራቸው በፊት “የአራዳ ልጅ ሰብሰብ በል *ቡሌ ቡሌ ከች ብሏል!”
ድምፁን ከፍ አድርጐ ወደተናገረው ወጣት ዞረው አዩ፡፡ በትልቅ ኘላስቲክ ከረጢት ሞልቶ ያንጠለጠለውን የሆቴል ቤት ትርፍራፊ ምግብ ይዞ ወደ ቤተ-ክርስቲያኑ አጥር ጥግ ስር እየሮጠ ድጋሜ ጮክ ባለ ድምፅ ተናገረ፡፡

“ቡሌ መጥቷል ሳያልቅብን እንድሄድ ስጠና?” አለው የአዲስ አበባው ወጣት፡፡
“አብረን እንሂድና እኔም ልብላ?” ጠየቃቸው አብነት፡፡
“ካልደበረህ ና!” አሉት የሚያሾፍ መስሏቸው በስላቅ፡፡
ምግቡ መሬት ላይ በተነጠፉ ሁለት ሰፋፊ ላስቲክ ላይ ተገለበጠና እኩል ተካፈለ፡፡
በአካባቢው የነበሩና ጥሪውን የሰሙ የጐዳና ላይ ህፃናት፣ ወጣት፣ ጐልማሳና አዛውንት ሁሉም በላስቲኮቹ ዙሪያ ከበው ተቀመጡ፡፡ ወድያውም እየተሻሙና እየተሳሳቁ መብላት ጀመሩ፡፡ አብነት እንደተቀመጠ በሀዘኔታ አያቸው፡፡
“ብላ እንጂ ታዲያ....” የአዋሳው አብነትን እያየው ተናገረ፡፡
እጁን ሰነዘረና ሁለቴ ደህና ጥቅሎችን እየተሻማ ጐረሰ፡፡ ወድያውም አፉ ውስጥ የምግብ ስሜት የሌለው ነገር ሲያኝክ ታወቀው፡፡ ቀስ ብሎ ሲያወጣው አገልግሎት ላይ የዋለ የሶፍት ጥቅልል ነበር፡፡ የጐረሰው ለመውጣት ሲተናነቀው አጠገቡ የነበረው ወጣትም ከአፉ ተመሳሳይ ሶፍት አውጥቶ በመወርወር ምንም እንዳልሆነ ሁሉ መብላቱን ቀጠለ፡፡
እሱም ቀስ ብሎ ጣለውና ያያቸው ጀመር፡፡ ‘ማነህ? ከየት መጣህ?ለምን በላህ.....’ የሚሉና መሰል ጥያቄዎችን ማንም ለማንም አያቀርብም፡፡ ሁሉም ይከብና በፍቅርና በአንድነት ይመገባል፡፡ ይሄኛው የዘረገፈው ምግብ ሳያልቅ ሌላ ወጣት ከየምግብ ቤቱ ለምኖ ያጠራቀመውን ይዞ መጣና ዘረገፈው፡፡ እሱንም በዛው ስሜት አጣጣሙት፡፡ ፍቅራቸው አስደሰተው፡፡ ዘረኝነት፣ ጐሰኝነት፣ አድልኦ፣

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ንቀት..... ብሎ ነገር አይታይባቸውም፡፡ ኢትዮጵያዊነት ፍንትው ብሎ ታየው፡፡ ቀጥሎም አንድ ትልቅ እውነታ ታወሰው

«.....እኔና ወንድሞቼ አለ በለዘብታ
ለራሱ እንዲያወራ የራሱን ሰሞታ
እኔና ወንድሞቼ ሁላችን....ሁላችን

ከባዶ አቁማዳ ነው የሚዛቅ ፍቅራችን
ይህ ነው አንድነታችን
ይህ ነው ባህላችን

.....»

የሚለው የኢትዮጵያዊው ባለቅኔ የደበበ ሰይፉ ውብ ስንኞች ታሰበውና እንባው በአይኖቹ ግጥም አሉ፡፡ ቀጠለ በሀሳብ

'የኢትዮጵያዊነት ፍቅር የጥቅምና የእከክልኝ ልከክልህ ዓይነት አይደለም.... አንዱ ሌላውን በኢትዮጵያዊነቱ ይወደዋል፡፡ ይሰዋለታል..... ወገኑን ለማኖር ሲል ጠላት ሆኖ በኢትዮጵያ ላይ ከመጣ አጥፊው ጋር አንገት ለአንገት ተናንቆ ይሞትለታል..... ድንቅ የሆነውና አቻ የሌለው ኢትዮጵያዊነት..... ዘመናትን ተሻግሮ እዚህ የደረሰ ታላቅ በረከት' አለ በውስጡ፡፡

በሌላ በኩል የነዚህ ህፃናት፣ ታዳጊዮችና ወጣቶች ህይወት ታሰበው፡፡ 'እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ምሁር፤ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሀብታም ሁሉም እንደ ደረጃው ስለነዚህ ትውልዶች ቀጣይ ህይወት መስተካከል እና ይቺን አገር ሰቅዞ ከያዛት የፖለቲካ ውጥንቅጥ የማላቀቅ ትልቅ ሀላፊነት አለበት፡፡ እንደ ልጆቹ ባይዝ ባይንከባከባቸውና ባያቅፋቸው እንኳ በአቅሙ ደጉሞና ረድቶ እንዲማሩ ማስቻል አለበት፡፡.....

'.....የሀብታሙ ደህንነት ተጠብቆና ተከብሮ መኖር የሚችለው የተጐሳቆሉ ወገኖቹን ህይወት ለማሻሻል ሲጥር ብቻ ነው፡፡..... ካለበዚያ በአውሬ የተከበበች ሚዳቋ ነው የሚሆነው፡፡ አንድም ተዘነጣጥሎ ይበላል፡፡ አልያም በስጋት ብቻ በራሱ ሞቶ ይገኛል፡፡.....' አለ ህሊናው፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ቀጠለ '....ይህ ተስፋ አስቆራጭ የድህነት ህይወት ከተባባሰ ማን በሰላም ወጥቶ ሊገባስ ይችላል?..... ማንስ ሰላማዊ ኑሮ አለኝ ማለት ይችላል.....? ልጆቹን በትልልቅ የዕውቀት ማዕድ ስፍራ በዓመት ሀምሳና ስልሳ ሺህ ብር እየከፈለ የሚያስተምር ሁሉ ጐዳና ላይ ህይወታቸው ከሚገፉት መካከል ለሁለት ሁለት ህፃናት፣ ታዳጊና ወጣት በየወሩ አርባ ሰላሳና ሃያ ብር እየከፈለ ቢያስተምር ቢያንስ ሶስት ትልልቅ ነገሮችን ማትረፍ በቻለ ነበር፡፡.....

'.....መጀመሪያ የህሊና እርካታ፡፡ ጥሩ ሰላምና እንቅልፍን፤ ቀጥሎ የአንድ ሰው ህይወትን ከጨለማ ወደ ብርሃን ለማምጣት በመቻሉ የዜግነት ግዴታውን እንዲወጣ ያስችለዋል፤ ሶስተኛ እየተበጠሰ ላለው የሀገር ተረካቢ ትውልድ ሰንሰለታማ ሂደት መጠገን ከምንም የማይስተካከል ትልቅ ስራን መስራት ያስችለዋል፡፡' አለ ለራሱ፡፡

ከበው ሲበሉ የነበሩት ተመግበው ከመጨረሳቸው በፊት ዥንጉርጉር ወታደራዊ ቀለም የተቀባ ላንድ ክሩዘር መኪና በፍጥነት ደርሶ ፍሬኑን በማንሸራተት አቆመ፡፡ በላዩ ሙሉ ትጥቅ የታጠቁ ሰባት ወታደሮችን ጭኗል፡፡ ገቢና ተቀምጦ ቡድኑን የሚመራው ምክትል መቶ አለቃ ወታደር "አታ ምንድነው እዛ ጋር ተበተን!" አለ በቁጣ፡፡
"እየበላን ነው" አለ አንዱ ታዳጊ በትህትና፡፡
"ዲንጋይ ብላና ተበተን!" ቁጣው እየናረ አዘዘ
" ጨርሰናል እኮ አንዶ..... "
ተናጋሪውን አላስጨረሰውም ከመኪናው ዘሎ ወረደና ክላሹን አቀባብሎ እየደገነባቸው ሲራመድ ሌሎቹም ወርደው ተከተሉትና ተመጋቢዎቹን ከበው ጭካኔ በተሞላው ሁኔታ በሰደፍ መቀጥቀጥ ጀመሩ፡፡

«««««««««« »»»»»»»»»»

ከሌሎቹ ትሻላለህ ተብሎ ወታደሮቹን የሚመራው ይህ ምክትል መቶ አለቃ፤ አይደለም እሱ እናቱ ራሷ በማታስታውሰው አንድ ወቅት ላይ በገምቦ ውሃ ቀድታ ስትመለስ ምንጭ ዳር ጠብቆ ጠልፎ ካገባት ሰው ወለደችው፡፡ ከዛ በኋላ እሱም ያደገው እዛው እናቱ የተጠለፈችበት አቅራቢያ በሚገኝ አንድ ጫካ ውስጥ ነው፡፡ ጫካውን በሚለማሰው ሾላና ኮሽም ምክንያት ይወደዋል፡፡ የሾላና የኮሽም ዛፎቹን ግን የበለጠ ይወዳቸዋል፡፡ ብዙውን ሰዓት ብቸኝነቱን የሚጋሩት ዝንጀሮዎች ስነሆኑ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

እነሱንም ይወዳቸዋል። ግን ሾላና ኮሽሙን ሲበሉበት ከደረሰባቸው ወድያው ጠላትነት በመካከላቸው ይፈጠራል።

ከዛም በወንጭፉ ውስጥ የተጠረቡ ጥቁር አለቶቹን እየከተተ ወርውሮ በመምታት ያባራቸዋል። ዝንጀሮዎቹ በሚያርፍባቸው ምት ምክንያት የሚያሰሙት የስቃይ ማጓራት ያስፈነድቀዋል። ከዛም የለቀቁለትን ሾላን በሚያህል ግዙፍ ዛፍ ላይ ይወጣና ብቻውን ከፍሬው ሲበላ ይውላል። ከዛ ሲወርድ ደግሞ ኮሽም ለቅሞ በጉያው በማቀፍ ወደ ቤቱ ይመለሳል።

ይህ ምክትል መቶ አለቃ ተወልዶ እዚህ እስከደረሰበት እድሜው ድረስ የሚኖርባት ፕላኔት ጠፍጣፋ ትሁን ሸራፋ ጨርማዳ ትሁን ቀዳዳ ምንም የሚያውቀው ነገር የለም። በኡዞን መሳሳት ምክንያት የሰሜን እና የደቡብ ግግር በረዶዎች መቅለጥን ተከትሎ በተከሰተው የሙቀት መጨመር ሳቢያ ዝናብ በመጥፋቱ የራሱ አከባቢ ገበሬዎች ተግተው ቢያርሱም እንኳ ምርት ማጨድ አቅቷቸው በረሀብ ባስ ሲልም በጠኔ እያለቁ መሆናቸውን አያውቅም። ከአጎቶቹና ከአክስቶቹ እንዲሁም ከጎረቤቶቻቸው መካከል በርካታ ሰዎች ወደ አዲስ አበባ ከተማ ተጉዘው አፄ ምኒልክ ለዓምልኮ ለምስጋናና ለዝማሬ ባሳነፁት ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ-ክርስቲያን ዙሪያ ለልመና መዳረጋቸውን አያውቅም። የሱ የሾላና የኮሽም ዛፍ በህይወት እስካሉ ድረስ ስለሌላው አስቦ አያውቅም።

ሌላው አስገራሚ ጉዳይ የሱ የሾላ ዛፍ የበቀለበት ግዙፍ እና ጥቅጥቅ ያለ ደን ከጥቂት ወራት በፊት «የመንግስት አማፂያን መሸሸጊያ ስፍራ ነው » ተብሎ መንግስት ራሱ በስውር ባሰማራቸው ሰዎች አማካኝነት በሚስጥር በተለኮሰ እሳት ሳቢያ ግማሹ ደን እንዲቃጠል መደረጉን አያውቅም። በሰፊው ደን ውስጥ እንደልባቸው ተራብተው ይኖሩ የነበሩት የዱር እንስሳትና አእዋፍት ግማሽ ያህሉ ደን ስለተቃጠለባቸው ወደ ተረፈው አካባቢ ስለሸሹ ደኑ በእጥፍ እየተራቆተ እንደሆነ አያውቅም። የሱ የሾላና የኮሽም ዛፎች እንኳ እንደበፊቱ የተትረፈረፈ ፍሬ ለመስጠት በመቸገራቸው አብዛኛውን ጊዜ ለምን ያልበሰለ ፍሬያቸውን እየበላ እንደሚመለስ አያውቀውም። ከደኑ መራቆት ጋር ተያይዞ እናቱ የተጠለፈችበት የምንጭ ውሃ ማመንጨቱን ከግማሽ በላይ መቀነሱን አያውቅም። የውሃው መቀነስ በአከባቢው ነዋሪ ላይ ባስከሰተው ሽሚያ ምክንያት በሚነሱ ፀቦች ሶስት ሰዎች መሞታቸውንና የሱም እናት ሁለት ጊዜ እንደተፈነከተች አስቦት አያውቅም።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

እንደውም ምንጩ ሙሉ በሙሉ ከደረቀ በጊቢያችን ውስጥ በሚኖረን ቧንቧ ውሃ መጠጣት እንችላለን ሲል ይመኛል። የቧንቧ ውሃ በጊቢያቸው ውስጥ እንዲኖር ግን እንደ አገር ማሰብ እና እንደ አገር ማስተዳደር የሚችል መንግስት መኖር እንዳለበት አያውቅም። ብቻ በምኞቱ አንድ ቀን ማለዳ ከእንቅልፉ ነቅቶ እያዛጋ መዝጊያ አልባ የሆነች ደሳሳ ጎጆ ቤታቸው በር ላይ የቆመውን ብረት ምጣድ ገፍቶ ሲወጣ ቧንቧ በጊቢያቸው ውስጥ እንደ ሾላ ዛፍ ከመሬት ውስጥ በቅሎ የሚገኝ ይመስለዋል። ቅዠታዊ ምኞት እንደተጠናወተው ግን አያውቅም።

አንድ ቀን የስራ ማስታወቂያ ወጣና ለስራው ከብቁ በላይ የሆነ ብቃት አለህ ተብሎ በአከባቢው አስተዳደር ተመለመለ። ተወሰደና «ሰለጠነ» ስልጠናው ጠመንጃ መተኮስ ነው። ስልጠናው ሲያልቅ «ልዩ ችሎታ አለህ» ተብሎ የአዲስ አበባውን ቤተ-መንግስት እንዲጠብቅ ከተላኩት ብጤዎቹ አንዱ ሆነ። ከጫካ ዛፎች ዝንጀሮ ጥበቃነት ወደ ቤተ መንግስቱ ጫካ «መንግስት» ጠባቂነት ሲዘዋወር ለሱ ከስልጣን ሁሉ በላይ የሆነ ስልጣን እንደተሰጠው እንዲሰማው ተደርጎ በአለቆቹ የፖለቲካ ስብከት ተሞላ።

በእርግጥ ወታደር ከሆነ በኋላ የኢትዮጵያ ባንዲራ ቀለማት «አረንጓዴ ቢጫና ቀይ» መሆኑን ለይቷል እንጂ ይህ ባንዲራ ስላለው ታላቅና የከበረ ትርጉምና ታሪክ ምንም የሚያውቀው ነገር የለም። ለተቀጠረበት የስራ ዘርፍ በአለቆቹ «በቂ እውቀት» እንዳለው «ስለተመሰከረለት» ሌላ እውቀት እንዲኖረው አይፈልግም። እንደውም ቀሪውን የኢትዮጵያ ህዝብ «ዲያፍንታም ነው» ብሎ ያስባል። ለዚህ እምነቱ ትክክለኛነት ማመሳከሪያ ሆኖ ከአለቆቹ የሚቀርብለትም አልፎ አልፎ በህዝብ የሚደረጉ ሰላማዊ ሰልፎችና የመብት ጥያቄዎች ናቸው። ይህ የህዝብ ሰልፍ እና የመብት ጥያቄ ግን ለመላው የአገሪቷ ህዝብ የእኩልነት የደህንነት የፍትህ ጥያቄና የዜግነት መብት መሆኑን አያውቅም። ህዝቡ በሰላማዊ ሰልፉ ውስጥ ይዞት የሚወጣው ጥያቄ የሱ አጎትና አክስት ጎረቤቶቹና ወገኖቹ እሱም ራሱ ጭምር ከልመናና ከድህነት እንዲላቀቁ መብታቸውን ለማስከበር መሆኑን አያውቅም።

ይህንን የቀረፀበት የማሰልጠኛ ካምፑ ሀላፊ በበላይ አለቆቹ አድርግ ተብሎ የተነገረውን ብቻ እንዲያርግ ቀርፆ አሰለጠነው። ከዛም ወደ ስራ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ከተሰማራበት ዕለት ጀምሮ የአለቆቹ ተቃዋሚ የሆነ ሁሉ የሱ ጠላት ነው። እንደውም ብዙ ጊዜ ህዝቡ በጠቅላላ የአለቆቹ ታዋሚ መሆናቸውን ሲያይ የኢትዮጵያ ህዝብ በጠቅላላ የአገሪቷ ጠላት ነው ብሎ ይደመድምና ህዝቡን ሁሉ መፍጀት ወይም ከአገሪቷ ማባበር ካልተቻለም ሰባ ሚሊዮኑንም ህዝብ ሰብስቦ ማሰር ያምረዋል። በቃ ህዝቡ የክብሩና የማእረጉ ጠላት..... የሚወደው ጫካ ጠላት..... የዝንጀሮዎቹ ጠላት..... የሾላና የኮሽም ዛፎቹ ጠላት..... ይሆኑበትና የሱም ጥላቻ በህዝብ ላይ ይንራል። ታዲያ እነዚህን ጠላቶቹን ጥይት ተኩሶ ግንባራቸውን መበርቀስ ለሱ በወንጭፍ ድንጋይ ወርውሮ ዝንጀሮን ከመምታት እጅግ የቀለለና በአለቆቹ ፊትም እጅግ አስመስጋኝ ስራ ሆኖለታል። እንደ ቀልድ ተኩሶ ከሚገድላቸው አፍላ ወጣቶች መካከል አብዛኞቹ ለዚህች አገር ህመም መድኀኒት መሆናቸውን አያውቅም። ለዚህች አገር ልክፍት ጠበል ሆናቸውን አያውቅም። ለዚህች አገር ነቀርሳ ፈውስ መሆናቸውን አያውቅም። ራሱንና ወገኖቹን ቀስፎ ከያዛቸው ድንቁርና ሊያላቁለት ከውልደታቸው እስከ ህልፈታቸው ተብትቦ ካሸመደመዳቸው ድህነት ሊያስመልጡለት ቀን እና ሌት እውቀትን ፍለጋ በየ ዩኒቨርስቲውና ኮሌጁ የሚባትቱለት ቀጣይ ትውልዶች መሪ ኮከቦቹ መሆናቸውን እነሱ ላይ ከመተኮሱ በፊት ላንዲት አፍታ ቆም ብሎ አስቦት አያውቅም።

ለነገሩ ፀሀይና ንፋስ ቀንና ለሊት በጋና ክረምት እየተፈራረቀበት የቤተ-መንግስቱ ዲንጋይ አጥር ስር እንደ ዲንጋይ ቆሞ የሚጠብቃቸው ግለሰቦች ለኢትዮጵያና ስለ ኢትዮጵያዊነት ያላቸው አመለካከት እና ፍቅር ምን እንደሆነ አያውቅም። ሁለት ጊዜ ወደ ሩዋንዳ ቡሩንዲ ተጉዙ ሰላም ማስጠበቅ ላይ ሲሳተፍ የተባበሩት መንግስታት ለዛ አደገኛ ግዳጅ ለሱና ለባላደረቦቹ በዶላር የከፈላቸውን በርካታ ገንዘብ አለቆቹ ወስደው የግል ካዝናቸው ውስጥ እንደከተቱት አያውቅም። እናትና ዘመዶቹ ለኪኒን መግዣ የሚያውሏት ተራ መጠን ያላት ገንዘብ አጥተው ከዓመት ዓመት በህመም እየቃተቱ ሲያልቁ አለቆቹ በሱ ዶላር ውስኪ እየተራጩና ኮረዳ እያማገጡ መሆናቸውን አያውቅም።

በቀጣይነት ሶማሊያ ሔዶ በሶማሊያ ግዛት ውስጥ ከሚገኙ የአገሬው ተላጆች ጋር ጦርነት እንዲገጥም ከተመለመሉት የመከላከያ ሰራዊት አባላት ውስጥ አንዱ መሆኑን አያውቅም። ይህን ግዳጅ ለኢትዮጵያ ደህንነት ሳይሆን ለአሜሪካ መንግስት ፍላጎት እና በቀል ሲባል በአለቆቹ ታዞ እንደሚያደርገው አያውቅም። እነሱ በአፀፈ፟ታው ከአሜሪካ መጠኑ የማይታወቅ ረብጣ ዶላር እንደሚቀበሉ አያውቅም። በማያውቀው አገር

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ላይ ለማያውቀው ግዳጅ ተታኩሶ በመውደቅ መቃብር እና ታሪክ አልባ ሆኖ እንደሚቀር አያውቅም... የማያውቃቸው ነገሮች አበዛዛቸውን ራሱ አያውቅም:: ባለማወቁ ውስጥ የሚያውቃቸውን ደመነፍሳዊ እውቀቱን እንደ ሀያል የእውቀት ባለቤት አድርጎ ራሱን እንዲቆጥር ስላመነ ገና ብዙ ማወቅ እንደሚገባው አያውቅም:: አያውቅም... አያውቅም... አያውቅም..... ሲያስፈራ!!!!

መጨረሻ ላይ እውነታውን ከሁሉም የከፋና አሳፋሪ የሚያደርገው ደግሞ ያለማወቁን ጭራሽ እንዳያውቅ ያነገተው ክላሽና የታጠቀው ሽጉጥ ህሊናውን ልቦናውን ነፍስያውን ሰብአዊ ተፈጥሮውን ማስተዋሉ ማሰቢያውን ጭምር አዳፍኖበታል:: ይብስ አደናቁሮለታል:: የጦር መሳሪያና ስልጣን መሀይማንና ደናቁርት እጅ ሲገባ ምን ያህል አጥፊ እነደሆነ በዚህ ወታደር እና በቢጤዎቹ እንዲሁም በኢ.ህ.አ.ዴ.ግ ሕ.ወ.ሀ.ት ባለስልጣናት የተረጋገጠ ሀቅ ሆኖ መታየች ችሏል:: የሚያሳዝነው ግን ይህንንም እሱም ሆነ እነሱ አያውቁትም:: ድንቁርና ጦር መሳሪያና ስልጣን ሲገጣጠሙ የሚያደርሱት ውድመት እኔ ነኝ ካለ ግዙፍ አሸባሪ ከሚያደርሰው ይበልጥ እጅግ የከፋ ጉዳትን ያስከትላል:: አሸባሪ ህንፃን ሊፈራርስ ችላል:: ደናቁራን መሳሪያና ስልጣን ሲገራጠሙ ግን አገር ትውልድ ማንነት ታሪክ ቅርስ የአገር ሀብት አንድነት ተያይዘው ይንኮታኮቱና ድህነት አገር አቀፍ ውርደት ጭካኔ ጥላቻ ሌብነት ዝርፊያ ልመና በሽታ ጠኔ ባለቤት አልባ አገር እና ሰብሳቢ አልባ ህዝብ ወይም አውሬያዊነት እና የአውሬ ኑሮ በአገር ላይ ተንሰራፍቶ ተደላድሎ እንደሚከትም አያውቅም::

ምግቡም ከኮሸም ወደ ኮሾሮ ተሻሽሎለታል:: አንዳንዴ ለበዓል ለበዓል ጥንጥዬዋ የቲማቲም ስልስ የምትታሸግበትን ጣሳ በምታክል ቆርቆሮ የታሸገ ወጥ (ዚግኒ) ይሰጠውና በሳንጃው ቀዶ ወጧን እንደ ውሃ ይጠጣታል::

ድሮ ለቅሞ በጉያው ስር በሚያቅፈው ኮሸም ፈንታም አሁን ክላሽ ይታቀፋል::

ይህ ምክትል መቶ አለቃና ቢጤዎቹ የህይውት ታሪካቸው እና እውቀታቸው ይችው ናትና ከዚህ ልቆ ማሰብም ሆነ መታሰብ አይችሉም::

«««««««««« »»»»»»»»»

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

በወታደሮቹ ሲደበደቡ የበነሩት ጎዳና ተዳዳሪዎች ምቱ ጋብ ሲልላቸው ተነስተው መበታተን ጀመሩ። ከመካከላቸው የተፈነከቱ፤ ያበጡ፤ የሚያነክሱ፤ በእድሜ ገፋ ያሉት መሄድ ያቃታቸውም ነበሩበት..... ወታደሮቹ ትልቅ ግዳይ የጣለ አምበሳ እይመስል እየተዝናኑ መኪናቸው ላይ ተጫጭነው ወደ ባምቢስ አቅጣጫ ጉዞ ቀጠሉ።

ሶስቱ ታዳጊዎች እና አብነት ባጋጣሚ በአንድ አቅጣጫ ስለነበር የሮጡት ወታደሮቹ ከሄዱ በኋላ ከየተወሸቁበት ጥጋ ጥግ በመውጣት ያረፈባቸውን ድብደባ ከመጢፍ ሳይቆጥሩ አብነትን ከበቡትና ምግብ ሲበሉበት የነካካቸውን ወጥ ድሪቶዋቸው ላይ እየጠረጉ "በል ስጠን" ጠየቀው የባህር ዳሩ።

ድፍን አምስት ብር አውጥቶ ሰጣቸው። በደስታ አፏጩ።

"የአራዳ ልጅ ነሽ እመብርሀንን..... እግዚያብሔር ይስጥሽ" አለው የአዲስ አበባው እውነተኛ በሆነ የክብር ስሜት።

"አሁን ወዴት ልትሂዱ ነው?"

"ቤንዚን ማደያ ሂደን የአንድ ብር ቤንዚን ጨርቅ ላይ እንዲያፈሱልን እናደርግና እንስበዋለን" አለ የአዋሳው።

"ለምን?"

"የለሊቱን ብርድ ስለማንችል ቤንዚን በመሳብ ነው የምንቋቋመው።" መለሰ የባህር ዳሩ።

ወድያው ዝናብ ማካፋት ጀመረ። አብነት ከዚህ በላይ ምንም ሊያደርግላቸው ባለመቻሉ አዘነ።

"አሁን የት ነው የምታድሩት?"

"ይሄ ክረምት ሲገባማ ማደሪያ የለንም። ዝናቡ ያሰቃየናል። ያለን አማራጭ አውቀን የሆነ ወንጀል በመስራት ከርቸሌ ገብተን ክረምቱን እዛ ማሳለፍ ነው።" የአዲስ አበባው ነበር።

"ማደሪያ ለማግኘት ስትሉ ነው ወንጀል ሰርታችሁ ከርቸሌ የምትገቡት!?" አብነት ተገርሞ ጠየቀ።

"አዎ....የአራዳ ልጅ በጠቅላላ ክረምትን ከርቸሌ ነው የሚያሳልፈው።" የጐዳና ላይ ተዳዳሪዎችን ማለቱ ነበር።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ቀጠለ “.....ዝናቡ መባስ ሲጀምር አንዱን ደብድበን ወይም የመኪና እቃ የምንፈታ አስመስለን እንያዝና እንገባለን፡፡” አለ አዲስ አበባው፡፡
“ሲይዟችሁ አይደበድቡዋችሁም?”
“ምን ታደርገዋለህ ታዲያ..... ሶስት ወር ሙሉ ዝናብ ከሚደበድብህና በብርድ ተሰቃይተህ ከምትሞት ለአንድ ሳምንት ፖሊስ ጣቢያ ውስጥ ተደብድበህ ለሶስት ወር ከርቸሌ መውረድ ይሻላል፡፡” አለ አዋሳው፡፡ እምባውን መቆጣጠር አልቻለም አብነት፡፡
“የፈለገ ነገር ቢደርስባቹ ግን አንድን እውነታ መርሳት የለባችሁም... ” ምን ሊለን ነው ብለው በዝምታ ማዳመጥ ጀመሩ
ቀጠለ “የፈለገውን ያህል በሰው ልጅ ተንኮል ብትንገላቱም ኢትዮጵያዊነታችሁን ግን ምንም ሊነጥቃችሁም ሆነ ማንም ሊሰጣችሁ መብት የለውም! ማንም! መንግስት ሆነ ሌላው ሁሉ፡፡ ቢያስፈራሩዋቹ ቢያስሯቹ ቢገሏቹ ጭምር ከነ ኢትዮጵያዊነታቹ ነው፡፡ የዚች ውድ አገር ውድ ልጆች ናቹ፡፡ በሉ ቻዎ.....” ብሎዋቸው የውስጡ ስሜት ከእልህ ጋር እየተናነቀውና የእንባውን ዘለላ ከጉንጩ ላይ እየጠረገ ወደ ቤቱ መመለስ ጀመረ፡፡ እነሱ ግን ከተናገረው ውስጥ አንድም ነገር አልገባቸውም ነበር፡፡ በተረበሸ ስሜት ቤት ደረሰ፡፡

ለስዕሉ ስራው የሚሆኑ ቁሳቁሶቹን አመቻቸና መስራት ሲጀምር ሲል መብራት ጠፋ፡፡ የመጣለት የስዕል ሀሳብ ደግሞ ካልወጣሁ እያለ ረፍት ሲነሳው ሁለት ቁራጭ ሻማ ለኩሶ ጠረጴዛው ላይ አቆማቸው፡፡
ከለሊቱ ሰባት ሰዓት እስከሚሆን ድረስ ሰራ ግን በስራው አልረካም፡፡ ረፍት ለማድረግ ወንበር ስቦ ተቀመጠ፡፡ በዛው ጭልጥ ያለ እንቅልፍ ይዞት ሄደ፡፡

ሻማዎቹ ነደው በማለቅ በቀለም የራሰውን ጠረጴዛና ቀለም ሲጠራርግባቸው የቆየባቸውን ብጥስጣሽ ጨርቆችን አያያዙት፡፡ ወድያውኑ የቀለም እቃዎቹ..... ቀጥሎ ለብሩሽ ማጠቢያ ብሎ የገዛውን የቤንዚን ጄሪካን..... በቀለጠው የጄሪካኑ አካል የሚፈሰው ቤንዚን እሳቱን በአንድ አፍታ በቤቱ ዙሪያ አዳረሰው፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

አብነት ከእንቅልፉ ሲባንን ክፍሉ በእሳትና በጭስ ታፍኖ ነበር፡፡ ደጋግሞ አሳለና ተነስቶ ወደ በሩ ለመሮጥ ሞከረ..... በሩ በየት አቅጣጫ እንደሆነ ጠፍቶት ሲደነባበር ወደ ሳንባው የገባው ጢስ አጥወለወለውና ራሱን ስቶ ወለሉ ላይ ተዘረረ፡፡

ጠባቧ ክፍል ምንም ሳይቀር ሁሉም በእሳት ተያያዘ፡፡ ለመጨረሻ ጊዜ ለመወራጨት ሞከረ.....

የመስፍን የሙት መንፈስ ሊቀበለው ከርቀት ፈገግ ብሎ ሲመጣ በነበልባሉ ውስጥ የሚታየው ይመስለዋል፡፡ ሁለት እጆቹን እንደ ክንፍ ዘርግቶዋቸዋል..... እንደተነፋፈቀ ሰው ተቃቀፉ፡፡.....

የሁሉም ነገር ፍፃሜ ሆነ፡፡

እጅግ ዘግይተው ያወቁት የአካባቢው ሰዎች ፋይዳ ያመጣ ተግባር አልከወኑም፡፡ እሳቱ በአስቸጋሪ ሁኔታ ከጠፋ በኋላ የቤቱ መሀከል ላይ የአብነት አካል በሚዘገንን ሁኔታ ተቃጥሎና ከስሎ ነበር፡፡

  

የማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ምዕራፍ 58

ጆንስ አዲስ አበባ ከገባበት ሁለት ቀን ቀድሞ ነበር በዋልተር የሚመራው ቡድን ወደ ፈረንሳይ ያመራው።።

ከኒውዮርክ የተነሳውና መቶ ሃምሳ ስድስት ሰው የጫነው ቦይንግ አውሮፕላን ፓሪስ ሲደርስ ሰዓቱ ከምሽቱ አስራ ሁለት ከሰላሳ ብሎ ነበር።።

የመንገዶችና የህንፃዎች ድምቀት የሚታየው ከፀሀይ ብርሃን ወደ መብራቶች ተለውጦ ነው።። ኒውዮርክ ሰማይ ጠቀስ በሆኑት ህንፃዎቿ ብዛት ከፓሪስ ብትልቅም ፓሪስ ደግሞ በስነ-ጥበብ ውበት እጅግ በረቀቀ ሁኔታ በተገነቡት ህንፃዎቿ ይበልጥ ውብና ማራኪ ነች።። ከዚህ ውጪ የስልጣኔው ጅረት በእኩል እየፈሰሰላቸው ስላለ አንዳቸው ከሌላኛው ለመመፃደቅ የሚያስችል የተለየ የዘመናዊነት ሚስጥር የላቸውም።።

በዕለቱ ምሽት ላይ ከኒውዮርክ ተነስቶ ፓሪስ በገባው ቦይንግ ውስጥ የአፍሮኢዝም አባል የሆኑና በዋልተር ዳግላስ የሚመሩ አስር ሰዎችን የያዘ ነበር።። ሁሉም ጥቁር አሜሪካውያን ናቸው።።
ከአየር መንገዱ እንደወጡ በሩ ላይ ይጠብቋቸው የነበሩትና ኑሮዋቸውን በፓሪስ ያደረጉ ሶስት ሰዎቻቸውን ተገናኙ።። ሁለት አስር አስር ሰው መጫን የሚችሉ ፎርድ መኪናዎችም ተዘጋጅተውላቸው ነበር።።
ጉዞውን ወደ ተቀበላቸው አንድ አባል መኖሪያ ቤት አደረጉ።። እንደደረሱም ጥቂት ረፍት ቀላል ምግብና ያልበዛ የፈረንሳይ ምርጥ ወይንን አጣጥመው ጨረሱ።። ወድያውም ወደ መጡበት ስራ ተገባ።።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

ዋልተር በፓሪስ ሁኔታዎችን አመቻችቶ እንዲጠብቀውና የበላይ ሀላፊነትን ወደ ወሰደው ሰው እያየ "ስለ ድርጅቱ አስፈላጊ መረጃዎችን ሰበሰብክ?" ጠየቀው፡፡
"አዎ.....ከአመሰራረቱ ጀምሮ እስከአሁን ድረስ ምን ሲሰራ እንደቆየ ይህ መዝገብ ያትታል" ብሎ አስጠጋለት፡፡ በርካታ ገፆች ነበሩት፡፡
ዋልተር ለደቂቃዎች ሲያገላብጠው ቆየና "መረጃን እያነፈነፈ የሚሸጠው ለፈረንሳይ መንግስት ብቻ ነው?"
"በመላው ዓለም ላይ ለሚቀጥረው አገርም ሆነ ግለሰብ....."
"ድርጅቱ የግል ነው የሽርክና?"
"ሉዊስ በተባለ ግለሰብ የተገዛ ነው፡፡"
"እሺ.....መጀመሪያ ባለቤቱን ማግኘት አለብን"
"ወደ መኖሪያ ቤቱ መሄድ ነዋ....."
"የት አካባቢ ነው?"
"በምዕራብ አቅጣጫ ከከተማው ወጣ ብሎ በተሰራው ቅንጡ አካባቢ ነው የሚኖረው፡፡"
"ስለመኖሪያ ቤቱ ሙሉ መረጃ አግኝተሀል?"
"ስለአካባቢው ብቻ ነው፡፡"
"ተጨማሪ መረጃ ማግኘት እፈልጋለሁ፡፡"
"በቤቱ አካባቢ አባሎችን ልከን እንዲያመጡልን እናድርጋ"
"ስለ አጠቃላዩ አሰራሩና ውስጣዊ ገፅታው ሳይቀር"
"ያን ያህል ሚስጥርማ በቀላሉ ማግኘት አይቻልም፡፡"
ዋልተር ለአምስት ደቂቃ ያህል በዝምታ ቆየና "አካባቢው የተሰራው መቼ ነው?"
"ቅርብ ነው.....ከሁለት ዓመት አይበልጠውም፡፡"
"በጣም ጥሩ፡፡ግንባታውን ያካሔደውን ተቋራጭ መስራቤት ታውቀዋለህ?"
"መፅሔቶች ላይ አድራሻውን ፈለግን ማግኘት እንችላለን፡፡" አለና ተነስቶ ሁለት የማስታወቂያ መፅሔቶችን ይዞ ተመለሰ፡፡ በሶስት ደቂቃ ውስጥ የተቋራጩ አድራሻ ተገኘ፡፡
"መኪና እንዲዘጋጅ እዘዝና አብረን እንሔዳለን" አለ ዋልተር፡፡
ከሃያ ደቂቃ በኋላ የተቋራጩ ቢሮ ያለበት ህንፃ ደረሱ፡፡ የማታ ተረኛ ሰራተኞች ግና መግባታቸው ስለነበረ ደንበኛን በአዲስ ስሜትና በጥሩ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ትህትና ነበር የሚያስተናግዱት፡፡ ዋልተር ወደ ዋናው ሀላፊ ቢሮ ገባ፡፡
“አረፍ ይበሉ.....” አለ ሀላፊው ከጠረጴዛው ፊት ለፊት ያሉት ወንበሮች ላይ እየጠቆመ፡፡
“ምን ልታዘዝ?”
“በፓሪስ ውስጥ ለመኖሪያነት የሚሆኑ የሃምሳ ቤቶችን ግንባታ በናንተ ተቋራጭ በኩል ለማሰራት ፈልገናል፡፡” አለው
“ይቻላል፡፡” መለሰ ሀላፊው በደስታ፡፡
“ስለሚነገቡት ቤቶች ይዘት ግን በቂ መረጃ ለማግኘት እንፈልጋለን፡፡”
“ኘላኖች በማየት መምረጥ ትችላለህ” ብሎ በፍጥነት ተነሳና በአቅራቢያው ከነበረ የመስታውት ቁም ሳጥን ውስጥ ሰባት ዓይነት የተለያዩ አሰራር ያላቸው ኘላኖችን ሰጠው፡፡
ዋልተር ማገላበጥ ሲጀምር ቀጠለ ሀላፊው “.....ከፈለጋችሁ ራሳችሁ በምትሰጡን ኘላን መሰረት መገንባት ይቻላል፡፡”
በመካከሉ ማየቱን አቋረጠና “የዛሬ ሁለት ዓመት አካባቢ በምዕራብ የከተማዋ ዳርቻ ላይ በሰራችኋቸው ቤቶች በጣም ስትደነቁ ሰምቻለሁ፡፡ የትኛው ነው ኘላኑ?” ጠየቀ ዋልተር፡፡
“አዎ....ምርጦች ናቸው፡፡” ሀላፊነው በሰማው ምስክርነት ኩራት ቢጤ እየዳዳው ኘላኑን መርጠ በማውጣት ለዕይታ አመቻቸለት፡፡
ግዙፍ የሆነ ቪላ ነበር፡፡ በንድፉ ላይ ሳሎኑ የመኝታ ክፍሎቹ ባኞው ማበሰያው.... ቁልጭ ብሎ ይታያል፡፡ በቀጣዩ ገፅ በሮችና መስኮቶች የት የት ላይ እንዳረፉ እና የስልክ የውሃ የመብራት መስመሮች ያለፉበትን አቅጣጫ በግልፅ ይጠቁማል፡፡
“በአካባቢው ላይ ያሉት ሁሉም ቤቶች ተመሳሳይ ናቸው?”ጠየቀ ዋልተር፡፡
“አዎ....”
“ጥሩ..... የሚወደድ ቤት ይመስላል.....”
አቋረጠውና “በጣም እንጂ”
“የኘላኑን ግልባጭ ማግኘት ብችል ሸሪኮቼን ለማሳመን ይረዳኛል፡፡”
“ልሰጥህ እችላለሁ፡፡”
ስለ ኮርኒሱና ግድግዳው ጠቃሚ ብሎ ያሰበውን ሁሉ ጠይቆ ከጨረሰ በኋላ “ለሃምሳ ቪላዎች የዋጋ ማቅረቢያ ይዘጋጅልኝ”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

የመጡበትን ጉዳይ ጨርሰው አመስግነውት ሲወጡ የተፈለገው መረጃ በተሟላ ሁኔታ እጃቸው ገብቶ ነበር። ወደቤት በመመለስ ላይ እያሉ ዋልተር ንድፉን ሲያጠና ቆየና አብረውት የመጡትን አባሎች ሰብስቦ የተግባር ክፍፍላቸውን አሳወቃቸው። ሁሉም አስፈላጊውን ትጥቅ በማዘጋጀት ተጠመዱ።

ለሊቱ ሊጋመስ አንድ ሰዓት ሲቀረው ጥቁር ቀለም ያለው ፎርድ መኪና ወደ ምዕራብ አቅጣጫ መክነፍ ጀመረ። በውስጡ ዋልተርን ጨምሮ ዘመናዊ የመገናኛ ራዲዮ፣ የጦር መሳሪያና ተጨማሪ ቁሳቁስ የታጠቁ ሰባት ሰዎችን ጭኗል።

ስፍራው ከከተማው ዳርቻ ላይ ነው የሚገኘው። ግርግርና ጫጫታ ስለሌለበት ለመኖሪያነት የተከለለ ቦታ መሆኑ ያስታውቃል።በሰፋፊ ይዞታ የታነፁት ተመሳሳይ ቪላዎች ይማርካሉ።

“ይሄኛዋ ነው።” አለ እየሾፈረ የነበረውና መረጃ እንዲያሰባስብ ተመድቦ የነበረው ፓሪስን አብጠርጥሮ የሚያውቃት አባል። የመኪናውን ፍጥነት አቀዝቅዞ እያቆመ።

አጥሩ በሰው ቁመት ልክ በተለያዩ ቅርፆች የተሰራ ዘርዛራ ብረት ነው። በሀያ ሁለት ሺህ ካሬ ሜትር ስፋት ያለው ጊቢ ዕለት ዕለት በሚስተካከሉ ሳሮችና አበቦች ተውቧል። አልፎ አልፎ ረጃጅም ዛፎችም ይገኙበታል።

ቤቱ ወደ ኋለኛው አጥር ጠጋ በማለት ፊቱን ወደ መንገዱ አዙሮ የተገነባ ሲሆን በስተግራው በኩል ሰፊ የዋና ገንዳ ተሰርቶለታል።

በቤቱ ዙሪያና በጊቢው ውስጥ የበሩት መብራቶች አልጠፉም።

ዋልተር ሁኔታውን ቃኝቶ ከኋላው ወደተቀመጡት ሰዎች ዞረና “የአደጋ ጩኸት የሚያሰሙ መሳሪያዎች በየቦታው ተገጥመዋል። በሮችና መስኮቶቹም በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ቁልፍ ነው ያላቸው። ስለዚህ በመጀመሪያ ማድረግ ያለብን የአደጋ ማስጠንቀቂያ ማሽኑ እንዳይጮህ ማበላሸት ነው። ከዛም የኤሌክትሪክ መስመሩን ማቋረጥ ” ብሎ ዋናው መስመር የሚያልፍበትን የግድግዳ ንድፍ የሚያሳየውን ወረቀት በመስጠት ሁለት በዚህ ስራ የተካኑ አባሎቹን አስቀድሞ ላካቸው።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ካለ ችግር አጥሩን ዘለው ገቡና በዛፎቹ መካከል እያቆራረጡ ከዕይታው እስኪሰወሩ ጠበቀ፡፡ ከዛም ድጋሜ ሌላ ንድፍ አውጥቶ ለሶስት ሰዎች እያሳየ “መብራቱ በጠፋበት ቅፅበት ትገባላችሁ” አላቸው፡፡

ሶስቱ ወደ ጊቢው አለፉና መብራቱ እስኪቋረጥ መጠበቅ ጀመሩ፡፡

የቤቱ በር መስኮትና ጣሪያ በአንድ ጣት ቢነካ እንኳ አካባቢውን የሚያናውጥ የአደጋ ጩኸት እንደሚፈጠር የሚያውቁት ሁለቱ ሰዎች ዋናው የኤሌክትሪክ መስመር የሚያልፍበትን ግድግዳና የሚጮኸው ማሽን የተገጠመበትን ቦታ በያዙት ፕላን እየተመሩ ለይተው አገኙት፡፡ አንደኛው በጀርባው ከያዘው ቦርሳ ውስጥ በጨረር ሀይል ማንኛውንም ነገሮች በቅፅበት ቆራርጦ ሚያወድም መሳሪያ አወጣና አብርቶት ወደሚፈልገው አቅጣጫ በማዞር መጠባበቂያውን ከፈተው፡፡

አረንጓዴ ቀለም ያለው ከፍተኛ እሳት መሳይ ጨረር ግድግዳው ላይ ማረፍ ሲጀምር የአደጋው ጩኸት ለመጮህ ሞከረ ግን ከማይክሮ ሰከንድ ባነሰ ቅፅበት ጨረሩ ግድግዳውን ሰርስሮ በማለፍ ማሽኑን አቀላለጠው፡፡ ቀጥሎም ወደ የኤሌክትሪኩ መስመር በማምራት አቅልጦ ስለበጣጠሰው ወዲያው ተቋረጠ፡፡

የመብራቱን መቋረጥ የሚጠብቁት ሰዎች ወደ ቪላው ፈጥነው ቀረቡና በገመድ እየተሳቡ ጣሪያው ላይ ወጡ፡፡ ጣሪያው ተገጣጣሚ በሆኑ አጫጭር ሩፍታይልስ የተሰራ ነበር፡፡ ሶስቱም ለመሹለኪያነት የሚበቃቸውን ያህል ሲያነሱ ኮርኒሱ ታየ፡፡

የጨለማ ውስጥ መመልከቻ መነፅራቸውን አጠለቁና በወጡበት ገመድ እየተንሸራተቱ ኮርኒሱን ደርምሰውት ገቡ፡፡
አንደኛው ሰው ሳሎን ሁለተኛው ሰው የሉዊስ መኝታ ክፍል ሶስተኛው ሰው ባኞ ቤት ውስጥ ነበር ያረፉት፡፡

በዛ ወቅት ውስጥ ሉዊስ ፈፅሞ ባልተለመደው የመብራት መጥፋት ሁኔታ ግራ ተጋብቶ ለሚመለከተው መስራቤት በስልክ ለማሳወቅ ከባኞው ቤት እየወጣ ነበር፡፡

በዘመናዊው ባኞ ቤት ሰፊ ቻኩዚ ገንዳ ውስጥ ገላውን እያጠቡትና እያዋዙ በወሲብ ሲያጫውቱት የነበሩት ሶስት የዕለቱ አዲስ የፓሪስ ሴተኛ አዳሪዎች ግን በሁኔታው ተደስተው በጨለማው ውስጥ ውሃውን

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

እየተረጫጩ እንደ ህፃን እየተሯሯጡና እየተንጫጩ ሳሉ ነው በኮርኒሱ በኩል አስደንጋጭ ግዙፍ አካል ድንገት የወረደባቸው፡፡

ወድያው ጠባቧን ክፍል በጩኸት አናወጧት፡፡ ግን በጥብቅ ግንባታ የተሰራው ግድግዳ ድምፅቸውን እዛው ውጠ አስቀረው፡፡

ዋልተር ሰዓቱን አየና ከመኪናው በመውረድ በእጥሩ ላይ ዘሎ ገባ ወደ ቪላው ዋና በር አመራና ሲደርስ ቁልፉ አካባቢ ደጋግሞ ድምፅ ማፈኛ በተገጠመለት መሳሪያው ተኩሶ በማላቀቅ ከፍቶ ገባ፡፡

አባሎቹ ሉዊስን የሳሎኑ ወለል ላይ አምበርክከውት እየጠበቁት ነበር፡፡ ሴቶቹን እዛው እንዳሉ አስፈራርተው ዝም በማሰኘት በሩን ዘግተውባቸዋል፡፡

“ክቡር ሉዊስ በቀላሉ ልናገኝህ ስለቻልን እድለኞች ነን” አለው ዋልተር፡፡

“ምንድነው የምትፈልጉት?” በፍርሃት እየተናጠ ጠየቃቸው፡፡

“በኢትዮጵያ ላይ ስላለው ኘሮጀክትህ የምናውቅ ቢሆንም ጥቂት መረጃዎችን ጨምርልን እስኪ.....”

“ምንድነው ኢትዮጵያ ማለት?”

“የተረት ርዕስ!” አለው በስላቅ

“አትቀልዱ!” የተቆጣ ለመምሰው ሞከረ፡፡

“እሺ የቀልዱ ርዕስ ይሁንልሃ.....”

ሁሉም ፊታቸውን በጥቁር ጭምብል ስለሸፈኑት ከቤቱ ጨለማነት ጋር ተዳምሮ በቤቱ መስታውት አልፎ በሚገባው የውጭ የምሽቱ ብርሀን ጭላንጭል ሊያሳየው የሚያስችለውን ያህል ብቻ ነበር ሊያያቸው የቻለው፡፡ ከግራና ከቀኙ ከኋላው መሳሪያ ተደግኖበታል፡፡ ዋልተር ፊቱ ይንጐራደዳል፡፡ እሱም ሽጉጡን ይዟል፡፡ ሉዊስ ፍርሃቱ አየለበት፡፡ ፈጣን ጭንቅላቱ ሚሸሸበት፡፡ አፉ ላይ እንደመጣለት መናገር ጀመረ፡፡ “ምንድነው የምትፈለጉት.....ገንዘብ?”

“እናመሰግናለን.... አንድ ቢልዮን ዶላር ከከፈልከን እኮ ገና ሳምንት አልሞላንም፡፡”

ቆሌው ግፍጉ አለ፡፡ ጉሮሮው ጠባ ምራቅ አላወርድ አለችው፡፡

“ስ...ለምን... እንደ...ምታወሩ.... አላውቅም”

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ዋልተር ተጠጋውና በሽጉጡ ሰደፍ የክንድና ትከሻው መጋጠሚያ አጥንት ላይ ቁልቁል አጮነው፡፡
“አ....” የሲቃ ድምፅ አሰማና “.....ልትገድሉኝ.....ነ....ው.....?”
“ሞተህ መነሳት ብትችል ሁሉ ድጋሜ እንገድልህ ነበር፡፡”
“ምንድነው....የም...ት...ትፈልጉት....እሺ.....”
“ስለ ኢትዮጵያው እቅድህ ሙሉ መረጃ እንፈልጋለን፡፡ ከጮን ለስራው እገዛ ሲያደርጉልህ የነሩትን መንግታቶችና ድርጅቶች እነማን ናቸው?..... ስራውንስ ከማን ጋር ነው ስትሰራ የቆየኸው?”

ሉዊስ በተጠናቀቀ ጉዳይ ላይ እየካደ ስቃዩን ከማብዛት ውጪ ማምለጥ የሚያስችለው ነገር እንደሌለው መረዳት ጀመረ፡፡ ቢሆንም ግን የአውሮፓ ኢስያና አሜሪካ መንግስታቶች እጅ ለሱም ቢሆን ግልፅ ባላደረጉለት መንገድ በጉዳዩ ተሳታፊ እንደነበሩ መናገር ስላልፈለገ “በራሴ ገንዘብ ነው ኘሮጀክቱን.... ማስፈፀም የጀመርኩት” አለ
“ሉዊስ እንዳትሞኝ፡፡ መረጃ አለኝ.....” ቀጠለ ዋልተር እያፈጠጠበት “ከአንድ ዓመት በፊት በአንተ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ውስጥ ተቀማጭ የነበረው ገንዘብ በአሜሪካ ዶላር ሲለወጥ ከሰባት መቶ ሺህ አይበልጥም ነበር፡፡ .....አስር ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ግን ከስድስት ቢልየን ዶላር በላይ ገቢ እንደነበረህ ነው የሚገልፀው፡፡ ይህ ገንዘብ ከየት መጣ? ለምን ዓላማ መጣ?”

ሉዊስ ወደየትም ሊያፈናፍን የሚያስችለውን ክፍተት አጣ፡፡ ተስፋ በቆረጠ ስሜት የእቅዱን ሀሳብ ከማፍለቅ ጀምሮ አሁን ያለበት ድረስ ያለውን ታሪክ ሽራፊ ሳያስቀር ዘከዘከለት፡፡
“ እንዲሁም ስለተጫኑት መሳሪያዎች ሙሉ መረጃ እንፈልጋለን! ” አለ ዋልተር፡፡
ነግሮት ሲጨርስ በጥላቻ እያየው “ሰላም በአፍሪካ ምድር ልክ እንደ አድማስ ሲቀርቧት የምትሸሽ ሲጠጓት የምትርቅ ምትሀት እንድትሆን ያደረጋችሁባት እናንተ ናችሁ..... ገፀ ነጭ ልበ ጥቁር” አለና ሽጉጡን ደግኖበት በውስጥ ያለው ጥይት እስኪያልቅ ድረስ አካሉ ላይ አርከፈከፈበት፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ቤቱን ሲፈትሹ ዋልተር ከንባብ ክፍሉ ውስጥ በራሱ በሊዊስ መፃፍ የተጀመረ ገና አራት ምእራፍ ድረስ ብቻ የተፃፈለት የመፅሐፍ ረቂቅ አገኘ። በእጅ ባትሪ እየታገዘ ከመጀመሪያው መስመሮች ላይ ያሉትን ፅሁፎች ማንበብ ሲጀምር « ወንጀል ማለት የቅጣት ህግ የወጣለት ደንብ መተላለፍ ሲሆን ፖለቲካ ደግሞ የቅጣት ህግ የሌለው ረቂቅ ወንጀል ማለት ነው።» የሚለውን አነበበና ለብቻው ሳቀ።

ፒየርን ተከታትለው በማግኘት የሚታዘዙትን እስኪፈፅሙ ድረስ እንዲጠብቁ የተከፈሉት ሁለተኛ ቡድኖች ከአስራ አምስት ደቂቃ በኋላ የሚገኝበትን የምሽት ጭፈራ ቤት አስታወቁና አፍነው እንዲያመጡት ታዘዙ።

ከግማሽ ሰዓት በኋላ ፒየር ሽንቱን ለመሸናት ወደ መፀዳጃ ሲያመራ ለሊቱን አብራው ልታሳልፍ ፈቃደኛ ሆና ስላገኛት አዲት ሞዴሊስት ውበት እያሰበ ነበር። በመፀዳጃ ቤቱ የጠበቀው ድንገተኛ ውርጅብኝ ግን በጀርባው በኩል ደብቆ የያዘውን ሽጉጥ እንዲጠቀምበት የሚያስችል ፋታ እንኳ አልሰጠውም። በርካታ የተቀባበሉ ሽጉጦች በዙሪያው ተነጣጥረዋል። የራሱ የሉዊስ ቤት አምጥተው ዋልተር ፊት አንበረከኩት።

አንደኛው አባል "ከሉዊስ የተላከልህ ነው ጊዜ ላለማባከን ምልክት ይሁንህ ብሏል!" አለውና እያሾፈ የያዘውን እቃ ሰጠው። እየቀለደ ነው ወይስ አይደለም በሚሉት ስሜቶች እየተበሳጨ ተቀብሎት ጥቅሉን ሲከፍተው በጥይት የተበሳሳና በደም የተጨማለቀው የሉዊስ ፒጃማ ወለሉ ላይ ወደቀ።
"ምንድነው ይሄ!?" ልብሱ ላይ እያፈጠጠ ጠየቀና በጨለማው ድንግዝግዝ ዙሪያውን ሲቃኝ የሉዊስን በድን ጥግ ላይ ተዘርሮ አየው።
"መልስ እንጂ ጠይቅ አልተባልክም!" ቀጠለ ዋልተር ጭካኔ የተሞላበት ገፅታ ፊቱ ላይ እየታየ ".....በኢትዮጵያ ላይ ስላለው እቅዳችሁ ንገረኝ!?"
"እኔ....እኔ..... እሱን ስራ....ሲ...ጀመር.... አንስቶ.... እስካ....ሁን ድረስ..... አላመንኩ....በትም ነ....በር...." አለ በተቆራረጠ ንግግር።
ዋልተር እየሳቀ "ባለማመን እውነታ ውስጥ ህሊናውን በሰው ጭንቅላትና አስተሳሰብ ስር የሚጥል ሰው ደደብ ስለሆነ ዋጋውን ሊቀበል ይገባዋላ...."

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

“አን...ዳንድ....ጊዜም እ...ኮ ባለማ...መን ስሜትህ ውስ...ጥ እንድታ....ምን የምትግደድበት.....ሁኔ....ታ ይፈ...ጥራል፡፡”
“እንዴት ሆኖ ባክህ!”
“ለምሳሌ....እኔ ይህን ስራ ለመ...ስራት የተ...ስማማሁበት ከፍተ....ኛ የገንዘብ ጥቅም..... አሳሳቶኝ ነው.....እንጂ እቅዱን....አል....ደግፈውም ነበር፡፡”
“ራስ ወዳድነትህ ማሰብ እስኪሳንህ ድረስ ደፍኖሀል፡፡ ለአንድ ራስህ ጥቅም ብለህ የሰባ ሚልየን ንፁህ ህዝቦች ህይወት ላይ የጦርነት ዝናብ እንዲዘንብ መሳተፍ ነበረብህ?”
“አይ.....አይደለም....”
ዋልተር አቋረጠውና “አንተ እንደውም ከሉዊስ የበለጠ ቅጣት ያስፈልግህ ነበር፡፡” አለውና የሽጉጡን ቃታ ሳበው፡፡አንጐልና ደሙ ተደባልቆ መሬቱ ላይ መሸኳለል ጀመረ፡፡

«««««««««««« »»»»»»»»»»»»

ለ “ለሉዊስ ወኪሎች” ተቋም ተቀጥሮ የሚሰራው የጥበቃ ሰራተኛ አይኖቹን ከፊት ለፊቱ ባሉት ስድስት የቴሌቪዥን መስኮቶች ላይ ተክሎ የህንፃውን ዙሪያ፣ የመውጫ ደረጃዎችንና የአሳንሰሩን እንቅስቃሴ በንቃት ይጠብቅ ነበር፡፡
አንድ ችግር ካለ ተጭኖ በመያዝ ብቻ ከፖሊስ ጋር የሚገናኝበት የመጥሪያ መሳሪያ በጠረጴዛው ስር ተቀምጦለታል፡፡
በውስጥ የቢሮ ክፍሎችም ከተቀጠሩ አጭር ወራት የሆናቸው ሶስት ሰራተኞች እንደየ ሙያቸው ስራቸውን በማከናወን ላይ ነበሩ፡፡ ሰዓቱ ወደ እኩለ ለሊት ተቃርቧል፡፡
ጠባቂው ሁለት ካፖርት የለበሱ ሰዎች የህንፃው መግቢያ ጋር ከታክሲ ወርደው ሲገቡ አያቸው፡፡ የምስል ማቅረቢያውን ተጫነና ገፅታቸውን ማየት ጀመረ፡፡ ሁለቱም ነጮች ናቸው፡፡ ወርቃማ ፀጉራቸውም በጆሮ ግንድና በግምባራቸው ላይ ተደፍቷል፡፡ እድሜያቸውም በሰል ያሉ ይመስላሉ፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

የድምፅ መሳቢያውን ከፈተና የሚነጋገሩትን ለመስማት ሞከረ፡፡በፈረንሳይኛ ቋንቋ በሉዊስ ድርጅት በኩል ስለሚያሰሩት ትልቅ ስራ ነው የሚያወሩት፡፡

‘ደንበኞች ይሆናሉ ሲል አሰበ፡፡’ ጠባቂው፡፡
ከአሳንሰሩ ወጥተው መግቢያው ጋር ሲደርሱ በኤሌክትሪክ የሚሰራው በር እንዲከፈትላቸው ማዘዣውን ቁልፍ ተጫነው፡፡
ገብተው ወደሱ መራመድ ጀመሩ፡፡ አንደኛው ሰው ኪሱ ውስጥ የነበረውንና በጓንት የተሸፈነ እጁን አውጥቶ ሊጨብጠው እየዘረጋ “የምሽቱ ቅዝቃዜ ያንዘፈዝፋል” አለው፡፡
“እኔ እንኳ ብዙም አልተሰማኝም ቤት ውስጥ ስለሆንኩ” ይህችን ምድር የተሰናበተባት የመጨረሻ ንግግሩ ነበረች፡፡ እየተንሸራተተ ወደ ወለሉ ወረደ፡፡ጥይቷ በስታው ከገባችው የግምባሩ ቀዳዳ ደም መፍሰስ ጀመረ፡፡

ሰዎቹ ጊዜ ሳያባክኑ የድምፅ ማፈኛ የተገጠመለት ሽጉጣቸውን በማስቀደም ወደ ውስጠኞቹ ክፍሎች አመሩ፡፡ በር መክፈት ቃታ መሳብ..... ሁሉንም ሳይዘጋጁ አግኝተው ገደሏቸው::

የሉዊስን ቢሮ በር ሰብረው ገቡ፡፡ በጠረጴዛው ላይ ካለው ኮምፒውተር ወደፊት በአፍሪካ ምድር ላይ ተፈፃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የታቀዱ በርካታ የሀሳብ ንድፎች አገኙ፡፡ ሁለቱም እይታቸውን ተክለው ርዕስ ርዕሳቸውን ማንበብ ጀመሩ፡፡ በውስጣቸው በሀይማኖት ምክንያት ሊያስነሱዋቸው ያሰቧቸው ግጭቶች፤ መፈንቅለ መንግስትን በማነሳሳት የሚፈፀሙ እልቂቶችን፤ በወደብ ጉዳዮች ላይ በሚነሱ ውዝግቦችን እንዴት ወደ ጦርነት እንደሚያስገቧቸው የሚገልፁ ሲሆን “የማትኖረው ኢትዮጵያ” የሚለው እቅድም ይገኝ ነበር፡፡

የጦር መሳሪያውን ስለጫኑትም መርከቦች የሚተነትን ግልፅና ሙሉ መረጃም አገኙ:: የፒየር ቢሮ ውስጥም ተመሳሳይ ነገሮችን አገኙ፡፡ ሁሉንም በኮምፒውተር ዲስኬት ላይ ገልብጠው ያዙዋቸው::

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

አንደኛው ሰው ከካፖርቱ የውስጥ ሰፋፊ ኪሶች በከፍተኛ ሁኔታ የመቀጣጠል ባህሪ ያላቸውን የተያያዙ የፈንጅ እሽጐችን አወጣና መዘረጋጋት ጀመረ፡፡ በእያንዳንዱ ቢሮ ዙሪያ ከለጣጠፉት በኋላ የሰዓት መሙያውን አስተካክለው ከህንፃው ወጡ፡፡

ወደ ቀኝ ታጥፈው አምስት ደቂቃ ያህል እንደተጓዙ የህንፃው ማዕከላዊ ክፍሎች በከባድ ፍንዳታ ተናወጡ፡፡ ወድያውም በቃጠሎ መጋየት ጀመሩ፡፡

ጐዳናዎቹ የአደጋ ጩኸት በሚያሰሙ የቃጠሎ ማጥፊያ፣የበሽተኛ ማንሻና የፖሊስ መኪናዎች ጡሩንባ ጩኸት ታወኩ፡፡በዛ ቅፅበት አካባቢው የእብዶች ጥርቅም የሚኖሩበት መንደር መሰለ፡፡

በህንፃው ውስጥ የነበሩት ንብረቶች ሙሉ በሙሉ ወደሙ፡፡ ሁለቱ ካፖርት የለበሱት ሰዎች ፎርዱ መኪና ቆሞ የሚጠብቃቸው ስፍራ ደረሱና በሩን ከፍተው ገቡ፡፡ ዋልተር በደስታ ፈገግ አለ፡፡ እነሱም ያጠለቁትን እና ነጭ ያስመሰላቸውን ወርቅማ አርቴፊሻል ፀጉር አወለቁ፡፡ ከዛም በፈረንጅ ፊት አምሳያ በጥንቃቄና በማያስታውቅ ሁኔታ ተሰርቶ በፊታቸውና አንገታቸው ዙሪያ እንዲለጠፍ የተደረገውን ስስ የፕላስቲክ ጭምብል መላጥ ጀመሩ፡፡

ሁለቱም ጥቁር አሜሪካዊ ፊታቸው በመታፈኑ የተነሳ በላብ ረጥቦ ነበር፡፡ ፎርዱ ጉዞ ቀጠለች፡፡

  

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

ምዕራፍ 59

የ "ሉዊስ ወኪሎች" ተቋም ውድቀት ለበርካታ ወራቶች በፓሪስ ለሚታተሙ ጋዜጦች ዓምድ ላይ ዋና የዜናና የመነጋገሪያ ርዕስ ሆኖ ሰነበተ፡፡ ስለተካሔደበት የጥፋትና የውድመት ድርጊት ምንም ዓይነት ማስረጃን ፖሊስ ማግኘት አልቻለም ነበር፡፡

ሲፃፉ የሰነበቱትን ጉዳዮች በጠቅላላ የበርካታ አገር ሰዎች እና መንግስታቶች ሲከታተሉት ቆይተዋል፡፡ እንዲሁም በሼባል ጐዳና ላይ አነስተኛ የሆነ የነዳጅ ማደያ የነበረው የሉዊስ ብቸኛ ወንድም አንዱ ነው፡፡

የቢሮው ጠረጴዛ በዕለታዊ ጋዜጦች ተሞልቷል፡፡ ሁሉንም ገፍቶ መሬት ጣላቸውና ማሰብ ጀመረ፡፡ ይህ የነዳጅ መሸጫ ስፍራ በድብቅ ለሉዊስ መስራቤት ከሶስት ዓመት በላይ አገልግሎትን ሲሰጥ ነበር የኖረው፡፡ እንደ ማዕከላዊ ስፍራ ሆኖ ከባድ የሆኑ የሚስጥራዊ ሰነዶች ግዢና ሽያጭ ሲካሄድበት ቆይቷል፡፡

ቦታው እንዲመረጥ ያስቻለው ምክንያት ውሎች በሆነ ምክንያት ቢፈርሱና አዋኪ ሁኔታዎች ቢከሰቱ ሰነዶች ወደ ሶስተኛ አካል ከመግባታቸው በፊት ከነዳጅ ማጠራቀሚያዎቹ ጋር የተያያዙትን በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ፈንጂዎችን በአንድ መቆጣጠሪያ ብቻ አዞ በማፈንዳትና በማቃጠል አመድ እንዲሆኑ ለማድረግ አመቺ ሆኖ ስላገኙት ነው፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

በዚህም የሉዊስ ወንድም በየወሩ ያልተቋረጠ ደህና የገቢ ፈሰስ ያገኝ የነበረ ሲሆን ከወንድሙ ሞት በኋላ ግን ይህ ገቢ ተቋርጠበታል።።

በሌላ በኩል ግን ብቸኛ ወራሽ እንደመሆኑ በሉዊስ የባንክ ቁጥር በቢልየን የሚቆጠር ዶላር የሚጠብቀው እሱን መሆኑን ያውቃል።። ይህንን ያህል ገንዘብ ሉዊስ በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዴት ሊያገኝ እንደቻለ ለሱ አዲስ አልነበረም።።

ከራሱ ጋር ሲሟገት ለረዥም ሰዓታት ከቆየ በኋላ ግልባጭ ሆነው እሱ ጋር የተቀመጡትን የ "ሉዊስ ወኪሎችን" ድርጅት ሰነዶችን ማከማቻ ከሆነው ኮምፒውር ከፍቶ ማንበብ ጀመረ።። ተጀምረው ያልፈፀሙና ገና የሚጀመሩ በርካታ ኘሮጀክቶች መኖራቸውን ሲያነብ ዋለ።። ከነሱ መካከል አንደኛው "የማትኖረው ኢትዮጵያ" የሚለው ነበር።። ጉዳዩን በሰፊው አሰበበት።። ከዛም "እትራፊ ማድረግ እስከ ቻለ ድረስ እቀጥለዋለሁ" አለ ለራሱ።።

ከአንድ ወር በኋላ ከፓሪስ ጀምሮ በመላው አውሮፓና አሜሪካ ድረስ ገናና በሆነ አንድ ታዋቂነት ያለው ጋዜጣ የፊት ለፊቱ ገፅ ላይ በጉልህ ቃላት የ"ሉዊስ ወኪሎች ተቋም ከበፊቱ በተሻለና በተጠናከረ ሁኔታ ስራውን ቀጥሏል" የሚል ሰፊ ዝርዝርን የያዘ ዘገባ አስነበበ።። ዜናው በዓለም ላይ ያሉ የበርከታ ሀያላን አገር ገዢዎችን ቀልብ መሳብ ቻለ።። መስራቤቱ በዛው በሼባል ጐዳና ላይ ከማደያው አምስት መቶ ሜትር ራቅ ብሎ የሚገኝ ባለ ስድስት ፎቅ ህንፃ ውስጥ ነው።።

በውስጡ ከቀድሞ የሉዊስ ሰራተኞች የተራረፉትን ጨምሮ በዓለም አቀፍ የስለላ ስራ ላይ ግማሽ እድሜያቸውን በማሳለፍ ጠንካራ ልምድ ያካበቱ ሰላሳ ሰባት ባለሞያዎችን አቅፏል።። ለስራቸው የሚጠቀሙባቸው መሳሪያዎች ዘመናዊነትም በርካታ አገሮችን በበታችነት የሚያስገነብስ ነበር።።
ስራዎች ሁሉ ቀጥለዋል።።

«««««««««««« »»»»»»»»»»»

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።።

ጊዜው መድረሻው አይታወቅም ይጓዛል፡፡ ወራቶች እንደዋዛ እየነጐዱ የቀደሙት እውነታዎች ወደኋላ በመቅረት ትዝታና ታሪክ ሲሆኑ አዳዲስ ክስተቶች እየተፈጠሩ ህይወት ቀጥሏል፡፡
ቤቲ ለአብነት ያረገዘችው ልጅ ሊወለድ ሁለት ወራት ቀርቶታል፡፡ የአብነትን መሞት በጀንስ በኩል ከሰማች ሶስት ወራት አልፈዋል፡፡ ሁኔታውን ሊሰሙበት የቻሉት ክስተት አስገራሚ ነበር፡፡

አብነት በዛን ዕለት ምሽት ቤቱ እየተቃጠለ መፈራረስ ሲጀምር ለጀንስ ለመላክ ፅፎ ያጠናቀቀውን አንድ ፖስታ በመኝታው ግርጌ በኩል በምትገኝ አነስተኛ በርጩማ ላይ ጣል አድርጓት ነበር፡፡ በሚፈርሰው የግድግዳ ጉማጅ ወንበሩ ተመቶ ሲወድቅ ፖስታው ተወርውሮ ግዳግዳው አቅራቢያ ይወድቃል፡፡ ወድያውም ሌሎች ፍራሾች እየወደቁ ቀበሩት፡፡ ቃጠሎው ጠፍቶ በቀጣዩ ዕለት ቤቱን ያከራዩት ሰዎች ከቃጠሎው የተራረፉ ፍልጦችን ሲያወጡ ከአፈሩ ስር ያንን ፖስታ አገኙት፡፡

ከዛ ፖስታ በስተቀር ለአብነት ተጠሪ መሆን የሚችል ምንም ነገር አልተረፈም፡፡ ሰዎቹ የደረሰበትን አደጋ በዝርዝር በመፃፍ እዛው ፖስታ ውስጥ ከተው በላዩ በተፃፈው አድራሻ መሰረት ወደ አሜሪካ ላኩት፡፡

ጆንስም በአማርኛ የተፃፉትን ደብዳቤዎች እዮብን ጠርቶ በማስነበብ ሁለቱም በከፍተኛ ሀዘን ተውጠው ሰነበቱ፡፡ ቤቲም የግድ ማወቅ ስለነበረባትና መደበቁ ምንም ፋይዳ እንደሌለው በማሰብ ሰጣት፡፡
ደብዳቤውን ባነበበች ሰሞን ልትቋቋመው ከከበዳት አስቸጋሪ የመንፈስ ስብራት ውስጥ ወድቃ ቆየች፡፡ አብነት ከነገራት ነገሮች ሁሉ በሀሊናዋ ሰርፆ እያስተጋባባት የቀረው “ይቺ ምድር ለጥሩ ሰዎች መኖሪያነት ተስማሚያቸው ስላይደለች ቶሎ ይነጠቃሉ” ያላት ነበር፡፡

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል::

አብዝቶ ሲናፍቃት በተቆረጠበት ወቅት ላይ ጥዬዋለሁ ብላ የዋሸችውና ወደ አሜሪካ ስትጓዝ ይዛው የሄደችው ፀጉሮቹን አውጥታ

ትደባብሳቸው ነበር፡፡ ከሰናይት ጋር የእህት ያህል ተቀራርበዋል፡፡ ሰናይት በጭንቅላቷ ላይ በደረሰባት ከፍተኛ አደጋ ምክንያት ስለ ማንነቷም ሆነ ስላከናወነችው ቀደምት ታሪክ ምንም የምታስታውሰው ነገር የለም፡፡

ሁሉም ግን የ«አፍሮኢዝም» አባል ሆነዋል፡፡ አፍሮኢዝምም ግቡን መምታት ቀጥሏል፡፡



የማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል፡፡

መደምደሚያ

የዚህ መፅሐፍ ሀሳብ የማንንም ፓርቲ እንቅስቃሴ፤ ፕሮግራምና ዓላማ የወከለ አይደለም። ይሔ ስራ የኔ ትውልድ እና የዚህ ትውልድ ዘመን ምን ይመስል እንደነበር በስነ-ፅሁፍ እይታ በዚህ መልኩ የተገለፀበት እንዲሁም ተቀርፆ የሚቀመጥበት የዘመኑን መልክ ማሳያ የጥበብ ስራ ብቻ ነው።

ስሞች እና ገፀ-ባህሪያት በአብዛኛው የምናብ ፈጠራዎች ናቸው። ሆኖም ግን ግንባር ላይ እንዳለ ጉልህ ጠባሳ በምንም ነገር ሊሸፈን በማይችል መልኩ (መሸፈኑን በግሌ ባላምንበትም) ተጋልጠው የወጡ የአንዳንድ ግለሰቦች ስም፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች ስም እና የአመለካከታቸው ውጤት የሆኑ ስራዎቻቸው በዚህ መፅሐፍ ውስጥ ሊያጋጥም ይችላል። «ለምን ይህ ሆነ?» ለሚል አስተዋይ ወይም ቁጡ ጠያቂ የምሰጠው ትሁት መልስ ይህ ነው.....

ይህ ዘመን አሁን የያዘውን መልክ እና ቅርፅ እንዲያገኝ የነዛ ሰዎች ብሎም ፓርቲዎች አስተሳሰብ እና ድርጊት ያበረከተው አስዋፅኦ በበጎም ይሁን በክፉ እጅግ የገዘፈ በመሆኑ (አተያዩ እንደተመልካቹ እምነት እና አመለካከት መለያየቱ እንደተጠበቀ ሆኖ) ልክ እንደ ግምባር ጠባሳ የማይሸሽግ ሆኖ ተገኝቷልና ነው። ሙግቱ ግለሰባዊ ሳይሆን ከሚራመደው እሳቤ እና ድርጊት ጋር ብቻ መሆኑን ማስገንዘብ ግድ ይላል።

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ኦ.ኢ.ን ፤ ት.ነ.ን ፤ ህ.ደ.ነ.ሀ ፤ አፍሮኢዝም የደራሲው የምናብ ፈጠራዎች ሲሆኑ የሶሪያው የባዝ ፓርቲ ያራምደው ከነበረው ዓላማው ጋር እና ቀሪዎቹ በስም የተጠቀሱት ፓርቲዎች ሁሉም በግርድፉ ከቀረቡት ታሪኮቻቸው ጋር ከእውነታ የተገኙ (በህልውና ላይ ያሉ ወይም የነበሩ) ናቸው። የዚህ መፅሐፍ ዓላማ የ«ታሪክ መፅሐፍ» ማዘጋጀት ስላልሆነ ታሪኮቻቸውን ከበርካታ መረጃዎች ላይ በማሰባሰብ ለዚህ ፅሁፍ ዝግጅት አስፈላጊ የሆነው ያህል ብቻ ተቀንሶ በአገልግሎት ላይ ውለዋል።

ይህች አነስተኛ መፅሐፍ የዘመኑን ዘርፈ ብዙ መልክ መሸከምና ማሳየት የቻለችው ይችን ታህል ቢሆንም እኔም መደምደሚያውን ይህን ብዬ ልቋጭ መረጥኩ..... ሰው ካልተባረከ ቢዘራም አያጭድም፤ ቢያፍስም አይጎርስም፤ ቢተኛም አያርፍም፤ ቢሮጥም አይደርስም። አገር ካልተባረከች እጅግ ያማረች ብትሆንም እንኳ የሞት እንጂ የህይወት መሰረት መሆን አትችልምና፦

እግዚአብሔር አፍሪካን ህዝቦቿን ይባርክ።

ያማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

ከዚህ በፊት በዲሬሲው የታተሙ መፅሐፍቶች



« ርዕስ ለልባ ግጥሞች ስና ...»
ስነ-ግጥም 1996 ዓ.ም
ታተመ ለዲስ ለበባ



« ርዕስ ለልባ ግጥሞች ስና.... »
ስነ ግጥም ቅፅ.2
ፈጅም ዕበ-ወለድ
ታተመ 2011 ደቡብ ለፍሪካ
ታተመ 2004 ዓ.ም ለዲስ ለበባ



« ያላበቁ ገፃች ...»
ፈጅም ዕበ-ወለድ
ታተመ 2010 ደቡብ ለፍሪካ
ታተመ 2002 ዓ.ም ለዲስ ለበባ

Email:- daniel_tad2004@yahoo.com

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቅር ኦሳትም መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።

የማይሸጥ

ከደራሲው በሚገኝ የፅሑፍ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር አሳትሞ መሸጥም ሆነ በማንኛውም መልኩ ለገቢ ማስገኛነት ማዋል በህግ ያስጠይቃል።